የሕይወት ቃል



አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው

(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና

የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ መምህር)

BSC CIVIL ENGINEERING

ኦርቶዶክሳዊ ሚዛን

ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ክፍል ፩

ብዙው ሰው እጁ እስኪላጥ ሲያጨበጭብ ከርሞ አሁን ደግሞ ላንቃው እስኪሰነጠቅ እየጮኽ ነው። በእርግጥ የመንጋነት ፍጻሜው ውድቀት እና ማፈር እንዲሁም ፀፀት ነው። አብዛኛው ሰው መንጋ ነው። የሰባኪ መንጋ አለ። የአጥማቂ ነኝ ባይ መንጋ አለ። የፖለቲከኛ መንጋ አለ። የአክቲቪስት መንጋ አለ። አንዳንዱ አሁንም ከመንጋነት ወደ መንጋነት የተዘዋወረ አለ። የሆነ ሰው መንጋ ሆኖ ይከርምና የተከዳ ሲመስለው እገሌ ግን ያን ጊዜም ትክክል ነበር ብሎ ለዚያ ሰው ወዶ ገብ መንጋ ይሆናል። እኒህ ሁሉ መንጋቸውን እንደፈለገ ይነዱታል። መንጋው ደግሞ አያሰላስልም። መንጋ እንደ ሸንበቆ ነው። ሸንበቆ ነፋስ ወደነፈሰበት ነው ሁል ጊዜም የሚያዘነብለው። ነገር ግን ነፋሱ በጣም አይሎ ነቃቅሎ ሲጥለው ያን ጊዜ ያማርራል። አብዛኛው ሰው መለኪያ የለውም። መስማት የሚፈልገውን እየነገሩ የሚወስዱት ሰዎች ብዙ ናቸው። በርበሬ ተወዶ ከሆነ ቤተክርስቲያን ሰባኪው አስተምሮ ሲጨርስ "ፈጣሪያችን የበርበሬን ዋጋ ይቀንስልን" ሲል "አሜን" የሚለውን መንጋ ብዛት አስተውልማ። ደንበኛው ሊቅ መጥቶ አስተምሮ ሲጨርስ "ንሥሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ያብቃን" ሲል አሜን የሚለው ይቀንሳል። ይሄ በጣም አሳዛኙ ክስተት ነው። ሰው መስማት ያለበትን ከሚሰማ ይልቅ መስማት የሚፈልገውን መስማትን እየመረጠ ነው። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተዋጀችው የክርስቶስ ሙሽራ የሆነችው ስለበርበሬ እንዲወራ ነው እንዴ!?። ማንኛውም ሰው ፕሮፌሰርም፣ ዶክተርም፣ ኢንጂነርም፣ ሳይንቲስትም፣ ፖለቲከኛም፣ ፓትርያርክም፣ ቄስም፣ ጳጳስም፣ መምህርም፣ ምእመንም፣ ዲያቆንም ሁሉም ፍጡራን ናቸው። እንደፍጡርነታቸው የሚለኩበት መለኪያም አንድ ነው። አንተ ሰው ለምን የፖለቲከኛ መንጋ ትሆናለህ!? ፖለቲከኛም እንደ አንተ ሰው መሆኑን ዘነጋሃው እንዴ!? እንደ አንተ ሰው ከሆነ አንተም እርሱም የምትዳኙበት መለኪያ አንድ ዓይነት ነው። አንድ ዓይነት ከሆነ ደግሞ ለምን ራስህን የፖለቲከኛና የሰባኪ መንጋ ታደርጋለህ!? የማንም መንጋ አትሁን። እግዚአብሔር ራስህን አስችሎ ስለፈጠረህ ራስህን ችለህ አስብ። በሌሎች ጭንቅላት ካልተመራሁ አትበል። ሩጥ ሲሉህ የምትሮጥ ቁጭ በል ሲሉህ ቁጭ የምትል ከሆነ ፈጣሪ በነጻነት ራስህ ተመራምረህ እንድትመርጥ የሰጠህን እድል መንጋ ለሆንክለት አካል አሳልፈህ ሰጠኽው ማለት ነው። ይህ ደግሞ እገሌ አይሳሳትም ወደማለት ጽንፍ ያወርድሀል። ከዚያ ያ ሰው ሲሳሳት አንተ ማፈሪያ ሆነህ ትቀራለህ። ኦርቶዶክሳዊው ሰው ግን ሁሉን የሚመረምርበት አእምሮ ከፈጣሪ ስለተሰጠው በራሱ መንገድ በራሱ መለኪያ ነገሮችን ይመረምራል እንጂ የማንም መንጋ አይሆንም። ታድያ በዓለማችን የሚደረጉ ነገሮችን ለመመርመር ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ያስፈልገናል። ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ሁልጊዜም ትክክል ነው። አያጸጽትም። ዘመናትን ተሻጋሪ ነው። ልበ ሙሉ ያደርጋል። ምክንያቱም የኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ባለቤት እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ምንድን ነው?! ከመንጋነት እንዴት እንላቀቅ የሚሉ ጉዳዮችን በ7 ክፍል እንመለከታለን። ይከታተሉ።

ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ክፍል ፪

የኦርቶዶክሳዊው ሚዛን መሠረቱ ፍቅር እና እውነት ነው። ዓለምን የምንመዝናት ከእግዚአብሔር ቃል አኳያ ነው። አንድን ነገር እውነት ነው ወይም ውሸት ነው፣ ውብ ነው ወይም አይደለም፣ የሚለውን የምንለካው በቃሉ መሠረት ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ፈራጅ ነው። በፈራጅነቱ ፈርዖንን በውሃ አስጥሟል። እግዚአብሔር መሐሪ ነው። በመሐሪነቱ ደግሞ አዳምን ከሲኦል አድኖታል። በደንብ ልንጠነቀቅበት የሚገባን ጉዳይ ለእግዚአብሔር ፈታሒነትም መሐሪነትም ገንዘቡ መሆናቸውን ነው። ለማንኛውም ኃጢኣታችን ፍርድ ይሰጥበታል። የምሕረት ደጁም ክፍት ነው። አዳም እግዚአብሔርን በደለ። ሕግ ተላለፈ። ለሕግ መተላለፉ 5500 ዘመን ያህል በሲኦል እንዲሰቃይ ፈርዶበታል። እንደገና አዳም ንሥሓ በመግባቱ ይቅር ብሎ ፍርዱ ካለቀ በኋላ ምሮታል። ለአዳም መማር ትልቁ ምክንያት ግን መጀመሪያ እግዚአብሔር መሐሪ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ግን አዳም ጥፋቱን አምኖ አጥፍቻለሁ ብሎ ፍርዱን በመቀበሉ ነው። ወደፊትም ጌታ በኃጥዓን ሊፈርድባቸው ለጻድቃን ሊፈርድላቸው በዳግም ምጽአት ይመጣል። ያን ጊዜ በኃጥዓን የሚፈርደባቸው ኃጢዓተኝነታቸው ተረጋግጦ ነው። ምሕረት ለማያስፈልገው ሰው ለዘላለም ይኖርበት ዘንድ ወደ ገሐነመ እሳት ይወረወራል። ምሕረት ለሚገባው ኃጢዓቱን አምኖ የቀደመ ሥራውን ለተወ፣ የቀደመ ክፉ ሥራውን የሚኮንን፣ ባለፈው ክፉ ሥራው ተጸጽቶ ንሥሓ ገብቶ ሥጋውን ደሙን ለተቀበለ ደግሞ ጌታ ምሕረት ሰጥቶ ዘላለማዊ ደስታ ወዳለባት መንግሥተ ሰማያት ያስገባዋል። ኦርቶዶክሳዊ ሰው ዋና ሚዛኑ ዘላለማዊ ሕይወት ነው። ይህም ማለት የሚያደርገው ነገር ዘላለማዊውን መልካም ሕይወት ለመውረስ ያበቃል ወይስ አያበቃም? የእግዚአብሔርን ሕግ ይቃረናል ወይስ አይቃረንም? የሚለውን ይመረምራል። ኦርቶዶክሳዊው ሰው ሁሉንም ሰው እንደራሱ አድርጎ ስለሚወድ ስለሌላው ሰው የሚናገረውን ነገር ሁሉ ለእርሱ እንደሆነ አስቦ ይናገራል። ምክንያቱም ትእዛዛት በፍቅር ይጠቃለላሉ። ፍቅር ደግሞ ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ ተብሎ ይከፈላል። ፍቅረ ቢጽ ለእኛ ሊደረግልን የምንፈልገውን ለሌሎች ማድረግና እንዲደረግላቸው መመኘት ነው። በእኛ ሊደረግብን የማንፈልገውን በሌላውም እንዲደረግ አለመፈለግ ነው። የፍቅር ትርጓሜ ይህ ነው። ስለዚህ የኦርቶዶክሳዊ ሰው እይታው አመለካከቱ ፍቅርን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት። ዮሐንስ አፈወርቅ ኃጥዓን ሲሞቱ ደስ ሊለን ይገባል ይላል። ምክንያቱም በህይወት ቢቀጥሉ ኖሮ ኃጢኣታችውን ጨምረው ፍዳቸውን ያበዙ ነበር። ቶሎ በመሞታቸው ግን ፍዳቸው ይቀንሳል ይላል። ስለዚህ የኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ዋና መሠረቱ ፍቅር ነው። ሌላው እውነት ነው። ፍቅር እውነትን የያዘ ነው። ይህም ማለት ለምሳሌ አንድ ሰው ኃጢኣተኛ ቢሆን ለኃጢኣቱ ቅጣት ያስፈልገዋል። ይህ እውነት ነው። ነገር ግን ቅጣቱን እኛ በእሱ ቦታ ብንሆን ምን እንድንቀጣ ነው የምንፈልገው? የሚለውን የያዘ መሆን አለበት። እኛ የፈለገ ብንበድል መቼም ሲኦልን አንመኛትም። ሲኦልን የሚመኝ ሰው ይኖር አይመስለኝም። ስለዚህ ሌላው ሰውም የፈለገ ትልቅ በደል ቢበድል ለእኛ ሲኦልን እንዳልተመኘናት ሁሉ ለዚያም ሰው አለመመኘት ነው። በጥፋቱ መቀጣት እንዳለበት ማመን እውነት ነው። ቅጣቱ ምድራዊ እንዲሆንለት መመኘት ደግሞ ፍቅር ነው። ስለዚህ የኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ዋና መሠረቶቹ ፍቅር እና እውነት ናቸው። ቅዱሳን መምህራን እውነትን የሚያስተምሩ እውነት እግዚአብሔር ስለሆነ እውነትን መናገር እውነትን ማወቅ ለእኛ

ለሰውነታችን ከምንም በላይ ታላቅ ጥቅም ስላለው ነው። ይህንን እውነት ሌላውን ለማስተማር የተጉት እስከ ሞት የደረሱት ደግሞ ሰውን ስለሚወዱ እና ሌላው ሰውም እውነቱን አውቆ እንዲጠቀም ካላቸው መልካም እሳቤ እና ፍቅር የተነሳ ነው።

ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ክፍል ፫

ታላላቅ ወንጀል የሠሩ ሰዎች በድሎት እየኖሩ ለእውነት የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ ይሰቃያሉ። ለምን እግዚአብሔር አይፈርድም!? የሚል ጥያቄ ብዙ ጊዜ ይጠየቃል። እግዚአብሔር እንደኛ እንዲፈርድ ከመፈለግ የመጣ ያለማስተዋል ጥያቄ ነው። በፍርድ ዙሪያ ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ምንድን ነው? የሚለውን በጥቂቱ እንመልከት። በዚህ ምድር ጻድቁም ወንጀለኛውም በስቃይ ሊኖሩ ይችላሉ። ድሎት የትክክለኝነት መለኪያ አይደለም። ጻድቁም ወንጀለኛውም ሀብታም ሊሆኑ ይችላሉ። ሀብት ማፍራት የትክክለኝነት መለኪያ አይደለም። ወንጀለኛውም ጻድቁም በጤና ይኖራሉ። ጤና ግን የትክክለኝነት መለኪያ አይደለም። ጻድቁም ወንጀለኛውም ሊታመሙ ይችላሉ። መታመም የጥፋተኝነት ምልክት አይደለም። ኃጥኡም ጻድቁም ድሃ ችግረኛ ሊሆኑ ይችላሉ። ድሀ መሆን የጥፋተኝነት ምልክት አይደለም። ታድያ ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን እነዚህን ነገሮች እንዴት ያያቸዋል? የሚለውን እንመልከት። ነዌ ሀብታም ነበር ግን ወንጀለኛ ነበር። አብርሃምም ሀብታም ነበር ነገር ግን ጻድቅ ነበር። ስለዚህ ሀብትን እግዚአብሔር ይሰጣል። እንግዳ ተቀብለው ሌላውን ለሚረዱበት ጽድቅ ይሆናል። ስግብግብ ሆነው ሌላውን ካልረዱበት ደግሞ እንደ ነዌ ያደርጋል። ሰባት አጋንንት የወጡላት ማርያም መግደላዊትም ታማሚ ነበረች። ኢዮብም ታማሚ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስም ታማሚ ነበር። ነገር ግን መግደላዊት የታመመችው በኃጢኣቷ ምክንያት ነው። እነ ቅዱስ ጳውሎስ የታመሙት ደግሞ መከራ ከበዛ ዘንድ ጸጋ ያገኙበታልና ነው። ስለዚህ ታማሚነት ብቻውን የጥፋተኝነት ምልክት አይደለም። በግብጻውያን 11 መቅሰፍት ወርዶባቸው ታላቅ መከራ ደርሶባቸዋል። ቅዱስ ጊዮርጊስም ሰባት ዓመት ሙሉ የተፈራረቀ መከራ ደርሶበታል። ነገር ግን ግብጽ በኃጢኣቷ ሲሆን ቅዱሳን ሰማእታት ግን ክብራቸው ይበዛ ዘንድ ነው። ሕመም፣ ስቃይ፣ መከራ፣ እና ማጣት በ3 ምክንያት ሊመጣ ይችላል። እነዚህም አንደኛ በኃጢኣት ምክንያት ሊመጣ ይችላል። ይህም ታማሚው ደንግጦ ንሥሓ እንዲገባ ሲሆን ሌላው ሰው ደግሞ የታመመውን ሰው አይቶ እንዲማርበትና ከክፋት እንዲመለስ ነው። እዚህ ላይ ኃጢኣት ሠርቶ በዚህ ምድር የተቀጣ ሰው ብጹዕ ነው። ከሰማዩ እዳ ትንሽ ይቀነስለታልና ነው። እንደ ነዌ ኃጢኣት እየሰራ በድሎት በጤና የሚኖር ሰው ግን ሊያዝን ይገባል። ለበደሉ ሁሉ በሰማይ ይጠየቅበታልና ነው። ሁለተኛ እንዳንታበይ መከራ ሊደርስብን ይችላል። እኛ ሚች በስባሽ መሆናችንን ተረድተን እንዳንታበይ ጌታችን በመከራ በበሽታ ሊጎበኘን ይችላል። እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻል የሚባለው ለዚህ ነው። እናት ልጇን በሕጻንነቱ የምትገርፈው በኋላ ሲያድግ ኑሮ ሲመሠርት መልካም ይሆን ዘንድ ነው። ጌታችንም መልካም ምግባር እንዲኖረን በመከራ በበሽታ ሊጎበኘን ይችላል። ሦስተኛ መከራ ክብራችን ይበዛ ዘንድ ሊመጣ ይችላል። መከራ ከበዛ ዘንድ ክብርም ይበዛልና። የሰው ልጅ በሰራው ኃጢኣት ሁሉ ሙሉ ፍርድ የሚሰጥ በዳግም ምጽአት ጊዜ ነው። በዚህ ምድር ላይ ኃጥኡ በድሎት ሊኖር ይችላል። አንዳንዱ ደግሞ መቅሰፍት ሊደርስበት ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ለቀሪው ትምህርት እንዲሆን የሚደረጉ ናቸው እንጂ ሙሉ አይደሉም። ሙሉ

ስላልሆኑም አንዳንዱ ኃጥእ መከራ ሲደርስበት አንዳንዱ ግን እስከ እለተ ሞቱ በድሎት ሊኖር ይችላል። ለሁሉ እንደሥራው ፍርድ የሚሰጥ በምጽአት ጊዜ ነው። አንድ ደራሲ እግዚአብሔር በዚህ ምድር ለክፉው እንደ ክፋቱ ለጻድቁ እንደ ጽድቁ የሚከፍለው ከሆነ ለዳግም ምጽአት ምን ሊያደርግ ይመጣል? ይላሉ። ስለዚህ ሙሉ ፍርድ በዚህ ምድር የለም።

ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ክፍል ፬

ኦርቶዶክሳዊ ሰው ኃጢኣትን እንጂ ኃጢኣተኛን አይጠላም። ብዙዎቻችን ጥላቻችን ከሰው ጋር እንጂ ከጥላቻ ጋር አይደለም። ይሄ በጣም አሳዛኝ ነው። በነገራችን ላይ ክፉን ብትገድለው ክፋት አይሞትም። እንዲያውም ይበረክታል። ለምሳሌ ገዳይን ብትገድለው የእርሱ ዘመዶች ደግሞ አንተን ለመግደል ይፈልጉሀል ቂም ይይዙብሃል። ስለዚህ ክፋት ግዛቱን አስፍቶ በሚቹ ቤተሰቦችም ይዛመታል። ክፋትን መግደል ግን ክፉን ይቀንሳል። ጌታችን በዚህ ምድር በሥጋ በተመላለሰ ጊዜ አይሁድን አላጠፋም። ክፋትን ግን በብዙ ወገን አጥፍቶታል። ትእቢት፣ ስስት እነ ፍቅረ ንዋይ ክፋቶች ናቸው። ነገር ግን በትሕትና በጸሊአ ንዋይ በትእግስት አሸንፏቸዋል። ቅዱሳን ሊቃውንት ትግላቸው ከክፋት ጋር ነበር። ያሸነፉትም ክፋትን ነው። አምርረን ልንታገለው የሚገባን ክፉ ሥራን እንጂ ሠሪውን አይደለም። ሠሪውማ ክፋትን የሚሰራው በክፉ ሥራ ቅኝ ግዛት ተገዝቶ ስለሆነ ልናዝንለትና እንዴት ከክፋት ባርነት ነጻ እንደምናወጣው ነው ማሰብ ያለብን እንጂ ልንናደድበት አይገባም። ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ትኩረቱ ክፋትን ማጥፋት ላይ እና ጽድቅን ማብዛት ላይ ነው እንጂ ክፉን ማጥፋት ላይ አይደለም። ክፉን መልካም ማድረግ ላይ ነው ትልቁ ትኩረት እንጂ ክፉን ማጥፋት አይደለም። ክፉ እስከ ምጽአት ይኖራል። ስለዚህ የክርስትና ዋናው መገለጫ ክፉዎችን ከክፋት እስራት ማውጣት ነው እንጂ ክፉዎችን ማጥፋት አይደለም። ነገር ግን ተመክረው ተነግረው አልሰማ ያሉ ክፉ ሰዎች ካሉ መዝ.34 ላይ ባለው ቃል "ግፍያመ እግዚአ ለእለ ይገፍኡኒ" ብለን ልንጸልይባቸው ይገባል። ነገር ግን ወደፊት ይመለሱ አይመለሱ የወደፊቱን ስለማናውቅ አለማወቅ ስለሚከለክለን የሆነን ክፉ ሰው አስበን ያንን ሰው ጌታ ሆይ አጥፋልኝ ማለት አይገባም። ጳውሎስ በመጀመሪያ ክፉ ነበር። ፍጻሜው ግን ቅዱስ ነበርና። እኛንም አለማወቅ ስለሚከለክለን እንዲሁ በጅምላ ማንኛውንም ሰው በሀሳባችን ሳናስገባ "ጌታ ሆይ ሰውን ሁሉ ከነፍጻሜው ታውቀዋለህና ከክፋቱ የማይመለሰውን ሰው አጥፋው ልንል እንችላለን"። የግፍያመ እና የሥረይ ሎሙ እርቅ ይህ ነው። ጌታ ሆይ ከክፋታቸው የማይመለሱትን ግፋቸው። ባለማወቅ የሚበድሉትን ግን ይቅር በላቸው እንላለን። ቅዱሳን ግን ሲበቁ በማንኛውም ሰው ላይ የሞት ፍርድን ሊፈርዱ ይችላሉ። ይኽውም የወደፊቱን በእግዚአብሔር ጸጋ እንደሚያውቁት ሁሉ። የሰውንም ፍጻሜ የሚያውቁበት ጸጋ አንዳንድ ጊዜ ስለሚሰጣቸው በፈጣሪ ፍርድ በወንጀለኛ ላይ ይፈርዱበታል። የጊዮርጊስ 70 ነገሥታትን ማጥፋት የቅዱስ ጴጥሮስ ሐናንያን በጸሎቱ ያጠፋበት መንገድ ይህ ነው። ስለዚህ ሁልጊዜም ሚዛናችን ሰው ተኮር መሆን የለበትም። ግብር ተኮር መሆን አለበት። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ኃጢኣትን እንጂ ኃጢኣተኛን አልጠላም ያለው ለዚህ ነው። ኃጢኣት ግብር ነው። ኃጢኣተኛ ግን ሰው ነው። ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ግብር (ሥራ) ተኮር እንጂ ገባሪ(ሠሪ) ተኮር አይደለም። ለምሳሌ ጠብ አንደኛው ክፋት ነው። ይህን ክፋት ግን አባቶቻችን በእርቅ ሲያጠፉት ኖረዋል። ጠብን በእርቅ ሲያጠፉት

የተጣሉት ሰዎች ግን በሰላም እንዲኖሩ ሆኗል። ጥላቻን በፍቅር አሸንፈውታል። ትእቢትን ከንቱ ውዳሴን በትሕትና፣ መከራን በትእግሥት፣ ስሜታዊነትን በጥበብ፣ ዘረኝነትን በአንድነት አሸንፈውታል። ኦርቶዶክሳዊነት ግንፍል ግንፍል እያሉ በስሜት የሚነዱበት አይደለም። ምሥጢራዊነትን ከሥራ ጋር ያስተባበረ ነው። ኦርቶዶክሳዊነት እሪሪ እያሉ መጮህ አይደለም። የኦርቶዶክሳዊነት መነሻው ራሱ አርምሞ ነው። ሥራን በዝምታ እና ውስጥ ለውስጥ መስራት ነው። ወተአቅብ ዘንተ ኩሎ ወትወድዮ ውስተ ልባ እንዲል።

ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ክፍል ፭

ኦርቶዶክስ ማለት ርቱዕ ቀጥ ያለ አመለካከት ማለት ነው። ኦርቶዶክሳዊው ሰው አክስቴ፣ አጎቴ፣ ወንድሜ፣ ልጄ፣ ሚስቴ፣ አለቃየ፣ ንሥሓ አባቴ..... ወዘተ ሳይል ሁሉንም በፍርድ ጊዜ እና በፍቅር ጊዜ በእኩል ማየት ነው። ኦርቶዶክሳዊነት አድሏዊነት የለበትም። የእግዚአብሔርን ሕግ ከተቃወመ የምታከብረውን ሰውም ሳታፍር ሳትፈራ ስህተቱን ገልጦ መንገር ነው። እየመረጡ ማልቀስ ሳይሆን ሁሉንም በእኩልነት የሚያይ ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ ንጉሡ ባጠፋ ጊዜ አፍሮ ዝም በማለቱ የትንቢት ጸጋው ተገፎበት ነበረ። ለምሳሌ ዘፋኝነት ኃጢኣት ነው። ስለዚህ አንድን ዘፋኝ ከዘፋኝነቱ ማስለቀቅ ሲገባን ብዙዎቻችን ግን የዘፋኙ አድናቂ ነን። ደግሞ ዘፋኙን ያደነቅነው ሰውነቱን አይተን ሳይሆን ዘፈኑን ሰምተን ነው። ኦርቶዶክሳዊው ሰው በሰው አይመራም። የሰው መንጋም አይደለም። የሰው አጨብጫቢ አይደለም። ኦርቶዶክሳዊው ሰው የሚመራው በእግዚአብሔር ነው። ሰውን ተከትሎ አይጠፋም። እንደምታውቁት በቅርብ ጊዜ ብዙው ሰው የበጋሻው ደሳለኝ ተከታይ ሆኖ ነበር። ይህ ሰው በጋሻው ያለው መሬት አይነጥብም ልክ ነው እያለ ሲጃጃል የኖረ ነው። ልክ በጋሻው መና*ቅ(ስም አይጠሩ) ሲሆን ሲወገዝ ያም ሰው በጋሻውን ተከትሎ ሄደ። ኦርቶዶክሳዊው ሰው ግን ሲጀምር የሰው መንጋ አይደለም። ማንኛውንም ሰው በፈጣሪው ትእዛዝ ይለካል እንጂ። ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን በብዛት፣ በእውቀት፣ በርዝመት፣ በባለስልጣን፣ በሹመት፣ ወዘተ አይለካም። ከ1000 ሰዎች ውስጥ በአንድ ጉዳይ ላይ 999ኙ ቢስማሙና አንዱ ተቃራኒቢሆን። ብዙ ሰው የደገፈው ትክክል ነው አይባልም። ያ ሰው የደገፈው ጉዳይ በቃለ እግዚአብሔር ተመዝኖ ትክክል የሆነው የአንዱ ከሆነ ትክክሉ አንዱ ነው ሊባል ይችላል። በቃለ እግዚአብሔር ተመዝኖ የ999ኙ ሰዎች ሀሳብ ትክክል ከሆነም የእነርሱ ትክክል ነው ይባላል። እውነት በእጅ ብልጫ አትዳኝም። እውነት እግዚአብሔር ነው። እውነት በእጅ ብልጫ እና በሰው ብዛት የምትለካ ቢሆን ኖሮማ ኖኅ ስህተተኛ በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች እውነተኛ በሆኑ ነበር። እውነት በእጅ ብልጫ ወይም በሰው ብዛት የምትለካ ቢሆን ኖሮማ ጊዮርጊስ ስህተተኛ ሰባው ነገሥታትና ብዙው ሕዝብ እውነተኛ በሆነ ነበር። ነገር ግን እውነት በመንጋ እና በአጨብጫቢ ብዛት አትለካም። እውነተኛ ሰውም አንድን ጉዳይ ብዙ ሰው ደገፈው ወይስ አልደገፈውም ብሎ ከብዙው ጋር የሚደመር ሳይሆን ጉዳዩ በእግዚአብሔር ቃል ልክ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አይቶ ይቆርጣል። በእውቀት ታላቅ የሆኑ ፕሮፌሰሮች፣ ሊቀ ሊቃውንቶች፣ መምህራኑ፣ ዶክተሮቹ ሀሳቡን ከደገፉት በቃ እንደነርሱ እሆናለሁ ማለትም አንደኛው የመንጋነት መገለጫ ነው። መቼም የእነ አርዮስን እና የእነ ንሥጥሮስን ሊቅነት የሚክድ ሰው ያለ አይመስለኝም። ነገር ግን ፍጹም የማይሳሳት እግዚአብሔር ነው። ከፍጡራን ድንግል ማርያም ናት። ሌላው በተለይ በሕይወተ ሥጋ ያለ

መምህር ወይም ሊቀሊቃውንት ወይ ሊቀ ምሁራን ወይ መጋቤ.... ሊሳሳት ይችላል። ስለዚህ አንድን ሀሳብ እገሌ የተባለ ሊቅ ስለተናገረው ብቻ ልክ ነው ብሎ ማጨብጨብ እና መከተል አይገባም። የዚያን ሊቅ ንግግር በኦርቶዶክሳዊው አረዳድና በቃለ እግዚአብሔር መዝነን ጥሩ ከሆነ እንያዘው። ችግር ካለበት እንተወው። ሌላውና ትልቁ አንድን ሐሳብ ባለስልጣን ተናገረው ማለት ልክ ነው ማለት አይደለም። መቼም መላእክት በተፈጠሩ ጊዜ ከዲያብሎስ የበለጠ ባለሥልጣን አልነበረም። በወንበሩ በሹመቱ ከሁሉም ከፍ ያለ ነበር። ነገር ግን በውሸት እኔ አምላክ ነኝ ባለ ጊዜ የኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ዋና መሠረቱ ሥልጣን፣ እውቀት እና የመሳሰሉት ስላልሆኑ በአእምሮ ፍጥረታዊ በሥልጣን ከእርሱ ዝቅ ይል የነበረው ቅዱስ ገብርኤል ሞግቶታል። ቅዱስ ገብርኤልም በዚህ ምክንያት ለድንግል ማርያም የምሥራች ዜና እንዲነግራት ተሸለመ። ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን መለኪያው ቃለ እግዚአብሔር ነው። ከዚህ ያፈነገጠ ነገር ከመጣ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው የሰማይ መልአክም ቢመጣ አንቀበለውም። ክርስቶስን ይከተሉ ከነበሩት የአምስት ገበያ ሕዝብ የተወሰነው ያበላል ሲባል ስለሰማ ሊበላ፣ የተወሰነው ይፈውሳል ስለተባለ ሊፈወስ፣ የተወሰነው ተአምር ለማየት፣ ጥቂቶች ግን የሕይወት ምንጭ የሆነውን ትምህርቱን ለመስማት ተከትለውታል። አሁንም በቤተ ክርስቲያን ግማሹ ለእንጀራ ለዳቦ ሲል ምንደኛ ቅጥረኛ ሆኖ የሚኖርባት አለ። ሲታመም ለሥጋ ፈውስ ብቻ የሚፈልጋት አለ። ገንዘብ ለማካበት፣ ታዋቂና ዝነኛ ለመሆን የሚፈልጋት አለ።

ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ክፍል ፮

ኦርቶዶክሳዊው ሰው ድርሻው ላይ ትኩረት ያደርጋል እንጂ የደረሰው ጥፋት ሁሉ በእነ እገሌ ምክንያት ነው እያለ ራሱን አስቀድሞ እንደ ነቃ ሰው አድርጎ ሌላው ገና እንዳልገባው አድርጎ አይናገርም። ኦርቶዶክሳዊው ሰው ሁሉም ሰው እንዲድን ከመፈለጉ የተነሳ ከግላዊ አካሄድ ይልቅ የቡድን ሥራ (Team Work) ያስደስተዋል። ከራሱ ጀብዱ ይልቅ ለሕብረተሰቡ ሕይወት ያስባል። በነገራችን ላይ ባሕታውያን በአካል ከሰው ተለይተው ጫካ ቢገቡም፣ ሰው ሲያዩ ቢሸሹም፣ ለሸሹት ሰው ምሕረትን ለመለመንና፣ በዚች በአጭሯ የዓለም ኑሮ ከመተያየት ይልቅ በዘላለማዊው ኑሮ ለመገናኘት እንዲያበቃቸው እየወደዱት ነው የሚርቁት። ኦርቶዶክሳዊው ሰው ሁሉንም ሰው ያከብራል። ሁሉንም ሰው ይወዳል። ኦርቶዶክሳዊ ሚዛን ያለው ሰው የሚናገረው ንግግር የሚፈርደው ፍርድ ሰውየውን በማክበርና በመውደድ ላይ ተመሥርቶ ነው። ኦርቶዶክሳዊው ሰው ራሱን እንደማይሳሳት አድርጎ አይቆጥርም። ሌሎችን በመናቅና በመስደብ እርሱ ነገሮችን ለማስተካከል እየሞከረ እንዳለና ሌላው ሰው ግን ተኝቶ እንዳለ አያስብም። ከዚያ ይልቅ እርሱ ትንሽ ቢሰራም በስውር የሚሰሩ ብዙ ሰዎች እንዳሉ በማሰብ ራሱን ዝቅ አድርጎ ይኖራል። ኦርቶዶክሳዊ ሚዛን ያለው ሰው ክፉን በክፉ አይቃወምም። በየሚዲያው ኡኡኡ እያለ ከመጮህ ይልቅ በምስጢር ውስጥ ለውስጥ ብዙ ሥራዎችን ይሠራል። በነገራችን ላይ የድንችን ፍሬ ወፍ የማይበላው ፍሬው በአፈር የተደበቀ ስለሆነ ነው። ወፍ የተባለ ዲያብሎስ ነው። እስመ ዖፈ ሰማይ ያወጽኦ ለነገርከ እንዲል። ጠላት መልሶ ማጥቃት እንዳይከፍትብን እኛም ጉዳያችንን በየሚዲያው ከማጮህ በቤታችን ቁጭ ብለን መነጋገርን እንልመድ። አሁን ሁሉም በግሉ ነው እየሄደ ያለው። ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት ማለትኮ የአንዱ የወይን ግንድ የክርስቶስ ቅርንጫፎች ነን ማለት ነው። ግላዊ አካሄድ የትም

አያደርሰንም። ያልተደራጀ ትግል ትርፉ ሽንፈት ነው። በግል ሮጦ መዳን የለም። መዳንም ማዳንም የምንችለው እኛ ከመነቃቀፍ ከመሰዳደብ ወጥተን አንድ ስንሆን ነው። ግንፍል ግንፍል የምንል ከሆንን፣ በስሜት የምንነዳ ከሆንን፣ እንኳን ታግለን ልናሸንፍ አስቀድመን በስሜት ተሸንፈናል። ከምንም በፊት ግን እያንዳንዱ ምእመን ድርሻውን ይወቅ። ድርሻየ ምንድን ነው? የሚለውን ሳያውቅ በሚመለከተውም በማይመለከተውም ጮሆ አይሆንም። ኦርቶዶክሳዊ ሚዛን ያለው ሰው በተሰጠው ጸጋ ያተርፍበታል እንጂ ያልተሰጠውን አይሻም። ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት። በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ያለን ሰዎች ደግሞ ግላዊ ሙገሣን ለማግኘት ከመላላጥ ቤ ተክርስቲያን ከፍ ብላ እኛ ዝቅ ብንል የተሻለ ነው።

ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ክፍል ፮

"የእኛስ ሀገራችን በሰማይ ነው" ብሏል ቅዱስ ጳውሎስ። ይህ ማለት ግን በምድር ላይ ስንኖር መኖሪያ ቤታችንን ሲቀሙን፣ የእርሻ ቦታችንን ሲቀሙን በአጠቃላይ ንብረታችንን ሲቀሙን "ሀገሬ በሰማይ ነው" እያልን ዝም እንድንል የተነገረ ቃል አይደለም። እግዚአብሔር ንጉሥ ነው ገገር ነው። ገገርነትን ደግሞ በጸጋ ለነገሥታት ሰጥቷቸዋል። እግዚአብሔር ፈራጅ ዳኛ ነው። በቸርነቱ ደግሞ ፍርድን ለዳኞች በጸጋ ሰጥቷቸዋል። ስለዚህ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በምድር ላይ ስንኖር ምድር የሁላችን ስለሆነች የእኛን ድርሻ ሌላው ሰው ከቀማን ለገገርው አካል ለዳኛ አቤቱታ ማቅረብ ይገባል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ንግሥቲቱ አውዶክስያ ድሃ በመበደሏ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያም እንዳትገባ ከልክሏት ነበር። እግዚአብሔር ለሁሉ ፍጥረት መጋቢ ሆኖ ሳለ እርሱ የሰጠንን የተፈጥሮ ጸጋ ለመጠቀም እኛ በስግብግብነት እርስ በእርስ እንዳንጣላ እና ፍቅር እንዳይፈርስብን ሀብተ መንግሥትን ለሰው ልጅ ሰጥቷል። ዳኛው ወይም መንግሥቱ ራሱ ሌባ ከሆነ ደግሞ ራሱን መሚገት ይገባል። ቅዱስ ጳውሎስ ሀገራችን በሰማይ ነው ያለው ይህቺ ምድር ምንም እንኳ ለጊዜው ብንኖርባትም ኃላፊ ናት። ዘላለማዊው መኖሪያ ሰማይ (መንግሥተ ሰማያት) ነው ለማለት የተናገረው ቃል ነው። ነገር ግን ዙሮ ዙሮ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት የሚያበቃንን ሥራ የምንሠራባት ቦታ ምድር ስለሆነች ኢፍትሐዊ ሥራ ከተሠራብን ለሚመለከተው አካል አቤቱታ ማቅረብ ይገባል። ኦርቶዶክሳዊ ሚዛን ያለው ሰው በዓይኑ ባላየው፣ በጆሮው በቅርበት ባልሰማው፣ አጠቃላይ በስሜት ሕዋሳቱ አማካኝነት በቅርበት ያልተረዳውን ነገር ከሌላ ሰው ሰምቶ ብቻ ፍርድ አይሰጥም። ያየውን የሰማውን ነገር እንኳ በብዙ መንገድ አረጋግጦ ነው የሚያወራው። ያውም ለራሱ ወይም ለሰሚው አካል የሚጠቅም ጉዳይ ከሆነ ነው። ለሰሚው የማይጠቅም ለራሱም የማይጠቀምበትን ጉዳይ አያወራውም። ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር አርዓያ የተፈጠረ ስለሆነ ክቡር ነው። ሐሳቦችን በውይይት ማስተናገድ ይገባል። የግድ የእኔ ሐሳብ ካልሆነ ብሎ መጫን አይገባም። የሃይማኖቱን ትምህርት ሁሉም ሰው ተምሮ ሊያውቀው ይገባል። ክርስትና ከሚያወሩት ይልቅ በተግባር የሚያሳዩት ነው። ስለዚህ ኦርቶዶክሳዊ ሚዛን ያለው ሰው ነገርን ብቻ ሰምቶ አይፈርድም። ድርጊቱን ለምን እንደተደረገም አውቆ ይናገራል እንጂ። መናበብ ያስፈልጋል። እኔ ያልኩት ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ ማለት አይገባም። ሕይወት ሙሉ ትርጉም የሚኖራት ኦርቶዶክሳዊ አኗኗርን መኖር ስንጀምር ነው። ምስጋና የሚገባው እግዚአብሔር ነው። እኛ ባለችን ትንሽ እውቀት አንዱን የሃይማኖት አርበኛ፣ ሌላውን ደግሞ አንበሳ እያልን ብናሞካሻው

እውነታውን አይለውጠውም። ደግሞስ ደረጃ መዳቢ ያደረገን ማን ነው?! እኛ ያሞካሸነው ሰውኮ ምናልባት በእግዚአብሔር ፍርድ ፍጹም ኃጢአተኛ ሊሆን ይችላል!? ስለዚህ የሰው መንጋ አንሁን። ለሰው ጻድቅ ነው ኃጥእ ነው እያልን ልንከራከርለት አንችልም። ኃጥኡንና ጻድቁን የሚለይ እግዚአብሔር ነው። እገሌ ይበልጣል እገሌ ያንሳል ማለትም አንችልም። የስውሩንም የአደባባዩንም ሥራ በትክክል የሚያውቅ እግዚአብሔር ስለሆነ እንዲህ ዓይነት ጉዳዮችን ለፈጣሪ እንተዋቸው። ለአንድ ሰው ብዙ ቢልየን ሕዝብ ጻድቅ ነው ብሎ መጽሐፍ ቢጽፍለት፣ በሚዲያ ቢያስነግርለት፣ ሐውልት ቢያሰራለት ወዘተ እግዚአብሔር በቸርነቱ ካላጸደቀው በቀር ጻድቅ መሆን አይችልም። በተቃራኒው አንድን ቅዱስ ቢልየን ሕዝብ ኃጥእ ቢለው ኃጥእ መሆን አይችልም። ኦርቶዶክሳዊው ሚዛን ሰባክያንን፣ መርጌቶችን፣ መምህራኑን፣ ካህናቱን፣ ጳጳሳቱን፣ ዲያቆናቱን፣ ምእመናኑን፣ ሕጻናቱን ያከብራል እንጂ በተለየ የሚያሸቃብጥለት አካል አይኖርም። ለሁሉም መልካምን ይመኛል። ስለዚህ ለሁሉም ነገር ዋናው መለኪያ ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ ማወቅ ነው። ይህንን ካወቅን ራሳችንንም ሌላውንም በአስተምህሮው እየለካን ቤተ ክርስቲያንንም ራሳችንንም መጠበቅ እንችላለን። በተረፈ ችግር በመኖሩ ከተስማማን ያን ችግር የምንፈታው ሚዲያ ላይ ባለ ጩኸት አይደለም። ቁጭ ብለን በተግባራዊ እና በተቀናጀ መልኩ በአንድነት መሬት ላይ ባለ አሠራር ነው። አንድነታችንን አንተው። ኢንጎድግ ማጎበረነ እንዳለ ሐዋርያው። ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ሰው

ሰው ክፍል 1

ዘላለማዊነት ካላቸው ፍጡራን አንዱ ሰው ነው። ሰው እግዚአብሔርን ይመስላል። ዘፍ.1፣27 "ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር" ተብሏል። ስለዚህ ሰው የእግዚአብሔር መልክ ነው። ሰውን ስናከብር እና ሰውን ስንወድ መሠረታችን ይህ ነው። የሰው ልጅ ያልነበረበት ዘመን ነበር። የመኖሩ መነሻ እለተ አርብ ነው። ፍጻሜ ግን የለውም። የሰው ልጅ ዘለዓለማዊ ነው። በዚህ ምድር የምንኖረው ኑሮ በእግዚአብሔር ቸርነት ለዘላለማዊው ሕይወት የሚያበቃንን ሥራ እንድንሠራበት ነው። ክቡርነታችንን እንረዳ። እግዚአብሔር በቸርነቱ በጸጋው አከበረን። እርሱ አክብሮን ሳለ ራሳችንን ኃጢአት እየሰራን አናዋርደው። ክቡራን ሆነን ሳለ ክብረ ቢስ አንሁን። እግዚአብሔር አክብሮ የፈጠረውን ፍጥረት እኛ አንንቀፈው። ፍጥረትን በፍጥረትነቱ መንቀፍ ፈጣሪን መንቀፍ ነውና። ከ10ሩ ሕግጋት አንዱ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚል ነው። ይህም መውደድ ከጥቅመኝነት የተለየ ሰውን በሰውነቱ ማክበር ነው። መውደድ በውስጡ መፍራትና ማክበር አለበት። የምንወደውን ሰው በተለየ እናከብረዋለን። እንደገና ደግሞ እርሱ የማይወደውን በእርሱ ፊት እንዳናደርግ እንጠነቀቅለታለን። ይህም በፍርህም አክብርም በአክብርም ፍርህም አለ ከሚለው ገለጻ ጋር በጥቂቱ ይመሳሰላል። ፍጥረታት፣ ወቅቶች፣ ቦታዎች ሁሉ ለእኛ ከፈጣሪ የተሰጡን ጸጋዎች በመሆናቸው ልንደሰትባቸው ይገባናል። በቸርነቱ ክቡር ፍጥረት አድርጎ የፈጠረን ክቡር እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

ሰው ክፍል 2

የሰው ልጅ እንበለ ግእዛን በግእዛን ተፈጥሯል። ይኽውም ያለ ነጻነት በነጻነት ተፈጥሯል ማለታችን ነው። ያለነጻነት ተፈጥሯል ማለትም ያለ እርሱ ፈቃድ በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ካለመኖር ወደ መኖር ተፈጥሯል። የሰው ልጅ አካሉ፣ ጸታው፣ ሰውነቱ፣ ቁመቱ፣ ርዝመቱ፣ ልቡ፣ ጎሊናው አጠቃላይ ተፈጥሯዊ ነገሮቹ በፈጣሪ ፈቃድ እንጂ ሰው ራሱ ወዶ ፈቅዶ ያመጣቸው ነገሮች ስላልሆኑ ያለ ነጻነት እንለዋለን። የሰው ልጅ ከተፈጠረ በኋላ ግን ጎሊናው መልካምና ክፉን የሚለይ ሆኖ ስለተፈጠረ የፈለገውን የማድረግ ሙሉ ነጻነት አለው። ጌታችን በወንጌሉ እውር፣ ዲዳ፣ ደንቆሮ እያለ በሰው አካላዊ ሁኔታ የሚሳለቅ ሰው የገሐነም ፍርድ ይፈረድበታል ብሎናል። ምን ማለቱ ነው? ከልጅነቱ ጀምሮ እውር ሆኖ የተወለደ ሰው ቢኖር እውርነትን ራሱ ሰውየው ፈልጎ ያመጣው ሳይሆን ሲወለድ የተሰጠው በመሆኑ ተሰጪውን ሰው ሳይሆን ሰጪውን እግዚአብሔርን መሳደብ ይሆናልና ነው። ስለዚህ በሰው መልክ፣ ቁመት፣ ጸታ፣ አካላዊ ቁመና እና በመሳሰሉት ልንሳለቅ አይገባም። እነዚህን የሚሰጥ ፈጣሪ ስለሆነ ፈጣሪ ደግሞ የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ መልካም እንደሆነ አየ ስለተባለ፣ የእኛ ውበትን የመረዳት የእይታ እጥረት እንጂ ሁሉም ሰው በተፈጥሮው ውብ ነው። እኒህ ነገሮች በፈጣሪ ፈቃድ እንጂ በእኛ ፈቃድ የተሰጡን አይደሉም። ሴት ልሁን ብላ አስተያየት ሰጥታ ሴት ሆና የተፈጠረች ሴት የለችም። ረጅም ልሁን ወይም ጥቁር ልሁን ወይም ቀይ ልሁን ብሎ አስተያየት ሰጥቶ የተፈጠረ የለም። የፈጣሪ ፈቃድ መልካም ነው። በመልካም ፈቃዱ እርሱ ፈጠረን እንጂ። ስለዚህ ይህ ያለእኛ ነጻነት በፈጣሪ ፈቃድ የተሰጠ ነው። ምክንያቱም ከመፈጠራችን በፊት አስተያየት እንስጥ ብንል እንኳ ሕልውና ስላልነበረን መስጠት አንችልም ለነጻነት ተፈጥረናል ማለት ደግሞ በፈጣሪ ፈቃድ ተፈጥረን ሕልውናን (መኖርን) ካገኘንበት ቀን ጀምሮ የፈለግነውን የማድረግ ሙሉ ነጻነት አለን ማለታችን ነው። ይህ ግን ሙሉ ኃላፊነትም አለበት። በዚህ ምድር መልካም ከሰራን የፈጣሪን ሕግ ካከበርን መንግሥተ ሰማያት ይጠብቀናል። ክፉ ከሠራን ማለትም የፈጣሪን ትእዛዝ ካላከበርን ገሐነመ እሳት ይጠብቀናል። ከሁሉቱ አንዱን መምረጥ የእኛ ፈንታ ነው። የእኛ ፈጣሪ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሌላ ፈጣሪ የለንም። ሙሉ ነጻነት ሙሉ ክብር ያለን ድንቅ ፍጥረት ነን። ነጻነታችንን ግን ለመልካም እናውለው። ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን። ልጁ መልከ መልካም ነው። እና አንዲት መልካም ልጅ ያገባት ዘንድ ጠየቀችው። እርሱ ግን በመልኩ ተመክቶ ንቆ ዞር በይልኝ ብሎ አመናጨቃት። ከዚያ ይህ በእንዲህ እያለ የመኪና አደጋ ደርሶበት ፊቱ ተበላሸ። ውበቱ ጠፋ። ከዚያ ወደ ልጅቱ ደውሎ "ያን የባለፈውን ጥያቄሽን አልረሳሁትም። የሰው ልጅ ዋናው ውበት የውስጥ ውበቱ ነው" አለና። እሺ አለ። የውስጥ ውበት ትዝ ያለው የውጭ ውበቱ ሲጠፋ ነበር። የሆነ ድሃ ልጅ ደግሞ የሆነችን ልጅ ያገባት ዘንድ ጠየቃት። እርሷም ድህነቱን አይታ "አንተ ነጭ ድሃ ሁለተኛ እንዳትጠይቀኝ ብላ ጆሮው ላይ ዘጋችበት" ከዚያ ያ ልጅ በሆነ መንገድ ባዕለ ጸጋ ይሆናል። ልጅቱ ይህን ስትሰማ ደወለችለትና "የሰው ልጅ በእንጀራ ብቻ አይኖርም። ዋናው ጤና ነው። ሀብቱን አንድ ላይ ሠርተን እናገኘዋለን" አለችው። ይህን ያለችው ግን ባዕለጸጋ መሆኑን ካወቀች በኋላ ነበር። ባዕለ ጸጋ መሆኑን ስታውቅ ውበቱ ጨምሮ አየችው። haha። የእኛ ሕዝብ ሐሜት ይችልበታል። ጅል ከጅል ሲጋባ "ቶፋ ግጥሙን አያጣም" ይልሀል። መልካም ከመልካም ሲጋባ ደግሞ "ባልና ሚስት ከአንድ ምንጭ ይቀዳሉ"

ይልሀል። የሰው ልጅ ማንነቱ ውስን ነው። ይኽውም በቦታ፣ በጊዜ እና በአካል የተወሰነ ነው ማለት ነው። በሁሉ ቦታ ምሉእ የሆነ የቦታዎች ቦታ የጊዜያት ጊዜ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ውስንነትን ማወቅ ትሕትናን ያጎናጽፋል። ፍጥረታት ሁሉ ወሰን አላቸው። የሰው ልጅ ስሜት የሚመራው የጥቅመኝነት ባሪያ መሆን የለበትም። ከላይ ያየናቸው ሰዎች ሁሉ ሕይወትን የሚተረጉሙት ከሥጋ ጥቅም ጋር አያይዘው ነው። ሥጋዊ ሕይወት ደግሞ መዳረሻው ሞት ነው። ሰው ክቡር ነው። ፍጥረታት ለእርሱ የተፈጠሩ ከሆነ፣ ውበቱ፣ ሀብቱ ከፈጣሪ የተሰጠ መሆኑን ካወቀ በሌላው አይመካም። ሰዎች ክቡር ነን። ክቡርነታችንን ያገኘነው ግን በእኛ ብቃት አይደለም። በእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ። ስለዚህ ትምክህት፣ ትእቢት ከእኛ ይራቁ።

ሰው ክፍል 3

ስድብን ተግሣጽ የሚል ሰው ሳይ ያስቀኛል። በበደሉ ንሥሓ ላለመግባትኮ ነው ስሙን የቀየረው። አንዳንዶች ዘፈን ኃጢኣት ነው ስለሚል ኃጢኣተኛ ላለመባል "የኪነ ጥበብ" ሰዎች ነን ይላሉ። ከመቼ ጀምሮ ነው ስድብ ተግሣጽ፣ ዘፈን ኪነጥበብ የሆነው?! የተግሣጽ መሠረቱ ፍቅር ነው። ዮሐንስ አፈወርቅ መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ ይባል ነበር። ነገር ግን ዮሐንስ ሲገሥጽ የሚወደውን ሰው ነው። ለአንድ ሰው ጥላቻ ኖሮህ የምትሳደበው "ስድብ" ነው የሚባል እንጂ "ተግሣጽ" አይባልም። አንድ ሰው ለሚገሥጸው ሰው ፍቅር ሳይኖረው እገሥጻለሁ ካለ ደንበኛ ተሳዳቢ ነው ማለት ነው። ታላቁ ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ኦሪት ዘፍጥረት ያለውን ቃል መሠረት አድርገው "ሰው እንፍጠር" የሚል ድንቅ ትምህርት እንዳስተማሩ ይነገራል። ከፍጥረታት ሁሉ ሰው ይከብራል። አሁን አሁን ሰው ወራዳ እየሆነ የመጣው ክብሩን ባለማወቁ ነው። የሰው ልጅ ክቡረ ዘመን፣ ክቡረ መካን፣ ክቡረ ግእዛን ነው። "ስለ ሰው ቀድጀ ልልበሰው" አይባልም። ለሰዎች ክብር የሌለው ሰው ቁጥሩ ከአራዊት ነው። የእግዚአብሔር ልጆች የሚታወቁት ሌላውን በማክበራቸው እና ሌላውን እንደራሳቸው በመውደዳቸው ነው። ጥሩ ሰው የሚባለው እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰውን የሚያከብር ነው። በፍጥረት ፈጣሪውን ያደንቃል። ከዚያም ጸጋዊ ጸጋ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ቅዱስ ዳዊት ልጁ ሰሎሞንን ሲመክረው ልጄ ሆይ ሰው ሁን ብሎታል። ሰውን መናቅ፣ መሳደብ አይገባም። ክፉ ሰው ቢያጋጥመን እንኳ ያንን ሰው ከክፋቱ የምናወጣበትን መንገድ ማሰብ ይገባናል። ክፋት በሰዎች አድሮ ያሳድደናል። ተጋድሏችን ከክፋት ጋር ነው ሊሆን የሚገባን። ሰው ክቡርነቱን ረስቶ ራሱን ከድኅነት ለማራቅ እንደ እንስሳ ሲሆን እና የስሜቱ ባሪያ ሲሆን ያሳዝናል። እውነታው ግን የሰው ልጅ የተፈጠረው ለታላቅ ልእልና ነበር።

ሰው ክፍል 4

1) እውነትና ፍቅር ሁልጊዜም አይለዩህ።

2) ንሥሓ ግባ።

3) ይቅርታ ተባባል መሓሪ ሁን።

4) ግላዊነትን ትተህ ኅብረታዊ ምልከታ ይኑርህ።

5) ፍርድህ የተቃና ይሆን ዘንድ አታዳላ።

6) ጹም፣ ጸልይ፣ ስገድ፣ መጽውት።

7) ትሕትናን ገንዘብ አድርግ።

8) ቅንዐትን፣ ምቀኝነትን አስወግድ።

9) ሁልጊዜም እለተ ሞትህን አስብ።

10) በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ።

ሁላችንም በክርስቶስ አንድ ነን። ከአንድነቶች ሁሉ ጠንካራውና ዘላለማዊው አንድነት በክርስቶስ ያለን አንድነት ነው። ኢንጎድግ ማጎበረነ አንድነታችንን አንተው የተባለ ይህንን አንድነት ነው። በክርስትና ግላዊነት የለም።ብቻን መጽደቅ ሳይሆን ሁላችንም በክርስቶስ አንድ ስለሆንን አንዱ ለአንዱ የሚያስብበት ጎብረታዊ ነው። ዘበልአ ባሕቲቶ ይመውት ባሕቲቶ ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል ይባል የለ። ንሥሓ ግባ ያልነው ደግሞ የሰው ልጅ እያወቀ በድፍረት ሳያውቅ በስህተት ኃጢኣትን ይሰራል። ነገር ግን ኃጢኣትነቱ ከታወቀን ወዲያውኑ ንሥሓ ልንገባበት ይገባል። የበደልነው ሰው ካለ ይቅርታ እንጠይቅ። የሻከሩ አንድነቶች ካሉ በይቅርታ እንጠግናቸው። ጠብ ምን ያደርግልናል። ከእኛ ጠብ አትራፊ የሚሆነው ሰይጣን ብቻ ነው። የሰይጣን አትራፊነት በእኛ ውድቀት ላይ የተመሠረተ ነው። እውነት እግዚአብሔር ነው። የሆነውን ሆነ ያልሆነን አልሆነም ማለት እውነት ነው። ነገራችሁ አዎ አዎ ወይም አይደለም አይደለም ይሁን ተብለናል። እውነት የተቃና ፍርድን እንድንፈርድ ያደርገናል። በእውነት አድልዎ የለም። ዘረኝነትና ሌሎች ኃጢኣቶች ውሸቶች ናቸው። ፍቅር ይኑረን ማለት ለእኛ ሊደረግልን የምንፈልገውን ለሌላው ማድረግ ነው። በእኛ ሊደረግ የማንፈልገውን በሌላው እንዲደረግ አለመፈለግ ነው። ሁሉንም ሰው እንደ አንተ አድርገህ አስበው ወይንም የአንተ እንደሆነ አስበው። በዚህ ጊዜ ምቀኝነት፣ ቅንዐት፣ ትእቢት፣ ስድብ የመሳሰሉት ኃጢኣቶች ብን ብለው ይጠፋሉ። እውነትና ፍቅር ያለው ሰው ፈጣሪውን ይመስላል። ርቱዕ ወይም ቀጥ ያለ አስተሳሰብ ይኖረዋል። ለሰው ክብር የሚሰጥ ሰው ሰውን ሁሉ የንጉሡ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብሎ በማሰብ ነው። ካህናትን ነገሥታትን የምናከብራቸው ፈጣሪ እኛን በሥጋ እና በነፍስ እንዲያስተዳድሩን ስለሾማቸው ነው። ሰው ከላይ ያሉትን ነገሮች ሲያደርግ የአእምሮ እረፍት የኑሮ ደስታ ያገኛል።

ሰው ክፍል 5

ስድስቱ ቃላተ ወንጌል

የሐዲስ ኪዳን ሕጎች ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከት ያስተማራቸው ሲሆኑ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

1) በወንድሙ ላይ በከንቱ የሚቆጣ ሁሉ እርሱ ይፈረድበታል። ወንድሙንም ጨርቅ ለባሽ የሚለው በአደባባይ ይፈረድበታል። ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ በገሀነመ እሳት ይፈረድበታል። ምሥጢሩ አለመሳደብ ነው። ማቴ.5፣22

2) ሴትን አይቶ የተመኛት ሁሉ ፈጽሞ በልቡ አመነዘረባት። ይህ ደግሞ ማንኛይቱንም ሴት እንደ እህት እንደ እናት ማየት እንደሚገባ የሚያስረዳ ሲሆን ከሰይጣናዊ ፍትወታዊ እይታ መከልከልን ያመለክታል። ማቴ.5፣28።

3) ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እርሱ ራሱ አመንዝራ ያደርጋታል። የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል። ይህ ደግሞ የትዳርን ክቡርነት የሚያሳይ ሲሆን ትዳር እስከ እለተ ሞት በፍቅር የሚኖሩበት እንጂ በችግር ጊዜ የሚፈታ በደስታ ጊዜ የሚቀጥል አይደለም። በደስታም በኀዘንም በፍቅር መዝለቅን ያመለክታል። ማቴ.5፣31

4) ከቶ አትማሉ። ይህ ደግሞ ነገራችን እውነት እውነት ወይም ሐሰት ሐሰት እንዲሆን እንጂ ሰውን ለማስረዳት መማል ተገቢ አለመሆኑን ያሳያል። ማቴ.5፣34

5) ክፉን በክፉ አትቃወሙት። ይህ ደግሞ ክፋትን በክፋት ሳይሆን ክፋትን በመልካም ሥራ ማሸነፍን ያመለክታል። በክፉ መንገድ ከመልካም ቦታ መድረስ አይቻልምና። ማቴ.5፥39

6) ጠላቶቻችሁን ውደዱ። የሚረግሟችሁን መርቁ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ። ማቴ.5፣44

ስድስቱ ቃላተ ወንጌል የሚባሉት እነዚህ ናቸው። የሰው ልጅ በእየ እለቱ አሥሩን ሕግጋት እና ስድስቱን ቃላተ ወንጌል በቃሉ አጥንቶ ራሱን ሊመዝንባቸው ይገባል። ወንጌል የትሩፋት ሕግ ናት።

ሰው ክፍል 6

ምጽዋት

ፍትሐ ነገሥቱ ምጽዋትን አምላክን የሚመስሉባት ግብር ብሎ ገልጿታል። የሚመጸውት ሰው አምላክን ይመስላል። መጽወተ ሰጠ ካለው የግእዝ ቃል ምጽዋት ስጦታ የሚለው ቃል ይወጣል። ይመልሱልኛል ሳይሉ እንዲሁ ለተቸገረ ሰው መስጠት ነው። ይኸውም ለምሳሌ ፈጣሪያችን ለእኛ አካላችንን ተፈጥሮን ሁለንተናችንን ሲሰጠን እርሱ በዚህ ምትክ ከእኛ የምንሰጠው ነገር የለንም። እንዲሁ በተሰጠን እናመሰግነዋለን እንጂ። ለተቸገረ ሰው የልብስ ወይም የምግብ ወይም የጉልበት ነጻ አገልግሎት መስጠት ነው ምጽዋት። መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በኃጥዓን ሊፈርድባቸው ለጻድቃን ሊፈርድላቸው ዳግም ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ምሥጢራቸው "ምጽዋትን" የተመለከተ ነው። ማቴ.25፥35-36 "እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። ተርቤ አብልታችሁኛልና። ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና። እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና። ታርዤ አልብሳችሁኛልና። ታምሜ ጠይቃችሁኛልና። ታስሬ ወደእኔ መጥታችኋልና" ይላል። እንግዲህ

የተራበን ማብላት የተጠማን ማጠጣት የታመመን መጠየቅ የታሠረን መጠየቅ እንግዳን መቀበል የታረዘን ማልበስ ዓውዱ ምጽዋትን የተመለከተ ነው። ጌታችን ቅዱስ ጳውሎስን በግብረ ሐዋርያት ምዕራፍ 9 ላይ "ለምን ታሳድደኛለህ ብሎት ነበር" ምእመናንን ለምን ታሳድዳለህ ማለት ነው። ምእመናን የክርስቶስ አካላት ናቸውና። ስለዚህ የተቸገሩ ምእመናንን ብናበላ ጌታ ብራብ አብልታችሁኛል ይለናል። ምጽዋት ስንሰጥ ግን በስውር እንድንሰጥ ታዘናል። ይኽውም ከንቱ ውዳሴ እንዳይሆንብን ነው። ማቴ.6፣3-4 "አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ። በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል" ተብሏል። ምጽዋት መጽውቶ ሰው ይወቅልኝ በሚዲያ ይነገርልኝ በዓውደ ምሕረት ካልተነገረልኝ ማለት አግባብ አይደለም።

ሰው ክፍል 7

አሥሩ ትእዛዛት

ሰው ፍጡር እንደመሆኑ መጠን ፈጣሪው ያዘዘውን በፍቅር የሚያደርግ መሆን አለበት። ከምንም በላይ አሥሩን ትእዛዛት አውቆ በየቀኑ ሰው ራሱን በእነዚህ መመዘን አለበት።

1) ከእግዚአብሔር ውጭ ሌላ አምላክ አታምልክ። ዘጸ.20፣3

2) የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ። ዘጸ.20፣7

3) ሰንበትን አክብር። ዘጸ.20፣8

4) አባትና እናትህን አክብር። ዘጸ.20፣12

5) አትግደል። ዘጸ.20፣13

6) አታመንዝር። ዘጸ.20፣14

7) አትስረቅ። ዘጸ.20፣15

8) በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር። ዘጸ.20፣16

9) ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማንኛውንም አትመኝ። ዘጸ.20፣17

10) ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ።ዘሌ.19፣18

አሥሩ ትእዛዛት የሚባሉ እነዚህ ናቸው። ሰማይንም ምድርንም ማንኛውንም ፍጥረት የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ የአምላክነት ክብር ለእርሱ ብቻ እንሰጣለን። ከሁሉም ይልቅ የምንፈራው እና የምናከብረው እግዚአብሔርን ነው። እግዚአብሔርን ማክበር መገለጫው ትእዛዙን በፍቅር መጠበቅ ነው። የእግዚአብሔር ስም ከስሞች ሁሉ የከበረ ስም ነው። ስለዚህ በከንቱ ነገር አይጠራም። ከንቱ ማለት የማይጠቅም ዘላለማዊ ያልሆነ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ሥም በመንፈሳዊ ነገር ይጠቀሳል እንጂ በሥጋዊና በከንቱ ነገር አይጠቀስም።

ሰንበትን አክብር የተባለው ቅዳሜን እና እሑድን የተመለከተ ነው። ቅዳሜ ፈጣሪ ከሥራ አርፎባታልና ትከበራለች። እሑድ ደግሞ የተጸነሰባት እና የተነሳባት ለሰው ልጅ የድኅነት ሥራን የፈጸመባት ስለሆነች ልዩ እለት ስለሆነች ሰንበተ ክርስቲያን እንላታለን። እናትና አባትህን አክብር ማለት ለእነርሡ መታዘዝ ነው። የእግዚአብሔርን ሕግ የሚሸር ነገር እስካላዘዙህ ድረስ ታዘዛቸው። እናትና አባትን ማክበር ለእነርሱ በመታዘዝ ይገለጣል። የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው። ስለዚህ ሰውን መግደል በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ስለሆነ ታላቅ በደል ነው። አታመንዝር ማለት የሰው ልጅ ክቡር ስለሆነ በፍትወታዊ እይታ ሳይሆን በክብር እና በመንፈሳዊ ፍቅር ውደደው ማለት ነው። እግዚአብሔርንም ሰውንም መሥረቅ አይገባም። እግዚአብሔርን መሥረቅ ማለት አሥራት በኩራት አለማውጣት ሲሆን። ሰውን መሥረቅ ማለት ደግሞ ሌላው የለፋበትን አጭበርብሮ መውሰድ ወይም በጉልበት መቀማት ማለት ነው። ውሸት የሰይጣን ገንዘብ ነው። ክርስቲያን ሁልጊዜም እውነትን ይናገራል እንጂ አይዋሽም። ለባልንጀራህ የተሰጠ ገንዘብ የባልንጀራህ ነው። ስለዚህ ለእርሱ የሚገባውን እግዚአብሔር ሰጥቶታል። ለአንተም የሚገባህን ፈጣሪ ሰጥቶሃል። ስለዚህ በተሰጠህ አመስግን እንጂ የሌላ የሆነን ገንዘብ አትመኝ። እነዚህ አሥሩ ሕግጋት በፍቅር ይጠቃለላሉ። ባልንጀራን እንደራስ መውደድ እና ፈጣሪን መውደድ ነው። ይህንን ባለፈው ክፍል አይተናል።

ሰው ክፍል 8

ሰው ንሥሓ ከገባ መቁረብ ይችላል። ወጣት አይቆርብም እያሉ ሰውን ከሕይወቱ የሚያርቁ ሰዎች ካሉ ምናልባት ከግንዛቤ እጥረት ነው ሊሆን የሚችለው። ቁርባንን በማንኛውም እድሜ ያለ ሰው ንሥሓ ገብቶ ጾሞ ጸልዮ መቀበል ይችላል። ያገባም ያላገባም ሰው መቁረብ ይችላል። ያረገዘች ሴትም ለመቁረብ የሚያስፈልጉ ሥርዓቶችን ማሟላት ከቻለች መቁረብ ትችላለች። ለመቁረብ 18 ሰዓት መጾም ይገባል። አሥራት ከአሥር አንድ ለቤተክርስቲያን የሚሰጥ ነው። የእኛ ገንዘብ አይደለም። ፈጣሪ እኛን ለመባረክ ራሱ ከሰጠን እንሰጠዋለን። በዚህም ለእርሱ ያለንን ፍቅር እንገልጣለን። የጽዋ ማኅበራት ጉዳይ ጽዋ ነዳያን የሚጠሩበት መንፈሳዊ ትምህርት የምንማማርበት ሊሆን ይገባን እንጂ እንዲሁ ሰው ተሰብስቦ ከንቱ ከንቱ ነገርን የሚነጋገርበት ሊሆን አይገባም። የሚያስተምር ቄስ ሊኖር ይገባል። በጽዋ ማኅበራት ሥም ብዙ ወንበዴዎች እየተነሱም ስለሆነ ካህናት ማንኛውንም ጽዋ መቆጣጠር አለባቸው። የካህናት ሥነ ምግባር የተበላሸ ሊሆን ይችላል። በዚያ ግን ፈጣሪ ራሳቸውን ይጠይቃቸዋል። እኛ ግን ምግባረ ብልሹነታቸውን አይተን ጸጋ አያሰጡም እያልን መጠራጠር የለብንም። ሁሉም የየራሱን ሸክም ይሸከም። የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እንወቅ።

ሰው ክፍል 9

መንግሥተ ሰማያት ከመግባት የሚከለክሉ የሥጋ ፍሬዎች የሚከተሉት ናቸው።ገላ.5፣19-21።

1) ዝሙት

2) ርኩሰት

3) መዳራት

4) ጣዖትን ማምለክ

5) ሟርት

6) ጥል

7) ክርክር

8) ቅንዐት

9) ቁጣ

10) አድመኝነት

11) መለያየት

12) ተጠራጣሪነት

13) ምቀኝነት

14) መግደል

15) ስካር

16) ዘፋኝነት

የሰው ልጅ በጋብቻ ካላገባው ሰው ጋር የመኝታ ግንኙነት ካደረገ ዘማዊ ይባላል። የዝሙት ፈተና እንዳይገጥመን ጋብቻ ተሠርቶልናል። በጋብቻ የሚያደርጉት ግንኙነት ዝሙት አይባልም። መኝታው ንጹሕ ነው ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ገልጸታልና። በአጽዋማት በዐበይት በዓላትና የመኝታ ግንኙነት በማይደረግባቸው እለታት ግንኙነት ማድረግም ቁጥሩ ከዝሙት ነው። ንጽሕና የሚባለው ራስን ከበደል ንጹሕ ማድረግን ነው። የሰው ልጅ በበደል ላይ በደል እየጨመረ ሲሄድ ንጹሕ አይባልም። ከዚያ ይልቅ ርኩስ ይባላል። የዝሙት መቅድም መዳራት ነው። በመጎናነጥ በመለካከፍ በመጠቃቀስ እና በመሳሰሉ ነገሮች ሊደረግ ይችላል። ይህም ስህተት ነው። ክርስቲያን ሥርዓትን በተሞላ መልኩ ይጠይቃል ሥርዓት ባለው መልኩ ይመልሳል እንጂ አይዳራም። መዳራት ኃጢኣት ነውና። አምላካችን እግዚአብሔር ነው። ልንመካበት የሚገባንም በእግዚአብሔር ነው። ከዚያ ውጭ በገንዘብ በጉልበት በመልክ መመካት ግን ጣዖት አምልኮ ነው። የፈጠረንን እግዚአብሔርን ትተን ፍጡር ካመለክን ጣዖት አምልኮ ይባላል። ታላቅ በደል ነው። ሟርት ሌላውን ሰው ለመጉዳት የሰይጣንን ሥም ጠርተው የሚያደርጉት ሰይጣናዊ ሥራ ነው። ይህም ሰውን ካለመውደድ የሚመነጭ ታላቅ የጥላቻ መገለጫ ነው። የእኔ ሐሳብ ተቀባይ ካልሆነ ብሎ የራስን አስተሳሰብ በሌላው ለመጫን በውይይት መካከል አላስፈላጊ ቃላትን መወራወር አይገባም። ከዚያም አልፎ መጣላት መኳረፍ

አይገባም። ጥል እና መለያየት የፍቅር አለመኖር ምልክት ነው። ፍቅር ሲኖር ኅብረታዊ ትሆናለህ እንጂ ለእኔ ብቻ አትልም። ምቀኝነትና ቅንዐት ፈጣሪ ለሌላው ሰው በሰጠው ጸጋ ማመፅ ነው። ፈጣሪን ለሁሉ እንደሚገባው ይሰጣል። ለእኛም የሚገባንን ሰጥቶናል። በተሰጠን እናመስግን። ያላሳደጉትን ውሻ እንደማይቆነጥጡት ሁሉ ያልመከሩትን ያላስተማሩትን ሰውም መቆጣት አይገባም። የሚገባና የማይገባ ቁጣ አለ። የሚገባ ቁጣ ሕጻናት ሲያጠፉ ወደፊት በጥፋታቸው እንዳይቀጥሉ፣ ዓላውያን ተጠራጣሪዎች ቤተ ክርስቲያንን ሲበድሉ መቆጣት ይገባል። የማይገባ ቁጣ ተሰደብኩ ተንቋሸሽኩ ተዋረድኩ ብሎ መቆጣት ነው። ይህንን እንድንታገሥ ተምረናል። ባንታገሥ ግን ቁጣ ከግድያ ያደርሰናል። መግደል ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕንጻ ማፍረስ ነውና ትልቅ ኃጢኣት ነው። ሌላውን ለመጉዳት በአንድነት መተባበር አመጽ ወይም አድመኝነት ይባላል። ራስን ከዚህ ማራቅ ይገባል። መተባበር ለመልካም ሥራ እንጂ ለክፉ ሥራ አይደለምና። በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት ምንም ጥርጥር የሌለበት መሆን አለበት። ከተጠራጠርን ግን መንግሥተ ሰማያት ከመግባት እንከለከላለን። የክርስቲያን ኑሮው በሥርዓት ነው። ልቅ አይደለም። መጠጡ ምግቡ በመጠን ነው። እስኪሰክሩ መጠጣት የክርስቲያን ምልክት አይደለም። የተፈቀደልን እንድንዘምር ፈጣሪን እንድናመሰግን ነው። ከዚያው ወጥቶ መዝፈን ኢክርስቲያናዊ ተግባር ነው። ዘጠኙ የመንፈስ ፍሬዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው (ገላ.5፣22)።

1) ፍቅር

2) ደስታ

3) ሰላም

4) ትዕግሥት

5) ቸርነት

6) በጎነት

7) እምነት

8) የውሃት

9) ራስን መግዛት

ደስታ አራት ወገን ነው። ሥጋዊ ደስታ ኃላፊ ጠፊ በሆነ ነገርና ከሞት በኋላ ላለው ሕይወት ምንም ጥቅም በማይሰጥ ጉዳይ ወይም ነገር መደሰት ነው። የቀበሮ ደስታ ይባላል። መቅድመ ወንጌል ላይ እንደተጻፈው ቀበሮ በረሃ ላይ የጣዝማ ማር ስታገኝ ከደስታዋ ብዛት የተነሳ ያገኘችው ማር እስኪጠፋት ድረስ ትዘላለች። ሌላው ፍሥሓ ኖሎት የሚባለው ነው። ጌታ በተወለደ ጊዜ እረኞች ተደስተዋል። የተደሰቱት ደስታ እነርሱን ከዘላለማዊው ሞት የሚያድናቸው መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ስለተወለደ ነው። ይህ ደስታ ከሥጋ ደስታ ከፍ ያለ እና ከዘላለማዊው ሕይወት ጋር ግንኙነት ያለው ነው። ሦስተኛው የደስታ ዓይነት የመላእክት ደስታ

ነው። አንድ ኃጥእ ንሥሐ በገባ ጊዜ በመላእክት ዓለም ታላቅ ደስታ ይደረጋል። ይህ ደስታ ከራሳቸው ጥቅም ጋር ያልተያያዘ ደስታ ነው። ሌላው ሲድን መደሰት ነው። በሌላው ሰው ስኬት እና ደስታ መደሰት ነው። አራተኛው የደስታ ዓይነት ፍሥሓ መስቴማ ወይል ሰይጣናዊ ደስታ የሚባለው ነው። ይህ ደግሞ ከቅዱሳን መላእክት በተቃራኒ የሆነ ሲሆን ሌላው ሰው ሲጎዳ ሲራብ ሲጨነቅ መደሰት ነው።በሌላው ስቃይ በሌላው ውርደት መደሰት ሰይጣናዊ ደስታ ይባላል። የመንፈስ ፍሬ የተባለው ደስታ ፍሥሓ ኖሎት እና ፍሥሓ መላእክትን ያቀፈ ነው። የደስታው ምንጭ እግዚአብሔር ነው። መዝ.94፣1 ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን እንደተባለ። መዝ.121፣1 ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ። የመሳሰሉት ናቸው።

ፍቅርን ባለፉት ክፍሎች አይተናል። ሰውን እንደራስ አድርጎ መውደድ እና መንከባከብ ሲሆን የፈጣሪን ትእዛዝ ማክበር ነው።ሰላም ምሥጢሩ ተሠናእዎ ወይም መስማማት ነው። የሐሳብ እና የልብ ስምምነት ነው። ትእግስት ፍርድን ለፈጣሪ ሰጥቶ በመከራ ጊዜም ቢሆን በተሰጠን ፈጣሪን እያመሰገንን ሳናጉረመርም ሳናማርር መኖር ነው። ቸርነት በውስጡ ፍቅር ከይቅር ባይነት እና ከርኅራኄ ያለው መሆን ነው። በጎነት ለሌላው መልካም ማሰብን፣ መናገርን እና ማድረግን ይመለከታል። እምነት የሚያኖረኝና በፍጥረታት አድሮ የሚመግበኝ እግዚአብሔር ነው ብሎ ትምክህትን በፈጣሪ ማድረግ ነው። የውሃት ኃዳጌ በቀል መሆን ነው። ድርሻን እየሰሩ ሰውን ሁሉ በጥርጣሬ ሳይሆን በፍቅር እያዩ መኖር ነው። Positive thinker መሆን ነው። ጠማማ ጠማማ አለማሰብ ነው። ቀና ቀናውን ማሰብ ነው። ራሳችንን በሕግ ማኖር አለብን። ራስን በሕግ ማኖርና የራስ ገዢ መሆን ራስን መግዛት ይባላል። ስሜት የሚሾፍረን ሳይሆን ስሜትን የምንቆጣጠር ስሜትን የምንገታ ሰዎች መሆን ነው።

ሰው ክፍል 10

ጾም ለተወሰኑ ሰዓታት ከምግብ መከልከል ለተወሰኑ እለታት ከጥሉላት ምግቦች መከልከል እና ለዘላለሙ ማለትም እስከ እለተ ሞት ደግሞ ከክፉ ነገር መከልከል ነው። ቅዱስ ያሬድ ዓይን ይጹም እዝንኒ ይጹም እምሰሚዐ ኀሡም ዓይን ይጹም ያለው እስከ እለተ ሞት ድረስ ክፉ ነገርን ከማየት፣ ከመስማት፣ ከመዳሰስ፣ ከመቅመስ መከልከልን ነው። ሰባቱ የአዋጅ አጽዋማት የሚባሉት፦

1) ረቡዕና አርብ (ጾመ ድኅነት)

2) የነነዌ ጾም

3) የገሐድ ጾም

4) የነቢያት ጾም

5) ጾመ ኢየሱስ (ዐቢይ ጾም)

6) ጾመ ማርያም (ፍልሰታ)

7) ጾመ ሐዋርያት

ናቸው። በጾም ጊዜ ከዘጠኝ ሰዓት በፊት አይበላም። በስድስት ሰዓት በሰባት ሰዓት የሚበላው ስህተት ነው። ረቡዕ እና አርብ በበዓለ ሃምሳ አይጾሙም። የብሉይ ኪዳን ጾም ከእለት መቅሠፍት ከሥጋ መከራ ያድናል እንጂ ነፍሳዊ ድኅነት አያሰጥም ነበር። በሐዲስ ኪዳን የምንጾመው ጾም ግን ነፍሳዊ ድኅነትንም ያሰጣል። የነነዌ ጾም ሁልጊዜም ሰኞ ጀምሮ እስከ ረቡዕ በዓመት ውስጥ ሦስት ቀን የሚጾም ጾም ነው። የገሐድ ጾም የልደት(የገና ዋዜማ) እና የጥምቀት ዋዜማ የምንጾመው ጾም ነው። የልደት ዋዜማን የምንጾመው ገሐድ ብለን ነው። የጥምቀትን ዋዜማ (ጥር 10) ቀንንም የምንጾመው ገሐድ ብለን ነው። ጥምቀት ሰኞ ቢውል የገሐድ ጾም እሑድ ብቻ ከጥሉላት ተከልክሎ ይጾማል። እንጂ ጥር 9 ቀንንም ጨምሮ መጾም አግባብ አይደለም። የጥምቀት ዋዜማን ገሐድ አለ እንጂ የጥምቀትን የዋዜማ ዋዜማ ገሐድ አይልም። የነቢያት ጾም በአራቱም ዘመናት ማለትም በዘመነ ዮሐንስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ማቴዎስ ሁልጊዜም ህዳር 15 ይጀመራል እንጂ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ህዳር 14 ይሆናል የሚባል ትምህርት የለም። የሥርዓት መጽሐፋችን ፍትሐ ነገሥት ነው። እርሱ ደግሞ ህዳር 15 ይጀመር ይላል እንጂ ከአራት ዓመት አንድ ጊዜ ህዳር 14 ይሁን አይልም። የፍልሰታ ጾም ነሐሴ 1 ጀምሮ እስከ ነሐሴ 16 ያለው ጾም ነው። የሐዋርያት ጾም ደግሞ ከጰራቅሊጦስ ማግሥት ጀምሮ እስከ ሐምሌ 5 የሚጾመው ጾም ነው። የጽጌ ጾም የፈቃድ ጾም ነው። ቅዳሜ ከቀዳም ሥዑር ውጭ ከምግብ ተከልክለን አንጾማትም። በአጽዋማት ወቅት ግን ቅዳሜ እና እሑድን ከጥሉላት ተከልክለን እንውላለን። ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበት አደባባይ ነው። ፍትሐ ነገሥታችን ጸሎት ብሂል ተናግሮ ምስለ እግዚአብሔር ብሎ ያመጣዋል። አንድ ክርስቲያን በቀን ቢያንስ ሰባት ጊዜ መጸለይ ይገባዋል። እነዚህም፦

1) ጠዋት 12 ሰዓት

2) ከጠዋቱ 3 ሰዓት

3) ቀትር 6 ሰዓት

4) ከቀኑ 9 ሰዓት

5) ሠርክ 11 ሰዓት

6) ከምሽቱ 3 ሰዓት

7) ከሌሊቱ 6 ሰዓት

ናቸው። የጠዋቱ ጸሎተ ኅግህ ይባላል። እነዚህ መደበኛ ይሁኑ እንጂ ማንኛውም ክርስቲያን ከእነዚህ በተጨማሪ በፈለገው ሰዓት እና ቦታ መጸለይ ይችላል። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሴቶች ጸጉራቸውን ተሸፍነው ይጸልዩ። በሰባቱም ሰዓታት ኢየሱስ ክርስቶስ አዳምን ለማዳን የተቀበላቸውን መከራ እያሰቡ መጸለይ ይገባል። ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ምጽአትን እያሰብን ልንጸልይ ይገባል። ጠዋት በሰላም ላሳደረን አምላክ ምስጋና አቅርበን ውሏችንን የሠመረ ያደርግልን ዘንድ የምንለምንበት ሊሆን ይገባል። ጌታችን ለሐዋርያት በጾም እና በጸሎት የሚሸነፉ አጋንንት እንዳሉ ነግሯቸዋል። ስለዚህ አጋንንትን ለማራቅ ሕይወታችን መልካም

እንዲሆን እንጹም እንጸልይ። በዓበይት በዓላትና በሰንበት አይሰገድም። ነገር ግን በሰሙነ ሕማማት ማንኛውም በዓል ቢውል ይሰገዳል። ለምሳሌ የስቅለት ቀን የማርያም በዓል ወይም በዓለ እግዚአብሔር ቢውል ይሰገዳል። ስቅለት ራሱ ከዓበይት በዓላት አንዱ ሲሆን የሚከበረው በስግደት ነውና። በስግደት ለፈጣሪ መገዛታችንን እንገልጣለን።

ውትድርና

ውትድርና ክፍል ፩

ፖለቲካ እርኩስ ነው እያሉ እኛን እንድንርቀው እያደረጉ እነርሱ ገብተው የሚያረክሱ ሰዎች አሉ። ፖለቲካ ሕዝብን የማስተዳደር ጥበብ ነው። ይህ ጥበብ ደግሞ ከፈጣሪ የተሰጠ ነው። ከፈጣሪ የተሰጠውን ሀብተ መንግሥት እንደ ናቡከደነጾር ከተጠቀምነው እርኩስ ይሆናል። እንደ ቆስጠንጢኖስ ከተጠቀምነው ይቀደሳል። ስለዚህ አሁን ላይ ያለው ፖለቲካ የተበላሸ ከሆነ ገብተህ የማስተካከል ድርሻው የአንተ ነው። የዲዮቅልጥያኖስ አስተዳደር ክርስቲያኖችን በአዋጅ የሚገድል ነበር። ይህንን የተበላሸ ፖለቲካ የቀየረው እና የክርስቲያኖችን መብት ያስጠበቀው ቆስጠንጢኖስ ነው። ስለዚህ ፖለቲካ በራሱ ርኩስ አይደለም። ሥልጣኑን ያገኙ ሰዎች ይህንን ተገን አድርገው ርኩሰት ሊሰሩ ይችላሉ። ይህ ከሆነ ገብቶ ማስተካከል እንጂ ርኩስ ነው ብሎ መራቅ የፈጣሪን ጸጋ መናቅ ነው። ሀብተ ክህነት ሀብተ መንግሥት ከፈጣሪ የተሰጡ ጸጋዎች ናቸው። እኒህን ገንዘብ ያደረገ ሰው ክፉ ሊሆን ይችላል። እኒህ ሀብቶች ግን ውድ ስጦታዎች ስለሆነ ከክፉ ሰው ፈልቅቀን ማውጣት ከእኛ ይጠበቃል። በመሠረቱ አዳም ከተፈጠረ በኋላ ከተሰጡት ሰባት ሀብታት አንዱ ሀብተ መንግሥት ነው። ይኼውም ፍጥረቱን ሕዝቡን በትክክል እንደሚገባው ማስተዳደር ነው። ይህ ሀብተ መንግሥት በዚያን ዘመን ወደቀጣዩ ንጉሥ የሚተላለፈው በቡራኬ ነበር። አዳም ሴትን ባርኮ በእርሱ ምትክ እንዲገዛ አድርጎታል። ሴት ሄኖስን እያለ ለብዙ ዘመን በዚህ መልኩ ገዥነት ይተላለፍ ነበር። ጊዮርጊስ ወልደ ሐሚድ የተባለውን መጽሐፍ መመልከት ይቻላል። የሚገርመው አዳም ሴትን ሴት ሄኖስን ባርከው ንግሥናን ሲያስተላልፉላቸው ዋና ንግግራቸው ሕዝቡን በመልካም አስተዳደር አስተዳድር፣ የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲጠብቁ አስተምር የሚል ነበር። የንጉሥነት ቀዳሚ ሥራ ሕዝቡን በእምነት መጠበቅ ነበር። ከዚያ ቀጥሎ ለሁሉም እንደሚገባው ያለ አድልዎ በፍቅር ማስተዳደር ነበር። ይህ ዓይነት ንግሥና እስከ ኖኅ ጊዜ ደርሷል። ከኖኅ በኋላ ይህች ንግሥና ለሦስት ተከፍላለች። ለሴም፣ ለያፌት እና ለካም ይህ እየበዛ እየበዛ ሄዶ አሁን ከ200 በላይ መንግሥታት አሉ። ወደፊትም ሊጨምር ይችላል። ወይም ሊቀንስ ይችላል። ወይም ባለበት ሊቀጥል ይችላል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 44 ከቁጥር 1530 ጀምሮ ስለ ነገሥታት ይናገራል። ቁጥር 1532 ላይ ወይኩን አሚኖቱ ፍጹመ በእግዚአብሔር ይላል። በእግዚአብሔር ይመን። የኢያሪኮ ግንብ በእምነት ፈርሷልና። በእምነት ጌዴዎን፣ ባርቅ፣ ዮፍታሔ እና ሶምሶን ጠላ*ትን አሸንፈዋልና። ወኮኑ መዋዕያነ በውስተ ጸብዕ እንዲል። ንጉሡ ከሃዲ ከሆነ ከዘመነ ወንጌል ወዲህ ንጉሥ አይባልም። ዐመፀኛ ነው እንጂ። ነገሥታትን የሚሾም እግዚአብሔር ነው። ንጉሥ መልካም ከሠራ ልንገዛለት ካልሠራ ልንቃወመው ይገባል። ቁጥር 1544 ወኢትንሣእ ንዋየ መኑሂ በኃይል በጉልበት የማንንም ገንዘብ አትውሰድ። አክአብና ኤልዛቤል የናቡቴን

የወይኑን ቦታ በመውሰዳቸው ተቀስፈዋልና ይላል። አስተውል ንጉሥ አመጸኛ ሲሆን መቃወም እንደሚገባን አብነታችን ነቢዩ ኤልያስ ነው። የናቡቴን ገንዘብ መልስ ብሎ ተቃውሟልና። ከላይ እንደተቀመጠው የንጉሥ ዳዊት፣ የባርቅ፣ የዮፍታሔ ንግሥና በሐዲስ ኪዳንም ተደንቋል። ቅዱስ ጳውሎስም በዕብ.11፣32 ገልጾታል። እኒህ የተጠቀሱ ሰዎች ደግሞ በዘመናቸው የነበረውን ጠላ*ት ያሸነፉት ወታደር ይዘው ነው። ያውም ጌዴዎን ጥራት ያላቸው ወታደሮችን ነው የያዘው። ከብዙ ሺ ወታደሮች እግዚአብሔር በነገረው መሥፈርት ብቁ ሆነው የተገኙትን ነው የመረጣቸው። ስለዚህ ወታደር በእግዚአብሔር መሥፈርት ማለትም ሕጉን ትእዛዙን የሚሠራ ልበ ሙሉ መሆን አለበት። በሥርዓተ መንግሥት ውስጥ ወታደር አለ። ዳኛ አለ። ሰብዓ ዓይን ወይም ሰላይ አለ ብቻ ብዙ ክፍል አለ። እያንዳንዱን በተወሰነ መልኩ በቀጣይ ክፍሎች አቀርባለሁ።

ወታደር ክፍል 2

ጀግና ወታደር የሚለካው አንደኛው በሥነ ምግባሩ ነው። ከጠላት ጋር ጦር በገጠመ ጊዜ ከጠላት ወገን ሴቶች ጋር ዝሙት አይፈጽምም። ጦርነት የገጠመው ዝሙት ለመፈጸም ሳይሆን ጠላትን ሊያጠፋ ነውና። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 44 ቁጥር 1549 ወሶበ ተሐውር ኀበ ጸብዕ ምስለ ሠራዊትከ ለፀቢዐ ጸርከ ተዐቀብ እምኩሉ ግብር እኩይ። ጠላትህን ለመውጋት ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለህ በዘመትክ ጊዜ ከዝሙት ተጠበቅ። ክርስቲያናዊ ወታደር በዚህ ይታወቃል። በነገራችን ላይ ማንኛውም ክርስቲያን ከካህናት ውጭ ወታደር መሆን ይችላል። ካህናት ግን መሣሪያ ይዘው ሰይፍ ይዘው እንዲገጥሙ አይፈቀድም። ካህናት የማንንም ደም እንዲያፈሱ አልተፈቀደም። ካህናት ክህነት ሲሾሙ የክርስቶስን ሥጋና ደም የሚፈትቱ ናቸውና። ስለዚህም ካህናት ሰው ከገደሉ ከክህነታቸው ይሻራሉ። ከካህናት ውጭ ያለ ምእመን ግን ወታደር ሆኖ በጦርነት ጊዜ ጠላትን በመግደሉ ኃጢኣተኛ አይባልም። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ጠላቱን መክስምያኖስን በመግደሉ ኃጢኣት አልሆነበትምና። ካህናት በጸም በጸሎት ሊያግዙ ይችላሉ። ከኃጢኣቱ የማይመለስ ሰው ካለ ወደፈጣሪ ጸልየው በጸሎታቸው ጠላትን ሊያጠፉ ወይም ሊገድሉ ይችላሉ። መሣሪያ ይዘው ሰይፍ ይዘው ግን ማንንም እንዳይገድሉ ሥርዓት ተሠርቷል። በጸሎት ግን ከኃጢኣቱ በማይመለሰው መዝ.34ን ግፍያሙ እግዚኦ ለእለ ይገፍኡኒ ጽብኦሙ እግዚኦ ለእለ ይጸብኡኒ ብለው ይጸልዩበታል። ከኃጢኣቱ ለሚመለሰው ደግሞ አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብለው ያስምራሉ። ቅዱስ ጴጥሮስ ሐናንያን እና ሰጲራን በጸሎቱ በመግደሉ በደለኛ አልተባለም። የሊቀ ካህናቱን ጆሮ በሰይፍ በመቁረጡ ግን ተወቅሶበት ነበር። ስለዚህ ካህናት በሰይፍ በጦር ከጠላት ጋር ገጥመው ሊገድሉ አይገባም። ምእመናን ግን ወታደር ሆነው ጠላትን በመግደላቸው በደል አይሆንባቸውም። ንጉሥ የተሾመ ያጠፋን ሊቀጣ መልካም የሠራን ሊሾም ነውና። ለፍጹማን የሚጠቀሰውን ጥቅስ ለወጣንያን እየጠቀሱ የሚያወናብዱ ሰዎች አሉ። ለምሳሌ በወንጌል ጌታችን ፍጹም ልትሆን ከፈለግህ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ተከተለኝ ብሏል። ይህ ትእዛዝ ለፍጹማን የተነገረ ነው እንጂ። ይህንን ላልቻለ ሰው ንብረት አፍርቶ ሚስት አግብቶ ቢኖር ኃጢኣት አይሆንበትም። ጠላትህን ውደድ የሚለው ጥቅስ ለምሳሌ በሁለት መልኩ ሊተረጎም ይችላል። አንደኛው ለፍጹማን ንብረታቸውን ሁሉ ቢዘርፋቸው ሚስታቸውን ሁሉ ቢቀማቸው እንደ

የዋሕ ጳውሎስ አንቺም የተባረክሽ ሁኝለት አንተም የተባረክ ሁንላት ብሎ ትቶ መሄድ ነው። ይህንን ማድረግ ያልቻለ ደግሞ ያለፍትሕ የእርሱ ያልሆነውን ገንዘብ ሌላ ሰው መጥቶ ሲወስድበት ጦር አንስቶ ቢገጥመው በደል አይሆንበትም። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ጣልያንን መግጠሚ በደል አይሆንባትም። ጠላትህን ውደድ ተብሏልና ምናለበት ያን ጊዜ ጣልያንን ወደን ብትወረንም ዝም ብንል የሚል ሰው ካለ የመጻሕፍትን ቃል አልተረዳም ማለት ነው።

ወታደር ክፍል 3

ወታደር ሞትን የማይፈራ ልበ ሙሉ ቆራጥ መሆን አለበት። ዮሐ.15፣13 "ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" እንዳለ ወታደር ሌላውን ሕዝብ ለማዳን ራሱን ለሞት አሳልፎ የሚሰጥ ነው።ለሌላው ሰው ሰላም እርሱ በውርጭ፣ በቀን፣ በሌሊት፣ በበረሃ፣ በደጋ ሳይሰቀቅ የሚዋጋ ነው። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 44 ቁጥር 1550 ለእመ ወጻእከ ለጸብዕ ላዕለ ጸርከ ጠላትህን ለመውጋት ብትወጣ። ወርኢከ አፍራሰ ወሰረገላተ ወሕዝበ ዘይበዝኑ እምኔከ ኢትፍራኅ እምኔሆሙ። ከአንተ የሚበዙ ብዙ ሕዝብ ብዙ ሠረገላ ብዙ ፈረስ ብታይ ከብዛታቸው የተነሳ አትፍራ። እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ምስሌከ። እግዚአብሔር ፈጣሪህ በረድኤት ከአንተ ጋራ ነውና። መዋጋት በጀመርክ ጊዜ ካህን እነሆ ጠላታችሁን ለመውጋት ትሄዳላችሁና ልቡናችሁ አይሸበርባችሁ ወኢትትገሐሡ እምቅድመ ገጸሙ። ከፊታቸው አትሸሹ ይበላቸው። ቁጥር 1551 ምእመናን ወደ ጦር ሲሄዱ በፊታቸው መስቀል አቁመው ይስገዱለት። ወታደር ብዙ የጠላት ወገን ሲመጣ የሚርበተበት የሚርድ መሆን የለበትም። ካህናት ጦር አንስተው ጠላትን መግጠም እንደማይገባቸው ባለፉት ክፍሎች ተመልክተናል። ነገር ግን ከጦሩ ጋር ሄደው የቆሰለ ማከም፣ ምግብ ማቀበል እና የመሳሰሉ ሥራዎችን ይሰራሉ። በጎንደር ዘመነ መንግሥት ንጉሡ የካቶላክ እምነትን በሀገሪቱ ለማስፋፋት ባሰበ ጊዜ የንጉሡ ባለሟሎችና አብዛኛው ሕዝብ ጦርነት ገጠመ። ጳጳሱ አቡነ ስምዖን ከአርቶዶክስ ምእመናን ጋር ሆነው ንጉሡን ጦርነት ገጠሙት። በዚህ ጊዜ ጳጳሱ ጦር አላነሱም። ከጦሩ መካከል ተገኝተው ግን ወታደሮችን አይዟችሁ በርትታችሁ ተዋጉ። ሃይማኖትን ለመለወጥ የተነሳን ንጉሥ ስትዋጉ ብትሞቱ ሰማእት ናችሁ እያሉ ያበረታቱ ነበር። በዚህ ጦርነት እሳቸውም በጠላት ጦር ተገድለዋል። በፋሺስት ዘመንም በኢትዮጵያ የሆነው ይሄው ነው። ሰማእቱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ከአርበኞች ጋር ሆነው ሀገራቸውን ከጠላት ለማዳን ይጥሩ ነበር። ነገር ግን እሳቸው ጳጳስ ስለሆኑ ጦር ይዘው ማንንም መግደል አይችሉም። የቆሰለን ማከም፣ የደከመን ማበርታት ግን ይችላሉ። ይህንን የተመለከተ ፋሽስት አቡነ ጴጥሮስን በአደባባይ ገድሏቸዋል። ወታደር ሞት አይፈራ መሆን አለበት። ሌላውን ሰው ለማዳን እርሱ ደረቱን ለጦር ሰጥቶ የሚዋጋ መሆን አለበት። ይህም ስለሌላው ራሱን አሳልፎ የመስጠት ፍቅር ነው።

ወታደር ክፍል 4

ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 44 ቁጥር 1553 ወለእመ በጻሕክሙ ኀበ ሀገር አው ኀበ ብሔር ከመ ትትቃተልዎሙ ለሰብአ ዚኣሃ ጸውዕዎሙ ለከዊነ ዕርቅ። በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ጠላቶች ለመውጋት ወደሀገሪቱ ብትሄዱ መጀመሪያ እንታረቅ በሏቸው። ከጠብ ምንም እንደማይገኝ

ጠቅሶ መታረቅ እንደሚገባ የእርቅ ጥያቄ አቅርብ። እርቁን አንፈልግም ብለው በጠላትነቱ ከቀጠሉ ግን ግጠማቸው። ቁጥር 1554 ወለእመ ኢተወክፉክሙ ለከዊነ ዕርቅ ወተጋደሉክሙ ወተጻብኡክሙ ጽብእዎሙ ወአዕፅቁ ላዕሌሆሙ አንታረቅም ብለው ቢወጓችሁ ግን አስጨንቃችሁ ውጓቸው። ቢገቡላችሁ እጃቸውን ቢሰጧችሁ ይቅር በሏቸው። እስመ እግዚአብሔር ይቤ ብጹዓን መሐርያን። እግዚአብሔር የሚምሩ ብጹዓን ናቸው ብሏልና። እጅ ለሚሰጥ ወታደር ምሕረት ይደረጋል። ጀግና ወታደር እጅ ለሚሰጥ ምሕረት የሚያደርግ፣ እጅ ለማይሰጥ ሰው ደግሞ እስከ ሞት ድረስ የሚፋለም ነው። ወታደር ወደ ጠላት ሀገር ገብቶ ሲገጥም ሽማግሌዎችን፣ ሕጻናትን፣ ባልቴቶችን፣ ካህናትን ሊገድላቸው አይገባም። ተዋጊውን ጠላት ለይቶ መፋለም ይገባል እንጂ። ቁጥር 1556 ወለእመ አገትካ ለሀገር ወነበርከ ላእሌሃ ብዙኅ መዋእለ ከመ ትትቃተል እስከ ያርኅው ለከ። ኢትግዘም አእዋሚሃ። ዛፎቿን ተክሏን አትቁረጥ አለ ካህናቱን ሕጻናቱን ባልቴቶቹን ሽማግሌዎችን አታጥፋ እስመ ዕፀወ ገዳም ኢይክሉ ጎይይ እምኔክሙ። እነዚህ ከእናንተ መሸሽ አይቻላቸውምና። ወለእዕሰ እንተ ኢትፈሪ ግዘምዋ። አርበኞችን ግን አጥፏቸው።ድል እስክትነሷቸው ድረስ ሰዎቿን ውጓቸው። ስለዚህ ወታደር እጅ ለሚሰጥ መሐሪ፣ እጅ ለማይሰጥ እስከ ሞት የሚፋለም መሆን አለበት። ጠላቱን ለይቶ የሚመታ መሆን አለበት። ሽማግሌዎችን እና ሰላማውያን ሰዎችን የማያስጨንቅ እና የማይጎዳ መሆን አለበት።

ወታደር ክፍል 5

የወገንን የጦር መረጃ ለጠላት የሚያቀብል ወታደር ወይም ጠላት ያሸንፍ ዘንድ መሣሪያ ለጠላት የሚሸጥ ቅጣቱ መቃጠል ነው።ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 44 ቁጥር 1561 ጠላቶች ድል እንዲያደርጉ የተመከረውን ምክር ለጠላት የሚናገር ቢኖር ወይም ወደእነርሱ ሸሽቶ ሂዶ መሣሪያ የሸጠላቸው ሰው ቢኖር ሰቅለው ያቃጥሉት። ጠላት የወገንን ጦር መረጃ ካወቀ ወገንን ለማጥቃት የሚረዳውን ዘዴ ያገኛል። ይህ እንዳይሆን ወታደር ምሥጢረኛ መሆን አለበት። ቢማረክ እንኳ ምሥጢሩን ከሚያወጣ ተገድሎ ሰማእትነትን ቢቀበል ይሻለዋል። ወታደር ለወገን መናገር ያለበትን ምሥጢር ይናገራል። ለሚመራው የጦር አዛዥ መናገር ያለበትን ምሥጢር ለአዛዡ ይናገራል። የራሱ ብቻ ምሥጢርም ሊኖረው ይችላል። ወታደር አይዋሽም። እውነትንም ግን በምሥጢር ይይዛታል እንጂ አይናገራትም። ለምሳሌ አንድ መንግሥት 100,000 ወታደር ቢያስመርቅ ይህ እውነት ቢሆንም መቶ ሺ ወታደር አስመረቅሁ ማለት ግን የለበትም። ምክንያቱም ጠላት የወታደሩን ብዛት ታሳቢ ያደረገ እና በቁጥር ብልጫ ይዞ ሊያጠቃ ይችላልና ነው። ወታደር ያለበትን መልክአ ምድር ማሳወቅ የለበትም። ለጠላት Geographical Advantage መስጠት ይሆናልና። ወታደር ጠላትን ለማሸነፍ የተለያዩ ዘዴዎችን ሊጠቀም ይችላል። ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፈ መሳፍንት እንደተነገረው 300 ቀበሮ ሰብስቦ በጅራታቸው መካከል ችቦ አብርቶ ጠላትን ያሸነፈ አለ። በሌላም በሌላም ዘዴ ጠላታቸውን ያሸነፉ አሉ። ስለዚህ ወታደር ለጠላት ሊጠቅሙ የሚችሉ ጂኦግራፊያዊ መረጃዎችን፣ የጦር መሳሪያ መረጃዎችን፣ የቁጥር መረጃዎችን እና የመሳሰሉት ነገሮች አሳልፎ ሊሰጥ አይገባም። እኒህን አሳልፎ የሰጠ ወታደር ከተገኘ በፍትሐ ነገሥቱ መሠረት ለሌላው ትምህርት ይሆን ዘንድ ሰቅለው በእሳት ያቃጥሉታል። ይህም ፍትሕ ሥጋዊ ነው።

ወታደር ክፍል 6

ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 43 ቁጥር 1562 ኃጢኣት ስለሠራችሁ እግዚአብሔር በጠላቶቻችሁ እጅ አሣልፎ ቢሰጣችሁ ማርከው ወደ ሀገራቸው ቢወስዷችሁ በሃይማኖታችሁ መጽናት ሕጋችሁን መጠበቅ ይገባችኋል። በመብል በመጠጥም ቢሆን መጽሐፍ ባዘዘው ሥርዓት መጽናት ይጠበቅባችኋል። በከመ ዳንኤል ወሠለስቱ ደቂቅ። ሠለስቱ ደቂቅና እነ ዳንኤል ተማርከው ባቢሎን በወረዱ ጊዜ ጥሬ በልተው ሃይማኖታቸውን ጠብቀው ቆይተዋልና። ስለዚህ ወታደር ቢማረክ እንኳ ሃይማኖቱን የማይለውጥ፣ ሥነ ምግባሩን የማይለውጥ መሆን አለበት። የማረኩት አካላት ከሃይማኖቱ የሚቃረን ነገር አድርግ ቢሉት እንኳ እምቢ ብሎ እስከ ሞት ድረስ መጽናት አለበት።መዝ.136 ውስተ አፍላግ ባቢሎን ህየ ነበርነ ወበከይነ ሶበ ተዘከርናሃ ለጽዮን። በባቢሎን ወንዞች አጠገብ ሆነን ጽዮንም ባሰብናት ጊዜ አለቀስን። ... ይልና ወበህየ ተስእሉነ እለ ጼወውነ ነገረ ማኅሌት በዚያም የማረኩን ሰዎች ዘምሩልን አሉን። እፎ ነሐሊ ማኅሌተ እግዚአብሔር በምድር ነኪር። የእኛ ባልሆነ ምድር በምርኮ ቦታ እንዴት እንዘምራለን ብለዋል። ይህ ዝማሬ በተለየ በቤተ መቅደስ የሚባል ዝማሬ ነው። ቤተመቅደስ ደግሞ ፈርሷልና እንዲህ አሉ። መማረክ ብቻውን ኃጢኣት አይሆንም። ወታደር የተቻለውን ያህል ተዋግቶ አልሆንለት ሲል ሊማረክ ይችላል። ነቢያቱ እነ ነቢዩ ኤርምያስ፣ እነ ነቢዩ ዳንኤል፣ እነ ነቢዩ ሕዝቅኤል ተማርከው ሄደው ነበርና። በጦርነት ጊዜ ተስፋ መቁረጥ አይገባም። እስከ መጨረሻው ጠላትን መዋጋት ይገባል እንጂ። ተስፋ ቆርጠን ራሳችንን ማጥፋት እና የመሳሰሉ ከእግዚአብሔር ሕግ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ልናደርግ አይገባም። እስከ ሞትክ ድረስ የፈጣሪን ሕግ ጠብቀህ ልትኖር ይገባል እንጂ። ስለዚህ ለወታደር ከእግዚአብሔር ውጭ የሚበልጥ ምንም ነገር ስለሌለበት የፈጣሪን ሕግ መጠበቅ አለበት። በመጽሐፈ ነገሥት እንደተጻፈው ኢዮስያስ ታላቅ ንጉሥ ነበረ። ነገር ግን በኋላ በጦርነት ሞቷል። በጦርነት መሞቱ ግን ክብሩን አልቀነሰበትም። ወታደር ክብር ያለው ነው። ስለዚህ ክብሩን መጠበቅ አለበት።

ወታደር ክፍል 7

ኦሪት ዘኍልቁ ምዕራፍ 13 ኢያሱ እና ካሌብ ሰላይ (ጉበኛ) ሆነው ሀገራቸውን አገልግለዋል። ይህም ሊዋጉት ያሰቡትን ጠላት መረጃ አስቀድሞ ለማወቅ ይጠቅማል። ታላቁ እስክንድር ዓለምን ሲገዛ ኢትዮጵያን አልገዛትም። እስክንድር ዓለምን ለመግዛት በዋናነት የጠቀመው ስለላ ነው። አስቀድሞ ወደዚያ ሀገር ተመሳስሎ ይገባና የሀገሪቱን መረጃ አጥንቶ ይመለሳል። ከዚያ ወታደር ይዞ ሀገሪቱን በእርሱ ሥር ያደርጋት ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ግን የሆነው ያልጠበቀው ነገር ነው። እስክንድር ስሙ ገናና ስለነበር የኢትዮጵያ ንግሥት ሰላይ አስልካ መልኩን አስቀርጻ አስመጥታ ታውቀው ነበርና ገና ሲገባ ተይዞ ማንነቱ ሲነገረው ተደንቋል ይባላል። ችግሩ አሁን አሁን ስለላ (ጉበኝነት) ለሀገር ሳይሆን ለጥቂት ፖለቲካዊ ቡድኖች ባሪያ እንዲሆን ሆኗል። ሰላዮችም አለማቀፋዊ እና አህጉራዊ መረጃን አይሰበስቡም። እዚያው እርስ በእርስ ሕዝቡ እንዲለያይ ባል ሚስቱን ሚስት ባሏን እንድትሰልል ነው እየተደረገ ያለው። ስለዚህ ደህንነት ወይም ስለላ የጥቂት ፖለቲካዊ ቡድኖች ባሪያ መሆን የለበትም። ሕዝባዊ እና ሀገራዊ መሠረት ሊኖረው ይገባል። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ያጠፋን እንዲቀጣበት ያለማን እንዲሾምበት ብለው 318ቱ ቅዱሳን ሊቃውንት ፍትሕ ሥጋዊን ሰርተውለታል። በፍትሕ

መንፈሳዊ ካህናት፣ ጳጳሳት ምእመናንን ይመሩበታል። በፍትሕ ሥጋዊ ነገሥታት መኳንንት ሕዝቡን ይመሩበታል። በፍትሕ መንፈሳዊ መግደል የለም። በፍትሕ መንፈሳዊ የመጨረሻው ቅጣት ከቤተክርስቲያን አውግዞ መለየት ነው። በፍትሕ ሥጋዊ ግን የመጨረሻው ቅጣት እስከ መግደል ይደርሳል። ነገሥታቱ መኳንንቱ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘውን ሳያዳሉ በሕጉ መሠረት መታሰር የሚገባውን ያሥሩታል። መገደል የሚገባውን ይገድሉታል። በንግሥና እና በፍርድ ወንበር ተቀምጠው በትክክል ካልፈረዱ ግን ሰማያዊ ቅጣት ይቆያቸዋል። ፈጣሪ ያነገሣቸው ጥፋተኛን ይቀጡ ዘንድ ሕዝቡን በሰላም ያስተዳድሩ ዘንድ ነውና። ስለዚህ ክርስቲያኑ በእያንዳንዱ የመንግሥት መስሪያ ቤት ገብቶ ሕዝቡን በመልካም አስተዳደር ሊመራው ይገባል። እንጂ ከሥልጣኑም ከውትድርናውም ከሁሉም እየሸሸን ቦታውን ለሌላ አሳልፎ መስጠት አይገባም። እመሰ ተአምር ባቲ ገረገራ ዋልድባ ይእቲ እንዲሉ። ከታወቀበት ሁሉም ለጽድቅ ይሆናል።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር

ከአሁን በኋላ የሆነ ግለሰብ ሆያ ሆየ ስላለ እሱን ተከትለው ምእመናን አላስፈላጊ መሥዋእትነት መክፈል የለባቸውም። ቀጥታ ከሲኖዶስ፣ ከወረዳ ቤተ ክህነት፣ ከሀገረ ስብከት፣ ከአጥብያ ካህናት ጋር እየተመካከርን ማድረግ ያለብንን በሚዲያ በመጮህ ሳይሆን ከቤት መክረን እናደርጋለን። ይህንን አጽንታችሁ ያዙልኝ። የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ አዳነች አቤቤ ወይም ዐቢይ አሕመድ እንዲወስኑልህ አትፍቀድ። እነርሱ በእኛ ቤተክርስቲያን ምንም አይመለከታቸውም። በእኛ ቤተክርስቲያን ጉዳይ የሚመለከተን ቀጥታ እኛን ነው። እኛ አንድ ሁነን እንምከር። ሃይማኖታዊ ቦታዎቻችንን ማንም እንዲነጥቀን አንፈልግም። ምክንያቱም የእኛ የክርስቲያኖች ርስት ቤተ ክርስቲያን ናት። እርሷ ሥርዐተ አምልኮዋን የምታደርግበትን ቦታ ማንም ሊፈነጭበት አይገባም። ይህ እውነታው ነው። እንዲህ ከሆነ ታድያ ሌላ መርሐ ግብር ሲካሄድበት የእኛ ምላሽ ምን ይሁን የሚለውን እኛው ከቤት ከጠቅላይ ቤተክህነቱ ከአጥቢያ ቤተክርስቲያናችን ከማኅበራት ጋር መክረን እናደርጋለን። የእኛን ለሌላው የሚሰጥ መሪ ወይም ፖለቲከኛ ካለም እኛን የማይመለከተን ስለሆነ እኛን የሚመለከተንን መሪ እኛው እንመርጣለን። ማንም እንዲጫወትብን እድል አንሰጥም። ይህንን አጥብቃችሁ ያዙልኝና እስከ ክፍል 12 ድረስ ትክክለኛ ትንቢት፣ ትክክለኛ ሕልም፣ ትክክለኛ ተአምር በምን ይታወቃል?! ሐሰተኛ ነቢያት እንዲህ ተብሏል እያሉ ይናገራሉ። ሕዝቡም እውነት እየመሰለው ራሱን ያስጨንቃል። ይኽውም ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ባለማወቁ ምክንያት ነው። መንፈሳዊ ትምህርት የጀመረው በማህበራዊ ሚዲያ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በአክቲቪዝም ስሜት ሆኖ ሊረዳው በመሞከር አብዛኛው ወደ ክህደትና ወደ ምን*ቅና (*=ፍ) ገደል እየገባ ነው። ስለዚህ በተቻለን አቅም ብሉይ ኪዳን ስለ ትንቢት ምን ይላል። የነቢያቱ መጻሕፍት ትንቢትን ምን ብሎ ይገልጸዋል? ቅዱስ ጳውሎስስ ስለ መንፈሰ ተነብዮ ምን ይላል? የሚለውን እናያለን። ለምሳሌ ዘንድሮ በጦርነት ነው ያሳለፍነው። ብዙው መሬት አልታረሰም ነበር። ስለዚህ ከየካቲት ጀምሮ ረሀብ ይሆናል የሚል ትንቢት ዛሬ ቢነግሩህ ይሄ ትንቢት ነው ወይ? የሚለውን እናያለን። ምክንያቱም ይሄ የምክንያትና የውጤት ሳይንስ (cause & effect) ነው እንጂ ትንቢት አይደለም። ከገደል ወርውሬህ አካሉ ይጎድላል ብየ ትንቢት ብናገር ከመቶ

95% ሊደረግ የሚችልን ነገር ነው የነገርኩህ። ምናልባት የፈጣሪ ነገር በተአምር ሊያድንህ ከቻለ ደግሞ ትንቢቱ ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርብኝ (ንሥሓ ከገባህ ወይም እግዚአብሔር በቸርነቱ ይቅር ካለህ ግን ምንም አትሆንም) እልና ራሴን አድናለሁ። ይህ ቀልድ ነው ወይስ ትንቢት?! ይህንን በሰፊው እንማማራለን። ሁለት አካላት ተሰዳድበው፣ ለግድያ እየተፈላለጉ መሆኑን ተረድተህ፣ አንደኛው መሳሪያውን እየወለወለ (የመሳርያ ትርኢት እያሳየ) ካየኸው በኋላ ጦርነት ይሆናል ብለህ ትንቢት ብትናገር ይሄ ትንቢት ይባላል እንዴ? ይሄኮ ሊሆን 90% የቀረው ድርጊት ነው። ታድያ ይሄ እውነት ትንቢት ነው? የሚለውን እናያለን። በዚህ ዙሪያ ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ካላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 1

ሕወሀት የመሳሪያ ትርኢት እያሳየች ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት ደግሞ በየሚዲያው ሕወሃትን ያጥላላልኛል ብሎ ባሰባቸው ነገሮች ሁሉ እያጥላላ ነው። በዚያም በዚህም ይህ ተጠናክሮ ቀጠለ። ከዚያ ኮድ ተፈጠረ ይሄውም ኮድ ለሕወሀት "የቀን ጅብ" የሚል ሲሆን ለኢትዮጵያዊው መንግሥት ደግሞ "ፋሺስት" የሚል ስም ወጣለት። በእነዚህ ኮዶች መቀጣቀጥ ተጀመረ። መካከል ላይ በረኽሞች እየተባሉ አባ ዘወንጌል እንዲህ አሉ እየተባለ ተነገረ። እድሜያቸውም 600 ዓመት እንደሆነ ተነገረ። (ሕዝቤ እውነት ግን 600 ዓመታቸው ነው ወይ? ብሎ አልጠየቅም ዝም ብሎ መከተሉን ተያያዘው)። አባ ዘወንጌል ታላቅ ጦርነት ይደረጋል በሽታ ይሆናል መጨረሻ ላይ ረኀብ ይሆናል አሉ ተብሎ ተነገረ። (ይህንን የራሳቸው አገልጋይ ረድኣቸውን ያገኙና ያናገሩ መምህር አባ ዘወንጌል እንዲህ ብለው እንዳልተናገሩ ነግረውናል)። ይህንን ጉዳይ ቀድሞ አምኃ ኢየሱስ የተባለ ሰውየ የ2008ቱን ግርግር ምክንያት አድርጎ ተናግሮ ነበር። በወረቀትም ተበትኖ ነበር። ፌጦ ሰብስቡ ጎንደር ትጠፋለች የሚል ነበረ። በወቅቱ የነበረውን የመንግሥት ሥርዐት ጎንደር ላይ 2008 ሕዝቡ ጠንካራ ተቃውሞ አድርጎ ነበር። በዚህም ምክንያት በ1997 አዲስ አበባ ላይ እንደሆነው የሕዝቡን ኃይለኝነትና በወቅቱ የነበረውን የመንግሥትን ግትርነት በማየት መሳሪያው ያለ ከመንግሥት ስለሆነ ሕዝቡን አጠፋለሁ ሲል ጎንደር ትጠፋለች በሚል ስሌት "የጎንደር ከተማ" ትወድማለች ብሎ አስነገረ። ጉዳዩ ሳይሆን ቀረ። ትንቢቱ ቀረበት። መካከል ላይ በሕወሀትና በማእከላዊው መንግሥት ያለውን መካረር ያዩ ሰዎች ደግሞ ከበረሃ ተናገሩ እየተባለ ጦርነት ይነሳል ረኀብ ወረርሽኝ ተነስቷል እየተባለ ተነገረ። ይችንኮ መገመት እንኳን ሀሁ የቆጠረ ሕሊና ያለው ሰው ሁሉ ያውቀዋል። ግማሹ ይህ ጦርነት እንዳይደረግ እርቅም ምንም ለማድረግ ይጥራል። ሌላው ደግሞ ትንቢቱ ነው አይቀርም እያለ መናገሩን ቀጠለ። ይህ ብቻ ይህንን የሚናገሩ ሰዎች የሆነን ብሔር መበደል ደጋግመው በማውራት የዚያ ብሔር ተወላጆች ቂም እንዲይዙ አደረጉ። ቂም ይዘውም ኃይለ ቃል መናገር ሲጀምሩ የሌላው ብሔር ደግሞ አጸፋዊ ምላሽ እየሰጠ ግንኙነቶቻችን እየሻከሩ እየባሱ ሄዱ። ሕወሀትና የማእከላዊው መንግሥት ቅራኔም ተባባሰና ጦርነቱ ጥቅምት 24 ተጀመረ። ከዚያ አሁን የሆነው ሆኗል። ስለዚህ የሕወሀትንና የሌላውን Political Issue ያወቀ ሰው ይህ ፍጻሜው ይህ እንደሚሆን ያውቀዋል። በዚህ ሰሞ የኤርትራ ፕሬዜዳንት ቃለ መጠየቅ አደረጉ ተብሎ ሲነገር በቃለ መጠይቁ ውስጥ "የጎሳ ፖለቲካውን ሰነድ አሳይተውኝ ነበር። እኔም ይህ ነገር መጨረሻው አያምርም። ለጠብ ይዳርጋል" ብየ ነበር

ብሏል። ከ30 ዓመት በፊት የአሁኑ ድርጊት ሊሆን እንደሚችል በpolitical analysis አውቆት ነበር። እንጂ ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ ከዐበይት ነቢያት አንዱ ሆነው አይደለም። ጥቅምት 24 ጦርነቱ ተጀመረ። ብዙ ውጣቶች አለቁ። ብዙ ወታደር ሞተ። በነገራችን ላይ 9ኛ ክፍል History ላይም ተምረነዋል። ከጦርነት ውጤቶች (The consequence of War) ውስጥ ይህን ተከትሎ ረሀብ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ በሽታ ወረርሽኝ ናቸው ተብለናል። ስለዚህ ይህንን ለማወቅ ነቢይነት አይጠይቅም። ምክንያቱም ኃይለ ቃል መነጋገር ወደ ጠብ ይመራል። ጠብ ወደመገዳደል ያደርሳል። መገዳደል ደግሞ ማኅበራዊ ቀውስ ያስከትላል። ኢትዮጵያ ላይ የሆነው ይህ ነው። ሰው ባሕታውያንን ይወዳል። ስለዚህ ጠላት የሚወደንን መስሎ ራሱ ሊያደርገው ያሰበውን ያደርጋል። ጎንደር ትጠፋለች። ወዘተ የሚል ትንቢት ካለ ጎንደርን ለማጥፋት የሚፈልገው አካል ያስነገረው ንግግር ሊሆን እንደሚችል መጠርጠር ያስፈልጋል። በጣልያን ዘመን ፋሽስት ያሸንፋል እያሉ ጣልያን ያሰለጠነቻቸው ባንዳዎች ነበሩ። እና የተወሰነው ሰው ትንቢቱ ነው እያለ ሳይዋጋ ለጣልያን አደረ። ኢትዮጵያም በጠላት እጅ ወደቀች። የጣልያን ተጽእኖ ጎጃም ላይ ቀላል ነበር። አርበኞቹ እነ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ፣ እነ ቢትወደድ መንገሻ ጀምበሬ፣ እና ሌሎችም አርበኞች ጣልያንን እረፍት ነስተው ለ5 ዓመታት እየተዋጉት ነበር። ምክንያቱ ምን መሰለህ የጎጃም አርበኞች ፀሐፊ ታላቁ ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ነበሩ። የሸዋን አርበኞች እየመሩ የነበሩት እስከ መሰቀል የደረሱት አቡነ ጴጥሮስ ነበሩ። ንግግራቸውን እዩት ትንቢቱ ስለሆነ ብለው ቁጭ አላሉም የ East Africa Geopolitics ትልቅ ስትራቴጂያዊ ቦታ ነው። ይህንን ቦታ ምዕራባውያንም ይፈልጉታል ሩቅ ምሥራቆችም ይፈልጉታል። በዚህ ምክንያት ጠብ ሊኖር ይችላል። የጥቅም ጉዳይ ሊያጣላቸው ይችላል። ይህንን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ምናልባት ሰላይ ከሆነ ሰባት የአረብ ሀገራትና ሁለት የምዕራባውያን ሀገራት ኢትዮጵያ ላይ ይገጥማሉ ብሎ ትንበያውን ትንቢት አድርጎ ሊናገር ይችላል። ይህ ሁለት ጥቅም ሊሰጥ ይችላል። አንደኛ የተወሰነው ሰው ካመናቸው አንድነትን ይሸረሽራል። እነርሱ ሊያደርጉት ሲያስቡ ፈተና የሚሆንባቸው የእኛ አንድነት ነው። ስለዚህ ግማሹን ትንቢት ብለው ሳይዋጋ እጁን እንዲሰጥ እና ካህናትን እየናቀ ጳጳሳትን እየተሳደበ አንድነቱን እንዲሸረሸር ያደርጉታል።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 2

ትንቢት ለክፉ ሰዎችም ለኃጥዓንም ሊሰጥ ይችላል። ትንቢት መናገር ብቻውን የጽድቅ ምልክት አይሆንም። በለዓም ጠንቋይ ነበር። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ፊቱን ጸፍቶ አፉን ከፍቶ የጌታን ልደት አስመልክቶ "ኮከብ ይሠርቅ እምያዕቆብ ወያአትት ኃጢኣተ ዓለም... ኮከብ ክርስቶስ ከያዕቆብ ይወለዳል። ተወልዶም ኃጢኣትን ያስተሠርያል" ብሎ ተናግሯል። ቀያፋም "ብዙ ሰው ከሚሞት አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል ብሎ በጌታ ላይ ተናግሯል"። እውነት ነው የአዳም ልጆች ሁሉ ከሚጠፉ ክርስቶስ ተሠቅሎ ቢያድናቸው ይበልጣል። ስለዚህ ትንቢት የተናገረ ሁሉ ጻድቅ ነው ማለት አንችልም። ጌታን ያሰቀለ ቀያፋ ትንቢት ተናግሯልና። ጠንቋዩ በለዓምም ትንቢት ተናግሯልና። ትንቢትን ቅዱሳን አባቶቻችንም ተናግረውታል። ስለዚህ አንድ ሰው እሆነ ወቅት ላይ የሆነች ትንቢት ተናግሮ ያች እውነት ብትሆንለት። የባለፈችዋን ተቀባይነት ይዞ የወደፊቱንም እመኑኝ ብሎ ሕዝብ ሊያስጨንቅ የራሱን ስሁት አስተሳሰብ ሊጭን ይችላል።

ይህን የምለው የብሉያት ትርጓሜ ስንማር የበለዓምን ፍጻሜ ሳየው ነው። ኦሪት ዘኍልቁ ምዕራፍ 22 እስከ ምዕራፍ 31 ያለውን አንብብ። መጀመሪያ እግዚአብሔር የባረከውን እኔ አልረግምም እያለ ነበር። ጥሩ ጥሩ ትንቢትንም ተናግሮ ነበር። በኋላ ባላቅን የመከረው ምክር ግን እስራኤላውያንን ያጠፋ ነበር። ትንቢት "ተነበየ=ተናገረ" ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ምእላድ ሲሆን ትርጉሙ በጊዜ፣ በቦታ፣ በሁኔታ ከእኛ የራቀውን ነገር በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት መናገር ማለት ነው። ስለዚህ ትንቢት ሦስት ነገሮችን ሊያካትት ይችላል። ይኸውም ያለፈውን ያሁኑንና የሚመጣውን ማወቅ ናቸው። ያለፈውን በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት መንገር እንደ ሙሴ ነው። ሙሴ ሊቀነቢያት ተብሏል። ዓለም ሲፈጠር አልነበረም። ነገር ግን የዓለም አፈጣጠር ተገልጦለት ጽፏል። ያለፈውን ያልነው ይህ ነው። አሁን ያለውን ማለት ደግሞ እንደ ነቢዩ ኤልሳዕ ነው። ኤልሳዕ ደቀመዝሙሩ ግያዝ የሶርያውን ንጉሥ ንእማንን ተከትሎ ሄዶ አጭበርብሮ ገንዘብ ተቀብሎ ሲመጣ በቦታው ሳይገኝ ባለበት ቦታ ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት አውቆ ነበር። ሦስተኛው ደግሞ የወደፊቱን ማወቅ ነው ይህ ደግሞ እንደ ነቢዩ ኢሳይያስ "እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች" ብሎ እንደተናገረው ነው። ትንቢት እኒህን ነገሮች ሁሉ ያጠቃለለ ቢሆንም በበዛው ግን የሚነገረው ትንቢት የሚለው የወደፊቱን ማወቅን ነው። በብሉያት ትርጓሜ እንደተማርነው ነቢያት በዋናነት ዐበይት ነቢያት እና ደቂቅ ነቢያት ብለን እንከፍላቸዋለን። ይህ አከፋፈል የጽሑፋቸውን ርዝመት መሠረት አድርጎ ነው። ዐበይት ነቢያት የሚባሉት 4 ናቸው እኒህም ሕዝቅኤል፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ እና ዳንኤል ናቸው። ደቂቅ ነቢያት የሚባሉት ደግሞ 12 ናቸው እኒህም፦ ናሆም፣ ዮናስ፣ ሆሴዕ፣ አብድዩ፣ ሶፎንያስ፣ ኢዩኤል፣ ዘካርያስ፣ ሐጌ፣ ሚክያስ፣ ሚልክያስ፣ ዕንባቆም እና አሞፅ ናቸው። ደቂቅነታቸው የጽሑፍ ነው። ትንቢታቸው በብዙ ጉዳዮች ላይ ያጠነጠነ ነው። አንዳንዱ በጊዜያዊው የእስራኤል ጉዳይ ያጠነጠነ ነው። አንዳንዱ ስለ ነገረ ክርስቶስ ነው። አንዳንዱ ጹሙ፣ ጸልዩ የሚል ትምህርት ነው። በየዘመናቱ ብዙ ሐሳውያን ነቢያት ነበሩ። ለምሳሌ በኤርምያስ ዘመን ኤርምያስ ከተናገረው በተቃራኒ ሕዝቡ መስማት የሚፈልገውን እየነገሩ ያደነገዙ የነበሩ ሐሰተኛ ነቢያት ነበሩ። እንዲያውም አንድ ጊዜማ ኤርምያስን ሸንት ቤት ሁሉ አስጥለውታል። ደግሞኮ የሐሰት ትንቢታቸውን ሲናገሩ "እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል" እያሉ በውሸትና በድፍረት ነበረ። ነቢይነት ለሁሉ የሚሰጥ አይደለም። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው 1ኛ ቆሮ.12፣10 ጸጋ ነው እንጂ።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 3

የትንቢት ዓይነቶች

#ትክክለኛ ትንቢት፦ ይህ ትንቢት 2ኛ.ጴጥ.1፣21 "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ"። 2ኛ ጴጥ.1፣20 "በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም በገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም"። የነቢያትን ትንቢት ማንም ለራሱ ዓላማ ሲል ቀየርየር እያደረገ ለራሱ ስሜት የሚስማማ እያደረገ ማቅረብ አይችልም። በገዛ ራሱ መተርጎም አይችልም። ከተነገረበት ዓውድ ተነስቶ ይተረጎማል እንጂ። 1ኛ ጴጥ.1፣10 "...ትንቢት የተናገሩ ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት"። የትክክለኛ ትንቢት መገለጫው ይህ ነው። ማዕከሉ ድኅነት ነው።

ድኅነት ደግሞ የማይነቅዝ እህል፣ በጨው የታሸ እህል፣ ፈጦ፣ የወይራ ቅጠል በመያዝ አይገኝም። ድኅነት የሚገኘው ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን በመፈጸም። ንሥሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን በመቀበል ነው። የትክክለኛው ትንቢት ሌላኛው መገለጫው ደግሞ መከራ እንደሚመጣ ቢታወቅንኳ ለዚህ እንደ ነነዌ ሰዎች ጾም ጸሎት ማወጅ ምሕላ መያዝ ነው እንጂ የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሂድ ትድናለህ አያሰኝም። ታድያ ሌላው ቤተ ክርስቲያን የማን ነው?! የኢየሱስ ሥጋ እና ደም የሚፈተትበት ባለቤቱ ክርስቶስ የሆነ አይደለምን!? በነቢዩ ኢሳይያስ እንደተነገረው ኢሳ.56፣5 "በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ሥም እሰጣቸዋለሁ" ብሎ ለቅዱሳን እግዚአብሔር ቃል ስለገባላቸው የገብርኤል የሚካኤል ይባል እንጂ የቤቱ ባለቤት ኢየሱስ ነው። ቅጥሬ እና ቤቴ ነው ያለ እንጂ ቅጥራቸው እና ቤታቸው አላለም። ይህንን ተረት ተረት የሚናገሩ "በረኽኛ እየተባሉ የሚንቀለጳጰሱ" ሰዎችን መስማት አይገባም። ምክንያቱም አንዲቷን ቤተክርስቲያን ለያይተዋታልና። #ሐሰተኛ ነቢያት ማቴ.7፣22 "....በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን ይሉኛል። እኔ ግን አላውቃችሁም እላቸዋለሁ" ብሎ ጌታ ተናግሯል። አስተውሉ ትንቢት ተናግረዋል። ትንቢት ሲናገሩ ደግሞ በጌታ ስም ነው። ጌታ ነግሮናል በማለት፣ በማስመሰል ወዘተ ይሰሩታል። ግን ነገሩ ውሸት ነው። እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያት የሕዝቡን ነባራዊ ሁኔታ አጥንተው፣ ሕዝቡ መስማት የሚፈልገውን እየተናገሩ የሚያታልሉ አጭበርባሪዎች ናቸው። ኤር.5፣31 "(ሐሰተኛ) ነቢያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ። ካህናትም በእነዚህ እጅ ይገዛሉ። ሕዝቤም እንዲህ ያለውን ነገር ይወዳሉ" ብሎ ታላቁ ነቢይ ኤርምያስ ይነግረናል። በዚያን ዘመን ሐሰተኛ ነቢያት የሚናገሩትን ሕዝቡ ይወደው ነበር። ነገር ግን ሕዝቡ የወደደው ትንቢቱ ልክ ስለሆነ አልነበረም። ስሜቱን ስለነገሩት ብቻ ነው እንጂ ውሸት ነበረ። ኤር.14፣14 "እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ ነቢያቱ ውሸት በስሜ ትንቢት ይናገራሉ። አላኳቸውም፣ አላዘዝኋቸውም....የልባቸውን ሽንገላ ይሰብኩላቸዋል" ይላል። አስተውልማ እኒህ ነቢያተ ሐሰት የራሳቸውን ግምታዊ እይታ ለሕዝቡ ትንቢት ነው እያሉ ይነግሯቸው ነበር እያለን ነው። ኤር.27፥10 "እናንተም እንድትጠፉ ሐሰተኛ ትንቢትን ይነግሯችኋል" ብሏል። ስለዚህ ሐሰተኛ ትንቢት እኛን ለማጥፋት የሚነገር ነው ማለት ነው። ሕዝ.13፣2 "ከገዛ ልባቸውም ትንቢት የሚናገሩትን የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ በላቸው" ይላል። ትንቢት በልብ ወለድ እና በመሰለኝ እንደማይነገር ደግሙ ከዐበይት ነቢያት አንዱ የሆነው ሕዝቅኤል ነግሮናል።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 4

ትንቢት ሊሻር ይችላልን?

በዚህ ረገድ ሁለት ዓይነት ትንቢቶችን እናስተውላለን። በፈቃደ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ትንቢት እና በግብረ ሰብእ ወይም በፈቃደ ሰብእ ላይ የተመሠረተ ትንቢት ነው። በሰው ሥራ ላይ የተመሠረተው ትንቢት እንደየሰው ሥራ ሊሻርም ላይሻርም ይችላል። በሰውየው ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው። ለምሳሌ የነነዌ ሰዎች ኃጢኣት ሠርተው ስለነበረ ነቢዩ ዮናስ በትንቢተ ዮናስ 3፣ 4 "በሦስት ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች" ብሎ ተነበየ። የነነዌ ሰዎችም ይህን በሰሙ ጊዜ ጾም፣ ጸሎት፣ ምሕላ አወጁ፣ ማቅም ለበሱ፣ ወደ እግዚአብሔርም ጮሁ። እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ። እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ

ከተናገረው ክፉ ነገር ተመለሰ። አላደረገውምም ይላል። የነነዌ መጥፋት እና አለመጥፋት ከእግዚአብሔር ምሕረት በተጨማሪ በሰዎች ግብር ላይ የተመሠረተ ነበር። ከክፉ ሥራቸው ባይመለሱ ኖሮ ነነዌ ትጠፋ ነበር። ከክፉ ሥራቸው ስለተመለሱ ደግሞ ነነዌ ሳትጠፋ ቀርታለች። ስለዚህ ይህ በሰዎች ሥራ ላይ የተመሠረተ ትንቢት ነው። ነገር ግን ረድኤተ እግዚአብሔርም ያልተለየው ነው። በሌላ ምሳሌም ሕዝቅያስ በመበደሉ ምክንያት 2ኛ ነገ.20፣1 "ትሞታለህ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል" ተብሎ ነበር። ነገር ግን ንሥሓ በገባ ጊዜ 2ኛ.ነገ.20፣6 "በእድሜህም ላይ 15 ዓመት እጨምራለሁ" ተብሏል። የመሞቱና ያለመሞቱ ትንቢት ግብረ ሕዝቅያስን መሠረት ያደረገ ነበር። ንሥሓ ባይገባ ይሞት ነበር። ንሥሓ በመግባቱ ግን 15 ዓመት ተጨምሮለታል። ስለዚህ ዐይነት ትንቢት ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ.13፣8 "ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም። ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል" ይላል። ይህ የሚሻረው ዓይነት ትንቢት ግብረ ሰብእን መሠረት ያደረገው ትንቢት ነው። የሰውን ነጻ ፈቃድ መሠረት ያደረገ ትንቢት ነው። እግዚአብሔር አዳምን በዘፍ.2፣17 "...ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ብሎ እፀበለስን አዳም ቢበላ እንደሚሞት ካልበላ ግን እንደማይሞት ተነግሯል። ይህ ትንቢት ነው። ነገር ግን ትንቢቱ በአዳም ነጻ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው። ስለዚህ አዳም ዕፀበለስን ካልበላ ትንቢቱ ይቀራል። እፀ በለስን ከበላ ግን ትንቢቱ ይፈጸምበታል። ይህ ዓይነቱ ትንቢት ግብረ ሰብእን ወይም ፈቃደ ሰብእን መሠረት አድርጎ እንደየሰው ፈቃድ ሊሻርም ላይሻርም የሚችል ነው። ሌላም በወንጌል ያመነ የተጠመቀ ይድናል፣ ሥጋየን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፣ የሚሉ ቃላት ለመዳን ዋናው የእግዚአብሔር ቸርነት ቢሆንም ነገር ግን እኒህን የተባልናቸውን ነገሮች በማድረጋችንና ባለማድረጋችን ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ሁለተኛው ፈቃደ እግዚአብሔርን መሠረት ያደረገ ትንቢት ሲሆን ይህ አይሻርም። መደረጉ አይቀርም። ይህ ተሻረ ከተባለ ግን እግዚአብሔር በየዘመናቱ ይለዋወጣል የሚል ክህደትን ስለሚያመጣ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ መቼም መች አይለወጥም። መዝ.101፣26-27 "ሁሉ እንደ ልብስ ያረጃል። እንደ መጎናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ ይለወጡማል። አንተ ግን ያው አንተ ነህ" ተብሎ እንደተጻፈው። ለምሳሌ በኃጢኣት የወደቀውን አዳምን ማዳን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ስለዚህ አዳምን ለማዳን ሰው ሆኗል። ለዚያ ነው ሊቃውንት በመዝሙረ ዳዊት የአንድምታ ትርጓሜ ላይ መዝ.44፣7 "አፍቀርከ ጽድቀ ወዐመፃ ጸላእከ" የሚለውን ሰው መሆንን ወደድክ አለመሆንን ጠላህ ብለው የሚተረጉሙት። በፈቃደ እግዚአብሔር ላይ ብቻ የተመሠረተ ትንቢት አይሻርም አይለወጥም። ይኽውም ኢሳ.7፣14 "እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች" እንዳለው ያለው ነው። በሁሉን ዓዋቂነቱ ድንግል ማርያም "ይኩነኒ" እንደምትል አውቆ ፈቃዷን አይቶ ከእርሷ እንደሚወለድ ያውቅ ነበርና መወለዱን በነቢዩ አናገረ። ለምሳሌ ዳግም ምጽአት እንዳለ ፍየሎችን ማለትም ኃጥዓንን በግራ በጎችን ማለትም ጻድቃንን በቀኝ እንደሚያቆማቸው ጌታችን በማቴ.25፣31 ተናግሯል። ይሄ ግብረ ሰብእን ወይም ፈቃደ ሰብእን መሠረት አድርጎ ሊሆንም ላይሆንም የሚችል ትንቢት አይደለም። ፈቃደ እግዚአብሔርን መሠረት ያደረገ ስለሆነ ዳግም ምጽአቱ በፍጹም አይቀርም። ነገሮችን ከመሆናቸው በፊት የሚያውቅ እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆነውንም ስለሚያውቅ ያንን እውቀቱን በጸጋ ለነቢያት ሰጥቶ ያናግራቸዋል። ሮሜ.9፣13 "ኤሳውን ጠላሁ ያዕቆብን ግን ወደድኩ" የሚለው ንግግር ያዕቆብ ካደገ በኋላ የሚሠራውን ኤሳውም ካደገ በኋላ የሚሠራውን

በሁሉን አዋቂነቱ ስላወቀ እንዲህ አለ እንጂ ያዕቆብን እንዲወደድ ኤሳውን እንዲጠላ አድርጎ ስለፈጠራቸው አይደለም።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 5

የሼህ ሁሴን ትንቢት

ሕወሀት መቀበሪያዋ ራያ ነው የሚል ይዘት ያለው በግጥም መልኩ የቀረበ ጽሑፍ የሼህ ሁሴን ነው ተብሎ በማኅበራዊ ሚዲያ እየተዘዋወረ ነበረ። አብዛኛው ሰው ከግጥሙ ውስጥ ያሉ የአንዳንድ ትንበያዎችን (Prediction) እውን መሆን አይቶ ሕወሀት ራያ ላይ ትቀበራለች የሚለውን ትንቢት ወደማመኑ እየተጠጋ ሄደ። ሕወሀትም ትቀበራለች በተባለችበት መጥታ Surprise አደረገችን። በአፋር በወሎ በኩልም ውጊያ አደረገች። በእርግጥ እንዲህ ዓይነት ትንቢት እየተባለ ሲናፍስ መጀመሪያ መጠየቅ ያለብን በእውነት ይህንን ያሉ ሼህ አሉ ወይ? ብሎ መጠየቅም ይገባል። ካሉስ የግል አስተያየታቸውን ወይም ምኞታቸውን ነው የጻፉት ወይስ ማን ነው የነገራቸው? የሚለውን ሁሉ አጥርቶ ማወቅ ይገባ ነበር። ያች ግጥም የአብዛኛውን ሰው ስሜት የምትገልጥ ስለሆነች ብቻ እውነተኛ ተደርጋ በአብዛኛው የዋህ ሰው ተወሰደች። በነገራችን ላይ እንዲህ ሞኝ እና ተላላ ሕዝብ ሲገኝ ሊያጠፋው የፈለገው አካልም በዚህ መልኩ ሊመጣበት ይችላል። ለምሳሌ ሕወሀት ራሷ ወይም ማእከላዊው መንግሥት ይህንን ትንቢት ሊያናግሩ ይችላሉ። ይሄውም በራያ በኩል ከሁለቱ አንዱ በቂ ዝግጅት አድርጎ ለመቅበር/ለመቀበር ወደ ራያ ሲሄድ አንድ በአንድ ለመልቀም ሊያመቻች ይችላል። ይኸውም ተዋጊው አካል ሌላ የመዋጊያ ግንባር እንዳያስብ ያደርጋል። ይህ ዘዴ ትንቢቱን ያናገረው አካል በጦርነቱ Advantage ለማግኘት ይጠቅመዋል። በነገራችን ላይ ትንቢት ለእስላሙም ለክርስቲያኑም ለፕሮቴስታንቱም ሊገለጥ ይችላል። እግዚአብሔር ዝናምን፣ ፀሐይን፣ ክረምትና በጋ ሳይለያይ ለሁላችን እንደሚሰጠን ሁሉ ትንቢትንም ራሱ እግዚአብሔር ባወቀ በተለያየ ምክንያት ለማንም ሊገልጥ ይችላል። በለዓም ጠንቋይ ነበረ ነገር ግን ትንቢት ተናግሯል። ያንን ትንቢት ያናገረው ግን እግዚአብሔር ነው።የተባለው የሼህ ሁሴን ትንቢት ጉዳዩ እውነት ቢሆን እንኳ የሃይማኖታቸውን ትክክለኝነት አያስረዳም። በለዓም ጠንቋይ ነበረ። ቁጥሩም ከአሕዛብ ነው። ትንቢት ስለተናገረ ግን ጠንቋይነት ወይም አሕዛብነት ልክ ነው ማለት አይደለም። አንድ ሰው የተነበየው ትንቢት ተፈፀመ ማለትም ያ ሰው በጎ ምግባር ያለው ሰው ነው ማለት አይደለም። ቀያፋ ጥሩ ትንቢት ተናግሮ ነበር። ነገር ግን ጌታን እንዲሰቀል ያደረገ ምግባረ ብልሹ ሰው ነበረ። እግዚአብሔር ለእስላሙም ለክርስቲያኑም እኩል ፀሐይን ስለሚያወጣ ሁለቱም ሃይማኖት ትክክል ስለሆነ ነው አይባልም። ሃይማኖት አንዲት ናት። ኤፌ.4፣4። ስለዚህ ወደፊትም ብዙዎች ሊያደርጉት ያሰቡትን ትንቢት እያሉ ሊያናግሩ ይችላሉ። እኔ አሁን "በረኽሞች እንዳሉት ካህናት ሊቃውንት፣ ጳጳሳት ያልቃሉ። ጥቂት ብቻ ይተርፋሉ" ተብሏል የሚል ሳይ የሚሰማኝ ስሜት "ካህናትን፣ ሊቃውንትን፣ ጳጳሳትን" ለመግደል ያቀደ አካል እንዳለ ነው የሚሰማኝ። ከዚህ ጋር አያይዘው ደግሞ እኒህ ሁሉ ካህናት የሚያልቁት "መቅደሱን ስላቆሸሹ ነው" የሚል ማስተባበያ መስጠታቸው ነው። እናም ምእመኑ አባቶቹን እንዲጠላ በሚዲያ በጣም እየተሰራ ነው ያለው። ወደ አባቶቹ ቀርቦ ንሥሓ ገብቶ ሥጋውን ደሙን የሚቀበለው ጥቂት ነው። ይህንን በንስር ዓይን ልናስተውለው ይገባል። እንዲህ ዓይነት

ንግግሮች አባቶቻችንን የሆነ አካል ቢያጠፋቸው እንኳ ተዘጋጅተን እንዳንጠብቃቸው ትንቢቱ ነው ብለን እጃችንን አጣጥፈን እንድንቀመጥ የሚያደርግ አደገኛ አደንዛዥ ንግግር ነው። ይልቅስ እንመራበት ዘንድ ከፈጣሪ ሕግ ተሰጥቶናል። በዚያ ሕግ መሠረት እንኑር። ከዚያ ውጭ በሆነ ባልሆነው እየሰጉ መኖር ክርስቲያናዊ አኗኗር አይደለም። ማህበራዊ ቀውስ ካለ ያንን ለመፍታት ውይይቶችን እያደረግን መፍታት። ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ካለ የሀገራችንን ኢኮኖሚ ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ። ፖለቲካዊ ቀውስ ካለ ፖለቲካውን ተረድቶ አሰላለፍን አሳምሮ መፍትሄ ማበጀት ነው እንጂ ትንቢት ነው ብለህ እህትህ ስትደፈር፣ ንብረትህ ሲዘረፍ ጫትህን እየቃምክ ዝም ብለህ አትቀመጥ። አንተ ጫትህን እየቃምክ ሌላ ሰው ከሌላ ቦታ መጥቶ እንዲያድንህ አትሻ።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 6

ቴዎድሮስ ይነግሣል

በቴዎድሮስ ሥም የሚያጭበረብሩ ራሳቸውን "ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን" የሚሉ አጨበርባሪዎች በዘመናችን ተነስተዋል።በተለያዩ ገድላትና ድርሳናት ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥብበኢትዮጵያ እንደሚነሳ እና በእርሱ ዘመን ተድላ ደስታ እንደሚኖር ተጽፏል። እነዚህን መሠረትብአድርጎ በትርጓሜ ወንጌል ላይም በሐተታ መልኩ ቀርቧል። ነገር ግን ቴዎድሮስ እንዴት ይነሳል? ከየት ይነሳል? ለሚሉ ጥያቄዎች ገድላቱም ዝርዝር ጉዳዮችን አይገልጹም። ከዚያ ይልቅ በንግርት ብቻ ከዚህ ነው ከዚህ ነው እየተባለ ይነገራል። ንግርት የሚባለው ብዙ ጊዜ ምንጩ የማይታወቅ እንዲሁ ይባላል እየተባለ የሚነገር ማለት ነው። እውነትም ሊሆን ይችላል ውሸትም ሊሆን ይችላል። እንግዲህ ንጉሥን የሚያነግሥ እግዚአብሔር ነው። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ንጉሥ አይነግሥም። ሕዝቡ ቢበድል ሕዝቡን ይቀጣ ዘንድ ዓላዊ ንጉሥን ሊያነግሥብን ይችላል። ይኽውም ለእኛ ጥቅም ነው። ከአመፃችን ተመልሰን በፍቅር እንድናመልከው ነው። ሕዝቡ መልካም ቢሆን ደግ ንጉሥ ያነግሣል። ለዚያ ነው በትርጓሜያችን ደግ ንጉሥና ደግ ጳጳስ ለማየት የፈለገ ሰው ደግ ይሁን የተባለው። ይህ የቴዎድሮስ ነገር ገድላቱ ላይ ይጻፍ እንጂ መቼ እንደሚሆን? እንዴት እንደሚሆን አይታወቅም። ነገር ግን ይህንን የገድላትን እና የድርሳናትን መጻሕፍት ያነበቡ እና ይህንን ነገርም ለራሳቸው ዓላማ ለማዋል የተነሱ በየዘመናቱ ተነስተዋል። ለምሳሌ በጎንደር ዘመነ መንግሥት እኔ ቴዎድሮስ ነኝ ብሎ ከቀሃ ወንዝ ተነስቶ ብዙ ሰዎችን ያስከተለ ሰው ነበር። ነገር ግን ንጉሡ አስጠርተው አስገደሉት። ልክ እንደዚህ ሰውየ በገድላት ስለቴዎድሮስ የተጻፈውን ለራሳቸው ዓላማ ሲሉ ብቻ በራሳቸው መንገድ እየተረጎሙ ኢትዮጵያን ለማበጣበጥ የተነሱ ሰዎች አሉ። "ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን" ብለው ራሳቸውን ሰይመው መታወቂያ እያደሉ ይህንን መታወቂያ የያዘ ንጉሡ ቴዎድሮስ በመጣ ጊዜ በሰላም ይኖራል እያሉ የዋሁን ሕዝብ ያታልሉበታል። ይገርማችኋል ገድላቱ እና ድርሳናቱ ላይኮ መታወቂያ የያዘ ይድናል አይልም። ተክለጻድቅ መኩሪያ በጻፉት የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮስ ባለው ላይ "እጓለ አንበሳ የተባለ መነኩሴ በቀሃ ወንዝ በኩል መጥቶ ጥሩንባ እያስነፋ ነግሻለሁ ሲል አዋጅ ነገረ። ስሜም ቴዎድሮስ ነው። ዘመነ መንግሥቴም እስከ ሺ ዓመት ነው እያለ ያስወራ ጀመር። እንደዚህም እያለ ጎንደር ከተማ ገባ።ከዚያ በወቅቱ የነበሩት ንጉሥ አንገቱን በሰይፍ ቆርጠው ገደሉት።

አሁንም በገድላቱ የተጻፈውን ለራሳቸው ዓላማ ለመጠቀም ሲሉ የሕዝቡን በጦርነት መቸገር አይተው ሕዝቡ መስማት የሚፈልገውን ቴዎድሮስ ነግሦ በተድላ በደስታ እንዲኖር በባዶ ተስፋ እየነፉ ብዙ የዋሃንን ወስደዋል። በነገራችን ላይ ንጉሥን የሚያነግሥ እግዚአብሔር ነው። እንጂ እኛ ተደራጅተን ቆይተን የምናነግሠው አይደለም። ቴዎድሮስን ተደራጅተን ቆይተን እንደምናነግሠውም ገድላቱ አይናገሩም። "ገዳም ነው የሚያድገው ሥውራን አባቶች ናቸው የሚያውቁት" የሚለውም ከተጠያቂነት ለመሸሽ የተፈጠረች ዘዴ ናት። እንለ አንበሳምኮ ከገዳም የመጣ መነኩሴ ነበር። ቴዎድሮስ ነኝ አለ ተገደለ። የመጻሕፍትን ቃል ለራስ ዓላማ ማዋል እንደማይገባ ቅዱስ ጴጥሮስ በሁለተኛ መልእክቱ 2ኛ ጴጥ.1፣20 "በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም በገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም" ብሎ ነግሮናል። ግርም ያለኝ ደግሞ ጎጃም አካባቢ ያሉ የዚሁ የኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን አባላት ይሄ ቴዎድሮስ የሚነሳው ጎጃም አድያማ ከተባለ ቦታ ነው ይላሉ። ጎንደር አካባቢ ያሉት ደግሞ ከስሜን ተራራ ነው ይላሉ። ወሎ አካባቢ ያሉት ደግሞ ከአቡነ አሮን ዘመቁት ገዳም ነው ይላሉ። ሸዋ አካባቢ ያሉት ደግሞ ከየረር ተራራ ነው ይላሉ። የሰውን ጎጠኝነት ከተረዱ በኋላ በጎጥ በጎጡ ተስፋ እንዲያደርግ አደረጉት። ስለዚህ የተጻፈውን ቴዎድሮስ በተሳሳተ መልኩ ለራሳቸው ዓላማ እየጠቀሱ የወሰዷችሁ ሰዎች ከእንቅልፋችሁ ንቁና ወደ እናት ቤተክርስቲያን ተመለሱ። ይልቅስ ዝም ብለህ ተቀምጠህ ቴዎድሮስን ከምትጠባበቅ ተደራጅተህ ሰፈርህን ጠብቅ። ቴዎድሮስን የሚያመጣው እግዚአብሔር ነው!። በምን መልኩ እንደሚያመጣው የሚያውቀውም እግዚአብሔር ነው። እንጂ አንተ ስለተደራጀህ አይመጣም። ቴዎድሮስን ተደራጅተው ለማምጣትማኮ የቀሃው መነኩሴው አድርጎት ነበር። በዚህ መልኩ ስለማይሆን አልሆነም እንጂ። የኢትዮጵያን አረጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ እያሳዩህ እነርሱ ወደሚፈልጉት ዓላማ እንዲወስዱህ አትፍቀድ። አያ በሬ ሆይ፣ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ እንደተባለው የምትወዳትን ባንዲራ እያሳዩህ ወደክፉ ዓላማቸው አይውሰዱህ።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 7

የመረጃ ነቢያት

በነገራችን ላይ የፍሥሓ ያዜ የሳጥናኤል ጎል በኢትዮጵያ የሚለው መጽሐፍ ልብ ወለድ ነው። አንዳንድ ሰዎች እንደ አዋልድ መጽሐፍ ሲጠቅሱት ሳይ ይገርመኛል። ዓለማቀፋዊውን የፖለቲካ አሰላለፍ (Geo-politics) ፣ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ በደንብ አድርጎ አጥንቶ ያዘጋጀው የልብ ወለድ መጽሐፍ ነው። እንደ ልብ ወለድነቱ እኔም በጣም አድንቄዋለሁ። ምንም እንኳ ልብ ወለድ ቢሆንም ልብ ወለድ የሚጻፈው የገሀዱን ዓለም መሠረት አድርጎ ስለሆነ አንዳንድ እውነታዎች ይኖራሉ። ይህ ደግሞ የልብ ወለድ አጻጻፍ አንዱ መርሕ ነው። እና እነዚያን ብቻ አይተን የሳጥናኤል ጎል በኢትዮጵያ የሚለው መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ እውነት ነው ማለት ግን አይቻልም። ወቅታዊውን ዓለማቀፋዊና ሀገራዊ የኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ መረጃዎች ቀምሞ ነው ያዘጋጀው። ስለዚህ እርሱ ከጻፈው መጽሐፍ ላይ አንዳንድ ነገሮች ሲደረጉ ስናይ ፍሥሓ ያዜ ነቢይ ሆኖ ተገልጦለት የጻፈው ሳይሆን መረጃውን ተንትኖ ሊደረግ የሚችለውን ነው በልብ ወለድ መልክ ያዘጋጀው። ይህንን የመሰሉ ጉዳዮችን በትክክል የሚያስረዳን ሊቁ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ስለ አባ እንጦንስ የጻፈው የበረሃው ኮከብ

የሚለው መጽሐፍ ነው። የመረጃ ነቢይነትን ጠንቋዮችም የሚያደርጉት ነገር ነው። ይኽውም መረጃን መሠረት አድርገው የሚናገሩት ነው። ይኽውም ለምሳሌ እኔ ከጎንደር ተነስቼ አዲስ አበባ ወዳለው ጠንቋይ ለመሄድ ብፈልግና ይህንን ጉዳይ ከጥቂት ሰዎች ጋር ብነጋገር እና ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ከጎንደር ስነሳ "ሰይጣን ረቂቅ ስለሆነ በፍጥነት ሄዶ አዲስ አበባ ላለው ጠንቋይ እንዲህ ያለ ሰው ወደአንተ ይመጣል ይለዋል"። በዚህ ጊዜ ጠንቋዩ ከሰይጣን ሰምቶ እዚያ ላሉት ሰዎች እንዲህ ዓይነት ሰው ከጎንደር ይመጣል ብሎ ልቡን ነፍቶ ይናገራል። እኔ ግን ሐሳቤን ቀይሬ አዘዞ ስደርስ ብመለስ የዚያ ጠንቋይ ንግግር ከንቱ ሆነ ውሸት ሆነ ማለት ነው። አዲስ አበባ ብደርስም ግን ያ ጠንቋይ የወደፊቱን አላወቀም። ከጎንደር መነሳቴን አይቶ ተናገረ እንጂ አስቀድሜ ከጎንደር ሳልነሳ አልተናገረውምና። ይህን ደግሞ እኛም ልናደርገው የምንችለው ነው። ከድሬድዋ ወደ አዲስ አበባ በባስ የሚሄድ ሰው ካለ በስልክ ደውለን አዲስ አበባ ላለ ሰው "እገሌ ይመጣል" ብንል ይህ መረጃን መሠረት አድርገን እየተናገርን እንጂ እየተነበይን አይደለም። ሌላው ልምድን መሠረት ያደረገ ትንበያ ወይም ትንቢት አለ። ብዙ ጊዜ ታላላቅ ሽማግሌ ገበሬዎችን ጠይቋቸውማ። በሆነ አቅጣጫ ሲፈልቅ ሲያዩ "ዛሬ ዝናብ ይዘንባል" ይላሉ። እንደተባለውም ሊዘንብ ይችላል። ይህ በእድሜያቸው ምክንያት ልምድን መሠረት አድርገውብየተናገሩት ነው። በዚያ በኩል ሲፈልቅ ብዙ ጊዜ ሲዘንብ ካስተዋሉ በኋላ የሚናገሩት ነው። ነገር ግን ይህም እንደፍጹም እውነት አይታይም። አልፎ አልፎ ከለመዱትና ካሉት በተቃራኒ ሊሆን ይችላልና። ሌላው ለምሳሌ ዘንድሮ የታረሰውን መሬት እና በአማካይ ያ መሬት ሊያወጣ የሚችለውን ምርት ካየን በኋላ ተመጋቢው በአማካይ የሚጠቀመውን አስልተን ምርቱ አነስተኛ መሆኑን ከተረዳን በኋላ ዘንድሮ ረኀብ ይሆናል ብንል ይህ በመረጃ የተመሠረተ ንግግር እንጂ ትንቢት አይደለም። ሰይጣንም የ7514 ዓመት ልምድ ያለው ስለሆነ አንዳንድ ነገሮችን በመገመት እና እነዚያ እውን በመሆናቸው ሰዎች ሊያምኑት ይችላሉ። ነገር ግን እንደገበሬዎቹ ልምድን መሠረት አድርጎ እንጂ ሰይጣን የወደፊቱን አያውቅም። እንኳን የወደፊቱን ሰይጣን የልብን አያውቅም። የቤተሰብህን መረጃ አሰባስቦ፣ የአንተን ብዙ ማስረጃ አስጠንቶ በሌላ ባሕታዊ መሰል ሰው ይልክብህና አንተ እገሌ አባትህ እገሌ እንዲህ ነበርክ.... ፈጣሪ እንዲህ እንድትሆን ከዛሬ ጀምሮ ጠርቶሀል እያሉ የሚያጭበረብሩ አሉ። አንተም ብዙ ምሥጢርህን ስላወቀ እግዚአብሔር ገልጦለት መስሎህ ቀጥሎ አድርግ ያለህን ታደርጋለህ። ይህን ጊዜ ትልቅ ኪሳራ ይደርስብሀል። የመረጃ ነቢያት መረጃ አሰባስበው የሚሆነውን የሚናገሩ ናቸው። የፖለቲካውን አሰላለፍ በጥሩ መረጃ ከተነተኑ በኋላ እገሌ ይነግሣል የሚሉ ናቸው። የወታደራዊ ምሥጢሮችን መረጃ ከያዘ በኋላ በዚህን ጊዜ ጦርነት ይደረጋል የሚል ሰው የመረጃ ነቢይ ይባላል። ትክክለኛው ከእግዚአብሔር የሚገለጠው ትንቢት ግን እንዲህ መረጃ ተሰብስቦ የሚታወቅ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ አለብሞ የሚገልጥልን ነው።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 8

የተወገዘ ሲኖዶስ

ምእመናን ከምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ተሳትፈው ድኅነትን እንዳያገኙ ሲኖዶስ ተወግሏል፣ ክህነት ረክሷል፣ እንደምታዩት ብዙው ቁስ ሌባ፣ ሙሰኛ፣ ዘማዊ፣ ሰካራም ሆኗል፣ ስለዚህ ክህነት አይሰራም ፣ እና በዚያ ምትክ ከመቅሰፍት ለመዳን ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን የሚባለው

አጭበርባሪ ድርጅት የሚሰጠውን መታወቂያ መያዝ እና ልሙጡን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ መያዝ መቅሰፍቱን እንድንሻገር ይረዳል የሚሉ የዋሃን አሉ። ንጉሡ ሲመጣ መታወቂያችንን እያየ ሁሉን ሲቀስፍ እኛን ይተወናል ይላሉ። እትየ ስመኝ የምትባል መልከ ጥፉ ነበረች ይባላል። እና አንድ ቀን ተኳኩላ ተጣጥና ትወጣለች። እና አስቀድሞ የሚያውቃት ወንድ እትየ ስመኝ ለማያውቁሽ ታጠኝ አለ ይባላል። ራሱ ክርስቶስ ሥጋየን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እያለ፣ ካህናትን በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሁን ብሎ ተናግሮ እያለ ከጌታ ቃል ይልቅ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን እንዳንፈጽም የሚከለክል ድርጅት የሰይጣን መሆኑን ልንገነዘበው ይገባል። ካህናት ኃጢኣተኛ ሊሆኑ ይችላሉ። በኃጢኣታቸው ግን ፈጣሪ ይቀጣቸዋል። ነገር ግን ኃጢኣተኛ ቢሆኑም ጸጋውን በእነርሱ አድሮ ይሰጠናልና በትሕትና ቀርበን ንሥሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን እኛ እንቀበል በኃጢኣታቸው ደግሞ ፈጣሪ ይፍረድ። ሌላው አለቃ አያሌው ሲኖዶስን አውግዘውታል ስለዚህ አሁን እኛ የተወገዝን ነን የሚሉ ጥቃቅን ሰዎችንም እየተመለከትን ነው። በነገራችን ላይ ሊቀ ጠበብት አለቃ አያሌው ታምሩ ለቤተክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ በመሆን ያገለገሉ ታላቅ አባት ናቸው። ቅዱስ ናቸው ግን አንልም። እንደማንኛውም ሰው ሊሳሳቱ ይችላሉ። ስለዚህ ያደረጉት ድርጊት በኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ይመዘናል እንጂ እሳቸው ያሉት በሙሉ ልክ ነው አይባልም። ሲጀምር በፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ ላይ እንደተቀመጠው ቁስ ጳጳስን፣ ጳጳሳ ፓትርያርክን ማውገዝ አይችልም። ቁስ የቁስን፣ ጳጳስ የጳጳስን፣ ፓትርያርክ የፓትርያርክን ግዝት ከሞተ በኋላ መፍታት ይችላል። ፓትርያርክ የጳጳስን፣ ጳጳስ የቁስን ግዝት ከሞተ በኋላም በሕይወት እያለም መፍታት ይችላል። አስተምህሮው ይህ ነው። በተረፈ ፓትርያርክ ያወገዘውን ሲኖዶስ ይፈታዋል። ስለዚህ የተወገዘ ሲኖዶስ የለንም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፓትርያርኩም፣ ቁሱም ሊበድሉ ይችላሉ። በዚህን ጊዜ በደላቸው ራሳቸውን ይጎዳል እንጂ በእነርሱ ምክንያት ቤተክርስቲያን አትቆሽሽም። በሰዎች ድርጊት የምትቆሽሽና በሰዎች ድርጊት የምትነጻ ቤተ ክርስቲያን የለችንም። የእኛ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የነጻች ንጽሕት ናት። ፓትርያርኩም በድለው ከነበረ በግላቸው በፈጣሪ ዘንድ ይጠየቁበታል። ቁሱም በድሎ ከሆነ እንዲሁ። በይሁዳ ክህደት ሐዋርያነት አልረከሰም። ይሁዳ ራሱ ቢክድ ራሱ ተጎዳ እንጂ። የእስክንድርያው ፓትርያርክ አትናቴዎስ ብዙ ጊዜ ከመንበሩ በአርዮሳውያን እየተሳደደ በምትኩ ሌላ አርዮሳዊ ፓትርያርክ እየተሾመ ነበር። አርዮሳዊ ፓትርያርክ ስለተሾመ የግብጽ ሲኖዶስ ተወገዘ የግብጽ ምእመናን ተወገዙ ግን አልተባለም አይባልምም። ስለዚህ የእኛ ሲኖዶስ ሐዋርያዊ ነው። ለምሳሌ የሮማው ፖፕ ልዮን ሁለት ባሕርይ ባለ ጊዜ ዲዮስቆሮስ አውግዞታል። ዲዮስቆሮስ ያወገዛቸው ደግሞ በልዮን ሐሳብ የተስማሙ ሙሉ የኬልቄዶን ጉባኤን ነው። በመዓርግማ ከተባለ ቅዱስ ገብርኤልስ ሳጥናኤልን አውግዞ የለምን ስለዚህ አለቃ አያሌውም አቡነ ጳውሎስ ክደው ከሆነ ማውገዝ ይችላሉ የሚል አስተያየት አለ። እውነት ነው አቡነ ጳውሎስ ክደው ከነበረ ማውገዝ ይችላሉ። ሲኖዶስን ግን ማውገዝ አይችሉም። ምክንያቱም ሲኖዶሱ አልካደም። በጥንተ አብሶ ዙሪያ የጻፉ አቡነ ጳውሎስ ናቸው። እንጂ ሲኖዶሱ አይደለም። ስለዚህ ነጥሎ የጻፈውን አካል ማውገዝ ይቻል ይሆናል እንጂ ሙሉ ሲኖዶስን ማውገዝ አይችሉም። አቡነ ጳውሎስም ተጠሪነታቸው ለሲኖዶስ ነው እንጂ ሲኖዶሱ የፓትርያርኩ ተጠሪ አይደለም። ስለዚህ በአቡነ ጳውሎስም በአለቃ አያሌውም ግላዊ ችግር

ሊኖርባቸው ይችላል። ሁለቱንም ቤተ ክርስቲያን ትዳኛቸዋለች እንጂ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እነርሱ አይወስኑትም። ሁለቱም ግለሰቦች ናቸው። ስለዚህ መጽሐፍ ጽፈው ከሆነ የጻፉት መጽሐፍ ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ካልተጣረሰ እንቀበለዋለን። ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በተቃራኒ ጽፈው ከሆነም መጽሐፋቸውን አንቀበልም። የቤተ ክርስቲያን እድሜዋ ብዙ ነው። ሁለቱ ግለሰቦች ግን በዚህ በ100 ዓመት ውስጥ የነበሩ ናቸው። ባደረጓቸው መልካም ሥራዎች እንወዳቸዋለን። ከሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ተቃራኒ ካደረጉም አንቀበላቸውም። ፓትርያርክ ቢያጠፉ ፓትርያርክ ይወገዛል እንጂ ፓትርያርክ ቢያጠፉ ሲኖዶስም ይወገዝ የሚል ትምህርት የለንም። ክህነታችን ሐዋርያዊ ነው አልተቋረጠም። ስለዚህ የተወገዘ ሲኖዶስ የለንም።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 9

ቶ

የ"ቶ" ን ምሥጢር ንገረን ያላችሁኝ ሰዎች። "ቶ" ማለት፦

ተ.....ቱ.....ቲ.....ታ.....ቴ.....ት.....ቶ

እንዲል የ"ተ" ሳብዕ ወይም ሰባተኛ ፊደል ነው። ሌላ ምንም ዓይነት ምሥጢር የለውም። የቶ መስቀል ምናምን እያልክ መጽሐፍ ላይ የሌለን በትውፊት ያላገኘኸውን ድሪቶህን ጣለው። በእርግጥ የፊደላት የየራሳቸው ትርጉም አላቸው። ለምሳሌ ከላይ ያሉትን ፊደላት የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደሚከተለው ተርጉመዋቸዋል።

#ተ ማለት ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ሰው ሆነ ማለት ነው። ተ ብሂል ተሰብአ ወተሠገወ እማርያም እምቅድስት ድንግል።

#ቱ ማለት ክርስቶስ የአብ ክንዱ ነው ማለት ነው። ቱ ብሂል መዝራዕቱ ለአብ።

#ቲ ማለት እግዚአብሔር ተመስጋኝ ነው ማለት ነው። ቲ ብሂል ተአኪቲ እግዚአብሔር።

#ታ ማለት እግዚአብሔር ትጉህ ነው ማለት ነው። ታ ብሂል ታው ትጉህ እግዚአብሔር።

#ቴ ማለት ብርሃንን እውቀትን ገላጭ ክርስቶስ ነው ማለት ነው። ቴ ብሂል ከሣቴ ብርሃን።

#ት ማለት ፍጹም ደስታ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። ት ብሂል ትፍሥሕት ወሐሴት።

#ቶ ማለት የክርስቶስን ልደት እናምናለን ማለት ነው። ቶ ብሂል ነአምን ልደቶ ለክርስቶስ።

ብሔራውያን ሊቃውንት ፊደላትን እንኳ ነገረ ክርስቶስን እና ነገረ ቅዱሳንን እንዲወክሉ እያደረጉ እንዲህ እንዲህ እያሉ ሁሉንም ፊደላት ተርጉመዋቸዋል። ከዚህ ውጭ "የቶ" መስቀል እያሉ የሚጃጃሉ ሰዎችን ስታይ የሃይማኖት ትምህርት ባለመማራቸው ምክንያት እንደሆነ ልትገነዘብ ይገባል። ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል "ቶ" ቅርጽ ያለው አይደለም። "ተ" ቅርጽ ያለው ነው እንጂ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በተለያዩ አገልግሎቶች

የምንጠቀመው መስቀል "ተ" ቅርጽ ያለው ነው። "ቶ" የሚባል መስቀል የለም። ስለዚህ በሌለ ነገር ባንሸወድ መልካም ነው። ድርሳነ ዑራኤል ላይ "ቶ" ይነግሥ "ሚ" ይነግሥ እያለ የነገሥታቱን ስም የመጀመሪያ ፊደል ያስቀምጣል። ስለዚህ "ሚ" ሚናስ ይሁን ሚሪንዳ ይሁን ሚዳቋ ይሁን አይታወቅም። "ቶ" ይነግሥ የተባለ ቴዎድሮስ ነው ከተባለም። እግዚአብሔር ጊዜው ሲደርስ ያንግሠው እኛ ምን ቤት ነን ደርሰን አንጋሽ የሆነው?! ይልቅስ ይችን ጫፍ ይዛችሁ በ"ቶ" የምትነግዱ ነጋዴዎች እግዚአብሔር በቅጣቱ እንዳያጠፋችሁ ንሥሓ ግቡ። የተጻፈውን ንግር ለእናንተ እንደሚመች እያደረጋችሁ አትተርጉሙ።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 10

ነጭ ውሸት

አዳም ጎጃሜ ነው። ኖኅ ጎንደሬ ነው። የኖኅ ሚስት ሐይከል የጭልጋ ሰው ናት። የኦሮሚያው ናዝሬት (አዳማ) ክርስቶስ ያደገበት ቦታ ነው። የሰው ዘር መገኛ ኢትዮጵያ ናት። ደቡብ ጎንደር ያለው ደብረ ታቦር ጌታ ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት ቦታ ነው። ሸዋ ውስጥ ያለችው ደብረ ሲና ሙሴ በግ ሲጠብቅ ሐመልማል ከነበልባል ተዋሕዶ ያየባት ቦታ ናት። አብርሃም ይሥሐቅን ሊሰዋ የሄደበት የኮሬብ ተራራ ማለት ኮረም ነው። ኮሬብ የሚለው ከጊዜ ብዛት ኮረም ተብሏል። የኖኅ መቃብር ፋሲል ግንብ ውስጥ ነው። በቆብ አስጥል በኩል ነው። እንዲያውም በዚያ ባጃጅ ስለሚሄድበት ነው አሁን መቅሰፍት እየወረደብን ያለው። እያሉ ምንም ተጨባጭ ማስረጃ በሌለበት ስሙን ብቻ መሠረት አድርገው በድፍረት የሚናገሩ ፊደል የቆጠሩ አጭበርባሪዎች እየተነሱ ነው። የሚያሳዝነው ይህን ሰምቶ እውነት ነው ብሎ እያጨበጨበ እልልልልል እያለ የሚከተላቸውም ሰው አለ። ይህንን በመጽሐፍ የጻፉ ሰዎችን ከምን አግኝታችሁ ነው ይህንን የጻፋችሁት ስትሏቸው በራእይ አይተን ነው ይሉሀል። መጽሐፋዊ ማስረጃ ማቅረብ ሲያቅታቸው ድክመታቸውን በራእይ ያሳብባሉ። ጥሩ በራእይ ወይም በሕልም ተገለጠልን ካሉ ደግሞ ሰይጣናዊ ሕልም አለ መልአካዊ ሕልም አለ። ሰይጣን የተሳሳተ መረጃ ነግሯቸውስ ቢሆን በምን አወቁት!? በሰይጣን ሽንገላ እየተታለሉ የዋሃንን የሚያታልሉ ሰዎች በዝተዋል። ስለ ሕልም፣ ቅዠትና ራእይ በቀጣይ ክፍል ለይተን ለይተን ስለምንማማር በዚያ እናየዋለን። መጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር ያልጻፋቸውን ነገሮች በግድ ጠምዝዘን የእኛ ለማድረግ መሮጥ ምን ይሉታል!? ኢትዮጵያ የእነ ቅዱስ ያሬድ፣ የእነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ የእነ አቡነ ተክለሃይማኖት እና የሌሎችም የብዙ ቅዱሳን መነሻ ሀገር ናት ብንል እውነት ይሆናል። ሰው ትሁን ዝንጀሮ ትሁን ያልታወቅችን ነገር "ድንቅነሽ ሉሲ" ብሎ እሷን ብቻ መሠረት አድርገን ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ ናት ሲባል አጨብጭበን የምንቀበል ከሆነ አእምሯችንን ተሰልበናል ማለት ነው። ሉሲ የወጣች በቅርብ ዓመት ያውም የተገኘው ቅሪተ አካል ብዙው ፐርሰንት የሰው ይመስላል ተብሎ እንጂ ሰው መሆኗ እንኳ 100% ሳይረጋገጥ ዝም ብሎ ማጨብጨብ አለ እንዴ!?። ቆይ ዓለምን ሁሉ መች ቆፈሩትና ነው ገና ሉሲን ብቻ አይተው የሰው ዘር መገኛ ያሉን!? በራሳቸው መሣሪያ ከሉሲ ቀድሞ የነበረ አጽም ከሌላ ቦታ ቢኖርስ!? ይሄ ሀገራዊ ውሸት ነው። ያለንን ለመንጠቅ ማስረጃ የሌለውን ነገር የእኛ እንደሆነ ይነግሩናል። ኖኅ ጎንደሬ ነው ይሉህና ቅዱስ ያሬድ ሮማዊ ነው ይሉሃል። ታሪካችንን ለመዝረፍ የሌለንን ታሪክ ይነግሩናል። ያለንን ይቀሙናል። ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና በሕገ ኦሪት በሕገ ወንጌል

እግዚአብሔርን ስታመልክ የነበረች እንደሆነ ትውፊት ያስረዳናል። በትውፊት ያልነበረን፣ በመጽሐፍ ያልተጻፈን ነገር እንደ አዲስ አምጥተው ያለምንም ማስረጃ ተቀበሉን የሚሉ ሰዎች እየበዙ መጡ። ገና የስም መመሳሰል ስላለ ብቻ ታሪክ ይዘረፋል እንዴ?! ከዚያው ከመጽሐፍ ቅዱስ እንኳ ለምሳሌ ሁለት ይሁዳዎችን ብናስተውል። ጌታን የሸጠው ይሁዳ አለ። የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ አለ። የግድ ይሁዳ፣ ይሁዳ ስለተባሉ ብቻ ታሪካቸውን መቀላቀል ይገባል እንዴ? አይገባም። ለምሳሌ የእንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ሐመረ ኖኅ ትባላለች። ታድያ የኖኅ መርከብ የእንጦጦ ቤተ ክርስቲያን ናት ይባላል እንዴ? ይህኮ በምሥጢር የመጣ ስያሜ ነው። በኖኅ መርከብ ነፍሳት እንደዳኑ በቤተክርስቲያንም ንሥሓ ገብተው ሥጋውን ደሙን ተቀብለው ነፍሳት ይድናሉና ምሥጢርን ከምሥጢር አገናኝቶ የተናገረው ነው። የሌሎችም ሀገር ስያሜዎች ለምን እንደተሰየሙ የየራሳቸው ታሪክ ይኖራቸዋል።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 11

ሕልም & ራእይ

የውሃ ባሕርይ ሲያይልብን በሕልማችን ከባሕር ገብተን ስንዋኝ፣ ውሃ ስንጠጣ፣ በውሃ ስንራጭ፣ ወንዞችን ስናይ፣ ዝናብ ሲዘንብ እናያለን። አዳሜ ስትዋኚ ስታድሪ "ከተማ ልገባ ነው ብለሽ ትተረጉሚያለሽ አይደል?" ነገሩስ የውሃ ባሕርይህ አይሎ ነው። የነፋስ ባሕርይ ሲያይልብን ደግሞ በሕልማችን እንደ ወፍ ስንበር፣ ስንሮጥ፣ እናድራለን። የመሬት ባሕርይ ሲያይልብን ደግሞ በሕልማችን የምናየው መቃብር ሲቆፈር፣ እርሻ ስናርስ፣ መሬቱ ገደሉ ሲናድ መሬት ተከፍታ ስትውጠን፣ መሬት ስትንቀጠቀጥ ወዘተ ዓይነት ሕልም እናያለን። የእሳት ባሕርይ ሲያይልብን ደግሞ በሕልማችን እሳት ስንሞቅ፣ አገሩ ዱሩ ገደሉ በእሳት ሲቃጠል፣ መብራት ሲብለጨለጭ፣ መብረቅ ሲበርቅ ወዘተ እናያለን። እነዚህ ሕልሞች በአራቱ ባሕርያት አለመስማማት የሚፈጠሩ ሲሆኑ ስማቸውም በልቀም፣ ሳፍራ፣ ሳውዳ፣ ደም ናቸው። የሰው ልጅ ሲፈጠር አራቱ ባሕርያት የተስማሙለት ስለነበር ፍትወተ ሥጋ አልነበረበትም። ነገር ግን አዳም ትእዛዝ አፍርሶ በወደቀ ጊዜ አራቱ ባሕርያት አንዱ ሲያይል አንዱ ሲበረታ እየሆነ መጥቷል። አንዳንዱ ከባድ ሕልም አየሁ ብሎ ሕልም አይቶ ይፈራል። አንዳንዱ ደግሞ ደስ የሚል ሕልም አየሁ ብሎ በሕልሙ ይደሰታል። በነገራችን ላይ ሕልም ምንም ዓይነት ይሁን ልንፈራውም ልንደሰትበትም አይገባም። ሕልም የሚፈራ ሰው ሊኖር አይገባም። ከሰይጣን የሚመጣ ሕልም አለ። ከመልአክ የሚገኝ ሕልም አለ። አራቱ ባሕርያተ ሥጋ ባለመስማማታቸው የሚመጣ ሕልም አለ። እያንዳንዱን ለማየት እንሞክራለን።ሕልም ብቻውን የቅድስና ምልክት አይሆንም። ምክንያቱም ናቡከደነጾርም አልሞ ነበር፣ ፈርዖንም አልሞ ነበር፣ ዮሴፍም አልሞ ነበር። ሕልምን ሁሉ አይተረጉመውም። መተርጉማነ ሕልም አሉ። ለምሳሌ የፈርዖንን ሕልም የተረጎመው ዮሴፍ ነው። የናቡከደነጾርን ሕልም የተረጎመው ደግሞ ዳንኤል ነው። ሕልምን ፈርዖንም ናቡከደነጾርም ዮሴፍም ሊያዩት ይችላሉ። ብቻውን የቅድስና ምልክት አይሆንም። መዝ.75፣5 "ሕልምን አለሙ ያገኙትን ግን የለም"። ሌላው መልአካዊ ሕልም ነው። ይህንንም የምናገኘው በማቴ.2፣13 "የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ ሕጻኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ምድረ ግብጽ ሽሽ አለው"። ይህ መላእክት ለሰው መልእክት ከሚያስተላልፉባቸው መንገዶች አንዱ ነው። በነገረ ማርያም እንደተገለጠው ድንግል ማርያም

ያለችበትን እየተከታተለ ለሄሮድስ በሕልም የሚነግረው ደግሞ ሰይጣን ነበር። ስለዚህ ሰይጣናዊ ሕልምም አለ። ታድያ አንድን ሕልም ስናልም ሰይጣናዊ ይሁን፣ መልአካዊ ይሁን፣ ወይም የአራቱ ባሕርያተ ሥጋ አለመስማማት ውጤት ይሁን በምን እናውቃለን!? ከተባለ በቅድስና እና በብቃት ካልሆነ በቀር አናውቀውም። ስለዚህ አንድ ሰው በሕልሜ እንዲህ ተገልጦልኛል ቢለን የእሱን ሕልም ሰምተን ልንደሰትም ልንከፋም አይገባም። ራእይ ከሕልም የሚለይበት በምንድን ነው ስንል? ሕልም ተኝተን ሳለ በእንቅልፍ ላይ ሳለን የምናየው ወይም የምንሰማው ነገር ነው። ራእይ ግን እንቅልፍ ሳይወስደን እንዲሁ በተመስጦ ቁጭ ብለን ሊሆን ይችላል ወይም ቆመን የምናየው ነገር ነው። ስለዚህ ማንኛውም ሰው በሕልሜ ወይም በራእይ እገሌ ተገለጠልኝ እያለ እንዳያታልለን መጠንቀቅ ይገባናል። ራእያት እና አሕላማትም በኦርቶዶክሳዊው አረዳድ ይመዘናሉ። ስለዚህ ከምንም በፊት ለኦርቶዶክሳዊው አረዳድ ትኩረት እንስጥ። ኮርስ እንማር፣ መጽሐፍ ቅዱስን እናንብብ ያልገባንን መምህራንን እንጠይቅ። የሁሉም ነገር መለኪያ ኦርቶዶክሳዊው አረዳድ ነው። ቅዠት የሚባለው እንደ ሕልም በእንቅልፍ ጊዜ የሚታይ ሲሆን ጭብጥ የሌለው እና የማይታወስ ነው። ስለዚህ አርሴማ ተገልጣልኝ እንዲህ አለችኝ፣ ቁርሎስ በሕልሜ መጥቶ እንዲህ አለኝ እያሉ የሚያጭበረብሩ ሰዎች ስላሉ ልንጠነቀቅ ይገባናል። የሆነ ልጅ ነበር የሆነችን ልጅ አፍቅሮ እርሷን ማግባት ይፈልጋል። እና ሱባኤ ገብቼ እንቺን እንደማገባ ተገለጠልኝ አለ ይባላል። እና እንዲህ እያሉ እገሌ ተገልጦልኝ እያሉ የራሳቸውን ስሁት ፍላጎት እና አስተምህሮ የሚጭኑ ሰዎች ስላሉ ለሕልም ትኩረት አንስጥ። ትኩረት መስጠት የሚገባ ለቤተ ክርስቲያን ትምህርት ነው። እሱን ከተማርን ለሕይወታችን አስፈላጊውን ነገር ያዝን ማለት ነው።

ትንቢት፣ ሕልምና ተአምር ክፍል 12

ተአምራት

ተአምር አመረ አመለከተ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ ምልክት ማለት ነው። ተአምርን ኃጥዓንም ሊያደርጉት ይችላሉ። ሃይማኖት የለሽ ሰዎችም ሊያደርጉት ይችላሉ። ቅዱሳንም ሊያደርጉት ይችላሉ። ስለዚህ ተአምር ያደረገ ሁሉ ትክክለኛ ሰው ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ ጌታችን በወንጌል ማቴ.7፣22 "በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። ያን ጊዜ ዐመፅን የምታደርጉ ሁላችሁ ከእኔ ራቁ እላቸዋለሁ" ይላል። ይህንን የአባታችንን የክርስቶስን ቃል አስተውለህ ስማልኝማ ወንድማለም። በስሙ ተአምራት የሚያደርጉ ግን ዐመፀኞች አሉ ማለት ነው። ያን ጊዜ ከእኔ ራቁ እላቸዋለሁ ነው ያለው። በክርስቶስ ሥም ተአምር የሚያድርጉ ግን ዐመፀኛ እና ጌታ ከእኔ ራቁ የሚላቸው ሰዎች አሉ ማለት ነው። ስለዚህ ተአምርን ሃይማኖት የለሽም ሊያደርገው ይችላል። ቅዱሳንም ሊያደርጉት ይችላሉ። ተአምርን የሚፈልግ ትውልድ ግን አመንዝራ እንደሆነ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮናል። ማቴ.16፣4 "ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይሻል" ብሏል። ተአምር ሃይማኖት ለሌለው ለማያምን ወደ ሃይማኖት ለማቅረብ ሊደረግ ይችላል። እንጂ የሃይማኖት ግቡ ተአምር አይደለም። የሃይማኖት ግብ ክርስቶስን የጸጋ ተዋሕዶ ተዋሕዶ መኖር ነው። ተአምራትን የፈርዖን ጠንቋዮችም አድርገውታል። ሙሴም አድርጎታል። ስለዚህ

የሰው ልጅ አንድን ሰው ሲገመግም ተአምር ያደርጋል ወይስ አያደርግም የሚለውን ሳይሆን ማየት ያለበት ኦርቶዶክሳዊ አኗኗርን እየኖረ ነው ወይስ አይደለም። ተአምሬን እዩልኝ ብሎ በvcd እየቸበቸበ ከንቱ ውዳሴን ይሸምታል ወይስ አይሸምትም? እኔ ከእገሌ ቅዱስ እበልጣለሁ ብሎ ይታበያል ወይስ አይታበይም? መንጋው ሲሰግድለት ይከለክላል ወይስ እንደ ፈጣሪ ስግደቱን ይቀበላል። የእርሱን ፎቶ ይዘው ከቅዱሳት ሥዕላት መካከል አስቀምጠው ሲማጸኑ ሲያይ ይደሰታል ወይስ አይደሰትም? ወዘተ የሚለውን መመርመር ከዚያ በተጨማሪ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቃል ወይስ አይጠብቅም የሚለውን ማየት አለብን። ለዚያ ነው ተአምር አድራጊዎችም ዐመፀኛ ሊሆኑ ስለሚችሉ የባሕታዊ ነኝ ባይና የአጥማቂ ነኝ ባይ ተከታይ አንሁን የምለው። ለእኛ የሞተልን ክርስቶስ ስለሆነ ልባችንን ሞልተን የምንናገርለት ክርስቶስ ነው። እንጂ አንተ የምትከተለው ባሕታዊ ሲሳሳት እና ስህተቱን ስንነግርህ እገሌ አይሳሳትም ብለህ ሽንጥህን ገትረህ የምትከራከርለት መሆን የለበትም። ምን እንደሚያስብ ልቡን ታውቀዋለህ አታውቀውም! ካላወቅከው ደግሞ የማታውቀውን አትከተል። አንተን ለማዳን በመስቀል ተሰቅሎ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሳውን ክርስቶስን ተከተል። የእርሱን ትምህርትም ስማ። አርዓያ ለማድረግ ከፈለግህ ደግሞ ተጋድሏቸውን ጨርሰው ያለፉ ቅዱሳንን እንጂ ገና በዚህ ምድር ላለ ሰው አይሳሳትም ተብሎ ሊከራከሩለት አይገባም። ይሁዳ ሐዋርያ ነበር በኋላ ካደ። ጳውሎስ አሳዳጅ ነበር በኋላ ሐዋርያ ሆነ። ማንኛውንም ነገር በቤተክርስቲያን አስተምህሮ እንለካው። በልበ ሙሉነት ልንከተለው የሚገባን ክርስቶስን ነው። የሰው ተከታይ አንሁን። የመምህራን ተከታይ አንሁን። ፍሬያማ ስብከት የሚታወቀው ምእመኑ ንሥሓ ገብቶ ሥጋ ወደሙን ተቀብሎ ክርስቶስን ሲከተል ስታይ ነው። አለበለዚያ የሆነን ግለሰብ ፎቶ ፕሮፋይል አድርገህ ብዙ አይሳሳትም እያልክ ብዙ ስላወራህለት የሚቀየር ነገር የለም። በተከታይ መንጋ ብዛት ቅዱስ አይኮንም። በሰዳቢ መንጋ ብዛትም ኃጥእ አይኮንም። ፍጹም ስህተት የሌለበት ፍጹም ንጹሕ እረኛችን ክርስቶስ ነው። የእሱ ተከታይ የእሱ መንጎች(በጎች) እንሁን። የቤተክርስቲያንን የመዳን ትምህርት ጠንቅቀን እንማር።

ብሕትውናና ምንኩስና

የመነኩሴ ልብስ ለብሶ የሚጨፍር፣ የሚሰክር፣ ከንቱ ውዳሴ የሚወድ ወዘተ። የዊግ ጸጉር ይገዛና የዋሓን ምእመናንን የሚሸውድ ከአዲስ አበባ ባሕር ዳር ከባሕር ዳር ጎንደር ከተማ ለከተማ እየተንሸራሸረ ርእሰ ባሕታዊ በሉኝ የሚል ሰው በጣም እየበዛ ነው። ይህም የሆነው አብዛኛው ሰው ስለምንኩስናና ስለ ብሕትውና ስለማያውቅ ነው። ሕዝቤ ቀሚስ የለበሰ ጸጉሩን ያስረዘመ አልፎ አልፎ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገረው ሁሉ ባሕታዊ እየመሰለው የማፍያ ቡድን ደጋፊ እየሆነ እየተቸገርን ነው። ትክክለኛ መነኮሳት በምን ይታወቃሉ? መገለጫቸው ምንድን ነው የሚለውን ከክፍል 1 እስከ ክፍል 12 እንማማራለን። በዚህ ዙርያ ጥያቄ ካላችሁ አምጡት። በነገራችን ላይ የእግዚአብሔርን ቃል ሰይጣንም ይናገረዋል። ለምሳሌ ስለአንተ መላእክትን ያዛቸዋል ተብሏል ብሎ ለጌታ በገዳመ ቆርንቶስ ጠቅሶለታል። ነገር ግን ሰይጣን ሲጠቅስ ብትሰማው ክፋቱን በጥቅስ እና በስብከት ለመሸፈን እንደሆነ እወቅ። ቀሚስ የለበሰ ሁሉ መነኩሴ አይደለም። ጸጉሩን ያስረዘመ ሁሉ መነኩሴ አይደለም። ተአምር ያደረገ ሁሉ

መነኩሴ አይደለም። በጌታ ስም ተአምር ሲያደርጉ የሚኖሩ በምጽአት ጊዜ ግን ጌታ ሆይ በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን ብለው እንደሚጠይቁትና ጌታም አላውቃችሁም እንደሚላቸው ወንጌል ተናግሯል። ስለዚህ ተአምር ማድረግ የታመመን መፈወስ ብቻ የትክክለኛ ባሕታዊና መነኩሴ ምልክት አይደለም። ትክክለኛ ባሕትውያንም ይፈውሳሉ። አጭበርባሪዎችም ሊፈውሱ ይችላሉ። ስለዚህ ፈውስ የትክክለኝነት መለኪያ አይደለም። ቅዱሳን ባሕታውያን ፈውሰው ሰው እንዳያውቅባቸው ራሳቸውን ይደብቃሉ። አጭበርባሪዎች ደግሞ ጻድቅነታችንን ሀገር ሁሉ ይይልን ብለው በሲዲ ሊቸበችቡት ሁሉ ይችላሉ። ከበሽታ ማዳንማ ሙስሊም ዶክተርም መድኃኒት ሰጥቶ ሊፈውስ ይችላል። ቃልቻም ሊፈውስ ይችላል። ስለዚህ ትክክለኛ ባሕታውያን የሚታወቁት በምንድን ነው? የሚለውን በሰፊው እንመለከታለን። አንዳንዱ ባሕታዊ ነኝ ብሎ ከመከራ ለመዳን ፈጦ ሰብስቡ ይላል። የወይራ ቅጠል ሰብስቡ ይላል። አንዳንዱ ደግሞ የኢየሱስ ቤተክርስቲያን ወዳለባቸው ቦታዎች ሂዱ ይላል። ማንኛውም ቤተክርስቲያንኮ የኢየሱስ ሥጋና ደም የሚፈተትበት የኢየሱስ ቤተክርስቲያን ነው። በጊዮርጊስ በጻድቃን በሰማእታት የተሰየመው በትንቢየ ኢሳይያስ እንደተነገረው መታሰቢያ እንዲሆናቸው ነው። እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ግን ባለቤትነቱ የኢየሱስ ነው። ሕዝቤ እየተሸወደ ነው ያለው። ስለዚህ እውነተኛውን ትምህርት በአጭሩ እስከ ክፍል 12 አድርጌ አቀርባለሁ። ጥያቄ ያለው ያቅርብ።

ሥርዓተ ብሕትውናና ምንኩስና ክፍል 1

መጀመሪያ ብሕትውና የሚለው ቃል ተባሕተወ ብቸኛ ሆነ ከሚለው የግእዝ ቀል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ "ብቸኝነት" ማለት ነው። ይኽውም ከሰው ተለይቶ አናብስት፣ አናምርት፣ አክይስት፣ አቃርብት ከሚኖሩበት በዱር በጫካ በበረሃ ብቻን መኖር ማለት ነው። ከተማ ለከተማ እያውደለዱ ባሕታዊ ነኝ ማለት የብሕትውናን ትርጉም ካለማወቅ የመነጨ አመለካከት ነው። ዕብ. 11፣37 ".... ዓለም የማይገባቸው እነዚህ ናቸው። ዱር ለዱርና ተራራ ለተራራ ዋሻ ለዋሻና ፍርኩታ ለፍርኩታም ዞሩ" ይላል እንጂ ከተማ ለከተማ ዞሩ አይልም። ምንኩስና ማለት ደግሞ "ሞት" ማለት ነው። መጽሐፈ ገነት ላይ "መነኮስ ብሂል ምውት ብሂል" ይላል። መነኩሴ ማለት የሞተ ማለት ነው። ሞት ማለት ደግሞ ምሥጢሩ መለየት ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ዓለም በእኔ ዘንድ የሞተች ናት። እኔም በዓለም ዘንድ የሞትኩ ነኝ ብሏል። ከዓለም የተለየሁ ነኝ ማለት ነው። ከዓለም መለየት ማለትም ሰማያዊ ጥቅም ለማያሰጡ ደስታዎች ተድላዎች መራቅ ማለት ነው። 1ኛ ዮሐ.2፣17 "ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል" ይላል። ምንኩስና ሁለት ዓይነት ሊሆን ይችላል። አንደኛው በድንግልናቸው የመነኮሱ ሲሆኑ 1ኛ ቆሮ.7፣38 "ያላገባም የተሻለ አደረገ" የሚለውን ቃል ይዘው የመነኮሱ ናቸው። ሌሎች ደግሞ ከትዳር በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች የሚመነኩሱ ናቸው። ይህም ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችንን ማቴ.19፣27 "ሁሉን ትተን ተከተልንህ" ያለውን አብነት አድርገው ነው። የተጋቡ ባልና ሚስት አንዱ መመንኮስ ቢፈልግ እና ባልና ሚስት ከተስማሙ መመንኮስ ይችላል። ካልተስማሙ ግን መመንኮስ አይችልም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመነኮሳትን ቦታ ለመባረክ በገዳመ ቆሮንቶስ 40 ቀን እየጾመ ተቀመጠ። ማቴ.4፣1-2። ጌታችን የምንኩስና ሕይወትን በተመለከተ በሉቃ.9፣62 "ቤቱ ወንድሙንና እህቱን አባቱንና እናቱን ሚስቱንና ልጆቹን ንብረቱን ትቶ በስሜ አምኖ የተከተለኝ

የዚህን ሁሉ መቶኛ እጥፍ ያገኛል። የዘለዓለም ድህነትም ያገኛል" ብሏል። ሥርዓተ ብሕትውና በአባ ጳውሊ (ጳውሎስ) ተጀምሯል። ሥርዓተ ምንኩስና ደግሞ በአባ እንጦንስ ተጀምሯል። በእርግጥ በብሉይ ኪዳን ዘመንም እነ ኤልያስ በሐዲስ ኪዳን መግቢያም እነ ዮሐንስ መጥምቅ በገዳም ኑረዋል። ለአኗኗሩ ሥርዐት የተበጀለት ግን ከላይ በተጠቀሱት አባቶች ነው። እንጦንስ ማቴ.16፣26 "ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል!?" ያለውን ቃል ሰምቶ ወደ በረሀ ሄዷል ከዚያም መልአክ ሰሌን እየታታ ከዚያ የጸሎት ጊዜያት ሲደርሱ እየጸለየ አሳየውና ከመ ከመዝ ግበር እንዲህ እንድህ እያደረግህ ብትኖር ከሰይጣን ፈተና ትድናለህ ብሎታል። ከዚያ በኋላ አባ እንጦንስ አባ መቃርዮስ ዘየዐቢን፣ አባ መቃርዮስ ዘየዐቢ አባ ጳኩሚስን፣ አባ ጳኩሚስ አባ ቴዎድሮስ ሮማዊን እያለ መነኮሳት እየበዙ መጥተዋል።

ሥርዓተ ብሕትውናና ምንኩስና ክፍል 2

መጽሐፈ ገነት ላይ የተቀመጠ አንድ ታሪክ አለ። አንድ አረሚ ለጣዖት እየሰገደ ለጣዖት እያጠነ ይኖር ነበር። ከእለታት አንድ ቀን የእርሱ ልጅ ወደ ጣዖት ቤቱ ሲሄድ ሰይጣናት ጉባኤ አድርገው ትልቅ ሰይጣን በዙፋን ተቀምጦ ሌሎች ሰይጣናት በየተራ ከውጭ እየገቡ በዙፋኑ ለተቀመጠው የሰሩትን ክፉ ሥራ ሪፖርት ሲያደርጉ ሕጻኑ ተደብቆ ያይ ነበር። ከዚያ አንዱ ሰይጣን በዙፋኑ ለተቀመጠው ሰይጣን "ማዕበል አስነስቼ መርከብ ሰብሬ ሰው ገድየ መጣሁ" ብሎ ሪፖርት አደረገ። በዙፋኑ ያለው ሰይጣንም ይህን ለማድረግ ስንት ቀን ፈጀብህ አለው። ሪፖርት አድራጊው ሰይጣንም ሦስት ቀን አለ። ከዚያ በሦስት ቀን ለምን ይችን ብቻ ሠራህ ብሎ በዙፋኑ የተቀመጠው ሰይጣን ሪፖርት አድራጊው ሰይጣን እንዲገረፍ አደረገ። ከዚያ ሌላኛው ሰይጣን ሪፖርት እንዲህ ብሎ አቀረበ "ከሠርግ ቤት ሄጄ የሙሽራውንና የሙሽሪትን ወገኖች አጣልቼ ደም አፋስሼ መጣሁ" አለ። ይህን ለማድረግ ስንት ቀን ፈጀብህ አለው። 40 ቀን አለ። ነገር ግን ለምን በ40 ቀን ይችን ብቻ ትሠራለህ ብሎ ይህኛውን ሰይጣንም እንዲቀጣ አደረገው። በመጨረሻ አንዱ ሰይጣን ገባ። በዙፋኑ የተቀመጠው ሰይጣንም አንተስ ምን ሠርተህ መጣህ አለው!? ያም ሰይጣን አንድ መነኩሴ አሳስቼ መጣሁ አለው። ምን ያህል ጊዜ ፈጀብህ አለው። አርባ ዓመት ብሎ መለሰ። ይህን ጊዜ በዙፋኑ ተቀምጦ የነበረው ሰይጣን ከዙፋኑ ተነስቶ "አንተን ሊሾመህ ይገባል" ብሎ ተነስቶ አቀፈው። ይህንን በድብቅ ሲያይ የነበረው ሕጻን 40 ዓመት አንድን መነኩሴ ለመጣል የታገሉት የምንኩስና ክብር ታላቅ ቢሆን ነው ብሎ ሕጻኑ በደብቅ ወጥቶ መነኮሷል። ይህ መነኩሴም ታላቅ አረጋዊ ሆኖ ይህንን ታሪክ ራሱ ለአበው ነግሯቸዋል። የምንኩስና ክብር ታላቅ ነው። ነገር ግን ባሕታዊው አባ ጳውሊ እንደተናገረው በመጨረሻው ዘመን አብዛኛዎች መነኮሳት ገንዘብ የሚወዱ፣ ሹመት የሚወዱ፣ ይህችን ዓለም የሚወዱ፣ ከተማ ለከተማ የሚያውደለድሉ እንደሚሆን በትንቢት መነጽሩ አይቶት ነበር። እና እንዲህ ዓይነት መነኮሳትን ስታይ ምንኩስናን እንዳትጠላው ተጠንቀቅ። ምንኩስና ክብሩ ትልቅ ነው። ዓለም ያሸነፈቻቸውን መነኮሳት ስታይ የሰይጣን ምርኮኛ መሆናቸውን አስብ እና እዘንላቸው። ምንኩስና ጌታችን በወንጌል ስለመንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን ጃንደረባ ያደረጉ አሉ ብሎ በተናገረው መሠረት ፍትወት ሥጋዊን በጾም በጸሎት አጥፍተው በድንግልና የጸኑ የደጋግ አባቶች ሕይወት ነው። መነኮሳትን በሥርዓተ ምንኩስና መዝናቸው እንጂ ሥርዐተ ምንኩስናን በመነኮሳት አትመዝነው።

ሥርዓተ ብሕትውናና ምንኩስና #ክፍል 3

ምንኩስና ተስፋ ቆርጠን የምንገባበት አይደለም። መነኩሴ ለመሆን ወይም ለመመነን የፈለገ ሰው አስቀድሞ ሊያደርገው የሚገባ ነገር አለ። ይኽውም እናት አባቱ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ቢሆንና እናት አባቱን የሚረዳ ሌላ ልጅ ከሌለ እነርሱን ትቶ መመንኮስ ወይም መመነን የለበትም። ዘጸ.20፣12 "አባትህንና እናትህን አክብር" የሚለው ሕግ ይፈርስበታልና። ሚስት ካለችው ሚስቱ ሳትፈቅድለት በዚህ ዓለም አልሞላለት ሲል እርሷን ሳያስፈቅድ መመነን መመንኮስ የለበትም። እርሷ ካልፈቀደችለት በቀር መመንኮስ የለበትም። ልጆች ያሉት ቢሆንና ልጆቹ ራሳቸውን ያልቻሉ በእርሱ የሚተዳደሩ ከሆነ እነርሱን ትቶ መመነን የለበትም። ልጆቹን አባት ሆኖ ስላላሳደጋቸው እግዚአብሔር ይጠይቀዋልና። መነኩሴ ነቢዩ ሙሴን መምሰል አለበት። ነቢዩ ሙሴ በደብረ ሲና ተራራ ነበልባል ከሐመልማል ተዋሕዶ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው ባየ ጊዜ የሚጠብቃቸውን በጎቹን በአንድ ቦታ አድርጎ ነበር የሄደ። ስለዚህ ለመመነን ወይም ለመመንኮስ የፈለገ ሰውም ከመመንኮሱ በፊት በዚህ ዓለም እያለ የነበረበትን ሥራ ቦታ ቦታ አስይዞ ነው መመንኮስ ያለበት። መጀመሪያ ሳያገባ የመነኮሰ የበለጠ አደረገ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም 1ኛ ቆሮ.7፣37 "እኔ ያለ ጎዘን ልትኖሩ እወዳለሁ ሚስት ያላገባ ሰው በሚያስደስተው ገንዘብ እግዚአብሔርን ያስበዋል" ተብሎ ተጽፏል። ስለዚህ መነኩሴ ማለት በአንድ ልብ እግዚአብሔርን ለማመስገንና ለማምለክ ወደ ልዩ ቦታ (ገዳም) የሄደ ማለት ነው። መነኩሴ ሁሉን ትቶ እግዚአብሔርን የተከተለ ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን ማቴ.19፣27 "ሁሉን ትተን ተከተልንህ" ብሎታል። መነኩሴ ከሆኑ በኋላ ገንዘብ መውደድ፣ ከንቱ ውዳሴን መውደድ፣ ሹመት ሽልማት መውደድ ሁሉን ትቶ አለመከተልን ያሳያል። የብሕትውናን ኑሮ ይኖሩ ከነበሩ ቅዱሳን በኦሪት ጊዜ አንዱ ነቢዩ ኤልያስ ነው። ዱር ለዱር ነው የኖረ። ለእግዚአብሔር ሕግ ቀንቶ ሁሉን ትቶ ፈጣሪውን የተከተለ ነበር። መልከ ጼዴቅም እንዲሁ ባሕታዊ ነበር። ካገባ በኋላ በእግረ ገነት 7 ዓመት ቆይቶ የተሰወረው ሄኖክም ካገቡ በኋላ ለመነኑ መነኮሳት ምሳሌ የሚሆን ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያጠመቀው መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስም ለ30 ዓመታት በረሀ የኖረ እህል ሳይቀምስ ጠጅ ሳይጠጣ የኖረ የበረሀ ማር እየበላ የኖረ የባሕታውያንን አኗኗር የኖረ ታላቅ ቅዱስ ነው።

ሥርዓተ ብሕትውናና ምንኩስና ክፍል 4

ቅዱስ ጳውሎስ በገላ.6፣14 "በእኔ ዘንድ ዓለሙ የሞተ ነው። እኔም በዓለሙ ዘንድ የሞትሁ ነኝ" ብሏል። ይህ ማለት ባሕታውያን መነኮሳት ክብርን፣ ሹመትን፣ ውዳሴን፣ ገንዘብን የማይወዱ ከእነዚህ ነገሮችም የራቁ መሆን አለባቸው ማለት ነው። ገንዘብን በተመለከተ ከዚህ ላይ መጽሐፈ ሐዊ ላይ የተጻፈ የአንድ ቅዱስ አባትን ታሪክ ማውሳት እፈልጋለሁ። ታሪኩ እንዲህ ነው። "ሁለት ወንድማማቾች እንመንን ይሉና መንነው ገዳም ይገባሉ። ከዚያ ሁለቱም በአንድ አቅራቢያ ካለ የተለያየ ዋሻ ገብተው ከሰይጣናት ከመናፍስት ጋር ተጋድሎ ያደርጋሉ። እና ሁለቱ ወንድማማቾች በጸጋ ይተያዩ ነበር። ጠባቂ መላእክቶቻቸውንም ለማየት እስከ መብቃት ደርሰው ነበር። ከእለታት አንድ ቀን አንደኛው መናኝ ከበአቱ ትንሽ ወጣ ብሎ ሳለ ከአንድ ቦታ ላይ ይሄዳል። ከድንገት ከዚያ ቦታ ላይ የሆነ ነገር ይመለከትና ደንግጦ ወደላይ ዘሎ በፍጥነት ወደ በዓቱ ይመለሳል። ያኛው መናኝ ወንድሙ ከበአቱ ሆኖ ይመለከተው ነበርና

ወንድሜ ምን አይቶ ነው ደንግጦ እንደዚያ ሮጦ ወደ በአቱ የገባው ይልና በሌሊት ወንድሙ ደንግጦ ከሄደበት ቦታ ሄዶ ይመለከታል። ሲመለከት አንድ ኬሻ ሙሉ ወርቅ ነው። ያ መናኝ ይህንን ኬሻ ሙሉ ወርቅ ሲያይ ነበር ደንግጦ ወደ በአቱ የሮጠ። ይህኛው መናኝ ወንድሙ ግን አይ ወንድሜ ወርቅ አይቶ ነው እንዴ እንደዚያ የሮጠው ይልና ያንን ኬሻ ሙሉ ወርቅ ይዞ ወደከተማ ይሄዳል። ከተማም ሄዶ በዚያ ወርቅ ወደ 80 የሚጠጉ ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናትን አሳነጸ ለእነዚያ አብያተ ክርስቲያናት አገልጋይ ካህናት የሚበቃ ደመወዝ ሰጥቶ የቀረውን ወርቅ ለነዳያን መጽውቶ አንድም ገንዘብ ሳያስቀር ወደ በአቱ ተመለሰ። ሲመለስ ግን ወንድሜ ይህንን ወርቅ ትቶ ወደ በአቱ ገብቶ ትቶት ነበር እኔ ግን ወርቁን ሸጬ አብያተ ክርስቲያናትን አሳነጽኩበት ነዳያንን ረዳሁበት ብሎ ከወንድሙ የተሻለ ነገር እንዳደረገ አሰበ። ከዚያ ከሄደበት ወደ በአቱ ሲመለስ ወትሮ ይጠብቀው የነበረው መልአክ ተቆጥቶ ይታየዋል። ይህን ጊዜ መናኙ ምነው ምን አጠፋሁ ብሎ ጠየቀ። መልአኩም አንተ ወርቁን ይዘህ ሄደህ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተሀል የተረፈውንም ለነዳያን መጽውተሀል። ነገር ግን አንተ ያደረግከው መልካም ሥራ ወንድምህ ወርቁን ባየ ጊዜ ንቆት ወደላይ ዘሎ ሮጦ ወደ በአቱ የገባትን አገባብ ያህል ዋጋ የለውም። ስለዚህ እኔም ከዛሬ በኋላ አልገለጽልህም። ወንድምህንም አታየውም አለው። ይህን ጊዜ በጣም አዝኖ 50 ዐመት አልቅሶ በመጨረሻ እግዚአብሔር ይቅር ብሎት ወንድሙን ለማየት በቅቷል። ይህ የሚያሳየን ከመነኑ በኋላ ገንዘብ መውደድ ሰውን ለመርዳት እያልን መሰብሰብ አይገባም። ሌላው መነኮሳት ቢሰድቧቸውም ቢያመሰግኗቸውም አይደንቃቸውም። ቢሰድቧቸው አይከፋቸውም። ቢያደንቋቸውም ደስ አይላቸውም። ታላቁ መቃርዮስ በአንድ ወቅት አንዱንብረድእ ወደ መቃብር ሂድና ሙታንን ስደባቸው አለው። ያ ረድእም ወደመቃብር ሄዶ ሙታንን ሰደባቸው። ከዚያ ተመልሶ ለአባ መቃርዮስ ዘየዐቢ ነገረው። መቃርዮስም ምን አሉህ አለው?ብረድኡ ምንም አላሉኝም አለው። በል ደግሞ አሁን ሂድና መርቃቸው አለው። ያ ረድእም ወደ መቃብር ሄዶ ሙታንን "እናንቱ ቡሩካን፣ ቅዱሳን" ወዘተ እያለ እያሞጋገሰ መረቃቸው። አባ መቃርስም ረድኡን ምን አሉህ አለው። ረድኡም ምንም አላሉኝም አለው። አባ መቃርዮስም መነኩሴ አኗኗሩ እንዲህ መሆን አለበት። ሲሰድቡትም ሲያመሰግኑትም ሁሉንም እንደ ሙታን ዝም ብሎ ያሳልፍ ተብሏል።ስለዚህ ኦርቶዶክሳዊው መነኩሴ እኔ እገሌ ከተባለው ቅዱስ እበልጣለሁ እያለ ሊናገር አይችልም። ራሱን ከሁሉ በታች እንደሆነ ይናገራል እንጂ። ይህም ትሕትና ነው።ትክክለኛው ትሕትና እኔ ትንሽ ማለት ብቻ ሳይሆን ትንሽ ነህ ሲሉትም የማይቀየም የማያዝን መሆን ነው። ሌላው መነኮሳት ሹመትን የማይወዱ በተቻላቸው አቅም ከሹመት የሚርቁ ናቸው። እንጂ ጵጵስና ለመሾም ጉቦ የሚከፍሉ፣ ጵጵስና አልተሾምኩም ብለው የሚያኮርፉ፣ የደብር አስተዳዳሪ ካልሆንኩ ብለው የሚጥሩ አይደሉም። ሊሾሙ ጭምጭምታ ካለ እንኳ ይሸሻሉ ይደበቃሉ እንጂ ለመሾም ልታይ ልታይን አያበዙም። እዚህ ላይ የአንድ መነኩሴን ታሪክ ማንሳት እፈልጋለሁ። በአንድ ወቅት ጵጵስና ሊሾሙት እንደሆነ ሰማ። ከዚያ ጵጵስና ላለመሾም ጆሮውን ቆረጠው። በወቅቱ ጆሮው የተቆረጠ ሰው ጵጵስና አይገባውም የሚል ሥርዐት ስለነበረ ከሹመት ለማምለጥ ይህንን አደረገ። አባቶቻችን ሹመትን ለመራቅ ይህንን ያህል አድርገዋል።ስለዚህ መነኩሴ ከሹመት፣ ከከንቱ ውዳሴና ከክብር እንዲሁም ከፍቅረ ንዋይ የራቀ መሆን አለበት።

ሥርዓተ ምንኩስና ወብሕትውና ክፍል 5

ፈጦ ሰብስቡ ከመቅሰፍት ትድናላችሁ፣ የወይራ ቅጠል ያዙ፣ በጨው የታሸ እና የማይነቅዝ እህል እያዘጋጃችሁ የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ወዳለበት ቦታ ሂዱ፣ ኢትዮጵያ ላይ መቅሰፍት ይወርዳል፣ ጎንደር ከተማ ትጠፋለች፣.... ንሥሓ የምንገባ ከሆነ መከራው ሊቀርልን ይችላል..... ወዘተ ወዘተ የሚሉ ንግግሮች ከባሕታውያን መጡ እየተባለ እየተነገረ ነበር። እውነት ትክክለኛ ባሕታውያን የሰው ልጅ እንዲድን ፈጦ ሰብስቡ የሚሉ ይመስላችኋል!? ሰብአ ትካት በንፍር ውሃ የጠፉት የወይራ ቅጠል ወይም ፈጦ አጥተው ነው እንዴ??? ይህን ሐሳብ እንኳን ዓለምን ንቄ ወደ ገዳም ገብቻለሁ ያለ ባሕታዊና መነኩሴ ይቅርና በዓለሙ የሚኖር ጨዋ ምእመንስ ይናግረዋል?? እረ ምእመናን ራሳችሁን ለተኩላ አስተላልፋችሁ አትስጡ!!! ፋሽስት ኢጣልያ ለወረራ ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቷ በፊት በገንዘብ ሰዎችን መልምላ ፋሺስት ይመጣል፣ ኢትዮጵያ ለፋሽስት ትገዛለሽ እንዲሉ ባሕታዊ አድርጋ እንደላከቻቸው ይነገራል። ይህንን ያደረገችበት ምክንያት ብዙ ኢትዮጵያውያን ለመነኮሳትና ለባሕታውያን የተለየ በጎ አመለካከት እንዳለው ስለሚያውቁ ነው። በእርግጥ ለኢትዮጵያውያን ትክክለኛ መነኮሳት እና ባሕታውያን ታላላቅ ሥራ ሰርተዋል። ብዙውን ሕዝብ አስተምረው ያጠመቁት አቡነ ተክለ ሃይማኖት መነኩሴ ናቸው። አባ ኢየሱስ ሞዐ መነኩሴ ናቸው። ኢትዮጵያን በብዙ መንገድ የረዷት ዘጠኙ ቅዱሳን መነኮሳት ናቸው። ይህንን የተመለከተ ፋሽስት ስለዚህ የመነኩሴ ቀሚስና ቆብ ሰዎችን አስለብሰን ማታለል እንችላለን ብሎ አሰበ። ያሰበውንም ተገበረ። ከዚያ በየአውራጃው በየክፍለ ሀገሩ ኢትዮጵያ በኃጢኣታችን ምክንያት በፋሽስት ትገዛለች በሚሉ ባሕታውያን ተጥለቀለቀች። ሰውም ፋሺስት ቀጥታ ስትመጣ ያው ትንቢቱ ነው እያለ የጦር ዝግጅት ሳያደርግ ለመገዛት ራሱን አመቻቸ። ይህ ሲሆን በጎጃም ክፍለ ሀገር የነበረው ዋናው አርበኛ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ነበር። እነ ቢትወደድ መንገሻ ጀንበሬ ሌሎችም ነበሩ። እና ኢጣልያ ከሌሎች ክፍለ ሀገሮች አንጻር ብዙ ተጽእኖ ያላደረሰው በጎጃም ነበር። በኋላ ምክንያቱ ሲጣራ "የአርበኞች ጸሐፊ እና ዋና አማካሪ" የነበሩት ታላቁ ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ነበሩ። እና እሳቸው የአጭበርባሪ ባሕታውያንን ሁኔታ ያውቁ ስለነበር። ሕዝቡም አርበኞችም እንዲህ ዓይነት የባሕታዊ ነን ባዮችን ስብከት እንዳይሰማ እና ጠላትን በተቻለው አቅም እንዲቃወም በማድረጋቸው ነበር። የክርስትና ሕይወት እንደወርቅ የጠራ ነው። በድለን ከሆነ ንሥሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን እንቀበላለን እንጂ ፈጦ አንሰበስብም። ጎንደር ወይም ጎጃም ትጠፋለች እያሉ የሚናገሩ ባሕታውያን ጎንደርን ወይም ጎጃምን ለማጥፋት ለሚፈልጉ ሰዎች የሚሰሩ ሰላዮች ሊሆኑ ስለሚችሉ እነርሱን መስማት አያስፈልግም። እያንዳንዱ ወጣት ራሱን ሀገሩን ለመጠበቅ መዘጋጀት አለበት እንጂ ትንቢቱ ነው እያለ እጁን አጣጥፎ ሊቀመጥ አይገባም። ሌላው ግርም ያለኝ እኒህ ባሕታውያን ነን ባዮች ንሥሓ ከገባን ይቀራል የምትል ማምለጫ ማስቀመጣቸው ነው። ጎንደርን ወይም ጎጃምን ለመውረር እቅዳቸው ካልተሳካ ያው ሕዝቡ ንሥሓ ስለገባ ቀረ ሊሉ ነው እንግዲህ። ሌላው ገራሚው ነገር የኢየሱስ ቤተክርስቲያን ወዳለበት ሂዱ ያሉት ነው። በነገራችን ላይ አብያተ ክርስቲያናት ባለቤትነታቸው ሁሉም የኢየሱስ ነው። በመልአክ ወይም በሰማእት ስም ለመታሰቢያነት ቢታነጹም ባለቤትነታቸው የኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ተለይተው በኢየሱስ ስም የታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚያ ግን ከሌላው ቤተክርስቲያን ይበልጣሉ ያድናሉ ሌላው አያድንም ማለት ትልቅ

ክህደት ያለበት ነው። ቤተክርስቲያን በወርቅም በግንብም በሳርም ብትሰራ ክብሯ አንድ ነው። ሌላው ግን ኢትዮጵያ ላይ እየተደረገ ያለው የታቀደ ጥፋት ነው እንጂ ትንቢት አይደለም። በአንድ ወቅት አንዲት ሴት ከሆነ መንደር ትገባና ቤታችሁ ይቃጠላል ንሥሓ ግቡ እያለች ትናገራለች። ከዚያ ሰው እየሳቀ ዝም ይላታል። ከዚያ ሁሉም ሰው ወደገበያ እንደሄደ ብዙውን ቤት እየዞረች እሳት ለኮሰችበትና አቃጠለችው። እና ሕዝቡ ከገበያ ሲመለስ ቤቱ ተቃጥሎ አገኘ። አንዳንዱ ትንቢቱ ነው እያለ ዝም አለ። ነገር ግን ይህ ትንቢት አይደለም። ኢትዮጵያ ላይ እየሆነ ያለውም እንዲህ ዓይነት ነው። ጠላት ያቀነባበረው ጥፋት ነው እየተደረገ ያለው።ችግሩን እንዳንፈታው ትንቢቱ ነው እያልን እጃችንን አጣጥፈን ተቀመጥን። ያሳዝናል። ኢትዮጵያን በእግዚአብሔር ረድኤት የእኛን ድርሻም በመወጣት ከፍ ማድረግ ስንችል ዝም ብለን ተቀመጥን። በዚህ ጉዳይ ወደ ፊት ከክፍል 1 እስከ ክፍል 12 ስለትንቢት የምጽፈው ይኖረኛል። ለጊዜው ግን በእንደነዚህ ዓይነት ባሕታውያን ሕዝቡሽእንዳይሸወድ ለማለት ነው።

ሥርዓተ ብሕትውናና ምንኩስና ክፍል 6

ማቴ.7፣22 "በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን በስምህስ አጋንንት አላወጣንምን በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን ይሉኛል። የዚያን ጊዜ ከቶ አላወቅኳችሁም እናንተ አመፀኞዎች ከእኔ ራቁ ብየ እመሰክርባቸዋለሁ"። አስተውል አጋንንትን ማስወጣት ተአምራት ማድረግ የትክክለኛ ባሕታዊ ዋና መገለጫ አይደለም። ኃጥዓንም ይህንን ያደርጉታል። ጌታም አመፀኞች ብሏቸዋል። የሚገርመው ተአምር ያደረጉት ደግሞ በስሙ ነው በክርስቶስ ስም በማርያም ስም ወዘተ እያሉ ስለፈወሱ ብቻ የትክክለኝነት መለኪያ አይደለም። ታድያ እንዲህ ከሆነ በምን እንለያቸው? የሚለውን እንመልከት። ቅዱሳን መነኮሳት ይፈውሱና እነርሱ መፈወሳቸው እንዳይታወቅ የተፈወሰውን ሰው ዝም በል ለማንም እንዳትናገር ይላሉ። ይህንንም የሚያደርጉት ከንቱ ውዳሴ እንዳያጠቃቸው ነው። የቅዱሳን መነኮሳትና ባሕታውያን ዋና ትኩረት ሰውን ማዳን እንጂ መፈወስ አይደለም። የክርስትና ግብም መዳን እንጂ መፈወስ አይደለም። ፈውስ ለእስላሙም ለፕሮቴስተንቱም ለክርስቲያኑም ሊደረግ ይችላል። ምክንያቱም እግዚአብሔር በደለኛ ጻድቅ ሳይል ለሁሉ ዝናም እያዘነበ ፀሐይ እያወጣ እንደሚመግብ ሁሉ። ፈውስም መግቦታዊ ሥራው ስለሆነ ለሁሉም የሚሰጥ ነው እንጂ ከበሽታ መፈወስ የጻድቅነት ምልክት አይደለም። መታመምም ሁሉ የኃጥዕነት ምልክት አይደለም። ምክንያቱም ቅዱስ ጳውሎስም የሥጋ በሽታ ነበረበት። ብዙ ቅዱሳን ታማሚዎች ነበሩ። በሥጋ ጤነኛ መሆንም የጻድቅነት ምልክት አይደለም። ብዙ ኃጥዓን ጤነኞች ነበሩና። ምሳሌ ነዌ ጤነኛ ነበር። አልዓዛር ደግሞ ታማሚ ነበር። ስለዚህ መታመም ወይም አለመታመም ወይም በአንጻሩ መፈወስም አለመፈወስም ብቻውን የጽድቅ ወይም የኃጢኣት መለኪያ አይሆንም። መጽሐፈ መነኮሳት ትርጓሜ ላይ አንድ ታሪክ አለ። 13 ሽፍቶች አንዱን ክርስቲያን ሊዘርፉት ወደቤቱ ሲሄዱ ያ ክርስቲያን ከርቀት ያያቸዋል። ከዚያ 12ቱ ሐዋርያት አንዱ ደግሞ ጌታየ ኢየሱስ ክርስቶስ ናቸው እኒህማ ይልና ወደቤቱ ሲመጡ እግራቸውን አጥቦ የእግራቸውን እጣቢ ታማሚ ልጅ ነበረው በዚያ ቢረጨው ታማሚው ልጅ ወዲያው ተፈወሰ። ስለዚህ ፈውስ ለታማሚው ሲባልም ሊደረግ ይችላል። አስተውል የሽፍታ እጣቢ ሰውን አይፈውስም። ልጁን የፈወሰው የአባትየው እምነት ነው። ሥጋዊ ፈውስ የክርስቲያኖች ዋና መሠረታዊ ጉዳይ አይደለም።

ሌላው አንዳንድ በሽታዎች የተወሰነ ጊዜ አመው በራሳቸው ሊለቁ ይችላሉ። ለምሳሌ ጉንፋን ለተወሰነ ቀን ያምና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በራሱ ይለቃል። አንዳንድ የጉንፋን በሽተኞች ወደ አጥማቅያን ይሄዱና አንድ ሰባት ቀን ተጠምቀው ተፈወስን ይላሉ። ይህን ጊዜ ባሕታዊው አጥምቆኝ ነው የዳንኩ ብለው ይቀውጡታል። እኒህ ሰዎች ሰባት ቀንኮ ከቤታቸውም ቢቀመጡ ጉንፋን በጠባዩ ጊዜያዊ ስለሆነ ይለቃቸው ነበር። አንዳንድ የስነልቡና ሕመሞች ደግሞ የሆነ ሰው ድነሀል ስላለህ ብቻ ሕመሙ ለቀቀኝ ልትል ትችላለህ። አንድ የገጠር ሰው ሐኪም ቤት ሄዶ ሐኪሙ በሽታው ቀላል ነው ብሎ ቀለል ያለ የሚዋጥ መድኃኒት ቢሰጠው የሚዋጥ መድኃኒት አያሽለኝም ብሎ ስነልቡናውን አሳምኖት ስለነበር በስነልቡናው ጫና አሳድሮ ሕመሙ ሳይሻለው ይቀራል። በሌላ ቀን ይህን የተረዳው ዶክተር ዝም ብሎ በውሃ አድርጎ መርፌ ይወጋዋል። ያን ጊዜ ዳንኩ አለ ይባላል። አንዳንድ ጊዜ በእኛው ስነልቡና የምናክማቸው በሽታዎችም ይኖራሉ። ትክክለኛ ባሕታዊ ፈውሶ ለማንም እንዳትናገር ይላል እንጂ እዩኝ ፈወስኩት እኔ አንበሳው እያለ በCD አይሸጥም። ሲጀምር ሰይጣን የውሸት አባት ነው። የሰይጣንን ምሥክርነት በCD አራብቶ ማሰራጨት አስቂኝ ነው። ትክክለኛ ባሕታውያን ሌላው የሚታወቁበት ትሕትናቸው ነው። ይኽውም ሰው ፈውሰው እግዚአብሔር እንጂ እኛ መፈወስ አንችልም ብለው ፈውስን ለፈጣሪ ይሰጣሉ። እኔ ከጊዮርጊስ ወይም ከአንድ ቅዱስ እበልጣለሁ እያሉ የትእቢት ቃል የሚናገሩ ካሉ እኒህ የሰይጣን ደቀመዛሙርት ይባላሉ እንጂ ባሕታውያን አይደሉም። አንድ ጊዜ አባ ኤልያስ የተባለን ታላቅ ቅዱስ ባሕታዊ ንጉሡ ይሄድና አንተ እንደ ነቢዩ ኤልያስ ነህ ይለዋል። ይህን ጊዜ ባሕታዊው ኤልያስ ሲመልስ "ንጉሥ ሆይ አይሳሳቱ እኔ ታላቅ ኃጢአተኛ ነኝ። ታላቁ ነቢዩ ኤልያስ በቁራ ምግብ ይመጣለት ነበር። እኔ ግን ምግብ ከውጭ ባሰጣ ቁራ ይወስድብኛል። እና እኔ እንደ ኤልያስ አይደለሁም" ብሎ መልሷል። ትክክለኛ ባሕታውያን እንዲህ ናቸው። ራሳቸውን ደብቀው ነው የሚኖሩት ሰው እንዲያውቃቸው አይፈልጉም። ደዌ በሦስት መንገድ ሊመጣ ይችላል። ለምሳሌ በኃጢኣት ምክንያት የሚመጣ ደዌ አለ። ይኽውም እንደየሙሴ እህት ማርያም ነው ። ይህ እግዚአብሔር ለተግሣጽ የሚያመጣብን ነው። ዋጋችን እንዲበዛ የሚመጣ ደዌ ወይም በሽታም አለ። ይህም እንደ ኢዮብ ሕመም ያለው በሽታ ነው። ኢዮብ ኃጢኣት ሰርቶ ሳይሆን ዋጋው ይበዛ ዘንድ ትእግሥቱ ለሁሉ ይታወቅ ዘንድ የመጣበት በሽታ አለ። ሌላው ለንጽሕና ለቅድስና አጋዥ ስለሆነ ብለው ቅዱሳን ጌታ ሆይ ደዌ ሥጋን ስጠን ብለው የሚያመጡት በሽታም አለ። ይህ ደዌ ዘንጽሕ ይባላል። እንደ ጢሞቴዎስ ያለው ነው። በአጠቃላይ በሽታ ሊፈወስ የሚችልበት ብዙ መንገድ አለ። ሆስፒታል በመሄድ በሐኪም እገዛ፣ በዕፀዋት፣ በጠበል፣ ንሥሓ በመግባት፣ በቅዱሳን፣ በኃጥዓን፣ በከሃድያን ሊፈወስ ይችላል። ድኅነት ግን በክርስቶስ ላመነ ለክርስቲያን ብቻ ይደረጋል እንጂ እንደፈውስ ለሁሉ አይደረግም። እገሌ ባሕታዊ እገሌ አጥማቂ ከበሽታየ ፈወሰኝ ስለዚህ የፈወሰኝ ሰውየው የእግዚአብሔር ሰው ቢሆን ነው ማለት ያለማወቅ ውጤት ነው። ክፉ ባሕታውያንም ደግ ባሕታውያንም ሊፈውሱ ይችላሉ። ይህንን የሚያስረዳን የጌታችን ቃል ከላይ መጀመሪያ ላይ የጠቀስነው ጥቅስ ነው። ክርስቲያን መትጋት ያለበት ለነፍሱ ድኅነት ነው። ለዘለዓለማዊው ድኅነት ነው። ፈውስማ ዙሮ ዙሮ ስንሞት ተከትሎን አይሄድም። ድኅነት ግን መልካም ሥራ በመስራት ንሥሓ በመግባት ሥጋውን ደሙን በመቀበል በረድኤተ

እግዚአብሔር ይገኛል።የአጥማቂ ነኝ ባይና የባሕታዊ ነኝ ባይ ከዳሚ እና መንጋ አትሁን። ክርስቶስን ተከተል። ተጋድሏቸውን የጨረሱ ቅዱሳንን ሕይወት አብነት አድርግ።

ባሕታዊና መነኩሴ ክፍል 7

ቴሌቭዥኔ ተበላሽቶብኝ ከዚያ ጠበል ረጨሁትና ሠራ። ምእመናን እልል በሉ እልልልልልልልልልልልልል አጨብጭቡ ጨብጨብጨብጨብ .....እረ ወዴት እየሄድን ነው ጎበዝ? ዓውደ ምሕረት ነገራተ እግዚአብሔር የሚነገርበት አደባባይ ነው ወይስ እንደዚህ መቀለጃ ነው!? በዚህ ሰሞን ደግሞ ከአንድ ቤተክርስቲያን "ባሌ አሥር አለቃ ነበር። ከዚያ አሁን መቶ አለቃ ሆኖልኛልና የደስ ደስ ጥላ አስገብቻለሁ" ስትል ሕዝቡ እልልልልልልልልልልልል ጨብጨብ ጨብጨብ..... ቆይ ግን በስንቱ እንፈር ግን!? የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማኮ ሰው ንሥሓ ገብቶ ቆርቦ እንዲድን ነው። ቴሌቭዥን እንዲሰራ፣ መቶ አለቃ እንዲሆን ነው እንዴ ጌታ ሰው የሆነው!? በነገራችን ላይ እንዲህ ዓይነት "ቅዳሴው ቢያልቅበት ቀረርቶ ተካበት" እንደተባለው ሰውየ አንዳንድ ሰባክያን ወንጌል ቃለ እግዚአብሔር እያለቀባችሁ ከተቸገራችሁ ጉባኤ ቤት ገብታችሁ ጨምራችሁ ተማሩ። እንጂ ቤተ ክርስቲያን መቀለጃ አይደለችም። እስኪ እንጠያየቅ እያንዳንዱ ምእመን በዓመት ስንት ጊዜ ይቆርባል? ስንቱ ንሥሓ ይገባል? ጌታችን በወንጌሉ ማቴ.12፣39 "ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይሻል" ብሏል። ተአምር ቁም ነገር አይደለም። ወንድሜ አመንዝራ ሆነህ ተአምር ፈልገህ ከባለዊግ መነኩሴ ነኝ አጭበርባሪ ወደ ባለዊግ ከገዳም ገዳም አትንከራተት። ንሥሓ ገብተህ ጠበል ተረጭተህ ሥጋውን ደሙን ተቀብለህ ደዌህ ካልለቀቀህ በቃ በጸጋ ተቀበለው። ጌታ ሆይ በበደሌ ምክንያት ይህንን ደዌ አድርሰህብኛልና በነፍሴም እንዳትቀጣኝ ማረኝ በል። ገዳም የምንሄድኮ በዚያ የነበሩ ቅዱሳን ካሉ የእነርሱን ገድል ሰምተን ጾም ጸሎት ይዘን ንሥሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን ተቀብለን ለመምጣት ነው ለሌላ ዓላማ አይደለም። ሳይታወቃችሁ ለሆነ መነኩሴ ነኝ ባይ አጭበርባሪ ደግፋችሁ ሽንጣችሁን ገትራችሁ የምትከራከሩ ሰዎች ሰው አምላኪ አትሁኑ። የሞተልህ ተሰቅሎም ያዳነህ ክርስቶስ ነው። እርሱን ተከተል። በተጨማሪ ተጋድሏቸውን ጨርሰው ወደዚያኛው ዓለም የሄዱ ቅዱሳንን አብነት አርዓያ አድርግ። በሕይወተ ሥጋ ላለ መነኩሴ ጥብቅና የምትቆም ከሆነ ግን ጣዖት አምልኮ ነው። ምክንያቱም ፍጻሜው አይታወቅምና። ይሁዳ ሐዋርያ ነበረ ግን ካደ። ጳውሎስ አሳዳጅ ነበረ በኋላ ግን ሐዋርያ ሆነ። ስለዚህ በዚህ ምድር ያለን መነኩሴና ባሕታዊ አትከተል መንጋ አትሁን። ብዙ አጭበርባሪዎች ተነስተዋልና እንዳትታለል። ንሥሓ አባት ያዝ ንሥሓ ግባና ሥጋውን ደሙን ተቀበል። ሲጀምር ተአምር ምክንያተ ድኅነት ሊሆን ይችላል እንጂ ራሱን የቻለ ድኅነት አይደለም። የመዳን ትምህርት ይሰጥ። ሕዝቡ ሊያደርገው የሚገባውን ይስማ። እንዲጾም እንዲጸልይ ትሩፋት እንዲሰራ እንዲሰግድ እንዲመጸውት የሚያበቃውን ትምህርት ሳይማር፣ ነገረ ሥጋዌን ሳይማር፣ በዓመት አንድ ጊዜ ቢመጣ በዓሉ ስለሚከበርለት ቅዱስ እና እግዚአብሔር ስላደረገለት ረድኤት ሳይነገር፣ ዓውደ ምሕረት እንዲህ የሰፈር ወሬ ማሰራጫ መሆን የለበትም። እግዚአብሔር ለሥጋችን የሚያስፈልገንን ይሰጠናል። ይህ የእርሱ መግቦት ነው። የእኛ ትኩረት ቴሌቭዥን ነው መሆን ያለበት ወይስ ጽድቁን መሻት። ጌታኮ በወንጌሉ ማቴ.6፣33 "አስቀድማችሁ ጽድቁን እሹ ሌላው ይሰጣችኋል" ብሏል። ብሉይ ሐዲስ ሊቃውንት መነኮሳት መች ተተርጉሞና ተሰብኮ ነው

የሰፈርህ ልጅ አሥር አለቃ የስብከት ርእስ የሚሆነው!? ምእመናን ሊቃውንት አስቡበት። ብፁዕ አቡነ እንድርያስ እንዳሉት ወንጌሉ ተዳፍኖ እየቀረ ነው። ሰው ከክርስቶስ ቃል ይልቅ የባሕታዊ እና መነኩሴ ነኝ ባይ አጭበርባሪ ቃል እየሰማ ወንጌሉን የምሥራቹን ሳያውቀው እየቀረ ነው። አጥማቂ ነን ባይ አጭበርባሪዎች የድኅነት ምክንያት የሆኑትን ካህናት ደፍተራ ጠንቋይ እያስባሉ ሰው እንዳይድን ቀጥታ ለሰይጣን እየሰሩ ነው። ሰውም የሰይጣንን ምስክር እየሰማ እገሌ የተባለው መርጌታ ነው እንዲህ ያደረገህ ያለውን የሰይጣን ቃል ሰምቶ ወደዚያ መርጌታ ሄዶ ይጣላል። መጀመሪያ የሰማሀው የሰይጣንን ቃል ነው። ሰይጣን ደግሞ ውሸታም ነው። በውሸት እያጣላህ ነው። እንዳው እውነቱን ነው የተናገረ ብለህ ብታስብ እንኳ ያ መርጌታ ጠላትህ ቢሆን ወንጌል ጠላትህን ውደድ የሚል ስለሆነ ቂም የማትይዝበትብየማትጣላው ነው መሆን የነበረበት። ግን ወንጌል ስላልተማርክ ይህንን አታውቀውም። መንጋነት ከዳሚነት የትም አያደርስም ይቅርብን። ክርስቶስን እንከተል። ተጋድሏቸውን ፈጽመው የሄዱ ቅዱሳንን አብነት እናድርግ።

ባሕታዊና መነኩሴ ክፍል 8

ሽንበቆን ከየትኛው ወገን ነህ ቢሉት ነፋስን ጠይቁት አለ ይባላል። ነፋሱ ወደ ግራ ሲነፍስ ሽንበቆውም ወደ ግራ ይላል። በቃ ሽንበቆ የሆነ መንጋ ነው እያስቸገረን ያለው። የሰባኪ አጨብጫቢ፣ የአጥማቂ አሸርጋጅ ከዳሚ እያጋጠመን ነው። ይህ ደግሞ የሆነው ሰው ኦርቶዶክሳዊ መለኪያ ስለሌለው ነው። ጳጳስም በለው ንጉሥም በለው መምህርም በለው ጨዋም በለው ቄስም በለው ዲያቆንም በለው የሚለኩት በኦርቶዶክሳዊው ትምህርት ነው። ከኦርቶዶክሳዊ ትምህርት ያፈነገጠ ፓትርያርክ ካለ ይወገዛል። ስለዚህ አንድን ጉዳይ ለመመርመር ዋና ጥያቄያችንና መለኪያችን የሚሆነው ፓትርያርኩ ወይም ጳጳሱ ፈቅዷል ወይስ አልፈቀደም? የሚለው ሳይሆን ፓትርያርኩ ወይም ጳጳሱ ራሱ በኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ልክ ነወይ የሚለው ነው። ንሥጥሮስ የተወገዘ ለዚያ ነው። የአራቱ ጉባኤያት ሊቅ ቢሆን እንኳ ከኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ አፈንግጦ የአጥማቂ ነኝ ባይ አጭበርባሪ መንጋ ከሆነ በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ተመዝኖ የቀለለ ቀላል ይባላል። አርዮስ ሊቅ ነበር። ነገር ግን ክህደቱን በብዙ ጥቅስ ቢሸፋፍናትም በዓይናማ ሊቃውንት በኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ቀሎ ስለተገኘ ተወግዟል። እንደምታውቁት በጋሻው ደሳለኝ በሲኖዶስ ከመወገዙ በፊት ብዙ አጨብጫቢ ነበረው። ለአጨብጫቢው የልብ ልብ የሰጡት ደግሞ ይባስ መጋቤ ሐዲስ ብለው ስም የሰጡት ጳጳስ ናቸው። ከዚያ በበጋሻው ላይ ጥያቄ ሲነሳ በጥያቄው ላይ ውሃ ለመቸለስ ይጥሩ የነበሩ አብረውት ፎቶ እየተነሱ ልጃችን በርታ የሚሉት ጳጳሳት ነበሩ። ነገር ግን በጋሻውም ይሁን ጳጳሳት በኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ይለካሉ እንጂ በመንጋ እና ሥልጣንን ወይም መዓርግን ተገን በማድረግ የሚያድበሰብሱት አስተምህሮ የለንም። ቀሎ የተገኘ ጳጳስ ካለ ይወገዛል። ቀሎ የተገኘ መምህር ካለ ይወገዛል። ለአንድ ከሃዲ የፈቃድ ወረቀት ፓትርያርኩ ወይም ጳጳሱ ሰጠው ማለት ያ ከሃዲ ትክክል ነው ማለት አይደለም። ከታሪክ የምንማረው ይህንን ነው። አርዮስን ተፍጻሜተ ሰማእት ቅዱስ ጴጥሮስ አውግዞ ለይቶት ነበር። በኋላ ፓትርያርክነት የተሾመው አኪላስ ግን አርዮስን ከግዝቱ ፈቶ እንዲያስተምር ፈቅዶለታል። ይህ የፓትርያርኩ ፈቃድ ግን አርዮስ ልክ ነው ለማለት መለኪያ አይሆንም። ቆይቶ በእለእስክንድሮስ

ፓትርያርክነት በ318ቱ ሊቃውንት አርዮስ ተወግሏል። ለዚያ ነው ማንኛውም ሰው በኦርቶዶክሳዊው አረዳድና አስተምህሮ ይለካል የምንለው። ስለዚህ ከሀገረ ስብከት ወይም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የፈቃድ ወረቀት ይዞ መጥቶ የሚያጭበረብር መነኩሴና ባሕታዊ ይኖራል። ይህ ሰው ለጥፋቱ መደበቂያ ደግሞ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ወይም ከሀገረስብከት አጽፌ ነው ሊል ይችላል። ይህን ጊዜ የሰውየውን ችግር ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አንጻር መዝግቦ ፈቃድ የሰጠውን ጳጳስ ወይም ፓትርያርክ ሂዶ መጠየቅ ይገባል። ችግሩንም አስረድቶ ማስወገዝ ይቻላል። ሁልጊዜም የማትሳሳት ቤተ ክርስቲያን ናት። የክርስቶስ ሙሽራ ናትና። ይህውም አስተምህሮዋ ነው። ስለዚህ ከአስተምህሮዋ ያፈነገጠ ፓትርያርክም ጳጳስም ቄስም ዲያቆንም መነኩሴም መምህርም ካለ በአስተምህሮዋ ተመዝኖ ቀሎ ሲገኝ ይወገዛል። ስለዚህ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ ምን ይላል የሚለውን እንወቅ እንጂ አባ እገሌ ወይም መምህር እገሌ ፈቀደ ወይስ አልፈቀደም? የሚለውን አይደለም። የፈቀደው አካልም ስህተት ከተገኘበት ይወገዛልና። ለግለሰቦች ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እንቁም።

ባሕታዊና መነኩሴ ክፍል 9

ማቴ.7፣15 "የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ"። አንዳንዱ ባሕታዊ ወይም መነኩሴ ነኝ ባይ አጭበርባሪ ራሱ ከሆነ ቦታ መስቀልና ወይም ታቦት ይቀብርና። ከዚያ ሣር ከበቀለበት በኋላ በዓመቱ ወይም በሁለት ዓመቱ በራእይ ከዚህ ቦታ ላይ የተቀበረ "መስቀልና ታቦት" እንዳለ እግዚአብሔር ገልጦልኛል ይላል። ከዚያ መለኪያና መመዘኛ የሌለው መንጋው እንግዲህ ከተገለጠልዎትማ እንቆፍር እንጂ ብሎ ከዚያ ቦታ ይቆፍራል። ልክ እንደተባለውም መስቀልም ታቦትም ይገኛል። ይህን ጊዜ ሕዝቡ ይህን ባሕታዊ እግዚአብሔር በራዕይ የሚያነጋግረው ስለሆነ ታላቅ ነው ይልና ያለውን ነገር በሙሉ ያደርጋል። ብር አውጡ ሲል እሺ እያለ በተኩላ ይበዘበዛል። ለአቋቋሙ ለድጓው ለመጽሐፉ ለቅኔው መምህር ሠርከ ጎብስት የማይሰጥ ምእመን ለተኩላ በፈቃዱ ይሰጣል። ያንንም ተኩላ ሊቃውንቱ ስህተቱን ስለሚገልጡበት ደፍተራ ጠንቋይ እያስባለ እውነቱን ሕዝቡ እንዳይቀበል ያደርጋል። አንድ ጊዜ አዲስ ዘመን ሦስት ሕጻናት ከሞት ተነሱ ተብሎ ተነገረና ሰው ከሞት የተነሳን ሰው ለማየት ይጎርፍ ጀመር። ነገሩ ግን እንዲህ ነበር። ለሦስት ቀን የሞተ ሰው የሚያስመስል ክኒን ሰጧቸው። ሕዝቡ ሞቱ ብሎ ሊቀብራቸው ሲል አንዱ ባሕታዊ ነኝ ይልና በራእይ ተገልጦልኛል እግዚአብሔር በእነዚህ ልጆች የሚያሳየው ድንቅ ነገር ይኖራል ተዋቸው አትቅበሯቸው ይላል። ሕዝቡም እሺ ብሎ ሦስት ቀን ቆየ። በሦስተኛው ቀን እንደተባለው ተነሱ። ከዚያ የሚናገሩትን ያ ባሕታዊ አስጠንቶ በሰማይ ያለው ነገር ምን ይደንቅ እያሉ ማውራት ጀመሩ። ሕዝቤ እነርሱን ለማየት ግፊያ ያዘ። ከዚያ ያን ባሕታዊ ብዙ ሰው ተከተለው። ሕዝቡም ገንዘቡን ጊዜውን አባከነ። ተበዘበዘ። ከእነዚያ አዲስ ዘመን ተነሱ ከተባሉት ሕጻናት አንዲቱ አሁን ሱሪ ለባሽ ፍንዳታ ናት ሲባል ሰምቻለሁ (ፍንዳታ ማለት ከባህሉ ከሃይማኖቱ ወጥቶ ፍጹም ሥጋዊ ማለት ነው)። አይ ሰማይን ያየ ሰው። ሲኦልን እና ገነትን አይቶ የፈነዳ ሰው አይተንም አናውቅ። ድራማ ነው እየተሰራ ያለውኮ። ከአንጥረኛ እያሰሩ ከሰማይ የወረደ መስቀል እያሉ የሚያታልሉ ባሕታዊና መነኩሴ መሳይ አጭበርባሪዎችም አሉ። ይህ ሁሉ ወንጀል ለምን በባሕታውያን እና በመነኮሳት አምሳል

እየተደረገ ይሠራል!? የሚል ጥያቄ ሊጠየቅ ይችላል። ተገቢ ጥያቄ ነው። ትክክለኛ መነኮሳትና ባሕታውያን ምድራውያን መላእክት ናቸው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ውለታ የዋሉም በታሪክ ባሕታውያን እና መነኮሳት ናቸው። እነ አቡነ ተክለሃይማኖት፣ እነ አባ ኢየሱስ ሞዐ፣ ተስዐቱ ቅዱሳን፣ እነ አቡነ ዘርዓቡሩክ እና ሌሎችም መነኮሳት ነበሩ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመነኮሳትና ለባሕታውያን ልዩ ፍቅር አለው። ስለዚህ አጭበርባሪዎችም የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመሸወድ ሕዝቡ በሚወደው አምሳል ብንሄድ ተቀባይነት እናገኛለን በማለት ነው። ቆቡን ልብሱን የመነኮሳት አድርገው ዓላማቸው ግን ሕዝቡን መበዝበዝ ነው። በገዳም ሥርዐት አንድ መነኩሴ መጀመሪያ ረድእ ሆኖ እያረሰ እየቆፈረ ምግብ እያበሰለ አባቶችን እየረዳ ይቆያል። በዚህ ጊዜ በአመክሮ ያለ ይባላል። ቆቡም የአመክሮ ቆብ ትባላለች። ከዚያ ምግባሩ የተመሰከረለት ሲሆን ይመነኩሳል። ከዚያ በምንኩስናው ሕይወት በትሩፋት በምግባር ሲያድግ ለብቻው እንዲኖር ገዳሙን ያስፈቅዳል። ገዳሙም ከዚያው ቦታ ለዚያ ሰው ልዩ ቦታ ይሰጠዋል። ያ ባሕታዊም ቤት ዘግቶ ማንም ሳያየው ይኖራል። ምግቡን የሚወስድለት የታዘዘ ረድእ ከቤቱ ደጃፍ ወይም በር እያደረገለት ይመለሳል። በዚህ መልኩ ባሕታዊ ከሆነ በኋላ ሰው ሳያየው ከበዓቱ ተከቶ ይኖራል። ባሕታዊን በዓታዊ (በበዓት ተከቶ የሚኖር) የሚያሰኘውም ይህ ነው። እንጂ ከከተማ ከተማ እያውደለደሉ ባሕታዊ የለም። የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላን ያልተማረ ሰው ለምዱን ብቻ አይቶ በግ ነው ሊለው ይችላል። የበግና የተኩላ መለኪያ የሌለው ሰው በግም ተኩላም ያው ናቸው። በግና ተኩላን የምንለይበት ብዙ መንገድ አለ። ቆዳ አንዱ ነው። ነገር ግን ተኩላም በግ ለመምሰል የበግ ቆዳ ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህ ሌላ ተጨማሪ መለኪያ ያስፈልጋል። ለምሳሌ በምግብ አበላል። በግ ሣር ቅጠላ ቅጠል ነው የምትበላ ውሃ ነው የምትጠጣ። ተኩላ ደግሞ ደም ይጠጣል ሥጋ ይበላል። ተኩላ ከበግ ጋር አይኖርም። ምናልባት ከድንገት ከበግ ጋር ካገኘኸው እንኳ አንዷን በግ ወስዶ ለመብላት ነው። ምግቡ ሥጋ ነውና።ስለዚህ ከአጭበርባሪ ባሕታውያን ነን ባዮችና መነኩሴ ነን ባዮች ራሳችንን እንጠብቅ።

ባሕታዊና መነኩሴ ክፍል 10

አሁን አሁን ባሕታዊ እና መነኩሴን መምሰል ዋና የቢዝነስ ምንጭ ሆኗል። ሥራ አጡ ስለበዛ አንዳንዱ የባሕታዊ ነኝ ባይ ከዳሚ ይሆንና ፍርፋሪ እየበላ በዚያ ይኖራል። ልብ ብላችሁ አስተውሉማ የባሕታዊ ነኝ ባይ አጭበርባሪዎች ዋና መንጋዎች በትምህርታቸው ብዙ ያልገፉ፣ ቤተ ክርስቲያንን በስም እንጂ አስተምህሮዋን የማያውቁ ሰዎች ናቸው። ለነፍሳቸው ድኅነት ሳይሆን ለሥጋቸው ፈውስ የሚጨነቁ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ አንድ ሰው ባሕታዊ ወይም መነኩሴ ሳይሆን በውሸት ባሕታዊ ነኝ ወይም መነኩሴ ነኝ የሚለው በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል።

1) ለገንዘብ ብሎ

2) ለክንቱ ውዳሴ

3) ለፖለቲካዊ ተልእኮ

ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ዘመናችን አጭበርባሪ የበዛበት፣ አጭበርባሪዎች ተናበው የሚሰሩበት ወቅት ስለሆነ በእነርሱ እንዳንታለል ራሳችንን መጠበቅ አለብን። ስለዚህ ከእያንዳንዱ ምእመን ምን ይጠበቃል ስንል፦

፩. የቤተክርስቲያንን አስተምህሮ ማወቅ

፪. የንሥሓ አባት መያዝ

፫. ንሥሓ ገብቶ መቁረብ

፬. መጾም፣ መጸለይ፣ መስገድ

፭. ሥርዐተ ቤተክርስቲያንን ማወቅ

ይጠበቅበታል። አንድን ሰው የምንለካበት መለኪያችን ይህ ነው። ኦርቶዶክሳዊ አረዳድ ይኑረን። መለኪያ ከሌለን ሁሉ ልክ ሊመስለን ይችላል። መዳረሻችንን ካላወቅን ሁሉም መንገድ ይወስደናል እንደሚባለው መዳረሻችንን አውቀን መንገዳችንን እንድንለይ ኦርቶዶክሳዊ አረዳድ ይኑረን። እንደየሁኔታው ወደፊትም በዚህ ዙሪያ ልጽፍ እችላለሁ። ለጊዜው ግን በዚህ ይብቃን። አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮም ላስፈጸመን ልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይገባል። እይውልህ ወንድማለም "የቴሌግራም በረኽኛ"ን አትስማ። ችግር በተነሳ ቁጥር መረጃውን ተንትነው ትንቢት አድርገው የሚያቀርቡልህን ቀበሮዎች አትስማ። It is not prophecy. ይሄ ትንቢት አይደለም። Political Analysis and Socio Economic Analysis ይሰራና ልክ እንደ ሜትሪዮሎጂ ትንበያ ይደረጋል። ይህንን ነው እየነገሩህ ያሉት። ደግሞኮ ብልጠታቸው ነው የሚገርመኝ ትንበያው የማይሳካ ከሆነ ንሥሓ ገብተን ነው የቀረ ይሉሀል። ሕዝቡ ግን ድጎነትን በማኅበራዊ ሚዲያ መፈለጉ ለምን ይሆን!? እንዴ አንዳንዱ ኑ 1000 ሺ ጊዜ ሼር አድርጉልኝ። ከዚያ ተዋሕዶ ታሸንፋለች ይልሀል። ቆይ ኮሜንት ማድረግና ሼር ማድረግ ከመቼ ጀምሮ ነው ማሸነፊያ የሆነው?! የራሳቸውን ዓላማ ለማሳካት ራሳቸው ሊያደርጉት ያሰቡትን በትንቢት መልኩ ይናገሩታል። ያች ዛሬ ቤት ይቃጠላል ንሥሓ ግቡ እንዳለችው ሴትዮ ነው። ገበያ ሲሄዱ ራሷ አቃጠለችው። ከዚያ ሕዝቡ ሲመለስ ቤቱ ተቃጥሎ አገኘ። አሁን አሁን ይሄ በረኽኛ እያሉ የሚገልጿቸው እንዲህ የሰለጠኑ ሌቦችን ነው። እይውልህ ትክክለኛ ባሕታውያን ረድእነትን ተሻግረው በምንኩስናቸው ብዙ አገልግለው በኋላ በገዳሙ ፈቃድ በዓት አጽንተው የሚይዙ ናቸው። መልክእት ካለም ባሕታዊው ለገዳሙ ይናገራል። ገዳሙ በሕጋዊ ደብዳቤ ለሲኖዶስ ይልካል። በሲኖዶስ በኩል ይደርሰናል። ይሄ በሰፊራ ሰፈሩ የሚነገረውን ሁሉ በረሃውያን ተናግረውታል እያልክ አትጃጃል። እውነት ነው ሀገራችን ችግር ውስጥ ገብታለች። ይህ ደግሞ የሆነ በሁላችንም የጋራ ጥፋት ነው። ይህንንም ማስተካከል የምንችለው እኛው ተመካክረን ያለፈ ቂምን ከተውን ነው። ንሥሓ መግባት እውነት ነው። ከዚያ ውጭ አንዱን ብሔር ከአንዱ ብሔር የሚያበላልጥ ባሕታዊ የለም። በማኅበራዊ ሚዲያ ጸሎት የሚለወጥ ምንም ዓይነት ችግር የለም። ባሕር ማዶ ተቀምጠህ የኢትዮጵያን ችግር ለመፍታት ብለህ መጠቆም አያስፈልግህም። እውነታውን ና እየውና ከእውነታው ጋር የተዛመደ መፍትሄ አምጣ። እግዚአብሔር ይረዳናል። የሚረዳን ደግሞ የእኛን ነጻ ፈቃድ ተጠቅሞ ነው። የእኛኑ

ችግር ለመፍታት እየጸለይን እንነጋገር። ተራራው ዝቅ ይበል። እኔ ያልኩት ካልሆነ የሚለው ሰው ዝቅ ይበል። ሽለቆው ይሙላ። የበታችነት ስሜት የሚሰማው ከዚያ ወጥቶ ሊያዛልቀን የሚችለውን ነገር እንወያይ መሬት ላይም በተግባር እንገናኝ። ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ፈተና ውስጥ ናት። ይህንን ፈተና ግን መፍታት የሚቻለው በግለሰብ ቀስቃሽነት በደም ፍላት ፖሊስ እያሯሯጠህ የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማን ነው እያልክ ዩዜን ቦልትን የሚያስንቅ ሩጫ እየሮጥክ አይደለም። ትላንት የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዳደረገው በመዋቅር ታቅፎ ውስጥ ለውስጥ ተነጋግረን ነው መፍትሄ የሚመጣው። ልክ እንደዛሬው ሲኖዶስ። ሲኖዶስ ይምከር።ከዚያ በሀገረ ስብከት ደግሞ ወረዳ ቤተ ክህነቶች ተሰብስበው ይምከሩ። ከዚያ ወረዳ ቤተክህነት ላይ ደግሞ የእያንዳንዱ አጥቢያ አስተዳዳሪዎች ይምከሩ። ከዚያ በእየ አጥቢያችን ደግሞ እያንዳንዱ ምእመን ይምከር። የሚያዛልቅ መፍትሄ እናምጣ። የሚዲያ ጩኸት ምስጢርን ከማባከን የዘለለ ሚና የለውም። እኛም ዘለን ጳጳሳትን ከመወረፍ አጥቢያህ ያለውን አስተዳዳሪ አስረዳኝ እንዴት እንዲህ ይሆናል ብለህ ወጥረህ ያዘው። ከዚያ በምክንያት እና በእምነት የተደረገ መፍትሄ ያዛልቃል። ይሄው ነው።

ሥነ ፍጥረት

ሥነ ፍጥረት ክፍል 1

መቼም ከእኛ በፊት የነበሩ ሰዎች ነበሩ።እኛ ያን ጊዜ አልነበርንም። አሁን ደግሞ እነርሱ የሉም።እኛ አለን። ወደፊት ደግሞ እኛ በሥጋ አንኖርም። አሁን የሌሉ ግን ያን ጊዜ ይኖራሉ።ብፀሐይን የሚያወጣ፣ መዓልትና ሌሊትን የሚያፈራርቅ ያልነበርን እኛን ወደ መኖር ያመጣን በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሕግን የሰራ ማን ነው? ማር ይጣፍጣል። ማርን እንዲጣፍጥ ያደረገው መልኩን ብርቱካናማ ያስመሰለው። ወተትን ነጭ ያደረገው ማን ነው። who is the reason of the reasons. የምክንያቶች ሁሉ ምክንያትን ማን ነው? የዝናብ ምክንያቱ ደመና ነው። የደመና ምክንያቱ ደግሞ ርጡብ አየርና ምውቅ አየር ነው። እንዲህ እንዳህ እያለ ወይ recycle ያደርጋል። ወይም ደግሞ በእኛ ዘንድ ምክንያቱ አልታወቀ ብሎ ይቀራል። ነገር ግን ደመና ዝናምን እንዲያስገኝ ያደረገው አካል ማን ነው? እኛን ግድግዳ እንዲከለክለን ያደረገው ማን ነው። መቼም ስንፈጠር ግድግዳ የማይገድበን የማይከለክለን ሆኖ ቢሆን ኖሮ ግዙፍ ስለሆንን ነው ግድግዳ የገደበን የሚለው አመክንዮ ውሸት ነበር። ሳይንስ ያለውን ይናገራል እንጂ። ያለውን እንዲኖር ያደረገው ማን ነው ለሚለው መልስ የለውም። ምናልባት መልስ አለኝ ካለ እንኳ pridiction እንጂ ቁርጥ ያለ ነገር የለውም። ያልነበረበትን ዘመን አሁን ባሉ ተፈጥሯዊ ሕጎች መደምደም የተለያዩ የአመክንዮ ስህተቶች አሉበት። ምሳሌ ማታ 1 ሰዓት የተወለደ ልጅ በደንብ መናገር ቢችል በዚህ ዓለም ብርሃን አለ ብትሉት አያምንም። because አላየውም።እርሱ ከተወለደ ጀምሮ እስከ ጠዋት ያለው ጨለማ ነው። ምናልባት ሊናገር የሚችለው ስለ ጨለማ ብቻ እንጂ ጨለማን ብቻ ስላየ ሌላ ብርሃን አለ ማለት አይችልም። If we throw a ball to the air. It returns back to the earth. What is the reason behind this? መቼም ሁላችንም because of gravity ማለታች አይቀርም። የእኔ ጥያቄ ግን መሬትን እንድትስብ ያደረጋት መነሻ ምክንያቷ ምንድን ነው? ምክንያቱም እኛ እየተናገርን

ያለነው ከሆነ በኋላ ስለሆነው እንጂ ለመሆኑ መነሻ ምክንያቱ ምን እንደሆነ መናገር አንችልም። ምክንያቱም አለማወቅ ይገድበናል። የአካል ውስንነት እንዳለን ሁሉ የእውቀት ውስንነም አለብን። ለፈጣሪ ግን እርሱ ራሱ እንደነገረን ለእውቀቱም ገደብ የለውም ለአካሉም ወሰን የለውም። የሆነ ሆኖ የተፈጥሮ ሕጎች ምክንያት የፍጥረታት ሁሉ መገኘት ምክንያት የአካላቸው የባሕርያቸው መሰረት እግዚአብሔር ነው።ፍጥረታትን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ እርሱ ነው። ይህ ከሆነ ለእግዚአብሔርስ ለመኖሩ ምክንያቱ ምንድን ነው ከተባለ መልሱ እግዚአብሔር የምክንያቶች ምክንያት እንጂ ለራሱ መኖር ሌላ ምክንያት የለውም። ለዚያ ነው ቅዳሴ ላይ እስመ አልቦ ውስተ ህላዌሁ አመክንዮ የምንለው።ፍጥረታት ሳይፈጠሩ እርሱ ነበረ። አኗኗሩ እንዴት ነበር ከተባለ ዛሬ እንደሚኖረው አኗኗር ነው። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ የኑሮ ለውጥ የለም። መዝ.101 አንተ ግን ያው አንተ ነህ እንዲል።ያን ጊዜ ፈጣሪ የሚኖርበት ሌላ ቦታ እና ጊዜ አልነበረም። ቦታውም ጊዜውም በቦታውና በጊዜው የሚኖረውም ራሱ እግዚአብሔር ነበር። ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ላይ ለሊከ ብከ ተከደንከ ወለሊከ ኪያከ አንጦላእከ ሥውር ብከ ዕበይከ ብሎ ያመጣዋል። ይህ አስቀድሞ የነበረ ያለ እና የሚኖር እግዚአብሔር የራሱ የሆነ አካል እና ባሕርይ አለው። ለባሕርይው ደግሞ ጸዳለ ባሕርይ ወይም ስነ መለኮት አለው። ፈጣሪነት፣ ፈታሒነት፣ መሓሪነት፣ ከሃሊነት፣ ሕያውነት እና የመሳሰሉ ነገሮች ስነ መለኮቱ ናቸው።በዚህ ግብረ ባሕርይው ፍጥረታትን ካለመኖር ወደ መኖር አመጣ። እኛ የምናውቃቸው ቦታ እና ጊዜ ራሱ ፍጡራን ናቸው። ይህንን ከምን አምጥተን ተናገርነው። ለነገራችን መሰረቱ ምንድን ነው ካልን ራሱ እግዚአብሔር ለእኛ ተገልጦ ፈጣሪነቱን ሁሉን ቻይነቱን እና ሌሎች ችሎታዎቹን ነገረን አሳየን። ለሙሴ ዘጸ.3፣6 ያለና የምኖር እኔ ነኝ ካለ በኋላ ፈጣሪነቱን ተአምራት በማድረግ እንጨትን ሕይወት ያለው እባብ አድርጎ ሕይወት ያለው እባብን ደግሞ እንጨት አድርጎ ፍጥረታትን ሲያዝዝ ገለጠለት አሳየው። ሙሴ ያየውን ለልጅ ልጆቹ ጽፎ አስተላለፈልን። ስለዚህም ሃይማኖት የፈጣሪ ለፍጡራኑ መገለጥ ተብሎ በምስጢራዊ የአተረጓጎም ስልት ይተረጎማል።

ሥነ-ፍጥረት ክፍል 2

እሑድ የተፈጠሩ ፍጥረታት 7 ናቸው። ኩፋ. ፪፣፮።

- 1 7ቱ ሰማያት
- 2 ጨለማ
- 3 መላእክት
- 4 እሳት
- 5 ውሃ
- 6 መሬት
- 7 ነፋስ

እግዚአብሔር እነዚህን ሰባቱን ፍጥረታት የፈጠራቸው (ያመጣቸው) ካለመኖር (እም ኀበ አልቦ) ነው።ሁሉን ቻይ አምላክ ስለሆነ ያልነበረን እንዲኖር ማድረግ ያለን ደግሞ እንዳልነበረ ማድረግ ይችላልና።ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ መላእክትን ማሰብ መናገር የሚችሉ አድርጎ ፈጥሯቸዋል። መላእክትን 100 ነገድ አድርጎ ፈጥሯቸዋል። ለ10ሩ ነገድ አንድ አንድ አለቃ እያደረገ ፈጥሯቸዋል። አለቆቹም ሳጥናኤል፣ ኪሩብ፡ ሱራፌ፣ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ሰላትያል፣ ሰዳካኤል፣ ዑራኤል... ናቸው። 10ሩ ነገድ የተባሉትም፦

- 1 አጋዕዝት
- 2 ሱራፌል
- 3 ኪሩቤል
- 4 ኃይላት
- 5 መናብርት
- 6 አርባብ
- 7 ሊቃናት
- 8 መኳንንት
- 9 መላእክት
- 10 ሥልጣናት

ናቸው። እኒህ 10ሩ ነገድ የሚኖሩባቸው ከተሞች ደግሞ 3 ናቸው እነዚህም፦

- 1 ኢዮር
- 2 ራማ
- 3 ኤረር

ናቸው። ነገር ግን ሳጥናኤል ውሸትን ከልቡ አፍልቆ ፈጣሪ ሳይሆን ፈጣሪ ነኝ ብሎ ሁከት ፈጠረ። ይህን ጊዜ አስተዋይ መላእክት ፈጣሪ በፍጥረቱ ይታወቃልና ፈጥረህ አሳየን አሉት። እፈጥራለሁ ብሎ እጁን ወደ እሳቱ ቢከት ተቃጠለ። ይህን ጊዜ አንተ አምላክ አይደለህም። አምላካችንን እስክናውቀው ድረስ በያለንበት እንቁም ብሎ ቅዱስ ገብርኤል መላእክትን አረጋጋቸው። ወአኀድኦሙ መልአከ ሰላም በቃሉ እንዲል። ከዚህ ጀምሮ የሰይጣን ሥራ ከእግዚአብሔር ሕግ በተቃራኒ መቆም ሆነ። ቅድም ሰባቱ ሰማያትም የተፈጠሩ እሑድ ነው ብለን ነበር። እነዚህ ሰባቱ ሰማያት የተባሉትም።

- 1 ኢየሩሳሌም ሰማያዊት

- 2 መንበረ ስብሐት
- 3 ጽርሐ አርያም
- 4 ሰማይ ውዱድ
- 5 ኢዮር
- 6 ራማ
- 7 ኤረር

ከ5-7 ያሉት የመላእክት ከተሞች መሆናቸውን ተመልክተናል። መንበረ ስብሐት የሚይታየው እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ በዘፈቀደ በዘይክሉ (እርሱ በወደደ እነርሱ ማየት ወይም መስማት በሚችሉበት መጠን) የሚገለጥበት ነው። ኢየሩሳሌም ሰማያዊት የሰው ልጅ ጽድቅ ቢሰራ ለዘላለም የሚኖርባት መልካም ቦታ ናት። የሆነ ሆኖ በእለተ እሑድ የተፈጠሩ ፍጥረታት እኒህ ናቸው።መላእክት ስሙን ቀድሰው እርሱን በማመስገን በደስታ እንዲኖሩ ተፈጥረዋል። አይ አናመሰግንም ያሉት የዲያብሎስ ሠራዊት ደግሞ በስቃይ ይኖራሉ። መላእክት ከተፈጠሩ ጀምረው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው እያመሰገኑ በታላቅ ደስታ ይኖራሉ። መላእክት ረቂቃን ፍጥረታት ናቸው። ከነፋስ የረቀቁ ናቸው።

ሥነ ፍጥረት ክፍል 3

በሁለተኛው ቀን እግዚአብሔር አንድ ፍጥረትን ፈጥሯል ይኽውም # ጠፈር ነው። ዘፍ.1፣3 ለይትጋባዕ ማይ ውስተ ምእላዲሁ። ብሎ ከምድር እስከ ብሩህ ሰማይ የነበረውን ውሃ ለ3 ከፍሎታል ይኽውም። የተወሰነውን ውሃ ከምድር በታች አድርጎታል። ምድር ያለችው በውሃ ላይ ነው። ይህች ውሃ "አንስቲያዊት ውሃ" ትባባላች። ሌላኛውን ውሃ ደግሞ ከምድር በላይ ከብሩህ ሰማይ በታች አድርጎታል። ይኽውም "ሀኖስ" ይባላል። ሀኖስን የተሸከመው ባቢል የሚባል ነፋስ ነው። ይህ በእለተ ሰኑይ የተፈጠረው ጠፈር የብርሃናት (ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ብርሃናት) መመላለሻ ነው።

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለምን ፈጠረ?

ፈጢረ ዓለም የሥላሴ የአሐቲ ባሕርይ ግብረ ባሕርይ ነው። ፍጥረታትን ለአንክሮ/ ለተዘክሮ/ አንዱ በአንዱ እንዲኖር አድርጎ ፈጥሯቸዋል። ለሰው ልጅ ምግብ እንዲሆኑ የተፈጠሩ ፍጥረታት አሉ። ለሰው ልጅ መኖርያ እንዲሆኑ የተፈጠሩ አሉ። ለአራዊት ለእንስሳት ምግብነት እንዲያገለግሉ የተፈጠሩ አሉ። እነርሱን ዓይተን እግዚአብሔርን እንድናደንቅ የሚያደርጉን ፍጥረታት አሉ። መጽሐፍ ጠፈር በእለተ ሰኑይ እንደ ተፈጠረ ይነግረናል። ሰነየ ሁለት አደረገ ከሚለው ቃል የተገኘ ሲሆን ሰኑይ ማለት ሁለተኛ ቀን ማለት ነው። ይኽውም ለፍጥረት ሁለተኛ ቀን ማለት ነው። እንደሚታወቀው በቤተክርስቲያን የእለታት እና የወራት ስያሜ ሳይቀር ከሥነፍጥረት ጋር የተያያዘ ነው። ይኽውም።

- 1 እሑድ....የመጀመሪያ ቀን
- 2 ሰኑይ.....ሁለተኛ ቀን
- 3 ሠሉስ....ሦስተኛ ቀን
- 4 ረቡዕ.....አራተኛ ቀን
- 5 ኀሙስ...አምስተኛ ቀን
- 6 አርብ...የፍጥረት መካተቻ ቀን
- 7 ቅዳሜ...የመጀመሪያ ሰንበት

ማለት ነው። ሁሉም የግእዝ ቃላት ናቸው። ትርጉማቸው ከላይ ያለውን ይመስላል።እሁድ በመጽሐፈ ኩፋሌ 2፣8 እንደተገለጸው 7 ፍጥረታት ተፈጥረዋል። ሰኞ አንድ ፍጥረት ተፈጥሯል። እርሱም ጠፈር ነው።

ሥነ ፍጥረት ክፍል 4

በዕለተ ሠሉስ (ማክሰኞ) የተፈጠሩ ፍጥረታት 4 ናቸው።ኩፋ. ፪፣፲፬።

- 1 አዝርዕት፣
- 2 አትክልት፣
- 3 እፀው እና
- 4 ዕፀወ ገነት ናቸው።

እፀው ለሰው ልጅ ለምግብነት፣ ለልብስ፥ ለመጠለያ፣ ለመድኃኒትነት ለተለያዩ የሰው ልጅ ፍላጎት ይውላሉ። እዕ የሐዩ ወእዕ ይቀትል።እዕ ይገድላል። እዕ ያድናል። ለአንዱ ፍጥረት የተመቸው ለሌላው ላይመች ይችላል። ለአንዱ ለምግብነት የሚያገለግለው እዕ ለሌላው መርዝነት ኖሮት ሊገድለው ይችላል።የፍጥረታት አፈጣጠራቸው ልዩ ልዩ ስለሆነ ጸባያቸውን ባሕሪያቸውን ጠንቅቆ የሚያውቀው የፈጠራቸው እግዚአብሔር ነው። ዕፀወ ገነት ያልናቸው በገነት ያሉ እፀውን ነው። ከእነዚህ እፀው ውስጥ ቅጠላቸው ሰፋፊ የሆኑ ፍሬያቸው ትልልቅ የሆኑ አሉ። አንዱን ፍሬ ስንቆርጠው ወዲያውኑ ይተካል።እኛ በምንኖርባት በዚህች ዓለም ካሉ እፀው የተለዩ እፀው ናቸው። ቅጠላቸው እስከ 12 ክንድ ስፋት ያላቸው አሉ። አዳም መጀመሪያ የሚኖር በገነት ነበር። በነገራችን ላይ አዳም እና ሔዋን ትእዛዘ እግዚአብሔርን ሳያፈርሱ በገነት በኖሩባቸው 7 ዓመታት የበሉት የጠጡት ወዝ ይሆናቸው ነበር። እንጂ ሽንት እና ሰገራ አልነበረባቸውም።(በዚህ ምድር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሲኖሩም እንዲሁ ነበር)። ዕፀው ለተለያዩ መድኃኒቶች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያገለግላሉ።የእፀውን ባሕርይ እና ስልት ከእኛ ሰውነት ጋር ያላቸውን አሉታዊና አዎንታዊ

ተጽእኖ እያጠናን ለሕይወታችን አስፈላጊ የሆኑትን ልንጠቀማቸው ይገባል።ፍጥረታትን በተሰጠን አእምሮ እየተመራመርን ልንጠቀምባቸው እንችላለን። እግዚአብሔር ጤፍን ፈጠረ። እኛ ደግሞ የተፈጠረውን ጤፍ ፍሬውን ለይተን ከዚያ ፈጭተን አብስተን እንጀራ አድርገን እንበላዋለን። ፍጥረታትን መፍጠር የፈጣሪ ሥራ ነው። የተፈጠሩ ፍጥረታትን እየተመራመርን እየተራቀቅን ለእኛ አገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ ደግሞ የእኛ ፈንታ ነው።

ሥነ-ፍጥረት ክፍል 5

ረቡዕ ማለት አራተኛ ቀን ማለት ነው። ለፍጥረት 4ኛ ቀን ነውና። ረቡዕ እለት 3 ፍጥረታት ተፈጥረዋል። እኒህም፦

- 1 ፀሐይ
- 2 ጨረቃ
- 3 ከዋክብት

ናቸው። በብርሃናት ላይ የተሾመ መልአክ ራጉኤል ነው። ፀሐይ በመዓልት ያበራ ዘንድ ጨረቃ እና ከዋክብት ደግሞ በሌሊት ያበሩ ዘንድ ተፈጥረዋል። ጨረቃ ከፀሐይ 11 ቀን ባነሰ እለት ታበራለች። ይህም ማለት ፀሐይ 365 ቀን ስታበራ። ጨረቃ 354 ቀን ታበራለች ማለት ነው። የፀሐይ ብርሃን ጠዋት ከ12 ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ 7 ሰዓት ብርሃኗ እና ሙቀቷ እየጨመረ ይሄዳል። ከ7 ሰዓት ጀምሮ እስከ ማታ 12 ሰዓት ደግሞ በየሰዓቱ እየቀነሰ ይሄዳል። ከዋክብት በጣም ብዙ ናቸው። 7ቱን እለታት የሚመግቡ (የሚያበሩ) ከዋክብት አሉ። 12ቱን ወራት ተካፍለው የሚማግቡ ከዋክብትም አሉ። 4ቱን ወቅቶች ማለትም ክረምትን፥ ጸደይን፥ በጋን፣ በልግን ተካፍለው የሚመግቡ ከዋክብትም አሉ።ለምሳሌ 4ቱን ወቅት የሚመግቡት የሚከተሉት ናቸው፦

- 1 ናርኤል
- 2 ብርክኤል
- 3 ሕልመልሜሌክ
- 4 ምልኤል

ናቸው። እኒህም ዓመቱን 91/91 ቀን ተካፍለው ይመግቡታል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ፀሐይ ከመፈጠሯ በፊት ያለው እለት ፀሐይ ስላልነበረች አቆጣጠሩ ስለማይታወቅ በሚልየን ወይም በቢልየን ሊቆጠር ይችላል ወይም በአንጻሩ በሰከንዶችም ሊቆጠር ይችላል የሚሉ አሉ። ነገር ግን ፀሐይ ከመፈጠሯ በፊትና በኋላ ያለውን እለት ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ አንድ ቀን... ሁለት ቀን እያለ እስከ ስድስተኛው ቀን ተናግሮ ቀን ቀን በማለት ስላስተካከለው ነገሩ ያልተመቸ ነው። እኛ ዓለም የተፈጠረ መጋቢት 29 በእለተ እሑድ ነው እንላለን። ይህንንም ስንል ወደኋላ ቆጥረን ነው። ፀሐይ ከመፈጠሯ በፊትም ቢሆን መዓልትና ሌሊትን የሚለይ

ብርሃን ነበር። ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ብርሃን ብሎ ከፀሐይ በፊትም መዓልትን እና ሌሊትን የሚለይ ብርሃን እንደነበረ ያስረዳናል። ወቅቶች ዓመታትን ሳምንታትን እንድንለይባቸው እንዲሁም እንድንሰፍርባቸው የተሰጡን ብርሃናት እኒህ ሦስቱ ናቸው።

ሥነ ፍጥረት ክፍል 6

በዕለተ ኀሙስ ፫ እና ኀሙስ ለአርብ በሠርክ ፫ ፍጥረታት ተፈጥረዋል። እኒህም የሚከተሉት ናቸው፦ በዕለተ ኀሙስ ከውሃ....

- 1 እንስሳት
- 2 አራዊት
- 3 አዕዋፋት

በዕለተ ዓርብ ከየብስ....

- 4 እንስሳት
- 5 አዕዋፋት
- 6 አራዊት

የሁለቱ ልዩነት የኀሙሶቹ የተፈጠሩት ከውሃ ሲሆን ኀሙስ ለአርብ ሠርክ ላይ የተፈጠሩት ደግሞ ከየብስ የተፈጠሩ ናቸው። ብሔሞትን በየብስ ሌዋታንን በውሃ አስፈራቸው። ብሔሞትና ሌዋታን የሚባሉ ግሩማን (አስፈሪ) ፍጥረታት አሉ። እግዚአብሔር በቸርነቱ እልፍ አእላፋት ፍጥረታትን ምግብ እንዲሆኗቸው አድርጓል። እግዚአብሔር አራዊትን፣ እንስሳትን፣ አዕዋፋትን ሲፈጥር ሴትና ወንድ እያደረገ ፈጥሯቸዋል። የእነዚህ ፍጥረታት መልካቸውም ግብራቸውም ልዩ ልዩ ነው። በአንዱ ሀገር ያሉ በሌላ ሀገር የሌሉ ብርቅየ እንስሳት ይኖራሉ። ሰው በእውቀት ያልደረሰባቸው ብዙ የእንስሳት የአራዊት እና የአዕዋፋት ዝርያዎች ሁሉ ይኖራሉ። ለምግብነት የሚያገለግሉ አሉ። ቆዳቸው ለልብስ የሚሆኑ አሉ። ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ አሉ። ለብዙ ነገር ያገለግላሉ።

ሥነ ፍጥረት ክፍል 7

በዕለተ አርብ አዳም ተፈጠረ። 20ው ዓለማት የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፦

- 1 ብሔረ ብፁዓን
- 2 ባቢል
- 3 ብሔረ ሕያዋን

- 4 በርባሮስ
- 5 ገነት
- 6 የምንኖርባት ምድር
- 7 ምድርን የተሸከማት ነፋስ
- 8 ሐኖስ
- 9 ጠፈር
- 10 ውቅያኖስ
- 11 የምድር ምንጣፍ የሆነች ውሃ
- 12 ኢዮር
- 13 ራማ
- 14 ኤረር
- 15 ኢየሩሳሌም ሰማያዊት
- 16 ሰማይ ውዱድ
- 17 መንበረ ስብሐት
- 18 ጽርሐ አርያም
- 19 ምጽንዐተ ሰማይ
- 20 ገሀነመ እሳት

ኻያው ዓለማት የሚባሉት እነዚህ ናቸው። ገነት አሁን ላይ በዚህ ምድር መልካም ሥራ የሰሩ ሰዎች የሚገቡባት ጊዜያዊ ቦታ ናት። ከምጽአት በኋላ በገነት የነበሩ ቅዱሳን ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት (መንግሥተ ሰማያት) ይገባሉ። በዚያም ለዘላለም ይኖራሉ። በርባሮስ ወይም ሲኦል ደግሞ በዚህ ምድር ክፉ የሰሩ ሰዎች ጊዜያዊ መኖሪያ ናት። ከምጽአት በኋላ የተፈረደባቸው ኃጥዓን የሚኖሩት በገሀነም ነው። ገነትና ሲኦል የምድር አካል ስለሆኑ ሰማይና ምድር ሲያልፍ ያልፋሉ። ብሔረ ብጹዓን ደጋግ ሰዎች የሚኖሩበት በዚህ ምድር ያለ ነገር ግን ከዚህ ዓለም የተሰወረ ቦታ ነው። በዚያ ያሉ ሰዎች ያገባሉ፣ ይጋባሉ፣ 3 ልጅ ይወልዳሉ። አንዱ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ይሆናል። አንዲቱ እናቷን አገልጋይ ትሆናለች። አንዱ ደግሞ አባቱን የሚያገለግል ነው። ብሔረ ሕያዋን ደግሞ በዚህ ምድር የነበሩ እግዚአብሔርን በምግባራቸው ያስደሰቱ በዚህም ምክንያት ሞትን ያልቀመሱ ቅዱሳን ለምሳሌ እነ ሄኖክ፣ እነ ኤልያስ፣ እነ ዕዝራ እና ሌሎችም ቅዱሳን ያሉበት ቦታ ነው። ይህ ቦታም ምድር ሲያልፍ ያልፋል። እንስሳት

የሚባሉ ሳር ነጭተው ውሃ ተጎንጭተው የሚኖሩትን ነው። አራዊት የሚላቸው ደግሞ ሥጋ በልተው ደም ጠጥተው የሚኖሩትን ነው። አዕዋፋት የሚላቸው በክንፍ የሚበሩትን ነው።በልብ የሚሳቡ በክንፍ የሚሽከረከሩ ፍጥረታት የተፈጠሩት በእለተ ኀሙስ ነው።

ስለ እጮኝነትና ጋብቻ

ስለ እጮኝነት ክፍል 1

ብዙ ጊዜ በእጮኝነት ጊዜ ሴቷም ወንዱም ጻድቅ ጻድቅ ነው የሚጫወቱት። አቤት ቅድስና፣ አቤት ብፁዕነት፣ አቤት ፍጹምነት.... እረ እረ እረ.... ሁለቱም እንደ ፓለቲካ ፓርቲዎች ምርጫ ቅስቀሳ መልካም መልካም ነገራቸውን ብቻ ነው የሚያወሯት። [በእጮኝነቱ ጊዜ የሞተ ሰው ግን ይኮነን ይሆን!? ማለቴ አብዛኛው በዚያ ሰዓት ጻድቅ ነው የሚመስለው]። ነገር ግን የእጮኝነት ጊዜ እንዲህ መልካም መልካሙን ብቻ የሚያወሩበት ሳይሆን ያለባቸውን ችግሮችም አብረው እያወሩ ሲጋቡ እንዴት ሊፈቱት እንደሚችሉ እየተወያዩ መቆየት ይገባል። እጮኝነት እውነተኛ ማንነትን የሚያሳውቁበት ነው እንጂ ጻድቅ ሳይሆኑ ጻድቅ ጻድቅ የሚጫወቱበት አይደለም። በዋናነት እጮኝነት ያለባቸውን ጉድለቶች የሚተዋወቁበት ነው። ይህም በትዳር ጊዜ እነዚያን ጉድለቶች ለመሙላት የስነልቡና ዝግጅት ለማድረግ ይጠቅማል። እጮኝነት ምንድን ነው? ትዳርስ ምንድን ነው? እጮኝነት ለምን? ትዳርስ ለምን? የሚሉ ርእሰ ጉዳዮችን በዚህ ክፍል እንመልከት። መጀመሪያ እጮኝነት ማለት መጠባበቅ ማለት ነው። ይኽውም ከትዳር በፊት አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ለትዳር ከመብቃታቸው በፊት እርሷ የእርሱ እርሱ የእርሷ መሆኑን ተማምነው እስከ ሠርጋቸው እለት መጠበቅ ማለት ነው። ትዳር ወይም ጋብቻ ማለት ደግሞ ሁለቱ እጮኛሞች በቁርባን አማካኝነት አንድ የሚሆኑበት ምሥጢር ነው። ማቴ.19፥5 "ስለዚህ ሰው አባቱን እና እናቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል። ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ"። ይላል። ሁለቱ አንድ የሚሆኑት እንዴት ነው ከተባለ አንደኛ በመኻታ አንድ ይሆናሉ ማለት ነው። እርሷ ከእርሱ እርሱ ከእርሷ ውጭ ከማንም ጋር ግንኙነት እንዳያደርጉ ማለት ነው። ሁለተኛው አንድ ይሆናሉ የተባለው ልጅ በመውለድ ነው። ሚስቱ ሴት ብትወልድ ሴቷ የአንቺ ናት ወንዱ የእኔ ነው ብሎ መለየት የለም። ሴትም ሆነ ወንድ የሚወለደው ልጅ የሁለቱም ልጅ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ነው አንድ ይሆናሉ ያለው። ሌላው አንድ ይሆናሉ ያለው ሁለቱም በአንድ ሆነው ያፈሩት ንብረት ይህ የእኔ ይህ የእኔ ሳይባባሉ በአንድነት ይጠቀሙበታልና ነው። እንጂ አካላቸው ተጨፍልቆ አንድ ይሆናሉ ማለት አይደለም። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 እንደሚናገረው ጋብቻ ለምን ያስፈልጋል ከተባሉ አንደኛ ዘር ለመተካት ነው።ዘፍ.1፣28 ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ተብሏል። ልጆችም እግዚአብሔር ለወላጆች የሚሰጣቸው ስጦታዎችና በረከቶች ናቸው። ሁለተኛው ለመረዳዳት ነው። ዘፍ.2፣20። እርሱ ቢደክም አይዞህ ብላ አጽናንታ እንድታበረታው እሷ ብትደክም አይዞሽ ብሎ እንዲያበረታት ነው። ሦስተኛው ለአቅልሎ ፍትወተ ሥጋ ነው። አዳም ከገነት ከተባረረ በኋላ ፍትወታት እኩያት ሰልጥነውበታል። ስለዚህ የሰው ልጅ በገነት እያለ የፍትወት ስሜት አይሰማውም ነበር። ከገነት ከወጣ በኋላ ግን ፍትወት እንስሳዊት ሰልጥናበታለች። ከአሥሩ ሕግጋት አንዱ አታመንዝር ነው። ዘጸ.20፣14 ማመንዘር ማለትም በትዳር የአንተ ካልሆነች ሴት ጋር የፍትወት

መገለጫዎችን ማለትም መሳሳም፣ በስልክ ወይም በአካል ተገናኝቶ ዝሙት ቀስቃሽ ንግግሮችን መነጋገር፣ ዝሙት ቀስቃሽ አካላዊ ንክኪዎችን ማድረግ የመሳሰሉትን ማድረግ ነው። ይህም ትልቅ በደል ነው። እኒህን ነገሮች ከተጋባህ በኋላ ከሚስትህ ጋር ማድረግ ትችላለህ። ገና ካላገባሀት እጮኛህና ከሌላ ሴት ጋር ግን ማድረግ ፈጽሞ ኃጢኣት ነው። ከአሥሩ ትእዛዛት አንዱን ማፍረስ ይሆናል። ይህ በወንጌልም ጸንቷል። ማቴ.5፣28 "ወደሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል" ተብሏል። ከዚህ ላይ ሴት ተብላ የተገለጠችው ከሚስትህ ውጭ ያሉትን ሁሉ የሚያመለክት ቃል ነው።

ስለ እጮኝነት ክፍል ሁለት

ሌላው ወደ እጮኝነት ከመግባታችን በፊት ለእጮኝነት ያሰብናት ሴት/ወንድ ከአራቱ ዝምድናዎች ውስጥ የሌለች/ለ መሆኑን መረዳት አለብን። አራቱ ዝምድናዎች የተባሉም።

- መንፈሳዊ ዝምድና
- 2) የአሳዳጊ አባትና እናት ዘመዶች
- 3) የሥጋ ዝምድና
- 4) የጋብቻ ዝምድና

የምታጫት ሴት ወይም የምታጪው ወንድ ከእነዚህ ዝምድናዎች ውጭ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24ን ይመልከቱ። የሥጋ ዝምድና ማለት የእናትህ እና የአባትህ ዘመዶችን ሁሉ ማግባት አይገባም። ይህም ማለት አክስት፣ አጎት አያት ቅድመ አየት እያለ ይቀጥላል። ይህም ዝምድና እስከ ሰባት ትውልድ ቀጥሎ በስምንተኛው መጋባት ይቻላል። ይህም ማለት ለምሳሌ አንተ እስከ ሰባተኛ የልጅ ልጅ ብታይና ወንድምህም እስከ ሰባተኛ የልጅ ልጅ ቢያይ የመጨረሻው ሰባተኛው የልጅ ልጅህና የወንድምህ ሰባተኛው የልጅ ልጅ መጋባት አይችሉም። በስምንተኛው ግን መጋባት ይቻላል ማለት ነው። የሰባት ትውልድ አቆጣጠሩ

- 1 አንተ ወይም አንቺ
- 2 እናትህ ወይም አባትህ
- 3 የእናትህ እናት እና አባት

  የአባትህ እናት እና አባት
- 4 የእናትህ እናት አባትና እናት

  የእናትህ አባት እናትና አባት

  የአባትህ እናት አባትና እናት

  የአባትህ አባት እናትና አባት

- 5. የእናትህ እናት አባት እናትና አባት

  የእናትህ እናት እናት አባትና እናት

  የእናትህ አባት እናት አባትና እናት

  የእናትህ አባት አባት እናትና አባት

  የአባትህ እናት አባት እናትና አባት

  የአባትህ እናት እናት እናትና አባት

  የአባትህ አባት እናት አባትና እናት

  የአባትህ አባት አባት እናትና አባት

- 6 የእናትህ እናት አባት እናት አባትና እናት

  የእናትህ እናት አባት አባት እናትና አባት

  የእናትህ እናት እናት አባት እናትና አባት

  የእናትህ እናት እናት እናት አባትና እናት

  የእናትህ አባት እናት አባት እናትና አባት

  የእናትህ አባት እናት እናት አባትና እናት

  የእናትህ አባት አባት እናት አባትና እናት

  የእናትህ አባት አባት አባት እናትና አባት

  የአባትህ እናት አባት እናት አባትና እናት

  የአባትህ እናት አባት አባት እናትና አባት

  የአባትህ እናት እናት እናት አባትና እናት

  የአባትህ እናት እናት አባት እናትና አባት

  የአባትህ አባት እናት አባት እናትና አባት

  የአባትህ አባት እናት እናት አባትና እናት

  የአባትህ አባት አባት እናት አባትና እናት

  የአባትህ አባት አባት አባት እናትና አባት

ወንድ ከሆንክ የምታገባት ሴት፣ ሴት ከሆንሽ ደግሞ የምታገቢው ወንድ ትውልዳችሁ ሲቆጠር በሰባቱ ትውልዶች በየትኛውም አቅጣጫ ማለቴ በእናትህ እናት እናት፣ ወይም ባጭሩ ከላይ በጠቀስናቸው ዝርዝሮች ውስጥ እስከ ሰባት ባለው ተመሳሳይ አያት ሊኖራችሁ አይገባም። እህት ወንድም፣ አክስት አጎት ወዘተ በላይኛው ይቆጠራል። ለምሳሌ የአጎትህን ልጅ የማታገባበት ምክንያት ስትቆጠር አንድ አንተ አለህ። ከዚያ በሁለተኛ አባትህ ወይም እናትህ አሉ። ከዚያ በሦስተኛ የእናትህ እናትና አባት ወይም የአባትህ እናት እና አባት አሉ። በሦስተኛው አያታችሁ ስለምትገናኙ መጋባት አይቻልም። በእንደዚህ ዓይነት አቆጣጠር እስከ ሰባት ባለው በሆነ አያት ወይም ቅድመ አያት የምትገናኙ ከሆነ የሥጋ ዝምድና ስላላችሁ መተጫጨት መጋባት አይገባም። የክርስትና አባት ወይም እናት ዝምድና ያልነው ደግሞ መንፈሳዊ ዝምድና ይባላል። መንፈሳዊ ዝምድና የሚባለው ደግሞ አንተን ክርስትና ያነሳህ ሰውየ ሥጋዊ ዘመዶቹ ሁሉ በመንፈሳዊ ዝምድና የአንተ ዘመዶች ይሆናሉ። ስለዚህ የክርስትና አባትህን ዘመዶች በሙሉ ማግባት አይቻልም ማለት ነው። የአሳዳጊ እናት ወይም አባት ዝምድና የተባለው ደግሞ አሳዳጊህ እንደ አባት ወይም እናት ስለሆኑ የአሳዳጊህ ዘመዶች በሙሉ በሥጋ ባይዘመዱህ እንኳ ዘመዶችህ ይሆናሉና ከዚያ አትጋባ ማለት ነው። የጋብቻ ዝምድና የሚባለው ደግሞ አንተና ሚስትህ በዝሙት ምክንያት ብትፋቱ እና እንደገና ሌላ ሚስት ለማግባት ብትፈልግ በሦስቱም ዝምድናዎች በኩል የሚስትህ ዘመድ ያልሆነች መሆን አለባት ማለት ነው። በንሥሓ አባት አንድ የሆኑ ልጆችን ከላይ በጠቀስናቸው ዝምድናዎች ካልተዛመዱ በስተቀር መጋባት ይችላሉ። ይህ በሐዲስ ኪዳን በፍትሐ ነገሥት የቀረበው ዝምድና ነው። የመንፈሳዊ ዝምድና እስከም የለው ብዙ ነው ካለ በኋላ አንድም እንደሥጋዊው ዝምድና እስከ ሰባት ነው ተብሎ ታትቷል። ይህም ቤተክርስቲያን ሰውን ለማዛመድ የሄደችበት ርቀት እጹብ እጹብ ብለን እንድናደንቅ ያደርገናል።

ስለ እጮኝነት ክፍል 3

የእንጀራ እናትህን/አባትህን ልጅ ምንም እንኳ በእናትም በአባትም ባትገናኙም ማግባት አትችልም። ምክንያቱም የጋብቻ ዝምድና ይፈርሳልና ነው። በእጮኝነት ጊዜ ሌላው ትልቁ ጉዳይ የእድሜ ጉዳይ ነው። ፍትሐ ነገሥት ሴት 12/15 ዓመት ሳይሞላት ወንድ 18/22 ዓመት ሳይሞላው ማግባት አይገባውም ይላል። እጮኛ ልያዝ ቢል እንኳ እድሜው ከዚህ ዓመት በታች ከሆነ በቤተሰቡ ፈቃድ እንጂ እርሱ ራሱ መርጦ ማጨት አይችልም። ነገር ግን ይላል ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ሴቲቱ በምኞት አድጋ በአካል የጠነከረች ከሆነ ቢያንስ በ12 ዓመቷ ታግባ ይላል። ከዚያ በታች ግን ማግባትም ማጋባትም አይቻልም። ወንዱም በምኞት ያደገ በአካል የጠነከረ ከሆነ በ18 ዓመቱ ማግባት ይችላል። ከዚያ በታች ግን አይቻልም። ወንዱ ወይም ሴቷ በቤተሰብ ሥር የሚተዳደሩ ከሆነ በቤተሰብ ፈቃድ ያጫሉ። ነገር ግን ራሳቸውን የቻሉ በአካል የጠነከሩ ከሆኑና በኑሮም በቤተሰቦቻቸው ጥገኛ ያልሆኑ ከሆነ ራሳቸው መርጠው ራሳቸው አጭተው ሽማግሌ አስልከው መጋባት ይችላሉ። የእድሜ ጉዳይ መነሻውን ተናገርኩ እንጂ ከዚያ በላይ ከሆኑ ፈቅደው ተፈቃቅደው መጋባት ይችላሉ። በእድሜ ወንዱ ሊበልጥ ይችላል። ሴቷም ልትበልጥ ትችላለች። ነገር ግን እድሜያቸው ተቀራራቢ ቢሆን ይመረጣል። ይኽውም መረዳዳት የሚለውን በሀሳብም ለመረዳዳት የእድሜ መቀራረብ አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

ዙሮ ዙሮ ግን በፍትሐ ነገሥቱ እንደምናየው የሴቷ አነስ ቢል የተሻለ ነው። ሴት 65 ዓመት ከሆናት በኋላ ማግባት አይገባትም። ሌላው በእጮኝነት ጊዜ ወደፊት ምን ሠርተው እንዴት ሠርተው ራሳቸውን እንደሚያኖሩ ማሰብ መወያየት ይገባል። ሌላው ነገር ደግሞ ለእጮኝነት ለመጠየቅ ሴትም ወንድን መጠየቅ ትችላለች። ወንድም ሴትን መጠየቅ ይችላል። ነገር ግን ከተጠያየቁ በኋላ ሽማግሌ ወደ ቤተሰብ የሚልክ ወንዱ ነው። ወንዱ ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ነው እንጂ ሴት ወደ ወንድ ቤተሰብ ሽማግሌ ልካ "ላገባው ነው" ማለት አይገባትም። ከእጮኝነት በኋላ ጥሎሽ ወይም ማጫ የሚሰጥ ደግሞ ወንድ ነው። ይኽውም ለአዳም መላእክት ወርቅ እጣን እና ከርቤ አምጥተው ሰጥተውታል። አዳምም ለሔዋን ማጫ አድርጎ ሰጥቷታልና የዚያ ምሳሌ ነው። የልጆቻችንን ከርስ ብቻ የምንሞላ ከሆንን እያሳደግን ያለነው ሮሆቦት እንጂ ሰው አይደለም። ከሮሆቦት የተሻሉ ልጆችን ማሳደግ ከፈለግን የተፈጠሩበትን ዓላማ እንዲያውቁ በስነልቡና ጠንካራ እንዲሆኑ በስነ ምግባር የታነጹ ልጆች እንዲኖሩን ከፈለግን ከልጅነታቸው ጀምረን ነገረ እግዚአብሔርን ሃይማኖትን ልናሳውቃቸው ይገባል። እኛ ሆዳቸውን ልብሳቸውን ብቻ እየቻልን አእምሯቸውን ግን በሌላ ሰው ሌላ ትምህርት ካስያዝነው እንደ ስልክ እኛ ቻርጅ እናደርጋለን ሶፍት ዌሩን ሌላ ባዕድ ይሞላዋል ማለት ነው። ሲጀምር ቤተ ክርስቲያን አንድን ልጅ አንዱ ክርስትና እንዲያነሳው ሥርዐት የሠራች የሃይማኖትን ትምህርት ጠንቅቆ እንዲያስተምረው ነው። አሁን አሁን ግን ይህ የለም። ነገር ግን የትዳር ዋናው ዓላማ የእግዚአብሔርን አምሳል የሆነ ልጅን ማስገኘት ነው። ስለዚህ ልጆቻችን በመሰረታዊነት ከምግበ ሥጋም ከልብሰ ሥጋም በተጨማሪ የሚያስፈልጋቸው ምግበ ነፍስ ነው። ስለዚህ በልጅነታቸው ቤተ ክርስቲያን እየወሰድን እናቆርባቸዋለን አበ እመ ማለት ሲጀምሩ ደግሞ በቃለ እግዚአብሔር አፋቸውን እናስፈታቸዋለን። እንግዲህ በትዳር አማካኝነት ባልና ሚስት የእግዚአብሔር አምሳል የተባለውን ሰው ያስገኛሉ። ይህም ትልቅ በረከት ነው። 1ኛ ዮሐ.2፣13 "...ልጆች ሆይ አብን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ" ተብሏል። ሃይማኖትን ማሳወቅ ይገባል።

ስለ እጮኝነት ክፍል 4

ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ሀብታም ወንድ ድሃ ሴትን አላገባም አይበል፣ ሀብታም ሴትም ድሃ ወንድን አላገባም አትበል። ባዕል መለኮት ነዳይ ሥጋን ተዋሕዷልና። ልዑል መለኮት ትሑት ሥጋን ተዋሕዷልና። እንዲያውም ሀብታሙ ወንድ ድሃይቱን ሴት ቢያገባ ሀብታሚቱም ሴት ድሃውን ወንድ ብታገባ ትልቅ ክብር ያገኛሉ። የእጮኝነት መሠረቱ ጸታዊ ፍቅር ነው። ይህም በመፈላለግ ይገለጣል። በአንድ ወንድ እና በአንድ ሴት መካከል የመፈላለግ ስሜት ካለ ሁለቱ ለእጮኝነት መጠያየቅ ይችላሉ። ነገር ግን ፍላጎቱ የአንዱ አካል ብቻ ከሆነ እና አንደኛው የማይፈልግ ከሆነ የፈለግሁትን ካላገኘሁ ሞቼ እገኛለሁ ብሎ ማስቸገር አይገባም። ጠይቆ እምቢ ከተባለ ያው ኃፍረቱን ተከናንቦ ሌላ ይፈልግና ይጠይቅ። ምንስ ቢሆን እርሱ እየወደዳት እርሷ ባትወደው ወይም እርሷ እየወደደችው እርሱ ባይወዳት ከማትወደው ከማይወዳት ሰው ጋር ለምን ለመኖር ይመኛል። አገባብስ እርሷም እርሱም ተዋደው ሲጋቡ ነው። አንድ ጊዜ አንዱ ጓደኛየ አንዷን ልጅ ፈለገና ሂዶ ጠየቃት ከዚያ እምቢ አለችው። ከዚያ ወረብ ሲያጠና "ንዲጎ ብእሲቶ (ሚስቱን ትቶ)" የሚለውን ወረብ ደጋግሞ ይወርብ ጀመር። መምህራችን ልጅቱ እምቢ እንዳለችው ሰምተው ኖሯል። በቃ እሱኛውን ወረብ በትክክል ብለኽዋል ወደቀጣዩ እለፍ

አሉት። አንድን ወረብ አጥንተህ በደንብ ከያዝከው ከዚያ ቀጣዩን ወረብ ታጠናለህ። የየኔታ ንግግር በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ነው። የመጀመሪያው ወረቡን ብለኽዋል ወደ ቀጣዩ እለፍ ማለታቸው ነው፡ ሁለተኛው ደግሞ በቃ የመጀመሪያ ጥያቄህን ያቀረብክላት ልጅ እምቢ ካለች ወደቀጣዩ እለፍ ማለት እርሷን ትተህ ሌላ ፈልግ ማለታቸው ነበር። ሀብታም ወንድ ሀብታሟን ሴት ድሃ ወንድ ድሃዋን ሴትም ማግባትም ይችላል። ሌላው በእጮኝነት ጊዜ በሐሳብ ያለመስማማት ነገር ካለ ቢለያዩ ኃጢኣት አይሆንም። ከተጋቡ በኋላ ግን መለያየት አይቻልም። የእጮኝነት ጊዜ ለየብቻቸው ነው መኖር ያለባቸው። እጮኛሞች እስካልተጋቡ ድረስ በአንድ ላይ መተኛት በአንድ ላይ ማደር አይገባቸውም።

ስለ እጮኝነት ክፍል 5

አንድ ወንድ አንዲት ሴትን ለማግባት ወይም አንድ ሴት አንድን ወንድ ለማግባት የግድ አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች አሉ። ከእነዚህም አንዱና ዋናው ሃይማኖት ነው። ሴቶች በሃይማኖት የማይመስላችሁን ወንድ አታግቡ። ወንዶችም እንዲሁ በሃይማኖት የማትመስላችሁን ሴት አታግቡ። ታድያ እንዲህ ከሆነ ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ.7፣14 "ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሷል። ያላመነችም ሚስት በባሏ ተቀድሳለች" ይላልሳ ምን ማለት ነው? ካልከኝ። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የተነገረበትን ምክንያት ማወቅ ሀሳቡን በትክክል እንድንረዳው ያደርገናል። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ያለው አሕዛብን አስተምሮ ወደ ክርስትና ሲመልስ ሚስት ክርስቲያን ትሆንና ባል ሳይሆን ይቀራል። ባል ክርስቲያን ይሆንና ሚስት ሳትሆን ትቀራለች። በዚህ ምክንያት ጠብ እንዳይነሳ ባል ክርስቲያን ከሆነ በጊዜ ሂደት አስተምሮ ክርስቲያን ያደርጋታል በማለት ይህንን ተናገረ። ይህንንም የሚያስረዳን ቁጥር 13 ላይ "ሴቲቱም የማያምንና ሚስቲቱን የሚያፈቅር ከእርሷም ጋር ሊኖር የሚወድ ባል ቢኖራት ባሏን አትፍታ" ይላል። የሚያፈቅራት ብሎ የገለጠው የሚወዳት ከሆነ ለእርሷ ሲል ትንሽ ቆይቶ እንደ እርሷ ሃይማኖት ይሆናልና እንዲህ አለ። ነገር ግን ተምሮም ተነግሮም ወደ ትክክለኛዋ ሃይማኖት ካልመጣ ልትፈታው እንደሚገባ ቅዱስ ጳውሎስ ከዚሁ ምእራፍ ቁጥር 15 ላይ "የማያምን ግን ቢፈታ ይፍታ" ብሎ ነግሮናል። ይህንን መነሻ አድርገው 318ቱ ቅዱሳን ሊቃውንት ደግሞ በፍትሐ ነገሥታቸው ክርስቲያን ክርስቲያንን ብቻ እንዲያገባ ሥርዐት ሠርተዋል። ስለዚህ አሁን ላይ አስተምረህ ወደ ሃይማኖት ከመለስክ በኋላ አጭተህ ማግባት ትችላለህ እንጂ ገና ወደ ትክክለኛዋ ሃይማኖት ሳትመጣ እያለች እርሷን አግብቼ ወደ እኔ ሃይማኖት እመልሳታለሁ ግን አትበል። ሥለዚህ ባልና ሚስት በሃይማኖት አንድ የሆኑ መሆን አለባቸው። በሃይማኖት አንድ ሆነው ከተጋቡ በኋላ ከሁለት አንዱ ሃይማኖቱን ቢቀይርሳ እንዴት ይሆናል የሚል ጥያቄ ከጠየቅከኝ ደግሞ መልሱ "ይፋቱ" ነው። ምክንያቱም በወንጌል ማቴ.10፣37 "ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም። ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" ይላልና ነው። ከዚህ ጥቅስ በታች ቁጥር 34 ላይ "ሰይፍን እንጂ ሰላም ለማምጣት አልመጣሁም" ብሏል። የዚህ ትርጉሙ በሃይማኖት ምክንያት እናትና አባት ባልና ሚስት ወላጅና ልጅ ቢለያዩ የሚገባ መለያየት መሆኑን ነው። ሰይፍ የተባለውም ይህ ነው። ከዚህ ላይ "ሰላም" ለማምጣት አልመጣሁም ያለው "አንተም በሃይማኖትህ አንቺም በሃይማኖትሽ ተባብለው በአንድ

ተስማምቶ መኖርን ነው ሰላም ያለው"። ይህ ሰላም ክርስቲያናዊ ሰላም አይደለም። ክርስቲያናዊው ሰላም ከክርስቶስ ጋር በመኖር በክርስቶሳዊ ሕይወት በመኖር የሚመጣ ሰላም ነው። ይህኛውን ሰላም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ.14፣27 "ሰላሜን እሰጣችኋለሁ" ብሎናል። ስለዚህ በሃይማኖት የማይመስለንን ሰው ማጨት ማግባት አይገባም። ከተጋባን በኋላ ሃይማኖቱን ቢለውጥ እንኳ መፋታት ይገባል ማለት ነው።

ስለ እጮኝነት/ትዳር ክፍል 6

ጋብቻ በሁለት መንገድ ይፈጸማል። አንደኛው ሁለቱም ክብረ ንጽሕናቸውን ጠብቀው ድንግልናቸውን ጠብቀው የሚጋቡ ከሆነ በተክሊል ይጋባሉ። እዚህ ላይ አጥብቀህ ያዝልኝማ ወንድማለም። አሁን አሁን ብዙ እጮኛሞች ከዚህ ቀደም ከሌላ ሳይገናኙ ነገር ግን እርስ በራሳቸው በእጮኝነት ጊዜያቸው ግንኙነት ይፈጽሙና በተክሊል ካልተጋባን ይላሉ። ይህ ፈጽሞ ስህተት ነው። ምናልባት በትምህርት ማጠር ምክንያት አንዳንድ ካህናት ይህንን ብለዋችሁ ከሆነም ከመምህራን ጋር አገናኟቸው። ተክሊል ጋብቻ እስከ ተፈጸመበት ጊዜ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለቆዩ ብቻ ነው የሚደረገው። ይኽውም የክብራቸው መገለጫ ነው። እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን ሌላው ነገር ምናልባት በሥራ ብዛት ወይም በሕክምና (ለምሳሌ ድንግልናን ሊያስፈርስ የሚችል ልዩ ኦፕሬሽን የሚደረግ በሽታ) ምክንያት ከወንድ ጋር ሳይገናኙ እንዲሁ ድንግልናቸው የጠፋ ሴቶች ካሉ በተክሊል መጋባት ይችላሉ። ተክሊልን ፍጹም የሚያደርገው ቁርባን ነው። ሁለተኛው የጋብቻ አፈጻጸም ደግሞ ተጋቢዎቹ ሥጋዊ ፈቃድ አሸንፏቸው ወይም በተለያየ ምክንያት ድንግልናቸውን አጥተው የነበሩ ከሆኑ በጸሎተ መዓስባን በቁርባን ይጋባሉ። ነገር ግን ከሁለት አንዳቸው ድንግል አንደኛው ደግሞ ድንግል ያልሆነ ከሆነ። ድንግል ለሆነው ተክሊል ይደረግለታል። ድንግል ያልሆነው ደግሞ ያለ ተክሊል ይጋባሉ። ስለዚህ በድፍረት ተክሊል ባናደርግ መልካም ነው። ይህንን የምታደርጉ ካህናት ካላችሁም ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን እያፈረሳችሁ ነውና አምላከ ሥርዐት እግዚአብሔርን ፍሩ። በጾም ወቅት ጋብቻ አይፈቀድም። ጋብቻ ያለ ሥጋው ወደሙ አይሆንም። ያለ ቁርባን የተደረገ ጋብቻ ቁጥሩ ከዝሙት ነው ብለዋል ሊቃውንት በሐተታቸው። ስለዚህ በሐገራችን በተለያዩ ተጽእኖዎች ምክንያት ያለ ቁርባን የሚጋባው ሰው ብዙ ስለሆነ ይህንን ግንዛቤ በመስጠት ካህናት የድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል። ያለቁርባን የሚደረግ ጋብቻ ቁጥሩ ከዝሙት ነው።በዚህ ዙሪያ ያው አሁን በሀገራችን በገጠሪቱ አካባቢ ባለማወቅ እና በግራኝ መሐመድ ተጽእኖ አብዛኛው ሰው ዝም ብሎ ያለ ቁርባን የተጋባ ነው። እንግዲህ ይህ ባለማወቅ የሆነ ስለሆነ ባለፈው ፈጣሪ ይቅር ይለን ይሆናል የሚል ግላዊ ምልከታ አለኝ። ከአሁን በኋላ የሚደረጉ ሰርጎችን ግን ይህንን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተን ሁሉም በቁርባን በተክሊል እንዲጋባ የተቻለንን እናድርግ። ባለፈው ይቅር ይበለን። ለወደፊቱ ደግሞ ይጠብቀን።

ስለ እጮኝነት/ትዳር ክፍል 7

ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ ፍቺ የሚፈቀድባቸው ምክንያቶች፦

- በዝሙት ምክንያት

- 2) በሃይማኖት ምክንያት
- 3) ባሏን/ሚስቱን ልታስገድለው/ሊያስገድላት በበቂ መረጃ ከተደረሰባት/ከተደረሰበት ናቸው።

አንድ ወንድ ሚስቱን ከሌላ ወንድ ጋር ግንኙነት እየፈጸመች ተኝታ ቢያገኛት መፍታት ይችላል። ተናዶ በእርሷ እና ከእርሷ ጋር ተኝቶ ባገኘው ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ የለበትም። በሃይማኖት ምክንያት የሚለውን ከዚህ ቀደም አይተናል። ከላይ ባሉት ሦስት ምክንያቶች ከሚስቱ የተፋታ ካህን ቢሆን ሌላ ሳያገባ ቢቀጥል ክህነቱ ይቀጥላል። ነገር ግን ሌላ ካገባ ወይም በዝሙት ምክንያት ሚስቱን ካገኛት በኋላ አብሯት የሚኖር ከሆነ ክህነቱ ይሻራል። ካህን በማንኛውም ምክንያት ሁለተኛ ካገባ ከክህነቱ ይሻራል። ክህነቱን አፍርሶ እንደገና ያገባት ሴት ብትሞትበት ግን ሦስተኛ እንዲያገባ አይፈቀድም። ካገባም እንደ አረሚ ይሁን ተብሎ ተነግሮበታል። ምእመን ሚስቱ ብትሞት ሌላ ያገባል። ያች ያገባት ብትሞትም እንደገና ቢያገባ ይፈቀድለታል። አራተኛ ግን ማግባት አይችልም። የምእመን አራተኛ የካህን ሦስተኛ እንደ አረሚ ይሁኑ ተብለዋልና። እስከዛሬ ባለማወቅ አድርገነው ከሆነ ለወደፊቱ እንጠበቅ። ከላይ ከተቀመጡት ምክንያቶች ውጪ ግን ማለትም ያለዝሙት ምክንያት፤ ሃይማኖት ሳይለውጡ፣ በማስገደል ሂደት ካልተገኙ በሌላ ምክንያት መፋታት አይቻልም። ጸባዩዋ ከፋ፣ ሰነፈች፣ ውበቷ ጠፋ፣ አረጀች፣ ወዘተ ብሎ መፍታት አይቻልም። እስከ እለተ ሞትህ ልትጠብቃት ይገባል እንጂ። ከላይ ካሉት ከሦስቱ ምክንያት ውጭ ሚስትህ ብትበድልህ እንኳ ያንን ታጋሽ ሆነህ አረጋግተህ በፍቅር ልትኖሩ ይገባል። የሚደርስብህን በደል ሁሉ ችለህ ኑር። ሴቷም ከላይ ካሉት ምክንያቶች ውጪ ከሆነ የሚደርስባትን በደል ሁሉ ታግሣ ትኑር። በሆነ አጋጣሚ ሚስት ወይም ባል የአካል ጉዳተኛ ቢሆኑ እንኳ እስከ መጨረሻው በፍቅር ሊኖሩ ይገባል እንጂ በዚህ ምክንያት መፋታት አይገባም።

ስለ እጮኝነት/ትዳር ክፍል 8

ከጋብቻ በኋላ ባልና ሚስት ሩካቤ ሥጋ በማይደረግባቸው እለታት ግንኙነት ማድረግ አይገባቸውም። ግንኙነት የማይፈቀድባቸው እለታትም፦

- በወር አበባዋ ወቅት
- ከወለደች ጀምሮ እስከ ክርስትና
- በእርግዝናዋ ወቅት።
- ከሁለት አንዳቸው ከቆረበ ከመቁረቡ በፊት ባሉት 3 ቀናት እና ከቆረበ በኋላ ባሉት 2 ቀናትም ግንኙነት ማድረግ አይገባም።
- በአጽዋማትና በዐበይት በዓላት ጊዜ።

ከእነዚህ እለታት ውጪ ግን ሚስት ወይም ባል ግንኙነት ማድረግ ፈልገው አንዱ እምቢ ማለት የለበትም። የእርሱ አካል የእርሷ የእርሷ አካል የእርሱ ሆኗልና። ፈቃዱን ወይም

ፈቃዷን ይፈጽምላት/ ትፈጽምለት እንጂ። ሌላው ቀርቶ ንሥሓ አባት ቀኖና ቢሰጥ እንኳ ሚስት ባልን ባል ሚስትን አሳውቆ መሆን አለበት። ሚስት ወይም ባል ንሥሓ ላይ እንዳሉ ከታወቀ ግን ንሥሓሃቸውን እስኪጨርሱ ከግንኙነት ይከልከሉ። ከዚያ ውጭ ግን መከልከል የለባቸውም። ወንዱ ግንኙነት ማድረግ ፈልጎ ሴቷ እምቢ ብትለው እና ሴቷ ግንኙነት ማድረግ ፈልጋ ወንዱ እምቢ ቢላት እናም በዚህ ምክንያት ፍትወት አናዶት ወንዱ ከሌላ ሴት ሴቷ ከሌላ ወንድ ብትደርስ በደሉ የጋራ ነው። የእሱ በደል የእሷ የእሷ በደል የእርሱ ይሆናል። ባልና ሚስት ግልጽ መሆን አለባቸው። ፈቃዳቸውን በግልጽ ሊነጋገሩ ይገባል። ሚስት አካሏን ሳይቀር ለባሏ ከሰጠች ባልም አካሉን ሳይቀር ለሚስቱ ከሰጠ ከዚህ የበለጠ ምሥጢር ምን አለ? ምንም። ስለዚህ ያለመጣጣምና ያለመስማማት ነገሮች ካሉ በግልጽ ሊነጋገሩ ይገባል። ብዙ ሴቶች በሕገ ወጥነት መንገድ ከሌላ ወንድ ይጸንሱና መጽነሳቸውን ወላጆቻቸው ወይም ይህን ጉዳይ የሚፈሩት ሰው እንዳያውቅ ብለው በማሰብ ጽንሳቸውን በድብቅ ያስወርዱታል። ይህ ግን ሁለት ታላላቅ በደሎችን የያዘ ነው። አንደኛው ባሏ ካልሆነ ሰው ጋር በመገናኘቷ ከአሥሩ ትእዛዛት አንዱ የሆነውን ዘጸ.20፣14 "አታመንዝር" የሚለውን ሕግ ማፍረስ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ዘጸ.20፣13 ያለውን "አትግደል" ያለውን ሕግ መተላለፍ ነው። ስለዚህ ከሌላ ወንድ ጋር ባትገናኙ መልካም ነበረ። ነገር ግን ደግሞ ሥጋዊ ፈቃድ አሸንፏችሁ ግንኙነት አድርጋችሁ ልጅ ቢጸነስ አታስወርዱት ይወለድ። ወላጅ ሰምቶ ያዝናል ብለን እግዚአብሔርን መበደል አይገባምና። ወላጅም ይሁን ወዳጅ ለጊዜው ሊያዝን ቢችልም። ልጁ ተወልዶ አበ እመ ማለት ሲጀምር ግን ኀዘናቸው ይቀንሳል። ሌሎች ደግሞ ግንኙነቱን ፈልገው ግን እንዳይጸንሱ በማለት የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚጠቀሙ አሉ። ይህም ትልቅ ስህተት ነው። ማሕጸን የተፈጠረው ለጽንስ ነው ። ስለዚህ ግንኙነትን መርጦ ልጅ እንዳይወለድ መፈለግ ብዙ ተባዙ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል ችል ማለት ነው። ምናልባት ጸንሰን ወላጆቻችን መጽነሳችንን ሲያውቁ እንዳይቆጡን እንዳያዝኑብን ብለን አስበን ከሆነም ከእግዚአብሔር ሕግ ይልቅ የእናትና የአባትህ ቁጣ የሚያስፈራህ ጣዖት አምላኪ መሆንህን ያሳውቃል። ክልክሉኮ ካላገቡት ሰው ጋር ግኑኝነት ማድረጉ ላይ ነው እንጂ መጽነሱ ላይ አይደለም። መጠበቅ ያለበት መሠረታዊው ሕግ "አታመንዝር" የሚለው ነው። አታመንዝርን ተላልፈሽ መጽነስሽ ለምን ያሳስብሻል። ሁለት በደል መበደል አይገባም። መጀመሪያ ካላገቡት ሰው ጋር ግንኙነት ማድረግ አይገባም። ሁለተኛ ሥጋዊ ፈቃድ አሸንፎሽ ብትሰናከዩ እንኳ የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቅመሽ ሁለተኛ በደል አትበድይ።አንድ ጊዜ የፊለገ ሊቃውንት ደብረ ድማህ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የሐዲሳትና የፍትሐነገሥት መምህር የነበሩት የኔታ ወልደ ኢየሱስ መቅጫ "ልጃችንን ወልደነው ምን እናበለዋለን ብላችሁ በመፍራት ገና ከጽንሱ የምታስወርዱ ሰዎች ይህንን ክፉ ሥራ አትሥሩ። ተውት ልጁን ውለዱትና እግዚአብሔር ከገደለው ይግደለው እንጂ እናንተ አታስወርዱ ያሉት ቃል ድንቅ ቃል ነው። ደግሞስ ጽንስን የምናስወርድ ለምንድን ነው? መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በኤልሳቤጥ ማሕጸን እያለ እኮ ነው ጌታን ያመሰገነው። ዮሐንስ ትዝ አይላችሁም እንዴ? ስለዚህ ጽንስን ማስወረድ አይገባም። የተጸነሰው በስርቆት ከሌላ ወንድም ቢሆን መጀመሪያ ትልቅ በደል በድላችኋል። ስለዚህ ሁለተኛ ታላቅ በደል ጽንስን በማስወረድ አትበድሉ።

ስለ እጮኝነት/ትዳር ክፍል 9

ባል ከሚስቱ ጋር ብገናኝ ብሎ ወይም ሚስት ከባሌ ጋር ብገናኝ ምን ችግር አለው ብለው በአደባባይ በሰው መካከል ግንኙነት ማድረግ አይፈቀድም። በአደባባይ ግንኙነት ቢደረግ ያንን ያየ ሰው በልቡ እንዲመኝ እና አታመንዝር ያለውን ሕግ እንዲሸር ስለሚያደርገው በዚህም ምክንያት እንዳይኮነንብን ነው። ባልና ሚስት የባልና የሚስት ወሬዎችን ማውራት ካለባቸውም እንኳ ልጆቻቸውም ቤተሰቦቻቸውም ጎረቤትም ሳይሰማ መሆን አለበት። ይኽውም ለሚሰማውና ለሚያየው አካል ፈተና እንዳይሆን ነው። በየአደባባዩ መሳሳም እና ፍትወት ቀስቃሽ ድርጊቶችን ማድረግ ግን አንደኛ ባልንጀራን መናቅ ነው። ሌላው በዚያ አካባቢ ያለ ሰው እናንተን ተመልክቶ እንደሚስት አስቡ። ሌላውን ሰው ፈተና ውስጥ የሚያስገባ ራቁትን የሚያሳይ ልብስ ወይም አካልን ጥብቅ አድርጎ በማሳየት የሰውነትን ቅርጽ የሚያሳይ ልብስ መልበስም የርካሽነት ሥራ ነው። የሰው ልጅ ክቡር ነው። ለዝሙት አልተፈጠረም። ዝሙትኮ የሚያኮራ ነገር አይደለም። እንስሳትም የሚያደርጉት ነገር ነው። ከእንስሳት ጋር የሚያመሳስለን ነገር ነው። እና ቢያንስ ከእንስሳት የተሻለ አኳኋን ይኑረን እንጂ። ወይፈንኮ ያረገዘች ላም ካየ አሽቶ ይመለሳል እንጂ አይሰቀልም። ሰው ግን ከወይፈንም አንሶ በእርግዝና ወቅት እንኳ ግንኙነት ካላደረግን ማለት አግባብ አይደለም። ሰው ከዝሙት ውጭ እንዳያስብ እያደረጉ ያሉት ደግሞ ጭፈራ ቤቶች፣ መጠጥ ቤቶች ናቸው። የትውልዱን አስተሳሰብ እያበላሹ ያሉት ደግሞ እኒህ ናቸው። ከእነዚህም በተጨማሪ አሁን አሁን በቴሌቭዥን መስኮት የሚታዩ ድራማዎች፣ ፊልሞች ትውልድ አምካኝ ጅል ትውልድ የሚያፈሩ ናቸው። የሰው ልጅ በፍትወት እንዳይናደድ ከፈለገ አግብቶ ይወሰን። ከዚያ ውጭ ከዚያም ከዚያም መድረስ የመኖርን ዓላማ ካለመገንዘብ የሚመጣ ደዌ ነው። ሌላው ትዳር ፈተና አለበት ይህንን ማወቅ ያስፈልጋል። ትዳር ሀብት ሲጠፋ ውበት ሲረግፍ የሚተውት አይደለም። አብርሃም እና ሣራ ከሀገር ሀገር ሲሰደዱ ኖረዋል። ስደት ቢመጣ፣ ሀብት ማጣት ቢመጣ፣ አካላዊ ጉዳት ቢመጣ እንኳ እስከ መጨረሻው አብሮ በፍቅር መኖር ያስፈልጋል። ሌላው ግን ምራትና አማት አይጥና ድመት ወይም ዓይንና አፈር መሆን የለባቸውም። ብዙ ጊዜ አይስማሙም ለምን እንደሆነ እኔ እንጃ። ነገር ግን ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይሆናል የተባለው ፍትወት ቢነሳበት ወንዱ ከእናቱ ሴቷ ከአባቷ ጋር ግንኙነት ማድረግ አይገባትም ማለት ነው እንጂ ሚስትየዋ የባሏን እናትና አባት ትጥላ ባልዮው የሚስቱን እናትና አባት ይጥላ ማለት አይደለም። ዘጸ.20 እናትና አባትህን አክብር የተባለው እስከመጨረሻው ነው። ምራትና አማትስ መሆን ያለባቸው እንደ ኑኃሚን እና እንደ ሩት ነው። መጽሐፈ ሩትን ከምዕራፍ አንድ ጀምራችሁ ተመልከቱትማ። ሩት ባሏ ሞቶ እንኳ አማቷን ኑኃሚንን አልተወቻትም። እንዲያውም "አምላክሽ አምላኬ ነው። ሀገርሽ ሀገሬ ነው" ብላ ተወልዳ ያደገችበትን ሀገር ትታ ከአማቷ ጋር ተሰዳለች። ጋብቻ መዛመድ ስለሆነ ሴቲቱ የወንዱን ወገኖች ወንዱ የሴቲቱን ወገኖች መውደድና ማክበር አለበት። ሴቲቱ የባሏን እናትና አባት ራሷን ዝቅ አድርጋ በትሕትና ልታገለግላቸው ልትታዘዛቸው ይገባል። ወንዱም ለሚስቱ አባትና እናት ክብር ሊሰጣቸው ይገባል።ባልና ሚስት አንዱ አንዱን ማስቀናት የለበትም። በፍጹም መከባበር፣ በፍጹም ፍቅር፣ በፍጹም መተማመን ሊኖሩ ይገባል። በባልና በሚስት ማንም ጣልቃ ሊገባ አይገባም። በቤተሰቦቿ/ቹ ወይም በጓደኞቿ/ቹ ተጽእኖ ሚስት ባሏን ልትፈታ ባል ሚስቱን ሊፈታ አይገባም።ባል ወይም ሚስት ልመንኩስ ቢሉ ከተፈቃቀዱ

መመንኮስ ይችላሉ። ባሏ ከፈቀደላት ሚስትየዋ መመንኮስ ትችላለች። ሚስቱ ከፈቀደችለት ባልየው መመንኮስ ይችላል። ሚስት ባሏ ሳይፈቅድላት ወይም ባል ሚስቱ ሳትፈቅድለት ግን ልመንኩስ ቢል መመንኮስ አይችልም። ከዚህ ላይ አጥብቀህ ያዝልኝማ አሁን አሁን አንዳንድ ባሕታውያን ነን ባዮች ባልና ሚስትን እያፋቱ ካላመነኮስን ይላሉ። ይህ ትልቅ ስህተት ነው። ያለ ባሏ ፈቃድ የመነኮሰች ሴት ካለች ከመነኮሰችበት አምጥቶ ከቤቱ ቢወስዳት ምንም ነውር የለበትም። ሚስቱ እንድትመነኩስ ከፈቀደላት በኋላ እሷም ከመነኮሰች በኋላ ሐሳቡን ቀይሮ እንደገና ምንኩስናዋን እንድትተው ቢፈልግ ግን አይቻልም።

ስለ እጮኝነት/ትዳር ክፍል 10

ፈጣሪ የፍትወት ስሜት እንደሚሰማን እያወቀ ለምን አታመንዝሩ ይለናል? የሚል ጥያቄ ይጠየቃል። ለመሆኑ የሰው ልጅ እድሜው ለአካለ መጠን ሲደርስ የፍትወት ስሜት ይሰማዋልና ይህ ተፈጥሯዊ ነው ወይ? ከሆነ እግዚአብሔር ተፈጥሯዊ የሆነን ነገር ተውት ለምን ይለናል? የሚል ጥያቄ ይጠየቃል። ነገር ግን የፍትወት ስሜት ተፈጥሯዊ አይደለም። አዳም ሲፈጠር ፍትወታዊ ስሜትም አብሮ አልተፈጠረበትም። ነገር ግን ሕገ እግዚአብሔርን ሽሮ እፀ በለስን በበላ ጊዜ ፍትወታት እኩያት ሰልጥነውበታል። ስለዚህ ፍትወታዊ ስሜት ተፈጥሯዊ ሳይሆን የድቀት ውጤት ነው። ይህንን በምሳሌ ላስረዳ አንድ ሰው ጤነኛ ሆኖ ከተፈጠረ በኋላ ራሱን ወደ ገደል ቢወረውር እና አካሉ ጎደሎ ቢሆን ይህ አካለ ጎደሎነቱ በመውደቁ ምክንያት የመጣ እንጂ ተፈጥሯዊ አይደለም። የፍትወት ስሜትም እንዲሁ ነው። ተፈጥሯዊ አይደለም። በአዳም ድቀት ምክንያት የደረሰብን ጉዳት ነው። ይህ ቢሆንም ግን እግዚአብሔር ባወቀ ፍትወታዊ ስሜት ቢሰማን እንኳ ከተፈቀደልን ሰው ጋር ግንኙነት እንድናደርግ የትዳርን መስመር ፈቅዶልናል። ስለዚህም ባል ከሚስቱ ሚስት ከባሏ የሚያደርጉት ግንኙነት ፍትወት አይባልም። ሕጋዊ ግንኙነት ይባላል እንጂ። ለዚያ ነው ሊቁ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው "ኦ ድንግል አኮ በፍትወተ ደነስ ዘተጸነስኪ። አላ በሩካቤ ዘበሕግ" ይላል። ድንግል ማርያም ሆይ በኃጢኣት ፍትወት የተጸነስሽ አይደለም። ሐናና ኢያቄም በሕግ ተጋብተው ባደረጉት ግንኙነት ተጸነስሽ እንጂ ይላል። ስለዚህ ሁለቱን ሕጎች ለመጠበቅ ይረዳን ዘንድ ስለ እጮ ኝነትና ስለትዳር በ11 ክፍል ተማምረናል። የቀረውን ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ መምህራንን በመጠየቅ ማስፋት ትችላላችሁ። መቼም እግዚአብሔር ያዘዘን ትእዛዛት ሁሉ እኛን የሚጠብቁ ብንጠብቃቸው እኛን የሚጠቅሙን እንጂ ጨቋኝ ሕጎች አይደሉም። ሕጻንን ልጅ እናቱ ካልበላህ እያለች ስትቆጣው እሱን ልትጠቅመው ነው እንጂ ልትጎዳው እንዳይደለ ማለት ነው። ከአሥሩ ሕግ ደግሞ አንዱ ዘጸ.20፣14 አታመንዝር የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከስድስቱ ቃላተ ወንጌል አንዱ ማቴ.5፣31 "ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እርሱ ራሱ አመንዝራ ያደርጋታል የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል" የሚለው ነው። ከዚህ ላይ ያለዝሙት ምክንያት ሰነፈች መከነች ወዘተ ብሎ ሚስቱን የሚፈታ ሰው ትልቅ በደለኛ ነው። በዚህ ምክንያት ሚስቱን የፈታን ሰው መልሰው ሊያስታርቁት ይገባል። 1ኛ ቆሮ.7፣10 "ሚስት ከባሏ አትፋታ ከተፋታችም ብቻዋን ትኑር። ያለዚያ ከባሏ ጋር ትታረቅ። ባልም ሚስቱን አይፍታ"። እምቢ አልታረቅም ካለ/ካለች ግን ሊያገቡት/ሊያገቧት አይገባም። አታመንዝር ያለን ሕግም እርሱ ባወቀ እኛን የሚጠብቀን ሕግ ነው። የእኛ ካልሆነች ሴት/ወንድ የሌላ ከሆነች/ከሆነ ሰው ጋር ግንኙነት

ለምን እናደርጋለን!? ይህስ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ያፈነገጠ ስለሆነ በነፍስ በሥጋ የሚጎዳን ስለሆነ ልናደርገው አይገባንም። 1ኛ ቆሮ.7፣2 "ነገር ግን እንዳትሴስኑ ሰው ሁሉ በሚስቱ ይወሰን። ሴትም ሁላ በባሏ ትወሰን። ለሚስትም ባሏ የሚገባትን ያድርግላት። እንዲሁ ሚስትም ለባልዋ የሚገባውን ታድርግለት"። ከተጽእኖ ነጻ የሆነ ትዳር ያስፈልጋል። ይህም ማለት ወንዱ የሴቲቱን እሷነቷን ሳይወድ ገንዘቧን ወይም የታላቅ ሰው ዘር ስለተባለች ብቻ ወይም በሌላ ምክንያት ሊያገባት አይገባም። ሴቲቱም የወንዱን እሱነቱን ሳትወድ በሌላ ተጽእኖ (ምሳሌ እድሜየ ሄደ፣ ቤተሰብ አግቢ እያሉ ጨቀጨቁኝ... ወዘተ በማለት) የማትወደውን ሰው ማግባት የለባትም። ሌላው ከተጋቡ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ወይም ከሴቲቱ ችግር ወይም ከወንዱ ችግር መውለድ የማይችሉ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ምክንያት ግን ትዳርን መፍታት እግዚአብሔርን እንደመስደብ ይቆጠራል። ልጅን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነውና። ስለዚህ በዚህ ምክንያት ልጅ ባላቸው መቅናትም እርስ በእርስ መጋጨትም አይገባም። ከሕግ ውጭ ግንኙነት ያደረጉ ሰዎች ተቀጥተዋል። ስለዚህ እኛም ከሕግ ውጭ የሆነ ግንኙነት አድርገን ዘላለማዊ ቅጣትን እንዳንቀበል እንጠንቀቅ። ከዚህ ቀደም በማወቅም ባለማወቅም አጥፍተንም ከሆነ ንሥሓ ገብተን ካሁን በኋላ ላለው ሕይወታችን እንጠንቀቅ። ሮሜ.7፣2 "ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና። ባሏ ቢሞት ግን ስለ ባል ከሆነው ሕግ ተፈታለች"። ስለሚል ከሚስት/ከባል አንዱ ቢሞት 10 ወር ቆይቶ ሌላ ማግባት ይፈቀዳል። 1ኛ ቆሮ.7፣8 "ነገር ግን ያላገቡትንና አግብተው የፈቱትን እንደ እኔ ሆነው ቢኖሩ ይሻላቸዋል እላለሁ። መታገሥ ባይችሉ ግን ያግቡ በፍትወት ከመቃጠል ማግባት ይሻላልና" ይላልና።

ቅዱሳት በዓላት

ቅዱሳት በዓላት ክፍል 1

በዓሉ የክርስቶስ የጥምቀት በዓል ነው። እነርሱ የሚያስተላልፉት ስለ ሎሚ ታሪክ ነው። በቃ ሎሚ ማክሰኞ ቀን ከተፈጠሩ እጽዋት አንዱ ነው። አለቀ። በዓሉ ዲያብሎስ በአዳም የጻፈው የሞት ደብዳቤ የተቀደደበት ነው። ሚዲያዎች ግን የዲያብሎስ የሞት ደብዳቤ የሆነውን ጭፈራ ያስተላልፋሉ። የጥምቀት በዓል ከጌታ ዐበይት በዓላት አንዱ ነው። ቅዱሳት በዓላት ደግሞ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ የሚገኝባቸው ሰው ንሥሓ ገብቶ ሥጋውን ደሙን የሚቀበልባቸው ልዩ እለታት ናቸው። ቅዱሳት በዓላት የሚከበሩት በማኅሌት፣ በዝማሬ፣ በትምህርተ ወንጌል ነው እንጂ በዘፈን፣ በፉከራ፣ በቀልዳቀልድ አይደለም። ነቢዩ "ግበሩ በዓለ በትፍሥሕት በዓልን በደስታ አክብሩ ብሎናል" በደስታ የምትለዋ ቃል ትርጓሜዋ መንፈሳዊ ደስታ ናት። መዝ.94 ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን እንዳለው በእግዚአብሔር መደሰት ነው። በእግዚአብሔር መደሰት ምን ማለት ነው? ከተባለ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቆ እግዚአብሔር የማይወደውን ጭፈራ ሽለላ ዘፈን፣ ስካር ትቶ ማክበር ነው። ብዙዎቻችሁ እስኪ በበዓል ትዝ የሚላችሁ ምንድን ነው? ስንባል መልሶቻችን በጉ፣ ሥጋው፣ አዲስ ልብስ፣ መጠጡ የሚል መልስ እንመልሳለን። ይኸውም በዓላቱ እንዲከበሩ ከተደረገበት ዓውድ ወጥተን በሰይጣናዊ ልማድ እያከበርነው ነው ማለት ነው። በበዓላት ወቅት አዲስ ልብስ ነጭ ልብስ መልበስ ጥሩ ነው። ለምን እንደሚለብሱት አለማወቅ ግን ትልቁ ችግር ነው። በበዓላት ወቅት ነጭ ልብስ አዲስ

ልብስ እንለብሳለን ይኽውም ለእግዚአብሔር ክብር ሰጥተን በእርሱ ፊት አፍኣዊ ንጽሕናንና ውሳጣዊ ንጽሕናን ይዘን የምንቀርብበት ነው እንጂ የሆነ ሰው ልብሳችንን አይቶ እንዲወደን ወይም ለመለከፍ አይደለም። ይህ ከሆነ ተርእዮ ወይም ከንቱ ውዳሴ የሚባለውን ኃጢኣት እየሰራን ይሆንብናል። በበዓላት ወቅት በጉ ሥጋው መጠጡ ትዝ የሚለን ከሆነም አስቸጋሪ ነው። በበዓላት ወቅት ንሥሓ ገብተን የክርስቶስን ሥጋ የምንበላበት የክርስቶስን ደም የምንጠጣበት ነው መሆን ያለበት። ከቤታችን የምናዘጋጀው መብል መጠጥ ሁለተኛ ነው። በተረፈ በበዓላት ወቅት የምንሰክርበት ሳይሆን ከቤታችን በግ አርደን፣ የሚጠጣ አዘጋጅተን ነዳያንን የምንጠራበት ነው መሆን ያለበት ይህ ሲሆን ብራብ አብልታችሁኛል የሚለውን ሕግ ፈጽመን በዓሉን በጥሩ ሁኔታ አክበርን ይባላል። አሕዛባዊ ልማድ በቅዱሳት በዓላቶቻችን ልናስገባ አይገባንም።ቅዱሳት በዓላትን በተመለከተ እስከ ክፍል 7 እንማማራለን። ነጭ ለብሰን የምንነሳው በትንሳኤ ጊዜ ነው። ታድያ በትንሳኤ በሰማያዊው ዙፋን ፊት ይዘመራል እንጂ አይጨፈርም። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት ናት። ስለዚህ ከምድራዊ ደስታ ይልቅ ሰማያዊውን ደስታ እያሰብን እናክብረው።

ቅዱሳት በዓላት ክፍል 2

ከዘጠኙ የጌታ ዐበይት በዓላት አንዱ የሆነው ጥምቀት ነው። ዘጠኙ የጌታ ዐበይት በዓላት የሚባሉትም፦

- ጽንሰቱ.....መጋቢት 29
- 2) ልደቱ.....ታኅሣሥ 29
- 3) ጥምቀቱ.....ጥር 11
- 4) ደብረ ታቦር....ነሐሴ 13
- 5) ስቅለት
- 6) ትንሳኤ
- 7) ዕርገት
- 8 ጰራቅሊጦስ
- 9) ሆሣዕና

ከ5 እስከ 9 ቁጥር ያሉት በባሕረ ሐሳብ በተውሳክ የሚታወቁ ናቸው። ከእነዚህ በዓላት ውስጥ ትንሳኤ፣ ሆሣዕና፣ ጰራቅሊጦስ እሑድን አይለቁም። ዘጠኙ የጌታ ንዑሳት በዓላት የሚባሉት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

- 1) መስቀል....መስከረም17 እና መጋቢት 10

- 2) ስብከት
- 3) ብርሃን
- 4) ኖላዊ
- 5) ጌና.....ታኅሣስ 28
- 6) ግዝረቱ.....ጥር 6
- 7) ደብረ ዘይት
- 8 ቃና ዘገሊላ.....ጥር 12
- 9) ልደተ ስምዖን....የካቲት 8

ስብከት፣ ብርሃን፣ ኖላዊ ልደት ከመዋሉ በፊት ባሉት ተከታታይ እሑዶች የሚውሉ ናቸው። ስለዚህ ከእነዚህ በዓላት ደግሞ እኒህ ሦስቱ እና ደብረ ዘይት እሑድን አይለቁም። ስለዚህ በአጠቃላይ ለጌታ 18 በዓላት 7ቱ እሑድ ይውላሉ ማለት ነው። ሌሎች እንደየዘመኑ እሑድም ቅዳሜም ሊውሉ ይችላሉ። ዕርገት ሐሙስ፣ ስቅለት አርብ ይውላሉ። ልደተ ስምዖን የተባለው ደግሞ ጌታ ወደ ቤተመቅደስ የገባበት እለት ሲሆን ልደተ ስምዖን ተብሎ የተሰየመው እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች የሚለውን የትንቢተ ኢሳይያስ ክፍል ይተረጉም የነበረው ስምዖን ይህንን ሰርዞ ወለት ትጸንስ እያለ ሦስት ጊዜ ቢያስተካክልም መልአክ ተገልጦ ይህንን ሳታይ አትሞትም ብሎታል። ጌታም በተወለደ በ40 ቀኑ ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ። ያን ጊዜ ስምዖን እንደገና አካሉ በርትቶ እንግዲህስ ባርያህን በሰላም አሰናብተው ብሏል። አካሉ ታድሷልና ልደተ ስምዖን ተብሏል። በዓል አብዐለ አከበረ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ነው። ክብር ማክበር መክብር ተብሎ ይተረጎማል። በዓላት ክቡር እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ልዩ እለታት ናቸው። መዝ.22፣23 እግዚአብሔርን የምትፈሩ አመሰግኑት፣ የያዕቆብ ዘር ሁላችሁ አክብሩት"። 1ኛ ቆሮ.6፣19 "...ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩት"። አሁን እግዚአብሔር ክብር የሌለው ሆኖ አይደለም። ክቡር ነው፣ ውዱስ ነው፣ ቅዱስ ነው፣ ልዑል ነው በሉ ማለት ነው። ስለዚህ በዓላት እግዚአብሔር ያደረገውን የማዳን ሥራ እያሰብን እርሱን የምናመሰግንባቸው እለታት ናቸው። በእነዚህ የጌታ በዓላት ጌታ ለእኛ ያደረገልንን የማዳን ሥራ እየተማማርን እርሱን በምስጋና እያመሰገንን በዓሉ እናከብረዋለን። እንጂ ጭፈራ፣ ዘፈን፣ ዳንኪራ፣ ስካር በበዓላት ወቅት ፈጽመው ሊደረጉ አይገባም። ይህን ስንል በጸናው መናገራችን ነው እንጂ በሌላውም ቀን ቢሆን ዘፈን፣ ዳንኪራ፣ ስካር አልተፈቀደም። በእነዚህ በበዓላት ቀና እኛም ሥጋውን ደሙን እየተቀበልን የምንቀደስባቸው እለታት ናቸው።

ቅዱሳት በዓላት ክፍል 3

በጥምቀት በዓል ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ገብተን ውሃው ተጸልዮበት እንጠመቃለን። ይህ ጥምቀት ግን የበረከት ጥምቀት ነው እንጂ የልጅነት ጥምቀት አይደለም። በተቀደሰ ውሃ መጠመቅ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ ያሰጣልና።በትርጓሜ ትምህርታችን አቃቤ ሰዓት አበሞ የተባሉ ሊቅ

እንኳ በግላቸው ውሃ አቀረብኩና 71 ጊዜ ጸለይኩበት። ያንን ውሃም ብጠጣው ምሥጢር ገለጸልኝ ብለዋል። በዚህ አንጻር በማኅበር ጸሎት በምሥጋና በከበረው ጥምቀተ ባሕር መጠመቅማ ምን ያህል በረከት ያሰጥ ይሆን!?። ስለዚህ ወደ ጥምቀተ ባሕር ገብተን ስንጠመቅ፣ ስንረጭ ልናስተውለው የሚገባን እግዚአብሔር ባወቀ የምናገኘው በረከተ ሥጋ ወነፍስ እንዳለ ነው። እንግዲህ ለዚህ ሥርዓት መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለዚህ የጥምቀት ሥርዓታችን መሠረቱ የጌታ ጥምቀት ነው። በኩረ በዓላት የምትባለዋ ቀዳሚት ሰንበት ናት። ይህች ቀን የምትከበርበት ምክንያትም እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ አርፎባታልና ተብሎ ነው። እኛም ቅዱሳት በዓላቶቻችንን ስናከብር ይህን መነሻ አድርገን ነው። ለምሳሌ ጥምቀት ጌታ በዮርዳኖስ ተጠምቆ ለእኛ አርዓያ የሆነበት እለት ናት። በበዓላት ወቅት ሥራ አይሰራም። በሥራ ዙሩያ አንተ፣ ሚስትህ፣ በሬዎችህ እንዳያርሱ፣ ልጆችህ ሥጋዊ ሥራ እንዳይሰሩ፣ ባሮችህም እንዲሁ እንዳይሰሩ ነው። ይህንን ሥርዓት በደንብ እናስተውለው እኛ አስቀድሰን እየመጣን ባሮቻችንን የምናሰራ ከሆነ በዓሉን እንዳከበርን አይቆጠርም። በቅዱሳት በዓላት የሚሠሩ ሥራዎች መንፈሳዊ ሥራዎችና ሥርዐቶች ናቸው። ዘጸ.20፥8-11 " የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ። ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው። አንተ፣ ወንድ ልጅህም፣ ሴት ልጅህም፣ ሎሌህም፣ ገረድህም፣ ከብትህም፣ በደጅህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ። እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፏልና። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም"። ሌላው እንደየበዓሉ ልዩ ልዩ ሥርዐቶች አሉን። ለምሳሌ ወደ ጥምቀተ ባሕር ወርዶ የመጠመቅ ሥርዐት ያለው በጥምቀት ጥር 11 ብቻ ነው። ይህም ጥንተ በዓሉ የተደረገው ጌታ ወደ ዮርዳኖስ ሄዶ በዮሐንስ በመጠመቁ ነው። ይህን የመሰለ እስራኤላውያን ከግብጽ የወጡበትን እለት በልዩ ልዩ ሥርዓት በየዓመቱ ያከብሩት ነበር። ለምሳሌ እስራኤላውያን ከግብጽ ምድር ከመውጣታቸው በፊት ሞተ በኩር እንዳያገኛቸው ያልቦካ ቂጣ በልተው፣ በግ አርደው ጫማ ተጫምተው ኩፌት ደፍተው ያከብሩት ነበር። ዘጸ.12፣1-51 ማየት ይቻላል። በዚሁ ምዕራፍ ዘጸ.12፣14 "ይህም ቀን መታሰቢያ ይሁናችሁ ለእግዚአብሔርም በዓል ታደርጉታላችሁ። ለልጅ ልጃችሁ ሥርዐት ሆኖ ለዘለዓለም ታደርጉታላችሁ" ብሏቸዋል። በእስራኤል ብዙ የተለያዩ በዓላት ነበሩ። አከባበራቸው እና የአከባበር ሥርዓታቸው ግን የተለያየ ነበር። ካህናቱም የሚያቀርቡት የመሥዋእት አቀራረብ የተለያየ ነበር። እኛም ይህን አብነት አድርገን ለተለያዩ በዓላቶቻችን ልዩ አከባበርና ሥርዓት አለን።

ቅዱሳት በዓላት ክፍል 4

በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚጠራው የእግዚአብሔር ሥም ነበረ። በእኛም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚባል ቀለም (ቃለ እግዚአብሔር) አለን። ጌታ የተጠመቀ፣ የተነሳ፣ የተወለደ፣ የተሰቀለ አንድ ጊዜ ቢሆንም በዓሉን የምናከብረው ግን በየዓመቱ ነው። እስራኤላውያን ከግብጽ የወጡት አንድ ጊዜ ነው። በዓሉን የሚያከብሩት ግን በየዓመቱ ነው። በዓሉን ሲያከብሩም በዚያ እለት ፈጣሪ ያደረገላቸውን ቸርነት ድንቅ ሥራ እያሰቡ ነበር የሚያከብሩት። እኛም በዓላትን ስናከብር በዚያ በዓል ፈጣሪ ያደረገልንን ድንቅ ሥራ እያሰብን

እናክብር። በነገራችን ላይ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ይህን ሥርዓት የተከተለ ነው። ዕለቱን የሚያዘክር ቃለ እግዚአብሔር ነው ማኅሌቱ። እኛም መዝሙራችን ከዕለቱ ጋር የተገናኘ ሊሆን ይገባል። ሁሉም ምእመን ለመያዝ ቀለል ያሉ መዝሙሮችን አጥንቶ ታቦት አጅቦ ሲሄድ እየዘመረ ቢሄድ መልካም ነው። ዝም ብሎ ከሚሄድ ፈጣሪውን እያመሰገነ መሄዱ መንፈሳዊ ጥቅምን ያስገኝለታልና። የቅዱስ ያሬድ በየዘመናቱ በየበዓላቱ የሚቀርቡ ዜማዎችን ብንመለከት ለምሳሌ የጥምቀት ማኅሌት ነገረ ጥምቀቱ ለክርስቶስን የሚያወሱ እያወሱም ለፈጣሪ ምሥጋናን የሚያቀርቡባቸው ናቸው። የልደት ማኅሌትን ብናይ ስለ ክርስቶስ ልደት ነቢያት የተናገሩትን ሐዋርያት የሰበኩትን ሊቃውንት ያመሰጠሩትን ነገረ ልደት በዜማ የሚያወሳ ነው። የሌሎች በዓላትም እኒህን የመሰሉ ናቸው። 2ኛ ዜና.20፣21 "ጌጠኛ ልብስም ለብሰው የሚያመሰግኑትን ለእግዚአብሔርም የሚዘምሩትን መዘምራን..." ይላል። በቅዱሳት በዓላት ወቅት መምህራኑ ጥንግ ድርብ፣ ካባ ለብሰው የሚያከብሩት ይህንን መነሻ በማድረግ ነው። እነርሱ ሊታዩበት ሊሞገሱበት አይደለም። በእነርሱ ምክንያት ፈጣሪ ይመሰገንበት ዘንድ ነው እንጂ። 2ኛ ዜና.7፣6 "ንጉሥ ዳዊት እግዚአብሔርን ለማመስገን የሠራውን የእግዚአብሔርን የዜማ እቃ ይዘው ቆመው ነበር። ካህናትም በፊታቸው መለከት ይነፉ ነበር" እንዲል በቅዱሳት በዓላት ጊዜ የዜማ እቃ የተባሉ ከበሮ ጸናጽል መቋሚያ መለከት (ጥሩንባ?) ወዘተ ይዘን ፈጣሪን እናመሰግናለን ማለት ነው። በበዓል ወቅት ማመስገን እንደሚገባም በመዝ.96፣12 "ጻድቃን በእግዚአብሔር ደስ ይላቸዋል።ለቅድስናውም መታሰቢያ ያመሰግናሉ" ይላል። ቅዱሳት በዓላት ደግሞ የሚከበሩት እግዚአብሔር በቅዱሳኑ አድሮ የሠራቸውን መልካም ሥራዎች በማሰብ እና እግዚአብሔር ለእኛ ለሰው ልጆች መዳን ያደረገልንን መልካም ሥራ እያሰብን ስለሆነ በዓላትን ቅዱስ ዳዊት የቅድስናው መታሰቢያ ብሏቸዋል። ምዕመናንም ልክ እንደ ካህናቱ በቅዱሳት በዓላት ጊዜ ጌጠኛ ልብስ የሚለብሱት ለራሳቸው ከንቱ ውዳሴን ሽተው ሳይሆን ለአምላካቸው ክብር መገለጫ እንዲሆን ነው። ስለዚህ በበዓል ወቅት ጌጠኛ ልብስ ለብሶ/ለብሳ ብታይ ለፈጣሪ ክብር መገለጫ ያደረገው ያደረገችው መሆኑን ልብ በል። ቅዱሳን መላእክትም በጌታ ትንሳኤ ጊዜ ነጭ ልብስ ለብሰው ታይተዋል። የደስታ ጊዜ ነው ሲሉ ነው። ዘፍ.37፣3 "እስራኤልም ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወደው ነበር...በብዙ ጎብር ያጌጠችም ቀሚስ አደረገለት" እንዲል ብዙ ጎብር ያለው ቀሚስ የተወደደ ልብስ ነው። ያዕቆብ ዮሴፍን ለመውደዱ መገለጫ ብዙ ጎብር ያለው ልብስን በመግዛት ገልጦታል። እኛም በበዓላት ወቅት ብዙ ጎብር ያለው ልብስ ለብሰን የምንሄደው ዮሴፍ ምሳሌው ለሆነው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጫ ነው። ይህ ሁሉ አፍዓዊ ጌጥ ነው። ጌታን መውደድ በበዓላት ወቅት ጌጠኛ ልብስ ለብሰን በመታየት ብቻ አይደለም። ንሥሓ ግቡ ሥጋውን ደሙን ተቀበሉ ባለን መሠረት መልካም ሥራን ሠርተን ክፉ ሥራን ትተን ወደ እርሱ የምንቀርብበትም ጭምር መሆን አለበት።

ቅዱሳት በዓላት ክፍል 5

የግዝት በዓላት

በየሳምንቱ ቅዳሜ እና እሑድ፣ ክፍል 2 ላይ ያያናቸው 18ቱ የጌታ በዓላት፣ በ12ቱ ወር የሚካኤል በ12 በ12፣ በ12ቱ ወር የበዓለ እግዚአብሔር በ29 በ29 እና 33ቱ የድንግል ማርያም

በዓላት ናቸው። የግዝት በዓላት እነዚህ ናቸው ከእነዚህ ውጭ ባለው ቀን ማንኛውም ሰው ሥጋዊ ሥራ መሥራት ይችላል። እነዚህም በጠቅላላው በዓመት ሲደመሩ ከሥር እንደተገለጸው ግፋ ቢል 121 ካነሰ ደግሞ 115 ቀናት ይሆናል። ይህ ቁጥር ከፍተኛ ሊሆን በሚችለው የተሠራ ሲሆን። ቁጥሩ ከዚህም ሊያንስ ይችላል። 33ቱ የድንግል ማርያም በዓላት የተባሉትም፦

- 1) መስከረም 10 ጴዴንያ
- 2) መስከረም 21
- 3) ጥቅምት 21
- 4) ኅዳር 6 ቁስቋም
- 5) ኅዳር 21
- 6) ታኅሣስ 3 በዓታ ለማርያም
- 7) ታኅሣስ 21
- 8) ታኅሣስ 22
- 9) ታኅሣስ 28 ጌና
- 10) ታኅሣስ 29 የጌታ ልደት
- 11) ጥር 21 አስተርእዮ
- 12) የካቲት 16 ኪዳነ ምሕረት
- 13) የካቲት 21
- 14) መጋቢት 21
- 15) መጋቢት 29 የጌታ ጽንሰት
- 16) ሚያዝያ 21
- 17) ግንቦት 1 ልደታ ለማርያም
- 18) ግንቦት 21
- 19) ግንቦት 22
- 20) ግንቦት 23

- 21) ግንቦት 24
- 22) ግንቦት 25
- 23) ሰኔ 8
- 24) ሰኔ 20
- 25) ሰኔ 21
- 26) ሐምሌ 21
- 27) ነሐሴ 7 የተጸነሰችበት
- 28) ነሐሴ 16
- 29) ነሐሴ 17
- 30) ነሐሴ 18
- 31) ነሐሴ 19
- 32) ነሐሴ 20
- 33) ነሐሴ 21

ናቸው። ከዚህ ላይ በደንብ ልናስተውለው የሚገባን ለምሳሌ ከ18ቱ የጌታ በዓላት የተጠቀሱት እለታት ከ33ቱ የድንግል ማርያም በዓላት ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ ታኅሣስ 28፣ ታኅሣስ 29 እና መጋቢት 29 ናቸው። ከላይ ያሉትን ሳንደርብ ብንቆጥራቸው። ማለትም ለምሳሌ ታኅሣስ 29 እሑድ ወይም ቅዳሜ ቀን ቢውል። በዓሉ ከጌታ ዐበይት በዓላትም አንዱ ነው፣ ከ33ቱ የድንግል ማርያም በዓላትም አንዱ ነው፣ በየወሩ ከሚከበረው የበዓለ እግዚአብሔርም አንዱ ነው። ስለዚህ ሁሉም በአንድ ቀን ስለዋለ በዚህ ቀን አንድ ተብሎ ይቆጥራል። እንዲህ እንዲህ እያልን በዓላቱን ብንደምራቸው፦

- መስከረም 1 ሰኞ ቢውል 118 ቀናት
- መስከረም 1 ማክሰኞ ቢውል 119 ቀናት
- መስከረም 1 ረቡዕ ቢውል 121 ቀናት
- መስከረም 1 ኃሙስ ቢውል 119 ቀናት
- መስከረም 1 ዐርብ ቢውል 117 ቀናት
- መስከረም 1 ቅዳሜ ቢውል 116 ቀናት

- መስከረም 1 እሑድ ቢውል 115 ቀናት

የግዝት በዓላት ናቸው ማለት ነው። ይህንንም በጣም ሊሆን በሚችለው ከፍተኛ ቁጥር አስልተነው ነው እንጂ ለምሳሌ በዓቢይ ጾም ውስጥ ያሉ በዓላት በተውሳክ የሚወጡ ስለሆነ ሊደረቡ ይችላሉ። ለምሳሌ መጋቢት 10 ቀን ደብረ ዘይት ቢውል በተጨማሪ መስቀል ነው ይህን ጊዜ ይቀንሳል ማለት ነው። እኒህም በመደረባቸው ምክንያት ቁጥሩን ሊቀነሱ የሚችሉ በዓላት መጋቢት 10፣ ግንቦት 1፣ ግንቦት 22፣ ግንቦት 23፣ ግንቦት 24፣ ግንቦት 25፣ ናቸው። በእነዚህ የግንቦት እለታት ዕርገት ሐሙስ ስለሆነ ለብቻው ብንቆጥረውም እነዚህ ሊደረቡበት ይችላሉ በዚህ ጊዜ አቆጣጠሩ ላይ ቀን መቀነሱ አይቀሬ ነው። እንግዲህ የግዝት በዓላት እነዚህ ናቸው። በተጨማሪ የደብራችን ታቦት በሚውልበት ቀን እንጨምራለን። ይኽውም ደብራችን የማርያም የሚካኤል የበዓለ እግዚአብሔር ከሆነ ተቆጥሯል። ካልሆነ በዚያን ቀን መንፈሳዊ ሥራ ሲሠሩ መዋል ነው። (ለዚህ እንኳ ማለቴ የደብርህ ታቦት የሚውልበትንም ለሚለው ትውፊታዊ እንጂ መጽሐፋዊ ማስረጃ አላገኘሁም)። ከእነዚህ በተጨማሪ ባሉት የጻድቃን የሰማእታት የመላእክት በዓላት እንደፈቃዱ መሥራትም አለመሥራትም ይችላል። በፈቃድ ነው። ቤተክርስቲያን በዓላት ብላ ቆጥራ የሰጠችን እና ሥጋዊ ሥራ እንዳይሰራባቸው የታዘዙ እለታት ከላይ ያሉት ናቸው። ቢሆንም ግን በእነዚህ እለታት መንፈሳዊ ሥራ ይሰራባቸዋል። ስለዚህ በእውነት ኢትዮጵያ እንዳትከብር ያደረጋት በዓል አብዝታ ነው የሚለው የግርድፍ አጥኚዎች አስተያየት እውነታ አለው ወይስ የለውም የሚለውም በቀጣይ ክፍል እናየዋለን።

ቅዱሳት በዓላት ክፍል 6

የበዓላት ቀኖና የሚጀምረው ከሠርክ ከ12፡01 ሰዓት ጀምሮ ነው። ይሄውም በእስራኤላውያን የቀን አቆጣጠር ማለት ነው። ፍጥረት መፈጠር የተጀመረው በእኛ ሀገር አቆጣጠር ቅዳሜ 12፣01 ሰዓት ጀምሮ ሲሆን በእስራኤል አቆጣጠር ግን እሑድ ነው። ከሠርክ ከ12፡01 ሰዓት ጀምሮ የሚቆጠረው ለቀጣዩ ቀን መጀመሪያ ተደርጎ ነው። ስለዚህ አርብ ከሠርክ ከ12፡01 ሰዓት ጀምሮ የሚቆጠረው ቅዳሜ ተብሎ ነው። ስለዚህ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ሥራ አይሠራም። በአንጻሩ እሑድ ሠርክ ከ12፡01 ሰዓት ጀምሮ የሚቆጠረው ሰኞ ተብሎ ነው። ስለዚህ በገጠሩ የሀገራችን ክፍል ማታ ጀምሮ በጨረቃ ጨፍ ይታጨዳል ሥራ ይሠራል። የበዓላት ቀኖና ከዋዜማው ጀምሮ እስከ ቀጣዩ ቀን ሠርክ ነው። በበዓላት ወቅት ሥራ አይሠራም ማለት ሥጋዊ ሥራ አይሠራም ማለታችን ነው። ሥጋዊ ሥራ ማለትም ማረስ፣ መቆፈር፣ ማጨድ የመሳሰለው ነው። በምትኩ በበዓላት መንፈሳዊ ሥራ ይሰራል። ይኽውም የተጣላን ማስታረቅ፣ የታመመን መጠየቅ፣ የታሠረን መጠየቅ፣ የታረዘን ማልበስ፣ የተራበን ማብላት፣ የተጠማን ማጠጣት እና የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ ሥራዎች ለማኅበራዊ ሕይወት ታላላቅ መሠረቶች ናቸው። በበዓላት ወቅት ቃለ እግዚአብሔርን መማር፣ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ማንበብ ይገባል። ስለዚህ በበዓላት ወቅት ሥጋዊ ሥራን ስላልሰራን ሥራ ፈት ልንባል አንችልም። ምክንያቱም በመንግሥት እንኳ ታላቅ በጀት ተበጅቶላቸው ቋሚ የሥራ ምንጭ ሆነው የሚሠሩ ነገሮች ለምሳሌ ምግብ፣ ልብስ የሌላቸውን ሰዎች ረድቶ ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ የመሳሰሉ ጉዳዮችን ክርስቲያኖች በራሳቸው ተነሳሽነት በፈቃደኝነት ለተቸገሩት ልብስን፣ ምግብን እየሰጡ

የሚረዱባቸው እለታት ናችው። ምንም እንኳ በማንኛውም ጊዜ የተፈቀደ ቢሆንም በበዓላት ደግሞ በበለጠ የሚረዳዱበት እለት ነው። ለምሳሌ የዕርቅ ኮሚሽን ብሎ መንግሥት ታላቅ በጀት በጅቶ ይሠራል። ይህንን ግን ምእመናን ምንም በጀት ሳያወጡ የተጣሉ ሰዎችን እያስታረቁ ይኖራሉ። በነገራችን ላይ ሀገራችንን ለምስቅልቅል የዳረጋት ቤተ ክርስቲያንን አታስፈልግም ብላችሁ የገፈተራችኋት ጊዜ ነው። አንዱ አከርካሪዋን ሰብራያለሁ ሲል፣ አንዱ ሰላማውያን ሰዎችን በበዓላቶቻችን ሲገድል፣ የሰላም ባለቤት የሆነችዋን ቤተ ክርስቲያን ገፍታችሁ ሰላምን ማምጣት አትችሉም። ስለዚህ ቤተክርስቲያን ለሀገር እድገት ዋናዋ ሆና ሳለ በብዙዎች ጸር እንደሆነች የሚነገረው ንግግር መሠረተ ቢስ ነው። በእርግጥ ሰይጣን ቤተክርስቲያንን አይወዳትም። ምክንያቱም የሰላማዊ ክርስቶስ ሙሽራ ናት። ስለዚህ ሰላሙ ያለ ከእርሷ ስለሆነ ሰይጣን ደግሞ ከሰላም ይልቅ ጥላቻን ስለሚወድ ቤተ ክርስቲያንን አምርሮ ይጠላታል። በዓላትን ስለምታበዛ ጸረ እድገት ናት ያሰኛታል። ነገር ግን እውነታው ከላይ እንዳለው ነው። በበዓላት ሥራው መንፈሳዊ ይሆናል እንጂ ከሥራ ቦዝነን አንውልም። ሰይጣን እርሷን ለማጥፋት ያላደረገው መከራ የለም። በዮዲት ጉዲት፣ በግራኝ አሕመድ፣ በፋሺስት፣ በደርቡሽ፣ በደርግ፣ በኢሕአዴግ፣ በብልጽግና አድሮ ብዙ ሰርቷል እየሰራም ነው። ግን እርሷን ማሸነፍ አይቻልም።

ቅዱሳት በዓላት ክፍል 7

በልደት፣ በጥምቀት እና በትንሳኤ ቅዳሴ መንፈቀ ሌሊት እንዲቀደስ ሠለስቱ ምእት በፍትሐ ነገሥታቸው አንቀጽ 19 ላይ ገልጸዋል። ቅዱሳት በዓላት ስለ እግዚአብሔር ክብር አብዝተን የምንዘምርባቸው፣ ስለ እግዚአብሔር ክብር አብዝተን የምንማማርባቸው፣ ሁሉን በቸርነቱ ለሰጠን እና ፍጥረታትን ፈጥሮ ለሚያስተዳድር ጌታ ምስጋና የምናቀርብባቸው ልዩ ዕለታት ናቸው። በቅዱሳት በዓላት ቀን በዓሉን የሚመለከቱ ትምህርቶች፣ መዝሙራት ይዘመራሉ እንጂ ከበዓሉ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ነገሮች ሊከናወኑ አይገባም። በዐበይት በዓላት ጊዜ መስገድ አይገባም። ስግደት ያደክማልና። ይኽውም ቅዱሳት በዓላት በመንግሥተ ሰማያት ለምንኖረው ኑሮ ምሳሌዎች ስለሆኑ በመንግሥተ ሰማያት ደግሞ ሥጋዊ ድካም የለም ጣር ጋር የለምና ነው። ቅዱሳት በዓላትን ምክንያት አድርገው የሚዘጋጁ የዘፈን ኮንሰርቶችን ልንቃወማቸው ይገባል። እንኳንስ በቅዱሳት በዓላት ቀን በሌላው ቀንም ዘፈን የሰይጣን መሥዋዕት ስለሆነ መዝፈን አይገባም። ዝማሬ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ፍሬ ከናፍር መሥዋእት ሲሆን ዘፈን ደግሞ ለሰይጣን የሚቀርብ መሥዋዕት ነው። ስለዚህ በበዓላት ወቅት ዘፈን፣ ስካር፣ እና ከበዓሉ ጋር ግንኙነት የሌላቸውን መርሐ ግብሮች አምርረን ልንቃወማቸው ይገባናል። በበዓላት ወቅት በተለይም በጥምቀት እና በቃና ዘገሊላ ብዙ ምእመናንን እናያለን። ይህንን ሁሉ ምእመን ቤተ ክርስቲያን ተከታታይ ትምህርት እየሰጠች ሁሉንም በእውቀት በምግባር የሰለጠነ ልታደርጋቸው ይገባል። በሀገራችን እስከ እያንዳንዱ ምእመን የሚደርስ መዋቅር አለን። ይህ መዋቅር ግን አሁን ላይ ደካማ ነው። እያንዳንዱ አጥቢያ በሥሩ ያሉ ሕጻናት ስንት እንደሆኑ ምን ላይ እንዳሉ ሕዝቡ ምን ላይ እንዳለ እያወቀ አይደለም። ስለዚህ እያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ክፍል፣ የሕጻናት ክፍል፣ የሽማግሌዎች ክፍል፣ የዘመናዊ ምሁራን ክፍል የመሳሰሉት ኖሮት ትምህርተ ወንጌሉን በትክክል አውቆ ለቤተ

ክርስቲያንም ለሀገርም የሚበጅ ሰው መሆን አለበት። የሰበካ ጉባኤው አደረጃጀት ምእመናንን ለመያዝ አቅም የሌለው፣ ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ ሰዎች መከራ ሲደርስባት መከላከል የማያስችል አደረጃጀት ከሌለው ሌላ አደረጃጀት እንዲፈጠር አባቶቻችን ጳጳሳትን ማማከር ይገባናል። መምህራን፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ ጳጳሳት፣ የደብር አስተዳዳሪዎች ደግሞ እንደ ምንደኛ (ቅጥረኛ) ሳይሆን እንደ ልጅ ሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን አገልግሏት።

ባህላችን

ባህል ክፍል 1

ሥርዓተ ምግብ

እግዚአብሔር በቸርነቱ በዚህ ምድር እስካለን ድረስ ለሥጋ መቆያ ምግብን ሠጥቶናል። የአበላልም ግን ሥርዓት አለው። ይህ ሁላችንንም የሚመለከት ነው። 3 ነገሮችን እንመልከት። እኒህም ቅድመ በሊዕ፣ ጊዜ በሊዕ፣ እና ድኅረ በሊዕ ናቸው። እነርሱን እንመልከት። ከመብላታችን በፊት ምግብን የሚሰጥ እግዚአብሔርን ስለሰጠን "አባታችን ሆይን እስከመጨረሻው" ብለን ልናመሰግነው ይገባል። በኦሪት ዘመን ሊቀ ነቢያት ሙሴ ለሕዝቡ ውሃ ሲያፈልቅላቸው ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ አመስግኖ ይሰጣቸው ነበር። አንድ ቀን ግን ሕዝቡ አስቆጥቶት ስመ እግዚአብሔርን ሳይጠራ እንኩ ጠጡ ብሎ ሰጣቸው። በዚያ ምክንያት ታላቅ መቅሰፍት መጣ። ሙሴም በዚህ ምክንያት ምድረ ርስት ከነዓንን በሩቅ አይቶ ሳይገባባት ቀርቷል። ስለዚህ እኛም ወሀቤ ኩሉ ሁሉን ሰጪ እግዚአብሔርን ከመብላታችን በፊት እናመስግነው። ሳያመሰግኑ መብላት ሰይጣናዊ እንጃ ስልጣኔ አይደለም። በምንበላት ጊዜ መጥነን ልንበላ ይገባናል። በቅዱሳት መጻሕፍት ከሦስቱ አርእስተ ኃጣውዕ አንዱ ስስት ነው። በስስት አንዷን እንጆራ አንድ ጉራሽ አድርጎ በእጅ እየሰገሰጉ መብላት አይገባም። መጥነን ተረጋግተን ለቁመተ ሥጋ ያህል ልንበላ ይገባል። ሌላው ቅዱሳን ሊቃውንት በየሐተታቸው ያስቀመጡት ከሰው ፊት እጃችንን ሰደን ልንበላ አይገባም። ከምግብ በኋላ ደግሞ የበላነውን የጤና እንዲያደርግልን ፈጣሪን "ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ። ለአብ ምስጋና ይገባል ለወልድም ምስጋና ይገባል ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል የሚለውም እስከመጨረሻው ልንደግማው ይገባል። ከዚህ በኋላ በእንተ አቡነ አቢብ ይቅር በለን ብለን ሦስት ጉራሽ እንበላለን። (ይህን የምናደርግበት ምክንያት እግዚአብሔር ለታላቁ ጻድቅና ሰማእት አቡነ አቢብ ቃል ኪዳን ስለገባላቸው ነው። አቡነ አቢብ ማለት የክርስቶስን ስቅለት እያሰቡ ሰውነታቸውን በስለት እየወጉ ይኖሩ የነበሩ ናቸው)። በቀጣይ ክፍል ስለ አለባበስ የምጽፍ ይሆናል። ያው ባህላችንን እየረሳን መሠረቱ ላልታወቀ ባዕድ ባህል ራሳችንን አሳልፈን እየሰጠን ስለሆነ ወደኛው ውድ ባህል እንድንመለስ በማለት አስቤ ነው።

ባህል ክፍል 2

የአለባበስ ሥርዓት

በነገራችን ላይ ለምን እንደምትለብሱ አስባችሁት ታውቃላችሁ? ብዙ ምክንያቶች አሉት።

አንደኛው ራስን ከፀሐይ፣ ከውርጭ እና ከመሳሰሉት ራስን ለመከላከል ነው። ነገር ግን የአለባበስ ሥርዓት ላይ የምናጠብቅበት ዋናው ፍሬ ምክንያት ከዝሙት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው። በአለባበስ ዙሪያ ቅዱስ መጽሐፍ በተለያዩ ቦታዎች ተናግሯል። የካህናት አለባበስ፣ የሴቶች አለባበስ ተገልጿል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሴቶች ግን ራሳቸውን ይከናነቡ ለምን አለ? ሙሴስ ሴት የወንድን ወንድ የሴትን ልብስ አይልበስ ለምን አለ። የወንድ ልብስ ምንድን ነው? የሴት ልብስስ ምንድን ነው? የሚለውን እንመልከት። በማየት የሚመጣ ፍትወት ከሴት ይልቅ በወንድ ይጸናል። በመስማት የሚመጣ ፍትወት ደግሞ ከወንድ ይልቅ በሴት ይጸናል። ወንድ ልጅ የሴትን ገላ ካየ ፍትወት ይነሳበታል። ፍትወት ከተነሳበት ደግሞ "ወደ ሴት አይቶ የተመኘ አመነዘረ" የሚለውን የፈጣሪ ሕግ ይሸራል። ሕግ ከሻረ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት አይገባም። በነገራችን ላይ ይህን ሰው መንግሥተ ሰማያት እንዳይገባ መሠናክል የሆነችው ሴትም መሰናክል ስለሆነች መንግሥተ ሰማያት አትገባም። ከታናናሾቹ ያሰናከለ ወዮለት ብሎ ጌታ የተናገረው ለዚያ ነው። ስለዚህ ብፁዕ ጳውሎስ ሴቶች ራሳቸውን ይከናነቡ አለ። ከዚህ ላይ ሴቶች የወንዶችን ልብስ አይልበሱ ሲል ሴቶች ሊለብሱት የሚገባ ልብስ ተብሎ የተዘረዘረ ነገር የለም። ነገር ግን ከሐዋርያው ጳውሎስ ንግግር እንደተረዳነው ተገልብቦ "መከናነብ" ራስን ላለማሳየት ነው። ስለዚህ ሴቶች በየትኛውም መስፈርት አካላቸውን የሚያንጸባርቅ ልብስ መልበስ የለባቸውም። ሰፋ ያለ ከአካላቸው ያልተጠበቀ ልብስ ሊለብሱ ይገባል። ወንድ ልጅም እንዲሁ ሴቶችን ለፍትወት የማይጋብዝ ልብስ ሊለብስ ይገባል። ልብስ የምንለብሰው እንዲያምርብን እና ሌሎችን በፍትወት ለመሳብ ብለን ከሆነ ልብሱ ምንም ይሁን ምን ሥርዓት አልባ አለባበስ ይባላል። በዋናነት ልብሱን የለበስንበትን ምክንያት እንመርምረው። ሌላው የወንድ ልብስ እና የሴት ልብስ የሚለውን በትውፊት እናውቀዋለን። እንደ ኢትዮጵያ ባህል ሴት ልጅ ዘረፍረፍ ያለ ሰፋ ያለ ቀሚስ ነው የምትለብስ "ቀሚስ በመልበሷም የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ትፈጽማለች"። በነገራችን ላይ ጥብቅ ያለ ቀሚስም ያው ሥርዓት አልባ አለባበስ ነው። ምክንያቱም የአካልን ቅርጽ ያሳያልና። ሌላው የካህናት አለባበስ በኦሪት ዘሌዋውያን በሰፊው ተገልጿል። ካህናት ጠምጥመው ልዩ ልብስ የሚለብሱት ስለ ክብረ ወንጌል ነው። እንጂ ካህናትም ይህንን አለባበሳቸውን ለተርእዮ ካዋሉት እንዲለብሱ አይፈቀድም። ቅዱስ መጽሐፍ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ ይላልና። በእኛ አለባበስ ምክንያት በሌላው ፈተና ከሆንን ሌላውንም ራሳችንንም ወደ ገሐነም የምንልክ ስለምንሆን ወዮልን። ኢትዮጵያዊ መጽሐፋዊ ትውፊታዊ አለባበስ ይኑረን። የባዕድ ሀገር አለባበስ ተገዥ አንሁን። የእኛ ባህል አብዛኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት። ቅዱስዮሐንስ አፈወርቅ ከጉልበቱ በላይ ጸምር ወይም አጎዛ ብቻ ይለብስ ነበር። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም በዚህ ምድር ስትኖር ሁለት ቀሚስ ልብስ ብቻ ነው የነበራት። ዮሐንስ ወንጌላዊውን ስታርፍ በአንዱ ቀሚሴ ገንዘኝ። አንዱን ቀሚሴን ደግሞ ለአንዲት ድሃ ሥጥልኝ ብለዋለች። ልብስ ለክዲነ ዕርቃን ነው። ታላላቁ ቅዱሳንም መንገድ ላይ የሆነ ልብስ ይጥሉና ሰው ንቆ ከተወው አንስተው ይለብሱታል። አንስቶ ይዞት ከሄደ ግን ለሰው ይማርካል ማለት ነው ስለዚህ ፈጣሪየ ከመልበስ አዳነኝ ብለው ይደሰቱ ነበር። ሥለዚህ ዕርቃናችንን የሚሸፍን ጥብቅ ያላለ ሰፋ ያለ ልብስ እንልበስ።ይህ ነው ኢትዮጵያዊው አለባበስ።

ባህል ክፍል 3

አነጋገር

በኢትዮጵያ ባህል የብልግና ቃላት አይነገሩም። ለሰሚው ምቾትን የሚሰጡ ቃላት ተመርጠው ይነገራሉ እንጂ።አሁን አሁን ግን የብልግና ቃላትን መናገር እንደ ሥልጣኔ እየተቆጠረ ነው። አንዴ ሰብሰብ ብለን እያወራን አንድ ጓደኛችን ከመካከላችን ተነሳ። እንዴ ወዴት ልትሄድ ነው? አልነው። እርሱም "አርዮስ ወደሞተበት" ብሎ መለሰልን። አርዮስ የሞተ ሽንት ቤት አንጀቱ ተዘርግፎ ነው። እና ወደ ሽንት ቤት እየሄድኩ ነው ሲለን ነው። ሽንት ቤት ከማለት ይልቅ "አርዮስ የሞተበት" የሚለው ቃል ለሚሰማው የተመቸ ነው። የብልግና ቃላት በአደባባይ የማይነገሩበት ምክንያት ምንድን ነው ካልን በዋናነት የገዘሙትን ነገር የሚናገሩ ከሆኑ ሰውን በገዘሙት ሐሳብ እንዳንጥለው ነው። በዚህ ምክንያት የጎልዮ በደል በድሎ መንግሥተ ሰማያትን እንዳያጣ ነው። ቅኔ ቤትም በሌላም ቦታ ጸያፍ የሚባሉ ቃላትን እንዳንጠቀም የምንከለከልበት ምክንያት ንግግራችንን ሁሉም ቢሰማው የሚመች እንዲሆን ታስቦ ነው። ንግግራችን ሰሚውን አካል እንዳይቆጣ እንዳይናደድ እንዳያዝን እንዳይሳደብ እንዳይበሳጭ እና በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር ሕግ የሚያወጡ ነገሮችን እንዳያስብ እንዳይናገር የሚያደርግ መሆን አለበት። ቢቻል ሰውን ወደ መልካም ሐሳብ የሚመሩ ንግግሮችን ልንናገር ይገባል። ባህል ሰፊ ነው። ንግግርን አለባበስን አመጋገብን ያካተተ ነው። ጴጥሮስ የጌታ ተከታይ መሆኑ የታወቀ በአነጋገሩ በአለባበሱ በአጠቃላይ ሁኔታው ነው። በሥርዓት መናገር ምንድን ነው? የሚለውን እንይ። እንግዲህ በንግግር ጊዜ ሦስት መሠረታዊ ነገሮች ይታሰባሉ። እነዚህም፦

- ፩ ሞገሥ ቃል
- ፪ ሳዕስዐ አፍ
- ፫ ጣዕመ ነገር

ናቸው። እያንዳንዳቸውን በተወሰነ መልኩ እንያቸው። ንግግራችን ሌላውን አስቆጥቶ ወደ በደል የሚያደርስ እንዳይሆን መጠንቀቅ። ቁጥብ መሆን ሌላው ሀሳቡን ተናግሮ እንዲጨርስ በጥሞና ማዳመጥ። ፈጠን ፈጠን አለማለት። ጉድይ ተኮር መሆን። ሰውየውን ወደ መልካምነት የሚመራ መሆን አለበት። ለመስማት የፈጠንክ ለመናገር የዘገየህ ሁን። ጌታችን በዚህ ምድር ሲያስተምር ከእርጋታው የተነሳ የተቀጠቀጠ ሸንበቆ አይሰብርም ተብሎ ተነግሮለታል። ክልብ ክልብ እያሉ መናገር ደንበኛ ባህል አይደለም። መጀመሪያ የሌላውን ሰው ሀሳብ በትክክል መረዳት ከዚያ የመናገሪያ ጊዜ ሲሰጥህ መናገር ይገባል። ታድያ ስትናገር ንግግርህ ሞገሰ ቃል ጣዕመ ነገር እና ሳዕስዐ አፍ ሊኖርህ ይገባል። ሞገሥ ቃል አስወድዶ መናገር ነው። የሚሰማህ አካል እንድትናገር የሚጓጓ መሆን አለበት። እንጂ ስልችት እስኪለውና መቼ ነው የሚጨርስ እስክትባል መሆን የለበትም። ጣዕመ ነገር አስወድደህ ስትናገር ፍሬ የሌለው ነገር መናገር የለብህም። ነገርህ የማይረሳና ሰማዕያኑ ሁልጊዜም እያስታወሱት ወደ መልካም ምግባር ወደብ የሚያደርሳቸው መርከብ መሆን አለበት። ሳዕስዓ አፍ ንግግርህ የተከናወነ ቅደም ተከተል ያለው ያልተድበሰበሰ ጥርት ያለ መሆን አለበት። በጠቅላላው ንግግራችን ረጋ ያለ፣ ፈጠን ፈጠን

ያላለ፣ ነገረ ዘርቅ የሌለበት። ለሰሚው የሚመቹ፣ የማያስጠሉ፣ የተመረጡ ቃላትን ልንናገር ይገባናል። ሌላው ንግግራችን ትዕቢት የሌለበት ትሕትናን የተሞላ መሆን አለበት። ልባቸው የገዘፈ እና የደነደነ ሰዎችን በሐሜት ላይ በተመሰረተ መረጃ ሳይሆን በተረጋገጠ ማስረጃ ተመሥርተን ሳንፈራ መገሠጽ ይገባል። ያዘኑትን ደግሞ ልናጽናናቸው ይገባናል።

ባህል ክፍል 4

በዓል አከባበር

አሁን አሁን በዓላትን ምክንያት በማድረግ ጭፈራ፣ የዘፈን ኮንሰርት፣ የመጠጥ መርሐ ግብር እና የመሳሰሉትን እያየን ነው። እኒህ ነገሮች ምንም ዓይነት ትውፊታዊና ሃይማኖታዊ መሠረት የሌላቸው እና እንዳውም በተቃራኒ መልካም እሴቶቻችንን የሚያጠፉ ነገሮች ናቸው። በዓላት በረከት ማግኛ ዕለታት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስም ግበሩ በዓለ በትፍሥሕት በዓልን በደስታ አድርጉ ይላል። ፈጣሪ ለእኛ በረከት ሊሰጠን ፈልጎ ሰንበትን አክብሩ፣ በዓላትን አክብሩ እያለ ነግሮናል። አሁን አሁን ግን ከባህላችንም ከሃይማኖታችንም ያፈነገጠ ነገር እየተደረገ ይገኛል። በዓላት በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ እንድናገኝባቸው ከፈጣሪ የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው። እንዲህ ሆነው ሳለ ግን በዓላትን ምክንያት አድርጎ አብዝቶ ጠጥቶ መስከር፣ መጨፈር፣ መዝፈን፣ ሆ ማለት ፣ የዘፈን ኮንሰርት ማዘጋጀት የመሳሰሉት በረከትን የሚያሳጡ ገንዘብን፣ ክብርን፣ የሚያሳጡ ነገሮች ናቸው። በኦሪት እንደምናገኘው ሰለጸአድ የተባለ ሰው በበዓል ቀን እንጨት ለቅሞ እግዚአብሔር ሞት ፈርዶበታል። እኛስ በበዓል ቀን ለበዓሉ የማይገባ ሥራን ብንሠራ ምን ይፈረድብናል ካልከኝ ያው ዘላለማዊ ሞት ነዋ ብየ እመልስልሀለሁ። በአንድ ቀን ጭፈራ ዘላለማዊ ሞትን መሸመት እንዳይሆንብን በዓላትን እንደ ሥርዓቱ እናክብራቸው።ታዲያ በበዓላት ቀን ምን ምን እያደረግን እንዋል ካላችሁኝ

- ፩ ቤተክርስቲያን መሄድ
- ፪ ፈጣሪን ማመስገን
- ፫ መንፈሳዊ ትምህርት መማር
- ፬ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ
- ፭ ንሥሓ ገብቶ መቁረብ

ቅዱሳት በዓላትን ስናከብር ብዙ ጊዜ ነጫጭ የባህል ልብሶችን እንለብሳለን። ለዚህም አብነት አለን። በጌታችን ትንሳኤ ጊዜ ሁለት መላእክት ነጫጭ ልብስ ለብሰው ታይተዋል። እኛም ይህንን መሠረት ይዘን ነጭ ነጭ ለብሰን እንውላለን ማለት ነው። ስለዚህ በእኛ መጽሐፋዊና ትውፊታዊ ባህል መሠረት በበዓላት ቀን ጠጥቶ መስከር ሳይሆን ንሥሓ ገብቶ መቁረብ፣ የጭፈራ ኮንሰርት አዘጋጅቶ ሲጨፍሩ ማደር ሳይሆን ቤተክርስቲያን ሄዶ ማኅሌት ቆሞ ማደር ነው። ይህ ነው ኢትዮጵያዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ባህላችን።

ባህል ክፍል 5

ሌሎች ምርጥ ባህሎቻችን

ተጋግዞ በደቦ መሥራት፣ የተቸገረን ሰው በእድር ማገዝ ታላላቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትነት ያላቸው ባህሎቻችን ናቸው። በኢትዮጵያችን "ዘበልአ ባሕቲቶ ይመውት ባሕቲቶ" ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል የሚል ስነ ቃልም አለን። ይህ ማለት የጎረቤታችን ደስታው ደስታችን ኀዘኑ ኀዘናችን መሆኑን ያመለክታል። ኢትዮጵያዊው ባህል ግለኝነት(Individualism) ወይም ራስ ወዳድነት አይደለም። ሁሉም ሰው ስለ ሁሉ ያስባሉ። አንዱ ስለሁሉም ያስባል። ሁሉም ደግሞ ስለ አንዱ ያስባሉ። (ይህ ውድ እሴታችን አሁን በዘረኞች እየተሸረሸረ ስለሆነ ልንታገለው ይገባናል)። ሕገ እግዚአብሔር መጨረሻው ፍቅር ነው። የሌላውን ደስታ ደስታ ማድረግ እና የሌላውን ኀዘን ኀዘን ማድረግ አንደኛው የፍቅር መገለጫ ነው። በሌላው የደረሰው ችግር ሁሉ በራሳችን እንደደረሰ አስበን መፍትሔ መፈለግ ነው ኢትዮጵያዊው እና ኦርጅናሉ ባህላችን።

ባህል ክፍል 6

የሥራ ባህላችን

ኢትዮጵያዊው ገበሬ ሌሊት 10 ሰዓት ላይ ይነሳና በሬዎቹን ፈትቶ ጭድ ወይም ገለባ አብልቶ ሞፈሩን እርፉን ቀንበሩን አዘጋጅቶ፣ ውዳሴ ማርያሙን ደግሞ፣ ቁርሱን በልቶ ጠዋት 12 ሰዓት ወደ እርሻው ማሳ ሄዶ ይጠምዳል። ልክ ማታ 12 ሰዓት ይጨርሳል። አርሶ አምርቶ ይኽው ከተሜውንም ገጠሬውንም እየመገበ ይኖራል። ካመረተው እህልም ለቤተ ክርስቲያን አሥራቱን በኩራቱን አውጥቶ ይሰጣል። እርሱ እንዲህ ሲያደርግ ሚስቲቱ ደግሞ አክርማ ወይም ሰበዝ ቀጭታ፣ ጥጥ አባዝታ፣ ያንን ጥጥ በእንዝርት ፈትላ፣ ለባሏም ለልጆቿም ለእርሷም ልብስ ታዘጋጃለች። ሰበዙን ደግሞ በወስፌ ሰፍታ መሶበ ወርቅ፣ ወስከንባያ ሠርታ ለቤቷ አስፈላጊ እቃወችን ታሟላለች፣ ለቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሙዳይ አዘጋጅታ ትሰጣለች። በዚህ ጠንካራ የሥራ ባህላችን ሙሉ በሙሉ ከጥገኝነት ወጥተን ቀጥታ ከተፈጥሮ የሚያስፈልገንን እናሟላ ነበር። አሁን ግን በራሳችን የምንሰራው ነገር እየጠፋ ፍላጎቶቻችን በሌላው አቅርቦት ላይ የተመሠረቱ እየሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ምናልባት ወደፊት ለአደገኛ ባርነት ያመቻቸናል። ስለዚህ ሀገር በቀል እውቀቶችን ባንተዋቸው እና ብናሳድጋቸው መልካም ነው። የሥራ ባህላችን እንዲህ ያለ ጠንካራ ነበር። አሁን አሁን ግን የእኛን የድሮውን ትተን የውጭ ፍለጋ መሄዳችን የባርነት መጀመሪያ ይመስላልና እንመለስ።

ማንበብ እውቀት

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ደረቅ ሐዲስ እየተባለ የሚጠራውን ትንቢተ ኢሳይያስ ሲያነብ እንደነበረ የሐዋ.8 ተገልጿል። ንግሥተ ሳባም የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት እስራኤል ድረስ ሄዳለች። ኢትዮጵያውያን ለጥበብ የተለየ ፍቅር ነበረን። ለትምህርት እና ለእውቀትም ልዩ ክብር ነበረን። የአብነት ተማሪው ባዶ እጁን ከቤተሰቡ ተለይቶ ሩቅ ሀገር ሄዶ ሲማር ምግቡን ልብሱን ችለው የሚያስተምሩት የሄደበት ሀገር ሰዎች ናቸው። ሌላው ፈሪሀ እግዚአብሔር ባህላችን ነበረ።

አንድ ሰው በአንዱ በደል ሲያደርስበት እግዚአብሔርን ፈርቼ ነው እንጂ... ይለዋል። እግዚአብሔርን ፈርቶ ማድረግ ከሚችሉት ወንጀል መከልከል ድንቅ ባህል ነው። የራሳችን ባህል የሆኑትን ነገሮች መሠረታቸውን ሳናውቅ በባዕድ ትምህርት ሚዛንነት ብቻ ማጣጣልና መናቅ አይገባም። ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

ነገረ ክርስቶስ

አጨብጫቢነት አይጠቅምም። የድንግል ማርያም ሥዕል በምክር ቤቱ ስለተሰቀለ "ሩሲያ ሃይማኖቷ የቀና ነው" የሚል ጨዋ እያየሁ ነው። ካቶሊኮችም የማርያምን ሥዕል ይይዛሉ። ሃይማኖታቸው የቀና ነው ማለት ነው እንዴ? ሩሲያን በሀገራዊ ጉዳይ ያላትን አሠራር አርአያ ልናደርገው እንችላለን። በሃይማኖት ግን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተቃራኒ ናት። ክርስቶስን የሚጠራ ሁሉ ክርስቲያን አይደለም። ክርስቶስን ፕሮቴስታንቱ ይጠራዋል። እኛ እንጠራዋለን፣ ካቶሊኮች ይጠሩታል፣ በዓለም ላይ ወደ 50000 የሚጠጉ እምነቶች ይጠሩታል። ማቴ.24፣5 "እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ" የክርስቶስን ማንነት አለማወቅ ትልቅ በደል ነው። ራሱብክርስቶስ ሐዋርያትን ሰብስቦ የጠየቃቸው ስለማንነቱ ነው። ማቴ.16፣15 "እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ" የሚል ጥያቄ ነበር። ነቢይ ነው ያሉት ነበሩ። አሁንም እንዲህ የሚሉ ሙስሊሞች አሉ። ከነቢያት አንዱ ነህ ያሉትም ነበሩ። ልክ ፕሮቴስታንቶች አሁንም ከአብ ያነሰ አምላክ ነው እንደሚሉት ያሉ ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ግን "አንተ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው" አንተ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎታል ትክክለኛው መልስ ይህ ነው። ክርስቶስን ነቢይ ሰው ብቻ የሚሉት ሁሉ ክርስቶስን ቢጠሩትም የእኛ ክርስቶስ እነርሱ የሚጠሩት ክርስቶስ አይደለም። ሩሲያ ኬልቄዶናዊ ናት። በካቶሊክ እምነትም ለ600 ዓመታት ያህል ቆይታለች። በ1054 ዓ.ም አካባቢ ካቶሊክ መንፈስቅዱስን ዘሠረጸ እም አብ ወወልድ ስትል። ክልኤ ባሕርይብየሚለውን ትምህርት ይዛ። ዘሠረጸ እም ወልድ የሚለውን ተቃውማ ምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተብላ ተገንጥላለች። ግሪክ፣ ሩሲያ፣ ዩክሬን ሌሎችም ሀገሮች ኦርቶዶክስ ይባሉ እንጂብኦርቶዶክስ አይደሉም። ሩሲያ መንፈስ ቅዱስን ዘሠረጸ እም አብ በማለቷ ከእኛ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጋር ይመሳሰላሉ። ሁለት ባሕርይ በማለታቸው ደግሞ ከካቶሊኮች ጋር አንድ ናቸው። ስለዚህ ግማሽ ጣዖት ግማሽ ታቦት ይሉሀል እነርሱ ናቸው። ሀገራዊ አንድነታቸው ዓለማቀፋዊ ተሳትፏቸው ግን አስደናቂ ነው። ማንኛውም ዓለም በዚህ ጉዳይ አርአያ ሊያደርጋቸው ይችላል። ክርስቶስ ዮሐ.6፣18 "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ" ብሎ አስተምሯል። ዮሐ.11፣25 "ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ" ብሏል። ሕይወት የሆነው ክርስቶስ ያላት ደግሞ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ብቻ ናት። አምስቱ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ላይ ነው ክርስቶስ ያለው። ግብጽ፣ ሶርያ፣ ሕንድ፣ ኢትዮጵያ እና አርማንያ። ኤርትራም እንዲሁ ከአኃት አንዲ ናት። ጥራዝ ነጠቅነት አይጠቅምም። ሃይማኖትን ጠንቅቆ አለማወቅ ከሕይወት ያርቃል። ኢየሱስ ክርስቶስን የሚወዱ ለማስመሰል "ኢየሱሴ" የሚሉ ሰዎች የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ሰዎች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አብርሃም እና ስለ ሣራ። ዘፍ.17፣5 ከእንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ አብርሃም ተብሎ ይጠራ እንጂ የሚስትህም የሦራ ሥም ሦራ ተብሎ አይጠራ ሣራ ትባል እንጂ ብሎ ነገሮታል። አስተውል "ሦ" ፊደል "ሣ" እንድትሆን ፊደልን ጠንቅቆ የተናገረ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ታዲያ

ስሙንም "ኢየሱስ" ትይዋለሽ ሉቃ.1፣31 ይላል እንጂ "ኢየሱሴ" ትይዋለሽ አይልም። ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው። ስለዚህ የፈጣሪን ሥም አቆላመጥን እያላችሁ አታበላሹ። አንዳንዱማ ስብከት ላይ ሳይቀር "ተክልየ፣ ሀብትየ፣ አብርሽ" ወዘተ ይላል። እንደ ቆይ አብራም ያለው አብርሃም ይሁን እያለን እኛ ምን ነክቶን ነው አብርሽ የምንለው?! ይሄ ብልግና ነው እንጂ የመውደድ ምልክት አይደለም። ደብረ ሊባኖስ ለአንድ ዓመት ያህል ተቀምጫለሁ አብዛኛው ምእመን "ተክልየ፣ ሀብትየ" ሲል የፍቅር መግለጫው ነው። የተማረው አካል ግን ይህንን ማሳወቅና በትክክል ስማቸው እንዲጠራ ቢያደርግ መልካም ነው። ሕዝቡ በፍቅር እንጂ በተንኮል አይደለም እንዲያንየሚለው።ገድላቸውም በቸገረው ጊዜ ስምህን የጠራ ረድኤት ያገኛል ሲል "ተክልየ" የሚለውን ሥም ሳይሆን "ተክለ ሃይማኖት" የሚለውን ሥም ነው። ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣ አማኑኤል፣ መድኃኔዓለም፣ ዳግማዊ አዳም የተባለው ያው የአንዱ ክርስቶስ ስሞች ናቸው። አማኑኤል እግዚአብሔር ምስሌነ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነንማለት ነው። መድኃኔዓለም የዓለም መድኃኒት ዓለምን በመስቀል ተሰቅሎ ያዳነ ማለት ነው። ክርስቶስ ማለት ቅቡዕ፣ መሢሕ ማለት ነው። ሰው የሆነ አምላክ አምላክ የሆነ ሰው ነው ክርስቶስ። በጊዜ ተዋሕዶ የቃል ገንዘብ ለሥጋ ሆኗልና ይህንን ለማመልከት "ቅቡዕ" እንለዋለን። ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው። "1ኛ ቆሮ.15፥45 "ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ሰው ሆነ። ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ" ስለሚል ዳግማዊ አዳም ይባላል። ይህንን የኢትዮጵያ የቁጥር ሊቃውንት ለእያንዳንዱ ፊደል ቁጥር አለው ይሉና አዳም የሚለው እና ኢየሱስ የሚለው ሁለቱም ሲደመሩ 144 ይመጣሉና ዳግማዊ መባሉ ሌላው ሌላው ምሥጢር እንዳለ ሆኖ በዚህም ያስኬዳል ይላሉ። የፊደላት ቁጥሩ

- ሀ=1
- ለ=2
- ሐ=3
- መ=4
- ሠ=5
- ረ=6
- ሰ=7
- ቀ=8
- በ=9
- ተ=10
- ነ=20

- ኀ=30
- ለ=40
- ከ=50
- ወ=60
- ዐ=70
- ዘ=80
- የ=90
- ደ=100
- ገ=200
- ጠ=300
- ጰ=400
- ጸ=500
- ፀ=600
- ፈ=700
- ፐ=800

ሸ፣ ጀ፣ ጨ፣ ገ፣ ቸ፣ ጨ፣ ቨ፣ ኸ፣ የግእዝ ፊደላት አይደሉም። የአማርኛ ፊደላት ናቸው። በዚህ መሠረት አዳም የሚለው አ=40፣ ዳ=100፣ ም=4 ሲደመሩ 144 ይሆናል። ኢየሱስ የሚለው ደግሞ ኢ=40; የ=90; ሱ=7; ስ=7 ሲደመሩ 144 ይመጣል። ስለዚህ ይህም አንዱ ነው ይላሉ። በትርጓሜ መጻሕፍት ግን ዳግማዊ አዳም መባሉ አንደኛው የአዳምን ሥጋ ለብሷልና ነው። ሌላኛው የቀደመው አዳም በደል ለሁሉ ደርሶ ነበርና። በኋለኛው አዳምብበክርስቶስ ቤዛነት በሐዲስ ተፈጥሮ መፈጠራችንን ለመግለጽ ያንን ቀዳሚ ብሎ ይህንን ዳግማዊ ይለዋል። ክርስቶስ የሚለው የግሪክ ቃል በዐረብኛ መሲሕ በግእዝ ቅቡዕ ማለት ነው። ትርጉሙ የተቀባ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ነገሥታት ሲሾሙና ንዋየ ቅድሳት በተለየ ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት እንዲሰጡ ይቀቡ ነበር። ክርስቶስ ማለት የተቀባ ማለት ነው ሲባል ግን አስቀድሞ ክብር የሌለው ነው ማለት አይደለም። ክርስቶስ ማለት ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ቢሆን የወጣለት የሥጋዌ ሥም ነው። ሁለት አካል የተባሉትም አካለ ሥጋ እና አካለ ቃል ናቸው። ሁለት ባሕርይ የተባሉትም ባሕርየ ቃል እና ባሕርየ ሥጋ ናቸው። በተዋሕዶ ግን ምንታዌ (Dualism) ስለጠፋ አንዱ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ይባላል እንጂ ሁለት አይባልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስን ከሙታን መካከል

አብ አስነሳው። መንፈስ ቅዱስ አስነሳው። በራሱ ሥልጣን ተነሳ የሚሉ ቃላት ይገኛሉ። ወተንሣእኩ በሥልጣነ ባሕቲትየ እንዲል። በዚህ ጊዜ አስነሽነትን ለሦስቱም አካላት አድሎ የተናገረው ሦስቱ አካላት በባሕርይ አንድ ስለሆኑ ነው። ክርስቶስ በራሱ ሥልጣን ተነሳ የሚለውና የተቀባ የሚለው በምሥጢርብተመሳሳይ ናቸው። የተቀባ የከበረ ስንል በጊዜ ተዋሕዶ ቃል ለሥጋ ክብር ሆኖታልና ቅቡዕ ተብሏል። ቃልም ሥጋን ሆኗልና ወልደ እጓለ እመሕያው ተብሏል። በዚህ አግባብ የተነገረ ነው። እንጂ ቅባቶች እንደሚሉት መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ሆኖት የከበረ አይደለም።ትክክለኛው ትምህርት ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ የሚለው ነው።ቃል ሥጋ ሥጋ ቃል ሲሆን ማለትም ቅዱስ ቄርሎስ እንዳለው "እንቲኣሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲኣሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል" እንዲል። በጊዜ ተዋሕዶ የቃል ገንዘብ የሆነው ሁሉ የሥጋ ገንዘብ ሆኗል። የሥጋ ገንዘብ የሆነው ሁሉ ደግሞ የቃል ገንዘብ ሆኗል። ይኽውም በተዋሕዶ በተዐቅቦ ነው። ቃል ጥንቱንም ክቡር ወይም ቅቡዕ ነው። ይህንን የቃል ገንዘብ በጊዜ ተዋሕዶ ሥጋ ገንዘቡ አድርጎታልና ቅቡዕ ክቡር ተብሏል። ክርስቶስ የባሕርይ ንጉሥ ነው። በዚህ ዙሪያ በሰፊው እመለስበታለሁ። የፍቅር ትክክለኛ ትርጉም ይህ ነው። አዳም በበደለ መድኃኔዓለም ተሰቀለ። በሰይጣን እስር ቤት የምንኖር እኛን በመስቀል ተሰቅሎ ነጻ አወጣን። የነጻነታችን ምክንያት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለ5500 ዓመታት ያህል በጨለማ እንኖር ነበር። የዓለም ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ ጨለማውን አጠፋልን። ኑ በብርሃኑ እንመላለስ። ረኃበ ነፍስ እንዳያገኘን ሥጋውን ደሙን ሰጥቶ ብሉ ጠጡ አለን። በዚች ምድር ሲመላለስ ከእኔ ተማሩ ብሎናል። ብፁዕ ጳውሎስም ተመሰሉ ኪያየ በከመ አነ እትሜሰሎ ለክርስቶስ ብሎናል። የጽድቅን መንገድ አሳይቶናል። 40 ቀን በገዳመ ቆሮንቶስ ጾሞ እንድንጾምብአመለከተን። ዓለምን ሲያስቧት ታደክማለች። ሁሉ ነገሯ ይሰለቻል። የማይሰለች ነገር የላትም። ሁል ጊዜ አዲስ፣ ሁል ጊዜ ጥዑም፣ ሁል ጊዜ የሚናፍቅ የማይጠገብ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስን የምንወድ ከሆነ ትእዛዙን እንጠብቅ። ሕጉ የፍቅር ሕግ ነውና። እኛን ከክፉ ነገር ሁሉ ለመጠበቅ እንዲያገለግለን የተሰጠን ነውና። ሰማዕታት ለክርስቶስ ያላቸውን ፍቅር እስከ ሞት በመታመን ገለጡ። መነኮሳት ከገዳም ገዳም ከዋሻ ዋሻ በመንከራተት ገለጡ። ሊቃውንት ኃይለ ቃል ጠቅሰው ፍቅሩን ለማስተማር ተጉ። ከሁሉ ነገር በፊት መድኃኒታችንን፣ ብርሃናችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እናስቀድም። ሌላው ከዚህ በኋላ የሚታሰብ መሆን አለበት። በዚህ ምድር እያለ ሰውን መንቀፍም ሰውን ማወደስም ሁለቱም ጣዖት አምልኮ ናቸው። ስለራስህ እንጂ ስለሌላው ሰው ብዙ የማታውቀው ነገር ይኖርሀል። ሁሉን አዋቂ ክርስቶስ ነው። እና ፍርድን ለእርሱ እንስጥ። ከእኛ የሚጠበቀው የሚጠበቅብንን እና ድርሻችንን መወጣት ነው። ጳውሎሳዊ እና ይሁዳዊ ጠባይ ያላቸው ሰዎች ይኖራሉ። ጳውሎሳዊ ጠባይ ያላቸው ሰዎች መጀመሪያ አሳዳጅ ይሆኑና በኋላ ግን ስለ ፈጣሪ ብለው እውነትን እያስተማሩ የሚሰደዱ ይሆናሉ። ይሁዳዊ ጠባይ ያላቸው ደግሞ መጀመርያ ከተመረጡት ከሐዋርያት መካከል ይሆኑና ቆይተው ግን ፈጣሪን የሚክዱ ናቸው። ለቅዱሳን የጸጋ ክብርና ምስጋናን የምናመሰግናቸው ተጋድሏቸውን ጨርሰው ከሄዱ በኋላ በሕይወት ዘመናቸው ያከናወኗቸውን መልካም ሥራዎች በማገናዘብ ነው። በሕይወተ ሥጋ ላለ ሰው ምስጋና መስጠት ግን ለውርደት ይዳርጋል። ቀድመው ይሁዳን ያደነቁ ሰዎች ጌታን ለብር ብሎ በሸጠው ጊዜ ማፈራቸው አይቀርም። በሕይወተ ሥጋ ያለ ሰውን መንቀፍ፣ መስደብና ማዋረድም ለውርደት ይዳርጋል። ቀድመው

ጳውሎስን የሰደቡ እና የነቀፉ ሰዎች ምርጥ ዕቃ ብርሃነ ዓለም ጳውሎስ መመለሱን ሲያዩ ማፈራቸው አይቀርምና። የሰው ልጅ የተፈጠረው ስለ ሰው ሊያወራ አይደለም። የራሱን ድርሻ ሠርቶ ለማለፍ ነው። አርዓያ የሚደረጉ እንደነ ቅዱስ ጳውሎስ ዓይነት ቅዱሳን ሲኖሩ ስለ እነርሱ በሰፊው እንነጋገራለን። ምክንያቱም የዚህን ዓለም ፈተና አልፈው በአሸናፊነት የሕይወት ጉዟቸውን ስላጠናቀቁ የእነርሱ ሕይወት ለእኛ ሕይወት ጥሩ ምሳሌ ስለሚሆነን ነው። በሕይወተ ሥጋ ያለ ሰው ግን ገና ተጋድሎውን አልጨረሰም። ስለዚህ ተጋድሎውን ጨርሶ አሸናፊ ሳይሆን ማመስገንም መስደብም ልክ አይደለም። ላልሞተ ሰው ጥሩ ተጋድሎ እያደረገ ካለ እስከ ሕይወት ፍጻሜው ጥሩ ተጋድሎ እንዲጋደል እንጸልይለታለን። በሰይጣን እየተሸነፈ ተጋድሎው ፈተና የበዛበት ከሆነም ፈተናውን ተወጥቶ አሸናፊ ይሆን ዘንድ እንጸልይለታለን። ከዚህ አልፎ በሕይወተ ሥጋ ያለን ሰው ማወደስ ግን አሸቃባጭነት ነው። ብዙው ሰው የአጥማቂ፣ የዲያቆን፣ የሰባኪ፣ የመምህር፣ የጳጳስ፣ የፓለቲከኛ አጨብጫቢ ነው። በዚህም ምክንያት የሚያመልከውን ክርስቶስ ረስቶ ለሚያጨበጭብለት ሰው ጥብቅና ሲቆም ይውላል። ስለዚያ ሰው ብሎ ሌላውን ሲሳደብ ይውላል። አምልኮ ጣዖት ይሉሀል ይህ ነው። ሁሉንም ሰው እኩል እናከብራለን። ነገር ግን አይሳሳትም ብለን የምንሚገትለት ሰው ካለ እንደ ፈጣሪ እያየነው ስለሆነ ባዕድ አምልኮ ይሆናል። መጽሐፍ ሰውን ሁሉ እንድንወድ አዞናል። ከሰው ልጅ መልካም ሥራውን አብነት እያደረግን ክፉ ሥራውን ደግሞ እየተውን እንሄዳለን እንጂ ሁልጊዜ ፍጹም ስለሆነ እገሌ ያለው በሙሉ ልክ ነው ማለት ልክ አይደለም። የእኛ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ፍጹም የማይሳሳት ሁል ጊዜም እውነት የሆነ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ የሰው መንጋ ከመሆን የአንድ የክርስቶስ በጎች እንሁን። እረኛችን ጠባቂያችን ክርስቶስ ቸር ነውና። አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር እንዳለን። የሕይወት መንገድ፣ የሕይወት እንጀራ ጌታችን መድኃኒተችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከሰይጣን ግዞት ነጻ ያወጣን ነጻ አውጪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱን እንመስለው ዘንድ ከእኔ ተማሩ ብሎናል። የሰው ልጅ ክፉም መልካምም ሊሰራ ይችላል። ከማንኛውም ሰው ጋር መልካሙን እየያዝን ክፉውን እየተውን በፍቅር እንቀጥላለን። የሕይወታችን ምክንያት፣ የመኖራችን ምክንያት እግዚአብሔር ነው። ብንበድል እንኳ ንሥሐ ገብተን ሥጋውን ደሙን ተቀብለን ከበደል የምንነጻበትን መንገድ ያመቻቸልን ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ብዙ ቅዱሳን ቀድሞ በድለው ነበር። ግን ንሥሓ ገብተው ዳግም ፈጣሪን ሳይበድሉ በመልካም ሥራ ስለጸኑ በፈጣሪ ዘንድ ተመስግነዋል። ብዙ ኃጥዓንም በድለው ነበር። ነገር ግን ንሥሓ ሳይገቡ ቀርተው ለዘለዓለም ኩነኔ ተዳርገዋል። ስለዚህ ንሥሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን እንቀበል። በፈጣሪ ሕግ እንመራ። የሕይወት ሙሉ ትርጉም የሚኖራት በእግዚአብሔር ሕግ ስንመራ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን እናንብብ። ነገረ መስቀሉን ማታም ጠዋትም ቀንም በማንኛውም ሰዓት እናስታውሰው። ፍቅረ ክርስቶስን በልባችን እንሳለው። በትሑት ስብእና ውስጥ ታላቅነት ግዘፍ ነስቶ ይታያል። በተሳዳቢ እና በትእቢተኛ ስብእና ውስጥ ደግሞ ትንሽነት ጎልቶ ይታያል። በትዕግሥተኛ እና በሰውን አክባሪ ሰው ውስጥ ብልህነት እና አዋቂነት ይታያሉ። ሌላውን ሰው በመናቅ፣ በመጥላት፣ በማዋረድ ውስጥ ደግሞ ድንቁርና እና የጭንቅላት ባዶነት ይታያል። የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ልዑልነት፣ ሁሉን ቻይነት፣ ፍቅሩን፣ መጋቢነቱን የተረዳነው ዝቅ ብሎ የሐዋርያቱን እግር በማጠቡ፣ በትዕግስቱ፣ የንሥሓ እድሜን

በመስጠቱ እና በመሳሰሉት ግብረ ባሕርያቱ ነው። በዲያብሎስ ያየነው ግን ከዚህ የተለየ ነው። ከሁሉ በላይ ተፈጥሮ ከሁሉ አነሰ። አመስግኑኝ በማለቱ ወራዳነቱ ታየ።በሸፍጥ በሽንገላ ብዙዎችን ከጎኑ በማሰለፉ ደካማነቱ ተረጋገጠ። ክርስቶስ እውነት ነው። ሣህል ወርትእ ተራከባ እንዲሉ ክርስቶስ ቅን ነው። ክርስቲያናዊው ሰው በሥራው ሴራ የሌለበት ቅን ሰው ነው። ክርስቲያናዊው ሰው የራሱን ፍላጎት ለማሟላት ብቻ የሚኖር አይደለም። ሌላውንም ሰው እንደራሱ ስለሚወድ የሌላው ሰው መልካም ፍላጎት እንዲሳካ የድርሻውን የሚወጣ ነው። ስቅለተ ክርስቶስ ይህንን ነው የሚያስተምረን አዳም መዳንን ይፈልግ ነበር። አዳም እንዲድን ደግሞ ክርስቶስ ተሰቀለለት። ክርስቶስ ለሰው ልጆች ድኅነት እስከ መሰቀል ደርሷል። እንግዲህ የእኛ ድርሻ ብቻ ይቀራል። እኛም ለማንኛውም ሰው ልናደርግለት የሚገባንን የድርሻችንን እንወጣ። በትግራይ እና በአማራ ክልል ባለው ውጥረት ምክንያት እንዲሁም በሌሎች ክልሎች ብዙ ምእመናን አካላዊ እና ስነልቡናዊ መንገላታቶች እየደረሱባቸው እንደሆነ በየሚዲያው እያየን ነው። መቼም ጦርነትን አይተነዋል። በጦርነቱ ያተረፈ አካል የለም። ፖለቲከኞች ግን አሁንም ያለፈው አልፏል። ወደፊቱ ላይ ጥሩ መስማማት ላይ ብትደርሱ መልካም ነበር። ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ሲያስተምር "ተራራው ዝቅ ይበል፣ ሸለቆው ይሙላ" ብሎ ነበር። በሁለቱም ወገን ያላችሁ ፖለቲከኞች ፍላጎታችሁ እንደ ተራራ የገዘፈ ከሆነ ትንሽ ወረድ በሉ። ፍላጎታችሁ እንደ ሸለቆ በጣም የወረደ ከሆነም ሞላ ይበልና ምቹ ሁኔታን ፍጠሩ። በእናንተ ምክንያት የእግዚአብሔር መልክ የሆነ ሰው አይሙት። መቼም በታሪክም ብዙ የተለያዩ ጦርነቶች ተደርገዋል። ከእልህ እና እኔ ያልኩት ካልሆነ ከሚል አስተሳሰብ ወጥተን ትላንት ላይ ተቸክለን ከምንቀር ነገውን አስበን ብንሰራ መልካም ነው። ክርስቶስ የሕይወት መንገድ ሆኖ ያስተማረን ምሕረትን ይቅርታን ሰላምን ነው። የሚታረቁ ብዑዓን ናቸው ነው የተባለው። ያለፈው ይብቃ። ሃይማኖት ክርስቶስን ማመን ለክርስቶስ መታመን ነው። የመጀመሪያው እና ዋናው ታዛዥነትን ለክርስቶስ ማድረግ ነው። የሃይማኖት ተቀዳሚ ሥራ ለፈጣሪ መታዘዝ ነው። የፈጣሪን ትእዛዝ የሚቃረን ትእዛዝ ሲመጣ እምቢ ብሎ ሰማእት መሆን ነው። ሰማእት መሆንም ከፈራን መሰደድ ነው። በሃይማኖት አንድ የሆኑ ሰዎች ቢጣሉ እንኳ ከአባትም በላይ አባት የሆነው እግዚአብሔርን አስበው ሊታረቁ ይገባል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ገብረ ሰላመ በመስቀሉ" ተብሏል። ጌታ እስከ መሰቀል ደርሶ የሞተለትን ሰው እኛ በምድራዊና ጅል ምክንያት እንዲጠፋ ባናደርገው መልካም ነው። ለሰው ልጅ ክብር ይኑረን። ፈጣሪ ያከበረውን እኛ ማዋረድ የለብንም። ክርስቶስ በመወለዱ፣ በመሰቀሉ ሰውና መላእክትን ሕዝብና አሕዛብን አንድ አድርጓል። ከራሱ ጋር አስታረቀን። ወደ እርሱ እንቀርብ ዘንድ እርሱ ወደኛ መጣ። የሰው ልጅ ሕብረታዊ ነው። ከሕብረታዊነቱ ወጥቶ ወደ ግላዊነት መጥበብ የለበትም። አንዳንዶች ጎጣቸውን ወይም ክልላቸውን የጠቀሙ እየመሰላቸው ከሰፊዋ ሀገር ይለዩታል። ነገር ግን ዲያብሎስ በራሱ ነገድ ብቻ ተወስኖ ቢለይ ራሱ ይጎዳ እንዳው እንጂ ሕብረቱ አይጎዳም። አልተጎዳም። አርቀው በማያስቡ ፖለቲከኞች ምክንያት ሀገር ስትበጠበጥ ማየት ለሕሊና እረፍት አይሰጥም። ከሀገራዊ ስሜት ወደ ክልላዊ ስሜት ከክልላዊ ስሜት ወደ አውራጃዊ ስሜት ከአውራጃዊ ስሜት ወደ ቀበሌያዊ ስሜት ሕዝቡን ሲያወርዱት የጠቀሙት ይመስላቸዋል። ክርስቲያኖች አንድ አባት ኢየሱስ ክርስቶስ አለን። ስለዚህ ሊያስታርቀን የሚገባ በዚህ በኩል ያለው ቤተሰባዊነት ነው እንጂ ከዚህ የበለጠ አስታራቂ ነገር የለም። እያንዳንዱ

ድርጊታችንን ፈጣሪ ይወደዋል ወይ የሚለውን ማሰብ ብንችል መልካም ነው። ክርስትና በእምነት ከማይመስሉን ሰዎች ጋርም በሰላም መኖርን ያስተምራል። በአንድ ሀገር ውስጥ የምንኖር ማናችንም ሰዎች ተስማምተን መኖር ይገባናል። ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ነው እንጂ የእስራኤል ብቻ አይደለም። በመስቀሉ ሰውን ሁሉ ነው ያዳነ። ከዚህ በኋላ የሰው ድርሻ ነው። ክርስቶስ ወደ ታላቅ ልዕልና አውጥቶናል። ከዚህ ልዕልና ወርደን ወደ ራስ ወዳድነትና ወደ ዘረኝነት ማምራት የለብንም። መሪዎች ከእልህ ውጡና ለሕዝቡ የሚበጅ እና የሚመጥን ሥራ ሥሩ። ጦርነቱንም አየነው። የትኛውም ወገን አላተረፈም። ሁሉም ወገን ብዙ ነገር እንዳጣ ነው የምናስተውለው። በእውነት እና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ውይይት አድርጉ። ሳጥናኤል (ዲያብሎስ) በሕብረታዊነቱ ጊዜ ክብሩ ከፍ ያለ ነበር። ከሕብረታዊነት ወጥቶ ወደ ግላዊነት ሲወርድ ክብሩ ቀነሰ። ከሞላ ጎደል በተፈጥሮ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎት ተመሳሳይ ነው።ብሰው እንደ ሰው ማሰብ ሲያቅተው እንደ አህጉር ያስባል። እንደ አህጉር ማሰብ ሲያቅተው እንደ ሀገር ያስባል። እንደ ሀገር ማሰብ ሲያቅተው እንደ ክልል ያስባል። እንደ ክልል ማሰብ ሲያቅተው እንደ ወረዳ ያስባል። እንደ ወረዳ ማሰብ ሲያቅተው እንደ ቀበሌ ያስባል። እንደ ቀበሌ ማሰብ ሲያቅተው እንደ ቤተሰብ ማሰብ ይጀምራል። እንደ ቤተሰብ ማሰብ ሲያቅተው ለራሱ ብቻ ያስባል። የዘረኝነት እና የመከፋፈል ሂደቱ ይህ ነው። እግዚአብሔር ከልብ ከተጸጸትን ይቅር ባይ ስለሆነ ባለፈው በደላችን ተጸጽተን ንሥሓ እንግባ። ንሥሓ ከገባን በኋላም ወደ ቀደመ ጥፋታችን ላለመመለስ መጣር አለብን። ያለፈው ዘመን ይበቃናል። ሮሜ.12፣17 "ለማንም ስለክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ። በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ"። ክፋትን ማሸነፍ የሚቻለው በክፋት ሳይሆን በመልካም ነው። ክርስቶስ ክፋትን በመልካም ሥራ እንዴት ማሸነፍ እንዳለብን አስተምሮናል። ክፋትን በክፋት ለማሸነፍ መሞከር ሌላ ክፋትን ይወልዳል። ሁልጊዜም ተስፋችንን በእግዚአብሔር እናድርግ። እግዚአብሔር እስካለ ድረስ ተስፋ መቁረጥ ብሎ ነገር የለም። ተስፋ የሚያስቆርጥ ከፈጣሪ ጋር መጣላት ብቻ ነው። ከእርሱ ጋር እንዳንጣላ እንጠንቀቅ። በገሐነም እንዳይፈርድብን ሕጉን ትእዛዙን እንጠብቅ። በሌሎች ምድራዊ ጉዳዮች ግን ተስፋ መቁረጥ አይገባም። ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ነጻነትን አጎናጽፎናል። ከዚህ በኋላ በኃጢዓት ባርነት መያዝ የለብንም። ለዚህ ደግሞ ነገረ መስቀሉን ሁልጊዜም በጥልቀት እናስበው። ኃጢኣትን ይቅር የሚል እግዚአብሔር ነው። ታድያ በሉቃ 23፣34 "ኢየሱስም አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ" የሚለው ትርጉሙ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ይነሳል። ከዚህ ጥቅስ ላይ # አብ # ይቅር ባይ እንደሆነ ይነግረናል። አንዳንዶች ግን ከዚህ ላይ የተገለጠውን የአብን ይቅር ባይነት ተቀብለው ወልድ ይቅር አይልም ወደማለት ድምዳሜ ይሄዳሉ። ትልቅ ስህተት ነው። ከዚህ ጥቅስ ላይ አብ ይቅር እንደሚል ተናገረ እንጂ ወልድ ይቅር እንደማይል የሚናገር ምንም ነገር የለውም።ሌላ ቦታ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ.9፣6 "ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢኣትን ያስተሰርይ ዘንድ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ በዚያን ጊዜ ሽባውን ተነሳ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው" ተብሏል። በዚህ ጊዜ አይሁድ ኃጢኣትን ይቅር የሚል እግዚአብሔር ብቻ ነው ብለው አንጎራጉረው ነበር። ሐሳባቸው ትክክል ነው ኃጢኣትን ይቅር የሚል እግዚአብሔር ብቻ ነው። የአይሁድ ትልቁ ችግራቸው ራሱ ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን አለመረዳታቸው ነበር። ስለዚህ በዚህኛው ጥቅስ የኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር ባይነት ሲጠቀስ በላይኛው ጥቅስ ደግሞ የአብ

ይቅር ባይነት ተገልጧል። ይህንን የመሰለ በክርስቶስ ትንሣኤ ዙሪያም የተነገረ ቃል አለ።ማቴ.27፣63 ላይ ራሱ ክርስቶስ የራሱ አስነሽ እንደሆነ ተነግሯል። በሌላ ቦታ ደግሞ የሐዋ. ሥራ 4፣ 10 ኢየሱስ ክርስቶስን ያስነሳው ሌላ እንደሆነ ተናግሯል። በትረጓሜያችን ወተንሣእኩ በሥልጣነ ባሕቲትየ በራሴ ሥልጣን ተነሳሁ ቢል አብ አንሥኦ አብ አስነሳው ቢል እና መንፈስ ቅዱስ አንሥኦ ቢል ምንም ዓይነት ተቃርኖ የለም። ሁሉም አንድ ነው። በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት አካላዊ ግብር እና ሥልጣናዊ ግብር የሚባል አለ። አካላዊ ግብር የሚባለው የአብ መውለድ ማሥረጽ የወልድ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ነው። ይህ ግብር አይፋለስም። ሥልጣናዊ ግብር የሚባለው ግን ሦስቱ አካላት በኩነታት ተገናዝበው አንዲት ባሕርይ አላቸው። የዚህች አንዲት ባሕርይ ደግሞ አንዲት ፈቃድ አንዲት ሥምረት አንዲት ክሂል አንዲት ግብረ ባሕርይ አላት። ፈጣሪነት፣ አምላክነት፣ ገዢነት፣ ኃያልነት፣ ይቅር ባይነት እና የመሳሰሉት ግብሮች የአንዲት ባሕርይ ግብራተ ባሕርይ ስለሆኑ ሦስቱም ይጠሩበታል። አብ አምላክ ይባላል። ወልድም አምላክ ይባላል። ሮሜ.9፥5፣ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ይባላል። ይህንን ስላልን ግን ሦስት አምላክ አንልም። በአንዲት ግብረ ባሕርይ ሦስቱም ተጠሩባት ይባላል እንጂ። ለዚያ ነው ጠንቅቀን በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ካልን በኋላ አሐዱ አምላክ እንላለን እንጂ ሠለስቱ አማልክት አንልም። ነቢየ እግዚአብሔር ምልክአም (ሙሴ) በኦሪት ዘዳግም ስማዕ እስራኤል አሐዱ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ብሎ ተናግሯልና። መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ ሲናገሩ ስለ ሰውነቱ በሚናገሩበት ጊዜ መለኮትነቱን ዘንግተው አይደለም። ስለ መለኮትነቱ(ቃልነቱ) ሲናገሩ ሰውነቱን ዘንግተው አይደለም። ለዚያ ነው ሊቁ ቦ ዘይቤላ መጻሕፍት በእንተ ትስብእቱ ወቦ ዘይቤላ መጻሕፍት በእንተ መለኮቱ ወቦ ዘይቤላ መጻሕፍት በእንተ ትስብእቱ ወበእንተ መለኮቱ ኅቡረ ተብሎ የተገለጠው። ሌላው ጌታችን በመስቀል ላይ ሆኖ አባት የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ያለን ለእኛ አብነት ለመሆን ነው። ጠላትህን ውደድ ብሎ አስተምሮ ነበርና። እርሱም ተመሀሩ እምኔየ እስመ የዋሕ አነ ብሏልና። በተግባር ይቅር ባይነትን ሲያስተምረን ነው። ሊቀ ዲያቆኑ ቅዱስ እስጢፋኖስን ይህን አብነት አድርጎ በድንጋይ ለሚወግሩት ሰዎች ይቅርታን ለምኗል። ሙስሊሞችም፣ ፕሮቴስታንቶችም፣ ካቶሊኮችም ካላችሁ በነጻነት እስከመጨረሻው መወያየት እንችላለን ኑ። ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረ በኋላም ዓለምን ለማዳን ሥጋ ሰብእን የተዋሐደ አምላክ ነው። ሮሜ ፱፣፭ "ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ ተወለደ እርሱም ከሁሉ በላይ የሆነ የዘላለም ቡሩክ አምላክ ነው" እንዲል። ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከመፈጠሯ በፊት ነበረ ስንል ግን በቃል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ዮሐ. ፩፣፩ "በመጀመሪያ ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ ሁሉም በእርሱ ሆነ ከሆነውም ሁሉ ያለ እርሱ ምንም የሆነ የለም" ። መሐመዳውያን ፈጣሪ በአካል አንድ ነው ቃሉ የዚያው የአንዱ ስለሆነ ልክ እንደሰው ነው ለምሳሌ እኛ አንድ ሰው ነን። ነገር ግን ቃል አለን። ቃል ስላለን ብለን ግንብበአካል ሁለት ነን አንልም ይላሉ። ነገር ግን ሰውና ፈጣሪ በባሕርይ የተለዩ ስለሆኑ የእግዚአብሔር ቃል እንደሰው ቃል ስላልሆነ ቃሉን የአካሉ ዝርው ንባብ አድርገን መውሰድ አንችልም። ምክንያቱም ለምሳሌ የእኛን የሰዎችን ቃል ብንመለከት እኛ ሰው ነን። ቃላችን ግን የሰው እንጂ ሰው አይደለም። በመሆኑም ቃላችን ሌላ አካል እኛ ሌላ አካል ተብለን ሁለት አንባልም። አንድ አካል እንባላለን እንጂ። የእግዚአብሔር ግን ከዚህ የተለየ ነው። ምክንያቱም

በመጀመሪያ ቃል ነበር ካለ በኋላ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ካለ በኋላ ቃል ራሱ እግዚአብሔር ነው ይላል። እኛ ሰው ነን። ቃላችን ግን ሰው አይደለም። ስለ እግዚአብሔር ስንናገር ግን አብ እግዚአብሔር ነው ቃሉም እግዚአብሔር ነው። በዚህ ቃል መሐመዳውያን ይረታሉ። ሌላው ኢየሱስ ክርስቶስን ነቢይ ነው። ፍጡር ብቻ ነው ይሉታል። ነገር ግን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐ. ፰፣፶፰ "አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ" ብሏል። በሌላ ቦታ ደግሞ በማቴ. ፩፣፩ "የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ" ብሎ በመናገር ኢየሱስ ክርስቶስ የአብርሃም ልጅ መሆኑን ተናገረ። ሁለቱም ልክ ነው። በቃል ከአብርሃም በፊት የነበረ የአብርሃም ፈጣሪ በሥጋ ከአብርሃም ዘር ተወለደ ስለዚህም የአብርሃም ልጅ ተባለ። ጥያቄ ለመሐመዳውያን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰው ብቻ ነው ፈጣሪ አይደለም ካላችሁ ከአባቱ በፊት የነበረ ልጅ አለ ወይ?። የለም በፍጡራን ዘንድ ከአባቱ ቀድሞ የነበረ ልጅ የለም። የዘካርያስ ልጅ መጥምቁ ዮሐንስ በሥጋ በመወለድ ከክርስቶስ ይቀድማል። ሉቃ. ፩፣፭-፸ ይመልከቱ። ነገር ግን ዮሐንስ ስለጌታ ሲናገር ዮሐ. ፩፣፳፯ "እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ ነገር ግን እናንተ የምታውቁት በመካከላችሁ ቆሟል ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት የነበረው" ብሎታል። ይህም በቃል ይቀድመዋል። ድንግል ማርያም የወለደችው ዮሐ. ፩፣፫ ላይ ሁሉ በእርሱ ሆነ የተባለውን እሷን የፈጠራትን ወልድን ነው። አፈ በረከት ኤፍሬም በሃይ. አበ. ፶፯፣፪ "ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው እርሱም እናቱን ፈጠረ" ይላል። አስቀድሞ "ቃል" የተባለውና ሰማይና ምድርን አጠቃላይ ፍጥረታትን የፈጠረው እርሱ አዳም በተሳሳተ ጊዜ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሀለሁ ብሎት ነበርና ሰውን ለማዳን ረቂቅ ኃያል በሁሉ ቦታ ያለ አምላክ በሁሉ ቦታ መኖሩን ሳይለቅ በድንግል ማኅፀን ተወሰነ፣ ረቂቁ እና የማይታየው የማይዳሰሰው አምላክ አለመዳሰስን ርቀትን እንደያዘ መዳሰስን ግዘፍን ገንዘብ አደረገ። ኃያሉ አምላክ ኃያልነቱን ሳይለቅ ድኩም ሥጋን ተዋሐደ።መዝ. 101፣27 አንተ ግን ያው አንተ ነህ ስለተባለ እግዚአብሔር መለዋወጥ የለበትምና። ለእኛ ያለውን ፍቅር ለእኛ ለማሳየት እኛ ባጠፋን እርሱ ስለእኛ ተሰቀለ። በኪሩቤል ጀርባ እንዳለ በተዋሐደው ሥጋ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ታየ። አዳም እፀ በለስን ከበላ የሞት ሞት እንደሚፈረድበት ዘፍ. ፪፣፲፯ "ከእርሱ (እፀበለስ) በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ብሎታል። አዳም ግን ትእዛዙን ተላልፎ ዘፍ. ፫፣፮ ላይ እንደተጻፈው በላ። ስለዚህ አዳም ሞተ ነፍስ አገኘው ከእግዚአብሔር ተለየ። ስለዚህ እንዴት አዳነው ስንል ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሀለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ገባለት። ገላ. ፬፣፬ "ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ" ይላል። ስለዚህ አዳምን ለማዳንብእግዚአብሔርነቱን ሳይለቅ ሰው ሆኖ ተወለደ። ሳይሰቀል ማዳን አይችልም ወይ ከተባለ ይችላል። ታድያ ለምን ተሰቀለ ከተባለ እኛ ልንከፍለው የሚገባንን እዳ እርሱ ከፍሎ ሲያድነን ለእርሱ ያለን ፍቅር ይጸና ዘንድ ነው። እንዲሁ ሳይሰቀል ኃጢአታችንን ይቅር አይለንም ነበር ወይ ከተባለ ደግሞ እግዚአብሔር በእውነት ፈራጅ ነው። መዝ. 50፣6 "እግዚአብሔር ፈራጅ ነው" እንዲል። አዳም ላጠፋው ጥፋት ፍርዱ ሞት ነው። እግዚአብሔር መሓሪም ስለሆነ የአዳምን እዳ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ከፈለለት። ታድያ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው? ሰው ብቻ ነውን ቢሉ መልሳችን አምላክም ሰውም የሆነ ነው እንላለን። "ሥጋ ረከበ ዕበየ ወብዙኀ ፍድፍድና በተሳትፎቱ ወበተዋሕዶቱ ምስለ ቃል" ቅዱስ አትናቴዎስ ሃይ. አበ. ፴፩፣፲፰። ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ የምንለው

ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርገን ነው። ቅዱስ አትናቴዎስ በግልጽ እንደተናገረው "ሥጋ ረከበ ዕበየ ወብዙኀ ፍድፍድና በተሳትፎቱ ወበተዋሕዶቱ ምስለ ቃል" ሥጋ ከቃል ጋር የአካል የባሕርይ ተዋሕዶን በመዋሐዱ ፍጹም የሆነ የአምላክነትን ክብር አገኘ። እንዘ መዋቲ ውእቱ ኢኮነ መዋቲ። የሚሞት ሲሆን የማይሞት ሆነ። ወእንዘ ሥጋዊ ኮነ መንፈሳዌ። ግዙፍ ሲሆን ረቂቅ ሆነ። ወእንዘ ምድራዊ ውእቱ ናሁ ኀለፈ አናቅጸ ሰማየ ሰማያት። ውሱን ሲሆን እነሆ ምሉዕ ሆነ። በጠቅላለው ሥጋ በተዋሕዶ የቃልን ገንዘብ ገንዘብ አደረገ። የቃል ገንዘብ ደግሞ ንጉሥነት፣ ክቡርነት፣ ከሃሌ ኩሉነት፣ ፈጣሪነት እና በጠቅላላው የአምላክነት ሥራዎች ናቸው። ሥጋ እኒህን ሁሉ ያገኘው በተዋሕዶ ነው። የቃል ገንዘብ ሁሉ የሥጋ ገንዘብ የሆነው በተዋሕዶ ነው። ቃል ቅድመ ዓለምም ክቡር ነው። ሁልጊዜም ክቡር ነው። ይህንን ክቡርነት (ቅብዕነት) ሥጋ ያገኘው ደግሞ ከቃል ጋር በመዋሐዱ ነው እንጂ "መንፈስቅዱስ ቅብዕ" ስለሆነው አይደለም። ለሥግው ቃል መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ሆነው ማለት ክሕደት ነው። ቅዱሳን ሊቃውንቱ እነ ቅዱስ ቄርሎስ፣ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ እነ ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱሳን ሐዋርያት ከአምላካቸው ተምረው ያስተማሩት ትምህርት "ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ" መክበሩን ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌል "ቃል ሥጋ ኮነ" ብሏል። ሥጋን የተዋሐደ በተለየ አካሉ ወልድ ነው። ተዋሐደ ማለት ደግሞ አንድ ሆነ ማለት ነው። በጊዜ ተዋሕዶ ደግሞ የቃል ገንዘብ ለሥጋ፣ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆኗል። ቅድመ ተዋሕዶ የቃል ገንዘብ የነበረውን አምላክነት ሥጋ ገንዘቡ ያደረገው በተዋሕዶ ነው። ሲዋሐድም ሲቀባም አንድ ጊዜ ነው። አንዳንድ ከኃድያን እንደሚሉት ከተዋሕዶ በኋላ ከበረ አንልም። በጊዜ ተዋሕዶ ከበረ እንላለን እንጂ። በጊዜ ተዋሕዶ ግዙፉ ሥጋ ግዙፍነቱን ሳይለቅ ረቂቅ ሆነ። ረቂቁ ቃል ርቀቱን ሳይለቅ ግዙፍ ሆነ። ውሱኑ ሥጋ ውሱንነቱን ሳይለቅ ምሉዕ ነው። ምሉዑ ቃል ምልዐቱን ሳይለቅ በማኅፀን ተወሰነ። ቅዱስ ቄርሎስ እንደተናገረው እንቲኣሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲኣሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል። ሥጋ ሰውነቱን ሳይለቅ አምላክ ሆነ። አምላክም አምላክነቱን ሳይለቅ ሰው ሆነ። በተዐቅቦ ያለመለወጥ፣ ያለመቀላቀል፣ ያለመጠፋፋት አንድ ሆነ። ሃይ. አበ. ፴፮፣፸፬ "ኢያፍለሰ ፈጣሪ መለኮቶ ለከዊነ ፍጡር። ወኢደምሰሰ ትስብእቶ ፍጡረ ለከዊነ ፈጣሪ" እንዲል። በተዋሕዶ ምንታዌ (ሁለትነት) ጠፍቷል። ተዋሕዶ በተዐቅቦ ደገኛው ትምህርታችን ነው።

በእንተ መንፈስቅዱስ

ከካቶሊካውያን ጋር ከምንለያይባቸው አስተምህሮዎች አንዱ በመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ዙሪያ ነው። እነርሱ መንፈስ ቅዱስን ከአብም ከወልድም ሠረጸ ይላሉ። እኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን ከአብ የሠረጸ ነው እንለለን። የምሥራቅ ኦርቶዶክሶች ማለትም ግሪክ፣ ሩስያ፣ ዩክሬን የመሳሰሉት ከካቶሊክ የሚለዩበትም በዚህ ነው። ክርስቶስን አንድ አካል ሁለት ባሕርይ በማለት ግን ከካቶሊኮች ጋር ይመሳሰላሉ። አምስቱ አኃት አብያተ ክርስቲያን ግን ከካቶሊኮችም ከግሪክና ከሩስያ ኦርቶዶክሶችም እንለያለን። ይኸውም ክርስቶስን ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በማለታችን ነው። ይኸውም ያለመጠፋፋት፣ ያለመለወጥ፣ ያለመቀላቀል በተዐቅቦ ነው። ዮሐ. ፲፮፣፳፮ "እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ጰራቅሊጦስ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል" ተብሎ እንደተገለጸው መንፈስቅዱስ ከአብ የሠረጸ ነው እንላለን። በሉቃ. ፲፣፳፪ "መንፈስ ቅዱስም የርግብ መልክ

ባለው አካል አምሳል በእርሱ ላይ ወረደ" ተብሎ እንደተገለጸው መንፈስቅዱስ አካላዊ ነው እንጂ ዝርው አይደለም። መንፈስ ቅዱስን ፍጡር ብሎ የተነሣው ከሓዲ መቅዶንዮስ ሲሆን በሁለተኛውብዓለማቀፋዊ ጉባኤ ማለትም በጉባኤ ቍስጥንጥንያ ተወግሏል። መንፈስቅዱስ የአብ የወልድ አካላዊ ሕይወታቸው ነው። ጸራቅሊጦስ ማለት

√ ከሣቲ___ምሥጢር ገላጭ

√ ናዛዚ___የሚያረጋጋ

√ መንጽሒ__ከኃጢአት የሚያነጻ

√ መጽንዒ__በመልካም ሥራ የሚያጸና

√ መስተፍሥሒ__በጸጋ የሚያስደስት

ማለት ነው። ማንኛውም ክርስቲያን የራሱን አስተምህሮ አውቆ ከሌሎች ቤተ እምነቶች የሚለይበትን ማወቅ አለበት። ከካቶሊኮች የምንለየው እነርሱ:-

√ክርስቶስን አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ማለታቸው

√ መንፈስ ቅዱስን ከአብም ከወልድም የሠረጸ በማለታቸው ነው። እኛ ደግሞ ክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንለዋለን። መንፈስ ቅዱስን ደግሞ ከአብ የሠረጸ እንለዋለን። ከሩሲያ፣ ከግሪክ (ከምሥራቅ ኦርቶዶክሶች) ጋር የምንለያየው ደግሞ እነርሱ ክርስቶስን አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ሲሉ እኛ ግን አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንላለን። የምሥራቅ ኦርቶዶክሶች ከካቶሊክ የተለዩት በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። ኦርቶዶክስ የተባሉትም ከዚያ በኋላ ነው። መንፈስ ቅዱስን ከአብ የሠረጸ በማለት ከእኛ ጋር አንድ ናቸው። አኃት አብያተ ክርስቲያን ማለትም የግብጽ፣ የኢትዮጵያ፣ የአርመን፣ የህንድ፣ የሶርያ አብያተ ክርስቲያን ግን ኦርቶዶክስ የሚለውን ስያሜ ያገኙት አርዮስ ከተወገዘ በኋላ በ325 ዓ. ም ነው። "ዘአንገሠ ለሥጋ አዳም በመንፈስቅዱስ ወረሰዮ ቅዱሰ ወማሕየዊ። ዘለብሶ ለአዳም መዋቲ" ሃይ. አበ. ፪፣፭-፮ (እልመስጦአግያ)። ብዙ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት ረቂቁን የእግዚአብሔር ሥራ ለመንፈስ ቅዱስ አድለው ይናገራሉ። ይህ ስለሆነ ግን ግብሩ የመንፈስቅዱስ ብቻ እንዳይመስለን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በባሕርያዊ ግብር የአንዱ ስም ቢጠቀስም ሁሉም ይጠሩበታልና። ለምሳሌ ዮሐ. ፫፣፭ "እውነት እውነት እልሃለሁ ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስቅዱስ ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" የሚለውን ብንመለከት ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ስላለ የምንወለደው ከመንፈስ ቅዱስ እና ከውሃ ብቻ እንደሆነ ልናስብ አይገባም። በጸጋ የምንወለደው ከሦስቱም ማለትም ከአብ ከወልድ ከመንፈስቅዱስ ነውና። ይኽውም አንድ ልደት ነው። በማቴ. ፳፰፣፲፱ "እንግዲህ ሂዱና በአብ በወልድና በመንፈስቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ" እንዲል የምንጠመቀው ጥምቀት በሦስቱም ስም ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ብቻ የምንወለድ ከአብ ከወልድ የማንወለድ እንዳልሆነ አስተውል። በተጨማሪም ማቴ. ፭፣፲፰ "ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች" የሚለውን ብንመለከት "በመንፈስ ቅዱስ" ፀንሳ ተገኘች ማለት ከሕገ ተፈጥሮ ከኅሊና በላይ በሆነ በእግዚአብሔር ድንቅ

ሥራ ያለ ወንድ ዘር መፅነሷን ይነግረናል። በግብረ መንፈስቅዱስ ፀንሳ ተገኘች ባለው በግብረ አብ በግብረ ወልድ ቢል ምሥጢሩ አንድ ነው። ሃይ.አበ. ፪፣፭ን በመጥቀስ ቅባቶች መንፈስቅዱስ ቅብዕ ማለት ነው ብለው በአእምሮ ሳይሆን በጉልበት ለመተርጎም ይሞክራሉ። ቅዱሳት መጻሕፍትን በመሰለኝ እና ወደራስ ሐሳብ በመጠምዘዝ መተርጎም ትልቅ ጉዳትን ያመጣል። እንደ አርዮስ ጫፍ ይዘው ተነሥተው ተሳሳቱ እንጂ ዝቅ ብለው ቁጥር ስድስት ላይ ቢመለከቱ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ማን እንደሆነ ያውቁ ነበር። እነሆ ትርጓሜው እንደሚከተለው ነው። "ዘአንገሠ ለሥጋ አዳም በመንፈስ ቅዱስ። የአዳምን ሥጋ በመንፈስ ቅዱስ አዋሐጅነት የተዋሐደው እርሱ ነው። አንድም የአዳምን ሥጋ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ተዋሕዶ የባሕርይ ንጉሥ ያደረገው እርሱ ነው። ወረሰዮ ቅዱሰ ወማሕየዊ። ክቡር ወሀቤ ሕይወት አምላክ ያደረገው እርሱ ነው ካለ በኋላ ዘለብሶ ለአዳም መዋቲ። መዋቲ ሥጋን የተዋሐደው እርሱ ነው ይላል። "ዘ" በቂ ሆና ለወልድ እንደተነገረ አስተውል። ይህንንም የሚያሳውቀን ቀጥሎ ዘለብሶ (የተዋሐደው) ያለው ቃል ነው። የተዋሐደው በተለየ አካሉ ወልድ ነውና። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛው ትርጓሜ ይህ ነው። ዘአንገሠ ለሥጋ አዳም በመንፈስ ቅዱስ ሲልም በመንፈስ ቅዱስ አዋሐጅነት የተዋሐደው እርሱ ነው ስላለ አዋሐጅ መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንዳልሆነ ልብ አድርግ። በማዋሐድ፣ በመፍጠር፣ በመግዛት፣ በመንግሥት፣ በክብር ሦስቱ አካላት አንድ ናቸውና በአንዲት ግብረ ባሕርይ መሆኑን አስተውል። በረቂቅ ግብሩ የአዳምን ሥጋ የተዋሐደ ወልድ መሆኑን ይነግረናል እንጂ ከዚህ የሃይማኖተ አበው ክፍል እንዳያችሁት መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ የሚል ምንም ዓይነት ጽሑፍ የለውም።

ቅድስት ሥላሴ

"መቅድመ ኵሉ ንሰብክ ሥላሴ ዕሩየ ወቅዱሰ ዘውእቶሙ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" ሃይ. አበ። ከሁሉ አስቀድመን ልዩ ሦስት የሚሆኑ አብ ወልድ መንፈስቅዱስን እንሰብካለን። ቅድስት ሥላሴ ማለት ልዩ ሦስትነት ማለት ነው። አንዱ እግዚአብሔር በአካል ሦስት በባሕርይ አንድ ነውና። ምሥጢረ ሥላሴን ካላወቁ ምሥጢረ ሥጋዌን መረዳት አይቻልም። በአካል ሦስት ይኽውም የአብ የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም አካል አለው። የወልድ የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ፣ ፍጹም አካል አለው። የመንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ ፍጹም አካል አለው። በአካል ስም ሦስት የአካላት ስሞች የተባሉትምን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። በባሕርይ አንድ ባሕርይ እንደየአገባቡ ይተረጎማል። የሦስቱ ኩነታት ተገናዝቦ (ሦስቱ ኩነታት አንድ የሆኑበት) ባሕርይ ይባላል። አንዲት ባሕርይ ያለመለየት በአዋን ሦስት ናት። በአዋን ሦስት አንዲት ባሕርየ ሥላሴ ሦስት ኩነታት አላት። አዋን እና ኩነት ትርጓሜያቸው ተመሳሳይ ነው። ሦስቱን ለመግለጽ ንዑስ አንቀጽ ስለማይበዛ በሳቢዘሩ ይጠቀማል እንጂ አዋን፣ ኩነት ሁለቱም መሆን የሚል ትርጉም አላቸው። ሦስቱ ኩነታትም ቃል፣ ልብ፣ እስትንፋስ ናቸው። አብ ልብ ነው። ወልድ ቃል ነው። መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ነው። በኩነታት ተገናዝቦ አለ። ይኽውም አብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ነው። ወልድ የአብ የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው። መንፈስ ቅዱስ የአብ የወልድ እስትንፋሳቸው (ሕይወታቸው) ነው። አብ ለራሱ ለባዊ ሆኖ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ለባውያን

ሆነው ይኖሩበታል። ወልድ ለራሱ ነባቢ ሆኖ አብና መንፈስ ቅዱስ ነባብያን ሆነው ይኖሩበታል። መንፈስ ቅዱስ ለራሱ ሕያው ሆኖ አብና ወልድ ሕያዋን ሆነው ይኖሩበታል። ሰውና መላእክትን በጸጋ ለባውያን፣ ነባብያን፣ ሕያዋን ብንላቸውም አለባውያን፣ ማሕየውያን፣ አንባብያን ግን አንላቸውም። ሥላሴ ግን ሕያዋን ብቻ ሳይሆኑ ማሕየውያንም ናቸው። ነባብያን ብቻ ሳይሆኑ አንባብያንም ናቸው። ለባውያን ብቻ ሳይሆኑ አለባውያንም ናቸው። ሦስቱ ኩነታት አንድ የሚሆኑት በተገናዝቦ ነው። አንዱ አንዱን በህልውና ገንዘብ ያደርገዋል። ወልድን ቃለ አብ ቃለ መንፈስ ቅዱስ እንለዋለን። መንፈስ ቅዱስን ሕይወተ አብ ሕይወተ ወልድ እንለዋለን። አብን ልበ ወልድ ልበ መንፈስ ቅዱስ እንለዋለን። በአካል ግብር ሦስት ሦስቱ አካላት በግብር አይገነዛዘቡም። በአካላዊ ግብር ተገናዝቦ የለም። የአብ አካላዊ ግብሩ መውለድ ማሥረጽ ነው። የወልድ አካላዊ ግብሩ መወለድ ነው። የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ግብሩ መሥረጽ ነው። አብ ወልድን ሲወልደው መንፈስ ቅዱስን ሲያሠርጸው በዘመን ያለመቀዳደም ነው። ይህ ከፍጡር ጎሊና በላይ ስለሆነ አባቶቻችን በሃይማኖተ አበው "ልደተ ወልድ ወፀአተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ይትነከር ወኢይትነገር ብለዋል። አንዳንዶች ዘኢየንልቅ ልደቱ የሚለውን ይዘው ሁልጊዜ ሲወለድ ይኖራል ይላሉ። ነገር ግን የዚህ ትርጉም ወልድ ወልድ ሲባል ይኖራል ማለት ነው እንጂ ሁልጊዜ ሲወለድ ይኖራል ማለት አይደለም። ሁልጊዜ ሲወለድ የሚኖር ቢሆን ኖሮስ ልደት ደኃራዊ ተዐውቀ በቀዳማዊ ልደት አይልም ነበር። ከዚያ ይልቅ ልደት ደኃራዊ ተዐውቀ በዘዘልፍ ልደት ባለ ነበር። ዘኢየንልቅ ልደቱ በልደቱ "ተመትሮ/መለየት" እንደሌለበት ያስረዳል። ይህም ማለት ለምሳሌ እናት ልጅን ብትወልድ ተመትሮ አለበት። ማለትም በህልውና ከማኅፀን ወደ አፍኣ ይወጣልና። አብ ወልድን ሲወልድ መንፈስ ቅዱስን ሲያሠርጽ ግን በህልውና አልተለዩትም። የግብር ተገናዝቦ ስለሌለ ወልድ ወልዶሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ አይባልም። ለይቶ ወልድ ወልዱ ለአብ ይላል እንጂ። በአካል ግብር ስም ሦስት ይኽውም አብ ወላዲ አሥራጺ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ የሚለው ነው። በባሕርይ ግብር አንድ ሦስቱ አካላት በባሕርይ ግብር አንድ ናቸው። ይኽውም በመፍጠር፣ በማክበር፣ በማዳን፣ በሥልጣን፣ በፈቃድ፣ በመንግሥት፣ በክብር እና በመሳሰሉት አንድ ናቸው ማለት ነው። በባሕርይ ግብር ስም አንድ ሥላሴ በባሕርይ ግብር ስም አንድ ናቸው። ይኽውም አብ ፈጣሪ፣ ወልድ ፈጣሪ፣ መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ እንላለን። አብ አምላክ፣ ወልድ አምላክ፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንላለን። አብ እግዚአብሔር፣ ወልድ እግዚአብሔር፣ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንላለን። አብ ቀባዒ፣ ወልድ ቀባዒ፣ መንፈስ ቅዱስ ቀባዒ እንላለን። አብ ንጉሥ፣ ወልድ ንጉሥ፣ መንፈስ ቅዱስ ንጉሥ እንላለን። ይህን ስላልን ግን ሦስት ፈጣሪ፣ ሦስት አምላክ፣ ሦስት ንጉሥ አለ ማለታችን አይደለም። በአንዲ የባሕርይ ግብር ሦስቱም ይጠሩባታልና አንድ አምላክ፣ አንድ ንጉሥ፣ አንድ ፈጣሪ እንላለን እንጂ።

ኢየሱስ ክርስቶስ

ትርጓሜ ወንጌል ዘማቴዎስ "ክርስቶስ የሚለው ስም የትስብእት ብቻ፣ የመለኮት ብቻ ስም አይደለም። ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ቢሆን የወጣለት ስም ነው እንጂ። ወዝ ስም ዘውእቱ ክርስቶስ ወፍካሬሁ ቅብዐት ምስለ አምጣነ ትስብእቱ ረከቦ ለዋሕድ እንዲል። ከበረ መባሉም በሥጋ ነው። ወቅብዓቱሰ ዘተወክፋ በትስብእቱ ይእቲ።

ወኢኮነ ቅብዐቱ አምሳለ ቅቡዓን እስመ እለ ይትቀብዑ ይፈቅዱ ቀሪበ ኀቤሁ ለከዊነ ወልድና ውእቱሰ አምላክ ውእቱ በጠባይዒሁ ዘእንበለ ፈቂድ እንዲል። ቦ እለ ይቤሉ እምቅድመ ተዋሕዶ ወቦ እለይቤሉ እምድኅረ ተዋሕዶ። ወገባሪሁሰ ለውእቱ ሥጋ መንፈስ ቅዱስ እስመ ውእቱ ቀብዖ ወተዋሐደ ቦቱ አምላክ ቃል ያለውን ይዘው ተቀብቶ ተዋሐደ የሚሉ አሉ። ተሠጊዎ ነሥአ ቅብዐተ በዘተሰብአ ተቀብዐ ያለውን ይዘው ሰው ሆኖ ተቀብቶ ተዋሐደ የሚሉ አሉ። ነገር ግን እንዲህ አይደለም። ሲቀባም ሲዋሐድም አንድ ጊዜ ነው። ከመ ቅዕበተ ዓይን። እለሰ ይሜህሩ ርቱዐ ይሜህሩ ከመ ተቀብዐ ቃል በሥጋሁ። ወእምአመ ኮነ ቃል ሥጋ አሜሃ አስተርአየ በመንፈስ ቅዱስ እንዲል" ይላል። ይህን ቃል ቅብዐቶች ክህደታችንን ይደግፍልናል ብለው ይጠቅሱታል። ነገር ግን እንዲያውም ክህደታቸውን የሚያፈራርስ ድንቅ ትርጓሜ ነው። ከበረ መባሉም በሥጋ ነው ብሎ እውነታውን በጥራት ያስቀምጣል። መንፈስ ቅዱስን ቀባዒ እንደሆነ "እስመ ውእቱ ቀብዖ" ብሎ በግልጽ ይነግረናል። በቀባዒነት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸውና። ለአንዱ የተነገረው ለሦስቱም ይሆናል። በሃይማኖተ አበው ወልድን ለሊሁ ቀባዒ ውእቱ ብሎ ገልጾታል። ከዚህ የመንፈስ ቅዱስን ገልጾታል። የአብን ቀባዒነት ደግሞ በዮሐ. ፭፣፳፮ "አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና" ተብሎ ተገልጿል። ይህ የማቴዎስ ትርጓሜም መንፈስቅዱስ ቀባዒ እንደሆነ ይነግረናል እንጂ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ እንደሆነ አይነግረንም። በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አስተምህሮ ሲቀባም ሲዋሐድም አንድ ጊዜ ነው። ተቀብቶ ተዋሐደ አንልም። ወይም ከተዋሕዶ በኋላ ተቀባ አንልም። ከመቅጽበት ሲቀባም ሲዋሐድም አንድ ጊዜ ነው። ሥጋ ቃልን ገንዘብ ቢያደርግ አብ ልቡ መንፈስ ቅዱስ ሕይወቱ ሆነ። ምክያቱም ቃል ሥጋን ሆኗልና። ሥጋም ቃልን ሆኗልና። ይኸውም በተአቅቦ ነው። አብና መንፈስቅዱስ ለሥጋ ምን አደረጉለት ቢባል። አብ የባሕርይ ልቡ፣ መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ ሕይወቱ ሆነ። ምክንያቱም ሥጋ ለቃል ሁለተኛ ለሥላሴ አራተኛ አይደለምና። ቅብዕ ማለት ክብር ነውና ክቡር ቃል ለሥጋ በተዋሕዶ ክብሩ ሆነ። ይህ የማቴዎስ ወንጌል ትርጓሜ ከላይ እንደምታዩት ወገባሪሁሰ ለውእቱ ሥጋ መንፈስ ቅዱስ ብሎ ገልጾታል። ከዚህ ላይም ሥጋን የፈጠረ መንፈስ ቅዱስ ነው ተብሎ ቢገለጽም ለመንፈስ ቅዱስ አድሎ መናገሩ ነው እንጂ በመፍጠር አንድ ስለሆኑ አብ ፈጠረ፣ ወልድ ፈጠረ ቢል አንድ ነው። ለምሳሌ በሃይማኖተ አበው ወልድ ሥጋውን እንደፈጠረ "ወኢተሳተፎ መኑሂ በፈጢረ ሥጋሁ" ተብሎ ተገልጿል። ቀብዖ ያለውም በዚህ አግባብ የተነገረ እንደሆነ ከላይ ጽፈናል። "እለሰ የአምኑ ርቱዐ ይሜህሩ ከመ ቃል ተቀብዐ በሥጋሁ" ቅዱስ ቄርሎስ። ቅባቶች ይህንን ቃል ይይዙና ቃል በሥጋ ተቀባ (ከበረ) ይላሉ። ይህ እጅግ አደገኛ ክህደት ነው። ቃል በሥጋ የሚቀባው (የሚከብረው) ቅድመ ዓለም ራሱ ክቡር አይደለምን? የመምህረ ዓለም ቅዱስ ቄርሎስን ቃል አጣሞ መተርጎም ትልቅ ነውር ነው። ሊቁ የትስብእትና የቃልን ተዋሕዶ በጋለ ብረት መስሎ አስተምሯል። ብረት በእሳት ሞቀ ይባላል እንጂ እሳት በብረት ሞቀ ይባላልን?! ሐሰ። አይባልም። እሳት በብረት ተያዘ ይባላል እንጂ ብረት በእሳት ተያዘ ይባላልን!? ሐሰ። አይባልም። ቃል በሥጋ ታመመ ይባላል እንጂ ሥጋ በቃል ታመመ ይባላልን?! በጭራሽ አይባልም። ቃል በሥጋ ከበረ ማለት ትልቅ ክህደት ነው። ቃል ቅድመ ተዋሕዶም፣ ጊዜ ተዋሕዶም፣ ድኅረ ተዋሕዶም ክቡር ነውና። ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስም ቃል በሥጋው ከበረ አላለም። ሊቁ ያለው "እለሰ የአምኑ ርቱዐ ይሜህሩ ከመ ቃል ተቀብዐ በሥጋሁ" ነው። የዚህም

ትርጉሙ እንደሚከተለው ነው። "በትክክል የሚያምኑ ቃል ሥጋን እንደተዋሐደ ያስተምራሉ" ማለት ነው። "በሥጋሁ" ሲል "በ" የሚለው አገባብ በግእዝ ቦታ የገባ ነው። ይኽውም በቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት ይገኛል። ቀስተ ዮናታን ኢተቀብዐት በቅብዕ ዘእንበለ ደመ ኃያላን ሲል "በቅብዕ" ያለው ቅብዐ ሲል ነው። ኦሪት ወነቢያት ሰበኩ በክርስቶስ ሲል "በክርስቶስ" ያለው ክርስቶስሀ ማለት ነው። "በ" በአገባብ "ን" ተብሎ ይተረጎማል። ስለዚህ በሥጋሁ ሲል "ሥጋውን" ተብሎ ይተረጎማል። "ተቀብዐ" ተዋሐደ ተብሎ ይተረጎማል። ስለዚህ "ቃል ተቀብዐ በሥጋሁ" ማለት ቃል ሥጋውን ተዋሐደ የሚል ትርጉም አለው። ሊቁ መምህረ ዓለም ቅዱስ ቄርሎስ የተናገረው ይህንን ነው። ቃልን በሥጋው ክብር አገኘ ማለት ቀድሞ ክቡር አልነበረም የሚል ትልቅ ክህደት ነው። ተቀብዐ-ተዋሐደ ተብሎ እንደሚተረጎም ተጨማሪ ምሳሌ በመጽሐፈ አርጋኖን "ዘተቀባዕከ ሥጋሃ ለማርያም" ይላል። በዚህ ጊዜ "የማርያምን ሥጋ የተዋሐድክ" ተብሎ ይተረጎማል። ቅባቶች ተዋሐደ ተብሎ አይተረጎምም ካሉ ግን የዚህ ትርጉም "የማርያምን ሥጋ የተቀባህ" የሚል ትርጉም ያመጣባቸዋል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ሥጋ ማርያም ቅብዕ ሊሆን ነው። ይህ ደግሞ ተሰምቶ የማይታወቅ ታላቅ ክህደት ነው። ዘተቀባዕከ ሥጋሃ ለማርያም- የማርያምን ሥጋ የተዋሐድክ ተብሎ ይተረጎማል። ይህም ቃል ከድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ መዋሐዱን ይገልጽልናል። በዚህ አገባብ ነው ቃል ተቀብዐ በሥጋሁ- ቃል ሥጋን ተዋሐደ ተብሎ የተተረጎመው። ዶክተር ሥርግው ገላው መራኁተ ቅብዐት ወተዋሕዶ በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 174 "ጌታ መንግሥቱን ክህነቱን ከባሕርይ አባቱ ተቀብሎታል" ይላሉ። ለዶክተሩ የምጠይቀው ጥያቄ ጌታ መንግሥቱን ከባሕርይ አባቱ የሚቀበለው በመንግሥትነትማ አብ ወልድ መንፈስቅዱስ አንድ አይደሉምን?! እንዲያ ከሆነ ደግሞ አንዱ ሰጪ አንዱ ተሰጪ አይሆንም። ይህ የተነገረ ቃልን በመዋሐዱ መንግሥትነትን ገንዘቡ ስላደረገው ሥጋ ነው። ሃይ. አበ. ፱፫ "ዕሩያን ሥላሴ በህላዌ ወበመንግሥት ወስባሔ ወበፈጢረ ኵሉ ፍጥረት ወበኵሉ ግብር ዘይደሉ ለእግዚአብሔር" እንዲል። ሥላሴ በመንግሥት፣ በምስጋና፣ በመፍጠር አንድ ናቸውና። ሥጋ በቃል ገንዘብ ንጉሥ ሲሆን መንግሥትነትን ማን ሰጠው ቢሉ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስቅዱስ ናቸው። ሀብትን በመስጠት ሦስቱ አካላት አንድ ናቸውና። ሥጋ ይህንን ሁሉ ክብር ያገኘው ደግሞ ቃልን በመዋሐዱ ነው።

የዶክተር ሥርግው ገላው ቅዠት

ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

ዶክተር ሥርግው ራሱ ውሸት ይፈጥርና ራሱ የፈጠረውን ውሸት እንደማስረጃ በመቁጠር ሌላውን ይከስበታል። ዋናውን የልዩነት ምክንያት ትቶ የሌለ ይዘባርቃል። በተዋሕዶ ነገረ ቅብዐት ብሎ ነገር የለም ብሎ በአደባባይ ይዋሻል። ሲጀምር በእኛ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶዎችና በቅባቶች መካከል ያለው ልዩነት "ነገረ ቅብዐትን" በመረዳት ላይ ነው። ቅባቶች ለክርስቶስ ሥጋ ክብር (ቅብዕ/ቅብዐት) የሆነው መንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ። እኛ ደግሞ ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ (ተቀብዐ) እንላለን። በተዋሕዶ መክበር ማለትም ሥጋ የቃልን ገንዘብ ገንዘብ በማድረጉ ከበረ ማለት ነው። ይኽውም ቅድመ ተዋሕዶ አምላክ ያልነበረ ሥጋ በተዋሕዶ አምላክ ሆነ ማለት ነው። ስመ ሥርጋዌው መምህረ ዓለም የተባለ ቅዱስ ቄርሎስ እንቲኣሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲኣሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል ይላል። በተዋሕዶ የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ

ለቃል ሆነ ይላል። ለመሆኑ የሥጋ ገንዘብ ምን ነበር ብንል ግዙፍነት፣ ውስንነት፣ ነዳይነት፣ ሐማሚነት እና በአጠቃላይ የሥጋ ባሕርይ የሆነው ሁሉ ነው። የቃል ገንዘብስ ምንድን ነው ብንል ረቂቅነት፣ ምሉዕነት፣ ባዕልነት፣ አምላክነት፣ ክቡርነት (ቅቡዕነት) እና የመሳሰሉት ናቸው። ቃል ቅድመ ተዋሕዶም ቅቡዕ (ክቡር) ነው። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በክብር (ቅብዕ) አንድ ናቸውና። ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ ማለትም ሥጋ አምላክ ሆነ ማለት ነው። ይህ ደግሞ የሆነው ቅድመ ዓለም አምላክ የሆነውን ቃልን በመዋሐዱ ነው። ቃል ሥጋ ኮነ (ዮሐ. ፩፣፲፬) ባልንበት አንጻር ሥጋም ቃልን ሆነ እንላለን። የቃል ገንዘብ ለሥጋ ሲሆን ለቃል የሆኑት አካላዊ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ እና አካላዊ ልቡ አብ ለሥጋም ሆነዋል። ስለዚህ እኛ ተዋሕዶዎችና ቅባቶች የምንለያየው ለሥጋ ክብር የሆነው ማን ነው? በሚለው ነው። እኛ ቃል ስንል ቅባቶች መንፈ ስቅዱስ ይላሉ። ይህ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆነ ወደማለት የሚያመራ ታላቅ ክህደት ነው። ዶክተር ሥርግው ባልዋለቡት ነገረ ክርስቶስ እፈተፍታለሁ ሲሉ ወደታላቅ ክህደት እየተንደረደሩ ነው። ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ያልኩዎት ለዚያ ነው። ቅዱስ ቄርሎስ በሃይ. አበ. 124፣34 "እስመ ክርስቶስ ኢተቀብዐ በእንተ መፍቅድ ዘቦቱ አላ ለሊሁ ቀባኢ ውእቱ። እጠቀም ብሎ የከበረ አይደለም። እርሱ ሌላውን ያከብራል እንጂ። ወዐርገ ኀበ ሥልጣነ መለኮቱ እንዘ ሰብእ ውእቱ ሰው ሲሆን በአምላክነቱ ሥልጣን ከበረ። ተብህለ በእንቲኣሁ ከመ ውእቱ ተለዐለ ፈድፋደ በእንተ ትሕትና ወሕፀፅ እንተ ዘትስብእት ወንደኅት ትሑት ሥጋን ስለተዋሐደ ከበረ ተባለ" ይላል። ክርስቶስ ማለት ቅቡዕ (የተቀባ) ማለት ነው። ይህም ሥለ ሥጋው የተነገረ መሆኑን ይህ ቃል በግልጽ ይነግረናል። በቃልነቱ ከጊዜ ተዋሕዶ በፊትም ክቡር ነውና። ቅድመ ተዋሕዶ አምላክ ያልነበረ ሥጋ በጊዜ ተዋሕዶ አምላክ መሆኑን ይነግረናል። ተቀብዐ ማለት ከበረ አምላክ ሆነ ተብሎ ይተረጎማል። ሥጋ አምላክ የሆነው ደግሞ ከቃል ጋር ሲዋሐድ ነው። ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ የሚባለው ለዚህ ነው። መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ (ክብር) ሆነው የሚል ትምህርት የለም። ይህን የሚሉ ቅብዐቶች ናቸው። ሥላሴ በክብር አንድ ናቸውና። በሥላሴ ዘንድ አብ ቀባዒ፣ ወልድ ተቀባዒ፣ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ የሚባል አካላዊ ግብር የለም። አካላዊ ግብር ወላዲነት፣ አሥራጺነት፣ ተወላዲነት፣ ሠራጺነት ነው። ኵነታትም ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ናቸው። አካላዊ ግብር ሦስቱ አካላት የሚለዩበት ነው። በአካላዊ ግብር ተገናዝቦ የለም። ይህም ማለት በአብ ወላዲነት ወልድ ይወልዳል አይባልም። በኵነታት ግን ተገናዝቦ አለ። ይህም ለምሳሌ በአብ ልብነት ወልድ ያስባል፣ በወልድ ቃልነት አብ ይናገራል እንላለን። አብ ለባዊ ለርእሱ ሆኖ በእርሱ ወልድ እና መንፈስቅዱስ ለባውያን ሆነው ይኖራሉ። አለባውያን ለፍጡራን ነው። ወልድ ነባቢ ለርእሱ ሆኖ በእርሱ አብና መንፈስቅዱስ ነባብያን ሆነው ይኖራሉ። አንባብያን ለፍጡራን ነው። መንፈስቅዱስ ሕያው ለርእሱ ሆኖ በእርሱ አብና ወልድ ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ። ማኅየውያን ለፍጡራን ነው። አብ ወልድ መንፈስቅዱስ በሥልጣናዊ ግብር አንድ ናቸው። በክብር፣ በሥልጣን፣ በመዓርግ አንድ ናቸው። በአንዲ ክብር ሦስቱም አካላት ይጠሩባታል። ይኽውም አብ ክቡር፣ ወልድ ክቡር፣ መንፈስቅዱስ ክቡር ቢል አንድ ክብር ነው። አብ ቀባዒ (አክባሪ)፣ ወልድ ቀባዒ (አክባሪ)፣ መንፈስ ቅዱስ ቀባዒ (አክባሪ) ቢል ይሆናል። ለዚያ ነው ሃይ. አበ. 124፣34 ወልድን ለሊሁ ቀባዒ ውእቱ ያለው። በሥልጣናዊ ግብር አንዱ አካል የተጠራበት ለሌኛው አካልም መጠሪያ ይሆናል። ወልድን አብ አስነሳው ሲል ብታየው ማስነሣት የአብ

ግብር ብቻ አይምሰልህ። በሌላ ቦታ ወልድ ወተንሣእኩ በሥልጣን ባሕቲትየ ሲል ይገኛልና። በሥልጣናዊ ግብር (ባሕርያዊ ግብር) አብ ወልድ መንፈስቅዱስ አንድ ናቸው። ሥላሴ በክብር አንድ ናቸው። ስለሆኑም አንዱ አክባሪ አንዱ ከባሪ አይደሉም። ሠለስቱ አካላት በክብር አንድ የሆኑ አክባርያን (ቀባዕያን) ናቸው እንጂ። ሃይ. አበ 113፣2 ዕሩያነ መዓርግ ወክብር እንዲል። ከበረ ሲል ብታገኘው እንኳ ስለተዋሐደው ሥጋ እየተናገረ መሆኑን ልብ በል። ምክንያቱም ቅዱስ ቂርሎስ በሃይ. አበ 74፣37 እንደገለጸው "ወመጻሕፍትሰ ቦ ዘይቤላ በእንተ መለኮቱ ወቦ ዘይቤላ በእንተ ትስብእቱ እንዘ ውእቱ ከመ አምላክ ወሰብእ ወቦ ዘይቤላ በእንተ መለኮቱ ወትስብእቱ ኅቡረ"። መጻሕፍት ስለአንዱ ክርስቶስ ሲናገሩ አምላክም ሆኖ ሳለ ስለሰውነቱ የሚናገሩበት ጊዜ አለ። በዚህ ጊዜ አምላክነቱን ዘንግተው አይደለም። ራሱ ክርስቶስ ሲያስተምር ብዙ ቦታ ላይ ራሱን የሰው ልጅ እያለ ይናገር ነበር። በዚህ ጊዜ አምላክነቱን ዘንግቶ አይደለም። ሰው ሆኖም ሳለ ስለአምላክነቱ የሚናገሩበት ጊዜ አለ። በዚህ ጊዜ ሰውነቱን ዘንግቶ አይደለም። በአንድ ጊዜ ስለሰውነቱም ስለአምላክነቱም የሚናገሩበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና ሲል ሁለቱን በአንድ ላይ እንደተናገረ ለቡ። ስለዚህ ጌታ ራሱን የሰው ልጅ ባለበት መንገድ ቅቡዕ ተብሏል። የከበረው ሰውነቱ ነውና። በቃልነቱማ ድሮም ክቡር ነው። ዶክተር ሥርግው ገላው ውሽታቸውን በመቀጠል እንዲህ ይላሉ መራኁተ ቅብዐት ወተዋሕዶ ገጽ 5 "በተዋሕዶ ትምህርት ቤት ቀብዐ-ቀባ ተብሎ አይተረጎምም አዋሐደ ነው እንጂ" ይላሉ። እውነታው ግን ቀብዐን እንደየአገባቡ እንተረጉመዋለን። ቀብዐ-ቀባ ብለን የምንተረጉምበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ ዘፀ. ፳፱፣፯ ላይ "ወትነሥእ እምቅብዕ ዘባረከ ወትክዑ ዲበ ርእሱ ወትቀብዖ" ሲል የቅባትንም ዘይት ወስደህ በራሱ ላይ ታፈሰዋለህ ትቀባውማለህ" ይላል። በዚህ ጊዜ ቀብዐ ቀባ ተብሎ እንደተተረጎመ ለቡ። ቀብዐ-ሾመ ብለንም እንተረጉመዋለን። ዘሌ. ፮፣፳፪ "ካህን ዘቅቡዕ ህየንቱሁ እምደቂቁ ይገብሮ" ሲል ከልጆቹም በአባቱ ፋንታ የተቀባው (የተሾመው) ካህን ያቀርበዋል ይላል። ለክህነት መሾምን፣ ለመንግሥትነት መሾምን ተቀብዐ ይለዋል። ይኽውም አስቀድሞ ንጉሥ ያልነበረ ሰው ሲቀባ የጸጋ ንጉሥ ይሆናል። አስቀድሞ ካህን ያልነበረ ሰው ሲቀባ የጸጋ ካህን ይሆናል። ቀብዐ- አዋሐደ ብለንም እንተረጉመዋለን። መዝ. ፵፬፣፯ "አፍቀርከ ጽድቀ ወዓመፃ ጸላዕከ። በእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር አምላክከ ቅብዐ ትፍሥሕት እም እለ ከማከ" ሲል እንዳንተ ያሉ ነቢያት ካህናት ከተቀቡት ልዩ የሚሆን ቅብዐ ትፍሥሕትን (ልዩ ተዋሕዶን) አዋሐደህ ይላል። "እምእለከማከ" ሲል "እም" ያለው አገባብ ዘይኄይስ (የሚበልጥ) የሚል ትርጉም አለው። ታዲያ ከነቢያት ተዋሕዶ በምን ይበልጣል ቢሉ እግዚአብሔር ቅዱሳንን ነቢያትን ቢዋሐዳቸው የጸጋ ተዋሕዶ ነው። እርሱ በእነርሱ አድሮ ያሠራቸዋል እንጂ አካሉ አካላቸው አካላቸው አካሉ አይሆንም። ባሕርያቸው ባሕርዩ ባሕርዩ ባሕርያቸው አልሆነም። ፍጹም ተዋሕዶ የለም። የጌታ ሰውነት ግን ቃልን በመዋሐዱ የቃል ገንዘብ ሁሉ ገንዘቡ ሆኗል። ቃልም ሥጋን በመዋሐዱ የሥጋ ገንዘብ ሁሉ የቃል ገንዘብ ሆኗል። ፍጹም ተዋሕዶ ነው። ይህም እንቲኣሁነቱን (ቅድመ ተዋሕዶ ያለውን ገንዘቡን) ሳይለቅ ነው። ስለዚህ ቀብዐን እንደየአገባቡ እንተረጉመዋለን እንጂ አዋሐደ ብቻ ብለን አንተረጉመውም። ለክህነት ለመንግሥት መሾምን ተቀብዐ ብለን እንደምንተረጉመው ከላይ ገልጸናል። የሰው ያለው መልካም ነገር ሁሉ ከፈጣሪ የተሰጠ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ "ምንት ብከ ዘኢነሳእከ እምካልእከ ወምንት ብከ ዘኢኮነ ውሁበ ለከ" እንዲል። ልዑል እግዚአብሔር የእርሱ የባሕርይው የሆነውን

ለፍጡራን በጸጋ ይሰጣል። እርሱ በባሕርይው ንጉሥ ሆኖ ሳለ መንግሥትነትን ለፍጡራን ይሰጣል። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ግን በመንግሥትነት አንድ ስለሆኑ መንግሥትነትን አብ ለወልድ ሰጠው አይባልም። ሃይ. አበ. ፱፫ "ዕሩያን ሥላሴ በህላዌ ወበመንግሥት ወስባሔ ወበፈጢረ ኵሉ ፍጥረት ወበኵሉ ግብር ዘይደሉ ለእግዚአብሔር" እንዲል። ሥላሴ በመንግሥት፣ በምስጋና፣ በመፍጠር አንድ ናቸውና። በሉቃ. ፩፣፸፪-፸፫ "ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል ወይሁቦ እግዚአብሔር አምላክ መንበረ ዳዊት አቡሁ። ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም። ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ" ይላል። ይህ ቃል ስለኢየሱስ ክርስቶስ መልአኩ ለድንግል ማርያም የነገራት ነው። እግዚአብሔር አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል። ለዘለዓለሙም በያዕቆብ ወገን ይነግሣል። ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ተብሏል። "ወይሁቦ እግዚአብሔር" የሚለውን ቃል ብንመለከተው መንግሥትነትን የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን ይነግረናል። እግዚአብሔር ደግሞ የሦስቱም አካላት መጠሪያ ነው። አንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዲል። መንግሥትነት ንጉሥነት የተሰጠው ማን ነው ስንል ግን ሥጋ ነው። ምክንያቱም ወልድማ ቅድመ ዓለምም ንጉሥ ነው። ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም እንዲል። በመንግሥትነት ሦስቱ አካላት አንድ ናቸው ተብሎ እንደተገለጸ ከላይ በሃይማኖተ አበው አሳይተናል። ስለዚህ ሥጋ ቃልን በመዋሐዱ ንጉሥ ሆነ እንላለን። ዶክተር ሥርግው ገላው በገጽ 161 "በሐዋርያትና በሁሉም ኦርቶዶክሳውያን አባቶች ቀቢ አብ ነው፣ ተቀቢ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው፣ ቅብእ መንፈስቅዱስ ነው" ብለዋል። ይህንን ሀሳባቸውን ገጽ 163 ላይም ደግመውታል። ይገርማል። ይህንን ሳነብ፦

ኩሉ ሰብእ ለሃይማኖቱ።

ይቀብዓ ስመ ምእት ሠለስቱ።

የሚለውን የአንድ ሊቅ ቅኔ አስታወሰኝ። ፍሬ ነገሩ ሁሉም የራሱን አመለካከት እና እምነት የሠለስቱ ምእት አስተምህሮ አድርጎ ያቀርባል እንደማለት ነው። ዶክተር ሥርግው ሐዋርያትን በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተፈበረከውን የቅብዐት እምነት ተከታዮች አድርጎ ያቀርባቸዋል። የትኛውም ኦርቶዶክሳዊ አባት ቀቢ አብ፣ ተቀቢ ኢየሱስ፣ ቅብዕ መንፈስ ቅዱስ እያለ አላስተማረም። እንዲያውም የኢየሱስ ሰውነት በመንፈስ ቅዱስ ከበረ የምትሉ ቅባቶችን ሊቃውንቱ አውግዘዋል። ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ቄርሎስ በድርሳኑ "እመቦ ዘይቤ ከብረ በመንፈስ ቅዱስ ከመ አሐዱ እም ቅዱሳን ውጉዘ ለይኩን" ከቅዱሳን እንደ አንዱ በመንፈስ ቅዱስ ከበረ የሚል ቢኖር የተወገዘ ይሁን ብሏል በተጨማሪም "ይቁድስ እንከ እስመ አምላክ ውእቱ በህላዌሁ ወይትቀደስኒ ምስሌነ ከመ አሐዱ እም ሰብእ"። ሰው እንደመሆኑ በሥጋ ከበረ እንደተባለ ተገልጿል። ይቁድስ እንከ እስመ አምላክ ውእቱ ካለ ለሥጋ ክብር የሆነው ቃል ነው ማለት ነው። ዶክተር ሥርግው በመጽሐፋቸው ገጽ 205 ላይ ደግሞ "ንስጥሮስ የተወገዘው በወልድ ተቀባዒ ፈንታ ትስብእት ተቀባዒ በማለቱ ነውና" ይላሉ። ይህም የአደባባይ ውሸት ነው። የንስጥሮስ ዋና ክህደት ክርስቶስን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ በማለቱ ነው። (ክልዔ ህላዌሁ ለክርስቶስ) የሚል ነው ክህደቱ። ክርስቶስ ደግሞ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የሆነ ማለት ነው። ከተዋሕዶ በኋላ ምንታዌ የለም። ቄርሎስ ፳፫ "ንሕነሰ ኢንቤ ክልኤቱ እምድኅረ ትድምርት። አላ ባሕቱ ንሌቡ ከመ እምክልኤ ህላዌ ተደመረ

አሐዱ ክርስቶስ ቃል" እንዲል። ተቀባዒ ሥጋ ነው። ይህ ደግሞ የሆነው በጊዜ ተዋሕዶ ነው። ቃል ተቀባዒ ነው እንዳንልማ አስቀድሞ ክብር የለሽ ቃል አለ ወደ ማለት የሚያደርስ ክህደት ነው። ሥላሴ በክብር አንድ ናቸው የሚለውን ይቃወማል። ከተዋሕዶ በኋላ ክርስቶስ ሲያስተምር ብዙ ጊዜ ራሱን የሰው ልጅ ይል ነበር። የሰው ልጅ የተባለው ከድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ ነው። እንደዚሁ ሁሉ ክርስቶስ ብሂል ቅቡዕ ብሂል ሲልም ቅቡዕ የተባለው በተዋሐደው ሥጋ አማካኝነት እንደሆነ ለቡ። ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው። ራሱ መድኃኒት ነው። እንጂ ለማዳን አብን የሚለምን አይደለም። በሥልጣን አብና ወልድ አንድ ናቸውና። ዮሐ. ፲፣፴ "እኔ እና አብ አንድ ነን" እንዲል። ስለዚህ ኢየሱስ ራሱ መድኃኒት ነው እንጂ ለማዳን ከአብ የሚለምን በሥልጣን የአብ ተወራጅ የሆነ አይደለም። ታድያ እንዲያ ከሆነ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐ. ፲፬፣፳፰ "ከእኔ አብ ይበልጣል" ለምን አለ ከተባለ የሚራብ የሚጠማ ሥጋን በመዋሐዱ እንዲያ አለ። በዚህ ምክንያት ዕብ. ፪፣፯ "ከመላእክት ጥቂት አሳነስከውም" ተብሏል። መላእክት የሚራብ የሚጠማ ሥጋ የላቸውምና በዚህ ምክንያት ነው። በክብር ከመላእክት እንደሚበልጥ ግን ዕብ. ፩፣፬-፯ "ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን በወረሰ መጠን እንዲሁ ከእነርሱ አብዝቶ ይበልጣል። የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ" ተብሏል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ አምላክ የሆነ ሰው ነው ብለናል። ስለዚህ አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውነትንም የአምላክነትንም ሥራ ይሰራል። ቅድመ ዓለም ነበረ ዓለምን ፈጠረ የምንለውም በኋላ ከድንግል ማርያም ተወለደ የምንለውም ያው አንዱን ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው እንደሆነ እንደሚነግሩን ሁሉ አምላክ እንደሆነም ይነግሩናል። ሃይማኖተ አበው ዘሄራኬዎስ ምዕራፍ ፯ ቁጥር ፲፱ "በከመ ይነግራነ መጻሕፍት ቅዱሳት ከመ ክርስቶስ ሰብእ ከማሁ እሙንቱ ይነግራነ ከመ ውእቱ አምላክ" እንዲል። ኢየሱስ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ተብሏል ማቴ. ፩፣፩። የዳዊት ጌታም ተብሏል። አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ የአምላክነትንም የሰውነትንም ሥራ ይሰራል። ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ለእኛ አርዓያ ለመሆን የሰራው ሥራ አለ፣ አምላክነቱን ለማሳወቅ የሰራው ሥራ አለ፣ ሰውነቱንብለማስረዳት የሰራው ሥራ የተናገረው ነገር አለ፣ ለቤዛነት የሰራው ሥራ አለ።ለእኛ አርዓያ ለመሆን የሰራቸው ሥራዎች መጾሙ፣ መጸለዩ፣ መጠመቁ እና የመሳሰሉ ሥራዎች ናቸው። ማቴ. ፲፩፣፳፱ "ከእኔም ተማሩ" ብሎናልና። እሱ በመጾሙ በመጸለዩ በመጠመቁ የተጨመረለት ክብር የለም እርሱ በባሕርይው ክቡር ነውና። የአምላክነት ሥራ ሲሰራ ያዩት አምላክ ብቻ ነው ሰውነት የለውም ሰው አይደለም የሚሉ ነበሩና ሰውነቱን ለማስረዳት ራሱን ሲጠራ ብዙ ጊዜ የሰው ልጅ እያለ ይጠራ ነበር። ማቴ. ፲፩፣፲፱ "የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ" ተብሏል። መራቡ፣ መጠማቱ፣ መድከሙ፣ መሰቀሉ ሁሉ ሰው ስለሆነ የሆነው ነው። ከኃጢአት በስተቀር የሰውን ሥራ ሁሉ ሰርቷል። ይህን አይተው ሰው ብቻ (ዕሩቅ ብእሲ) ለመሰላቸው ደግሞ አብርሃም ከመወለዱ በፊት አለሁ ብሎ በመናገር የአምላክነትን ሥራ ማለትም በደረቅ ግንባር ዓይን መፍጠር እና የመሳሰሉ ሥራዎችን ሰርቷል። ማቴ. ፲፱፣፳ "የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና" ተብሏል። ሌላው ለቤዛነት (ለካሣ) ነው። የአዳምን በደል ይቅር ለማለት አዳም ሊያደርገው የሚገባውን ሁሉ አድርጓል። አምላክ ሆኖ ሳለ "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ" ብሏል። ተሰቅሏል። ተቀብሯል። በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነስቷል። መሥዋእት ወልድ በመስቀል ተሰቅሎ ራሱ ሊቀ ካህናት መሥዋእት አቅራቢ ሆኖ

አዳምን ከአብ፣ ከራሱ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አስታርቆታል (ታርቆታል)። አዳምም ድኅነትን ስላገኘ ወደ ገነት ገብቷል። ሥጋ ደካማ ነው። በቦታ የተወሰነ ነው። በጊዜ ተዋሕዶ ቃልን በመዋሐዱ የቃልን ርስት ወረሰ ማለትም የቃልን ገንዘቦች ረቂቅነትን፣ በሁሉ ቦታ መኖርን ገንዘብ አደረገ በዚህም ምክንያት ለሥጋ ስለሆነው ነገር ዮሐ. ፫፣፭፮ "የሰው ልጅም ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው" ተባለ። ማቴ. ፳፰፣፲፰ "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ" ብሏል። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሥልጣን አንድ ናቸው። አንዱን ብቻ ቢጠራ አድሎ መናገሩ ነው። ለምሳሌ ትንሣኤውን በተመለከተ ራሱ ወልድ በራሴ ሥልጣን ተነሳሁ ይላል። በሌላ ቦታ አብ አስነሳው ይላል። ሁለቱም አንድ ነው። በአንዲት ግብረ ባሕርይ ሦስቱም ይጠሩባታልና ነው። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስንናገር ራሱ ስለራሱ የነገርንን እና እርሱ ያስተማራቸው ሐዋርያት ስለእርሱ የተናገሩትን መሰረት አድርገን ነው። ክርስቶስ ያልሆነውን ነገር ነው ማለት እና የሌለውን ማንነት መስጠት ግን ሰይጣናዊ ሥራ ነው። ወተት ነጭ ሆኖ ሳለ የሌለውን ማንነት በልብ ወለድ ወይም በውሸት ጥቁር ነው ማለት የሰይጣንና የግብር ልጆቹ ሥራ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን በመሰለኝ እየተረጎሙ ከተጻፉበት ዓውድ አያወጡ እየተረጎሙ ብዙውን ዓለም እያታለሉ ያሉ የሰይጣን የግብር ልጆች አሉ። የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር ራሱ ቃሉን ባስተላለፈበት ዓውድ ይነገራል እንጂ ቃሉን እኛ በተረዳንበት ልክ ብቻ አይነገርም። የሰው ልጅ በእውቀት የተወሰነ ስለሆነ ማለት ነው። ፪ኛ ጴጥ. ፫፣፲፮ "ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ" እንደተባለው ራሳቸው ለፈጠሩት ግላዊ አመለካከት ብለው የመጻሕፍትን ቃል የሚያጣምሙ ሰዎች በዝተዋል። በዋናነት ግን የሚጎዱት ራሳቸውን ነው። ምክንያቱም ሕይወትም መድኃኒትም ከሆነው ኢየሱስ ራሳቸውን አግልለው ራሳቸው በሕሊናቸው ለፈጠሩት ማንነት ለሰጡት ነገር ይገዛሉና። ድንግል ማርያም ወልዳ የታቀፈችው አብ ቅድመ ዓለም ያለ እናት በዘመን ሳይቀድም የወለደውን ነው። ከካቶሊክ ጋር ያለን ልዩነት በዋናነት በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ካቶሊኮቹ ክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ነው ይላሉ። እኛ ኦርቶዶክሳውያን ደግሞ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው እንላለን። መጀመሪያ ኦርቶዶክስ የሚለው ስያሜ የተሰጠን በ325 ዓ. ም በኒቅያ ነው። ቀጥ ያለ ትክክለኛ እምነት ማለት ነው። በሐዋርያት ዘመን ደቀ መዛሙርት እንባል ነበር። የሐዋ. 11፣26 "ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ" ይላል። ክርስቲያን የተባሉት ቀድመው ደቀመዛሙርት ይባሉ የነበሩት ናቸው። በኋላም ኦርቶዶክስ የተባሉት ቀድሞ ክርስቲያን የተባሉት ናቸው። በ431 ዓ. ም ደግሞ ተዋሕዶ ተብለናል። በአካል አንድ በባሕርይ አንድ ከማለታችን በፊት አካል ምንድን ነው? ባሕርይስ ምንድን ነው የሚለውን መተርጎም ያስፈልጋል። አካል ባሕርይ ያልሆነ ነገር ግን የባሕርይ መገለጫ የሆነ ነው። በግሡ ከሄድን አከለ-በቃ ካለው የሚወጣ ዘመድ ዘር ነው። መብቃትን ያመለክታል። መብቃት ደግሞ በሁለት ይተረጎማል ወሰን ያለው መብቃት እና ወሰን የሌለው መብቃት ነው። ለምሳሌ በእንስራ ውሃ እያደረግን ሲሞላ በቃ እንላለን ወሰን እንዳለበት ለማመልከት ነው። አካል ስንል በሌላ መንገድ መብቃትን ማለትም ምንም እንከን የለሽ መሆንን ያመለክታል። አካል ለእግዚአብሔር ሲነገር ወሰን የለሽ እንከን የለሽ ፍጹም መሆንን ያመለክታል። ስለዚህ አካለ እግዚአብሔር ሦስት ነው። አብ የራሱ የሆነ በዓለም የመላ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ አለው። የወልድም የመንፈስ ቅዱስም እንዲሁ ነው። በአካል

ሲኖሩም አንዱ ካለበት ቦታ ሁሉ በህልውና ሌላኛው አለ። ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐ. 14፣10 "እኔ በአብ አለሁ አብም በእኔ አለ" ያለው ይህንን ነው። ባሕርይ ማለት ደግሞ መሠረት ተብሎ ይተረጎማል። አካል ያልሆነ ነገር ግን በአካል ያለ አካል የገለጠው ባለቤት ነው። ከአካል የማይለይ አካል የሚገልጠው ነው። የኩነታት በሕልውና መገናዘብ ባሕርይ ይባላል። አንዲት ባሕርየ ሥላሴ ሦስት ኩነታት አላት መባሏም በዚህ መሰረት ነው። ወልድ ቃል ነው። ዮሐ.1፣1 "በመጀመሪያ ቃል ነበር" እንዲል። አብ ልብ ነው መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ነው። አንዲት ባሕርየ ሥላሴ በኩነት ትለያለች። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የሆነ ነው ስንል ሁለት አካል የተባሉ አካለ ሥጋና አካለ ወልድ ናቸው። አካለ ቃል በዓለም የመላ ረቂቅ ነው። አካለ ሥጋ በሦስት ክንድ ከስንዝር የተወሰነ ግዙፍ ነው። ሁለቱ በተዋሕዶ አንድ ሆኑ ማለት ነው። አንድ ሲሆኑ ግን ከተዋሕዶ በፊት ያላቸውን ማንነት ለውጠው ወይም አጥፍተው አይደለም። መምህረ ዓለም ቅዱስ ቄርሎስ "እንተኣሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲኣሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል" ቅድመ ተዋሕዶ የቃል ገንዘብ የሆኑት ሁሉ ማለትም ረቂቅነት በሁሉ ቦታ መኖር ለሥጋ ገንዘቡ ሆኑ። ይህም ሲሆን በተዓቅቦ ነው። ተዐቅቦ ማለትም ሥጋ ረቂቅ የሆነው ግዙፍነቱን ሳይለቅ ነው። ቃልም የሥጋን ገንዘብ ገንዘቡ አደረገ ማለትም ረቂቅነቱን በሁሉ ቦታ መኖርን እንደያዘ ግዙፍነትንና በድንግል ማኅጸን መወሰንን ገንዘብ አደረገ ማለት ነው። ክርስቶስ በአካል አንድ ነው ማለት ይህ ነው። በባሕርይ አንድ የምንለው ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆነ ማለታችን ነው። ሁለት ባሕርይ የተባሉት አሐቲ ባሕርየ ሥላሴ እና ባሕርየ ትስብእት ናቸው። ባሕርየ ሥላሴ በግብረ ባሕርይ ትገለጣለች። ይኽውም ሁሉን ቻይነት፣ ፈጣሪነት፣ ቀዳማዊነት፣ አለመራብ፣ አለመጠማት የመሳሰሉት ናቸው። ባሕርየ ሰብእ የሚባለውም በመገለጫ የሚራብ፣ የሚጠማ፣ የሚታመም፣ እና የመሳሰለው ነው። ሃይማኖተ አበው ዘሱኑትዩ "ኢይትረከብ ህላዌ ዘእንበለ አካል ወኢአካል ዘእንበለ ህላዌ" አካል ያለ ባሕርይ ባሕርይ ያለ አካል አይገኝም ብሏል። የባሕርይ ምንታዌ ስለሌለ የማይሞተው ሞተ ተባለ። ይህም የሆነው መዋቲን በመዋሐዱ ነው። መዋቲው ሕያው ተባለ ይህም የማይሞተውን በመዋሐዱ ነው። ስለዚህ ክርስቶስ አምላክ የሆነ ሰው ሰው የሆነ አምላክ ነው። ሰው እንደመሆኑ በምራቁ ጭቃን ለወሰ ለመለኮት ምራቅ የለውምና። አምላክ እንደመሆኑ በምራቁ አፈርን ለውሶ ዓይንን አበራ። ካቶሊኮቹ የሚያነሱት ሐሳብ ባሕርየ ሥላሴ አንዲት ከሆነች እርሷ የሰውን ባሕርይ ከተዋሐደች አብና መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆኑ ያሰኛል የሚል ነው። ነገር ግን ባሕርየ ሥላሴ ባሕርየ ሰብእን በቃልነቷ ከዊን ተዋሐደች የሚል መልስ ነው ያለን። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ዮሐ. ፩፣፲፬ "ቃል ሥጋ ኮነ" በማለቱ ነው። አካል ብቻ ቢዋሐድ ኖሮስ በአካል ስሙ ወልድ ሥጋ ኮነ ባለ ነበር። ቃል ሥጋ ኮነ በማለቱ ግን የካቶሊካውያንን ነገር አፈረሰው። ሮሜ ፭፣፲ "ጠላቶቹ ስንሆን እግዚአብሔር በልጁ ሞት ታረቀን" እንዲል የአብ ልጅ የማርያም ልጅ ነው። ወልደ አብ ወልደ ማርያም አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በአካል አንድ ነዉ በባሕርይም አንድ ነው። አንድ ስለሆነም ዮሐ. ፫፣፲፮ "አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና" ተብሏል። ቅዱሳት መጻሕፍትም ክርስቶስን ሁለት ያሉበት ቦታ የለም። እኛና ካቶሊኮች "በመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ጉዳይ" ያለንን ልዩነት በቀጣይ ክፍል አቀርባለሁ።

አነ ዘክርስቶስ

እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ እኔ የኬፋ ነኝ፣ እኔ የአጵሎስ ነኝ የሚለው አስተሳሰብ የትም የማያደርስ ትንሽ ሐሳብ ነው። ደንበኛውና ትልቁ ሐሳብ እኔ የክርስቶስ ነኝ የሚለው ነው። የክርስቶስ መሆን መቼም መች አያሳፍርም። ሰውን ቢከተሉት ፍጻሜው አይታወቅም። ይሁዳ ሐዋርያ ነበር። በኋላ ግን የከሃድያን አብነት ሆነ። ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ ዋና አሳዳጅ ነበር። በኋላ ግን በትምህርቱ የዓለምን ድንቁርና ያራቀ ብርሃነ ዓለም ሆነ። ሰውን ብትከተል መዳረሻውን አታውቀውም። ክርስቶስን ብትከተል ግን መዳረሻው ዘኢየኃልቅ ፍሥሓ (የማያልቅ ደስታ) ነው። ሁልጊዜም ችግር ሲፈጠር ዋና ዳኛችን እውነት ሊሆን ይገባል። እውነት ራሱ ክርስቶስ ነው። እውነት በሥርዐት በዶግማ በቀኖና ትገለጣለች። ሥርዐትን አፍርሶ እውነት የለም። የሰው መንጋ መሆን አደገኛ መሆኑን በደንብ የተረዳችሁ ይመስለኛል። ብዙዎች የሰባክያን አጨብጫቢ ሆነው ሰባክያኑ ሲክዱ አብረው ክደዋል። ብዙዎች የዘማሪ አጨብጫቢ ሆነው ዘማሪው ሲክድ አብረው ክደዋል። ይህ በኢትዮጵያችን በዘመናችን ያየነው እውነታ ነው። አሁንም የሰው ተከታይ ብዙ ሰዎች አሉ። የሚከተሉት ሰው ቢሳሳትንኳ ለስሕተቱ ማስተባበያ የሚሰጡ ከእውነት ያፈነገጡ ከሕሊናቸው የተጣሉ ብዙ ናቸው። ሰውን ውደደው እንጂ ከእውነት ጋር ሲጣላ እርሱን ተከትለህ ከእውነት ጋር አትጣላ። እውነትን ያሸነፈ አንድም ውሸት በታሪክ የለም። እውነት የሚባለው ክርስቶስ ያስተማረው ሐዋርያት የሰበኩት ሊቃውንት ያስፋፉት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ትምህርት ነው። ሰው ሊጠላህ ሊሰድብህ ይችላል። ያ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን እንደሰቀሉት ሊሰቅልህ ሁሉ ይችላል። እውነትን ከያዝክ ግን ዓለም በሙሉ ቢጠላህም ዓለምን የያዘው እግዚአብሔር ከአንተ ጋር በመሆኑ ከሁሉ በላይ ነህ። እንደ ታላቅ ወንድም የሚያስቡልን ቅዱሳን መላእክት ይወዱሃል። ሁሉንም በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ለካው እንጂ በግለሰቦች ግላዊ አስተሳሰብ ለመለካት አትሞክር። ኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ጎብረታዊ አረዳድ ያለው እንጂ በግለሰቦች መሰለኝ የተመሰረተ አይደለም። ሁሉም ከቤተ ክርስቲያን በታች ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕግ ካፈረሰ ይወገዛል። የቤተክርስቲያን ራሷ ክርስቶስ ነው። ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮና ሥርዐት ካፈነገጠ ማንም ቢሆን ይወገዛል ይታረማል። አርዮስን፣ ንስጥሮስን የመሳሰሉ ሊቃውንትም ተወግዘዋል። ከቤተክርስቲያን ትምህርት ያፈነገጠ ግላዊ መሰለኛቸውን ትክክለኛ ትምህርት አስመስለው ሲሰብኩ ተገኝተዋልና። ጳጳሱም፣ ዲያቆኑም፣ መነኩሴውም፣ ቄሱም፣ ንጉሡን፣ መኳንንቱም፣ መምህሩም ሁሉም ከቤተ ክርስቲያን በታች ነው። የቤተ ክርስቲያንን ሕጓን ሥርዐቷን ካፈረሰ በእኛ ዘንድ የተናቀ ነው። ችግርን መጋፈጥ እንጂ በአድር ባይነት ካባ ተውጦ ማለባበስ መፍትሄ አይሆንም። ችግርን ቢያለባብሱት እየቆየ ትልቅ ችግር ሆኖ ይመጣል። ሁሉም የክርስቶስ አካሉ በሆነችው በቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ይመዘን። ማንም በራሱ ፈቃድ ጳጳስ የሚሆንበት የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የለም። ይህንን ስሕተት የሰሩ ሰዎች ንሥሓ ገብተው ቢመለሱ መልካም ነው። ካልሆነም ግን ከእግዚአብሔር ሕግ የማይበልጡ ተራ ሰዎች ስለሆኑ ተወግዘው ይለያሉ። ተወለደን ተጸነሰ ይቀድመዋል። ተጸነሰን ደግሞ በቅድምና ነበረ የሚለው ይቀድመዋል።ጌታ ሰው ሲሆን ሥጋን ከሰማይ ይዞ ወረደ አንልም ከእመቤታችን ነሳ እንላለን እንጂ።ከሰማይ ይዞት ከወረደማ ከእመቤታችን ተወለደ አያሰኝም ስለዚህ ከሰማይ ሥጋን ይዞ ወረደ የሚለው አያስኬድም። አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ ስንል ተዋሕዶው

እንዴት ነው ቢሉ በምሳሌ ዘየሐጽጽ እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ ነው። ሰው ነፍስና ሥጋ ቢኖሩትም አንድ ሰው ይባላል እንጂ ሁለት አይባልም።ሰው መባል የሁለቱ ተዋሕዶ ውጤት ነው።ይህንንም ሰፋ አድርገን ስንመለከተው ለምሳሌ የሚራብ የሚጠማ ሥጋችን ነው ወይስ ነፍሳችን? ነፍሳችን ነው እንዳይባል የሰው ልጅ በነፍሱ እንደመላእክት እንደሚኖር ተገልጹዋል መላእክት ደግሞ አይበሉም አይራቡም አይጠሙም። ስለዚህ ነፍስ አትበላም ማለት ነው። ሥጋ ነው የሚራብ የሚጠማ እንዳንል ነፍስ የተለየችው ሥጋ አይራብም አይጠማም። ስለዚህ የተራበው የተጠማው ማን ነው ስንል? ሰው ነው። የቃል እና የሥጋ ተዋሕዶ በዚህ አምሳል ነው።ቃል በሥጋ ተራበ ተሰቀለ እንላለን።ሥጋ በቃል ረቀቀ መላ እንላለን ከተዋሕዶ በኋላ ለያይተን አንናገርም። እንግዲህ ልደት ሲነሳ የወለደችው እናቱም ትነሳለች። ማርያም ግን በልቧ ትጠብቀው ነበር ይላል። የሚደረገውን ምስጢር እያየች እንደ ዘመናችን ሰው ልናገረው አትልም ነበር።በልቧ ትጠብቀው ነበር ብሎ ወንጌላዊ ሉቃስ ገልጾልናል። ጌታን ከእመቤታችን የበለጠ የሚያውቀው ሰው የለም። እናቱ ናት አንዳንዶች እናቱን ሲሳደቡ ያሳዝናሉ በእውነት።እናት እና አባትህን አክብር ብሎ ሕግን የሰራ ጌታን እናቱን ካከበረ ከሃድያን ግን እርሷን መጥላታቸው የእምነታቸውን መሠረት ሰይጣናዊነት ከማስረዳት ውጭ ሌላ አያስገነዝበንም። ጌታ እኔን ምሰሉ ብሎ እርሱን እድንመስል ሕግን እየሰራ አሳይቶናል።ስለዚህ እናቱንም እንወዳታለን እርሱንም እንወደዋለን እንጂን አንዱን ጥለን አንዱን አንጠልጥለን አንሄድም። ስለ ዘመነ ልደት ነቢያት አስቀድመው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ከመንፈስ ቅዱስ ያገኙትን ተናግረዋል።ነቢያት ብቻ አይደሉም ጠንቋዮችም ተናግረዋል።ጥንቁልናንማ እግዚአብሔር ይጠላ የለምን ቢባል አዎ ይጠላል።ነገር ግን ለካዱትም ለተጠራጠሩትም ለአመኑትም ዝናምን የሚያዘንም ፀሐይን የሚያወጣ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ትንቢቱንም በክፉዎች አድሮ ሊያናግር ይችላል። ይህም ቸርነቱን ያስረዳናል። ለምሳሌ በቀያፋ አድሮ ይህ ሁሉ ሰው ከሚሞት አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል ብሎ ትንቢት አናግሮታል። በለዓም ጠንቋይ ነበረ ነገር ግን ኮከብ ይሰርቅ እምያዕቆብ ወያአትት ኃጢአተ ዓለም ብሎ ትንቢት ተናግሯል። ከያዕቆብ ዘር ኮከብ ይወጣል የዓለምን ኃጢአትም ያስወግዳል ብሎ ትንቢት ተናግሯል። ቅዱሳን ነቢያትም በየበኩላቸው ተናግረዋል ኢሳ.7፥14 እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ብሎ በድንግልና እንደምትወልደው ተናግሯል። ቅዱስ ዳዊት ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ ብሎ ሰው አምላክ ሆነ የሚለውን ምሥጢር ተናግሯል። በምሳሌም ሙሴ ሐመልማልና ነበልባል ተዋህደው አይታል ለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ.1፣1 በብዙ ምሳሌ እንደነገራቸው ገልጾልናል። ዳንኤል መቅደስ ትትሐነጽ እስከ ክርስቶስ ንጉሥ ወእምዝ ትትመዘበር ብሎ ተነበየ። የነቢያትን ትንቢት ለመፈጸም ጌታ ሰው ሆነ የምንለው ስለዚህ ነው። ሕዝቅኤል በተዘጋ የምስራቅ ደጃፍ እና በንጉሥ አምሳል የእመቤታችንና የጌታ ነገር ተገለጸለት። ይህንን አይተው ኖኅትሰ ድንግል ይእቲ ብለው እነ ቅዱስ ኤፍሬም ተረጎሙት። ነቢያተ ጽድቅ እንዳሉ ሁሉ ነቢያተ ሐሰትም በብሉይ ነበሩ። ቅዱሳን ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ነው ያሉትን ነቢያተ ሐሰት ደግሞ ከልባቸው አፍልቀው ከሰይጣን ሰምተው አይደለም ይሉ ነበር። በዘመናችንም እንዲህ ዓይነት የሐሰት ነቢያት ሊኖሩ ስለሚችሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛንነት መምህራንን በመጠየቅ እውነተኛውን ትንቢት ማወቅ አለብን። በጠቅላላ በብሉይ ስለ ጌታ መወለድ የተነገሩ ብዙ ምሳሌዎች ብዙ ትንቢቶች አሉ። እነዚህን ትንቢቶች አይሁድ ሳይቀሩ ያውቋቸው ስለነበር

ለሄሮድስ የሚወለድበትን ጊዜ ከነ ቦታው ነግረውት ጌታን እገድላለሁ ብሎ 14 እልፍ ከ4 ሺሕጻናትን አስገድሏል። ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ። የዓለም ሁሉ መድኃኒት ዛሬ ተወለደ። አንድም ስለሁሉ ዓለም ዛሬ ተወለደ ይላልዓለም በጭንቅ የነበረበት ዘመን ዘመነ ብሉይ ዓመተ ኩነኔ ዓመተ ፍዳ በመባል ይታወቃል። ምንም እንኳ ጻድቃንን የሲኦል እሳት በጸጋ እግዚአብሔር ባያገኛቸውም ይኖሩ የነበሩት ግን በሲኦል ነበር። ቅዱሳን ነቢያት ጽድቃችን እንደ መርገም ጨርቅ ሆነ ብለዋል። ምንም ጽድቅ ቢሰሩ መግቢያቸው ሲኦል ነበርና እንዲህ በምሳሌ ተናገረው። ስለዚህ ሰውን ሁሉ ለማዳን የዓለም መድኃኒት ዛሬ ተወለደ።በኀዘን ለነበረው ሰው መልአኩ ለእረኞች ወይም ለኖሎት እንደነገራቸው በሉቃስ ወንጌል እስመ ናሁ ተወልደ ለክሙ ዮም መድኅን ዘይከውን ለክሙ ዓቢየ ፍሥሓ ብሎ ታላቅ ደስታ የሚሆንላችሁ እነሆ መድኃኒት ተወልዶላችኋል። ብሎ በሥቃይ በኀዘን የነበሩ ሰዎች በክርስቶስ ልደት እንደተደሰቱ ይናገራል። የተደሰቱትም መላእክትም ጭምር ናቸው ምክንያቱም መላእክት እንደ ታላቅ ወንድም ናቸውና የእኛ መዳን ቢያስደስታቸው። ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ ብለው አመስግነዋል።በአንድ ኃጥእ በንሥሓ መመለስ በመላእክት ዘንድ ደስታ ይሆናል ይላል። በኃጥእ አዳም ወደ ገነት መመለስ ተደስተዋልና ነው። ይሁንና አዳነን ስንል ምን ማለታችን ነው ስንል በመዳን ሂደት ውስጥ የእግዚአብሔር ድርሻ አለ። ከእኛም የሚጠበቅ ድርሻ አለ። በእግዚአብሔር በኩል ያለው የመዳን ሂደት ሙሉ በሙሉ ተደረገ ማለት ነው። ከዚህ በኋላ የእኛ ድርሻ ይጠበቅብናል። ድርሻችንንም ራሱ እንዲህ እንዲህ አድርጉ እያለ ነግሮናል። ለምሳሌ ያልተጠመቀ አይድንም ተብለናል ስለዚህ መጠመቅ የእኛ ፈንታ ነው ማለት ነው። ስጋዬን ያልበላ ደሜን ያልጠጣ የዘላለም ህይወት የለውም ብሏል ስለዚህ ሥጋውን ደሙን መቀበል የእኛ ፈንታ ነው ይህንና ይህን የመሳሰሉ ከእኛ የሚጠበቁ ድርሻዎች አሉ። እነዚህን ሳናደርግ ብንቀር ችግሩ ከእኛ እንጂ እግዚአብሔር አላዳነንም ተብሎ ሊተረጎም አይገባም። ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ። የደስታችን ምንጭ ዛሬ ተወለደ ስለዚህ ሰብአ ሰገል ሄደው አይተው ተደሰቱ። መላእክት አመሰገኑ እረኞች አይተው ደስ አላቸው። ስለዚህም ሊቃውንቱ በማኅሌት ርእይዎ ኖሎት አእኮትዎ መላእክት..... አንፈርአጹ ሰብአ ሰገል እያሉ በቅዱስ ያሬድ ማህሌት ደስታቸውን ይገልጻሉ። እንግዲህ ሃይ.አበ 90፥18 ላይ አብና መንፈስ ቅዱስ ሰው አልሆኑም ብለናል። አምላክ ሰው ሆነ ካልን አብና መንፈስ ቅዱስ አምላክ አይደሉምን? አምላክ ሰው ከሆነ አብ መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆኑ አያሰኝምን የሚል ጥያቄ በአእምሯችን ሊመጣብን ይችላል። ስለዚህ በዚህ ክፍል ይህንን ለማስረዳት እንሞክራለን። ይህንን ለመረዳት ምሥጢረ ሥላሴን መረዳት ይገባል። እግዚአብሔር አንድ ነው። ይህን ዓለም የፈጠረ እግዚአብሔር በመለኮት አንድ በአካል 3 ነው። ለአብ የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ ፍጹም አካል አለው። ለወልድም ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ ፍጹም አካል አለው። ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም መልክ ፍጹም ገጽ ፍጹም አካል አለው። አብ በአካሉ በሁሉ ያለ የመላ ነው። ወልድም በሁሉ ያለ የመላ ነው። መንፈስ ቅዱስም በሁሉ ያለ በሁሉ የመላ ነው። እንግዲህ እንዲህ ከሆነ ተደራርበው ነው የሚኖሩት ማለት ነው ወይስ እንዴት ነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። አብ ካለበት ቦታ ላይ በሙሉ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አሉ። በሥላሴም ተዋሕዶ አለ ሥላሴ በተዋሕዶ ወተዋሕዶ በሥላሴ ይላል ሃይማኖተ አበው። የሥላሴ አንድነት በሕልውና ነው። ምሥጢረ ሥላሴ ታላቁ ምሥጢር ያለው ኩነት ላይ ነው። አብ ልብ ወልድ

ቃል መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ይባላል። በአብ ልብነት ያስባሉ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ። ይህ ኩነት እንደ አካላት ተከፍሎ የለበትም። ሥላሴን በተዋሕዶ የሚያገናዘብ ይህ ነው። ቃል ሥጋ ኮነ ይላል ዮሐ.1፥14 ቃል ሰው ሲሆን ከአብ ሳይለይ ነው የተባለው በኩነታት ተከፍሎ ስለሌባቸው ነው። ከአብ ሳይለይ በተለየ አካሉ ሰው ሆነ ስንልም እንደ ፀሐይ ብርሃን ነው። የፀሐይ ብርሃን እና ሙቀቱ አይለያይም ብርሃኑ ባለበት ሙቀቱ አለ ይህም ማለት ብርሃን ከሙቀት ተከፍሎ የለበትም ማለት ነው።ነገር ግን ተለይቶ ከዓይናችን ጋር ተዋሕዶ እንድናይ የሚያደርገን ብርሃኑ እንጂ ሙቀቱ አይደለም።ይህንን እንዴት እንረዳዋለን ቢሉ። ሙቀትማ በጨለማ ጊዜም ኑሮ ግን እንድናይ አይረዳንምና ነው። ስለዚህ አብና መንፈስ ቅዱስ ሰው አልሆኑም ሰው የሆነ በተለየ አካሉ ወልድ ነው ማለት ይህ ነው። ስለዚህ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አብና መንፈስ ቅዱስን ከመለኮትነት አላወጣናቸውም ማለት ነው። አንድ የሚሆኑ በሕልውና በመለኮት ነው እንጂ በአካል አይደለምና በተለየ አካሉ ሰው ሆነ ስንል በምልዓት አብ ካለበት ሁሉ የሚኖረው ወልድ ምልአቱን ሳይለቅ ሰው ሆነ እንላለን። ሥላሴ በሕልውና አንድ ናቸው ያልነው ምስጢር ሰው ሲሆን አልፈረሰም። መፍጠር ማዋሐድ እና የመሰሉ ግብሮች የሥላሴ የአንድነት ግብራቸው ወይም ሥልጣናዊ ግብራቸው ነውና። አብ አዋሐደው ወልድ አዋሐደው መንፈስ ቅዱስ አዋሐደው ቢል አንድ ነው። ብዙ ጊዜ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች ሲል። ግብረ አብ ግብረ ወልድ ቢል ያው ነው። አካላዊ ግብር ግን አይፋለስም። አካላዊ ግብር የሚባለውም የአብ መውለድ ማስረጽ የወልድ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ መስረጽ ነው። አብ አጸናት መንፈስ ቅዱስ አነጻት ሲል ብታይ ማንጻት የመንፈስ ቅዱስ ብቻ ማጽናት የአብ ብቻ አይምሰልህ። ስልጣናዊ ግብር ስለሆነ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አጸናት አብ ወልድ አነጻት ቢልም ያው ነው። ጌታ ከሰማየ ሰማያት ወረደ እንላለን ነገር ግን ወረደ የሚባለው በሁሉ ቦታ የሌለ ነው ይህ ነገር እንዴት ነው ቢሉ። ወረደ ሰው ሆነ ተዋሐደ ተብሎ ነው የሚተረጎም። ምክንያቱም ከሰማይ ወረደ ካልን በምድር የለም ኖሯል እንዴ ያሰኛል። እግዚአብሔር ደግሞ በሁሉ ቦታ ያለ ነውና። ወረደ፥ ኮነ፣ ኀደረ ሲል ብታገኘው ተዋሐደ ሰው ሆነ ተብሎ እንደሚተረጎም አስተውል። በሊቃውንት መጽሐፍ ላይ መላእክት ከቦታ ወደ ቦታ እንደሚሄዱት ከሰማይ የመጣ አይደለም መላእክትስ ከሰማይ ወደ ምድር ሲላኩ ከሰማይ ይታጣሉ ከምድር ይገኛሉ። ከምድር ወደ ሰማይ ሲያርጉ ከምድር ይታጣሉ ከሰማይ ይገኛሉ ጌታ ግን ከሰማየ ሰማያት ወረደ ስንል ብትሰማ እንደ መላእክት ከዚያ ሲመጣ ከዚህ የሚገኝ ከዚያ የሚታጣ አይደለም ሰው ሲሆን ምልአቱንም አልለቀቀም እንጂ ይላል። አኮ ዘፈለሰ እመካን ውስተ መካን ከመ መላእክት እስመ እሙንቱ ይትጋጥኡ እመካኖሙ ሶበ ይትፈነው ለመልእክት ውእቱሰ ነስአ ሥጋ እንዘ ምሉእ ውእቱ በኩለሄ እንዲል። የጌታ ልደት ሁለት ነው። አንደኛው ቀዳማዊ ልደት የሚባለው ሲሆን ከአብ አካል ዘእም አካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተወለደው ነው። በዚህ ልደት አንድ ጊዜ ቅድመ ዓለም ተወልዷል እንጂ ሁልጊዜ አይወለድም። ሃይማኖተ አበው ላይ ዘኢየነልቅ ልደቱ ተብሎ ቢገለጽ ወልድ ወልድ ሲባል ይኖራል ማለት ነው እንጂ ሁልጊዜ ሲወለድ ይኖራል ማለት አይደለም። ይህም አብ በዘመን ሳይቀድም ወልድን ወለደው እንላለን። መውለዱ ግን ከሰው ጎሊና ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ስለሆነ ሊቁ እንዳለው ልደተ ወልድ ወጸአተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ይትነከር ወኢይትረከብ ብሎ አድንቆ ዝም ይባላል። ሁለተኛው ከድንግል ማርያም የተወለደው

ልደት ነው። እመቤታችን የወለደችው ከአብ የተወለደውን በሥጋ ነው። ስለዚህም ሥጋ በመለኮት ወልደ አብ ተባለ። ቃል ደግሞ በሥጋ ወልደ ማርያም ተባለ። ያው አንዱ ኢየሱስ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ተባለ። ለዚህ እርሱ ብርሃን እንደተባለ እርሷ እመ ብርሃን እርሱ አምላክ እንደሆነ እርሷ እመ አምላክ ተባለች።ሃይ.አበ 35፤17 ላይ በምድር አባት በሰማይ እናት የለውም ብሏል። በቀዳማዊ ልደቱ ከአብ ያለ እናት ተወለደ። በደኃራዊ ልደቱ ከድንግል ማርያም ያለ አባት ተወለደ። ድንግል ማርያምም በድንግልና እንደጸናች ሃይ.አበ.53፥2 ወነበረት ድንግል በድንግልና ከመ ቀዳሚ ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ ይላል። አብ እና መንፈስ ቅዱስ ሰው አልሆኑም ሰው የሆነው በተለየ አካሉ ወልድ ነው። ሃይ.አበ 90፥18 አብ ወመንፈስ ቅዱስ ኢተሠገው ወኢኮኑ ሰብአ ይላል። እመቤታችን ጌታን የጸነሰችው ይኩነኒ ባለችበት ቅጽበት ነው። ሰው ሆነ የምንለውም ከዚያ ጀምረን ነው። ጌታ ሰው ሲሆን የሥጋ ገንዘብ ለቃል የቃል ገንዘብ ለሥጋ ሆነ ይህንንም ቅዱስ ቄርሎስ እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል ብሎ በድርሳኑ ገልጾልናል። ሃይ.አበ 26 ላይ ሥጋ ወዘአልቦቱ ሥጋ ተደመሩ ኅቡረ በከዊነ አሐዱ ሕላዌ ወበአሐዱ ገጽ ወአሐዱ አካል ይላል ምን ማለት ነው።ሥጋ እና መለኮት በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆኑ ማለት ነው።

በልደት ወይም በሥጋዌ ዙሪያ የተነሱ ክሓድያን

1ኛ ሰባልዮስ፦ ይህ ከሃዲ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ገጽ ናቸው ያለ እና በ220 ዓ.ም አካባቢ የነበረ ሰው ነው። ይህ ሰው ጌታችን የእውነት መንፈስ ጸራቅሊጦስን ይልክላችሁ ዘንድ እኔ አብን እለምንላችኋለሁ ባለው የወንጌል ቃል ይረታል። አንድ ገጽ ቢሆን እልክላችኋለሁ ያለውና የሚላከው የተለያዩ አካላት ባልሆኑ ነበርና።

2ኛ ከ310-390 ዓ.ም አካባቢ የነበረው አቡሊናርዮስ የተባለ ከሃዲ ነው። ክርስቶስ ልብና ነፍስ የለውም። በልቡና በነፍሱ ምትክ መለኮቱ አለ ያለ ከሃዲ ነው። ይህ ደግሞ በዮሐ.10፥17 ነፍሴ እስከ ሞት ተጨነቀች ባለው ይረታል።ነፍሴ ያለው መለኮትን ነው እንዳይል መለኮት አይጨነቅምና በዚህ ይረታል። በተጨማሪም ጌታ ተፈጸመ አለ ራሱን አዘነበለ። ነፍሱም ተለየች ባለው ይረታል። ነፍሱ መለኮቱ ከሆነች መለኮት የሌለበት ቦታ የለምና ሞተ ማለት ትርጉም አይሰጥምና በዚህ ይረታል።

3ኛ ንስጥሮስ ወልድ ከነቢያት እንደ አንዱ ነው አለ። ይህ ከሃዲ ከ351-451 ዓ.ም አካባቢ የነበረ ሰው ነው። ንስጥሮስ ግን ዮሐንስ መጥምቅ በተናገረው ቃል ይረታል ይኸውም "ከእኔ በፊት ያለው እርሱ ከእኔ በኋላ ይመጣል" ይመጽእ እምድኅሬየ ዘሀሎ እምቅድሜየ ባለው ይረታል። እንደነቢያት እግዚአብሔር በጸጋ ያደረበት ቢሆን ኖሮ ከዮሐንስ በፊት ሊኖር አይችልምና። ከዮሐንስ በፊት የነበረው ከዮሐንስ በኋላ በሥጋ የተወለደው የባሕርይ አምላክ መሆኑን ይናገርበታልና በዚህ ይረታል።

4ኛ አርጌንስ ይህኛው ደግሞ ከወልድ አብ ከመንፈስ ቅዱስ ወልድ ይበልጣል ከመላእክት መንፈስ ቅዱስ ይበልጣል ብሎ ያበላለጠ ነው። ነገር ግን እኔና አብ አንድ ነን ባለው አምላካዊ ቃል ይረታል። ከእኔ አብ ይበልጣል ይል የለምን ቢሉ ሕማም የሚስማማው ሥጋን ስለለበሰ

ከአብ ብቻ አይደለም ከመላእክትም ጥቂት አሳነስከው ተብሎ ተጽፏልና ስለ ሥጋ ሐማሚነት ተናገረ እንጂ በሥልጣን በፈቃድ በባህርይስ አንድ ናቸውና መበላለጥ የለም።

5ኛ አርሲስ ወይም አርሲሳን የሚባሉ ከሃድያን ደግሞ ጌታ ነፍሳትን ለማዳን ሥጋውም ወደ ሲኦል ሄዷል ብለዋል። ነገር ግን ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ሥጋውን እንደገነዙት ስለሚናገር በዚህ ይረታሉ።

6ኛ መነናውያን ከ216 እስከ 270 ዓ.ም አካባቢ የነበሩ ከሃድያን ናቸው። የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ነው የሚሉ ናቸው። ምትሐት ማለት እንደ ጥላ ያለ የማይዳሰስ ማለት ነው። ነገር ግን ታመመ ተሰቀለ ስለሚልባቸው ጥላ ወይም ምትሐት ደግሞ አይታመምምና በዚህ ይረታሉ።

7ኛ ልዮን የተወለደው ኢየሱስ አንድ አካል ሁለት ባህርይ ሁለት ፈቃድ ነው። መለኮት የመለኮትን ስራ ይሰራል ሥጋም የሥጋን ስራ ይሰራል ያለ ከሃዲ ነው። የሚያድን መለኮት ነው ይል ነበረ። ይህ ከሆነ ሐዋርያት በመርከብ ሲሄዱ አድነን ብለው ሥጋን ቀስቅሰውታል። መለኮት ብቻ የመለኮትን ስራ ይሰራል ከተባለ መለኮት አይተኛምና ለምን ቀሰቀሱት ፈቃዳቸውን አይቶ አያድናቸውም ነበርን። ይህንና ይህን በመሰለ ኃይለ ቃል ይረታል። በመለኮት እንቅልፍ የሌለበት አንዱ ጌታ በሥጋ ተኛ ተባለ። ከተዋሕዶ በኋላ አንድ ፈቃድ እንጂ ሁለት ፈቃድ የለም። አንድ አካል ካሉ አንድ ባሕርይ ማለት አለባቸው። ሁለት አካል ካሉ ሁለት ባሕርይ ማለት አለባቸው። ሊቁ ሱኑትዩ አካል ያለ ባሕርይ፣ ባሕርይ ያለ አካል የለምና ብሎ እንደገለጸው።

8ኛ አውጣኪ የክርስቶስ ሥጋ የማይደክም የማይታመም ነው ያለ ከሃዲ ነው። በተጨማሪም መለኮት ሥጋን ውጦታል ብሎ የክርስቶስ ሰውነቱን አጥፍቶ አምላክ ብቻ ይል የነበረ ከሃዲ ነው። ነገር ግን ዮሐ.4፣6 ወደኪሞ እግዚእ ኢየሱስ በሐዊረ ፍኖት ነበረ ህየ ባለው ይረታል።

የኛ ትምህርት ግን ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ። ሰው የሆነው አምላክ ነው አምላክም የሆነው ሰው ነው።ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ ከሁለት አካል አንድ አካል አዳምን ለማዳን ሰው የሆነ ከድንግል ማርያም የተወለደው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ነው ብለን እናስተምራለን። እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮ በገነት ካኖረው በኋላ አዳም ሊያደርገው የሚገባውን ነገር ነግሮታል ይኽውም ከእጸ በለስ እንዳይበላ ነው። ምሥጢሩ ጾም ነው።በዚህ ጉዳይ ሦስት ነገሮችን እናስተውላለን ሕግ ምርጫ እና ነጻነትን። ሕግ ፈጣሪ ለአዳም የሰጠው ነው። ነጻነት ደግሞ ሰው የሚጠቅመውንና ይሻለኛል ያለውን ለመምረጥ የተሰጠ በአእምሮ የሚመራ ነው። ምርጫ ደግሞ ነጻነትን ተጠቅሞ የሚመርጡት ነው። አዳም ዕፀ በለስን ቢበላ የሞት ሞትን እንደሚሞት ነግሮታል። ሞት ማለት ነፍስ ከሥጋ መለየት ማለት ነው። የሞት ሞት ማለት ደግሞ ከእግዚአብሔር መለየት ነው። አዳም ግን ነጻነቱን ተጠቅሞ እጸበለስን በላ። ከበላ በኋላ ልጅነቱን አጣ ልጅነት ማለት ክብር ማለት ነው። ይኽውም የጸጋ ክብር ነው። የጸጋ ማለትም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ማለት ነው። ጸጋውን ወይም ልጅነቱን ካጣ በኋላ ግን እግዚአብሔርን በመበደሉ አእምሮው ወደ ጸጸት ተመለሰ። እግዚአብሔርም የአእምሮውን መመለስ አይቶ ባጠፋው ጥፋት ፈታሒ በጽድቅ በእውነት ፈራጅ ነውና 5500 ዘመን ቀጥቶ

ደግሞም መሐሪ ነውና በቸርነቱ ተወልዶ ስለእርሱ ተሰቅሎ ወደ ቀደመ ክብሩ መልሶታል። ስለዚህ ነገረ ልደት የእግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለው ጥልቅ ፍቅር የተገለጸበት ሰውና መላእክት አንድ ላይ ያመሰገኑበት ትልቅ ምሥጢር ነው። አምላክ ሰው የሆነበት ሰውም አምላክ የሆነበት ትልቁ ምሥጢር እኛን ከስቃይ አድኖ ወደ ዘላለም እረፍት ለመመለስ መሆኑን ስናስብ የጌታችን ፍቅር ምን ይረቅ ብለን አድንቀን አድንቀን አድንቀን ግን ስለማንጠግብ ዕፁብኬ ዕፁብ ውእቱ እስመ ለዕፁብ ትርጓሜ አልቦቱ ብለን እናቆማለን። ሊቃውንቱም ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ እያሉ ገልጸውታል። እንግዲህ የልደት ምስጢሩ ሰው አምላክ ሆነ አምላክ ሰው ሆነ የሚለው ነው። ምን ሆነ ስንል ተወለደ። የት ተወለደ ስንል በቤተ ልሔም ተወለደ። መቼ ተወለደ ስንል የዛሬ 2015 ዓመት ወደኋላ ስንቆጥር በምናገኘው ዓመት ታኅሣስ 29 ቀን። ለምን ተወለደ ስንል አዳምን ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ ነው። የተወለደው ማን ነው ስንል እግዚአብሔር። እግዚአብሔር ማለት አምላክ ፈጣሪ ሰማያት ወምድር ማለት ነው። ከማን ተወለደ ስንል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት ተወለደ እንላለን። የተወለደው እግዚአብሔር ከሆነ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ያለ ረቂቅ ሁሉን ቻይ ነው። ዓለምን የፈጠረ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረ ነው። ሰው ደግሞ ውስን የተፈጠረ ድኩም ነው። ስለዚህ አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ ስንል ምን ማለታችን ነው ቢሉ። እንበለ ውላጤ ያለመለወጥ ነው። ይህም ማለት አምላክ ወይም ፈጣሪ ተለውጦ ሰው ፍጡር ሆነ ማለት አይደለም። አምላክ አምላክነቱንና የአምላክነቱን ግብር ሳይለቅ ምልዐቱን ርቀቱን ሳይለቅ በሥጋ ገዘፈ ዘመን ተቆጠረለት የሚዳስሰ የሚጨበጥ የሚታመም ሆነ። ሰውም ውሰንነቱን ሳይለቅ በመለኮት ረቀቀ ዘመን የማይቆጠርለት ሆነ መላ ማለት ነው። ሲጠቃለል ወልድ ዋህድ በተዋሕዶ ከበረ ማለት ነው። ይህንን ምሥጢር በመተው እነ ፎጢኖስ የክርስቶስ ህልውና ከማርያም ወዲህ ነው ብለው ክደዋል። ግን ራሱ ጌታ አብርሃም ሳይወለድ ነበርኩ ባለው ቃል ይረታሉ። እምቅድመ ይትወለድ አብርሀም ሀሎኩ አነ እንዲል። ቅዱስ ኤፍሬም በሃይማኖተ አበው ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው ይላል። ድንግል ማርያምን የፈጠረ ጌታ ከድንግል ማርያም ተወለደ። አርዮስ ወልድ ፍጡር በመለኮቱ አብ እርሱን ፈጠረ እርሱ ደግሞ ፍጥረታትን ፈጠረ ብሎ ካደ። ነገር ግን ዮሐ.1፥3 ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም ባለው ይረታል። ጌታ ሊወለድ 24 ቀን ሲቀረው ማለትም ከታኅሣሥ 5 ጀምሮ ቤተልሔምን በመላእክት በተለየ አስጠብቋታል። እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ያለው የኢሳይያስ ትንቢት ታኅሣስ 29 ተፈጸመ። ኢሳ.7፥14 እግዚአብሔር በአካል ሦስት ስለመሆኑ የሚያስረዱንን ከአራቱ ጉባኤያት ለማየት እንሞክራለን። በብሉይ ምሥጢረ ሥላሴ ለጥቂቶች ካልሆነ በቀር ለብዙው አይታወቅም ነበር። እግዚአብሔር ግን ስለራሱ በብዙ አምሳል እና ትንቢት እንደተናገረ ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ.1፣1 ገልጾልናል። በብሉይ ዘፍ.1፥26 ላይ ሰውን በአርአያችን በምሳሌያችን እንፍጠር ይላል። በዚህ ቃል እንደምንረዳው መፍጠር የፈጣሪ ስራ። ይህ ፈጣሪ ግን እንፍጠር ብሎ የአካልን ከ2 በላይ መሆን ገልጾልናል። ሌላው ዘፍ.11 ላይ ንዑ ንረድ ወንክዐው ነገሮሙ ለከለዳውያን በሚለው ደግሞ ንዑ ባይ አካል አንድ እና። ንዑ የሚባሉ ደግሞ 2 ወይም ከዚያ በላይ አካላት ሊኖሩ እንደሚችሉ ይጠቁማል። ሥላሴ 3 ለመሆናቸው ደንበኛውን ምስጢር የምናገኘው ማቴ 28፣19 ላይ ሑሩ ወመሐሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም ወአጥምቅዎሙ በአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ የሚለው ነው። መጠመቅ

ደግሞ በፈጣሪ እንጂ በፍጡር አይደለምና የአካላትን ሦስትነት ያስረዳናል። ይህ አካለ ሥላሴ እንዴት ነው ቢሉ ለእግዚአብሔር ራስ እንዳለው ዳን.10፣4 ጆሮ ዓይን እንዳለው መዝ.10፥4 ጣቶች እንዳሉት ዘጸ.31፥18 እግር እንዳለው ኢሳ.8፥1 እጆች እንዳሉት መዝ.101 አፍንጫ እንዳለው ወአጼነው መዓዛ መሥዋእቱ ለኖኅ ሲል ይገኛል። ደረት እንዳለው ወጾሮሙ በእንግድዓሁ ይላል። አፍ እንዳለው ወትስማእ ምድር ቃለ አፉየ ይላል። በአጭሩ ይህ እግዚአብሔር በአካል 3 እንደሆነ እና የሰው አምሳል የእግዚአብሔር አምሳል እንደሆነ ራሱ በዘፍ.1፣26 ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ብሎ ገልጾታል። ሌላው ለእግዚአብሔርም ለመላእክትም ለሰው ነፍስም የሴትም የወንድም ጾታ የላቸውምም አይነገርላቸውም። ይህ አካለ ሥላሴ ግን በሁሉ ያለና የሚኖር ነው። በብዙ ገጸ ንባብ አብ ወልድን ወልድየ ሲለው ወልድም አብን አቡየ ሲለው ይስተዋላል። ይህ አብነት የባሕርይ አብነት ነው። ይህ ወልድነት የባሕርይ ወልድነት ነው። አብ አብ ስለተባለ ከወልድ አይበልጥም። ወልድም ወልድ ስለተባለ ከአብ አያንስም። ከአብ ያለ እናት ተወለደ ስንልም እንዴት ተወለደ ለሚለው ባሕርይ ዘእምባሕርይ አካል ዘእምአካል ነው። አብ ወልድን ወለደ ስለተባለ ከወልድ ቀድሞ የነበረበት ዘመን አልነበረም። ሃይ. አበ. አሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ ወዕሩያን እሙንቱ በቅድምና እንዲል። የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ቅድምና አንድ ነው። በዘመን አንዱ ከአንዱ አይበልጥም። በመፍጠር በማዋሐድ በማጽናት በማንጻት አንድ ናቸው። ምንም እንኳ አንዱን ጉዳይ ለአንዱ ሰጥቶ ቢናገር በአካላዊ ግብር ካልሆነ በስተቀር በሥልጣናዊ ግብር አንድ ናቸው። ይህንንም የሚያሳየን ጌታ ስለ ትንሳኤው። ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ ወበሠሉስ ዕለት አነሥኦ... ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስተኛው ቀን አስነሳዋለሁ ብሎ ይኽውም ስለ ሥጋው እንደሆነ ተጽፋል። ስለዚህ ወተንሣእኩ በሥልጣነ ባሕቲትየ ይላል። በራሴ ሥልጣን ተነሣሁ ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ አብ አስነሣው ይላል። በሌላ ገጸ ንባብ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ አስነሣው ይላል። ይሕ ሥልጣናዊ ግብር ስለሆነ ለአንዱ አካል አድሎ ቢናገርም በተገናዝቦ የሚሰሩት ስራ ነው። ተገናዝቦ የሌለበት አካላዊ ግብር ነው። አካላዊ ግብር የሚባለው የአብ መውለድ ማስረጽ ነው። የወልድ መወለድ ነው። የመንፈስ ቅዱስ መስረጽ ነው። ሦስቱ አካላት ለየራሳቸው ናቸው ያሉ ነበሩ። ይህ ግን ስህተት ነው የሚያገናዝባቸው መለኮት አለና። እንደ ሰባልዮስ አንድ ገጽ ያሉም አሉ። ነገር ግን እፌኑ ለክሙ ጸራቅሊጦስሃ መንፈስ ጽድቅ ካልዐ ዘይወጽእ እም አብ ብሎ። ካልዐ ብሎ በአካል ሦስት መሆናቸውን ስለሚያስረዳ። ጉዳዩ ፈራሽ ሆኖ ይገኛል።

መልካም ሐሳብ

ለሥጋም ለነፍስም የማይጠቅም መልካም ሐሳብ የለም። እንዲሁ በሥጋም በነፍስም ጉዳትን የማያመጣ ክፉ ሐሳብም የለም። ሐሳብ ሲቀደስ ንግግርና ተግባርም ይቀደሳሉ። ሐሳብ ሲረክስ ደግሞ ንግግርና ተግባርም ይረክሳሉ። ሰው ልዑል ጎሊና ሲኖረው በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል። ትምክህቱም፣ ደስታውም እግዚአብሔር ይሆናል። በሥጋዊ ጥቅም የማይታለል፣ ሥጋዊ መከራን የማይሰቀቅ፣ ለእውነት ያደላ ንጹሕና ልዑል ጎሊና ሊኖረን ይገባል። ብዙዎቻችን ለምን እንደምንኖር አላወቅንም። በዚህ ምድር ሳለን የምንናገረው፣ የምናስበው፣ የምናደርገው ነገር ሁሉ ከሞት በኋላ ለምንኖረው ዘለዓለማዊ ሕይወት ግብዓት የሚሆን መሆን ሲገባው በቀልድ፣

ለማንም በማይጠቅም ንግግር፣ ጊዜያችንን ስናባክን ይስተዋላል። እያንዳንዱ ድርጊታችን ከፈጣሪ ዘንድ እንጠይቅበታለን። መልካም ከሆነ እንሸለምበታለን። ክፉ ከሆነ ለዘለዓለም እንሰቃይበታለን። ስለዚህ ያለንበትን ሁኔታ ቆም ብለን አስበን በክፉ መንገድ ካለን ንስሓ ገብተን ወደ መልካም መመለስና በመልካም መንገድ ካለን ደግሞ በዚሁ ለመጽናት መጣር አለብን።

ቤተ ክርስቲያን

ወርቅ በእሳት በተፈተነ ቁጥር ጥራቱ እየጨመረ ይሄዳል። እንዲያውም በትርጓሜያችን ወርቅን ሰባት ጊዜ በከውር (በወርቅ ማቅለጫ) ሲያቀልጡት ከወርቅ የበለጠ ዕንቁ ይሆናል ይላል። ሰውም እንዲሁ ነው በመከራ በተፈተነ ቁጥር እንደ ወርቅ እየጠራ ይሄዳል። ሰማዕታት መከራውን አልፈው ቅድስናቸውንና ንጽሕናቸውን ገለጡ። ከመ ወርቅ በእሳት ፈተኖሙ የተባሉ ሰማዕታት ናቸው። እሳቱ የበለጠ ቢነድ ወርቁን የበለጠ ያጠራዋል። እሳት የሚያስፈራው ገለባን እንጂ ወርቅን አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ንጽሕት ናት። የንጽሕናዋ ምንጭ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከውስጥም ከውጭም የሚፈትኗት ብዙዎች ቢሆኑም ይህ ፈተናና መከራ ንጽሕናዋን የበለጠ ይገልጣል እንጂ በፈተናው አትጠፋም። የቤተ ክርስቲያን ራሷ ክርስቶስ ነው። በእርሱ ሁልጊዜ ደስ ይለናል። ቤተ ክርስቲያን ለክፉዎች ሰይፍ ናት። እርሷን ተመርኩዘው በስሟ ቢነግዱ የሚጎዱት ራሳቸው ናቸው እንጂ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም። በሽተኞች መድኃኒታቸውን ቢያቃጥሉ በሽተኞች ራሳቸው ይሞታሉ እንጂ መድኃኒቱ አይጎዳም። ፈተናዎች እስከ ዕለተ ምጽአት መልካቸውን እየቀያየሩ ቢመጡ እኛ የበለጠ እየጠነከርን መሄድ አለብን እንጂ ተስፋ መቁረጥ አይገባም። "ዝናብም ወረደ፥ ጐርፍም መጣ፥ ነፋስም ነፈሰ፥ ያንም ቤት ገፋው በአለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም" ማቴ. ፯፣፳፭። ራሳችንን ዐለት በተባለ በክርስቶስ አስተምህሮ ላይ መመሥረት አለብን። ፍቅረ እግዚአብሔር በልባችን ካልነገሠ ሆዳም፣ ሙሰኛ፣ ዘረኛ የመሆን እድላችን ሰፊ ይሆናል። ለምን ይመስላችኋል ዘረኛ ጳጳሳትን እያየን ያለነው? እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ኃላፊ ጠፊ ለሆነው ለሥጋዊ ፍላጎታቸው ይኖራሉ። ካድሬ ካድሬ የሚያጫውታቸው የብልጽግና ጳጳሳትን የምናየው ለምንድን ነው??? መልሱ ቀላል ነው። እነዚህ ሰዎች እውነታውን ተናግረው እግዚአብሔር ከሚያከብራቸው ይልቅ ዋሽተው ካድሬ ቢያከብራቸው ይመርጣሉ። መለካውያን ናቸው። ከአንድ ቤተክርስቲያን እስከ 40 ሚሊዮን ብር የሚዘርፉ ካህናት ለምን ይመስላችኋል?? እነዚህ ሰዎች "ንብላዕ ዮም ወንሙት ጌሠመ" ዛሬ እንብላ ነገ እንሙት የሚል ሥጋዊ ፍልስፍና ስላላቸው ነው። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን አያውቁቱም። ስለዚህ ምእመናን በእነዚህ አካላት መደንገጥ የለብንም። አብነት ማድረግ ያለብን ሕጓን ጠብቀው ያለፉ ቅዱሳንን ነው። ፍጹም አርዓያ ማድረግ ያለብን ራሱን ክርስቶስን ነው። ወንትልዎ ለፍጹም መልአክነ እንዲል። ነገር ግን ለሁሉ እንደሥራው የሚከፍል ልዑለ ልዑላን እግዚአብሔር በመጨረሻው ሰዓት ይፈርድባቸዋል። ሞት ላይቀር ፈርቶ እውነትን መደበቅ ነውር ነው።

ቅዱስ መርቆሬዎስ

"ሰማዕታት የዚችን ዓለም ጣዕም በእውነት ናቁ። ስለመንግሥተ ሰማያትም መራራ ሞትን ታገሡ" እንዲል ቅዱስ ኤፍሬም የሰማዕታት ዓለማቸውና ደስታቸው ክርስቶስ ነው። ከእርሱ

የሚለያቸው ነገር ሲመጣ ማንንም ሳይፈሩ፣ ማንንም ሳያፍሩ በፍቅር ይገሥጻሉ። ካልተመለሰ ያወግዛሉ። ለሃይማኖታቸው አስተምህሮ እስከሞት ድረስ ይታመናሉ። እንደሀገሩ ይኖሩ፣ እንደ ወንዙ ይሻገሩ ብለው ከክፋት ጋር ተስማምተው አልኖሩም። ሹመታቸው፣ ሽልማታቸው፣ ንብረታቸው ክርስቶስን ከማምለክና ለክርስቶስ ከመገዛት አልከለከላቸውም። ክርስቶስ ለሰማዕታት አብነት ለመሆን በመስቀል ተሰቀለ። ሰማዕታት ከእግዚአብሔር ውጭ የሚፈሩት ኃይል የለም።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ጥንቆላን፣ ሙስናን፣ ዘረኝነትን አምርራ ትጠላለች። በውስጧ የሚኖሩ አንዳንድ ቄሶች፣ ዲያቆናት፣ መምህራን፣ ጳጳሳት፣ ምእመናን ወዘተ እኒህን ነገሮች ሲያደርጉ ቢገኙ በሕግ አፍራሽነት እንዳደረጉት ማስተዋል ይገባል። በእነርሱ ምክንያት ክርስቶስ ራሷ የሆነላትን ቤተ ክርስቲያን መሳደብ አላዋቂነት ነው። የቤተ ክርስቲያን ልኳ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ ሁልጊዜም ትክክል የሆነውንና የሕይወት አባት እርሱ ጌታን ማሰብና በፍጹም ልቡና መከተል ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ንጽሕት ናት። የንጽሕናዋ ምንጭ ደግሞ ራሱ ክርስቶስ ነው። የሕይወት ግምጃ ቤት ናት። ስለዚህ ወደ እርሷ ጠዋትም ማታም እየሄድን አእምሯችንን ማደስ ይገባናል። የንጽሕና ምንጭ፣ የሕይወት ግምጃ ቤት ናት። ሰላም ለክሙ ማኅበራኒሁ ለክርስቶስ ሰላም ለክሙ። ወትረ ሐውጽዋ ለቤተ ክርስቲያን ።

ጾም

"ንጹም ጾመ

ወናፍቅር ቢጸነ

ወንትፋቀር በበይናቲነ"

ይላል ቅዱስ ያሬድ በድጓው። የተከበረው የነቢያት ጾም ደረሰ። እንኳን አደረሳችሁ። ጾም በሦስት መንገድ ይፈጸማል። እነዚህም:-

- ፩) መዋዕለ ጾም እስኪፈጸም የፍስክ ምግብ አለመብላት።
- ፪) የጾሙ ሰዓት እስኪደርስ ምንም ምግብ አለመብላት። ለምሳሌ የነቢያት ጾም የሚጾመው እስከ ዘጠኝ ሰዓት ነው። እስከዚያ መቆየት ነው።
- ፫) እስከ ዕለተ ሞታችን ክፉ ነገርን ከመናገርና ከማሰብ እንዲሁ ከማድረግ መከልከል ናቸው። ሰባት የአዋጅ አጽዋማት አሉ እነዚህም፡-
    - ✓ ፩) የነቢያት ጾም (ሁልጊዜም ህዳር 15 ይጀምራል)
    - ✓ ፪) የነነዌ ጾም
    - ✓ ፫) የገሐድ ጾም

- ✓ ፬) ዐቢይ ጾም
- ✓ ፭) የሐዋርያት ጾም
- ✓ ፮) ጾመ ድኅነት (ረቡዕና ዓርብ)
- ✓ ፯) የፍልሰታ ጾም ናቸው

እኒህን አንድ ሰው ሰባት ዓመት ከሆነው ጀምሮ ሊጾማቸው ይገባል እንደሚገባ በትውፊት ይነገራል።

ሰማዕትነት

ጳጳስ እንደ አቡነ ጴጥሮስ እውነቱን ተናግሮ ይሞታል። ይህን ማድረግ ካልቻለ ደግሞ ዝም ቢል ይመረጣል። መንቀሻቀቻር የለበትም። ከፖለቲከኛ ጳጳሳት ፍትሐዊ ንግግርን መጠበቅ ጅልነት ነው። እውነተኛ ንግግር የሚነገረው ከእውነተኛ ጳጳሳት ነው። ከፖለቲከኛ ጳጳሳት እውነትን መፈለግ እንደዚህ ሰውየ መሆን ነው። የእውነት ልክ ክርስቶስ ስለሆነ ሁል ጊዜም እርሱን አብነት እናደርጋለን እንጂ በየጊዜው እንደ እስስት የሚለዋወጡ በዚህ ምድር ያሉ ጳጳሳትን፣ ቀሳውስትን፣ ፖለቲከኞችን፣ እና የመሳሰሉ አካላትን መከተል አይገባም። በተጨማሪም የዚህ ምድር ሕይወታቸውን ድል አድርገው ያለፉ ቅዱሳንን እናስባለን እንጂ ያልሞተን ሰው መከተል ፍጻሜው ውድቀት ሊሆን ስለሚችል ራሳችንን እንጠብቅ። ኖረህ ብታየው ደስ ይለኝ ነበር። ብዙ ጊዜ የምሰማው የተሳሳተ ንግግር ነው። ብዙ ሰዎች ወዳጃቸው፣ አባታቸው፣ እናታቸው፣ ወንድማቸው፣ እህታቸው እና የመሳሰሉ ሰዎች ከሞቱ በኋላ በደስታቸው ቀን ዛሬ ወዳጄ በሕይወት ኖሮ ቢሆን እያሉ ይመኛሉ። ነገር ግን ሟቾች አሁን እኛ ያለንበትን ሁኔታ የበለጠ ወደሚያውቁበት ዓለም ስለሆነ ያሉት ያዩናል፣ ይሰሙናል፣ ስኬታችንንም ውድቀታችንንም ያዩታል። አብርሃም ነዌን አንተ በሕይወት ዘመንህ ተደስተኻል እንዳለው ማለት ነው። ይህች ምድር የኑሯችን መጨረሻ አይደለችም። ወደተሻለ ዓለም ለመሄድ የምንዘጋጅባት ቦታ ናት። ስለዚህ ሞትን በፍቅር የምንጠብቀው እንጂ የምንፈራው አይደለም። ሞትን ከፈራነው እንኳ የሚያስፈራን ከሞት በኋላ ላለው መልካም ሕይወት የሚያበቃ ሥራ ካልሠራን ብቻ ነው። ሰማዕታት እውነትን ይዘው ለመሞት የሚፋጠኑት ከዚህ ዓለም የተሻለ የደጋጎች ዓለም እንዳለ ስለሚያውቁት ነው። ውሸትን አንግቦ በዚህች ምድር ሺ ዓመት ከመኖር ይልቅ፣ እውነትን ይዞ አንዲት ሰዓት ብቻ በዚህች ምድር መኖር ይሻላል። እውነትን ይዛችሁ ውሸትን የምትቃወሙ ሁሉ በያላችሁበት ሰላም።

አይጥ የጎረሰች ድመት

ባለፈው ታላላቅ የቤተ ክርስቲያኒቱን ቀኖና ጥቂት ግለሰቦች ሲሸሩ ብዙ መምህራን አይጥ እንደጎረሰች ድመት ዝም ጭጭ ብለው ነበር። ከዚህ የሚከፋው ደግሞ የቀኖናውን መጣስ የሚናገሩትን መምህራን ሲሳደቡ ነበር። ለካ ነገሩ ወዲህ ነው። ከእግዚአብሔር ይልቅ ገንዘብና ክብር በልጦባቸው ኖሯል። አንዳንዶች ደግሞ መኻል ሰፋሪ ሆነው ነበር። እንዳይናገሩ ገንዘብ የሚቦጭቁላቸው ጳጳሳት ሊከፉባቸው ሆነ። ዝም እንዳይሉ ሕዝብ ሊከፋባቸው ሆነ። እና

ያልበላቸውን ሲያኩ ነበር። ልቅሶ ቤት ሄደው ስለሰርግ እንደ መስበክ ያለ መኻል ሰፋሪነትን አስተውለናል። በእውነት በመስቀል ተሰቅሎ ካዳነን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ይልቅ ከንቱ ውዳሴና ጥቅማጥቅም በልጦባችሁ ነውን? በእውነትና በውሸት መካከል ሌላ ጠየም ያለ ቦታ የለም። ለእውነት እንኑር። ከሁሉ በላይ እግዚአብሔርን እናስቀድም። ቤተ ክርስቲያን ንጽሕት ስለሆነች ሁልጊዜም እርሷን እንከተላት።

እከብር ባይ ልቡና

ለተወደደ ክርስቲያናዊ ሕይወት "እከብር ባይ ልቡናን መተው" ዋናውና ወሳኙ ነገር ነው። እከብር ባይ ልቡናን ካልተውን እውነተኛ መሆን አንችልም። ሐዋርያት እከብር ባይ ልቡናን ትተው ጌታን ተከትለውታል። ኀደግነ ኵሎ ወተለናከ እንዲል። ሰው እከብር ባይ ልቡናን ሲተው ቢነቀፍ፣ ቢሰደብ፣ ቢተች፣ ቢናቅና የመሳሰሉ ነገሮች ቢደርሱበት አያዝንም። ሁልጊዜም ማድረግ ያለበትን እያደረገ በጌታ ደስ ይለዋል እንጂ። እከብር ባይ ልቡናን የጣለ ሰው ከፈጣሪ ውጭ የሚፈራውም የሚያፍረውም ነገር አይኖረውም። አድርባይነትና ፍርሀት ከሁሉም ሰው መወገድ አለባቸው። ፈሪና አድርባይ ሰው ለምንም አይጠቅምምና። ሁልጊዜም ከራሳችን ይልቅ ቤተ ክርስቲያንን እናስቀድም። ቤተ ክርስቲያናችንም ላይ፣ ሀገራችንም ላይ በአስተዳደር የተቀመጡት አብዛኛዎቹ ማፍያዎች ናቸው። ይህንን ማስተካከል የምንችለውም እኛ ራሳችን ነን። እኒህን አካላት ለመቃወም መጨከን አለብን። መሥዋዕትነትን የሚፈራ ነጻነትን ፈላጊ ሰው ሊኖር አይገባም። ሞት ለሁሉም ሰው የተሠራ ስለሆነ ከሞት የሚያመልጥ አንድም ሰው የለም። እውነትን ይዞ ለእውነት መሞት ግን ትልቅ ዕድል ነው። ከውሸት ጋር ተስማምቶ ከመኖር ሞት እጅግ በጣም የተወደደ ነው። ድኩማኑን እያወረድን ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚመጥኑ አገልጋዮችን ወደፊት ማምጣት ይገባናል። አቅመ ቢስ ፖለቲከኞችን ከወንበር አውርዶ የሀገር ፍቅር ያላቸውን ምሁራንን ወደወንበር ማውጣት ይገባል። እውነቱን ስንነጋገር ብልጽግና እንኳን ሀገርን ቀበሌን የማስተዳደር አቅም የለውም። መሪውም የፓርቲው አባላትም ደካማ ሰዎች ናቸው። እውነትን ይዞ የሚታገል ሰው ኖሮም ጀግና ነው። ቢሞትም ጀግና ነው። ስለዚህ እውነትን ይዛችሁ ለእውነት ስለእውነት የምትታገሉ ጀግኖች በያላችሁበት ፈጣሪ ይርዳችሁ።

መድኃኔዓለም

ሊቃውንት ፍቅሩን የማዳን ሥራውን ቸርነቱን በቅኔያቸው በትርጓሜያቸው በማኅሌታቸው ይገልጻሉ። ሊቁ በሞት የተገለጠ ፍቅር እንዳሉት። ክርስቶስ እኛን ለማዳን በመስቀል ተሰቀለ። እውነት በአደባባይ ተሰቅሎ ሁሉ አየው። ጌታችን ሆይ በቸርነትህ በቀኝህ ከሚቆሙት ደምረን። የቤተ ክርስቲያን ልኳ ይህ ነው። በመስቀል ተሰቅሎ በደሙ አነጻት፣ ቀደሳት ስለዚህም ንዒ ኀቤየ እንቲኣየ ሠናይትየ ዘበእንቲአኪ ተረግዘ ገቦየ ይላታል። ብንኖርም ስለእርሱ እንኖራለን። ብንሞትም ስለእርሱ እየተናገርን እንሞታለን። በእርሱ ሁልጊዜም ደስ ይለናል።

ክርስትና

ክርስትና በሁሉ ነገር ንጹሕ መሆን ነው። ክርስቲያን ሐሳቡ፣ ንግግሩ፣ ድርጊቱ ሁሉ የተቀደሰ

ነው። በማንም ቂም አይዝም። ቂም፣ጥላቻ፣ምቀኝነት የሰይጣን ገንዘቦች ናቸው። ክርስቲያን መረን የለቀቀ ኑሮ የለውም። ዶግማ፣ ሥርዓት፣ ቀኖና የተባሉ አጥሮች አሉት። መልካም ስነ ምግባር በሌለው ክርስቲያን አጋንንት እንደሚያፈዙ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ተጽፏል። ቅዱስ ያዕቆብም ሃይማኖት ያለ ምግባር የሞተች ናት ብሏል። ስለዚህ ክርስቲያን:-

- ✓ ፩) ውሸት የሌለበት
- ✓ ፪) ሐሜት የሌለበት
- ✓ ፫) ቂም በቀል ጥላቻ የሌለበት
- ✓ ፬) የይቅርታ ልብ ያለው
- ✓ ፭) እውነት ተናጋሪ
- ✓ ፮) ፍትሓዊ የሆነ
- ✓ ፯) ዘረኛ ያልሆነ
- ✓ ፰) ፍቅረ እግዚአብሔር ያለው
- ✓ ፱) ፍቅረ ቢጽ ያለው
- ✓ ፲) ትሑት
- ✓ ፲፩) ታጋሽ
- ✓ ፲፪) ንስሓ የሚገባ
- ✓ ፲፫) ሥጋውን ደሙን የሚቀበል

ወዘተ መሆን አለበት። ራሳችንን መመርመር አለብን። በትክክለኛው የእግዚአብሔር ሕግ እየተመራን ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በየዕለቱ መገምገም ይገባል።

ዝምታ

መልካም ነገር መናገር ካልቻልክ ዝም በል። ቢያንስ ክፉ ነገር አትናገር። አንደበትን መግራት ያስፈልጋል። ጽድቅ ከሚመስሉ ኃጢአቶች ራስን መጠበቅ ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ቃል ይምራን። ስሜታችንን በእግዚአብሔር ቃል እንግራው። ዝምታ መልስ የሚሆንበት ጊዜ አለ።

ክርስትና

ክርስትና ከምንም በላይ እግዚአብሔርን መውደድ ነው። በመቀጠል ሰውን መውደድ ነው። ክርስትና እውነት ነው። ይህንን እውነት ለማስለቀቅ ብዙ ውሸታሞች ቢመጡ እውነትን ባለመልቀቅ እስከሞት መታመን ነው። ማንም ቢሆን የማይቀርለትን ሞትን መፍራት

አይገባውም። ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የሚለይ ሥራ እንዳይሠራ ይጠንቀቅ። ለእውነት፣ በእውነት መኖር ይገባል። ልንፈራው የሚገባን እግዚአብሔርን ነው። ፍጡርን ምንም ያህል ባለሥልጣን ቢሆን፣ ባዕለጸጋ ቢሆን፣ ጉልበታም ቢሆን ልንፈራው አይገባም። ማንኛውንም ሰው ማክበር እንጂ መፍራት አይገባም። ልናፍረውም ልንፈራውም የሚገባን እግዚአብሔር መሆን አለበት።

ያልተቋረጠ የክህነት ቅብብሎሽ

- ፩) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
- ፪) ቅዱስ ማርቆስ
- ፫) አናንዮስ
- ፬) መልዮስ
- ፭) ካርዳኖስ
- ፮) ፕሪሙስ
- ፯) ዮስጦስ
- ፰) አማንየስ
- ፱) ማርያኒስ
- ፲) ክላንድንያስ
- ፲፩) አግሪጳኖስ
- ፲፪) ዩልያኖስ
- ፲፫) ዲሜጥሮስ ፩ኛ (ባሕረ ሐሳብ የተገለጠለት)
- ፲፬) ኤራቅሊስ
- ፲፭) ዲዮናስዮስ
- ፲፮) ማክሲመስ
- ፲፯) ቴዎናስ
- ፲፰) ጴጥሮስ ፩ኛ (ተፍጻሜተ ሰማዕት)
- ፲፱) አኪላስ

- ፳) እለእስክንድሮስ ፩ኛ (የጉባኤ ኒቅያ አፈጉባኤ)
- ፳፩) አትናቴዎስ
- ፳፪) ጴጥሮስ ፪ኛ
- ፳፫) ጢሞቴዎስ ፩ኛ (የጉባኤ ቁስጥንጥንያ አፈጉባኤ)
- ፳፬) ቴዎፍሎስ
- ፳፭) ቅዱስ ቄርሎስ ፩ኛ (የጉባኤ ኤፌሶን አፈ ጉባኤ
- ፳፮) ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ፩ኛ
- ፳፯) ጢሞቴዎስ ፪ኛ
- ፳፰) ጴጥሮስ ፫ኛ
- ፳፱) አትናቴዎስ ፪ኛ
- ፴) ዮሐንስ ፩ኛ
- ፴፩) ዮሐንስ ፪ኛ
- ፴፪) ዲዮስቆሮስ ፪ኛ
- ፴፫) ጢሞቴዎስ ፫ኛ
- ፴፬) ቴዎዶስዮስ ፩ኛ
- ፴፭) ጴጥሮስ ፬ኛ
- ፴፮) ድምያኖስ
- ፴፯) አንስታትዮስ
- ፴፰) እንድራኒቆስ
- ፴፱) ብንያሚ ፩ኛ
- ፵) አጋቶን
- ፵፩) ዮሐንስ ፫ኛ
- ፵፪) ይስሐቅ
- ፵፫) ስምዖን ፩ኛ

- ፵፬) እለእስክንድሮስ ፪ኛ
- ፵፭) ቆዝሞስ ፩ኛ
- ፵፮) ቱምድሮስ ፩ኛ
- ፵፯) ሚካኤል ፩ኛ
- ፵፰) ሚናስ ፩ኛ
- ፵፱) ዮሐንስ ፬ኛ
- ፶) ማርቆስ ፪ኛ
- ፶፩) ያዕቆብ
- ፶፪) ስምዖን ፪ኛ
- ፶፫) ዮሴፍ ፩ኛ
- ፶፬) ሚካኤል ፪ኛ
- ፶፭) ቆዝሞስ ፪ኛ
- ፶፮) ሱንትዩ ፩ኛ
- ፶፯) ሚካኤል ፫ኛ
- ፶፰) ገብርኤል ፩ኛ
- ፶፱) ቆዝሞስ ፫ኛ
- ፷) መቃርዮስ ፩ኛ
- ፷፩) ቱምፋኖስ
- ፷፪) ሚናስ ፪ኛ
- ፷፫) አብርሃም
- ፷፬) ፊላታሞስ
- ፷፭) ዘካርያስ
- ፷፮) ሱንትዩ ፪ኛ
- ፷፯) ክርስቶዶሉስ

- ቁርሎስ ፪ኛ
- ሚካኤል ፬ኛ
- መቃርዮስ ፪ኛ
- ገብርኤል ፪ኛ
- ሚካኤል ፬ኛ
- ዮሐንስ ፭ኛ
- ማርቆስ ፫ኛ
- ዮሐንስ ፯ኛ
- ቁርሎስ ፫ኛ
- አትናቴዎስ ፫ኛ
- ገብርኤል ፫ኛ
- ዮሐንስ ፯ኛ
- ቴዎዶስዮስ ፪ኛ
- ዮሐንስ ፭ኛ
- ዮሐንስ ፱ኛ
- ብንያሚ ፪ኛ
- ጴጥሮስ ፬ኛ
- ማርቆስ ፭ኛ
- ዮሐንስ ፲ኛ
- ገብርኤል ፬ኛ
- ማቴዎስ ፮ኛ
- ገብርኤል ፭ኛ
- ዮሐንስ ፲፩ኛ
- ማቴዎስ ፪ኛ

- ፸፪) ገብርኤል ፯ኛ
- ፸፫) ሚካኤል ፰ኛ
- ፸፬) ዮሐንስ ፲፪ኛ
- ፸፭) ዮሐንስ ፲፫ኛ
- ፸፮) ገብርኤል ፯ኛ
- ፸፯) ዮሐንስ ፲፬ኛ
- ፸፰) ገብርኤል ፰ኛ
- ፸፱) ማርቆስ ፰ኛ
- ፹) ዮሐንስ ፲፭ኛ
- ፹፩) ማቴዎስ ፱ኛ
- ፹፪) ማርቆስ ፯ኛ
- ፹፫) ማቴዎስ ፬ኛ
- ፹፬) ዮሐንስ ፲፯ኛ
- ፹፭) ጴጥሮስ ፰ኛ
- ፹፮) ዮሐንስ ፲፯ኛ
- ፹፯) ማርቆስ ፯ኛ
- ፹፰) ዮሐንስ ፲፰ኛ
- ፹፱) ማርቆስ ፰ኛ
- ፺) ጴጥሮስ ፯ኛ
- ፺፩) ቀርሎስ ፬ኛ
- ፺፪) ዲሜጥሮስ ፪ኛ
- ፺፫) ቀርሎስ ፰ኛ
- ፺፬) ዮሐንስ ፲፱ኛ
- ፺፭) መቃርዮስ ፱ኛ

- ፱፲፮) ዮሳብ ፪ኛ
- ፱፲፯) ቂርሎስ ፮ኛ
- ፱፲፰) አቡነ ባስልዮስ ዘኢትዮጵያ
- ፱፲፱) አቡነ ቴዎፍሎስ ዘኢትዮጵያ
- ፱፳) አቡነ ተክለሃይማኖት ዘኢትዮጵያ
- ፱፳፩) አቡነ መርቆሬዎስ ዘኢትዮጵያ
- ፱፳፪) አቡነ ጳውሎስ ዘኢትዮጵያ
- ፱፳፫) አቡነ ማትያስ ዘኢትዮጵያ

የክህነት ምንጭ ከሆነው ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮ እስከአሁኑ ፓትርያርካችን እስከ አቡነ ማትያስ ያለው የክህነት ቅብብሎሽ ከላይ ያለውን ይመስላል። የእያንዳንዱ ቂስ፣ ዲያቆን፣ ጳጳስ ክህነት ቢቆጠር ነቁ እና የክህነቱ ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በጉልበት ራሳቸውን የሾሙ እና ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ባፈነገጠ መልኩ የተሿሿሙ ሰዎች ክርስቶሳዊ የሆነው ክህነት የላቸውም። ይህም ማለት ቀድሰው ምሥጢራትን አይለውጡም። ጸጋ እግዚአብሔርን አያሰጡም። ስለዚህ ሕገወጥነትን አምርረን ልንቃወም ይገባናል።

መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል

የጌታን ደም በብርሃን ጽዋ ተቀብሎ ዓለምን የረጫትና የቀደሳት ይህ ግሩም መልአክ ነው። ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ እንዲል። ዑራኤል አንድም ዑርኤል ይለዋል። ዛሬም እግዚአብሔር ባወቀ ቤተ ክርስቲያን የሚታነጽ በት ቦታ የጌታ ደም የነጠበበት ልዩ ቦታ ነው። በመብረቅ በነጎድጓድ የተሾመ መልአክ ነው። ዋልያ ከጸነሰች በኋላ ስትወልድ የወለደችው ግልገል ግማሽ አካሉ ከማኅፀኗ ወጥቶ ግማሽ አካሉ በሆዷ ቀርቶ ብዙ ቀናት ይቆያል። በዚህ ጊዜ ግማሽ አካሉ ከሆድ ግማሽ አካሉ ከውጭ ወጥቶ ሳር እየበላ ለጥቂት ጊዜ ይቆያል። ቅዱስ ዑርኤል ነጎድጓድና መባርቅትን ባሰማ ጊዜ ያ የዋልያ ግልገል ደንግጦ አፈትልኮ ከእናቱ ማኅፀን ይወጣል። መላእክት ብዙ ናቸው። ዕፀዋትን፣ እንስሳትን፣ ግዑዛን ፍጥረታትን ሁሉ ይጠብቁ ዘንድ በፈጣሪ የተሾሙ ናቸው። ዑራኤል ነቢዩ ሄኖክን የረዳ መልአክ ነው። መብረቅ በበረቀ ጊዜ አበቦች ይፈካሉ። ፍጥረታትን ሁሉ የሚመግብ እግዚአብሔር ይመስገን።

መፍትሔ

መፍትሔ የሌለው ችግር የለም እውነተኞች አልጸና ብለው ቆይተው ሐሰተኞች ሊሆኑ ይችላሉ። ሐሰተኞችም ንስሓ ገብተው በሌላ ጊዜ እውነተኞች ሊሆኑ ይችላሉ። እውነት ግን

ቆይታ ሐሰት አትሆንም። ሐሰትም ቆይታ እውነት አትሆንም። ለዚያ ነው ሰው እውነትን ከያዘ በማንም ፊት በደስታ ይኖራል። የሚያፍረውም የሚያሳፍረውም አይኖርም። ከምእመን እስከ ፓትርያርክ፣ ከካደሬ እስከ ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ ካልተማረ ሰው እስከ ሳይንቲስት እስከ ፕሮፌሰር ያሉ ሰዎች ሊሳሳቱ ስለሚችሉ በእነርሱ ላይ የተመሠረተ እውነት ሊኖረን አይገባም። እውነታችን ክርስቶስ ይሁን። ቁስ ቢሰክር፣ ጳጳስ ዘማዊ ቢሆን፣ መነኩሴ ዘረኛ ቢሆን እኒህ ሰዎች ቆቡን አደረጉት እንጂ ክርስቶስ ባስተማረው እውነት የማይመሩ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ ራሳቸውን ችለው ራሳቸውን ይጎዳሉ። ስለዚህ በእነርሱ ምክንያት ራሳቸው ይሸማቀቁ እንጂ ሌላው ክርስቲያን ሊሸማቀቅ አይገባም። የክርስቲያን ዋና አብነት ስሕተት የሌለበት ሁልጊዜም ንጹሕ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሁልጊዜም እርሱን እንመልከት። ሌላውንም በእርሱ ትእዛዝ እንመዝን። ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜም ንጽሕት ናት። በቁሶች፣ በጳጳሶች፣ በመነኩሴዎች ምክንያት የምትረክስ ቤተ ክርስቲያን የለችንም። በኖኅ መርከብ ውስጥ እባብም ርግብም ነበሩ። እባብ ስላለ ከኖኅ መርከብ አልገባም አይባልም። በኖኅ መርከብ የተመሰለችዋ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ እባቦች ቢኖሩ በእነርሱ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን አልሄድም፣ አልቀርብም፣ ንስሓ አልገባም አይባልም። በቁሶች በዲያቆናት በመምህራን በጳጳሳት ምግባረ ብልሹነት ምክንያት የምንርቃት ቤተክርስቲያን የለችንም። የቤተ ክርስቲያን ሕይወቷ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ ሁልጊዜም በደስታ ወደእርሷ እንቀርባለን። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የነጻች ንጽሕት ቅድስት ናት። እውነትን እስከመጨረሻው ልንይዛት ይገባል። ነጻ የምታወጣን እውነት ናት። መፍትሔ የሌለው ችግር የለም። ለክርስቶስ መንግሥት ሳይሆን ለምድራዊ መንግሥት የሚያገለግሉ ጳጳሳት ሊኖሩ ይችላሉ። ለምድራዊ ሕይወት ለገንዘብ፣ ለሹመት የሚኖሩ ስለወዲያኛው ዓለም የማያስቡ ሰዎች ይኖራሉ። በእነርሱ ምክንያት ቤተ ክርስቲያንን መራቅ አይገባም። እንዲያውም እነዚህን ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን የበለጠ ቀርበን ልናስወግዳቸው ይገባል። የቤተ ክርስቲያን የማይሳሳት አባቷ ክርስቶስ ነው። አካሏ ነው። ምእመናንን ከኀጢ ከፈሰሰው ውሃ ወለዳቸው። በደሙ አነጻቸው። ስለዚህም ምእመናን የሚመኩበት ትምክህታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሁልጊዜም እርሱን እንመልከት። የእግዚአብሔርን ሕጉን ትእዛዙን እንጠብቅ።

በቤተ ክርስቲያን ያሉ ነገሮች ምሳሌዎቻቸው

፩) ቤተክርስቲያን_____የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ

፪) መቅደስ_____የቀራንዮ ምሳሌ

፫) ታቦት፣መንበር____የእመቤታችን ምሳሌ

፬) ኩስኩስት_____የእመቤታችን ምሳሌ

፭) ማይ_____የማይ ሕይወት ክርስቶስ

፮) መሠረቱ_____ከአዳም እስከ ኖኅ ያሉ የአስሩ አበው ምሳሌ

፯) ሦስት ደጃፍ_____የሥላሴ ምሳሌ

፰) ትልልቅ መስኮቶች___የዐበይት ነቢያት ምሳሌ

፱) ትንንሽ መስኮቶች____የደቂቀ ነቢያት ምሳሌ

፲) የውስጥ አዕማድ_____የሐዋርያት ምሳሌ

፲፩) የውጭ አእማድ_____የ፵፪ቱ አርድእት ምሳሌ

፲፪) ፬ ማዕዘን_____የአራቱ ወንጌላውያን፣ የኪሩቤል ምሳሌ

፲፫) መብራት_____የሊቃውንት ምሳሌ

፲፬) በሮች_____የቅዱሳን አበው ምሳሌ

፲፭) ጠርብ_____የሰማእታት ምሳሌ

፲፮) ማገር_____የረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ

፲፯) ሣሩ_____ሄሮድስ ያስፈጃቸው ሕፃናት ምሳሌ

፲፰) መጋረጃ_____የመላእክት፣የረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ

፲፱) የሰጎን እንቁላል___የተዘክሮተ እግዚአብሔር ምሳሌ

፳) አፀደ ቤተክርስቲያን፣ ቅጽረ ቤተክርስቲያን__የመላእክት ምሳሌ

፳፩) ደጀሰላም___የገነት ምሳሌ

፳፪) ሁለቱ ቅጽር__አንዱ የናዜብ አንዱ የአድማስ ምሳሌ ናቸው። ሁለት ቅጽር ማለት እንደ ጎንደር ቅዱስ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን እንደ አዲስ አበባ አራዳ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሁለት ቅጽር ያለው ቤተ ክርስቲያንን ያመለክታል። "እሪያ አብሮ የሚኖረው መልኩን ላለማየት እውነተኛ መልኩን ያሳየውን ዕንቁ ረግጦ ይሰብረዋል። ችግሩኮ የመልኩ ክፉነት ነው እንጂ ዕንቁውማ ያለውን መልኩን ነበር ያሳየው። ዓለማችን በኃጢአት የበለዘ ፊቷን የሚያሳዩዋትን የእውነት መቅረዞች እንደምንም ተሯሩጣ መርገጥ ትፈልጋለች" ይላሉ ሊቀ ሊቃውንት ስምዐኮነ መልአክ። ቅድስት ቤተክርስቲያን ራስን ማያ ንጽሕት ናት። ፖለቲከኞች እና ዓለማውያን ሰዎች ይጠሏታል። ምክንያቱ ግን ቤተ ክርስቲያን የምትጠላ ሆና ሳትሆን የእነርሱን ቆሻሻነት በጠራ እና ንጹሕ በሆነ አስተምህሮዋ ስለምትገልጥባቸው ነው። በመሆኑም እርሷን ለማጥፋት በርትተው ይሠራሉ። ንጽሕቷን እመቤት ለማጥፋት ከመሞከር ግን የራስን ቆሻሻ ማራገፍ ይገባ ነበር። ከሕግ ውጭ የሆኑ በዘረኝነት የታወሩ ጳጳሳት፣ መነኮሳት፣ መምህራን፣ ምእመናን ቤተ ክርስቲያንን ይጠሏታል። ምክንያቱም ድርጊታቸውን በቀኖናዋ በዶግማዋ በአስተምህሮዋ ስለምትቃወምባቸው ነው። አባት መስለው ሊያጠፏት የቀረቡ ብዙ ናቸው። እርሷ ግን መሠረቷ እና ሕይወቷ ክርስቶስ ስለሆነ ለዘለዓለም ትኖራለች።

ከዋክብት

፩) ምልክኤል_____መጋቢት 26- ሰኔ 25

፪) ሕልመልሜሌክ___ሰኔ 26-መስከረም 25

፫) ብርክኤል____መስከረም 26-ታኅሣሥ 25

፬) ናርኤል_____ታኅሣሥ 26-መጋቢት 25

ከዋክብት የተፈጠሩት በዕለተ ረቡዕ ነው። የዕለት መጋቢ ኮከብ አለ፣ የወር መጋቢ ኮከብ አለ። ከዋክብት ብዙ ናቸው። ከላይ ያሉት አራቱ ከዋክብት የአራቱ ወቅቶች መጋብያነ ከዋክብት ናቸው። አራቱ ወቅቶች የተባሉትም።

- ፩) በልግ (ተወን፣ጸደይ)
- ፪) ክረምት
- ፫) መጸው
- ፬) ሐጋይ (በጋ)

አራቱ ባሕርያት የሚባሉት ደግሞ እሳት፣ ነፋስ፣ ውሃ፣ መሬት ናቸው። የእነዚህም የየራሳቸው ግብር አላቸው።

- ፩) የእሳት ግብሩ ብሩህነት፣ ሞቃትነት፣ ደረቅነት
- ፪) የነፋስ ግብሩ ሞቃትነት፣ ቀዝቃዛነት፣ ጥቁርነት
- ፫) የውሃ ግብሩ ብሩህነት፣ ርጥብነት፣ ቀዝቃዛነት
- ፬) የመሬት ግብሩ ደረቅነት፣ ጥቁርነት፣ ርጥብነት

ይህ የአራቱ ባሕርያት ግብር ነው። የሰው ልጅ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከአንዲት ባሕርየ ነፍስ ተፈጠረ ይባላል እንጂ ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ አይባልም። የነፍስ ባሕርይ አንድ ነው። የነፍስ ግብራተ ባሕርይ ግን ሦስት ናቸው። እነዚህም:- ነባቢነት፣ ለባዊነት፣ ሕያውነት ናቸው። እኒህን ባሕርይ ካልን ግን የአራቱ ባሕርያትም ሦስት ሦስት ግብራተ ባሕርይ ስላላቸው የሰው ልጅ ከ12 ባሕርያት ተገኘ ያሰኛል። ይህ ግን ልክ አይደለም። ደንበኛው ትምህርት በአሪት ዘፍጥረት ትርጓሜ እንደተገለጠው ሰው ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ እና ከአንዲት ባሕርየ ነፍስ ተፈጠረ ቢል ነው።

የአምስቱ ቅንዋት ቦታ

- ✓ ፩) ሳዶር:- መስቀሉን ያመሳቀሉበት

- ✓ ፪) አላዶር፡- ቀኝ እጁን የቸነከሩበት
- ✓ ፫) ዳናት፡- ግራ እጁን የቸነከሩበት
- ✓ ፬) አደራ፡- ሁለት እግሩን በአንድ አድርገው የቸነከሩበት
- ✓ ፭) ሮዳስ፡- ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሥ አይሁድ ብለው ጽፈው በመስቀሉ ጫፍ ሮዳስ በተባለ ችንካር አያይዘውበታል። ከሥዕለ አድኅኖው ጫፍ ላይ "ኢ. ና. ን. አ" የሚለው "ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሥ አይሁድ" የሚለው በምሕፃረ ቃል ተጽፎ ነው።

ከ፲፫ቱ ሕማማተ መስቀል ጋር የሚቆጠሩት ግን ፬ቱ ቅንዋት ናቸው። እነዚህም ሳዶር፣ አላዶር፣ ዳናት እና አደራ ናቸው። መስቀሉን ያመሳቀሉበት ሳዶር እያለፈ አካሉን ይወጋው ነበርና።

ቤተ ክርስቲያን

የቤተ ክርስቲያን አካሏ ሕይወቷ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለሆነም ሁልጊዜም ንጽሕት ናት። ለመዳን እርሷን የተጠጉ ሰዎች ግን ከምእመን እስከ ፓትርያርክ ሊሳሳቱ ይችላሉ። ቢሳሳቱ ግን ስሕተታቸው በዋናነት ራሳቸውን ይጎዳል እንጂ የቤተ ክርስቲያንን ስም አያጠለሽም። ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ቅድስት ንጽሕት ናትና። የቤተ ክርስቲያን ልኳ ሕይወቷ ክርስቶስ ነው። እርሱን ሁልጊዜም እናስብ።

አምስቱ ኀዘናት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተለየ ያዘነችባቸው ፭ቱ ኃዘናት የሚከተሉት ናቸው።

- ፩) ስምዖን ጌታን እንደሚሰቅሉት በተነበየ ጊዜ
- ፪) በቤተመቅደስ ሦስት ቀን ፈልጋ ባጣችው ጊዜ
- ፫) ልጇን ጌታን እጁን አስረው አይሁድ ሲገርፉት
- ፬) ልጇ ኢየሱስ በሸፍቶች መካከል ሲሰቀል
- ፭) ጌታን በሥጋው በመቃብር ሲቀብሩት

ጌታም እነዚህን አምስቱን ኀዘናት አስቦ አቡነ ዘበሰማያት የሚለውን እምረዋለሁ። መንግሥቴንም አወርሰዋለሁ ብሏታል። ተገቢ ኀዘን እና ተገቢ ያልሆነ ኀዘን አለ ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን ግፍዐ ሰማእታትን እያሰቡ ማልቀስ በደልን እያሰቡ በንስሓ ማልቀስ ዋጋ ያለው ልቅሶ ነው። ሥጋዊ ነገር አጣሁ ብሎ ማልቀስ ግን አይገባም።

ተስዓቱ ቅዱሳን

- ➢ ፩) አባ አረጋዊ

- ፪) አባ ሊቃኖስ
- ፫) አባ ይምአታ
- ፬) አባ ጽሕማ
- ፭) አባ ጉባ
- ፮) አባ አፍጼ
- ፯) አባ ጸንጠሌዎን
- ፰) አባ አሌፍ
- ፱) አባ ገሪማ (አባ ይስሐቅ?)

በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ዘረኝነት በጣም የተጠላ ተግባር ነው። ስለሆነም ጻድቃንን የትም ይወለዱ በየትኛውም ዘመን ይነሡ በእኩልነት እንወዳቸዋለን። ተስዓቱ ቅዱሳን ከውጭ ሀገር መጥተው ለኢትዮጵያ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ውለታ የዋሉላት አባቶቻችን ናቸው።

ቤተ ክርስቲያን

ቤተክርስቲያን ሁልጊዜም ንጽሕት ናት። ይህንን ማንኛውም ሰው ጠንቅቆ ሊረዳው ይገባል። አንድ ጳጳስ ወይም ፓትርያርክ ወይም መምህር ቢያጠፉ ራሱን ይጎዳል እንጂ በእርሱ ምክንያት የምትጎዳ ቤተ ክርስቲያን የለችም። ስለዚህ መደንገጥ አያስፈልግም። ከዚያስ እንደዚህ በፍቅረ ሢመት ያበዱ ሰዎችን ሊቃውንቱ፣ ምእመናን፣ ካህናት እየተመካከርን ከቤተ ክርስቲያን የመለየት ሥራ ብንሠራ ጥሩ ነው። ሁሉም ሕገ ወጦች በሕገ ወጥነታቸው ራሳቸውን ይጎዳሉ እንጂ ሌላውን አይጎዱም። ስለዚህ እየተመካከርን ከክፋታቸው እስኪመለሱ አጠንክረን መቃወም ይገባናል። ሁሉም ክርስቲያን ንስሓ እየገባ፣ እየቆረበ፣ ከደብሩ ካህናት ጋር በየአጥቢያው እየመከረ በፍቅር ይኑር። ቤተ ክርስቲያን የበለጠ እንቅረባት።

ኪሩቤል

የአራቱ ኪሩቤልን ስም ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ይላቸዋል

- ✓ ፩) ባራማራ
- ✓ ፪) እግረማጣ
- ✓ ፫) ሱርትዮን
- ✓ ፬) መሊጦን

ይላቸዋል። ሃይማኖተ አበው ላይ ስለዚህ ኪሩቤል ሲናገር መናብርት ነባብያን ይላቸዋል። የሚናገሩ መናብርት ይላቸዋል። ከሱራፌል ነገድና ከኪሩቤል ነገድ ሁለት ሁለት ተመርጠው

በጠቅላላው አራት ኪሩቤል አሉ። እንደገና በኢዮር ከሚገኙት አርባ ነገዶች አሥሩ ነገድ ኪሩቤል ይባላል። ሰአሉ ለነ ኀበ እግዚአብሔር ጸባዖት___ቅ. ያሬድ። (ኪሩቤል ሆይ ወደአሸናፊ እግዚአብሔር ለምኑልን)

የቀበሮ ፍርድ

ክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል በአንድ መጽሐፋቸው በግጥም መልኩ ያስቀመጡት ድንቅ ነገር አለ። ይኽውም በአንድ ወቅት በእንስሳት እና በአራዊት ዓለም ታላቅ መከራ ይደርሳል። እና አራዊቱ እንስሳቱ ይሰበሰቡና ይህ ሁሉ የሆነው በኃጢአታችን ምክንያት ስለሆነ ንስሓ እንግባና ፈጣሪ ምሕረቱን ያውርድልን ይባባላሉ። ከዚያ ሁሉም መናዘዝ ይጀምራሉ። አንበሳ ሲናዘዝ "አንድ ወጣት ልጅ ላም እየነዳ ሳለ አንድ ቀን ላሚቱንም ሰውየውንም በልቻቸዋለሁ" ይላል። ይህን ጊዜ ቀበሮ የተከበሩ አንበሳ ያ ልጅ በእርስዎ በመባላቱ እንዲያውም እድለኛ ነው። እርስዎ ያጠፉት ምንም ዓይነት ጥፋት የለም ብላ ትናገራለች። እንዲህ እንዲህ እያሉ ሁሉም ከተናዘዙ በኋላ መጨረሻ ላይ አህያ መናዘዝ ጀመረች። እኔ አንድ ቀን ጌታዬ ጭኖኝ ወደ ገበያ ስሔድ ባለቤቱ ሳያየኝ ከሰው ማሳ አንድ ጉራሽ የሚሆን ሣር በልቻለሁ ትላለች። ይህን ጊዜ ቀበሮ አህያን "አንች አመዳም ለካ ይህ ሁሉ ግፍ የደረሰብን በአንቺ ምክንያት ነው" አለቻትና ሁሉም ተረባርበው በሏት ይላሉ። ቀበሮዎች ፍርዳቸው እንዲህ ነው። በገንዘብ በጉልበት በሥልጣን ከእነርሱ የሚበልጥ ሰው ከመጣ ቢሳሳትም እንደ ጽድቅ ይቆጥሩለታል። የሰው ልጅ አእምሮ እስካለው ድረስ ውንብድናን በእኩልነት መቃወም አለበት። አድሏዊነት የትንንሽ ሰዎች ሥራ ነው። የሁላችንም መመሪያ እውነት ነው መሆን ያለበት። እውነት ደግሞ እግዚአብሔር ነው። አንዳንዶችን ዘረኝነት አውሯቸው የእነርሱ ዘር የመሰላቸው ሲያጠፋ ዝም ይላሉ። የሌላ ነው ብለው ያሰቡት ሲያጠፋ የእውነት ሰዎች መስለው ዓይናቸውን በጨው አጥበው ይመጣሉ። [እትየ ስመኝ ለማያውቁሽ ታጠኝ]። መፍትሔ የሌለው ችግር የለም። መፍትሔውን ለማምጣት ግን በችግሩ ዙሪያ ያለን እይታ ተቀራራቢ መሆን አለበት። የቤተክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በእርሱ ሕግ ከተመራን በቀላሉ ችግሮችን መፍታት እንችላለን። ከቀበሮ ፍርድ መውጣት ይገባል። እውነት፣ ቀኖና፣ ደግማ፣ አስተምህሮ እንዲኖኙ እድል ይሰጣቸው።

ኢየሱስ ክርስቶስ

የሕይወታችን መሠረት እርሱ ነው። እርሱ ተሠቅሎ ዓለምን አዳነ። የቤተ ክርስቲያን አባቷ ባለቤቷ እርሱ ነው። ሌላው አስተናጋጅ ነው። አስተናጋጅ ሲያጠፋ ለባለቤቱ መንገር ከሁላችንም ይጠበቃል። ከሁልጊዜው በበለጠ ለባለቤቱ ለክርስቶስ በጸሎት ማሳሰብ ይጠበቅብናል። በእርግጥ እርሱ ሁሉንም ያውቃል። ግን ደግሞ በልጅነት አንደበት ብንጠይቀው ቸር አባት ስለሆነ መፍትሔ ይሰጠናል።ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ከመቼውም ጊዜ በላይ ነቅቶ ማስተማር ይጠበቅባችኋል። ሰይጣናት የጳጳስ ቆብ ለብሰው ከመጡ ቆይተዋል። ስለዚህ እነርሱን በሙሉ ኃይላችን መቃወም ይገባናል። የቤተ ክርስቲያን አካሏ ይህ ነው። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተመሠረተች ንጽሕት ቅድስት ናት። ለመዳን ወደእርሷ የተጠጉ ሰዎች ግን ከጨዋ እስከ ፓትርያርክ እስከ ሲኖዶስ ሊሳሳቱ ይችላሉ። በእነርሱ ምክንያት እርሷን መስደብና መንቀፍ ይቁም። ክርስቶስንምኮ ይከተሉት ከነበሩት አምስት ገበያ ሕዝብ ዓላማቸው ልዩ ልዩ ነበረ።

አንዳንዶቹ ለከርሣቸው፣ አንዳንዶቹ ለትምህርቱ ተከትለውታል። አካሏ ክርስቶስ የሆነላትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አንዳንዱ ለሆዱ፣ አንዳንዱ ለፖለቲካዊ ርእዮተ ዓለሙ፣ አንዳንዱ ለመዳን ይጠንታል። ለመዳን የተጠንት ነፍሳቸውንም ሥጋቸውንም ጠቀሙ። ለሌላ ዓላማ የተጠንት ግን ራሳቸውን ከመጉዳት የዘለለ ምንም አያመጡም። ሰይፍን ቢመረኮዙ ራሳቸው ይጎዳሉ እንጂ።

ቀኖና ሊሻሻል ይችላልን ?

መልሱ አዎ ቀኖናን ማሻሻል ይቻላል የሚል ነው። ቀኖናውን የሚያሻሽለው ግን ማን ነው? እንዴት ነው? ለምን? ለሚሉ ጥያቄዎች ፍትሐ ነገሥት በቂ ምላሽ አለው። እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ። ፍት. ነገ. ፶፩፣፲፱፲፮ ወዘሰ ብውሕ ለሊቅ ዘውእቱ ሊቀ ጳጳሳት ከመ ይወስክ ዲቤሁ ወያንትግ እምኔሁ። በተጻፈው ላይ ይጨምር ዘንድ ከተጻፈው ይከፍል ዘንድ ለሊቀ ጳጳሳት የሚገባው ይህ ነው። ቁ. ፲፱፲፯ ወለዘተጽሕፈሰ ኢይከውኖ ለመኑሂ ከመይወስክ ዲቤሁ ወከመ ያንትግ እምኔሁ። በተጻፈው ላይ መጨመር ከተጻፈው መክፈል ግን ለማንም ለማን አይገባውም። በግልጽ የተጻፈን ቀኖና ማንም ማን ቢሆን ሊጨምርበትም ሊቀንሰውም አይችልም። ይህ ሠለስቱ ምእት የሠሩልን ቀኖና ነው። ፲፱፲፲፭ ወካልእኒ ዘኢተግህደ በመጻሕፍት እንተ አእመርነ ኪያሃ። ሁለተኛውም አስቀድመን በተናገርነው መጽሐፍ ያልታወቀ ነው። ወኢኮነ ክሡተ ይግበሩ ባቲ። ሊያደርጉት ያልተገለጠ ነው። ፲፱፲፱፲፱ ወለዝንቱ ባሕቲቱ ቦቱ መባሕት ከመ ይፍታሕ ወይእሥር። ለኤጲስ ቆጶስ ያሥር ይፈታ ዘንድ በዚህ ማዘዝ መሠልጠን ይገባዋል እንጂ። ቅዱስ ሲኖዶስ፣ ጳጳሳት ሊያሻሽሉት የሚችሉት ጉባኤ ያልቆመለትን በግልጽ በመጽሐፍ ያልተጻፈን ጉዳይ ነው ይላል። በግልጽ ሥርዓት የቆመለትን ጉዳይ ግን ማሻሻልም መለወጥም አይችሉም። ወባሕቱ ይግበር በሥርዓተ ውሳኔ። ነገር ግን በተወሰነ ሥርዓት ያድርግ። ሥርዓት ያልቆመለት ጉዳይ ቢኖር እንኳ ቀኖና ለመሥራት የሚከተሉትን መሥፈርቶች ማሟላት አለበት።

- ፩) ሊቀ ጳጳሳቱ መጽሐፍ አዋቂ ይሁን
- ፪) ሊቀ ጳጳሳቱ ሃይማኖቱ የቀና ይሁን
- ፫) ሊቀ ጳጳሳቱ መልካም ምግባር ያለው ይሁን
- ፬) ሊቀ ጳጳሳቱ ሊቃውንቱን፣ ካህናትን፣ ጳጳሳትን፣ ደጋግ ሃይማኖተኛ መኳንንትን ያማክር
- ፭) ሥርዓቱ የሚሠራላቸው ምእመናን ሊተገብሩት ይችላሉ ወይስ አይችሉም የሚለውን መርምሮ ይወቅ።
- ፮) ሊቃውንቱ፣ ካህናቱ፣ ኤጲስ ቆጶሳቱ፣ ሃይማኖተኛ መኳንንቱ ጉዳዩን በጥልቀት ከመከሩበት በኋላ ሁሉም ተስማምተውበት ቀኖና ይሠራ። የተሠራው ቀኖናው በየአብያተ ክርስቲያናቱ ይነበብ ይላል።

ቀኖና ሲሻሻልም ሲሠራም የሚደረገው እንዲህ ነው። ከዚያ ውጭ አንዱ ፓትርያርክ ብድግ ብሎ አሻሽያለሁ ተቀበል ማለት አይችልም። ሊቃውንቱ፣ ካህናቱ፣ ጳጳሳቱ፣ ደጋጎቹ መኳንንት ሳይመክሩ ሲኖዶስ ብቻውን ወስኛለሁ እያለ የሚሠራው ወይም የሚያሻሽለው ቀኖናም የለም። በነገራችን ላይ ቀኖናና ሥርዓት ከሌለ በየቦታው ሁሉም ጳጳስ ነኝ፣ ሁሉም ካህን ነኝ እያለ መነሣቱ አይቀሬ ነው። ይህ ደግሞ ግልጽ የፕሮቴስታንቲዝም አካሄድ ነው። ቤተ ክርስቲያን ጉባኤያዊት ናት። ስለዚህ አንድን ጉዳይ ሁሉም በአንድ መክሮ መሥራት ይገባዋል እንጂ ጳጳሳት ብቻ ፈላጭ ቆራጭ የሆኑባት ቤተ ክርስቲያን አትኖርም። ሊቃውንቱ መምህሮቻችን ይጠሩ ጉዳዩን ከካህናቱ ከሊቃውንቱ ከአበምኔቶቹ ከገዳማውያን ጋር ሲኖዶስ ይምከርና ችግሩን ይቅረፍ። ይህ ካልሆነ ግን አስቸጋሪ ጊዜ መምጣቱ አይቀሬ ነው። በደንብ መረዳት ያለባችሁ አቶዎች ካህን ሹመናል እያሉ ሙሉ ትውልዱን ከቤተ ክርስቲያን ጸጋ ይከለክሉብናል። ምክንያቱም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሞ ምእመናን ጸጋ የሚያገኙት በካህናት አማካኝነት ነው እንጂ አቶው መቅደስ ገብቶ ቢያደርገው ከጸጋ የተራቆተ ምእመን ይኖረናል። ከሕይወት የተለየ ምውት ምእመን ይኖረናል። ይህ እንዳይሆን አሁንም ጊዜው አልረፈደም ጉዳዩን ከላይ ከተጠቀሱት አካላት ጋር ተነጋግሮ መፍታት ቢቻል መልካም ነው። ይህ ካልሆነ ግን ምእመናን ሕይወት አልባ ሆነው እንዳይኖሩ ትክክለኛ ሐዋርያዊ የክህነት ቅብብሎሽ ካላቸው አካላት ክህነትን እስከ መቀበል የሚደርስ አካሄድ መሄድ ከሁሉም ይጠበቃል። ጉዳዩ የሕይወት ጉዳይ ስለሆነ። ቀዳሚሃኒ ከመ ይኩን ፍጹመ ልቡና በአእምሮ ጠባይዓዊ። መጀመሪያ በአእምሮ ጠባይዕ። ወረባሐዊ። በአእምሮ መንፈሳዊ ፍጹም ሊሆን ይገባል። ፲፱፰፱፳ ወዳግምኒ ከመይኩን ጽሩየ በሃይማኖት ዘየዐቅብ ቦቱ ሕገ ሃይማኖት ዘሀሎ ዲበ መሠረታቲሁ ዘዘልፍ። ሁለተኛው በብሉያት በሐዲሳት ያለውን የሃይማኖት ሥርዓት በሚጠበቅበት ሃይማኖት የጸና ይሁን። ፲፱፰፱፳፩ ወሣልስ ከመይኩን ምክር በፄ ዐሥራው። አምላክ አዝዞ ያጻፋቸው የአምላክን ነገር የሚናገሩ የመጻሕፍትን ንባባቸውን ከምሥጢሩ ጋር የሚተባበር ትርጓሜያቸውን የተማረ ሊሆን ይገባል። ሁለተኛው ሊቃውንት አንድ የሆኑበትን የተባበሩበትን። ወነምስ ከመ ይኩኑ ትሩፈ ምግባር በውስተ ነፍሱ ወሥጋሁ በዘይከውን ውኩፈ ትእዛዘ ዚኣሁ በጎበ ሕዝብ። ወሳድስ ከመ ይርአይ ዘይሠርዎ ሎሙ ዘይትከሀሎሙ ፀዊሮቱ በመዋዕሊሁ። በዘመኑ መሥራት ይቻላቸው እንደሆነ አይቻላቸው እንደሆነ ማወቅ ይገባል። ወሳብዕ ከመ ይትማከር በዘይፈትሕ ወየአስር ምስለ ማእምራን ወንጹሓን እምካህናቲሁ ወሕዝቡ ወመኳንንቲሁ ወቅሩባኒሁ ዘታሕተ ሥልጣኑ በባሕቲቶሙ ወተጋብኡ። እየራሳቸው አድርጎ ሰብስቦ መማከር ይገባል። ወእምድኅረ ተሰነአዉ ቦቱ ይጽሕፉ ተዝካረ ነገር ምክንያተ ዘተጋብኡ በእንቲኣሁ። ከተስማሙበት በኋላ የነገሩን መታሰቢያ ሊሆን ስለእርሱ የተሰበሰቡበትን ምክንያት ይጻፉ። ፲፱፰፱፳፩ ይደሉ ከመ ይትጋብኡ በእንቲኣሁ ኤጲስ ቆጶሳት ወዐበይተ ካህናት ወመኳንንት ወዘቦቱ አእምሮ ወገቢረ ጽድቅ።

ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ልኳ ክርስቶስ ነው። በእርሱ ሁል ጊዜም ደስ ይለናል። ጳጳስ በተሳሳተ ቁጥር እርሷን መንቀፍ ነውር ነው። ዘረኛ ጳጳስ፣ ሆዳም ጳጳስ፣ ስለራሱ ክብር እንጂ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ የማያስብ መምህር እና የመሳሰሉትን የሰው ትንሾች አይተናል እያየንም

ነው። ይህ አሁን የጀመረ አይደለም። ድሮም ሆዳሞች፣ ዘረኞች ነበሩ። እነርሱን አብነት አናደርግም። ሕገ ቤተ ክርስቲያንን እና በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እስከሞት በመታመን ጠብቀው ሰማዕት የሆኑትን ቅዱሳን ሊቃውንት፣ ቅዱሳን መነኮሳት፣ ቅዱሳን ጳጳሳት እና ሌሎችንም ቅዱሳን አብነት እናደርጋለን እንጂ። የሆዳም አምላኩ ሆዱ ነው። ሆዳም የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ቢፈርስ፣ ዶግማዋ ቢፈርስ፣ አስተምህሮዋ ቢጠፋ ጉዳዩ አይደለም። በሆዱ ከመጣችሁበት ግን እስከሞት ድረስ ይታመናል። የዘረኛ ሰው አምላኩ ዘሩ ነው። የሚቆምለት እውነትና መርሕ የለውም። ሌባም ይሁን፣ ወንበዴም ይሁን፣ ዘማዊም ይሁን ዘሬ ነው ብሎ ያሰበው አካል ምንም ያድርግ ሁልጊዜም ልክ ነው ብሎ ነው የሚያስብ። ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ እስከመጨረሻው ድረስ መጠበቅ ይገባዋል እንጂ ንጉሥ የወደደውን፣ ዘመን ያነሣውን ብሎ መኖር አይገባውም። ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በዘመኑ ስለነበሩ ከኃድያን ሲናገር ዝም ስንል ከኃድያን ነገራችን እውነት ቢሆን ነው እንጂ እስከማለት እንደሚደርሱ ይናገራል። ወንበዴን ዝም ስትለው ውንብድናው ትክክል ሊመስለው ይችላል። የዚህ መድኃኒቱ ውንብድናውን ሳይፈሩ ሳያፍሩ መንገር ነው። የምንፈራው እግዚአብሔር እንጂ የምንፈራው ሚች ሰው ሊኖር አይገባም። ጳጳስን ጳጳስ ነው ብለን በተለየ በአባትነት እንድናከብረው ያደረገን ቀኖናው ነው። ቀኖናውን ካፈረሰ ግን አባትነቱን በራሱ እየሻረው ስለሆነ እንደሌሎች ሸማግሌዎች ብቻ ይሆናል። ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን እያፈረሱ ለቤተ ክርስቲያን አባት መሆን አይቻልም።

አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት

ማንኛውም ክርስቲያን እነዚህን ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅበታል። እነዚህም የዶግማ መሠረት ናቸው። የቤተክርስቲያን ትምህርት አምስቱን አዕማደ ምሥጢራት ማዕከል ያደረገ ነው። እነዚህም:-

- ፩) ምሥጢረ ሥላሴ
- ፪) ምሥጢረ ሥጋዌ
- ፫) ምሥጢረ ጥምቀት
- ፬) ምሥጢረ ቁርባን
- ፭) ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

ናቸው። ምሥጢረ ሥላሴ እግዚአብሔር አንድም ሦስትም እንደሆነ የምንማማርበት ነው። ምሥጢረ ሥጋዌ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ አዳምን ለማዳን ሰው መሆኑን የምንማማርበት ነው። ምሥጢረ ጥምቀት ስንጠመቅ የእግዚአብሔር ልጆች እንደምንሆን የምንማማርበት ነው። ምሥጢረ ቁርባን ንስሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን ብንቀበል ኃጢአታችን እንደሚሠረይልን የምንማማርበት ነው። ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ማንኛውም ሰው እንደ ሞተ እንደማይቀርና በምጽአት ጊዜ ሁሉም ተነሥቶ በዚህ ምድር ጽድቅ የሠሩ ወደዘለዓለም ደስታ፣ በዚህ ምድር ክፋትን ያደረጉ ደግሞ ወደዘለዓለም መከራና ሰቆቃ እንደሚገቡ የምንማማርበት ነው።

ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን

- ፩) ምሥጢረ ንስሓ
- ፪) ምሥጢረ ክህነት
- ፫) ምሥጢረ ሜሮን
- ፬) ምሥጢረ ተክሊል
- ፭) ምሥጢረ ቁርባን
- ፮) ምሥጢረ ጥምቀት
- ፯) ምሥጢረ ቀንዲል

ናቸው። በምሥጢረ ንስሓ ሰው ቢበድል እግዚአብሔርን በቁሱ አማካኝነት ይቅርታ ቢጠይቅ በደሉ እንደሚቀርለት የምንማማርበት ነው። ምሥጢረ ክህነት ከዐዛዊ ኖኅት እስከ ፓትርያርክ ያሉ ሰዎች እንዴት እንደሚሾሙ የምንማማርበት ነው። ምሥጢረ ሜሮን ሰው ከተጠመቀ በኋላ ማኅደረ እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ስለሚቀባው እንዲሁም ንዋየ ቅድሳት ስለሚከብሩበት ቅዱስ ቅብዐት (ዘይት ዘጽሉይ) የምንማማርበት ነው። ምሥጢረ ቀንዲል ከምእመናን አንዱ ቢታመም ካህናትን ጠርቶ መብራት አብርተውለት ጸሎት ጸልየውለት እንደሚፈወስ የምንማማርበት ትምህርት ነው። ምሥጢረ ቁርባን የቁርባንን ሥርዓት የምንማማርበት ነው። ምሥጢረ ጥምቀትም የጥምቀትን ሥርዓት የምንማማርበት ነው። ምሥጢረ ተክሊል ደግሞ የሚያገቡ ሰዎች ሲያገቡ ሥርዓቱ ምን እንደሆነ የምንማማርበት ነው። የጋብቻን ክቡርነት የምንማማርበት ትምህርት ነው። ሁሉንም ለየብቻቸው በጥልቀት ወደ ፊት እንማማራቸዋለን።

13ቱ ሕማማተ መስቀል

- ፩) አክሊለ ሦክ (የእሾህ አክሊል)
- ፪) ተኮርዖተ ርእስ (ራስን በዱላ መመታት)
- ፫) ተጸፍዖ መልታሕት (ፊትን በጥፊ መመታት)
- ፬) ወሪቀ ምራቅ (ምራቃቸውን በጌታ መትፋት)
- ፭) ተቀስፎ ዘባን (ጀርባን መገረፍ)
- ፮) ተአሥሮ ድኅሪት (የኋሊት መታሰር)
- ፯) ኩትፈተ እድ (እጅን መታሰር)
- ፰) ጸዊረ መስቀል (መስቀልን መሸከም)

- ❖ ፱) ሰትየ ሐሞት (ሐሞት መጠጣት)
- ❖ ፲) አራቱ ቅንዋት (በችንካር መቸንከር)

ናቸው። አራቱ ቅንዋት የሚባሉትም ሁለቱ ከግራና ከቀኝ እጁ፣ አንዱ ሁለቱን እግሩን በአንድ አድርገው የቸነከሩበት፣ አንዱ መስቀሉ የተያያዘበት ችንካር ሲሆን እያለፈ ጎኑን ይወጋው ነበርና ተቆጥሯል።

ሰባቱ አጽርሐ መስቀል

- ✓ ፩) ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ
- ✓ ፪) አባ አመሐጽን ነፍስየ ውስተ እዴከ
- ✓ ፫) አባ ሥረይ ሎሙ በዘኢየአምሩ ይገብሩ
- ✓ ፬) ጸማዕኩ
- ✓ ፭) ዮም ትሄሉ ምስሌየ ውስተ ገነት
- ✓ ፮) ነዋ ወልድኪ ወነያ እምከ
- ✓ ፯) ተፈጸመ

ሰባቱ አጽርሐ መስቀል የተባሉት ጌታ በመስቀል ሆኖ የተናገራቸው ንግግሮች ናቸው።

ሰባቱ ተአምራት

ጌታ በመስቀል ሳለ የተደረጉ ሰባቱ ተአምራት የሚከተሉት ናቸው።

- ፩) ፀሐይ ጨለማለች
- ፪) ጨረቃ ደም መስላለች
- ፫) ከዋክብት ረግፈዋል
- ፬) ሙታን ተነሥተዋል
- ፭) መቃብራት ተከፍተዋል
- ፮) አዕባን ተፈትተዋል
- ፯) መንጦላዕተ ምኩራብ ተቀዷል

ሁል ጊዜም ቢሆን እኛን ለማዳን በመስቀል የተሰቀለውን ጌታችንን ማሰብ አለብን። ቅዱሳን ነገረ መስቀሉን እያሰቡ ኃጢአት ከመሥራት ተከለከሉ። በአንጻሩ ጽድቅን ለመሥራት ተፋጠኑ።

የቅድስና መዓርጋት

አስሩ የቅድስና መዓርጋት የሚከተሉት ናቸው።

- ፩) ጽማዌ (አርምሞ)
- ፪) ልባዌ
- ፫) ጣዕመ ዝማሬ
- ፬) አንብዕ
- ፭) ኩነኔ
- ፮) ፍቅር
- ፯) ሐሰት
- ፰) ንጻሬ መላእክት
- ፱) ተሠጥሞ ብርሃን
- ፲) ከዊነ እሳት

ከአንድ እስከ ሦስት ያሉት የንጽሐ ሥጋ መዓርጋት ናቸው። ከአራት እስከ ሰባት ያሉት የንጽሐ ነፍስ መዓርጋት ናቸው። ከስምንት እስከ አስር ያሉት የንጽሐ ልቡና መዓርጋት ናቸው። ሐሰት ካለበት ቦታ ሆኖ ካሰቡበት ቦታ መድረስ ነው። ፍቅር ሰውን ሁሉ እኩል መውደድ ነው። ኩነኔ ሥጋን ለነፍስ ማስገዛት ነው። ንጻሬ መላእክት መላእክትን ማየት ነው። አምስቱ ተውላጣት የሚባሉት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

- ፩) ሙኃዘ አንብዕ ዘያስተፈሥሕ
- ፪) ሙኃዘ ንባብ መንፈሳዊ
- ፫) ሞት መንፈሳዊ
- ፬) ዘኢይጸሐፍ በመጽሐፍ
- ፭) ምግባረ ኅሊና ቀዳማዊ ከመ ኃምሳዊ

ናቸው። አንድ ቅዱስ ከአንዱ የቅድስና ደረጃ ወደ ሌላው ሲሸጋገር የሚያሳያቸው ለውጦች ናቸው ተውላጣት። ጽገኞች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

- ፩) የኩነኔ ጽገኛ ዐቃቤ ነው
- ፪) የልባዌ ጽገኛ አንብቦ ነው

- ፫) የአንብዕ ጽገኛ ሰጊድ ቅድመ መስቀል ነው
- ፬) የሑሰት ጽገኛ ብርሃን (እሳት) ነው

ናቸው። ጽገኞች አጋጉች እንደማለት ያሉ ናቸው። ኩነኔን ዐቃቤ (መጠበቅ) ይረዳዋል። ልባዌን አንብቦ ይረዳዋል። አንብዕን ሰጊድ ቅድመ መስቀል ይረዳዋል እንደማለት ነው።

፳፪ቱ ፍጥረታት

22ቱ ፍጥረታት የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው። እሑድ ሰባት ፍጥረታት ተፈጥረዋል። አንዳንድ ሰዎች ስምንት ይላሉ። ነገር ግን መጽሐፈ ኩፋሌ ሰባት ብሎ በማያሻማ ቃል ስለነገረን ስምንት የሚለው ተቀባይነት የለውም።

- ✓ ፩) ሰባቱ ሰማያት
- ✓ ፪) እሳት
- ✓ ፫) መሬት
- ✓ ፬) ነፋስ
- ✓ ፭) ውሃ
- ✓ ፮) ቅዱሳን መላእክት
- ✓ ፯) ጨለማ
- ✓ ፰) ጠፈር
- ✓ ፱) በእጅ የሚለቀሙ ጥቃቅን ዕፀዋት
- ✓ ፲) በማጭድ የሚታጨዱ መካከለኛ ዕፀዋት
- ✓ ፲፩) በምሳር የሚቆረጡ ታላላቅ ዕፀዋት
- ✓ ፲፪) የገነት ዕፀዋት
- ✓ ፲፫) ፀሐይ
- ✓ ፲፬) ጨረቃ
- ✓ ፲፭) ከዋክብት
- ✓ ፲፮) ከውሃ የተፈጠሩ በክንፋቸው የሚበሩ
- ✓ ፲፯) ከውሃ የተፈጠሩ በእግራቸው የሚሽከረከሩ

- ✓ ፲፰) ከውሃ የተፈጠሩ በሆዳቸው የሚሳቡ
- ✓ ፲፱) ከየብስ የተፈጠሩ በክንፋቸው የሚበሩ
- ✓ ፳) ከየብስ የተፈጠሩ በእግራቸው የሚሽከረከሩ
- ✓ ፳፩) ከየብስ የተፈጠሩ በሆዳቸው የሚሳቡ
- ✓ ፳፪) ሰው

ናቸው። ማክሰኞ አራት ፍጥረታት ተፈጥረዋል። እሑድ ሰባት ፍጥረታት ተፈጥረዋል። ሰኞ አንድ ፍጥረት ተፈጥሯል። ረቡዕ ሦስት ፍጥረታት ተፈጥረዋል። ኃሙስ ሦስት ፍጥረታት ተፈጥረዋል። ዓርብ አራት ፍጥረታት ተፈጥረዋል። በጠቅላላው 22ቱ ፍጥረታት የሚባሉት እነዚህ ናቸው። አንዳንዶች ብርሃንን እንደ አንድ ፍጥረት ይናገሩታል። ነገር ግን ብርሃን በእሳት ይቆጠራል። ብርሃን፣ ሙቀት የእሳት ግብረ ባሕርይዎች ናቸው እንጂ ራሳቸውን የቻሉ ፍጥረታት አይደሉም። ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ብርሃን ሲል እንኳ ይገለጥ ማለት እንጂ ግብር እም ግብር የተፈጠረ መሆኑን የሚገልጥ አይደለም። የእሑድ ፍጥረታት እምኀበ አልቦ ኀበቦ ተፈጥረዋል። ከእሑድ በኋላ ያሉት ደግሞ ግብር እም ግብር ተፈጥረዋል።

የክህነት መዓርጋት

ክህነት ፲ መዓርጋት አሉት። እነዚህም

- ፩) ሊቀ ጳጳሳት
- ፪) ጳጳስ (መጥሮጶሊስ)
- ፫) ኤጲስ ቆጶስ
- ፬) ቆሞስ
- ፭) ቄስ
- ፮) ዲያቆን
- ፯) ንፍቀ ዲያቆን
- ፰) አናጉንስጢስ
- ፱) መዘምር
- ፲) ዐፃዌ ሥጋት

ናቸው። እነዚህም በሦስቱ ከተማ የሚኖሩ የቅዱሳን መላእክት አምሳል ናቸው። በሦስቱ የመላእክት ከተሞች የሚኖሩ መላእክትና አለቆቻቸውም የሚከተሉት ናቸው።

ነገድ_____አለቃ

- ፩) አጋዕዝት_____ቅዱስ ሚካኤል
- ፪) ኪሩቤል_____ገጸ ሰብእ ገጸ አንበሳ
- ፫) ሱራፌል_____ገጸ ንስር ገጸ እንስሳ
- ፬) ኃይላት_____ቅዱስ ሚካኤል
- ፭) አርባብ_____ቅዱስ ገብርኤል
- ፮) መናብርት_____ቅዱስ ሩፋኤል
- ፯) ሥልጣናት___ቅዱስ ሱርያል
- ፰) ሊቃናት_____ቅዱስ ሰላትያል
- ፱) መኳንንት_____ቅዱስ ሰዳክያል
- ፲) መላእክት_____ቅዱስ አናንኤል

ናቸው። ሁሉም ነገድ በአንድ ላይ መላእክት ይባላሉ። እንደገና ከአስሩ ነገድ አንዱ ነገድ ለብቻው በነገድ ስሙ መላእክት ይባላል። እንደገና የመቶው ነገድ ሰባት አለቆች አሉት እነዚህም፦

- ፩) ቅዱስ ሚካኤል
- ፪) ቅዱስ ገብርኤል
- ፫) ቅዱስ ሩፋኤል
- ፬) ቅዱስ ሳቁኤል
- ፭) ቅዱስ ዑራኤል
- ፮) ቅዱስ ራጉኤል
- ፯) ቅዱስ አፍኒን

የአጋእዝት አለቃ ቀድሞ ሳጥናኤል (ዲያብሎስ) ነበር አሁን ግን እርሱ ሲወድቅ ቅዱስ ሚካኤል የኃይላትም የአጋዕዝትም አለቃ ነው።

ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ተሳስታ አታውቅም። በጣም የሚገርመው ወደፊትም ለዘለዓለም አትሳሳትም።

ስለዚህ ተሳስቼ ነበር ይቅርታ አትልም። ቤተ ክርስቲያን የምትባለው የቅዱሳን ሰማዕታት፣ የቅዱሳን መላእክት፣ የቅዱሳን መኰሳት፣ በጠቅላላው የቅዱሳን ሰዎች፣ እና በዚህ ምድር ያሉ ምእመናን ጎብረት ናት። የጎብረቱ ራስ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ ጎብረት የሚመራው በቃለ እግዚአብሔር ነው። በዶግማ፣ በቀኖና፣ በሥርዓት ነው። የቤተ ክርስቲያን ራሷ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ደግሞ አይሳሳትም። ለመዳን ወደእርሷ የተጠጉ ጳጳሳት፣ ምእመናን፣ ካህናት፣ መምህራን ወዘተ ግን ሊሳሳቱ ይችላሉ። በእርግጥ እያንዳንዱ አማኝም በአንደኛው የቤተ ክርስቲያን ትርጓሜ ቤተ ክርስቲያን ይባላል። ይኽውም የክርስቶስ ወገን ማለት ነው። ይህ ሊሳሳት ይችላል። ሲሳሳት ግን ራሱን ችሎ ተሳስቻለሁ ይበል እንጂ አያጭበርብር። ቤተ ክርስቲያን አትሳሳትም እያልን ያለነው ግን ክርስቶስ ራሷ የሆነላትን ጎብረታዊቷን ቤተ ክርስቲያን ነው። እያንዳንዱ ምእመን ሲሳሳት ቤተ ክርስቲያን ተሳሳተች አይባልም። ጳጳሱ ሲሳሳት ቤተ ክርስቲያን ተሳሳተች አይባልም። ሲኖዶስ ሲሳሳት ቤተክርስቲያን ተሳሳተች አይባልም። ማጭበርበር አያስፈልግም። ከተሳሳትክ ራስህን ችለህ እኔ ተሳስቻለሁና ይቅርታ በል እንጂ በአንተ በደል ቤተ ክርስቲያን ይቅርታ ትጠይቃለች ብለህ በደልህን በጎብረታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ለመደበቅ አትጣር።

ሰማዕትነት

ቤተ ክርስቲያን እውነትን ታስተምራለች። ከእውነት የሚቃረን ነገር ከመጣ እስከ ሞት ድረስ መቃወም እንደሚገባ ታስተምራለች። ብዙ ቅዱሳን ሰማዕታት የኖሩት በዚህ ዓውድ ነው። አሁን አሁን ከአንዳንድ ትንንሽ ሰዎች የምናየውና የምንሰማው ነገር ደግሞ የሥጋ ሞት ከምንሞት ለጊዜው ከውሸት ጋር ብንስማማ የሚል ነው። ይህ ግን ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ አይደለም። Secularized የሆነ ሐሳብ ነው። የሥጋ ሞትን የሚፈሩ ሰዎች ዓውደ ምሕረት ላይ ወጥተው ስለሰማዕትነት ይሰብኩን ይሆን? ትክክለኛው አስተምህሮ ግን እስከ ሞት ልንታመንለት የሚገባ የቤተ ክርስቲያን ዶግማ፣ ቀኖና፣ ሥርዓት፣ አስተምህሮ መኖር አለበት የሚለው ነው። ስሜትን በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መግራት ይገባል እንጂ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ለእኛ ስሜት ወደሚስማማ መለወጥ አይገባም። የቤተ ክርስቲያን ራሷ ክርስቶስ ነው። ቤተ ክርስቲያን የምትመራውም በሕገ እግዚአብሔር ነው። ሁሉም ሰው በሕጉ መሠረት ይዳኛል። ቤተ ክርስቲያን የሁላችን እናት ናት። ከምእመን እስከ ፓትርያርክ ካኪደሬ እስከ ከፍተኛ መኳንንት የሁሉ እናት ናት። ቤተ ክርስቲያንን መራቅ ሞት ነው። ከቤተ ክርስቲያን መቅረት ከሕይወት መራቅ ነው። ታላላቅ ፈተናዎች ቢመጡብን እንኳ የበለጠ ወደ ቤተ ክርስቲያን ቀርበን ንስሓ እየገባን፣ ሥጋውን ደሙን እየተቀበልን፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀን ለማስጠበቅ ሁላችንም ድርሻችንን መወጣት ይገባናል። ከደጋግ ካህናት፣ ጳጳሳት፣ መምህራን፣ ምእመናን ጋር አንድነታችንን እያጠነከርን ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀን ማስጠበቅ ይገባናል። በእርግጥ የቤተ ክርስቲያን ባለቤት ራሱ ክርስቶስ ነው። ነገር ግን እኛ ድርሻችንን ብንወጣ መልካም ዋጋን ይከፍለናል። አጥፍተንም ከሆነ በግልጽ ይቅርታ እየተጠያየቅን ቤተክርስቲያንን ለቀጣዩ ትውልድ ከነሙሉ ክብሯ ማስረከብ ይገባናል። ከዚያ ውጭ ስሕተትን እውነት አስመስሎ ማቅረብ ግን ቤተ ክርስቲያንን ከመናቅ የመነጨ ነው። ፈሪሀ እግዚአብሔርን ማስቀደም ይገባል።

ቀኖና መንፈስ ቅዱስ

1) የሐዋርያት ሲኖዶስ ትእዛዝ ፲፱ "በታወቀ/ኃጢአት በትክክል የተሻረ ኤጲስ ቆጶስም ቢሆን ቄስም ቢሆን ዲያቆንም ቢሆን ከተደፋፈረና ሥልጣን ባለው ጊዜ ይሠራው የነበረውን መሥራት ከጀመረ ፈጽሞ ከቤተ ክርስቲያን ይራቅ"። በዚህ መሠረት ተወግዘው የነበሩ ሰዎች የጳጳስ ልብሳቸውንና አስኬማቸውን እንደለበሱ የጳጳስን ሥራ እየሰሩ እስካሁን ቆይተዋል። ስለዚህ በምን መስፈርት ነው ወደ ጵጵስና የሚመለሱት??? ከሐዋርያት ቀኖና ጋር መጋጨት አይሆንም ወይ??

2) የሐዋርያት ሲኖዶስ አብጥሊስ ፷፮ "ባደረገው በደል ከቤተክርስቲያን ያስወጡት ኤጲስ ቆጶስ___በግድም ያለ ፍርሀት የቤተክርስቲያንን አገልግሎት ቢፈጽም እስከመጨረሻው ከቤተ ክርስቲያን ይሰናበት"። ሦስቱ ጳጳሳት በግልጽ የተቀመጠውን ፓትርያርኩ ሳይፈቅዱ መሾምን ስላደረጉ ተወግዘው ሳለ እንኳ አስኬማቸውን እንደለበሱ መስቀል እንደያዙ ከቤተ ክርስቲያን እየገቡ የክህነት ሥራ እየሰሩ ነበር። (ያውም ደግሞ ሰው እያስገደሉ)። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ደግሞ እስከ መጨረሻው ይሰናበቱ ብለው ሐዋርያት ሰርተዋል። ይህ ሥርዓት ወዴት ተጣለ?!

3) በዝሙት የተገኘ ጳጳስ ካለ ከክህነቱ ይሻራል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፱፣ ፫፻፲፱ "ወዘተረክበ በዝሙት አው በስርቅ አው በመሐላ ዘሐሰት ይትመተር እምክህነቱ" በዝሙት በስርቆት እና በሐሰት በመማል የተገኘ ካህን [ከጳጳስ-ዲያቆን] ከክህነቱ ይሻር። ወኢይሰደድ። ይሻር ማለታችን ተወግዞ ከምእመናን ይለይ ማለታችን አይደለም። ክህነቱ ተሸሮ እንደምእመን ሆኖ ይኑር ማለታችን ነው። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፵፰፣ ፲፻፯፻፵፭ "ወለእመ ተረክበ ኤጲስ ቆጶስ በምንትኒ እምዝሙት ይደቅ እመዓርገ ክህነቱ። ኤጲስ ከዝሙት በማናቸውም ዝሙት ቢገኝ ከሹመቱ ይሻር። ወኢይትመየጥ ኀቤሃ ዳግመ። ዳግመኛ ወደ ሹመቱ አይመለስ። ወለእመ ነስሐ ኢይክልእዎ እምተደምሮ ምእመናን። ይቅርታ ቢጠይቅ ግን ክህነት የሌለው ምእመን ሆኖ ይኑር።

4) ከዲያቆናት እስከ ጳጳሳት ያሉ ካህናት ሰው ከገደሉ ክህነታቸው ይሻራል።ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፵፯፣ ፲፻፯፲፫ "ካህን እመ ተቃተለ ምስለ አሐዱ ወይዘብጦ እስከ ይመውት ይትመተር" ።ካህን ከሰው ጋር ቢጣላና ለሞት የሚያበቃ በትር ጨክኖ ቢመታው ስለልቡናው ጽናት ከሹመቱ ይሻር"።

5) ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭፣ ፻፹፫ "ኢይእስር ወኢያውግዝ ዘእንበለ ርትዕ" ኤጲስ ቆጶስ በማይገባ ያለ ሥርዐት አያውግዝ። ይህንን ካደረገ ግን ይኸን ውእቱ እሡረ ወውጉዘ እምኀበ እግዚአብሔር ። እርሱ ራሱ በእግዚአብሔር የታሰረ ነው። ሌሎችን ያወገዘው ውግዘትም አይቆጠርም ወፈ ገዝት ነው።

ቤተ ክርስቲያን

ሐዋርያዊት በሆነች በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን። ቤተክርስቲያን የምትመራው በመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ነው። የሲኖዶስም ድርሻ የመንፈስ ቅዱስን ትምህርት መጠበቅ

እንጂ መለወጥ አይደለም። ለቤተ ክርስቲያን ብርሃኗም መሠረቷም እግዚአብሔር ነው። በሕይወት በሰላም በፍቅር ትጠብቀን ዘንድ ኑ እንጠበቃት። ጥቃቅን ቀበሮዎች የወይን ቦታችን ቤተ ክርስቲያንን እንዳያበላሹ እናጥምዳቸው። አስግሩ ለነ ቆናጽለ ንዑሳነ እለ ያማስኑ አፀደ ወይንነ እንዲል። በኖኅ መርከብ ውስጥ የሚበሉም የማይበሉም በአንድነት ይኖሩ ነበር። ከማሁ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በኖኅ መርከብ በተመሰለችው በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ደጋጎችም ክፉዎችም ይኖራሉ። ክርስቶስ ለፍርድ ሲመጣ ጻድቃንን ከኃጥዓን ይለያቸዋል። ለጻድቃን ንጉሣቸው ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል። በደንብ ተደራጅተን መሥራት ያለብን ቆብ በለበሱ ተኩላዎች ምእመናን እንዳይበሉ ማስገንዘብ፣ ማስተማር ነው። በጎቿን የሚጠብቁ እረኞች ለቤተክርስቲያን ያስፈልጓታል። ነገር ግን ተኩላዎች እረኛ መስለው ሲመጡ ተኩላነታቸውን ማሳወቅ ይገባል። በጎቹ እንዳይበሉ ማለት ነው። ተኩላን ከእረኛ በምን እንለየዋለን የሚል ጥያቄ ካለ በመለኪያ በሚዛን እንለየዋለን። ሚዛኑ መለኪያው ምንድን ነው ካልከኝ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ነው። የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ደግሞ ዶግማን ቀኖናን ሥርዓትን ሥነ ምግባርን አጠቃሎ የያዘ ነው። በጳጳሳት ምርጫ ላይ ፍትሐ ነገሥቱም የሐዋርያት ሲኖዶስም እንደሚናገረው ምእመናን ቀጥተኛ ተሳትፎ አላቸው። አብዛኛው ምእመን ያልወደደው ሰው ሊሾም አይችልም። ስለዚህ በአሁኑ ምርጫም የምእመናን ድምፅ የሊቃውንት ሐሳብ የብፁዓን አባቶች ስምምነት ሊሰማ ይገባል። ይህ ሁሉ ጥንቃቄ ያስፈለገው ቀበሮ የበጎች እረኛ ሆኖ እንዳይሾም ነው። የቤተ ክርስቲያን ንጉሧ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ንጉሣችን እርሱ ነው።

ቴዎድሮስ

ቴዎድሮስ የሚባል ሰው ይነግሣል ብላችሁ በጅል ተስፋ የተወጠራችሁ ጅሎች ሆይ እባካችሁ ከክፉ ጎዳናችሁ ተመለሱና ክርስቶስ አካሏ ወደሆነላት ቤተ ክርስቲያን በንስሓ ተመለሱ። ክርስቶስ የነገሠላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አለችን። በድለህ ከሆነ ንስሓ ግባ። ሳትበድል መከራ እየደረሰብህ ከሆነም መከራውን በደስታ ተቀበል። ይህ የሰማዕታት መንገድ ነውና። ሰማያዊ ንጉሥ ላላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምድራዊ ንጉሥን ተስፋ ማድረግ ቂልነት ነው። የቤተ ክርስቲያን አለኝታዋ አካሏ ክርስቶስ ነው። የቤተ ክርስቲያን የሁልጊዜም ተስፋዋ ክርስቶስ ነው። ምድራዊ ንጉሥን ተስፋ አድርጉ ተብለን አልተማርንም። ስለዚህም ተስፋ የምናደርገው ምድራዊ ንጉሥ የለም። ማንኛውም ንጉሥ ቢነግሥ መልካም ቢሠራ ራሱን ይጠቅማል። ክፉ ቢሠራም ራሱን ይጎዳል።

ዕለተ ዓርብ

- ፩) አዳም የተፈጠረበት & ሔዋን ከአዳም ጎን የተገኘችበት
- ፪) አዳምን ለማዳን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል የተሰቀለበት
- ፫) ነፍሳት ከሲኦል እሥራት ነጻ የወጡበት ዕለት ነው።

ጌታችን እርሱ ተሰቅሎ እኛን አዳነን። የፍቅርን ትርጓሜ በተግባር አሳየን። እርሱን ሁልጊዜ ማሰብ ለሕሊና ዕረፍት፣ ለሕይወት ሰላምን ይሰጣል። ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበን

ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ጉባዔያዊት ናት ስንል የ70 ጳጳሳት ስብስብ ብቻ ናት ማለታችን አይደለም። በአፀደ ነፍስ ያሉ የቅዱሳን ሰማዕታት፣ በአፀደ ሥጋ ያሉ የካህናት፣ የምእመናን፣ የሥውራን አባቶች፣ የጳጳሳት፣ የቅዱሳን መላእክት ሁሉ ጎብረት ናት ማለታችን ነው። የዚህ ጎብረት ራስ (መሪ) ደግሞ ክርስቶስ ነው። ጎብረቱ በዘፈቀደ አይመራም። በሕገ እግዚአብሔር ይመራል። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ ያለው መሪው እርሱ መሆኑን ለመግለጥ ነው። ስለዚህ ሁሉም በተቀመጠለት ሕግ ቢመራ ዋጋውን የሚሰጥ፣ ቢያጠፋ የሚፈርድበት አምላክ ወሰብእ ኢየሱስ ክርስቶስ አለ። ማንም ቢሆን ከእግዚአብሔር በታች ነው። ማንም ቢሆን ሊመራ የሚገባው በእግዚአብሔር ቃል ነው። ካህናት በምድር ባለችው የእግዚአብሔር መንግሥት (ቤተክርስቲያን) ተሿሚዎች አስተናጋጆች ናቸው። ሹም ደግሞ የተሾመበትን የሥራ ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት አለበት። ካልተወጣ ግን የሹመቱ ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ እንደ ሥራው ይከፍለዋል። ምእመናንም፣ ካህናትም፣ ጳጳሳትም ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል። ጳጳሱ ድርሻውን ካልተወጣስ በደሉ በማን ይሆናል ካላችሁ በራሱ ይሆናል። እርሱ ስላጠፋ ቤተ ክርስቲያን አትነቀፍም። ምእመኑ፣ ካህኑ ቢያጠፋ እና ድርሻውን ካልተወጣ በደሉ በማን ይሆናል ካላችሁ ሁሉም የራሱን በደል ራሱ ይሸከማል። ቤተ ክርስቲያን መሪዋ ክርስቶስ ስለሆነ አስተናጋጅ አጠፋ ተብሎ ባለቤት አይከሰስም። አስተናጋጁ በራሱ ይጠየቅበታል እንጂ። በቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ደስተኞች ነን። መቼም ቢሆን አዝነን አናውቅም። አስተናጋጆችን ግን ጉቦ የለመዱ፣ መለካውያን ሁነው ስናገኛቸው ያው በደስታ እንቃወማቸዋለን። አንድ ጳጳስ በደል ቢገኝበት በዚህ ምክንያት ይወገዝ ዘንድ ወይም ቀኖና ይሰጠው ዘንድ ለቅዱስ ሲኖዶስ ደጋግሞ ማሳወቅ ከእያንዳንዱ ምእመን ይጠበቃል። እኛ አሳውቀን ሲኖዶስ ዝም ካለ ግን ፍርዱ በሲኖዶሱ ይሆናል። በእኛ የሚቀርብን ጸጋ ግን የለም። እስከ ዕለተ ሞታችን ሕገወጥነትን እያወገዝን በመጽሐፍ ጽፈን ለትውልድም እየተናገርን እንኖራለን። በምጽአት ጊዜ ራሱ ክርስቶስ ለሁሉም እንደየሥራው ይከፍለዋል። ለምሳሌ አንድ ካህን ሰው ገድሎ ነገር ግን ይህንን ማንም ሳያውቅበት ቅዳሴ ገብቶ ቢያቆርበን፣ ቢያጠምቀን፣ ምሥጢራትን ቢፈጽምልን ጸጋው አይቀርብንም። በትክክል እንደገደለ ካወቅን ግን ለሲኖዶስ ማቅረብ ነው። ሲኖዶስ በዚያው በክህነቱ እንዲቀጥል ካደረገው ከዚያ ሰው ሳይሆን በሌላ ካህናት መቁረብ መጠመቅ ያስፈልጋል። ሳያውቁ ከዚያ ሰውዬ የሚቆርቡ የሚጠመቁ ቢኖሩ ጸጋ አይቀርባቸውም። እያወቁ ከዚያ ሰውዬ የሚቆርቡ የሚጠመቁ ካሉ ግን የወንበዴ ተባባሪ ይሆናሉ። ካህኑ ያጠፋው ጥፋት ክህነት የማያስሽር ከሆነ ግን ከእርሱ መጠመቅ መቁረብ ይቻላል። በራሱ በደል እግዚአብሔር ይጠይቀዋል። ይህንንም ፍትሐ ነገሥት በወርቅ ማኅተም እና በሌላ (እንጨት) ማኅተም መስሎ ተናግሮታል። ሁለቱም በወረቀት ተመሳሳይ ማኅተም ይኖራቸዋል። ክፉ ካህንና ደግ ካህን ሁለቱም ተመሳሳይ ጸጋ ያሰጣሉ። ራሳቸው ግን በፈጣሪ ዘንድ የተለያየ ቦታ ይኖራቸዋል።

ቅዱስ ሲኖዶስ

ቅዱስ ሲኖዶስ መሪውን መንፈስ ቅዱስን ሊያከብር ይገባል። ከጴንጤዎቹ ከሽመልስ አብዲሳ እና ከዐቢይ አሕመድ ጋር በተስማማነው መሠረት ሳይሆን ማለት ያለባቸው መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት በቅዱሳን አድሮ በሠራው ቀኖና መሠረት ሊሉ ይገባል። ከ25ቱ የባለፈው ሕገወጥ ኤጲስ ቆጶስ ሆንን ባዮች አንዱስ እንኳ ለእጩነት መቅረብ አይችልም። ይህ ብቻ ሳይሆን በቅስና እና በቁምስና መዓርግ እንኳ መቀጠል አይችሉም። ስለዚህ እነዚህን ሰዎች ቅዱስ ሲኖዶስ ክህነታቸውን አንስቶ በንስሓ በጨዋነት (ጨዋ ሆነው እንዲኖሩ) እንዲኖሩ ቢያደርግ መልካም ነው። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን ቀኖና የሚያዝዘው ይህንን ነው። ካልጸጸስኩ አገባለሁ የሚል ካለም ያግባ። ቅዱስ ሲኖዶስ ባለፈው የሠራውን ስሕተት ሁለተኛ መድገም የለበትም። ባለፈው እነ አባ ሳዊሮስን፣ አባ ዜና ማርቆስንና አባ ኤፆስጣቴዎስን የሐዋርያትን ቀኖና ሽሮ ነበር የመለሳቸው (ይህንን በጊዜው የብዙ አጨብጫቢ አድርባዮችን ስድብ ታግሼ ድርሻዬን ለመወጣት ጽፌ ነበር)። ቢቻል ይህንንም እንደገና ዐቢይ እና ሽመልስ ፊት ተስማምተናል በሚል እሳቤ ሳይሆን እግዚአብሔር ምን ይለናል በሚለው ለክታችሁ ወደ ጨዋነታቸው ብትመልሷቸው መልካም ነው። ይኽው አሁን የሲኖዶሱ ፈተና ሆኑ። የእግዚአብሔርን ሕግ ሽራችሁ የምታደርጉት ነገር በሙሉ መጀመሪያ በእናንተው ላይ ነው መከራ የሚያመጣው። በመንፈስ ቅዱስ መመራት ያለበት ቅዱስ ሲኖዶስ በመለካውያን ትእዛዝ እና ዛቻ የሚመራ ከሆነ ግን ምእመናን ለመንፈስ ቅዱስ አድልተው ይቃወሙታል። ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ሕግ እና ቀኖና ትመራለች እንጂ በእጅ ብልጫ እና በመንግሥት ጫና አትመራም። ለቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አድልቶ እምቢ የሚል መኖር አለበት። የእግዚአብሔርን ቀኖና ከማስፈጸም ይልቅ የመንግሥትን ጉዳይ አስፈጽማለሁ የሚል ጳጳስ ካለ ግን ወደ ሀገረ ስብከቱ እንዳይመጣ፣ በእነርሱ ላይም እንዳይሾም ምእመናን እምቢ ማለት ይችላሉ። ቤተ ክርስቲያን የሁላችን ናት እንጂ ጳጳሱ እንደፈለገ ያለቀኖና እና ዶግማ የሚያዝዝባት አይደለችም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በቀኖናዋ መሠረት ትመራለች። ቀኖናዋን ሳያውቁ ጸጽሰው መለካዊ ሆነው ካስቸገሩ ደግሞ እነዚህን አውግዞ መለየት ይገባል። ውግዘት የተሠራው ለዚህ ነውና። ለቤተ ክርስቲያን ዶግማና ቀኖና መከበር እስከመጨረሻው መታመን ያስፈልጋል። ሥጋዊ መከራን ፈርቶ የቤተ ክርስቲያን ዶግማና ቀኖና ሲፈርስ ዝም ማለት ትልቅ ነውር ነው። ፈሪ ጳጳስ መኖር የለበትም። ለእውነት እስከ መጨረሻው የሚቆም እንደ አቡነ ጴጥሮስ (በፋሽስት የተገደሉት) ለእግዚአብሔር የታመነ ጳጳስ መሆን ያስፈልጋል። ብዑዓን አባቶቻችን ዶግማውንና ቀኖናውን መሠረት አድርጋችሁ ከወሰናችሁ እስከሞት ድረስ በፍቅር እንታዘዛችኋለን። እንደባለፈው ስብሰባችሁ መለካዊ ውሳኔ ብትወስኑ ግን ተቃውሟችንን እንገፋበታለን። የተወሰነ ቀን ጨክን ዝም የምንለው ጉዳይ አይደለም። ይህ ሃይማኖት ነው። በሃይማኖት ቀልድ የለም።

ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ

የቤተ ክርስቲያን በር ጠባብ ነው። ቆራጥ አባት ያስፈልገናል። የዶግማ ጥሰት ጥሶ ኮብልሎ የነበረ ሰው ከመሬት ተነሥቶ ቀጥታ ወደመድረክ መውጣት የለበትም። ቀድሞ በሠራው የዶግማ ጥሰት አፍሮ ዝም ብሎ ነው መኖር ያለበት። አባቶች ሲፈቅዱለት ቀኖናውን በአግባቡ

ከጨረሰ በኋላ ነው ለአገልግሎት ወደ ዓውደ ምሕረት መቆም ያለበት። ኢየሱስን ሳያውቁ ስለኢየሱስ ካልዘመርን ብሎ መቀወጥ አይገባም። መጀመሪያ ኢየሱስን ይወቁት። ስለ ኢየሱስ ከአብ ጋር የተካከለ መሆኑን ሳያውቁ ከአብ የሚያንስ የአብ ተወራጅ አድርገው እያሰቡ ቢዘምሩ ምን ዋጋ አለው?? መጀመሪያ ከአባቶች ሥር ቁጭ ብሎ ስለኢየሱስ መሠረታዊውን ትምህርት ይማሩ። ሲጀምር ይህ ካሴት ልናወጣ ነው እንዘምር እያሉ በራሳቸው ዓለም ዜማ ፈጥረው የሚመጡ ሰዎችን ቅዱስ ሲኖዶስ አንድ ነገር ቢያደርግልን ብየ አስባለሁ። በዓውደ ምሕረት በመደበኛነት ለመዘመር የሚፈልግ ሰው ካለ መጀመሪያ ድጓ እና አቋቋም ቢያስመሰክር መልካም ነው። የዜማ ስልትን በትክክል የሚያሳውቁ እነዚህ ትምህርቶች ናቸውና። በተጨማሪ ከመጻሕፍት በአንዱ ቢያስመሰክር መልካም ነው። አሁን እያየነው ያለው ግን ከመሬት ተነሥቶ በራሱ ዜማ ፈጥሮ ለሰው ሥጋዊ አስተሳሰብ የተመቸ መዝሙር እያዘጋጁ ሰው ወደሥጋዊነት እንዲያዘነብል ማድረግ ነው። እግዚአብሔርን በጎበረት የምናመሰግንባቸው ምስጋናዎች አሉ። ለምሳሌ ቅዳሴ አንዱ ነው። ስለዚህ ምእመናን የቅዳሴ ትምህርትን መማር አለባቸው። ሁለተኛው ማኅሌት ነው። ስለዚህ በማኅሌት ተገኝቶ እግዚአብሔርን በሥርዓት ማመስገን ነው። ከዚያ ውጭ በማናቸውም ሰዓት እግዚአብሔርን ማመስገን ከፈለግን ደግሞ በትውፊት ተገልጠው በሚታወቁ በዜማ፣ በጸሎት መጻሕፍት አማካኝነት ማመስገን ነው። በአዲስ ምስጋና ማመስገን ከፈለግን ደግሞ ቅኔ አለልን። ከዚያ ውጭ ቤተ ክርስቲያን በማታውቀው የዜማ ስልት እየተነሡ ካልዘመርን ማለት ተገቢ አይደለም። ሲጀምር ይህ ነገር 60 ዓመት አልሞላውም። በቅርብ የመጣ ግን ሁሉም ቸል ብሎት ዝም ያለው ድርጊት ነው። አንዳንድ ዘማሪ ነን ባዮች እግዚአብሔርን ያህል ንጉሥ ቤተ ክርስቲያንን ያህል እናት ክዳችሁ ሄዳችሁ ነበረ። በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት ወደእናታችሁ ተመልሳችሁ ይሆናል። ነገር ግን ዘላችሁ ወደ ዓውደ ምሕረት ካልወጣን አትበሉ። ከሓዲዎች እንደነበራችሁ እናስታውሳችሁ እንዴ!?!? በትሕትና ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ መኖርን ልመዱ እንጂ። ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ የሚባል እኮ እንደ እናንተ ዓይነቱ ነው። ወይም መጀመሪያውንም የተመለሳችሁት ከልባችሁ አይደለም ማለት ነው። ሌላ በጎችን ለማስከብለል የመጣችሁ ተኩላዎች ልትሆኑ ትችላላችሁ።

የእኛ ድርሻ በቤተ ክርስቲያን!!!

በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የሚመለከታቸው ጳጳሳት ብቻ፣ ካህናት ብቻ የሚመስለው ብዙ ሰው ሊኖር ይችላል። በቤተክርስቲያን ጉዳይ ማንኛውም አማኝ ይመለከተዋል። ብዙ ሰው ጳጳሳቱ እና ካህናቱ የፈለጋቸውን ያድርጉ ምእመናን ዝም ይበሉ ዓይነት ሐሳብ ያነሣል። ግን ይህ ትልቅ ስሕተት ነው። ሁሉም ድርሻ አለው። ድርሻውን አውቆ መሥራት ከሁሉም ይጠበቃል።

የምእመናን ድርሻ

፩) በጳጳሳት ሹመት ዙሪያ ምእመናን ትልቅ ድርሻ አላቸው። ከግማሽ በላይ የሆነው ምእመን ካልፈቀደለት ማንኛውም ሰው ጳጳስ መሆን አይችልም። ስለዚህ ሕዝቡ ለጵጵስና ብቁ ያልሆነውን ሰው እንዳይሾምበት ማድረግ ይችላል። ቢሾምበት እንኳ አልቀበልም ብሎ ለቅዱስ ሲኖዶስ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

፪) ምእመኑ እናጠምቅሃለን እያሉ የሚያጭበረብሩ ባሕታውያን ነን ባዮች ሰዎችን አለመከተል ሙሉ ሥልጣን አለው። ሙሰኞችን፣ መተተኞችን፣ ጠንቋዮችን አለመከተል ነው።

፫) አንድን ስሕተት ሲኖዶስ ስላላወገዘው እያልን ወደ ስሕተቱ አንሂድ። ሲኖዶስ ባለማውገዙ ራሱ ይጠየቅበት። እኛ ግን እንደ ምእመን ከእግዚአብሔር የተቀበልነው እውነት አለ። ያን የሚቃረኑ አካላትን አለመከተል ይገባል። ለምሳሌ ስንዱን ሲኖዶስ ምንም አላላትም። ትክክል ስለሆነች ነው ማለት ነው?። ስንዱን የሚከተል ዥዋዥዌ መነኩሴ ካለ አባ ስላደረጉት እንከተላት ማለት ነው?! በጸም ወቅት ምእመኑን ሥጋ ስታስበላው ዝም የሚል ጳጳስ ስላለ እንከተላት ይባላል እንዴ? አይባልም።

የመምህራን ድርሻ

፩) መምህራን እውነታውን ሳያፍሩና ሳይፈሩ መግለጥ ነው። ምንም ሰሚ ባይኖር እንኳ የተማሩትን እውነት ለሌላው ይናገሩ። እንዲህ በማድረጋቸው ራሳቸውን ያድናሉ።

፪) መምህራን እውነትን እውነት ሐሰትን ሐሰት ማለት ይገባቸዋል። ንጉሥን ፈርተው፣ ጳጳስን ፈርተው እውነትን የማይናገሩ ከሆኑ ገና መምህራን አልሆኑም። ማንንም ቢሆን መመልከት ያለባቸው ከእውነት በታች ነው። እውነት ደግሞ እግዚአብሔር ነው።

፫) መምህራን የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተምህሮ ሌት ከቀን ሳይሰለቹ ለምእመናን ማስተማር አለባቸው። የእነርሱ ድርሻ ማስተማር ነው። ምእመናን ትምህርቱን ሰምተው ከተለወጡ መልካም ነው። ካልተለወጡም ግን የመምህራን ዋጋ አይቀርባቸውም።

የጳጳሳት ድርሻ

፩) የጳጳሳት ድርሻ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፬ እና አንቀጽ ፭ ላይ ተገልጿል። በዚያ መልኩ ሕዝቡን ማስተዳደርና ራሳቸውም መመራት አለባቸው።

፪) ጳጳሳትም፣ ካህናትም፣ ምእመናንም ከእግዚአብሔር በታች ናቸው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሕግ ሽረው ከተገኙ ቀኖና ይሰጣቸዋል። በደላቸው ክህነትን የሚያስሽር ከሆነ ይሻራሉ። ይህንን ደግሞ ማድረግ የጳጳሳቱ ድርሻ ነው። ይህንን ባያደርጉ ግን ፈጣሪ ይጠይቃቸዋል።

ቀኖና ሲሻር መሻሩን እስከ ዕለተ ሞታችን ለምእመናን ማሳወቅ ይገባል። በመጽሐፍም ጽፈን እነማን ቀኖናን እንዳፈረሱ ለትውልድ እናስተላልፈዋለን። በአንድ ወቅት ተናግረን ብቻ ዝም የምንለው አይደለም። ችግሩ በቀኖናው መሠረት ሲፈታ ብቻ ችግሩ በቀኖና መሠረት መፍትሔ መሰጠቱን እንናገራለን። ከዚያ ውጭ ያለ ቀኖና በመ*ፍቅ ንጉሥ ፊት በተስማማነው ስምምነት ተብሎ የቤተክርስቲያን ቀኖና ተሽሮ ዝም አንልም። እስከ ዕለተ ሞታችን ይህንን ግልጽ ቅጥፈት ለምእመናን እያሳወቅን እንቀጥላለን። የሲኖዶስ ስብሰባ በመጣ ቁጥር ብቻ እየተናገርን የምናልፈው ጉዳይ አይሆንም። ይህ ደግሞ የድርሻችን አንዱ አካል ስለሆነ በደስታ የምናደርገው ነው።

ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ሦስት ትርጉም አለው። እኒህም:-

- ✓ ፩) እያንዳንዱ አማኝ ቤተ ክርስቲያን ይባላል
- ✓ ፪) ጎብረተ ምእመናን ቤተ ክርስቲያን ይባላል
- ✓ ፫) ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ይባላል

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ማደሪያ ናት በምንልበት ጊዜ እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው ማለታችን ነው። በጎብረተ ምእመናን እግዚአብሔር እንደሚኖር መግለጣችን ነው። በሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በረድኤት ይኖራል ማለታችን ነው። እግዚአብሔር በአካሉ የሌለበት ቦታ የለም። በሁሉ ቦታ ይኖራል። በቤተ ክርስቲያን አለ ማለት በሌላው የለም ማለት አይደለም። ከሌለው ቦታ በተለየ ጸጋውን አብዝቶ የሚሰጥባት ቤተ ክርስቲያን ናት ማለታችን ነው እንጂ። የቤተ ክርስቲያን ራሷ ክርስቶስ ነው። ይህም ማለት መሪዋ እርሱ ነው ማለታችን ነው። ቤተ ክርስቲያን የምትመራው ደግሞ በእግዚአብሔር ሕግ ነው።

ሕገ እግዚአብሔር

ይህንን ሕግ አፍርሼ እንደሚመቹኝ አደርገዋለሁ ማለት አይቻልም። ሕጉን የማሻሻልም የመተውም ዋና ሥልጣን የእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር በቅዱሳን አድሮ ሕግን ሥርዓትን ቀኖናን ይሠራል። ይህንን ሕጉንና ቀኖናውን የሚያፈርስ ሲመጣ ግን ሳያፍሩና ሳይፈሩ መቃወም ይገባል። ተቃራኔ እግዚአብሔር ነውና። ከሕይወታችን ከእግዚአብሔር የሚለየን ክፉ አረመኔ ነውና። የሕይወታችን ምንጭ እግዚአብሔር ነው። ከምንም በላይ ቅድሚያ የምንወደው እግዚአብሔርን ነው። ሰውን የምንወደው ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ነው። ሰውን መውደድ ማለትም እንደ ራስ አድርጎ ማየት ነው። ለራሳችን የምንመኘውን ለሌላውም መመኘት ነው። ለራሳችን እንዲሆንብን የማንፈልገውን በሌላውም እንዲደረግ አለመፈለግ ነው። የሌሎችን ደስታ እንደ ራስ ማየት፣ የሌሎችን ኀዘንም እንደ ራስ አድርጎ አይቶ ማዘን ነው። ቤተ ክርስቲያንን መውደድ ስንል እያንዳንዱን ምእመን መውደድ ነው። አንድ ሰው ቤተ ክርስቲያንን እወዳለሁ ሲል ሕጓን፣ ቀኖናዋን፣ አስተምህሮዋን፣ አካሏን እግዚአብሔርን እወዳለሁ ማለቱ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የሕይወት መገኛ ስለሆነች እንውደዳት። ሁልጊዜም እናስባት። ሰላም ለክሙ ኦ አፍላገ ወንጌሉ ለክርስቶስ ወትረ ሐውጽዋ ለቤተ ክርስቲያን ።

ባህል

መልካም ባህሎቻችንን ብንጠብቃቸውስ?

ሰላምታ:-ሰላም ስንል ምላሽ እግዚአብሔር ይመስገን ማለት። በሰላምታችን እግዚአብሔርን እየገለጥን ነው ማለት ነው። በቀን ባገኘናቸው ሰዎች ልክ እግዚአብሔርን እንደማመስገን ምን ደስ የሚል ነገር አለ። ስለዚህ የሰላምታ አሰጣጣችን እንደ ቀድሞው ቢሆን!?

አበላል:- ስስትን በሚያሳውቅ መልኩ አንዷን እንጀራ ሦስት ጉራሽ እያደረጉ መብላት ተገቢ አይደለም። (በእርግጥ አሁን አሁን የሚጋገረው እንጀራ ከመሳሳቱ የተነሣ እፍኙ ስትለው ብድግ ሊል ይችላል)። መጽሐፈ መነኮሳት ላይ እንደተገለጠው ስንበላ ከአፋችን እንዳይነጥብ ልብሳችንን እንዳንበክል ጓደኞችንን ወጥ እንዳንቀባ ከሰው ፊት ሳንበላ በሥርዐት መመገብ ብንችል። ይህ መጽሐፋዊ የሆነ ድንቅ ባህላችን ስለሆነ ብናስቀጥለው። መጽሐፈ መነኮሳት ትርጓሜ ላይ ሊቃውንቱ ሲናገሩ "አለፍ አለፍ እያልክ እንግዳው "ብላ እንጂ" በለው ይላል። እንዳይሰቀቅኮ ነው። አያበቃም እንዴ ይሉኛል ብሎ እንዳያስብ ደስስስ ብሎ ይበላ ዘንድ ማለት ነው። ከመብላታችን በፊትና በልተን ከጨረስን በኋላ እግዚአብሔርን እናመስግን። በቀን ሦስት ጊዜ የሚበላ ሰው በምግቡ ጊዜ እንኳ እግዚአብሔርን ቢያንስ ስድስት ጊዜ ያመሰግነዋል።

አለባበስ:- የልብስ ዋና ፍሬ ነገር እርቃንን ለመሸፈን ነው። በዚህም ምክንያት ሰውን ከዝሙት ሐሳብ ለመጠበቅ ነው። ይህ ከሆነ ሴትም ወንድም ሰውነቱን ጥብቅ አድርጎ የሚያሳይ ልብስ መልበስ የለበትም። ሰፋ ያለ ልብስ መልበስ ይገባል። መጽሐፈ ሐዊ እና ፍትሐ ነገሥት በዚህ ዙሪያ ጥሩ አድርገው ገልጸውልናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ መጽሐፍ ያዘዘውን ይኖር ስለነበር ባህላችን እስከ መሆን ደርሶ ነበር። አሁን አሁን ግን ሴቱም ወንዱም ሰውነቱን ጥብቅ አድርጎ የሚያሳይ ልብስ እየለበሰ ይስተዋላል። ይህ እንዳይሆን የቀድሞ ባህላችንን ብንጠብቅ። ሴት መሸፋፈን አለባት ተብሏል። ጸጉሯን በሰርመዴ (በሻሽ) ትሸፍን ተብሏል። ስለዚህ ለምን አሁን ላይ ሴቶቻችን ጸጉራቸውን እያሳዩ ይሄዳሉ?! በጸሎት ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ቦታ ሴት ልጅ ጸጉሯን መሸፋፈን አለባት ተብሏል።

አነጋገር:- የቀድሞ አባቶቻችን እናቶቻችን አነጋገራቸው ቁጥብ ነበር። አሁን ቀለብላቦች እየሆንን መሰለኝ። ይህንን ቀንሰን የምንናገረውን እያስተዋልን ተራ ጠብቀን ብንነጋገር መልካም ነው። ሌላው ሰው እየተናገረ ካለ ተደርበን አለመናገር ይገባል። ሲናገር ለተናጋሪው ትኩረት መስጠት አለብን። ማድመጥን መለማመድ አለብን። በባህላችን ስድብ ትልቅ ነውር ነው። አሁን ግን ብዙ ሰው በማኅበራዊ ሚዲያ ሲሳደብ ይውላል። አንዳንዱ በብዕር ስም ተደብቆ ይሳደባል። ይህንን እግዚአብሔር አይወደውም። ምስጋና ከሚወጣበት አፍ ስድብ ሊወጣበት አይገባም። ተሳዳቢነትን ተግሣጽ ብሎ ማሸሞንሞንም አይገባም። ግእዙም ስድብን ጽእለት ነው የሚለው። በተግሣጽ ጊዜ ከአፍ የሚወጣ ስድብ የለም። በተግሣጽ ጊዜ የሚወጣው ቃል የጠራ እውነት ነው። ይኽውም ማንንም ሳይፈሩ እውነትን በመመስከር ይገለጣል እንጂ በመሳደብ አይገለጥም። ስድብ ብልግና ነው። ይህንን ብንተው መልካም ነው።

ክብር:- የቀድሞ እናቶቻችን አባቶቻችን ሰውን ሁሉ ያከብራሉ። ሽማግሌዎች ክቡራን ናቸው። ቀሳውስት ክቡራን ናቸው። ጳጳሳት ክቡራን ናቸው። ስለዚህ በግለሰቦች ላይ ያነጣጠረ ስድብን መሳደብ አይገባም። ስሕተት ሰርቶ ቢገኝ እንኳ ሳይፈሩ ሳያፍሩ ስሕተቱን መግለጥ እንጂ መሳደብ አይገባም። በስድብ የሚስተካከል ሰው የለም። ኃያል እውነት ናት። እውነታውን አብዝቶ መግለጥ እና ስሕተቱን ስሕተት መሆኑን በማስረጃ መሞገት ይገባል እንጂ መሳደብ ሃይማኖታችንም አይፈቅድም። በባህላችንም ነውር ነው። አሁን አሁን ግን ሴቷም ብድግ ብላ ትልልቅ ሰዎችን በአደባባይ ስትሳደብ ትውላለች፣ ጨዋው ይነሳና ካህናትን ሲሳደብ ይውላል። ካህናትም ጨዋውን ሲሳደቡ ይውላሉ። ይህ ብልግና ነው። ሰው እውነትን በማስረጃ ይገልጣል።

ስሕተትንም በማስረጃ ሳይፈራና ሳያፍር ይገልጣል። ሰውን ማናናቅ፣ ማጥላላት፣ እና መሳደብ ግን የሰይጣን ገንዘቦች ስለሆኑ ገንዘቡን እንመልስለት። ለቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ ነን ካልን ተቆርቋሪነታችንን በመሳደብ መግለጥ አሳፋሪ ነው። ይህኮ አይሁድ እግዚአብሔርን እንወዳለን ብለው ጌታን እንደሰቀሉት ያለ ፌዝ ነው። ለቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ የሆነ ሰው እውነትን በእውነትነቷ ይገልጣታል። ስሕተትን ደግሞ ሳይፈራና ሳያፍር ሳይሳደብ በትክክል ይገልጣል። ይህንን እንልመድ።

ምሥጢራዊነት፦ አንዳንድ ሰዎች ሲጣሉ ምሥጢራቸውን ለሌላ ይገልጣሉ። ይህ ግን ትንሽነት ነው። ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወንጌላዊው ሉቃስ ሲጽፍ "ይህንን ሁሉ በልቧ ትጠብቀው ነበር" ተብላለች። ብዙ ነገር አይታ ግን በልቧ ትጠብቀው ነበር። እኛም ያየነውን ሁሉ የምንለፈልፍ መሆን አይገባንም። ምሥጢራዊነትን ገንዘብ ልናደርግ ይገባል።

መረዳዳት፦ በሀገራችን ደቦ የሚባል ድንቅ ባህል አለን። እርስ በእርስ መረዳዳት ትልቅ ባህላችን ነው። የፍቅረ ቢጽ መገለጫ ነው። ሲረዳዱት ብዙው ሥራ ትንሽ ይሆናል። ደራሲ፦

ሐንካስ በእግረ እውር ሖረ

እውርኒ በዓይነ ሐንካስ ነጸረ

ወበክልኤሆሙ ወይንየ ተመዝበረ

ያለው መረዳዳትን የሚገለጽ ነው። ዓይነ ስውሩ በአንካሳ ዓይን ቢያይ፣ አንካሳው በእውሩ እግር ቢሄድ በጋራ ትልቅ ነገር መስራት ይችላሉ።

እርቅ፦ ሰው በተለያየ ምክንያት ሳይግባባ ይቀርና ይጣላል፣ ይሰዳደባል ወዘተ። እስከ መደባደብ እስከ መገዳደል ሊደርስ ይችላል። ያለፈውን በደል ትቶ በአዲስ ልብ የወደፊቱን ሕይወት በፍቅር በደስታ ለመኖር ላለፈው ይቅር መባባል ለወደፊቱ መጠበቅ ይገባል። በልብ ቂምንና ጥላቻን መያዝ ጥሩ አይደለም። ልባችንን አናቆሽሸው። ኩራትን እንጣለው። ተቀራርቦ መነጋገርን እንልመድ። በዚህ ጊዜ አለመግባባት ይወገዳል።

በአሁኑ ሰዓት ያለዕረፍት ቤተ ክርስቲያንን እየፈተኗት ያሉ

- 1 ሰይጣን
- 2 ቤተክርስቲያንን በውሸት የሚከሱ ፖለቲከኞች
- 3 መሰኖች፣ ሌቦች፣ ጉቦኞች
- 4 ዘረኞች
- 5 መተተኞች፣ ጠንቋዮች
- 6 ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን

- 7 እናጠምቃለን እያሉ የሚያጭበረብሩ ባሕታውያን ነን ባይ አጭበርባሪዎች
- 8 ግላዊ አመለካከታቸውን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አስመስለው የሚያቀርቡ ያልተማሩ ሰዎች
- 9 ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ግላዊ ክብራቸው የበለጠባቸው ሰዎች፣
- 10 ቤተ ክርስቲያንን ለሥጋዊ ጥቅማቸው ብቻ የተጠጓት ምንዱባን

ወዘተ ናቸው። ታዲያ እነዚህ ችግሮች ከሆኑ ምን እናድርግ ከተባለ መጀመሪያ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን እንደማይወክሉ መረዳት አለብን። እነ ስንዱን ሲኖዶስ ስላላወገዛቸው ትክክል ናቸው ማለት ነውር ነው። ሲኖዶስ አለማውገዙ የትክክለኝነት ምልክት አይደለም። ከላይ ከጠቀስናቸው አካላት ጋር አንዳንድ የሲኖዶስ አባላትም በአንድ ላይ ፎቶ ተነሥተው ብታዩዋቸው ትክክል ስለሆኑ አይደለም። ስንዱ አሁን በዐቢይ ጾም ትንሣኤ ነው እያለች ምእመናንን ሥጋ እያበላች ነበር። ግን ትንፍሽ ያለ አባት የለም። ሥራዋ ስሕተት መሆኑ ተገልጦ ምእመናን ከእርሷ እንዲታቀቡ መልእክት ያስተላለፈ ጳጳስ አላየሁም። ምናልባት መረጃ ካለ መረጃውን አጋሩኝ። የቤተክርስቲያን ልኳ ክርስቶስ ነው። እነ መምህር እገሌ፣ እነ አባ እገሌ ከስንዱ ጋር ስላጨበጨቡ ልክ ናቸው ማለት ተገቢ አይደለም። እነርሱ ያጨብጭቡ ተዋቸው። ራሳችሁን ግን አድኑ። ለማንኛውም ነገር መለኪያችን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ይሁን። በግለሰብ ግላዊ አመለካከት ላይ የተመሠረተ እምነት አይኑረን። ሁሉንም በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እንመዝነው። መዝነን መልካሙን እንያዝ ክፉውን እንተው። እንፈውስሃለን እያሉ በመቁጠሪያ ሲገርፉህ ሲውሉ ዝም ብለህ አትከተል። መቁጠሪያ በትውፊታችን እንደ ስመ መቁጠሪያ ነው እንጂ መግረፊያ አይደለም። መቁጠሪያ ማለትም መነኮሳት አባቶች ጊዜያት ሲያደርሱ፣ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ሲሉ 41 ፍሬ ያለው ይሆንና እስከ ጉጠቱ ድረስ ይሉበታል። አንድን ነገር ዝም ብሎ መቀበል አይገባም። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን አለ፣ ቅዱሳን ሐዋርያት ምን አሉ፣ በእነርሱ የተተኩ ቅዱሳን ሊቃውንት ምን አሉ የሚለውን መያዝ ያስፈልጋል። እንጂ ሰዎችን ከምእመን እስከ ፓትርያርክ አይሳሳቱም ብሎ አስቦ ሲሳሳቱም የስሕተታቸው ተባባሪ መሆን አይገባም። የግለሰብ፣ የሰባክያን፣ የመምህራን አጨብጫቢ መሆን አይገባም። መልካም ነገር ሲናገሩ ቃለ ሕይወት ያሰማልን እንላለን። ከመጻሕፍት የማይገጥም የራሳ

ቸውን መሰለኝ ሲናገሩ ደግሞ እንቃወማቸዋለን። ለዚህ ደግሞ መለኪያችን ሁልጊዜም ትክክል የሆነችዋንና የማትሳሳተዋን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እንያዝ። ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት። በእርሷ ሁላችንም በክርስቶስ አንድ ነው። የዘረኝነትን እሳቤ ከአእምሮ ውስጥ ነቃቅሎ መጣል ያስፈልጋል። ክፋትን በእኩልነት ማውገዝ፣ መልካም ነገርንም በእኩልነት መቀበል ይገባል። በብሔሩ ምክንያት ጻድቁን ኃጥእ፣ ኃጥኡን ጻድቅ ማለት አይገባም። ክርስትና እውነትን እውነት፣ ሐሰትን ሐሰት ማለት ነው። ዘረኛ ሰው ክርስቲያን ነኝ አይበል። ክርስቲያን ከሆነ የክርስቶስ ነው። የክርስቶስ የሆነ ደግሞ ሰውን በሰውነቱ በግል ማንነቱ ይለካዋል እንጂ በጅምላ አይናገርም። ከጅምላ ፍረጃ፣ ከዘረኝነት መላቀቅ ያስፈልጋል።

ነገረ ማርያም

የብሉያት መተርጉማን ከዚህ ላይ እመቤታችንን "በትረ ሕይወት" ይሏታል። ኢሳ. ፲፩፣፩ "ወትወፅእ በትር እም ሥርወ እሴይ። ወየዐርግ ጽጌ እምኔሃ"። ይህ በብሉያት ትርጓሜ በ፫ ያስተረጉማል። አንደኛ ከነገደ እሴይ ሕዝቅያስ ዘሩባቤል ይወለዳል፣ ከሕዝቅያስ ከዘሩባቤል ደግሞ ምግባር ሃይማኖት ይገኛል ማለት ነው። ሁለተኛ ከነገደ እሴይ በትረ ሕይወት እመቤታችን ትወለዳለች። ጽጌ ክርስቶስም ከእመቤታችን ይወለዳል ማለት ነው። ሦስተኛ ከነገደ እሴይ ከተወለደች ከእመቤታችን ጌታ ይወለዳል። ከጌታ ደግሞ ክብር ልጅነት ይገኛል ማለት ነው። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን "ጽጌ" ይላታል። አበባ ማለት ነው። አበባ ፍሬን ያስገኛል። ድንግል ማርያምም ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስን በሥጋ ወለደችልን። በዚህ ጊዜ ልጇን ክርስቶስን "ፍሬ ሕይወት" ይለዋል። የሕይወት ፍሬ ማለት ነው። የሰው ልጆች ይህንን ፍሬ እየበሉ ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ። ይህ በአንደኛው ትርጓሜ ነው። በሌላኛው ትርጓሜ ግን ከእሴይ ወገን በትር እመቤታችን ትወለዳለች። ከበትር እመቤታችን ደግሞ ጽጌ ክርስቶስ ይወለዳል ይላል። አበባ መዓዛ አለው። ክርስቶስም መዓዛ ሕይወት ነውና። የሕይወታችን መልካም መዓዛ ክርስቶስ ነው። በሉ ኑ ንሥሓ እየገባን የሕይወት ፍሬ ሥጋ ክርስቶስ ደመ ክርስቶስን እንቀበል።

አንድ ወንድ ለሰባት ሴት

ወንድ ወንዱ በጦርነት አልቆ ጥቂት ወንዶች ብቻ ይቀራሉ። ያን ጊዜም ሴቱ ስለሚበዛ አንዱን ወንድ ሰባት ሴቶች አግባን ይሉታል። ያ ጊዜ መቼ እንደሆነ ግን አልተገለጸም። ኢሳ. ፬፣፩ "በዚያም ቀን ሰባት ሴቶች። የገዛ እንጀራችንን እንበላለን የገዛ ልብሳችንንም እንለብሳለን፤ ስምህ ብቻ በእኛ ላይ ይጠራ፥ መሰደባችንንም አርቅ ብለው አንዱን ወንድ ይይዙታል" ተብሎ ተጽፏል። ይህ ለጊዜው በትንቢቱ እንደተገለጸው ሰሙ ወንዱ አንሶ ሴቱ ይበዛልና ነው። ወርቁ ግን ወንድ የተባለ ክርስቶስ ነው። ወብእሲ ተወልደ በውስቴታ ተብሏልና። ሰባት ቁጥር በዕብራውያን ትርጓሜ ፍጹም ነው። እስመ ጉልቁ ሳብእ በጎበ ዕብራውያን ፍጹም ውእቱ እንዲል። ሴቶች የተባሉ ምእመናን ናቸው። ሰባት ሴቶች ማለት ፍጹማን ምእመናን ማለት ነው። የገዛ እንጀራችንን እንበላለን ማለት ምግባር ትሩፋት እንሰራለን ማለት ነው። ስምህ ብቻ በእኛ ላይ ይጠራ ማለት አንተ ክርስቶስ እንደተባልክ እኛም ክርስቲያን እንባል ማለት ነው። መሰደባችንን አርቅ ማለት ጣዖት አምላኪ መባላችንን አርቅ፣ አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ ያለውን የዕዳ ደብዳቤ ደምስስልን ማለት ነው። የስም ክርስቲያን አንሁን። በኑሮም፣ በንግግርም፣ በሥራም ክርስትናችንን የሚገልጽ እንሁን። የወሬ ብቻ ሳይሆን የተግባር ክርስቲያንም እንሁን። ጥላቻን በፍቅር፣ በደልን በይቅርታ እናስወግድና ሰላማውያን እንሁን።

ኒቋስጣኑ ኒቋስጣጣኑ

በዓለመ መላእክት ሳጥናኤል ቅዱሳን መላእክትን በገጠማቸው ጊዜ ያሸነፉት በረቂቅ ክንፋቸው የነበረውን መስቀል አሳይተው በረድኤተ እግዚአብሔር ነበር። መስቀል የአሸናፊነት ምልክት ነው። መስቀል በኂላም ክርስቶስ ሰይጣንን ከምድር ከፍ ከሰማይ ዝቅ አድርጎ ያሰቃየበት አደባባይ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም መዳን ደሙን ያፈሰሰበት መስቀል ነው። ቅዱስ ያሬድ

በድጓው መስቀል ሞዐ ሞት ተሞዐ ብሏል። መስቀል አሸነፈ ሞት (ዲያብሎስ) ተሸነፈ ማለት ነው። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በሰማይ ኒቁስጣኑ ኒቁስጣጣኑ ተብሎ ተጽፎ አየ። በእኛ ሀገር ትርጉም በዚህ መስቀል ጠላቶችህን ታሸንፋለህ ማለት ነው። ንጉሡም ከጦሩ የመስቀል ምልክትን አድርጎ ከመክስምያኖስ ጋር ጦርነት ቢገጥም መክስምያኖስን አሸንፎታል። ስለዚህ መስቀል አሸናፊ ነው።ንክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀሉ ተአምር እያደረገ ስህተታቸውን ስለገለጠባቸው አይሁድ ቀበሩት። በኋላ ግን ንግሥት ዕሌኒ አረጋዊው ኪራኮስን (ኪሪያኮስን) አማክራ ከተቀበረበት ከ300 ዓመታት ገደማ በኋላ አውጥታዋለች። ደመራ አስደምራ በደመራው ዕጣን ጨምረችበት። ጢሱም ከፍ ከፍ ብሎ መስቀሉ የተቀበረበትን አሳየ። በዚህ መልኩ ተቆፍሮ ወጥቷል። ዘዕጣን አንጸረ ሰገደ ጢስ መባሉ ለዚያ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ይቅር አለን። ነገረ መስቀሉን ሁልጊዜም እናስበው ዘንድ መሓሪ እግዚአብሔር ይርዳን።

በሰማይ የሀሉ ልብክሙ።

ከዘረኝነት እሳቤ ወጥተን ልባችንን በሰማይ እናድርገው። በዚያ መላእክት አሉ፣ ቅዱሳን ጻድቃን አሉ። ምድር ለምድር ስንርመሰመስ በሰማይ ያለውን አንዘንጋ። ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ I hate racism_ዘረኝነትን እጠላለሁ። እስራኤል (አውቱዝራማ) የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ እና እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም የተወለዱባት ቦታ ናት። ቅዱሳኑ ነቢያት እነ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ ወዘተ የተወለዱባት ናት። ሐዋርያቱ እነ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ የተወለዱባት ናት። ይህን የመሳሰለውን ሁሉ ጠቅሰን እስራኤል ከሀገር ሁሉ ትበልጣለች ይባላልን?!። በጭራሽ አይባልም። ነቢያትም ስለ ዓለም ድኅነት ተነበዩ፣ ሐዋርያትም ለዓለም ድኅነት ሰበኩ፣ ክርስቶስም ለዓለም ድኅነት ተሰቀለ። ምድር መላዋ የእግዚአብሔር ናት። የፍጥረታት ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ነው። ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ ከጠበቀ የእግዚአብሔር ወዳጅ ይባላል። ማንኛውም ሰው የሚለካው በሀገሩ የት ተወለደ በሚለው ሳይሆን ምን ሰራ በሚለው ነው። እስራኤላውያን የአብርሃም ልጆች ነን በማለት ይመኩ ነበር። ከአብርሃም መወለድ ግን የሚያስመካ ነገር አልነበረም። የትም ሀገር መወለድ አያስመካም። የጎንደር ግምጃ ቤት ማርያም የትርጓሜ መምህር የነበሩት የኔታ ሊቀ ማእምራን (መጋቤ ሐዲስ) ወልደ ሰንበት ሀገር በውሸት አትከብርም ይሉ ነበር። በውሸት የከበረ ሀገር የለም። ሰይጣን በውሸት ከሁሉ እበልጣለሁ አምላክ ነኝ ቢል የደረሰበትን ሁላችንም እናውቃለን። ማንም ሀገር ከማንም ሀገር አይበልጥም። ማንም ሀገር ከማንም ሀገር አያንስም። የሰው ልጅ ሁሉ የእግዚአብሔር መልክ ነው። አንድ ሀገር ቅድስት የምትባለው በውስጧ የሚኖሩ እያንዳንዳቸው ሰዎች ደጋጎች የማይጣሉ የማይገዳደሉ ከሆኑና የእግዚአብሔርን ሕግ ሲጠብቁ ነው። ለማንኛውም ሰው ክብር አለን። የቅዱሳንን ሥራ ለአንዲት ጎጥና ቀበሌ እያደሉ መጥራት ክርስትናን ያለመረዳት በሽታ ነው። ቅዱሳን የጸለዩት ጸሎት ለሰው ልጅ ሁሉ ነው። እነርሱ በጎጥ አያስቡም። ለዓለም ሥርየት ሲለምኑ ነው የኖሩት። ከሃድያን ቢነሱ አፈ ጉባኤ ሆነው በእግዚአብሔር ረድኤት ከሃድያንን የረቱ እነ ቅዱስ ቄርሎስ እነ ቅዱስ አትናቴዎስ እነ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ እነ ቅዱስ ጢሞቴዎስ ሀገራቸው በሰማይ ነው። ጌታችን ወደ ግብጽ ሲሰደድ የአስቁጥስን ቦታ ባረካት ይላል። እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጠየቀችው እርሱም እስከ እለተ ምጽአት ስሜን የሚያመሰግኑ ምድራውያን መላእክት መኮሳት ወደፊት ይነሳሉ

ብሏታል። ግብጻውያን ይህን ይህን ጠቅሰው ከዓለም ሀገራት እንበልጣለን ቢሉ አያሳፍርምን!?። ያሳፍራል። ይህ ለእነርሱ የተሰጠ ጸጋ ነው። ኢትዮጵያ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ስለተገለጠላት ታቦተ ጽዮን ስላለች፣ የመልከ ጼዴቅ ሀገር ስለሆነች (በአንዳንድ ሰዎች አባባል ነው እንጂ መልከጼዴቅ ሴማዊ ነው የሚሉ ሊቃውንትም አሉ) እና በመሳሰሉት ከዓለም ሁሉ ትበልጣለች ይባላልን!?። ሐሰ። አይባልም። ክርስቶስ የሞተ ለዓለም ነው። ሐዋርያት የሰበኩ ለዓለም ነው። ሁሉም ሀገራት በተፈጥሮ የተሰጣቸው ልዩ ልዩ ጸጋ ይኖራል። ሁሉም የየራሱን ታሪክ እያወራ እበልጣለሁ የሚለውን ከንቱ ነገር ትቶ አሁን ላይ ያለውን እውነታ ተቀብለን መኖር ይገባል። አነቃቂ ስሜታዊ ንግግር ሌላ ነው። ሃይማኖታዊ ትምህርት ሌላ ነው። በንጹሑ ወንጌል ላይ እንክርዳድ እየጨመራችሁ አታስተምሩ። አሁን ምድር ላይ ያለው እውነታ ኢትዮጵያ ወንድማማቾች የሚገዳደሉባት፣ ዘረኝነት የነገሠባት፣ ጥላቻ መለያየት የሰፈነባት ናት። ይህን እውነታ ተቀብለን ጉራውን ትተን ከዚህ በሽታ የምንወጣበትን መንገድ ብናስብ ይበልጣል።

ውስንነትን ማወቅ

በሁሉ ረገድ ፍጹም የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው። የሰው ልጅ አካሉ የተወሰነ ነው። እውቀቱ የተወሰነ ነው። ምንም እንኳ ከተፈጠረ በኋላ ዘላለማዊ ቢሆንም ያልኖረበት ዘመን ነበረ። ይህ ሁሉ ተደምሮ የሰው ልጅ ውሱን እውቀት ውስን እይታ ስላለው ፍርዱ አስተያየቱ ፍጹም አይሆንም። በፍርዱ ስህተት ሊገኝበት ይችላል። ለዚያ ነው አንድን ነገር በምልዐት ስለማናውቀው "እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ" የተባልነው። ማቴ.7፣1። ለሁሉ ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ የተባለውም ሌላውን ሰው ስለማናውቀው ምናልባት መልአክ ወይም እግዚአብሔር ሊሆን ስለሚችል ነው። መልአክ ወይም እግዚአብሔር በብዙ አምሳል ይገለጣሉና። ስለዚህ አጥርተን በማናውቀው ጉዳይ ዝም ብንል የተሻለ ይሆናል። እኛ ለሌላው ሰው ይጠቅማል ለእኛም ነፍሳዊ ጥቅም ያሰጠናል ብለን የምናስበውን እንናገር እንኑር። እኛ ለመልካም አስበነው ነገር ግን ለእኛም ለሌላውም አሉታዊ ነገር ካሳደረ ግን ይቅርታ እንጠያየቅ። ይቅርታ የተመሠረተው በማወቅም ባለማወቅም የሠራነውን በደል ለማራቅ ነውና። ውሱንነቱን የተረዳ ሰው አይታበይም፣ ከንቱ ውዳሴን አይፈልግም፣ አይዋሽም፣ ሰውን ከማማት ይልቅ አይድረስ ይላል፣ ዲያብሎስ የወደቀ ውሱንነቱን ባለመረዳቱ ነበር። ውሱንነቱን የተረዳ ሰው አይኮራም፣ በማንም አይፈርድም። ፍጥረታት በሙሉ ውሱን ናቸው። ቁመታቸው፣ ስፋታቸው፣ ዘመናቸው፣ አጠቃላይ ልኬታቸው በተለያዩ መለኪያዎች ተለክቶ የሚታወቅ ነው። ለእርሱ ወሰን የሌለው ፍጥረታትን ግን የሚወስን በሁሉ ሙሉ እና ፍጹም የሆነ እግዚአብሔር ነው። መምህራንም ቢሆኑ የተማሩት ጥቂቱን ስለሆነ ሁሉን ማወቅ ስለማይችሉ የማያውቁትን ጉዳይ በግምት እና በመሰለኝ ከማውራት ይልቅ አላውቀውም ማለት ይገባቸዋል። እውቀትን ሁሉን ለሚያውቅ መንፈስቅዱስ እንስጥ። የነገሮችን መገጣጠም እያየን ግምት በጣም ግፋ ቢል ጥሩ ግምት ልንናገር እንችላለን እንጂ እውነታውን ላናውቀው እንችላለን። ስለዚህ የምናውቀውን እየተናገርን ያየነውን እየመሰከርን የማናውቀውን እና ያላየነውን ግን ሳናወራ ልንኖር ይገባል። ለዚያ ነው ሐዋርያ "በዘነአምር ንነግር ወበዘሰማእነ ሰማእተ ንከውን" ያለው። በሉ ኑ ውስንነታችንን ተረድተን በሁሉ ፍጹም የሆነ እግዚአብሔርን እናመስግነው።

ለልጅዎ የግእዝ ስም ማውጣት ከፈለጉ

ግእዝ_____አማርኛ

፩) መዓርዒር_____ጣፋጭ

፪) አሜር_____ፀሐይ

፫) አርያም_____ሰማይ

፬) አምኃ_____እጅ መንሻ

፭) ብሥራት___የምስራች

፮) ሰሎሜ_____ሰላም

፯) አሜን_____እውነት/ይሁንልኝ

፰) ሠዊት_____እሸት

፱) ጸገየ_____አበበ

፲) አስካል____ፍሬ

፲፩) ልዑል____ከፍ ያለ

፲፪) ሣህሉ____ይቅርታው

፲፫) ቀጸላ_____አክሊል

፲፬) ሐመልማል___የለመለመ

፲፭) ከሃሊ_____የሚችል ቻይ

፲፮) ጸዳሉ_____መብራቱ

፲፯) ፈትለ ወርቅ____የወርቅ ፈትል

፲፰) ፊደል_____ፊደል

፲፱) ማኅቶም____ማቶሚያ

፳) ሥዩም_____የተሾመ ሹም

፳፩) ስብሐት____ምስጋና

፳፪) ስቡሕ_____ምስጉን

፳፫) ተቅዋም_____መቅረዝ

፳፬) ንጹሕ_____የነጻ

፳፭) ሰላማ_____ሰላም

፳፮) አዳም_____ያማረ

፳፯) ዳግም_____የደገመ

፳፰) ግሩም_____ተፈሪ

፳፱) ጥዑም_____የሚጣፍጥ

፴) ፍጹም_____የተቀባ

፴፩) ይቴይስ_____ተሻለ

፴፪) ሐዳስ/ሐዲስ___አዲስ

፴፫) ሕዳሴ_____መታደስ

፴፬) ሰንኮሪስ_____መምህር

፴፭) መቅደስ_____ማመስገኛ

፴፮) ሞገስ_____ባለሟል የተወደደ

፴፯) ትዕግሥት_____መቻል

፴፰) ንጉሥ_____የነገሠ

፴፱) ወራሲ_____ወራሽ

፵) ውዳሴ_____ምስጋና

፵፩) ጌራወርቅ_____የወርቅ ሥራ

፵፪) ማኅደር_____ማደሪያ

፵፫) ምሕረት_____ይቅርታ

፵፬) መሓሪ_____ይቅር ባይ

፵፭) ሠምረ_____ወደደ

፵፮) ሥሙር_____ተወዳጅ

፻፲) ሥምረት_____መወደድ

፻፳) ነጸረ_____ተመለከተ

፻፴) ምሥጢሩ_____ምሥጢሩ

፻፵) መራሒ_____መሪ

፻፶) ፍሥሓ_____ደስታ

፻፷) አእመረ_____አወቀ

፻፸) አእምሮ_____እውቀት

፻፹) ፍቅር_____መውደድ

፻፺) ክቡር_____የከበረ

፻፻) ደብሩ_____ተራራው

፻፻፲) ተግባር_____ሥራ

፻፻፳) ረቂቅ_____ረቂቅ

፻፻፴) መብረቁ_____መብረቁ

፳) ነጸብራቅ_____ነጸብራቅ

፳፩) ይባቤ_____እልልታ

፳፪) ጥበቡ_____ብልሃቱ

፳፫) መሠረት_____መሠረት

፳፬) ብሑት_____ስልጡን

፳፭) ትሕትና_____ትሕትና

፳፮) ተከሥተ_____ተገለጠ

፳፯) ሃይማኖት_____ሃይማኖት

፳፰) በየነ_____ፈረደ

፳፱) መኰንን_____ገዢ

፴) በጽሐ_____ደረሰ

፫፩) መስፍን_____የሚገዛ

፫፪) ምስፍና_____ግዛት

፫፫) ክርስቲያን_____ክርስቲያን

፫፬) ወሰን_____ድንበር

፫፭) መዋዒ_____አሸናፊ

፫፮) ትንሣኤ_____መነሳት

፫፯) ነቅዐ ሕይወት_____የሕይወት ምንጭ

፫፰) ገዛኢ_____ገዢ

፫፱) ምሕርካ ክርስቶስ___የክርስቶስ ምርኮ

፬) ባራኪ_____ባራክ

፬፩) መልአክ_____አለቃ

፬፪) በረከት_____በረከት

፬፫) ህላዌ_____መኖር

፬፬) ኂሩት_____ቸር የሆነች

፬፭) ልባዌ_____ማስተዋል

፬፮) ቤዛዊት_____ያዳነች የምታድን

፬፯) ስርጋዌ_____ሽልማት

፬፰) ስርጉት_____የተሸለመች

፬፱) ተስፋ_____ተስፋ

፭) ኬንያ_____ብልሃተኛ

፭፩) ኖላዊ_____ጠባቂ

፭፪) መርዓዊ_____ሙሽራ

፭፫) ማዕዶት_____መሻገሪያ

፭፬) ወልታ_____መከታ/ጋሻ

፮፫) ሐዋዝ_____ያማረ

፮፮) ግእዛን_____ነጻነት

፮፯) ሕሊና_____ሕሊና

፮፰) ማጎሌት_____ምስጋና

፮፱) ጎሩይ_____ምርጥ

፯) ሲሳይ_____ምግብ

፯፩) ሠናይ_____ያማረ

፯፪) ፈታሒ_____የሚፈርድ

፯፫) ሐሴት_____ደስታ

፯፬) ትርሲት_____ሽልማት

፯፭) ተዋናዩ_____ተጫዋች

፯፮) ዐቢይ_____ከፍ ያለ

፯፯) ትውፊት_____ስጦታ

፯፰) ኃያል_____የበረታ

፯፱) ጽጌ_____አበባ

፰) ፍሬሕይወት_____የሕይወት ፍሬ

፰፩) ምዕዳን_____ምክር

፰፪) ንኡድ_____ያማረ

፰፫) ነገደ_____ሄደ

፰፬) ነጎድጓድ_____ነጎድጓድ

፰፭) ጸዓዳ_____ነጭ

፰፮) ሠረጸ_____በቀለ

፰፯) ደምፀ_____ተሰማ

፰፰) ሮሐ_____ወለወለ/አራገበ/አናፈሰ

፻፲፱) ናርዶስ_____ሽቱ

፻፳) ዕፀ ሕይወት___የሕይወት እንጨት

በእንተ ጽድቅ ስለ እውነት

ሰው ሐሰትን ትቶ እውነትን ሲናገር ፈጣሪውን ይመስላል። ሐሰት የእውነት ተቃራኒ ነው። ሐሰትን ከልቡ አፍልቆ የተናገራት የመጀመሪያው ፍጡር ዲያብሎስ ነው። ሐሰት ያልተደረገውን እንደተደረገ የተደረገውን እንዳልተደረገ አድርጎ ማውራት ነው። ሐሰት ያልሆኑትን እንደሆኑ የሆኑትን እንዳልሆኑ አድርጎ ማውራት ነው። ቅዱሳን እውነትን እየተናገሩ ኖሩ። እውነትን የያዘ ሰው ሁልጊዜም አሸናፊ ነው። ከመዋሸት እውነቱን ተናግሮ መፍትሄ መፈለግ ይሻላል። ውሸት ውሸትነቷ መገለጡ አይቀርም። እውነትን የያዘ ሰው ሁልጊዜም አይፈራም አያፍርምም። ጌታችን ሲያስተምር መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ ያፈራል። መልካም ልብ መልካም ነገር ይናገራል ብሏል። በቸርነቱ የሰውን ልጅ ለክብር የፈጠረ ልዑል እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። እውነት የፈጣሪ የባሕርይው ነው። ቅዱሳን ሁሉ እውነተኞች (ጻድቃን) ናቸው። እውነትን በመናገርህ ምክንያት የሚደርስብህ መከራ ካለ በደስታ ተቀበለው የትእግስትን ዋጋ ያሰጥሀልና። ውሸት ተናግረህ ከብረህ ከሆነም ውሸትህ መታወቁ አይቀርምና ፍራ። እውነትን የያዘ ሰው አይፈራም። እውነት እግዚአብሔር ነው። እውነት እንደ እግዚአብሔር ሕግ መኖር ነው። ውሸት የሰይጣን ገንዘቡ ስለሆነ እንመልስለት። የተወሻሻችሁ እጮኛሞች ካላችሁ እውነታው ሲታወቅ እንዳታፍሩ ወይም ግንኙነታችሁ እንዳይቋረጥ። በእውነት ተነጋገሩ። እጮኛሞች መዋደድ ካለባቸው በእውነተኛ ማንነታቸው ተዋውቀው መሆን አለበት። ከአሥሩ ሕግጋት አንዱ "በባልንጀራሕ ላይ በሐሰት አትመስክር" የሚለው ነው። ምሥጢሩ አትዋሽ ማለት ነው። ሰው ለምን ይዋሻል? ሰይጣን መከበርን ፈልጎ ያልሆነውን ማንነት አምላክ ነኝ ብሎ ተዋረደ። በሌለን ማንነት ለመከበር ስንል ለምን እንዋሻለን?! አንዳንዱ ለሥጋዊ ጥቅም ሲል ውሸት ይናገራል። ይህም ሚችነትን ካለማስታወስ የሚመጣ በደል ነው። ውሸት እያደር ያቀላል። እውነት ግን ሁልጊዜም ያስከብራል።

ኑ እውነት እውነቷን እንነጋገር

ኑ ጽድቅ ጽድቋን እንነጋገር።

ትሕትናና ትዕቢት

እግዚአብሔር በቸርነቱ ለክብር ፈጥሮናል። እኛ የተገባን ሆነን ሳይሆን እርሱ ሰውን ወዳጅ ስለሆነ ጸጋን አጎናጸፈን። ስለዚህ ያለን ጸጋ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው። ይህ ከሆነን የግላችን የሆነ ነገር እና ከሌላ ያልተቀበልነው ነገር ስለሌለን የምንመካበት የምንኮራበት ሌላ ነገር አይኖርም። ያለንን ሁሉ በሰጠን በእግዚአብሔር እንመካለን እንጂ። በጥበባችን እንዳንመካ ጥበብን የሰጠን እግዚአብሔር ነው። በሀብታችን እንዳንመካ ለተቸገሩ መጽውተን ክብርን እንድናገኝበት ሀብትን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው። በኃይላችን እንዳንመካ ኃይላችን ከፈጣሪ በጸጋ የተሰጠን ነው። በውበታችን እንዳንመካ ፈጣሪ ፈቅዶ የሰጠን እንጂ እኛ አስተያየት

ሰጥተን አልተፈጠርንም። ስለዚህ ኑ እንደ ሳሙኤል እናት እንደ ሐና "ኢይትመካህ ጠቢብ በጥበቡ፣ ኢይትመካህ ባዕል በባዕሉ ወኢይትመካህ ኃያል በኃይሉ። ዘሰ ይትሜካህ በዝ ለይትመካህ በአእምሮ ወበለብዎ እግዚአብሔር" እንበል። ልንመካበት የሚገባን ሁሉን ለእኛ ጥቅም በሰጠን በእግዚአብሔር ነው። ትዕቢት የእግዚአብሔርን የቸርነት ሥራ ካለማስተዋል የሚመጣ ደዌ ነው። ሳጥናኤልን ፈጥሮ ከሁሉ በላይ አድርጎ ሾሞት ነበር። ነገር ግን በተሰጠው ማመስገን ሲገባው ያልተሰጠውን በመሻት ከልእልናው ወደቀ። ነቢዩም "እፎ ወድቀ ኮከበ ጽባሕ" ብሎ ይደነቃል። ትዕቢት ውስንነትን እና ማንነትን ካለመረዳት የሚመጣ በሽታ ነው። እኛ ያልነበርንበት ጊዜ ነበር። ነገር ግን ፈጣሪ ከሌሎች ፍጥረታት አክብሮ ወደ መኖር አመጣን። በዚች ምድር ከጽንሰት እስከ ሞት እንኖራለን። ሞት ያለብን ሰዎች ምን ሊያስታብየን ይችላል? ሚች ሰው ለምን ይኮራል? አገባብስ መዋቲነትን ተረድቶ ራሳችንን ዝቅ አድርገን ለክብር ለፈጠረን ጌታ ምስጋና እናቅርብ። በቸርነቱ ኃጢኣታችንን ይቅር እንዲለን በተሰበረ ልብ ሆነን እንለምነው። እስኪ ኃጢኣት ያልሠራ ማን ነው? ሐሜት በደል እንደሆነ ነግሮናል። እስኪ ያላማ ማን ነው? ስድብ፣ ውሸት እና ፌዝ፣ ቀልድ ኃጢኣት ነው። በዚህ ያልበደለ ይኖር ይሆን። ይህስ ይቅር በሀሳቡ ያልበደለ ሰውስ ይኖር ይሆን? ነገር ግን ፍጹም ቸርና መሐሪ የሆነው እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነውና ንሥሓ ገብተን በቸርነቱ እንዲምረን ፈቃዱ ይሁንልን። የሁሉም ሰው ኃጢኣት በግንባሩ የሚጻፍ ቢሆን ኖሮ በትእቢት የሚራመድ በትእቢት የሚናገር ሰው ይኖር ነበር ይሆን? እንደኔ ይኖር አይመስለኝም። እንዲያውም የሠራት አሳፋሪ ኃጢኣት እንዳትታወቅበት ከቤት አይወጣም ነበር። እግዚአብሔር ግን ሕሊናን ዳኛ አድርጎ ፈጥሮ እኛ በሁሉ ፊት እንዳናፍር በንሥሓ አባታችን አማካኝነት በደላችንን ተናግረን እንዲሠረዝልን አደረገን። አንተ ትምክህተኛ አንተ ትእቢተኛ አንተም የምትመካበትም ኃላፊ መሆኑን አላወቅክምን? የቅዱሳን ትምክህት በማያልፈው ይልቁንም ሁሉንም በሚያሳልፈው በእግዚአብሔር ነው። ስለሌላው የምናውቀው እውቀት ሙሉ ስላልሆነ በማንኛውም ሰው ፊት ራሳችንን ዝቅ አድርገን በትሕትና እንኑር። በግምት እና በመሰለኝ ልናወራ አይገባም። አጥርተን በማናውቀው ጉዳይ ዝምታን እንምረጥ። የምናውቀው ነገር እንኳ ቢሆን ለሰሚው ጥቅም ካልሰጠ ዝም እንበል። ይልቅስ በብዙ ረገድ ደካማ መሆናችንን ተረድተን በሁሉ እግዚአብሔር እንዲረዳን ረድኤተ እግዚአብሔርን እንጠይቅ። በበደል ያሳለፍነው ዘመን ከአሁን ጀምሮ ይብቃን። በንሥሓ አዲስ ሕይወት እንጀምር።

ፍቅርና ጥላቻ

ፍቅር የግእዝ ቃል ነው። ትርጉሙ የልብ ስምምነት በልብ መዋደድ ማለት ነው። አንድ ሰው አንድን ነገር ወደደ ማለት ያ ነገር ለልቡናው ተስማሚ ወይም ምቾት የሚሰጥ ነው ማለት ነው። አንድ ሰው ለአንድ ነገር ጥላቻ አለው ማለት ደግሞ በሁለቱ መካከል የንግግር ወይም የሀሳብ አለመስማማት አለ ማለት ነው። አንድ ሰው ፍቅረ እግዚአብሔር አለው የሚባለው ሀሳቡ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ጋር የተስማማ ሲሆን ነው። አንድ ሰው ፍቅረ ቢጽ (ሰውን ሁሉ መውደድ) አለው ማለት ደግሞ ከሰዎች ጋር በስምምነት በመዋደድ መኖር ሲችል ነው። ፍቅር የደስታ መሠረት፣ የአንድነት ምሰሶ ነው። ፍቅር ያለው ሰው ዓለምን የሚያይበት እይታ ልዩ ነው። በዚህ ምድር ሲኖር አይሰለችም። ፍቅር ያለው ሰው በእርሱ ሊደረግበት የማይፈልገውን

ነገር በሌሎች እንዲደረግ አይፈልግም። የሌሎች ሕመም ሕመሙ ነው። የሌሎች ደስታ ደስታው ነው። ፍቅር ያለው ሰው የተጎዳ ሰው ሲያይ ራሱ እንደተጎዳ አድርጎ በመቁጠር የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ፍቅር ያለው ሰው ለእርሱ ሊደረግለት የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ለሌላው እንዲደረግ ይፈልጋል። ራስ ወዳድነት የለበትም። ብቻውን ጸጋና በረከት ማግኘት አይፈልግም። የአንድነት ስሜቱ የጠነከረ ነው። ፍቅር ያለው ሰው ብቻውን መጽደቅ ብቻውን መሰልጠን ብቻውን መበልጸግ አይፈልግም። ሰው ሁሉ እንዲጸድቅ እንዲሠለጥን እንዲበለጽግ ይፈልጋል እንጂ። ፍቅር ለሌላው ምቾት ራስን አሳልፎ መስጠት ነው። ጌታችን ሲያስተምር መልካም እረኛ ራሱን ስለበጎቹ አሳልፎ ይሰጣል እንዳለ። ለበጎቹ ፍቅር ያለው መምህር ወይም ቄስ ራሱን ለበጎቹ አሳልፎ ይሰጣል። በፍቅር ውስጥ ትእቢት የለም። በፍቅር ውስጥ ፉክክር የለም። በፍቅር ውስጥ ከንቱ ውዳሴ የለም። በፍቅር ውስጥ መሰዳደብ የለም። የፍቅር መገለጫው መከባበር መተሳሰብ መተዛዘን ነው። ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ነው። ፍቅር ያለው ሰው በሌሎች ውድቀት አይደሰትም። ሌላውን ሰው እንደራሱ አድርጎ ስለሚወድ የሌሎችን ውድቀት እንደራሱ ውድቀት በማሰብ ያዝናል እንጂ። ፍቅር ያለው ሰው በሌሎች ሰዎች አይቀናም። ምክንያቱም ሌሎችንም እንደራሱ አድርጎ ስለሚወድ የእነርሱ ስኬት የእርሱ ስኬት እንደሆነ በማሰብ ይደሰታል እንጂ። ፍቅር ያለው ሰው ባልንጀራው የማይወደውን ነገር አያደርግም። ስለባልንጀራው ሲል የራሱን ፈቃድ ይሠዋል እንጂ። ፍቅር ያለው ሰው ሌሎች ሰዎች ታላቅ በደል በድለው ሲያይ ንሥሓን ይመኝላቸዋል። ፍቅር ያለው ሰው ለሰዎች ሁሉ ይራራል። ፍቅር መሥዋዕትነት አለበት። ጌታችን ፍቅርን በመስቀል ተሰቅሎ ገለጠው። በደለኛው አዳምን ለማዳን ምንም በደል ሳይኖርበት ስለአዳም በመስቀል ተሰቅሎ አዳምን ነጻ አወጣው። ፍቅር እስከዚህ ነው። ለዚያ ነው ሊቁ ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት። ኃያል ወልድን ለሰው ልጅ ያለው ፍቅሩ ሰው እንዲሆን አደረገው። ሰው ሆኖም በመስቀል ተሰቅሎ አዳምን አዳነው። ቅዱስ ያሬድ ንጹም ጾመ ወናፍቅር ቢጸነ ወንትፋቀር በበይናቲነ ብሏል። ጾምን እንጹም ባልንጀራችንን እንውደድ እርስበራሳችን እንዋደድ ብሏል። ጌታችንም ተፋቀሩ በበይናቲክሙ በከመ አነ አፍቀርኩክሙ እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ ብሏል።

ምስጋናና ጸሎት

ከፈጣሪያችን ውጭ እኛን አጥርቶ የሚያውቀን የለም። ስለዚህም ለእኛ ሰውነት የሚጠቅመውን እና የሚጎዳውን በትክክል የሚያውቀው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ለዚያ ነው እያንዳንዱ ያዘዘን ትእዛዛቱ እኛን ከብዙ አእምሯዊ እና አካላዊ ችግሮች እንዲሁም እሱ ባወቀ ከብዙ ችግሮች በትእዛዛቱ እንድንድንባቸው ነው። እኛ ትእዛዙን በመፈጸማችን እርሱ የሚጨመርለት እና የሚያገኘው ልዩ ጥቅም የለም። ሕግ የተሰራው ለእኛ ጥቅም ሲባል ለእኛ ነው። ሕጉ ለኑሯችን አስተማማኝ መንገድ ነው። ፈጥሮ ያልተወን፣ ለፍጥረታችን የሚስማማ ሥር ዐትንና ሕግን የሰጠንን ፈጣሪ ሁልጊዜ ከማመስገን ውጭ ምን እንላለን። ከሐዋርያው ጋር "ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን" እንበል እንጂ። ፈጣሪ ከፍቅሩ የተነሳ ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር እንድንነጋገር ሥ ር ዐት ሠራልን። ጸሎት ብሂል ተናግሮተ ሰብእ ምስለ እግዚአብሔር ጸሎት ማለት የሰው ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው ተብሏል። እርሱም አባታችን ነውና

የምንፈልገውን መልካም ነገር ሁሉ ሄደን በፍቅር እንጠይቀዋለን። እርሱም ለእኛ የሚጠቅመንን ይሰጠናል። ምግብን ብንበላው የምንጠቀመው እኛ ነን እንጂ ምግቡ አይደለም። እግዚአብሔርን ብናመሰግነው የምንጠቀመው እኛ ነን እንጂ እግዚአብሔርስ የሚያገኘው ያልነበረው ነገር የለም። እኛ እንድንጠቀም ክርስቶስ ሥጋየን ብሉ ደሜን ጠጡ አለን። ለእኛ ጥቅም ብሎ ሥጋውን ደሙን ሰጠን። ታድያ ይህንን ነገር ሁልጊዜ ካሰብነው "ስቡሕ ውዱስ ቅዱስ" እያልን ብናመሰግን ራሱ ልባችን መች ይረካል?!። በእርግጥ ቅዱሳን መላእክትም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ሲያመሰግኑት "15 ደቂቃ የቆዩ አይመስላቸውም" ይላል። ማንኛውም ክርስቲያን ቢያንስ በቀን ሰባት ጊዜ መጸለይ አለበት። እኒህም ጠዋት 12 ሰዓት፣ በ3 ሰዓት፣ በ6 ሰዓት፣ በ9 ሰዓት፣ በ12 ሰዓት፣ ከምሽቱ በ3 ሰዓት፣ ሌሊት 6 ሰዓት ናቸው። በእነዚህ ሰዓታት ቢያንስ አቡነ ዘበሰማያትን እንድገም። ከቻልን ጠዋት ውዳሴ ማርያሙን መዝሙረ ዳዊቱን እንድገም። በሉ ኑ ይትባረክ እግዚአብሔር ዘፈጠረ ኪያነ ከመ ናምልኮ። እናመልከው ዘንድ እኛን የፈጠረ እግዚአብሔር ይመስገን እያልን እናመስግነው። በጸሎት ውስጥ ምሥጋና አለ ልመናም አለ። አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ ብለን ምስጋናን አቅርበን የእለት እንጀራችንን ስጠን ብለን ደግሞ ልመናን እናቀርባለን። እርሱም የእኛን ፈቃድ አይቶና ሰምቶ ልመናችንን ይቀበልልናል። አስቀድሞ ፈቃዳችንን የሚያውቅ ቢሆንም ነገር ግን ጌታችን የነጻነት አምላክ ስለሆነ እኛ ፈቅደን ስንጠራው ነው ጸጋውን የሚያድለን። ለዚያኮ ነው መጻጉእን ልትድን ትወዳለህን? ብሎ የጠየቀው። ሊድን እንደሚወድ እያወቀ የጠየቀውኮ የነጻነት አምላክ ስለሆነ ነው። የባሕርይ ምስጋና የሚገባው ልዑል እግዚአብሔር ነው። ከንቱ ውዳሴን እና ተርእዮን መፈለግ ግን ለእግዚአብሔር የሚገባውን ምስጋና የግድ ለእኛ ለማድረግ የምንሮጥ አሳዛኝ ሰዎች እንሆናለን። ሰዎች ባለማወቅ ቢያመሰግኑንም ቢያሞግሱንም ያንን ምስጋና ግን ምስጋናው ለሚገባው ለእግዚአብሔር እንመልስለት።

በእንተ ንሥሓ ስለ ንሥሓ

የእግዚአብሔር ቸርነቱ ምን ይደንቅ! ለሰው ያለው ፍቅርስ ምን ይረቅ! እፀበለስን በልተን ኃጢዓት ሠርተን ብንበድለው እርሱ ግን በመስቀል ተሰቅሎ ወደ ቀደመው ቦታችን መለሰን። ጴጥሮስም ይሁዳም ጌታችንን በድለውታል። ነገር ግን ጴጥሮስ ንሥሓ በመግባቱ በኋላ ዕቀብ አባግዕየ በጎቼን ጠብቅ ተብሎ ፓትርያርክነት ተሾመ። ንሥሓ ወደ ታላቅ መዓርግ ታሳድጋለች። ይሁዳ ግን ንሥሓ ስላልገባ የክፉ አብነት ሆኖ ሲጠቀስ ይኖራል። የይሁዳ ነገር ግን ሁልጊዜም ግርም ያደርገኛል። ይሁዳ ማለት የስሙ ትርጓሜ ታማኝ ማለት ነው። ነገር ግን ይሁዳ ጌታውን የከዳ ነበር። ታማኝ ተብሎ ከሃዲ ሰው ነበር። እኛም ክርስቲያን ተብለን ግን ክርስቶስ ያዘዘንን ካልሠራን ያው እንደ ይሁዳ ሆንን ማለት ነው። በእርግጥ ብዙዎች በመልካም ስም ጭምብል ውስጠ ተግባራቸው ግን ክፉ የሆኑ አሉ። ውይ የእኔ ነገር ወደ ንሥሓ ልመለስ። ዳዊት ኦርዮንን አስገደለ። ከሌላ ሰው ሚስት ጋር አመነዘረ። ነገር ግን በኋላ ጥፋቱን አምኖ በመጸጸቱ ጌታችንም ልበ አምላክ አለው። ንሥሓ ስንገባ ከዚህ ቀደም የሰራነው በደል ይሰረዝልናል። ነገር ግን ገደል ወድቄ ከዚያ እታከማለሁ ብለን ከገደል እንደማንወድቅ ሁሉ መቼም ንሥሓ እገባለሁ ብለን ኃጢኣትን እንዳንሠራ እንጠንቀቅ። በዚያው ኃጢኣት እየሰራን እያለ መሞትም አለና። አዳም እፀበለስን መብላቱ ትልቅ በደል ነበር። ነገር ግን ይህንን

ክፉ አጋጣሚ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ በመስቀል ተሰቅሎ ለሰው ያለውን ፍቅሩን በመግለጥ ወደመልካም ነገር ቀይሮለታል። ክፉ ሊደርስብን ይችላል። ብንችል ከዚያ ክፉ ነገር እንዴት መራቅ እንዳለብን እናስብ። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ መከራን ባለመሰቀቅ የነበረውን ክፉውን ነገር ወደመልካም አጋጣሚ መለወጥ እንችላለን። ንሥሓ የበደለውን እንዳልበደለ ዘማዊውን ድንግል

ታደርጋለች። ንሥሓስ ትሬስዮ ለዘአበሰ ከመ ዘኢአበሰ ወለዘማዊ ድንግለ እንዲል። አስተውልልኝማ ወንድማለም። ዘማዊውን ድንግል ታደርገዋለች ያለው የነፍስን ድንግልና ማለቱ እንጂ የሥጋ ድንግልናን ማለቱ አይደለም። ንሥሓ ብትገባም የሥጋ ድንግልናህ አይመለስም። ወጣቶች ድንግልናችሁን ጠብቁ። የሚያገባችሁ ሰው ከነክብራችሁ ሊያገኛችሁ ይገባል። ነገር ግን ደግሞ ቀን ጥሎን ሥጋዊ ፈቃድ አሸንፎን የበደልን ሰዎች እግዚአብሔር መሓሪ ነውና ንሥሓ እንግባና ለወደፊቱ እንጠበቅ። በሉ ኑ ንሥሓ እንግባ። ጌታችን በኢሳይያስ አድሮ ኃጢኣታችሁ እንደ አለላ ብትቀላ በንሥሓ እንደ ባዘቶ ትነጣለች ብሎናል። እንደምታውቁት አለላ ቀይ። ኃጢኣት አቅልቶን ቢሆን ንሥሓ ብንገባ ኃጢኣታችን ተፍቆ እንደ ባዘቶ እንነጣለን ማለት ንጹሕ እንሆናለን። ቆይ ግን መቼ ነው ንሥሓ መግባት የፈለግከው? ለምን ለሌላ ቀን ታቅዳለህ። ዛሬ ሌደህ ንሥሓ ገብተህ አትነጻምን? ምናልባት ዛሬ የምትሞት ብትሆንስ? እኮ የምትሞትበትን ጊዜ አታውቀውምና ንሥሓ ገብተህ መልካም ሥራ እየሰራህ እለተ ሞትህን ጠብቅ።

ስለምጽዋት

ሲጀምር በሥጋም በነፍስም የማንጠቀምበትን ነገር ጌታ አያዝዘንም። ያዘዘን ነገር ሁሉ እኛን በሥጋም በነፍስም ክቡራን እንድንሆን የሚያደርግ ነው። ያዘዘን ትእዛዞች ሁሉ እኛን ለሕይወታችን ክፉ ከሆኑ ነገሮች የሚያድኑን ነገሮች ናቸው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኃጥዓን ሊፈርድባቸው ለጻድቃን ሊፈርድላቸው በሚመጣበት ጊዜ በዋናነት የሚጠይቀው ጥያቄ አንቀጸ ምጽዋትን የያዘ ነው። እኒህም በስድስት መልኩ ይደረጋሉ። ማቴ.25፥35-36

- ተርቤ አብልታችሁኛል
- 2) ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል
- 3) እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል
- 4) ታርገፔ አልብሳችሁኛል
- 5) ታምሜ ጎብኝታችሁኛል
- 6) ታስሬ ጠይቃችሁኛል

መቼም ለጌታችን ከትንሳኤ በኋላ ተራበ ተጠማ ተብሎ አይነገርለትም። ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስንም የሐዋ.ሥራ.9፣4 ለምን ታሳድደኛለህ ብሎታል። ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ለክርስቲያኖችን አባታችን ስለሆነ እኛም አካሉ ስለሆንን ለምን ታሳድደኛለህ ብሎታል። ስለዚህ

የታመመ የታረዘ የተጠማ የታሰረ የተራበ ሰው ስናይ ቸል ማለት የለብንም። እርሱን መርዳት ለእኛ የአእምሮ እረፍት ከመሆኑ በተጨማሪ ሰማያዊ ዋጋ የሚያሰጠንም መሆኑ ነው። የተጠየቅነው ማድረግ የምንችለውን ነገር እንጂ ከአቅማችን በላይ የሆነውን አይደለም። የታመመን መጎብኘት የታሰረን መጠየቅ ለሁሉም ሰው ከባድ አይደለምና። እንግዳን መቀበል የሚቸግር አይደለምና። ቢቻልማ እንግዳ ሲመጣ እግሩን አጥበን፣ ቤት የእግዚአብሔር ነው ብለን ሳይሸማቀቅ በነጻነት እንዲያድር ልናደርገው ይገባል። የታመመን መጠየቅስ ቢሆን የሰው ልጅ ታማሚ መሆኑን ኃላፊ መሆኑን የምናስታውስበትኮ ነው። እግዚአብሔር ይማርሕ። አይዞህ እኛ እያለን ስለሌላ ነገር አታስብ ማለት ይገባል። ይህንን በማድረጋችን እኛ በረከት እናገኛለን እንጂ ምንም የምናጎድለው ነገር የለም። የተጠማ ማጠጣትስ ቢሆን ውሃን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። ውሃን ሁላችንም እናገኘዋለን። ስለዚህ የተጠማን ማጠጣትም ለእኛ ክብር ለመስጠት ሲፈልግ ያዘዘን ቀላል ትእዛዝ ነው። የታሠረን መጠየቅስ ምን የሚከብድ ነገር አለው። ምክንያቱም ከሥር ቤት ሄዶ እግዚአብሔር ያስፈታህ ማለት ምኑ ይከብዳል። ለታሳሪው ግን ትልቅ ትርጉም ነው። ጠያቂ ስላገኘ ደስ ይለዋል። ተርቤ አብልታችሁኛል ያለው ሕግም ቢሆን ቀላል ነው። ምክንያቱም ጌታችን ሠርተን እንድንኖር እርሱ በጋ እና ክረምትን እያፈራረቀ ካፈራልን ፍሬ ለእኛ በመሠረታዊነት የሚያስፈልገንን ይዘን ከዚያ ውጪ ያለውን ለነዳያን ለተቸገሩ እንድንሰጥ ነው የታዘዝነው። ስለዚህ ይህም ቀላል ነገር ነው። እግዚአብሔር ነዳያንን ወይም የተቸገሩትን መመገብ አቅቶት አይደለም። ነገር ግን እኛ እነርሱን መግበናቸው በረከት እንድናገኝ የተሰጠን የፍቅር ሕግ ነው። የታረዘን ማልበስም እንዲሁ ነው። ሌላው ሰው ፀሐይ መጥቶት ሙቀትና ቅዝቃዜ ተፈራርቆበት እንዳይሞት ልብስ ገዝተን መስጠት ነው። እኒህ ነገሮች ሁሉ ቀላል የሆኑበት ምክንያት ነዳያን ጥቂቶች መካከለኛ ሕይወት ያለው ሰው ብዙ ስለሆነ ሁሉም ለተቸገረ ቢረዳ ኑሮ ሀገሩ ሰላም በሆነ ነበር። ነገር ግን ብዙው ሰው ባይመጸውትም አንተ ግን የምትችለውን እርዳታ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው አድርግ። ጌታችን ማድረግ የምንችለውን እንጂ ማድረግ የማንችለውን አላዘዘንምና። ፍትሐ ነገሥት 16 ምጽዋት አምላክን የምታስመስል ታላቅ ሥራ መሆኗን ይገልጻል። ምጽዋት ከአሥሩ ሕግጋት አንዱ የሆነውን ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚለውን ቃል በተግባር የምታሳይ ደገኛ ሕግ ናት።

ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት

=> በ1197 ዓ.ም ታኅሣሥ 24 ቀን ተወለዱ

=> የክርስትና ስማቸው ፍሥሓጽዮን ነው።

=> ጻድቁ የተወለዱበት ቦታ ቡልጋ (ጽላልሽ) ነው።

=> የተጋድሎ ቦታቸው ደብረ ሊባኖስ ነው።

=> በተወለዱ በሦስተኛ ቀናቸው አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ በአካላዊ ግብሩ ወላዲ አሥራጺ በተለየ ባልተለየ ከዊኑ ልብ የሆነው አብ ልዩ ጽኑ ቅዱስ ነው። በአካላዊ ግብሩ ተወላዲ በተለየ ባልተለየ ከዊኑ ቃል የሆነው ወልድ ልዩ ጽኑ ቅዱስ ነው። በአካላዊ ግብሩ ሠራጺ በተለየ ባልተለየ ከዊኑ እስትንፋስ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ልዩ

ጽኑ ቅዱስ ነው ብለው አመሰገኑ። የዛሬው በዓል ዋናው ኃይለ ቃል ይህ ነው። ምሥጋናን መሠረት ያደረገ ነው። ማኅሌቱም ይህንን መሠረት አድርጎ <<ከሠተ አፉሁ ወልሳኑ ነበበ አእኮቶ ወባረኮ ለእግዚአብሔር መልአ መንፈስ ቅዱስ ላእለ ተክለሃይማኖት>> ይላል። ጸጋ መንፈስቅዱስ በተክለ ሃይማኖት ላይ መላ። ተክለ ሃይማኖትም ነገር ጀመረ በአንደበቱም ተነገረ። እግዚአብሔርንም ፈጽሞ አመሰገነው እንዲል። የተወለድነው የተፈጠርነው እግዚአብሔርን አመስግነን በደስታ እንድንኖር ነው። እግዚአብሔርን በማመስገናችን ለእግዚአብሔር የሚጨመርለት ምንም ነገር የለም። እኛ ብንመሰገን ሙገሣው ክብሩ ሊያስደስተን ይችል ይሆናል። እግዚአብሔርን ግን እኛ ስላመሰገንነው ምንም ለእርሱ የሚጨምርለት ነገር የለም። ባናመሰግነውም በእርሱ ምንም አይጎድልበትም። ነገር ግን እኛ እግዚአብሔርን ባናመሰግነው ብዙ ነገር ይጎድልብናል። ክብር እናጣለን ክብረ ቢስ እንሆናለን። ይህ ብቻ ሳይሆን ወራዳ እንሆናለን። ሰይጣን ከነበረበት ክብር ወርዶ በመከራ ቦታ የሚማቅቀውኮ ከክህደቱ በተጨማሪ ከዋክብት በተፈጠሩ ጊዜ ወአመ ተፈጥሩ ከዋክብትየ ሰብሑኒ መላእክትየ እንዲል መላእክት የከዋክብት ፈጣሪ የሆነውን እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ እርሱ ግን አላመሰግንም በማለቱ ነው። ካለመኖር አምጥቶ የፈጠረን፣ ከእናት ከአባት እንድንወለድ ያደረገን፣ በቸርነቱ ከእናታችን ጡት ወተትን አዘጋጅቶ ያንን እየመገበ የሚያሳድገን፣ ለመኖር የሚያስፈልገንን ተፈጥሮን የሰጠን፣ ነጻነታችንን ተጠቅመን ከክብራችን በወረድን ጊዜ እርሱ ራቁቱን በመስቀል ተሰቅሎ ወደ ቀደመ ክብራችን የመለሰንን፣ ብንበድል ንሥሓ እንድንገባ ንሥሓን የሰጠን፣ ሥጋውን ደሙን በልተን ጠጥተን የዘላለም ሕይወት እንድናገኝ የፈቀደልን ልዑል እግዚአብሔርን በደስታ ማመስገን ይገባል። ኑ በቸርነቱ ያከበረንን እግዚአብሔርን ሕጉን ትእዛዙን እየጠበቅን እናመስግነው።

ልደት

ሃይ.አበ ዘቅዱስ ኤፍሬም "ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው እርሱም እናቱን ፈጠረ"። ልደት ማለት መወለድ ማለት ነው። የልደት በዓል ከጌታችን ዐበይት በዓላት አንዱ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ታኅሣሥ 29 ቀን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በበረት ተወለደ። እግዚአብሔር አዳምን በልጅነት አክብሮ ጸጋን አጎናጽፎ ፈጥሮት ነበር። አዳም ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፉ በራሱ ላይ ሞትን አመጣ። ነገር ግን አዳም በበደሉ ተጸጽቶ ንሥሓ ቢገባ መሐሪና ይቅር ባይ እግዚአብሔር ከ5500 ዓመት በኋላ ከልጅ ልጁ ተወልዶ እንደሚያድነው ቃል ኪዳን ሰጠው። ገላ.4፣4 "ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ" እንዲል በቀጠሮው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ። በጨለማ ይኖር የነበረ ዓለም ብርሃን ተወለደለት። ኖሎት ከመላእክት ጋር ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ እያሉ አመሰገኑ። ሰብአ ሰገል ከሩቅ መጥተው ወርቅ እጣን ከርቤ ገበሩለት። የሰው ልጅ ደስታ የሚሆን ጌታ ተወለደልን። በበረት ተኛ በጨርቅም ተጠቀለለ። የማይታየው ቃል የማይታይነቱን ሳይለቅ ሥጋን ገንዘቡ በማድረጉ በሥጋው ታየ።

ቅድስት ሥላሴ

ዓለማትን ፈጥሮ የሚያስተዳድር፣ መንግሥቱ ዘለዓለም የሆነ፣ መለወጥ የሌለበት፣ በአካል ሦስት በባሕርይ አንድ የሆነ እግዚአብሔር፣ ለእኛ መኖር፣ ለእኛ መወለድ፣ ለተፈጥሮ መኖር ምክንያት የሆነ እግዚአብሔር ክቡር ነው። ምስጉን ነው። ኩሉ ይሰግድ ለሥላሴ ለሥላሴ ኩሉ ይሰግድ። ወይትቀነይ ኩሉ ለመንግሥተ ሥላሴ ሥላሴ ኩሉ ይትቀነይ። ሁሉ ለሥላሴ ይሰግዳል። ሁሉም ለሥላሴ ይገዛል። በሉ ኑ እግዚአብሔርን እናመስግን። እኛን ካለመኖር ለክብር የፈጠረን። በጸጋ ልጆቹ የደረገንን ፈጣሪ ኑ እናመስግነው።

ራስን መሆን

ትላንት የሆነች ልጅ ናት ከእርሷ የሚበልጥ ልጅ ታቅፋ አየኋትና ምክር ለመለገስ ብየ "ከአንቺ የሚበልጥ ትልቅ ልጅ ለምን ትታቀፊያለሽ!? በእግሩ ይሂድ አንቺም አትድከሚ አልኳት"። እርሷ የመለሰችልኝ መልስ ግን "ማቀፍ ደስ ስለሚለኝ ነው" የሚል ነበር። እኔም ውይ ነው እንዴ ይሁን ብየ ዝም አልኩ። በኋላ ግን ነገሩ ገርሞኝ ሳብሰለስለው ሳብሰለስለው ቆየሁ። ልጅቱ ምን ዓይነት ሞኝ ናት በከንቱ ለምን ትደክማለች? አልኩ። ምርመራየን ቀጠልኩ። ይህችን ምክንያት አድርጌ የማያሰላስለውን መንጋውን መገሥጥ ፈለኩ። በነገራችን ላይ አንዳንዱ መንጋ ባሕታዊ መሳይ አጭበርባሪን የታቀፈ ነው። አንዳንዱ አክቲቪስት መሳይ ሰባኪ ነኝ ባይን የታቀፈ ነው። አንዳንዱ በየትኛውም የቤተክርስቲያን ሙያ ሳይመረቅ በግብረንዲቁናዋ ብቻ "መምህር" ሲሉት እርሱም ደስ ብሎት የሚያጭበረብርን ሰው የታቀፈ ነው። አንዳንዱ በሰባኪ ሥም ጧፍ የሚነግዱ ሰዎችን የታቀፈ ነው። ያች ልጅ ያን ልጅ በመታቀፏ ብዙ መጓዝ እና መፍጠን ሌላም ታላቅ ሥራ መሥራት እየቻለች። ራሷን በራሷ አደከመች። ያ ልጅኮ በራሱ መራመድ የሚችል ብቻ ሳይሆን ከእርሷም የበለጠ መፍጠን የሚችል ልጅ ነው። ግን እርሱም እምቢ ብሎ በራሱ መፍጠን እየቻለ እርሷም እርሱን አውርዳ መፍጠን እየቻለች ሁለቱም ማዝገምን ፈልጉ። መንጋው እንዲህ ነው። ለሆነ ሰባኪ ወይም ለሆነ ዲያቆን ወይም ለሆነ ባሕታዊ መሳይ አጭበርባሪ መንጋና እና ደጋፊ ከሚሆን እኒህን ሁሉ ትቶ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ቢከተል ብዙ መፍጠን ይችል ነበር። እነዚያ በሰው ጭብጨባ የደነዘዙ ሰባክያን ዲያቆናት እና ባሕታውያን መሳይ አጭቤዎችም ራሳቸውን እንዲያዩና ከከንቱ ውዳሴ ወጥተው በትሕትና እንዲኖሩ ያደርጋቸው ነበር። ምእመኑን ወደ ክርስቶስ ያቀርቡ ነበር እንጂ ወደራሳቸው አያቀርቡም ነበር። አንዳንዱማ ክርስቶስን ደስ እንዲለው ሼር አድርጉልኝ ይልሃል። ቆይ ከመቼ ጀምሮ ነው በfacebook ሼር ክርስቶስ መደሰት የጀመረው?! ነፍሴ ሐሴት እንድታደርግ ሼር አድርጉልኝ የሚሉም ነበሩ። በዚህ ሰሞን ደግሞ የስልካችሁ መጥሪያ የእኔ መዝሙር እንዲሆንልዎት ከፈለጉ 822 ምናምን ምናምን ይደውሉ የሚሉ ኃፍረት ያልፈጠረባቸው ሰዎች ሁሉ አሉ። ቆይ በስንቱ እንፈር ግን?! እንዳንፈጥን አንቀው የያዙንን ነገሮች በሙሉ እናራግፋቸው። ራሳችንን እስካልሆንን ድረስ መከራችን ይቀጥላል። ሌላው ሲጮህ የምንጮህ ሌላው ሲገረም የምንገረም ሌላው ሲስቅ የምንስቅ ከሆነ አደጋ አለው። እግዚአብሔር በነጻነት እንድናስብ አእምሮን ሰጥቶናል። ፈጣሪ የሰጠንን አእምሮ ለማንም አሳልፈን አንስጥ። ራሳችንን ችለን እናስብ። የታቀፍናቸውን ሸክሞች እናራግፍና እንፍጠን።

የዘረኝነት የዘር ሐረግ

ዲያብሎስ ራስ ወዳድነትን ከልቡ ራሱ አስገኛት። ከራስ ወዳድነትም ከንቱ ውዳሴን ይወልዳል። ከንቱ ውዳሴ ቅንዓትና ምቀኝነትን ትወልዳለች። ቅንዐት ጥላቻን ትወልዳለች። ጥላቻ ስድብን ትወልዳለች። ስድብ ቁጣን ትወልዳለች። ቁጣ ጠብን ትወልዳለች። ጠብ ሞትን ትወልዳለች። ሞት የሞት ሞትን ትወልዳለች። የሞት ሞት ዘላለማዊ ስቃይን ትወልዳለች። የዘላለማዊ ስቃይ አገሯ ገሐነም ነው።

ዋዜማ ቅኔ 17/05/2014 ዓ.ም

ለብእሴ ዓለም ጊዮርጊስ

ሐዋዘ ኩሉ ይብላሁ አቀጽለ ይድራስ አንስት።

ይጸዋዕ በላእለ ዚኣነ ስምከ ብሉት።

በሳምናዊት ዘመን አምጣነ አልቦ ተባዕት።

ወንሁብ ለከ ጦማረ ጸሐፍት።

እንዘ አንተ ትሄሉ በሞት።

ምሥጢሩ በስምንተኛው ሺ ብዙ ሴቶች አንዱን ወንድ አግባን ምግባችንን እኛ እንችላለን ስምህ ብቻ በእኛ ላይ ይጠራ ይላሉ የሚለውን የነቢዩን ቃል ይገፍ ቅዱስ ጊዮርጊስ አጥንቱ ተፈጭቶ በደብረ ይድራስ በተበተነ ጊዜ በዚያ ያሉ ቅጠሎች

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕቱ ለክርስቶስ

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕቱ ለክርስቶስ

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕቱ ለክርስቶስ

የሚል ተጽፎ ተገኝቶባቸዋል። ያን ለማስታወስ ነው።

ድንግል ማርያም

ጊዜ እረፍታ ለማርያም ጊዜ ጊዜ ጊዜ እረፍታ ለማርያም። ወረደ ወልድ ዲበ እምዲበ ልዕልና ወረደ።ድንግል ሆይ ተርበን ሳለ እንበላው ዘንድ የሕይወት እንጀራን ወለድሽልን። ድንግል ሆይ ተጠምተን ሳለ እንጠጣው ዘንድ የሕይወት ውሃን ወለድሽልን። ድንግል ሆይ በጨለማ ውስጥ በነበርን ጊዜ ጨለማውን የሚያስወግድ የዓለምን ብርሃን ወለድሽልን። ሞት ሰልጥኖብን ነበር። ሞትን የሚገድል ሕይወትን ወለድሽልን። ስለዚህም እመ ሕይወት እንልሻለን። እመ ሕይወት ሆይ የሕይወት እናት ብትሆኝም ልጅሽ የቀመሰውን ሞት አንቺም በዛሬዋ ቀን ቀመስሽው። በአንቺና በልጅሽ ሞት ምክንያት እኛም ሞትን ናቅነው። ትንሣኤን ተስፋ አድርገን እንሞታለንና።

ኪዳነ ምሕረት

አስተብጽእዋ ወይቤልዋ ኃጥዓን እለ ይነብሩ ፈለገ እሳት። ሰአሊ ለነ ማርያም ቅድስቱ ለእግዚአብሔር። በእሳት ባሕር ውስጥ የሚኖሩ ኃጥአን ድንግል ማርያምን የእግዚአብሔር ቅድስቱ ሆይ ለምኝልን እያሉ ለመኗት። መዝ.88፣3 "ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ" ከመረጥኳቸው ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ። እግዚአብሔር በመልካም ሥራቸው ላስደሰቱት ቅዱሳን ቃል ኪዳን ሲገባላቸው ኖሯል። አዳም ንሥሓ ገብቶ "ፈጣሪየ ሆይ በድያለሁ በማለቱ" ጌታ ክልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ የሚል ቃል ኪዳንን ሰጠው። ይህም ኪዳነ አዳም ይባላል። ከጥፋት ውሃ በኋላ ለኖኅ ምድርን ዳግመኛ እንደማያጠፋት ቃል ኪዳን ሰጥቶታል። የቃል ኪዳኑ ምልክትም ቀስተ ደመና ነበረ። ለአብርሃም ዘሩ እንደሚባረክ ቃል ኪዳን ተገብቶለታል። የቃል ኪዳኑ ተጠቃሚ የሚሆኑትም የተገዘሩት ነበሩ። ይህም ኪዳነ አብርሃም ይባላል። ለዳዊት መንግሥት ክልጅ ልጅህ አይወጣም ተብሎ ቃል ኪዳን ተገብቶለታል። በዚህም ለዘላለም ንጉሥ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳዊት ተወልዷል። ይህም ኪዳነ ዳዊት ይባላል። ከላይ የተጠቀሱት ቅዱሳንን እግዚአብሔር ይወዳቸው እንደነበር በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተገልጧል። ዳዊትን እንደልቤ ይለው ነበር። በስሟ ለሚማጸኑ ምሕረትን እንደሚሰጣት ደግሞ ለወለደችው እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን ገብቶላታል። ቃል ኪዳኑም "ኪዳነ ምሕረት" ይባላል። እስከ እለተ ምጽአት ለሚነሱ ቅዱሳን ምርጦቹ ቃል ኪዳን እየገባ በቃል ኪዳናቸው እየረዳን የሚኖር እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን። እግዚአብሔር ቃል ኪዳንን የሚሰጠን እኛን በልዩ ፍቅር ስለሚወደን ነው። ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያም ስምሽን የጠራ ዝክርሽን የዘከረ በስምሽ የተቸገረን የሚረዳውን እምረዋለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶላታል። ለምርጦቹ ቃል ኪዳንን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው።

መድኃኔዓለም

በለኒ መሐርኩከ በለኒ መሐርኩከ በእንተ ማርያም።እስመ አልቦ ዘእንበሌከ ዘይሜህር ቃለ መድኃኔዓለም። ከሐሳቦች ሁሉ የሚበልጠው ሐሳብ ይችን ዕለት ሁልጊዜ ማሰብ ነው። ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ያዳነን መጋቢት 27 ቀን ነው። ከዕለታት ዓርብ ከቀናት ደግሞ 27 ለእኛ ልዩ ቀን ነው። ነገረ ስቅለቱን ሁልጊዜ እናስበው።

አምኖን

ሳይታመም ታሞ።

አልጋው ላይ ተጋድሞ።

እህቱን አምጣልኝ።

እሷ ብትመግበኝ።

እፈወሳለሁኝ።

ብሎ በመዋሸት

ለዝሙት ፈልጓት።።

ካስጠራ በኋላ

ከክብር አሳነሳት።።

ትእማርን እስኪያገኝ ቢላትም እኅቱ።።

ካገኛት በኋላ ውጭልኝ ከቤቱ።።

እያላት አምኖን የዘረኞት አባት።።

ሲፈልጋት እህት ሳይፈልጋት ጽልዕት።።

ጽልዕት ማለት የተጠላች ማለት ነው።። አምኖን የራሱ ወንጀል ስለሚያሳፍረው ዳዊት አባቱ ነው ሊል ይችላል።። ዘረኞችም የራሳቸው ችግር ጎልቶ ሲታያቸው ያመለጡ እየመሰላቸው በወንዝ ይደበቃሉ።። ዳዊት የሚለካው በዳዊትነቱ ነው።። አምኖንም የሚለካው በአምኖንነቱ ነው።። አምኖን ማን ነው? የምትሉኝ ትኖሩ ይሆናል።። አምኖን የዳዊት ልጅ ነው።። እህቱን ትእማርን ወዶ ሳይታመም ታመምኩ ብሎ ተኛ አባቱ ዳዊት ሊጠይቀው ሲሄድ እህቴ እንጎቻ ሰርታ ታብላኝ እድን እንደው አለ።። ዳዊትም እህትህማ አዎ ትርዳህ አለው።። አምኖን ግን በተንኮል ወስዶ በዝሙት አስነወራት።። በዝሙት ካስነወራት በኋላ ማየት አልፈልግም ብሎ አባረራት።። ዘረኛ ሰው አምኖንን ይመስላል።። የራሱን ፍትወት ለማሟላት በወንዝ በጎጥ ራሱን ይደብቃል።። ነገር ግን ፍትወቱን ካሟላ በኋላ ሕዝቤ የሚለውን አካል ዞሮ አያይም።። ክርስቲያን ግን በክርስቶስ አንድ የሆነ ስለሆነ በወንዝ አያስብም።። አሁን አሁን አንዳንድ ጳጳሳት፣ ካህናት፣ መምህራን፣ ፖለቲከኞች....ወዘተ በዘረኝነት ደዌ ተይዘው ይታያሉ።። ዘረኝነት ውሸት ነው።። ሰው የካም ዘር ነኝ የሴም ዘር ነኝ የያፌት ዘር ነኝ እያለ ይጣላል።። እውነታው ግን አስተሳሰቡን ትንሽ ከፍ ቢያደርግ ኖሮ።። የያፌት፣ የካምና የሴም አባት ኖኅ እንደሆነ ትዝ ይለው ነበር።። ሌላው ግን ከ10 በላይ ትውልድ መቁጠር ሳይቻል እንዲሁ በደፈናው የዚህ ዘር ነኝ ማለትም ትልቅ ነውር ነው።። የካም ዘር ነኝ ያለ እስከ ካም ድረስ በእናቱም በአባቱም በኩል ትውልዱን ቆጥሮ ይንገረን እስኪ።። አአይ አላውቀውም ካለ ደግሞ ታድያ ምንን መሠረት አድርጎ ነው እኔ የሴም ዘር ነኝ እኔ የካም ዘር ነኝ የሚባለው!? በቋንቋ እንዳንመድበው ቋንቋን ማንም ተምሮት ይናገረዋል።። ኢትዮጵያ ተወልዶ ውጭ ሀገር ሄዶ ሌላ ቋንቋ ለምዶ ይኖራል።። ይህ ከሆነ ዘረኝነት ውሸት ነው።። ብዙው ሰው ዘረኛ የሆነ በዘረኞች ምክንያት እንደሆነ ይነገራል።። ነገር ግን ዘረኞች አንድነትን በማሰብህ ቢያገሉህ ቢያሰቃዩህ እና መከራ ቢያደርሱብህም እስከ መጨረሻ እውነት ለሆነው አንድነት መታገል ይገባል እንጂ ዘረኝነት ጎትቶ እንዳያስገባህ መጠንቀቅ አለብህ።። በዚህ ምድር ዘረኝነትን የምትቃወም አንድነትን የምትደግፍ ብቸኛ ሰው ብትሆን እንኳ በደስታ ኑር።። ቢያንስ ራሱ ልዑል እግዚአብሔርና ቅዱሳን መላእክቱ ከአንተ ጋር ናቸውና።። ዳዊት በዳዊትነቱ ተመዝኖ ቢበድልም ንሥሓ ገብቶ ልበ አምላክ እስከመባል በቅቷል።። አምኖንም በአምኖንነቱ ተመዝኖ ከእኅቱ የደረሰ እርኩስ ስለሆነ ኃጥእ ነው።። አምኖን በአባቱ በዳዊት ልበ አምላክነት ለመመካት የሚያበቃ ምንም ምክንያት የለውም።። ሰው በራሱ ይለካል እንጂ በአባቶቹ ወይም

በልጆቹ አይለካም። ትክክለኛ ፍርድ ይህ ነው። ጌታም በልጅ ኃጢኣት አባትን በአባት ኃጢኣት ልጅን አይቀጣም። ለሁሉ እንደሥራው ይከፍለዋል እንጂ። የትም ቦታ በየትኛውም ጊዜ ደጋጎች ነበሩ ክፉዎችም ነበሩ። ክፉን ከደግ በወንዝ ሒሳብ ቀላቅሎ ከመናገር ደግ ደጎችን ያለ ወንዝ መለኪያ ማድነቅ ክፉ ክፉዎችን ደግሞ መገሠጽ ይገባል። ቆሻሻን የወንዜ ልጅ እያልክ ብትደብቀው በሽታን ነው የሚያተርፍልህ። ደጎችን የወንዜ ልጆች አይደሉም ብለህ ብታርቃቸው ረዳቶችህን ክንዶችህን እንዳጣህ እወቅ።

ቡና ይጠጣል

ቡና መጠጣት የሚፈልግ ይጠጣ። ቡና የሚጠጣን ሰው የሚነቅፍ ሰው ግን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ያላነበበ ሰው ነው። የማይበላ የሚበላውን አይንቀፈው ይላልና። ሃይማኖታችን ቡና አይጠጣም ብላ አትከለክልም። ልክ እንደ ውሃ እንደ ጠላ ሁሉ ቡናንም መጠጣት ይቻላል። ነገረ ሃይማኖት እያስተማርኩ ነገር ግን በMessenger የምጠየቀው ጥያቄ ቡና ይጠጣል ወይስ አይጠጣም የሚል ተልካሻ ጥያቄ ነው?! ስንት ጊዜ ልጻፍ ቆይ በዚህ ጉዳይ!? አሁን አሁን መቅድመ ኩሉ ንሰብክ ሥላሴ ዕሩየ ወቅዱሰ ዘውእቶሙ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ከሚለው ድንቅ የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ይልቅ ሰው በጣም የሚወደው ስለ "ቡንየ" ብታወራለት ነው። እረ ጎበዝ መጀመርያ ነገረ ሃይማኖትን እንማር ሌላው ሌላው ጥያቄ ስንማር በራሱ ጊዜ የሚመለስ ነው። ድርሳነ ጽዮን፣ ዜና ሥላሴ፣... ወዘተ ገድላት ላይ አንድ ቃል ተጽፎ ቢገኝ በአሥራው መጽሐፍ ተገምግሞ የሚያዘው ይያዛል። የማይያዘው አይያዝም። የሊቃውንት ጉባኤ በጠቅላይ ቤተ ክህነት መምሪያ የተዘጋጀውም ለዚሁ ዓላማ ነው። ቅዱሳት ገድላት እና ድርሳናት ላይ አንዳንድ ክፉ ሰዎች እንዲሁም ሚሲዮናውያን የጻፏቸው አንዳንድ ጽሑፎች ሲኖሩ ይታረማሉ። በነገራችን ላይ በጉባኤ ቤት ደረጃ ቡና አይጠጣም የሚል ጉባኤ ቤት አላገኘሁም። አንድ ሁለት መነኮሳት ብቻ እየዞሩ አይጠጣም ይላሉ። ያልተማረ ዲያቆን ቅዳሴ ቢያልቅበት ቀረርቶ ተካበት እንዲሉ። ነገረ ክርስቶስን፣ ነገረ ሥላሴን ማመስጠር ሲያቅታቸው ዝም ብለው ትንንሽ ጉዳዮች ላይ ሲርመሰመሱ ይታያሉ። መጽሐፈ መነኮሳት ፊልክስዩስ ላይ ክፍል 15 ተስእሎ 195 ላይ እንተቀመጠው ምንም ዓይነት አምልኮ ሳታመልክ እግዚአብሔርን እያመሰገንክ ጠላም ቢሆን፣ ቡናም ቢሆን፣ ጠጅም ቢሆን ብትጠጣ የተፈቀደ ነው። የቡናውን ቁርስም ቡናውንም በልተህ ጠጥተህ ፈጣሪህን አመስግን። ምግብ መጠጥ የተሰጠ በልተን ጠጥተን ፈጣሪን እንድናመሰግንበት ነውና። ቡና የሰይጣን ሽንት ነው የሚሉ ሰዎችም አሉ። እኒህ ሰዎች መሠረታዊ የሃይማኖትን ትምህርት ስላልተማሩ እንጂ ቢማሩ ኖሮ ሰይጣን ረቂቅ ፍጥረት ስለሆን እንኳን ሽንት መሸኛ እንደሌለው ያውቁ ነበር። ወደ ጉባኤ ቤቶች፣ ወደ መንፈሳዊ ኮሌጆች፣ ወደ ግቢ ጉባኤያት፣ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤቶች እየገባን እንማር። ከሁሉ በፊት የሃይማኖታችንን አስተምህሮ ጠንቅቀን እንማር።

ሆሳዕና

በፊልክስዩስ መቅድም ስለሰሌን የሚከተለውን ይላል።

1ኛ) አብርሃም ይስሐቅን ሲወልድ ሰሌን ይዞ እግዚአብሔርን አመስግኖታል።

2ኛ) ዮዲት ሆለሆርኒስን አሸንፋ ስትመጣ ሰሌን ይዘው አሸናፊ ነሽ ሲሉ ተቀብለዋታል።

3ኛ) አብርሃም ነገሥተ ኮሎዶጎሞርን ድል ነሥቶ ሲመጣ ሰሌን ይዞ ፈጣሪን አመስግኗል።

4ኛ) ኢሳይያስ እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች የሚለውን ትንቢት ሲናገር ሰሌን ይዞ አመሰግኗል።

5ኛ) እስራኤል ባሕሩን በተሻገሩ ጊዜ ሰሌን ይዘው አመስግነዋል።

6ኛ) ሕጻናት ጌታን በዕለተ ሆሳዕና ሰሌን ይዘው አመስግነውታል።

7ኛ) አባ እንጦንዮስ ሥርዓተ ምንኩስናን ከመልአክ ሲማር ሰሌን እየታታ አይቶያል።

ሰሌን መያዝ የአሸናፊነት እና የእውነተኛ ደስታ ምልክት ነው። በዚህ አንጻር አቤቱ ሁሉን አድን እያሉ ሕጻናት ጌታን አመስግነውታል። እንኳን ለበዓለ ሆሳዕና በሰላም አደረሳችሁ።

በሰሙነ ሕማማት

1ኛ) ወርኃዊ በዓላት ማለትም የሚካኤል የማርያም እና የበዓለ እግዚአብሔር ቢውልም በሰሙነ ሕማማት ይሰገድባቸዋል።

2ኛ) መስቀል ማሳለምም መሳለምም አይቻልም።

3ኛ) ዓመታዊ የቅዱሳን በዓላት እንዲሁም ሌሎች በዓላት ቢውሉም በሰሙነ ሕማማት ንግሥ አይደረግም። ከትንሣኤ በኋላ ባሉ ቀኖች በዓሉ ይከበራል እንጂ።

4ኛ) ግብረ ሕማማቱ ከሚያዛቸው መልክኦች ውጭ መልክአ መልክ አይደገምም።

5ኛ) መዝሙረ ዳዊት በስፋት ይጸለያል። ውዳሴ ማርያምም መድገም ይቻላል።

በተጨማሪ ለማወቅ ፍትሐ ነገሥት ትርጓሜን እና ግብረ ሕማማትን ይመልከቱ። ሰሙነ ሕማማትን ክርስቶስ ለእኛ ሲል ያደረገውን የማዳን ሥራ እያስታወስን በጾም በጸሎት በስግደት እናሳልፈዋለን።

ሀገራዊ ውሽት (ቀደዳ)

ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ናት ብለን እንደ ሀገር የተቀበልነው ሀገራዊ ውሽት ነው። ይገርመኛል መንግሥት ድንቅነሽ (Lucy) እሆነ ወቅት ላይ ታስታርቃለች ተብሎ በየሀገሩ ስትዞር፣ ሰው ትሁን ጦጣ ትሁን የማትታወቅ ሴትዮ ያውም ራሳዋ ማለቴ አጥንቷ ያስታርቃል ተብሎ ሲታሰብ ምን ይሄ ብቻ ስትጎበኝ ስታይ የሀገራችንን ታሪክ አዳፍኖ ሌላ የውሸት ታሪክ ለመፍጠር የሚንቀሳቀስ አካል እንዳለ ነው የሚሰማኝ። ሀገር በውሸት አትከብርም ይሉ ነበር የኔታ ወልደ ሰንበት፣ ኢትዮጵያን የሚያኮራት እኮ ድንቅ ድንቅ ታሪክ አለን። ያንን እያጠፉ ምንም ዓይነት ማስረጃ የሌለው ልብ ወለድ መፍጠር ትልቅ ነውር ነው። በእርግጥ ትልቅ ፕሮፌሰር ተብሎ ሲያጠምቋችሁ አማራ ነው የሚያደርጓችሁ ብሎ የሚያስብ ምሁር ባለበት

ሀገር ብዙ ነገር ባይለወጥ ነበር የሚገርመኝ (አይ ፕሮፌሰርነት)። አይ ምሁርነት እንዲህ ይርከስ ግን!? እውነቱን ተነጋግረን መፍትሔ ብናመጣ አይሻልም ጎበዝ!? ለመሆኑ ሉሲን መሠረት አድርጎ ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ናት ሲሉን ዝም ብለን አጨብጭበን ከመቀበል ይልቅ መጠየቅ አልነበረብንም?!

1ኛ) ከዚህ ድምዳሜ ለመድረስ የዓለም ከርሠ ምድር ሁሉ ተቆፍሮ ኢትዮጵያ የተገኘው በመመርመሪያችሁ ታላቅ ሆኖ ተገኝቶ ነው ወይ?/ዓለምን ሁሉ ቆፍራችሁ ጨርሳችሁታል ወይ?

2ኛ) መመርመሪያው ራሱ ምን ያህል ትክክል ነው? ዝም ብሎ 3.2 ሚልየን ዓመት ይሆናታል ስትሉ አታፍሩም ወይ? መመርመርያው ትክክል ለመሆኑስ በምን እንመርምረው? አይ የሚታወቅ ሬሳ ላይ ሞክረነው ስለሠራ ካልችሁ ታድያ ያ መሣሪያ 3000 ዓመት በላይ ላሉ አጥንቶች የማይሠራ ቢሆንስ? አንዳንድ ፎርሙላዎችኮ እስከ 1000 ሰርተው ከዚያ በላይ የማይሰሩ አሉ። Numerical Method።

3ኛ) የሉሲ አጥንት ኢትዮጵያ ውስጥ ቢገኝ እንኳ እና እርሷ የመጀመርያ ሰው ናት ብትባል እንኳ (ውይ ለካ አርዲ መጥታለች) ኢትዮጵያን የሰው ዘር መገኛ የሚያሰኝ ምን አመክንዮ አለ? ምክንያቱም ኢትዮጵያ ተወልደው አሜሪካ የተቀበሩ አሉ።

የራሳችንን ታሪክ ራሳችን ባለን ነገር እንጻፈው ማንም ውጫዊ አካል ታሪካችሁ እንዲህ ነው ባለን ቁጥር እያጨበጨብን አንቀበል። ሀገር በውሸት አትከብርም።

ኢየሱስ ክርስቶስ

ንሕነሰ ንሰብክ ክርስቶስሃ ዘተሰቅለ። በነገራችን ላይ ሰሙነ ሕማማት ማለት የመከራ ሳምንት ማለት ነው እንጂ የበሽታ ሳምንት ማለት አይደለም። ክርስቶስ ታመመ በምንልበት ጊዜም በፈቃዱ መከራን ተቀበለ ብለን ነው የምንተረጉመው። የማይታመመው ታመመ ማለት ምን ማለት ነው? የማይታየው በታየበት አንጻር፣ የማይዳሰሰው በተዳሰሰበት አንጻር ነው። የማይታመመው ቃል የሚታመም ሥጋን ገንዘቡ ስላደረገ በሥጋ ታመመ እንላለን። የሚታመመው ሥጋ ደግሞ የማይታመም ቃልን ገንዘቡ ስላደረገ በቃል አልታመመም እንላለን። አንዱ አካል ክርስቶስ ሐማሚ ኢሐማሚ ነው። የሚታመም የማይታመም ነው። ይህ ከሆነ ሐመ በፈቃዱን መዘንጋት የለብንም። እኛ መከራ ቢደርስብን ያለ እኛ ፈቃድ ነው። እርሱ ግን ከአይሁድ መከራን የተቀበለ እኛን ያድነን ዘንድ ፍቅሩን ያሳየን ዘንድ በፈቃዱ ነው። የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ምን ይደንቅ። ፍቅሩን በመስቀሉ ገለጠልን። ስለዚህ መስቀል የፍቅር አደባባይ ነው።

እንበለ ደዌ ወሕማም፣

እንበለ ጻማ ወድካም፣

አመ ከመ ዮም፣

ያብጽሐነ ያብጽሕክሙ፣

እግዚአብሔር በሰላም።

የደጋጎች ደሴት

የደጋጎች ደሴት እውነት ናት። ደጋግ ሰዎች የሚኖሩት በውሸታም ሕዝብ መካከል እውነትን ይዘው በእውነት ውስጥ ነው። ንግግራቸው ሁልጊዜም እውነት ነው። ፍርዳቸው እውነት ነው። ክርስቶስ እውነት ነው። በውሸታም አይሁዶች መካከል የነበረ፣ ውሸታሞች ይጠሉት የነበረ እውነት ነው ክርስቶስ። የደጋጎች ደሴት ክርስቶስ ነው። መርሶሔሙ ለኅዙናን እንዲል። በነገራችን ላይ በሀገራችንም አጠቃላይ በዓለም ውስጥም ቀድሞም አሁንም ወደፊትም ደጋጎች ነበሩ፣ አሉ፣ ይኖራሉ። እነርሱን እያሰብን ካልኖርን በስተቀር ክፉ ሰዎችን ብቻ ካየን ይሰለቸናል። መኖር ራሱ አሰልቺ ይሆናል። ደጋጎች በዚህ ምድር ሲኖሩ ሁልጊዜም ደስተኞች ነበሩ። ክፉዎች በነገር፣ በሥራ መከራ ቢያደርሱባቸውም የሚደርስባቸው መከራ ደስታቸውን አልቀነሰውም። ደስታቸው በእግዚአብሔር ስለሆነ ነው። ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን አይደል ያለ ቅዱስ ዳዊትስ። ቤተ ክርስቲያን የእውነት አደባባይ ናት። ነገር ግን እውነትን አጥፍተው በእውነት ምትክ ለግል ፍላጎታቸው ገበያ ያደረጓት አይሁድ ነበሩ። አሁንም ቤተ ክርስቲያንን ለሥጋ እንጀራ ብለው የሚመዘብሯት አሉ። ትሕትና እውነት ነው። አንደኛው የደጋጎች ደሴት ትሕትና ነው። ሌላው ትክክለኛ ፍርድ ነው። ትልቁ የደጋጎች ደሴት ደግሞ ፍቅር ናት። ክርስቶስ በመስቀሉ የገለጣት ሰውን እንዲያድን ያደረገችው አጋንንትን እንዲያሥር ያደረገችው ፍቅር ናት። ኑ ወደ ደጋጎች ደሴት እንሂድ።

ስቅለት

ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ። አቤቱ በመንግሥትህ አስበን። አዳም እፀበለስን በልቶ ከገነት የተባረረ አርብ ቀን ነው። አዳም የተፈጠረውም አርብ ቀን ነበር። ወደቀደመው የክብር ቦታ ገነት የተመለሰውም አርብ ቀን ነው። ዓርብ ኀብስት ሕይወት ጽዋዕ ሕይወት ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ እኛን ያዳነባት እለት ናት።የእኛን ሞት ሞቶ የእርሱን ሕይወት ለእኛ ሰጠን።

ትንሣኤ ልቡና

ዛሬ የትንሣኤ በዓልን እያከበርን ነው። ትንሣኤ ማለት መነሣት ማለት ነው። ብዙዎቻችንም እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሰን እያልን ነው። ፖለቲከኛውም፣ ሰባኪውም፣ ጳጳሱም፣ ዘፋኙም፣ አርቲስቱም፣ አክቲቪስቱም ሁሉም እንኳን አደረሳችሁ እያለ ነው። ጌታ ተነሳ ስንል እኛም መነሣት አለብን። አክቲቪስቱ ከከፋፋይነት መቃብር ወጥቶ ኢትዮጵያውያንን አንድ የሚያደርግ ሐሳብ ማንሣት አለበት። ሁሉንም ኢትዮጵያውያን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሐሳብ እና አሰራርን ሊከተል ይገባል። ፖለቲከኞች በቂም በቀል እና በሴራ መቃብር ውስጥ ሆናችሁ እንኳን አደረሳችሁ ብትሉን ራሳችሁን የምትዋሹ ትሆናላችሁ። ከመቃብር ውጡ። ትንሣኤያችሁን ሐዋርያት ይመልከቱት። በመቃብር ሆነን ስለ ትንሣኤ ብናወራ አያምርብንም። ኑ በሉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተነሣ እኛም ትንሣኤ ልቡናን እንነሣ። የዘረኝነት፣ የውሸት፣ የጥላቻ፣ የበቀል፣ የሐሜት፣ የከንቱ ውዳሴ፣ የትዕቢት፣ የራስ ወዳድነት

መቃብርን ፈንቅለን እንውጣ። ኑ እንነሣ። ስንነሣ ደግሞ ልባችን ብርሃንን ይሞላል። ችግሮቻችን ሁሉ ከእኛ በታች ነበሩ። ነገር ግን ትንሣኤ ልቡናን ባልተነሡ ሰዎች ምክንያት እንደ ተራራ የገዘፉ ሆኑብን። ኑ በትንሣኤው እንነሣ።

ይሁዳነት

በአፋችሁ እንኳን አደረሳችሁ እያላችሁን በልባችሁ ግን ቀጣይ ዓመት እንዳንደርስ እየገደላችሁን ከሆነ ይሁዳነት ነው። ይሁዳ በአፉ ሰላም እያለ ነው ጌታን የሸጠው። ሁሉም ከተንኮል፣ ከሽንገላ መቃብር ይውጣ እና የፍቅር ትንሣኤን ይነሳ።

ኦርቶዶክሳዊነት

ኦርቶዶክሳዊነት ማለት ቀጥ ያለ ርቱዕ እና ትክክለኛ እምነት ማለት ነው። ክርስቲያን እውነት ይናገራል። በእውነት ለእውነት ይኖራል። ለእውነት ይሞታል እንጂ ፈርቶ እውነቱን ውሸት ብሎ በአድር ባይነት አይኖርም። ሞት በክርስቶስ ትንሳኤ ተሸንፏል። ቅዱስ ጳውሎስ "አይቱ መዊኦትከ ሲኦል" መቃብር ሆይ ማሸነፍህ ወዴት አለ? ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ብሎ እንደተናገረው ክርስቲያን ከሞት በላይ ነው። ሰማእቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ሠራዊት ነበር። ነገር ግን ሐሳቡ ዘለዓለማዊ ስለነበር ለእውነት መሞትን መረጠ። ኦርቶዶክሳዊነት ፍርዱ የቀና ነው። ፍቅሩ እውነት ነው። ኦርቶዶክሳዊነት ጥፋትን በይቅርታ የሚያልፍ በንሥሓ ኃጢኣትን የሚያርቅ ነው። ፈጣሪንም ሰውንም በድለን ከሆነ ንሥሓ ገብተን ከፈጣሪም ከሰውም እንታረቅ። ንሥሓ አሮጌውን መንገድ አጥፍቶ አዲስ መንገድ የሚከፍት ነው። ክርስቶስ እውነት ነው። ከክርስቶስ ጋር ያለን አንድነት እውነት ነው። ከምንም በላይ እኛ የምንፈራው እግዚአብሔርን ነው። እግዚአብሔርን መፍራት ማለትም ከምንም በፊት ለእርሱ ትእዛዝ በፍቅር መገዛት ማለት ነው። እኛ ኦርቶዶክሳውያን እንደ አባቶቻችን እንደነ ቅዱስ ጳውሎስ ብንሞትም ለእግዚአብሔርን እንሞታለን ብንኖርም ለእግዚአብሔር እንኖራለን። ደስታችን በእግዚአብሔር ነው። ኦርቶዶክሳዊ ንጉሥ ለፍርዱ እውነት እና የቀና ነው። የሚመራውንም ሕዝብ እንደ ፈጣሪው ሳያዳላ በእኩልነት ይመራል። ኦርቶዶክሳውያን ሆይ ዳኞችም፣ ወታደሮችም፣ ፖለቲከኞችም፣ ካህናትም፣ ምእመናንንም፣ ነጋዴዎችም፣ ወታደሮችም ሁላችሁም ለእውነት በእውነት ኑሩ። አድርባይነትን አውልቃችሁ ጣሉት። ሥጋዊ ሞት እንደሆነ ለማንም አይቀርም። ሞት ካልቀረ ደግሞ ቀሪ ጊዜያችንን እስኪ ሰው ሆነን እናሳልፈው። ቤተ ክርስቲያናችንን እንጠብቅ። አንድነታችንን እናጽና። ከክርስትና ማማ አውርደው በጎጥ በወንዝ በክልል የሚያጥሩንን ሰዎች ሐሳብ አንቀበል። የትም እንሁን የት ለእውነት እንኑር። ዘረኝነት ውሸት ነው። ፍቅር እና አንድነት ግን እውነት ነው። ሁላችንም የተጠመቅን ጊዜ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል። ራሳችን እና መሪያችንም ክርስቶስ ነው። ከዚህ የበለጠ አንድነት የለም። ይህንን አንድነት ሰይጣን በብሔር በቋንቋ ሊከፋፍለው ይጥራል። ይህ ግን የሰይጣን ተንኮል ስለሆነ እንንቃበት። እርስ በእርስ ያላግባቡን ጉዳዮች ቢኖሩ እንኳ ከክርስትና በታች ስለሆኑ በፍቅር በይቅርታ የሚታለፈውን በይቅርታ በካሣ የሚታለፈውን በካሣ አልፈን አንድነታችንን እናጠንክር። እግዚአብሔር አባታችን፣ መንግሥተ ሰማይ ርስታችን፣ ቅዱሳን ወዳጆቻችን፣ ድንግል ማርያም እናታችን እንበል።

ኦርቶዶክሳዊው ውትድርና

ኦርቶዶክሳዊው ወታደር ካልደረሱበት አይደርስም። አያዳላም። ሁሉንም ያከብራል። ነገር ግን በአመፅ ከመጡበት ምንም ፍርሀት የሚባል ነገር የሌለበት እስከ መጨረሻው የሚዋጋ ነው። ታላቅ ተዋጊ የነበረ ቅዱስ ቴዎድሮስ በናድሌዎስ ነው። እነ ቅዱስ ጊዮርጊስም ወታደሮች ነበሩ። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ለክርስቲያኖች ዕረፍትን ያመጣው ክርስቲያኖችን በግፍ ያሰቃይ የነበረውን ዲዮቅልጥያኖስ አስወግዶ ነው። ክርስቲያን ከፈጣሪ ውጭ የሚፈራው ምንም ነገር የለም። ራሱን ለእውነት ያስገዛል። ፈጣሪውን ያመልካል። ሰውን ያከብራል። ከዚያ ውጭ በግፍ የመጣበትንም ልክ ያገባል። ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ሰማእታት ይባላል። በ27 ዓመቱ ሰማእትነትን የፈጸመ የክርስቶስ ወታደር ነው። 7 ዓመት ዓላውያን ነገሥታትን በእውነት ሲሞግታቸው ሐሰታቸውን ሲገልጥባቸው እነርሱ ደግሞ በቃል በእውነት ማሸነፍ ሲያቅታቸው በሰይፍ እየገደሉት ሦስት ጊዜ ሞቶ እየተነሳ በኋላ በተአምራት እሳት ከሰማይ አውርዶ ሰባ ነገሥታትን አጥፍቷል። በዓለማዊው ሥራ ኢታማዦር ሹም (ሊቀ ሠራዊት) የነበረ ቢሆንም ከማንኛውም ሥጋዊ ሹመት፣ ገንዘብ እና ክብር ይልቅ ሰማያዊና ዘላለማዊውን ክብር አብልጦ ለእውነት ሲጋደል ኖሯል። ማንኛውም ሰው ከምንም ነገር አስቀድሞ ለሃይማኖቱ ቅድሚያ ይስጥ። ሥልጣንህ ንብረትህ ሹመትህ ክብርህ ከሃይማኖትህ በታች ነው። ስለዚህ ከአድር ባይነት ተላቀህ በእውነት ኑር። ለእውነት ኑር። ትክክለኛው የኑሮ ትርጉም ይህ ነውና። ማንኛውም ክርስቲያናዊ ወጣት ከሱስ ወጥቶ ንሥሓ ገብቶ የፈጣሪውን ሕግ የሚያከብር መሆን አለበት። ምእመናንን መጠበቅ አለበት። በየሰፈሩ በየቤተክርስቲያኑ ተደራጅቶ መቀመጥ አለበት። እስላም ክርስቲያን ሳይል ሁሉንም ሰው ማክበር አለበት። ቤተ ክርስቲያኑን ሊያቃጥል ወይም ምእመናንን ሊጎዳ የሚመጣ አካል ሲመጣ ግን ተደራጅቶ መመከት እና ለሕግ አሳልፎ መስጠት ይገባዋል። አንድነታችንን አንተው። ከኃድያን ክፉ ክፉ ትምህርትን ሲያስተምሩ ኃይለ ቃል ጠቅሶ መርታት ከሊቃውንት ይጠበቃል። ዓላውያን ጦር ሰብቀው ሲመጡ መጠበቅ ደግሞ ከምእመናን ይጠበቃል። በነገራችን ላይ ኦርቶዶክሳዊው ወታደር እጅ ለሚሰጡት የሚራራ እጅ አንሰጥም ያሉትን ደግሞ እስከመጨረሻው የሚዋጋ ነው። ከዚህ ቀደም ስለ ውትድርና በጻፍኩት ማየት ይቻላል። ፍትሐ ነገሥትም ይህንን በሰፊው ይናገራል።

ብንኖርም ለእግዚአብሔር እንኖራለን

ብንሞትም ለእግዚአብሔር እንሞታለን።

የመነናዊነት ትልቁ ችግር

ከአስተማሩኝ መምህራን አንዱ የነገሩኝ ታሪክ ትዝ ይለኛል። "የሆነ ልጅ የሆነችን ልጅ ይወድና ሱባኤ ይገባል። ከዚያ ሱባኤውን ጨርሶ ሲመጣ ያችን ልጅ ሱባኤ ገብቼ ነበር እና አርሴማ አንችን እንደማገባሽ ነግራኛለች ይላታል። ልጅቱም ዞር በል እምቢ አለችው" አሉኝ። ጎበዝ እንዲህ ዓይነት አጭበርባሪ ሲመጣ አርሴማህን ፈልግ በሉት። በታላቂቱ ቅድስት ሰማእት አርሴማ አትነግድ በሉት። መነናውያን እግዚአብሔርን የሚለኩት በእነርሱ እቅድ ልክ ነው። እግዚአብሔር እስከዚህ ቀን እንዲህ ካደረገ አለ እላለሁ ካላደረገ የለም እላለሁ ይሉሀል። ማኒ ባሕታዊ ነበር አንድ ቀን አህያ ነበረውና ጠፋው ከዚያ አህያየን ካገኘሁት ፈጣሪ አለ እላለሁ

ካላገኘሁት ግን የለም እላለሁ ብሎ ፍለጋ ጀመረ። እግዚአብሔርን ደግሞ በትሕትና ቢለምኑት እንጂ በትዕቢት ቢለምኑት ጸሎትን አይቀበልምና ቅርብ የነበረውን አህያ አራቀበት ይታይ የነበረውን ግዙፉን አህያ አረቀቀበት። ማኒም አህያው ጠፍቶት ሲቀር "ለዚች ዓለም አስተዳዳሪ ገገር የላትም ፀሐይ በልማድ በምሥራቅ ወጥቶ በምእራብ ይገባል ክረምትና በጋ በልማድ ይፈራረቃል" ብሎ ፈጣሪውን ካደ። እርሱን የመሰሉ ከኃድያን መነናውያን ይባላሉ። መነናውያን በአሁኑ ዘመንም ተበራክተዋል። አንዳንዶቹ ገዳም ይሄዱና ይህ ከተደረገልኝ ፈጣሪ ፈቅዷል ማለት ነው። ካልተደረገልኝ ደግሞ አልፈቀደም ማለት ነው ይሉሀል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በእነርሱ ቅድመ ውሳኔያዊ ፍላጎት ለመለካት ያምራቸዋል። አንዳንዱ ሊሰርቅ ሲሄድ ፈጣሪ ካልፈቀደ ራሱ በሚያውቀው ምክንያት ያስቀረኝ ነገር ግን ከሰረቅሁ ፈጣሪ ፈቅዷል ማለት ነው ብሎ ያስባል። ፈጣሪ ሌብነትን መቼም ፈቅዶ አያውቅም። አንዳንዱ ሱባኤ ሲገባ ከዚህ ገዳም 40 ቀን ቆይቼ ከወጣሁ የማገባት እገሊትን ነው ካልወጣሁ እና ከሞትኩ ግን እሷን አላገባም ብሎ ገዳም ይገባል። ልክ 40 ቀን ሞልቶት ሲወጣ እርግጠኛ ሆኖ ያችን ልጅ ካላገባሁ ይልሀል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በእኛ ቅድመ ውሳኔያዊ ምኞት ማጠርኮ መነናዊነት ነው።

ይህን ያውቁ ኖሯል

1) ሴት በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ከቤተ ክርስቲያን ውጭም በማንኛውም ጊዜ ጸጉሯን ትከናነብ።

2) ሴት ልጅ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ መከናነብ አልፈልግም የምትል ከሆነች ደግሞ ጸጉሯን ተላጭታ ያለ ክንንብ መሄድ ትችላለች። ይህ በገጠር እንዳሉ እናቶቻችን ማለት ነው። ይህ ሕግ ለከተሜም ለገጠርም ለማንኛውም ክርስቲያን የተነገረ ነው። ለከተማ እና ለገጠር የተለያየ ሥርዓት የለም።

3) የጥፍር ቀለም መቀባት የሰይጣን ሥራ ነው። ይህንን የሚያሰራው ሰይጣንም መንፈሰ ትውዝፍት ይባላል። መጽሐፈ ሄኖክ ትርጓሜን ይመልከቱ።

ምንጭ ፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ አንቀፅ 11 በእንተ ሕዝባውያንን ይመልከቱ። ጸጉርን ካሳደጉ በሻሽ (በሰርመዴ/ባውንድ) ይከናነቡ። ጸጉራቸውን ከተላጨ ግን ያለ ክንብንብ እንዲሁ መሄድ ይችላሉ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን የተላጩትም ቢሆኑ መከናነብ አለባቸው። አየህ የገጠር እናቶቻችን በኑሮ ጥርት ያሉ ክርስቲያኖች ናቸው። ኑሯቸው የመጻሕፍት ትርጓሜ ነው። የከተማም ሆኑ የገጠር ሴቶ ማናቸውም ሴቶች ጸጉራቸውን ካሳደጉ በቤተ ክርስቲያንም ከቤተ ክርስቲያን ውጭም መከናነብ አለባቸው። አይ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ሌላ ቦታ አንከናነብም የሚሉ ከሆነ ግን እንግዲያውስ ጸጉራቸውን ይላጩ። አለመከናነብ የሚፈቀደው ከተላጩ ብቻ ነው።

ቅዱስ ያሬድ

ቅዱስ ያሬድ የትርጓሜ ሊቅ ነው። የብሉያትና የሐዲሳት ትርጓሜ መምህር ነው። ድጓው ለዚህ ምስክር ነው። ልዩ ተርጓሚ መሆኑ በዚያ ይታወቃል። ኢትዮጵያን በእግዚአብሔር ምስጋና

እንድታሸበርቅ ያደረጋት እርሱ ነው። አሠርገዋ ለኢትዮጵያ በስብሐት ወበሀሌሉያ እንዲል ደራሲ። የቅዱስ ያሬድ ታሪክ የኢትዮጵያን የቀድሞ ሃይማኖታዊ ታሪክ በጉልህ የሚያስረዳ ኢትዮጵያ በነገረ መለኮት ትምህርት የነበራትን እና ያላትን ጥልቅ አስተምህሮ የሚያሳይ ነው። የቅዱስ ያሬድ ዜማ ኀዘንን የሚያስረሳ ልብን በሐሴት የሚሞላ ሰማያዊ ስጦታ ነው። የሰው ልጅ የተፈጠረው እግዚአብሔርን እያመሰገነ በዚያ ደስ ብሎት እንዲኖር ነበር። ቅዱስ ያሬድ መናኝም ነበር። መልአክ ዘበምድር ነው።

የአክዓብ ችግር

አክዓብ ሀገሩ ረኃብ ውስጥ የገባች በራሱ ጣዖት አምላኪነት ሆኖ ሳለ ችግሩን በኤልያስ ለማላከክ (ለማሳበብ) ሞክሮ ነበር። አንተ ውእቱ ዘትገፈትዖሙ ለእስራኤል ብሎ ነቢዩ ኤልያስን ወቅሶት ነበር።1ኛ ነገ.18፥17። ራሱ አክዓብ ጣዖት አምላኪ ነበር።1ኛ ነገ.16፣33። ጣዖት ማምለኩ እስራኤልን ለችግር ዳርጓታል። ኢትዮጵያ ላይ ለተከሰተው ችግር ኃላፊነት የሚወስድ አካል ማን ነው? የችግሩ ባለቤት ራሱ አክዓብ ሆኖ ሳለ ንጹሑን ኤልያስን የችግሩ ምንጭ ነው በማለት አሳዶታል። እውነቱ ግን ይህ አልነበረም። ኤልያስ ቀናዒ ለአምላኩ ነው። ኤልያስ እውነትን ሲናገር አይፈራም ነበር። ኤልያስን ያሳደዱት ሰዎች የኋላ ኋላ የኤልያስ እውነት የእነርሱ ውሸት ስለተጋለጠ በመቅሠፍት ሞተዋል። የብዙ ሰው ትልቁ ችግር ይህ ነው። ራሱን ከማየት ይልቅ ለችግሮች ሁሉ ኃላፊነት የሚወስድ ሌላ ሰው ይፈልጋል። አዳም ዕፀበለስን በልቷል ለችግሩ ግን ሔዋንን ተጠያቂ ለማድረግ ጥሯል። ሔዋንም የራሷን ችግር በዲያብሎስ አሳባለች። ነገር ግን ፈታሒ በርትዕ እግዚአብሔር የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ያለው ስለሆነ ለሚያደርገው ለእያንዳንዱ ነገር ተጠያቂው ራሱ ነው በማለት በአዳምም በሔዋንም ፈርዶባቸዋል። ውሸት የምትጎዳው በዋናነት የዋሸውን አካል ነው። ለሁለት ጠበኞች የተሻለው መንገድ እርቅ ነው። ያጠፋው ይቅርታ ጠይቆና ካሣ ከፍሎ፣ የተበደለውም ከልቡ ይቅር ብሎ የወደፊቱ ሕይወታቸውን ያማረ ያደርጋሉ። ነገር ግን እርቅ ከሁለቱም ወገን ሲሆን እንጂ አንዱ እየፈለገ አንዱ በአመፁ ከቀጠለ አይሆንም። ነገር ግን ጊዜያዊ ትርፍን ሳይሆን ወደፊት ላለው ትውልድ ሁሉ ታስቦ በሁሉም ወገን የሚያስማማ ሥራ ቢሠራ መልካም ነው። አንድን አካል ጎድተህ የምታመጣው ድል ጊዜያዊ ነው። የተጎዳው አካል ጊዜ ጠበቆ መበቀሉ አይቀርም። ባለፉት ዘመናት አርቀው በማያስቡ ሰዎች የተፈጠሩትን ችግሮች አሁን ላለ ትውልድ በማሸከም የቀድሞዎች ባጠፉ የአሁኑ ትውልድ የሚሰቃይበት ምንም ምክንያት የለም። የአሁኑ ትውልድ ዛሬ ላይ እና ነገ ላይ ያተኩር። ትላንት ላይ መቸከል አይገባም። እንደ አክዓብ የራስን ችግር በሌላው በማሳበብ ችግሮች አይፈቱም። ከሁሉም ያሉ ችግሮችን በጋራ መፍታት ይገባል። ከዚያም ከዚህም ያሉ በቆሻሻ አስተሳሰብ የተበከሉ ሰዎች ማጥራት ማስተማር እና ንጹሕ ማድረግ ይጠበቃል። የራስህን ቆሻሻ በቤትህ አስቀምጠህ በሌላው ቤት ስላለው ቆሻሻ በማውራት መጠመድ አይገባም። ቆሻሻ ቆሻሻ ነው። የአንተም የሌላውም አይጠቅሙም። ሁለቱንም ማስወገድ ለጤናማ ሕይወት ይጠቅማል። ጎረቤቱ ቆሻሻውን ስላላስወገደ የእኔንም አላስወግድም ግን አይባልም። የራስህን አጥራ። የሌላውን ራሱ ባለቤቱ ይጨነቅበት። ንጽሕናን ገንዘብ እናድርግ። ራሳችንን እንመልከት ከቂም በቀል እና ጥላቻ እንውጣ። ትክክለኛውን መንገድ እንከተል። ሰው ስላበደ አብረን ማበድ የለብንም። በውሸት እና በዘፈን የተገነባ ስብዕና እውነት

የመጣ ጊዜ ይፈራርሳል። ሁልጊዜም በነጻነት የሚያኖር እውነት ነው። እውነትን የያዘ ሰው ሁል ጊዜም በራስ መተማመን ውስጥ ይኖራል። አያፍርም። አይፈራም። ሙሉ ኢትዮጵያውያን ያመጡትን ድል ለጥቂት ግለሰቦች መስጠት ነውር ነው። ችግር ሲመጣብህ እረ የሰው ያለህ ብለህ ትጮሀለህ። ሙሉ ኢትዮጵያውያን ተረባርበው ችግርህን ከፈቱልህ በኋላ ችግሩን የፈታሁት በዋናነት እኔ ነኝ ብለህ የብዙውን ድል ለጥቂት አካላት መስጠት ቁጥሩ ከውሸት ነው። የሰው መድኃኒቱ ሰው ነው። ሰው ብቻውን ምንም ነው። ብዙ ጊዜ ዘፈን እና ሽለላ ከእውነት ይልቅ ለስመት ይቀርባሉ። ስሜት ደግሞ ሁልጊዜ ትክክል ነው አይባልም። ስሜት በአእምሮ መመራት አለበት። ብዙ ነገሮችን ምን ውጤት ሊያመጡ እንደሚችሉ ሁሉ አስቀድሞ በንስር ዓይን ማየት ጥሩ ነው። በጥላቻ እና በቂም በቀል ታውረህ ነገን ሊያከብድብህ የሚችል ነገርን አታድርግ። ሁልጊዜም ለሁሉም ሰው ጥሩ የምትለውን አማራጭ ተጠቀም። ከጠባብ አስተሳሰብ ውጣ። ነጻነትህን ማንም አይንጠቅህ። በፍርሀት እና በይሉኝታ የማትፈልገውን ነገር አታድርግ። ምንም ይሁን ምን ግን ሁልጊዜም እውነትን ፍቅርን ያዝ። የሰው ልጅ መልካም ዘመናት የሚባሉት መከራን፣ ሽንገላም፣ መከዳትም፣ ስድብም...ወዘተ ነገሮች ሲደርሱበት ሳይቀር እውነትን እና ፍቅርን ይዞ የኖረባቸው ጊዜያት ናቸው። ቅዱስ ቂርቆስ በዚች ምድር ሦስት ዓመት ነው የኖረ ነገር ግን እውነትን እና ፍቅርን ይዞ መከራ የተቀበለባቸው ዘመናት ስለሆኑ ልዩ ናቸው። ፈያታዊ ዘየማን በሽፍትነት ነው የኖረ ነገር ግን ከብዙ የሽፍትነት ዘመኑ ይልቅ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ በተናገራት እውነት ምክንያት ገነት ገብቷል። የቀረህ እድሜ ትንሽ ብትሆን እንኳ በእርሷው ለእውነት ለመኖር ቆርጠህ ተነሳ። የሰው ልጅ አሸነፈ የሚባለው በእውነት ሲኖር ነው። ከፈጣሪ ሕግ ውጭ ያመጡት ድል የተሸናፊነት ውጤት ይባላል እንጂ አሸናፊነት አይባልም። የፈጣሪን ሕግ ይዞ ስለ እውነት መሳደድ፣ መገደል ግን አሸናፊነት ይባላል። ሰማእታትን አሸናፊዎች (መዋዕያን) የምንላቸው ለዚህ ነው። ከሐሰት ጋር ተስማምቶ ሺ ዓመት ከመኖር እውነትን ይዞ አንድ ሰዓት ቆይቶ መሞት ይሻላል።

በእውነት እንደሰት

በእውነት እንኑር

ለእውነት እንሙት

ለእውነት እንቁም

መልካምነት

መልካም ሥራ በዋናነት የሚጠቅመው ለሠሪው ነው። ክፉ ሥራም የሚጎዳው በዋናነት ክፉ ሠሪውን ነው። ቤተክርስቲያን በሐሳብ፣ በንግግር እና በድርጊት ክፉ አትሥሩ የምትለን ክፋት እንዳይጎዳን ነው።እያንዳንዷ መልካም ነገር ጥቅም እንዳላት ሁሉ እያንዳንዷ ክፋት ደግሞ ጉዳት አላት። ጉዳት የማያመጣ ክፉ ሥራ የለም። መልካም እየሠሩ በክፉዎች መሳደድ፣ መታሰር፣ መገደል ክርስቶሳዊነት ነው። ስሙም ሰማእትነት ይባላል። ክፉ ሠርተህ እንደ ሕጉ መታሰር ግን ትክክለኛ ፍርድ ነው። ንጹሕ ሆነህ ሳለ ሲያሳድዱህ ደስ ይበልህ። ምክንያቱም በዋናነት እስረኞች እያሳደዱህ ያሉት ናቸው። አንተ ግን ብትታሠርም ነጻ ነህ። የሰው ልጅ ፍቅር፣

ትክክለኛ ፍርድ፣ እውነት (ርትዕ)፣ ይቅርታ ከሌለው የሰይጣን የመሆን እድሉ ከፍተኛ ነው። አእምሮ የተሰጠን በነጻነት እውነትን ከውሸት እንድንለይበት ነው። ፈርተህ፣ ወይም ለሥጋዊ ፍላጎትህ ብለህ የማትቀበለው እውነት ሊኖር አይገባም። ለእውነት እስከሞት መድረስ ትልቅ እድል ነው። ከምንም በፊት ማንም እግዚአብሔርን ሊፈራ ይገባል። ከምንም በፊት ሰው ከቂም በቀል እና ከጥላቻ እንዲሁም ከዘረኝነት እስር ቤት መውጣት አለበት። በእግዚአብሔር ፊት የተሻለውን መንገድ ይምረጥ። የሰው መንጋ አንሁን። ያደነቅነው ያጨበጨብንለት ሰው ሲሳሳት እንዳናፍር ለማንኛውም ሰው ማሸቃበጥ አይገባም። እውነትን እንያዝ። በሚዛናዊነት ሰበብ ይሁዳ ጌታን መሳሙ ጥሩ ነበር። መሸጡ ግን ልክ አልነበረም ዓይነት አባባል አንጠቀም። የይሁዳ መሳም መጀመሪያውንም ለመሸጥ ነውና። መለኪያችን በብልጭልጭ ነገር ሳይሆን ኅብረታዊ ይሁን። እያንዳንዱን ሕዝብ ይጠቅማል ወይሥ አይጠቅምም የሚለውን ነው መገምገም።

ዕርገት

ሥጋ ክብርን ያገኘ እና የርኅቀት ያይደለ የርቀት ዕርገት ያረገ የጽንሰቱ ጊዜ መጋቢት 29 ነው። ከትንሳኤ በኑዋላ ደግሞ በ፵ኛው ቀን የርቀት ያይደለ የርኅቀት ዕርገት ዐረገ። ሊቃውንት በትርጓሜ የቃል ዕርገት በ፵ ቀን የሥጋ ዕርገት በማኅፀን ያሉት ለዚያ ነው።

የሰው ነገር

የሚወዱት ሰው በአደባባይ የክህደት ትምህርት ሲጽፍ እና አንተ ደግሞ ተው በሉት የጻፈው ክህደት ነው ብለህ ስትጽፍ መንጋው "ወንድምህ አይደለ እንዴ? በውስጥ አትመክረውም? እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ ይላል ከእናንተ ምን እንማር?" ይልሀል። አንዳንዱ ደግሞ ከሰውየው በላይ ሰውየውን አውቀዋለሁ ባይ "ተጠልፎበት ነው የእርሱ አይደለም" ይልሀል። የመንጋነት ጥግ። በነገራችን ላይ ጥቅስ ያለቦታው አይጠቀስም። በተቃራኒው የሚጠሉት ሰው በአደባባይ የክህደት ትምህርት ሲጽፍ እና አንተ ደግሞ ተው በሉት የጻፈው ክህደት ነው ብለህ ስትጽፍ መንጋው "መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ ቃለ ሕይወት ያሰማልን" ይልሀል። እውነታው ምንድን ነው? ስንል ማንኛውም ሰው ከእውነት በታች ነው። እውነት ደግሞ እግዚአብሔር ነው። አንድ ሰው እግዚአብሔራዊውን እውነት ሲክድ ዝም ካልክ አሸቃባጭ ነህ ማለት ነው፡ የሃይማኖትህ አስተምህሮ ቢጣስ ባይጣስ ጉዳይህ አይደለም ማለት ነው። ከሃይማኖትህ ይልቅ የሚያሳስብህ ግለሰብ ነው። ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን በመውደድህ ጣዖት አምላኪ ነህ። ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር በላይ መውደድ ጣዖት አምልኮ ነውና። ማቴ.10;33 "በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ"እንዲል። እንደ አኪላስ የባልንጀራነት ፍቅር አገብሯችሁ እግዚአብሔራዊውን እውነት ለማስተባበል የሞከራችሁ ሰዎችም ፈጣሪ ይቅር ይበላችሁ። የአደባባይ ክህደት በአደባባይ ይመለሳል። ምክንያቱም ክህደቱ እውነት መስሏቸው አንብበው የጠፉትን ሰዎች ለመመለስ ሲባል ነው። ሌላው ሰው ስህተትን እና ክህደትን መለየት አለበት። ስህተት በዳህፀ ልሳን ሆን ተብሎ ሳይሆን ባለማስተዋል ከድንገት የሚያመልጥ ንግግር ነው። ተናጋሪው ሆን ብሎ ተው እየተባለ ሦስት አራት ጊዜ ከጻፈው ግን ክህደት ይባላል። ትክክለኛ ሰው የሚባለው

አንድ ሰው መልካም ሲሠራ የሚያበረታታ ሲሳሳት ደግሞ ተው የሚል እና የሚገሥጽ ነው። የፍቅረ ቢጽ ትርጉሙ ይህ ነው። ሲሳሳት ዝም እያልን መልካም የሠራ ሲመስለን አጨብጫቢ ከሆንን ግን መንጋ ነን ማለት ነው። ሰውየውንም እንጎዳዋለን። መልካም ሲሠራ ዝም ብለን ክፉ ሲሠራ ብቻ የምንናገረው ከሆነ ደግሞ ጥላቻ አለብን ማለት ነው። ሁለቱም ልክ አይደሉም። የመጣው ሁሉ እንዳይወስደን የእናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት እንማር። እናታችንን እንወቃት። በመጨረሻም ቅዳሴ እየተቀደሰ እንዲሁም በጉባኤ የእግዚአብሔር ቃል እየተነገረ በመካከል መምህሩ የተናገራት ደስ አለችኝ ተብሎ facebook ገብቶ ካልፖስትኩ አይባልም። እግዚአብሔር እየተናገረ አንተ ወደ facebook ምን ያስሮጥሀል?? ከጉባኤ በኋላ ይደርሳልኮ።

ማተብ

ማተብ ማድረግ የተጀመረው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በያዕቆብ ዘእልበረዲ (ያዕቆብ ዘአልቦ ረዳኢም ይሉታል) በእርሱ ጊዜ ነው። እርሱ ሲያስተምር ያመኑትንና ያላመኑትን ለመለየት ላመኑት ማተብ ያደርግላቸው ነበር። ስለዚህ ማተብ የእኛ መለያ ነው። አንዳንድ ጋዜጠኞች ለፕሮቶኮል ብለው ማተባቸውን ያወልቃሉ። ግን ትልቅ ስህተት ነው።የእኛ መለያ ስለሆነ እምቢ ማለት አለብን። ማተብን የሚያስወልቅ ፕሮቶኮል ሰይጣናዊ ነው። የቤተክርስቲያንን ትምህርት እንማር። ክልማድ ሕይወት ወጥተን እንጠይቅ እናንብብ።

ነገረ መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ በሁሉ ቦታ ያለ ነው። ታድያ ለሐዋርያት ወረደ ማለት ምን ማለት ነው? ወረደ የሚለው በአካል በሁሉ ቦታ ላለ አይነገርምና። ወረደ ማለት ጸጋውን ሰጠ ተብሎ ይተረጎማል። ይህ ጸጋም ከአብ እና ከወልድ ተለይቶ የመንፈስ ቅዱስ ብቻ የሆነ የተለየ አካላዊ ግብር አይደለም። የሦስቱም ባሕርያዊ ግብር (ሥልጣናዊ) ግብር ነው እንጂ። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ጸጋ ዘአብ ያለውን ቅዱሳን ሊቃውንት ደግሞ በቅዳሴ ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ብለውታል። ባሕርያዊ ግብር ስለሆነ ሦስቱም ይጠሩበታልና። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል ወረደ ማለት ጸጋ ለሰው ተሰጠ ማለት ነው። ጸጋ መንፈስ ቅዱስን መንፈስ ቅዱስ ይለዋልና። ይህን ጸጋ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ተቀብላ እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚነሱ ሰዎች ስታድል ትኖራለች በዚህም ምክንያት የጸጋው ግምጃ ቤት ትባላለች። በነገራችን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ከምጽአት በኋላም እየተሰጠ ለዘለዓለም ይኖራል እንጂ አያልቅም። ይህንንም የመጻሕፍተ መነኮሳት መተርጉማን ተወስኮ ዘነሳእያን ይሉታል። መንግሥተ ሰማያትን ገንዘብ ላደረጉ ሰዎች እየተጨመረ የሚኖር ጸጋ ማለት ነው። ቤተክርስቲያን በዕለተ ጰራቅሊጦስ ተወለደች መባሉ ሙሉ ጸጋን አግኝታ ጸጋን የምትሰጥ ሆነች ለማለት ነው። ሐዋርያት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ካገኙ በኋላ ፈሪ የነበሩት የማይፈሩ ሆኑ። እስከሞት ድረስ እውነትን እየመሰከሩ የሐሰትን ሐሰትነቱን እየገለጡ ኖሩ። ሃይማኖት የራስን እውነት መናገር ብቻ አይደለም። የሌላውንም ስህተት ሳይፈሩ ስሕተትነቱን መናገር ነው። ቅዱሳን ሊቃውንት እነ ዮሐንስ አፈወርቅ የሚታወቁትም በዚህ ነው። እዉነትን በአደባባይ ይሰብካሉ። ውሸትን ደግሞ በአደባባይ ያጋልጣሉ። ሃይማኖተኝነት ይህ ነው። የአንተን እውነት ብቻ እየተናገርክ በሁሉ ዘንድ

መወደድ ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ውሽት በመናገር በብዙዎች ዘንድ መጠላትም አለበት። ዮሐንስ አፈወርቅ ግዞት የተፈረደበት የንግሥቲቱን ክፉ ስራ በማጋለጡ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ሲወርድ ጥቡዓን ሆኑ ማለት ይህ። ማንንም ሳይፈሩና ሳያፍሩ የውሸትን ውሸትነት የእውነትን እውነትነት በአደባባይ ገለጡ ማለት ነው። ይህንንም በማድረጋቸው ብዙው ሰው ይጠላቸው ይሰድባቸው ነበር። ያ ብቻ አይደለም ይገድሏቸውም ነበር።

ቅዱስ ሚካኤል

✿ ቅዱስ ሚካኤል የቅድስት ድንግል ማርያም ጠባቂ መልአክ ነበር።

✿ ዲያብሎስን በመዋጋት ቀዳሚው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ነው።

✿ ቅዱስ ሚካኤል በነገድ የኃይላት አለቃ ነው።

✿ እንደገና ደግሞ የመቶው ነገድ አለቃ ነው።

✿ መልአከ ምክሩ ለእግዚአብሔር ይባላል።

✿ እስራኤላውያን ከግብፅ ምድር ሲወጡ ፈርዖንን በኤርትራ ባሕር አስጥሞ ለእስራኤል ደግሞ ቀን ዋእዩ እንዳያስቸግራቸው ደመና ጋርዶ የረዳቸው መልአክ ሚካኤል ነው።

✿ ነቢዩ ዳንኤልን የረዳ መልአክ ነው።

✿ አፎምያን፣ ባሕራንን ሌሎች ቅዱሳንንም የረዳ ቅዱስ መልአክ ነው።

እኛንም የመልአኩ ረድኤት አይለየን። ከፍቅሩ ጽናት የተነሳ ይጠብቁን ዘንድ ቅዱሳን መላእክትን የሰጠን ልዑል እግዚአብሔር ይመስገን።

ዝናመ ምሕረት

በመልአከ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል በዓል ዝናመ ምሕረትን አገኘን። ሀገራችን በብዙ መከራ ውስጥ ናት። እስካሁን ዝናብ አልነበረም። ገበሬው አልዘራም። ነገር ግን ፈጣሪ አዛኝ መሐሪ ስለሆነ በዛሬው ዕለት አዝንቦልናል። በድጋሚ እንኳን አደረሳችሁ። ብዙ ሰዎች በዘረኝነት በጥላቻ ታመናል። የጥላቻ ፍሬ የሆነውን መገዳደልንም ተያይዘነዋል። እግዚአብሔርን መፍራት የለም። ሲጀምር ሰውን እንድንወድ ታዘዝን። ነገር ግን አልቻልንም። ነገር ግን መውደድ ባንችል እንኳ ለምን እንጠለዋለን። ለውጥ ከራሳችን እንጀምር። ልበ ሙሉ እንሁን። ከምንም በላይ የፈጠረን እግዚአብሔር አለንና። በእርሱ የድርሻችንን እንወጣ። የገበሬ ድርሻ ማረስ፣ መቆፈር፣ መዝራት ነው። ዝናብን ማዝነብ ማብቀል ማሳደግ ደግሞ የፈጣሪ ስራ ነው። የፈጣሪን ለፈጣሪ ሰጥተን የእኛን ድርሻ ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገን እንወጣ።

ክፉ ሐሳብ

Negative thinker መሆን በእያንዳንዱ ጉዳይ ሥር አሉታዊ ነገር ማመንጨት ሲሆን ከቅንዐት

ከምቀኝነት ሊመነጭ ይችላል። ዓላማ የለሽ ሰው አስተሳሰቡ አሉታዊ ነው። ማንም ቢሆን ትኩረት ማድረግ ያለበት ጊዜያዊ የሥጋ ደስታ ከሚሰጡት ላይ ሳይሆን ለዘለዓለማዊው ሕይወት የሚያበቁት ላይ መሆን አለበት። አእምሯችን የመልካም ሀሳቦች መኖሪያ እንዲሆንልን ከፈለግን ክፉ ሀሳቦችን መጀመርያ ጠርገን እናውጣ። የነገሮችን መልካም ጎናቸውን እየያዝን ክፉውን እየተውን እንንዝ። አንድን በግ እረኛዋ ከሆነ ነገር ሲከለክላት እርሷን ስለሚወዳት እንዳትጎዳበት በማሰብ ነው። ይህን ጊዜ በጊቱ የከለከላት መስሏት ተደጋጋሚ ሙከራ ታደርጋለች። ግን እውነታው ያ አይደለም። ወይም ደግሞ በጊቱን በውሻ ሊያስመልሳት ይችላል። ውሻው ከበጊት የከበረ ሆኖ አይደለም። በውሻው ምክንያት እርሷ ከዚያ እንድትታቀብ ነው እንጂ። ምእመናን አምሳለ በግዕ፣ ኖሎት አምሳለ ካህናት፣ ውሾች የኃጥዕ ምሳሌ ናቸው። ካህን በምእመናን በጭራሽ ሊናደድ አይገባም። ሊያዝንላቸው ሊራራላቸው ይገባል። ክፉ ቢሆኑንኳ ይህ ባለማወቅ ስለሆነ በጊቱ ያን መርዝ ያለው እፅ ካልበላሁ ብትል ይበላት ብለህ አትተዋትም። እየራራህ ሌላ የምትበላው እያቀረብክ ከዚያ እንድትርቅ ትጥራለህ። ከአንተ ቁጥጥር ውጭ ሆና ያን መርዛማ ቅጠል በልታ ስትሞት በጣም እዘንሃለሁ። የበጓ መሞት ለሥጋህ ምግብን ገንዘብን ስለሚያስቀር ያስቆጫል። የምእመናን ሞትም አንተ ሳታስተምረው ሲሞት የነፍስ ዋጋ ታገኝበት ነበርና ሲቀር ያሳዝናል። ከኃጥኣንም ቁም ነገር ይገኛል። ጌታም ቃሉን በኃጥኣን አድሮ የሚናገርበት ጊዜ አለ። በቀያፋ በበለዓም ለአባ እንጦስ እመሰ ኮንከ መነኮሰ ብለው አእኑስ ነግረውታል፡ ስለዚህ ማንኛውም ሰው ምንም ቃል ይናገር የእግዚአብሄር ሐሳብም ሊሆን ስለሚችል በትሕትና ስማው።

የዘመኑ እጮኛሞችና ባለትዳሮች

ሲጠራሩ ራሱ "የእኔ ማር፣ የእኔ ጣፋጭ፣ ሆዴ" ወዘተ ነው የሚባባሉ። በደንብ እዩትማ አጠራሩ ከከርስ ጋር የተያያዘ ነው። በከርስ ይጋባሉ፣ በከርስ ይፋታሉ። አጠራርን አዳም ይጥራት። ሚስቱን ማን እንዳላት ታውቃለህ? ሕይወቴኮ ነው ያላት። እሷም ጌታየ አለችው። ፍቅር በገንዘብ አይወሰን። በሚደርቅ አበባ እየታለላችሁ እስከመቼ?። ከማንም በፊት እግዚአብሔርን ውደዱ። ከእግዚአብሔር ሕግ የሚያስወጣ ፍቅር ፍቅር አይደለም። ከጋብቻ በፊት ግንኙነት አልተፈቀደም። ክብራችሁን ጠብቃችሁ ቆዩ።

ሐዋርያነት

ሐምሌ ፩ ቀን ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ጴጥሮስ ሰማዕትነት የተቀበሉበት መታሰቢያ ዕለት ነው። ሐዋርያነት እስከ ሞት ድረስ እውነትን መናገር ነው። ሐዋርያነት ንጉሡ ኔሮንን እንዳይከፋው ተብሎ እውነትን ባለመናገር መተባበር አይደለም። መከራን፣ሞትን ሳይሰቀቁ እውነትን በአደባባይ መናገር ነው። ሐዋርያነት ፍቅርን ትእግስትን፣ ትሕትናን መሠረት አድርጎ እውነትን በአደባባይ መመስከር ነው። እውነትን መናገር ብቻ ሳይሆን ውሸትንም በአደባባይ መቃወም ነው። ሐዋርያነት ሁሉን ትቶ መከተል ነው። ራሱ ቅዱስ ጴጥሮስ ጎደሜነ ኵሎ ወተሎናከ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ምንተ እንከ ንረክብ እንግዲህ ምን እናገኛለን ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ጠይቆት ነበረ። ቅዱስ ጴጥሮስ ምን ትቶ ተከትሎታል ቢሉ አንድ አህያ ነበረችው እርሷን ትቶ ተከትሎታል። ከምንም በላይ ግን "እከብር ባይ ልቡናን" ትቶ ተከትሎታል ብለው

መተርጉማን ይናገራሉ። ሐዋርያ የእግዚአብሔርን ቃል በደስታ የሚናገር ነው። እውነትን በአደባባይ የሚመሰክር ነው። ይህን በማድረጉ ሰዎች ሲጠሉት ሲሰድቡት እና መከራን ሲያደርሱበት በደስታ የሚቀበል ነው። ሐዋርያ ለክብረ ቤተክርስቲያን የሚኖር፣ ፈጣሪውን የሚፈራ፣ በሰው መወደድን እና መከበርን የሚጠላ፣ ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚሰጥ፣ ሁሉን እንደራሱ የሚወድ ፍቅር ያለው፣ ለራሱ ድኅነት እና ለሰዎች መዳን የሚተጋ ነው። የቅዱሳኑ ሐዋርያት በረከት ይደርብን።

ቅድስት ሥላሴ

ዓለምን ካለመኖር የፈጠሩ፣ ፈጥረውም የሚያስተዳድሩ ሥላሴ በአካል ሦስት ሲሆኑ በባሕርይ አንድ ናቸው።

√ በአካላዊ ግብር ሦስት ናቸው። በአካላዊ ግብር ስምም ሦስት ናቸው። ይህም ወላዲ አሥራጺ፣ ተወላዲ፣ ሠራጺ መባል ነው።

√ በሥልጣናዊ (በባሕርያዊ) ግብር አንድ ናቸው። በባሕርያዊ ግብር ሥምም አንድ ናቸው። ይህም አምላክ፣ ፈጣሪ፣ እግዚአብሔር ወዘተ የመሳሰለው ነው።

√ በከዊን ሦስት ናቸው። እኪህም ቃል መሆን፣ ልብ መሆን፣ እስትንፋስ መሆን ናቸው። በዚህም ሥላሴ ነባብያን፣ ሕያዋን፣ ለባውያን መሆናቸውን እናውቃለን።

√ በባሕርይ አንድ ናቸው። ይህም ማለት የሦስቱ ኩነታት ተገናዝቦ አንድ ሕይወተ አንድ ባሕርይ ይባላል።

√ በአካል ሦስት ናቸው። በአካል ሥምም ሦስት ናቸው። ይህም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ መባል ነው።

መልካም ወጣት

መልካም ወጣት መሆን ከፈለጉ

- ፩) ግቢ ጉባኤ ይማሩ
- ፪) ሰንበት ትምህርት ቤት ገብተው ይማሩ
- ፫) ወደ መንፈሳዊ ኮሌጆች ገብተው ይማሩ
- ፬) ወደ አብነት ትምህርት ቤቶች ገብተው ይማሩ

በጠቅላላው ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ፣ መምህራንን በመጠየቅ፣ የሠርክ ጉባኤያትን በመከታተል፣ ቅዳሴ በማስቀደስ፣ በመጾም፣ በመጸለይ እና በመሳሰሉት መልካም ወጣት መሆን ይችላሉ። ከከሓዲ ተምረው ታማኝ መሆን አይቻልም። የዲያብሎስን ትምህርት ሰምተው ቅዱስ የሆኑ የሉም። ሁሉም አጋንንት ሆኑ እንጂ። ስለዚህ በፍርኖ ዳቦ እና በሻይ እያታለሉ መልካም

ወጣት እናድርግህ ያለውን መከተል አይገባም። መልካም ፍሬ የሚያፈራ መልካም ዛፍ ነው። ከክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ መጠበቅ ትልቅ ጅልነት ነው። ከየግቢ ጉባኤው ለክረምት ወደየቤተሰቦቻችሁ ስትሄዱ ሕጻናትን ወጣቶችን እየሰበሰባችሁ የተማራችሁትን አስተምሩ።

ሦስቱ መስማት የተሳናቸው ሰዎች

አለቃ አያሌው ከጻፉት መጽሐፍ ያገኘሁት ነው። ሦስት ደንቆሮዎች በአንድ ሰፈር ይኖሩ ነበር። እና አንድ ቀን አንዱ ደንቆሮ ፍየል ትጠፋዋለች። እና ፍየሉን ሲፈልግ አንዲት ደንቆሮ ሴት ልጅ አዝላ አረም ስታርም ያገኛታል። እና "ፍየል አየሽ ወይ?" ብሎ ይጠይቃታል። እርሷ ግን መስማት ስለማትችል "አረም እንዴት ነው?" ብሎ ይሆናል የጠየቀኝ ብላ በእጇ ያረመችውን እየጠቆመች "ይህን ይህን አርሜያለሁ" ትለዋለች። ጠያቂውም መስማት ስለማይችል "ፍየሏ በዚያ በኩል ነው የሄደችልህ" ያለችው መስሎት በጠቆመችው ቦታ ስሄድ ፍየሉን ተሰብራ ያገኛታል። ከዚያ የተሰበረች ፍየሉን ይዞ ወደምታርመዋ ደንቆሮ ይሄዳል። ከዚያ "በጠቆምሽኝ ጥቆማ መሠረት ፍየሌን አግኝቻታለሁ። ስለዚህ ለእኔ ብዙ ፍየሎች ስላሉኝ ይችን የተሰበረችዋን ፍየል ያገኘኋት በአንቺ ጥቆማ ስለሆነ ለአንቺ ሸልሜሻለሁ ለአንች ይሁንሽ ይላታል" ። ከዚያ እርሷ ደግሞ አንቺ ነሽ የሰበርሽው እያላት መስሏት "እኔ አልሰበርኩም እያለች" ስትመልስለት ይቆያሉ። ሁለቱ ማለትም ፍየል የጠፋው ደንቆሮ እና ልጅ አዝላ አረም ታርም የነበረችው ደንቆሮ እየተከራከሩ ሳለ ሌላ ሦስተኛ ደንቆሮ ይመጣል። እና የተጣሉት ባዘለችው ልጅ ምክንያት መስሎት ፍየል ለጠፋው ደንቆሮ "አንተ ልጅ አትከራከር ይህ ያዘለችው ልጅ መልኩ ቁርጥ አንተን ስለሚመስል የአንተ ልጅ ነው እመን" አለው ይባላል። ሀገሬን የገጠማት እንዲህ ዓይነት ነገር ነው። መሬት ላይ ካለው እውነት ይልቅ ብዙው የየራሱን ይመስለኛል እውነት አድርጎ ነው እየኖረ ያለው። የራሱ መሰለኝ እያሳደደው ያለ ብዙ ሰው አለ። ከመሰለኝና ከግምት ዓለም እንውጣ።

ለእውነት እንሙት

በእውነት እንኑር

ጽድቅ ትመውዕ (እውነት ታሸንፋለች)

ወታደር

"ሀገርን ከውጭ ወራሪ ከውስጥ ባንዳ መጠበቅ መልካም ነው። ወታደር የሌላውን ሕይወት ለመጠበቅ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ነው። ይህ ደግሞ የፍቅር ትርጓሜ ነው"።

ፍቅር፣ መስቀል፣ ማማተብ

የክርስትና መሰረቱ ፍቅር ነው። ፍቅር ደግሞ እግዚአብሔር ነው። ፍቅር ያለው ሰው ደግሞ የሰውን ዘር ሁሉ ይወዳል። መውደድም ሲተረጎም ክብር መስጠት፣ ማክበር፣ ለእኛ ሊያደርጉልን የምንፈልገውን ለሌሎች ማድረግና ሲደረግላቸው መደሰት ነው። በእኛ ሊሆንብን ሊደረግብን የማንፈልገው ነገር በሌሎች ሲደርስባቸው በእኛ እንደደረሰ አስበን ማዘን ነው።

ሐዋርያው ካዘኑት ጋር እዘኑ ከተደሰቱት ጋር ደስ ይበላችሁ ያለው የፍቅር መሠረታዊ ትርጉም ነው። ፍቅርን በተግባር ያሳየን ቃለ አብ ቃለ መንፈስቅዱስ ወልድ ነው። ያዘነ አዳምን ለማዳን የሚያዝን የሚተክዝ ሰውነትን ገንዘብ አደረገ። የአዳምን ጸሎት ጸለየ። እንደ አዳም በመሆኑ ዳግማዊ አዳም ተባለ። እርሱ አምላክ ሆኖ ሳለ የአዳምን ጸሎት "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ" ብሎ ጸለየ። የአዳምን መከራ በመስቀል ተሰቅሎ አራቀለት። መስቀሉን ስናይ፣ ስናማትብ የክርስቶስ ፍቅር በልባችን የሚሞላው ለዚያ ነው። ክርስቶስ ፍቅርን ሲያስተምር "ራስን ስለ ሌላው አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ፍቅር የለም" ብሎ ነበር። ይህን ትምህርቱን አዳምን ለማዳን ስለ አዳም በመስቀል ተሰቅሎ አሳየን። ይህንን ያስተዋለው ሌላኛው ሊቅ "ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት" ብሎ አመሰጠረው። ሰይጣን መስቀልን ይጠላዋል። ምክንያቱም ሰይጣን ማለት መስተቃርን ማለት ነው። መስቀል ፍቅር የተገለጠበት ነው። ሰይጣን ደግሞ ጥላቻ ስለሆነ ነው። ሰይጣን መስቀለኛ ነገርን ባየ ቁጥር አይወድም። ስናማትብ እልፍ አእላፋት አጋንንት ወደ ኋላ ይወድቃሉ። መስቀል ሞቶ ማሸነፍ የተገለጠበት ነው። መስቀል የይቅርታ አደባባይ ነው። የሰይጣን ዋና ዓላማ ሰዎች ተጣልተው እንዲኖሩ ነው። ይቅርታ የፍቅር ፍሬ ነው። እግዚአብሔር አዳምን ስለሚወደው በደሉን ይቅር ብሎ አድኖታል። ብዙ ተጎዳድተን ይሆናል። ነገር ግን ጉዳታችንን ሳናስብ መታረቅ የፍቅር ትርጓሜ ነው። መታዘዝ፣ ትእግስት፣ ትሕትና፣ እውነተኛነት እና ትክክለኛ ፍርድ የፍቅር ትርጓሜዎች ናቸው። በፍቅር ግላዊነት የለም። ወኢንጎድግ ማኅበረነ እንዲል አንዱ ስለሁሉ የሚያስብበት ሁሉ ስለአንዱ የሚያስብበት ነው። ለማኅበረ ምእመናን ክብር ይኑረን። ፍቅር ራስን ስለ ሌላው አሳልፎ መስጠት ነው እንጂ ሌላውን ስለ ራስ አሳልፎ መስጠት አይደለም። ፍቅር ከራስ ወዳድነት መራቅ ነው። ፍቅር ሁለት ነው። አንዱ ከምንም በፊት እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዙን በተግባር መፈጸም ነው። ሁለተኛው ሰውን መውደድ ማክበር ነው። እርስ በእርሳችን እንዋደድ። ምቀኝነትን ቅንዐትን እናስወግድ። እውነት፣ ፍቅር፣ ቅንነት፣ ትክክለኛ ፍትሕ አይለዩን። እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ከንቱ ውዳሴን ይጠላል። ምክንያቱም ምስጋና የሚገባው ለእግዚአብሔር እንደሆነ ያውቃልና። ምስጋናን ሁሉ ለፈጣሪ ይሰጣል። ፍቅር ያለው ሰው አይታበይም። እርሱን ከምንም ፈጥሮ ያከበረው እግዚአብሔር እንጂ እርሱ ምንም መሆኑን ይረዳልና። ፍቅር ያለው ሰው በነገሩ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ሥራንም ይሰራል።

ቅዱስ ገብርኤል

√ ሳጥናኤል ባመፀ ጊዜ መላእክትን በያለንበት እንቁም ብሎ ያረጋጋ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ነው።

√ ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ያዳናቸው ይህ መልአክ ነው።

√ ለሰው ሁሉ የምሥራች የሆነውን የጌታ መጸነስ ለድንግል ማርያም ያበሰረ መልአክ ነው።

√ ሕጻኑ ቅዱስ ቂርቆስንና እናቱን ቅድስት ኢየሉጣን የረዳቸው መልአክ ይህ ነው።

√ ቅዱስ ገብርኤል መልአከ ሰላም፣ መጋቤ ሐዲስ ይባላል። እኛንም ሀገራችንንም ከመከራ ያድነን።

መስቀል አደባባይ

ይቅርታ የታወጀበት

ፍቅር በተግባር የተገለጠበት

እውነት ከሁሉ ከፍ ብሎ የታየበት

ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን በዓለም ተሰደበ፣ በዓለም ተሰቀለ። ልታድኑት የምትፈልጉት ሕዝብ ሊሰድባችሁ ሊሰቅላችሁ ይችላል። በጨለማ ላለ ሕዝብ ብርሃንን ይዘህ ስትቀርብ በጨለማ ያለው ሕዝብ ወደ ግብጽ ሊያሳድድህ ይችላል። ሕዝብህ ምንም ቢጠላህና ቢሰድብህ ግን ለሕዝብህ መልካም ማድረግን አትተወው። እስኪሰቅሉህ ድረስ መልካም ማድረግህን ቀጥልበት። ሁልጊዜም ዕለተ ስቅለትን እናስባት። እኛን ለማዳን ክርስቶስ ተሰቀለ ምን ዓይነት ፍቅር ነው!! ሕይወት ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ወደራሱ አቀረበን። ሕይወትን ሰጠን። መንፈሳችንን ቀደሰው። ሰው ሞቶ አይቀርም። ትንሣኤ አለው። ሰው ዘላለማዊ ነው። በዚህ ምድር የምንኖረው ኑሮም ለዘላለማዊው ሕይወት የሚያበቃንን ሥራ እንድንሠራበት ነው። ቅዱሳን በዚህች ዓለም ቆይታቸው ለዘላለማዊ የደስታ ሕይወት የሚያበቃ ሥራን ሰሩባት። የፀሐይ መውጣት የመወለዳችን ምሳሌ፣ ስታበራ መዋሏ በዚች ዓለም ለጥቂት ዓመታት የመኖራችን ምሳሌ፣ ማታ በምዕራብ መጥለቋ የመሞታችን ምሳሌ፣ መልሳ ጠዋት መውጣቷ የትንሣኤያችን ምሳሌ ነው። በክፉ አስተሳሰብ ያለን ሰዎች ለባለፈው ንሥሓ ገብተን ትንሣኤ ልቡናን ገንዘብ እናድርግ። አዲስ ሕይወት አዲስ ልብ ገንዘብ እናድርግ። ሰማያዊ ዓላማ ይኑረን። የኑሮ መርሐችን/ቀመራችን የእግዚአብሔር ቃል ይሁን። አጥፍተን ይሆናል። በድለንም ይሆናል። እግዚአብሔር በመስቀል የተሰቀለለትን ሰው አስቀይመንም ይሆናል። የእግዚአብሔርን ሕግ በመሻር ኖረንም ይሆናል። ነገር ግን ያለፈው ዘመን ይበቃናል። ላጠፋነው ይቅርታ እንጠይቅ። ለወደፊቱ እንደ ሕገ እግዚአብሔር እንኑር። የፈጣሪ ሕግ ለእኛ ፍኖተ ሕይወት ነው። ለዓለም የሚጠቅም ነው። ባጎር ሰሎሞን በመጽሐፉ "ከንቱ ከንቱ ኩሉ ከንቱ" ብሏል። እውነትም በዚህ ምድር ያለ ነገር ሁሉ ከንቱ ነው። ኃላፊ ነው። የማያልፍ ሰው ነው። በሚያልፍ ነገር የማያልፍ ሰውን ማስቀየም አይገባም። መጣላት፣ መገዳደል፣ መሰዳደብ፣ አይገባም። የእግዚአብሔርን ቃል በመናገርህ ስትሰደብ፣ ስትገደል ግን ደስ ይበልህ። ሰማእትነት ነውና። እውነትን በመናገርህ የምትሞትንኳ ብትሆን ሙት። ለእውነት መሞት፣ በእውነት መኖር የክርስቲያን የኑሮ ቀመሩ ነው። እውነትን በፍቅር ፍቅርን በእውነት መያዝ ይገባል። የሰውን ልጅ ስሜት ሊገዛው አይገባም። ከስሜቱ በላይ ሆኖ ስሜቱን በእውነት የሚገራ መሆን አለበት። የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እንወቅ። በነጻነት እናስብ። ቤተ ክርስቲያንን የሚፈትኗ ብዙ አጭበርባሪዎች አሉ። እነርሱን እስኪለዩ ድረስ መታገል ይገባል። ሐሰተኛ አጥማቂያን፣ ሐሰተኛ ነቢያት፣ ሐሰተኛ መምህራን፣ ሐሰተኛ መነኮሳት፣ ሐሰተኛ ባሕታውያን በዝተዋል። በእነርሱ እንዳንታለል የእናታችንን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እንወቅ።

ዕለት ኅሪት (የተመረጠች ቀን)

√ ዓለምን ፈጥሮ ያረፈባት ቅዳሜ የተመረጠች ቀን ናት

√ ዕለት ኅሪት ንሥሓ የምንገባባት ቀን ናት።

√ ዕለት ኅሪት የክርስቶስን ሥጋውን ደሙን የተቀበልንባት ቀን ናት።

√ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጸነሰባት፣ ትንሣኤ የሆነባት ዕለተ እሑድም ዕለት ኅሪት ናት።

√ በመስቀል ተሰቅሎ ዓለምን ያዳነባት ዕለተ ዓርብም ዕለት ኅሪት ናት።

√ ዕለት ኅሪት ክርስቶስ ከድንግል ማርያም የተወለደባት ዕለተ ማክሰኞ ናት።

√ ዕለት ኅሪት ክርስቶስ ሥጋውን ደሙን የሰጠባት ዕለተ ኃሙስ ናት።

√ ዕለት ኅሪት መልካም ሥራ የሰራንባት ዕለት ናት።

ሰውን ማክበር

ሰውን እናክብር፣ ሰውን እንውደድ፣ እግዚአብሔር ያዘዘንን ትእዛዝ በደስታ እንስራ። ፍቅር ይኑረን። በእኛ ሊደረግብን የማንፈልገውን ነገር በሌሎች አናድርግ። ወይም በሌሎች እንዲደረግ አንፈልግ። ለእኛ ሊደረግልን የምንፈልገውን እኛም ለሌሎች እናድርግ። አንደበታችን ቁጥብ ይሁን። ከአፋችን ስድብ አይውጣ። እግዚአብሔርን እናመስግን። እንደ አይሁድ አንሁን። አይሁድ እግዚአብሔርን እንወዳለን ብለው እግዚአብሔርን ሰቀሉት። ለራሳቸው ሥጋዊ ጥቅም ብለው እየሰሩ እግዚአብሔርን እያገለገሉ ይመስላቸው ነበር። እከብር ባይ ልቡናን እንተወው። የብዙዎቻችን ችግር እንደ አይሁድ መሆናችን ነው። ለቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ አሳቢ ነን ብለን እናስባለን። ነገር ግን ጳጳሳትን፣ ካህናትን፣ መምህራንን፣ ምእመናንን ስንሳደብ እንውላለን። አይሁድም ለእግዚአብሔር ሕግ የቆሙ አድርገው ራሳቸውን ስላዩ ችግር ውስጥ ገቡ። ለእግዚአብሔር ሕግ እንቆማለን ብለው እግዚአብሔርን ሰቀሉት። ተነበይ ለነ ክርስቶስ መኑ ጸፍዐከ እያሉ ሰደቡት ተዘባበቱበት። ትሑት ስብእናን እንያዝ። ፍቅር፣ ትሕትና፣ እውነት፣ ሰውን አክባሪነት፣ ታዛዥነት ሳይኖረን እግዚአብሔርን እንወዳለን ማለት ውሸት ነው።

ጾም

አክሱማዊው መልአክ ዘበምድር ቅዱስ ያሬድ "ጾም ትፈውስ ቁስለ ነፍስ ጾም የነፍስን ቁስል ታድናለች" ካለ በኋላ "ትሜህሮሙ ጽሙና ለወራዙት" ይላል። ጾም ለወጣቶች ጽሙናን፣ እርጋታን፣ ዝምታን ታስተምራለች አለ። ፯ሚ ሰው ከስሜቱ በላይ ይሆናል። ስሜቱን ይመራዋል እንጂ ስሜት አይመራውም። የራሱ ገዥ ይሆናል። በጾም ክፉ ሐሳብ ይሸነፋል። ንጹም ጾመ ጾምን እንጹም። ወናፍቅር ቢጸነ ባልንጀራችንን እንውደድ። ሰባቱን የቤተ ክርስቲያን የአዋጅ አጽዋማት እንደ ሥርዓታቸው እንጹም። የፍልሰታ ጾም፣ የገና ጾም፣ የሐዋርያት ጾም፣ የነነዌ ጾም፣ እና ጾመ ድኅነት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ይጾማሉ። ሕገ እግዚአብሔርን እንጠብቅ፣

ሥርዓት ይኑረን፣ ሰውን ማፈር እግዚአብሔርን መፍራት ይኑረን። በሰባቱ የጸሎት ጊዜያት እንጸልይ።

አንድነት እንዴት ይምጣ???

የአንድነት መሠረቱ ልዩነት ነው። ለምሳሌ ዓይን፣ ጆሮ፣ እግር፣ እጅግ አጠቃላይ የሰውነት አካሎቻችን ልዩ ልዩ ናቸው። የእነርሱ አንድነት ማሰብ ማሰላሰል መሮጥ ማየት መስማት መቅመስ ማሽተት የሚችል አንድ ሰውን ያመለክታል። ወይም በሌላ እይታ አንዱ ሰው የተለያዩ ሕዋሳት አሉት። የሕዋሳት መለያየት ግን ለአንዱ ሰው ጥቅም እንጂ ጉዳት አይደለም። ዓይንና እግር የተለያዩ ናቸው። ዓይን እግርን አታስፈልገኝም ልትለው አይገባም። ዓይን አውሬ ብታይ ከአውሬው ለማምለጥ እግር ያስፈልጋታል። እግር እሾህ እንዳይወጋው ዓይን ታስፈልገዋለች። እግር የሌላት ዓይን ሽባ ናት። ዓይን የሌለው እግር እውር ነው። አንድ እንሁን አንድነት ጥሩ ነው ስንል ማንነታችንን እንተው ማለታችን አይደለም። ዓይን እጅ እግር በአንድ ሰውነት ሲኖሩኮ ዓይን ዓይንነቱን ለቆ ጆሮም ጆሮነቱን ለቆ እግርም እግርነቱን ለቆ አይደለም። የራስን ማንነት እንደያዙ የሌላውንም እንደ ራስ ማየት ነው።የሌላው መጎዳት የራስ ጉዳት እንደሆነ መረዳት ነው። ስለዚህ ሁሉም የሰውነት ክፍሎች ጤንነታቸው ይጠበቅ ዘንድ ሁሉ ለእያንዳንዱ እያንዳንዱ ለሁሉ መኖር አለበት። የሰው ልጅ እንደ መልኩ ሁሉ በአስተሳሰብ በአኗኗር የተለያየ ነው። በሁሉም ነገር መስማማት ላይጠበቅብን ይችላል። ነገር ግን ልዩነቶቻችንን ለመፍታት በርቀት ከመጠዛጠዝ እና በሰማነው መረጃ ብቻ ተንተርሰን እይታችንን ከምናበላሽ ይልቅ የፊት ለፊት ውይይቶችን መልመድ አለብን። ፊት ለፊት ስንነጋገር ውሸታም ያፍራል። በግምት ከመጎዳት ፊት ለፊት ማውራት ይገባል። የአንድነት መሰናክሎች የራሳችን የፍላጎት መረን የለሽነት እና አሉሽ አሉሽ ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አንድነታችንን አንተው ብሏል። በክርስትና ትምህርት ሰው ሕብረታዊ ነው። ክርስቶስ የወይን ግንድ ሆኖ እኛ ደግሞ ቅርንጫፎች ነን። ስለዚህ ከክርስቶስ ጋር ያለን አንድነት እና ከምእመናን ጋር ያለን አንድነት መልካም ሊሆን ይገባል። ፍርድ ስንሰጥ ደግሞ የአንድ ወገን መረጃ ብቻ ተቀብለን መሆን የለበትም። ጉዳዩን ከባለጉዳዩ መስማትም ይገባል። አለበለዚያ ፍርዳችን አድሎ ያለበት ሰይጣናዊ ፍርድ ይሆናል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ግላዊ ችግራቸውን በተቋም ለማሳበብ፣ ግላዊ ቂማቸውን በተቋም ሥም የሚወጡ ሰዎች ይኖራሉ። ስለዚህ ብዙ ጉዳዮችን ሰፋ አድርገን ለማየት እንጣር። ከአንድ ሰው ጋር በሆነ ነገር አልተስማማህም ማለት ከተቋሙ ጋር አልተስማማህም ማለት አይደለም። ሰዎች ተቋምን ለግል ዓላማ መጠቀሚያ እንዳያደርጉት ተቋምን መጠበቅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ተቋም የአንድነት ፍሬ ነውና። ሰይጣን የሚሸነፈው በመስቀልና በፍቅረ እግዚአብሔር ነው። አንድም በስመ እግዚአብሔር ነው። በጠላታችን በሰይጣን እንወቅበት። ፍቅርን እውነትን ትሕትናን ይዘን በረድኤተ እግዚአብሔር ድል እናድርገው።

የሰይጣን ፕሮፖጋንዳ

በፕሮፖጋንዳ አቋማቸውን የቀየሩና የነበሩበትን ጠንካራ ምሽግ ትተው ወደተሳሳተ ወጥመድ የገቡ ብዙ ናቸው። እውነታው አንድ ነው። ሃይማኖት አንዲት ናት ኤፌ.4፥4። ነገር ግን

ከዚያች ሃይማኖት የሰው ልጅ ይሸሽ ዘንድ እና ሰይጣን ወደፈለገው ዓላማ ያፈገፍጉ ዘንድ ሰዎች ያሉበትን ጠንካራ ምሽግ ሃይማኖት እየተው ወደ ክህደት ጫካ የገቡ ብዙ ናቸው። ለዚያ ነው ቅዱሳን የሰይጣንን ፕሮፖጋንዳ ሳይፈሩ ፊት ለፊት ቢጋፈጡት ሰይጣን ራሱ እየጮኽ ይሸሻል። ካለንባት ጠንካራ ምሽግ ርትዕት ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አናውጦ ወደ ክህደት ጫካ በርእዮተ ዓለም ታሽጎ የመጣ የሰይጣን ፕሮፖጋንዳ ሊያታልልለን አይገባም። ከቤታችን ሆነን ጠላት ሰይጣንን እስከመጨረሻው መታገል ያስፈልጋል። ከሰይጣን ጋር በሚደረግ ጦርነት ብትሞትም ሰማዕት ነህ። አሸናፊ ነህ። ነገር ግን ከሰይጣን ጋር በሚደረግ ጦርነት ቤትህን ለቀህ ብትኖርም የሞትክ ነህ። ከሸሸህበት ሆነህ ብትሞትም ያው የሰይጣንን ምርኮኛ ነህ። ለዚያ ነው ሰይጣን ዋና አቅሙ ፕሮፖጋንዳ ነው። በዚያ ካለህበት ጥሩ ቤትህ እንድትወጣ ይጥራል። ይህን ጊዜ አንተ ማድረግ ያለብህ እንደሰይጣን የውሸት ፕሮፖጋንዳ መንዛት ሳይሆን በእውነት ላይ የተመሠረተ ትግል ነው። ለአንተ ረዳት ቅዱሳን መላእክት አሉህ። በእርግጥ ሰይጣን ለፕሮፖጋንዳው ትንሽ እውነትን ሊጠቀም ይችላል። ያ እውነታ ግን ለእርሱ ዋና ውሸት ፊታውራሪ እንጂ ዋና አይደለም። ወይም ከዓውድ ውጭ እየዋሸ ይጽፋል። ለጌታ እንደጠቀሰው ያለ። ወይም የእርሱን ልጆች እንዲያሸብሩ ይልካል። ሰይጣንን እየተዋጋን ነው ብለው የሚያስቡ ትልልቆችን በትእቢትና በደንበኛ ትንታኔ ይወጥርና ሌላውን አሳንሰው እንዲያዩ እያደረገ ከፍቅርና ከትሕትና ይጋርዳቸዋል። ክርስቶስ ከሙታን ተነስቶ እያለ አልተነሳም የሚል የውሸት ፕሮፖጋንዳ ይለቃል ሰይጣን። በዚህም ብዙዎችን እያሸበረ ከሀይማኖት አስወጥቶ በጫካ ክህደት አስገብቷል። በውሸት ጀግና ያልሆኑትን የጀግንነት ስም ሰጥቶም ዋና ጀግኖችን ሰውሯል። ከንቱ ውዳሴ በሠርጎ ገቦች እንድትታወቅና በአጭር ስትታገል እንድትሞት ለጠላት ሰይጣን ጥሩ መረጃ መስጠት ነው። ከባቴ አበሳ ራስን ዝቅ ማድረግ እና ተርእዮ አለማብዛት ግን በጭንቅ ጊዜ ወገንን ከጥፋት የሚያድንና ለጠላትም ኪሳራ ነው። ሰላዮች እንዳያውቁት አስቀድሞ ራሱን ደብቆ ነው የኖረውና። ምሥጢር ጠባቂነት ለዚህ ይጠቅማል። የሰይጣን ፈተና ውስብስብ ነው። ከእርሱ ወጥመድ ለመዳን ዋናው መፍትሔው ኦርቶዶክሳዊ መሆን ነው። ረድኤተ እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ነው።

የፍቅር ትርጓሜ

ፍቅር የአንዱን ድካም አንዱ ሲሸከም ነው። ሰማዕትነት የሌለበት ፍቅር ፍቅር አይባልም። በአፍ ብቻ እወድሃለሁ እወድሻለሁ ማለት ውሸት ነው። ይህንንስ ባላገሩ "የአፍ ዘመድ ከገበያም አይገድ" ብሎ ተርቶበታል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐ. ፲፭፣፲፫ "ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" ብሎ የፍቅርን ትርጓሜ አስተማረን። ፍቅር በአፍ የሚናገሩት ብቻ አይደለም በሕይወት የሚኖሩትም ነው እንጂ። ለዚያም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን በቃል ከተናገረ በኋላ በተግባር ደግሞ አዳምን ለማዳን በመስቀል የተሰቀለ። መስቀል ፍቅር በተግባር የተገለጠበት አደባባይ ነው። ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት ብሎ ሊቁ የገለጠው ይህንን ነው። ፍቅር ራሱ እግዚአብሔር ነው። ፩ኛ ዮሐ.፬፣፰-፳ "ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና----ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው" ይላል። ይህ የሚነግረን በፍቅር ጥላቻ እንደሌለ ነው። ፍቅር ሌላውን እንደ ራስ መውደድ ነው። ማቴ.

፮፣፲፪ "ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው" ተብሎ እንደተጻፈ ሰውን መውደድ በእኛ ሊደረግብን የማንፈልገውን በሌላውም እንዲደረግ አለመፈለግ ሲሆን እግዚአብሔርን መውደድ ደግሞ ትእዛዙን በመፈጸም ይገለጣል። ዮሐ. ፲፬፣፳፩ "ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው" እንዲል። ማቴ. ፮፣፳፩-፳፫ "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን ይሉኛል። የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብየ እመሰክርባቸዋለሁ" እንዲል የጌታን ስም ብዙ ጊዜ ብትጠራ፣ በስሙ ተአምራትን ብታደርግ፣ በስሙ ትንቢትን ብትናገር፣ በስሙ አጋንንትን ብታወጣ ይህ የፍቅር ምልክት ተደርጎ አይያዝም። እግዚአብሔርን የመውደድ ዋናው ምልክቱ ፈቃዱን መፈጸም ነው። ፈቃዱ ምንድን ነው ከተባለ ዘጸ. ፳፣፭ ጀምሮ ያሉ አስሩን ሕግጋት መፈጸም ነው። ማቴ. ፲፱፣፲፯ "ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ" እንዳለ። ዮሐ. ፲፬፣፱ "ትእዛዙም የዘለዓለም ሕይወት እንደሆነች አውቃለሁ" እንዲል። ቅዱስ ጳውሎስ ፍቅርን ጠቅለል አድርጎ ሲያቀርበው እንዲህ ብሎታል። ፩ኛ ቆሮ. ፲፫፣፩-፰ "ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ድኾችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም። ፍቅር ይታገሣል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፣ ፍቅር አይቀናም፣ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፣ የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ በደልን አይቆጥርም፣ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለዓመፃ ደስ አይለውም። ሁሉን ይታገሣል፣ ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም" ብሎ ገልጾታል።

ደብረ ታቦር

ማቴ. ፲፯፣፬ "ጌታ ሆይ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው"። ደብረ ታቦር የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነው። በቤተክርስቲያን መኖር ለእኛ መልካም ነው። እግዚአብሔር ምሥጢረ መለኮቱን የሚያሳይባት ቅድስት ደብረ ታቦር ቤተ ክርስቲያን ናት። በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መኖር ለእኛ መልካም ነው። ቤተ ክርስቲያን የሕይወት ትምህርት የሚሰጥባት ናት። ሕይወታችን የተስተካከለ ይሆን ዘንድ በቤተ ክርስቲያን መኖር ለእኛ መልካም ነው። በእውነት በአንድነት በፍቅር መኖር ለእኛ መልካም ነው።

እረኛዬ

እረኛዬ ያላስለቀሰው ሰው ካለ ጤነኛ ነው ብየ አላስብም። እስኪ አስቡት ጥልን ለመቋጨት አንተ ሙተህ ለሌላው አንድነትን ፍቅርን መስጠት አያስገርምም ነው የምትሉ? አንድ ባለቅኔ የተቀኙት አንድ ቅኔ ትዝ አለኝ። ቅኔው ሚበዝኑ ይባላል። እና ምን ይላሉ መሰላችሁ "በይነ ጣዕዋሃ ሐንካስ ትትበላእ ላሕም አምስጦ ዘይትከሃላ" ብለው ይጀምራሉ። ትርጉሙ "ስለ አንካሳ ጥጃዋ ብላ ማምለጥ የምትችለው ላም (በአውሬ) ትበላለች" እንደማለት ነው። ላሚቱ አንካሳ

ጥጃዋን ስለምትወድ ጥጃዋን ለማዳን እርሷ ትበላለች። እረኛዬ ይህንን ነው ያስተማረን ስለ ሕዝብ አንድነት እና ፍቅር ራስን እስከ ሞት ማድረስ ድንቅ ነው። በአሁኑ ዘመን ሌላውን መሥዋእት አድርጎ ራሱን ማዳን የሚፈልግ ትውልድ ነው ያለ። እረኛዬ ግን ራስን ለሌሎች መዳን ሲሉ አሳልፎ መስጠትን በተግባር አስተምሮናል። እረኛዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በእርሱ ደም መፍሰስ ከፈጣሪው ተጣልቶ የነበረው አዳም ታረቀ። የፍቅር ትርጉሙ ራስን ለሌላው ሲሉ አሳልፎ መስጠት ነው። ዮሐ. ፲፣፲፩ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ" ብሏል። የእረኛቸውን ሞት እያሰቡ ሰማእታት ራሳቸውን ለስለት አሳልፈው ሰጡ መነኮሳት ግርማ ሌሊቱን ድምጸ አራዊቱን ታግሠው ይኖራሉ። ምእመናን ጥረው ግረው ካገኙት እየመጸውቱ ይኖራሉ። ይልቁንም ዮሐንስ ወንጌላዊ እረኛው ተሰቅሎ ካየው በኋላ እስከ ዕለተ ሞቱ ፊቱ በጎዘን ተውጦ (ቍጹረ ገጽ ሆኖ) ይኖር ነበር። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ጥቅም ያለው እንባ እና ልቅሶ ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን ግፍዐ ሰማእታትን አስቦ ማልቀስ ነው ብሏል። እንዲሁም ኃጢኣትን እያሰቡ ማልቀስ ጥቅም ያለው ልቅሶ ነው ብሏል። ባለቅኔው ቀጥሎ ለይእቲ ላሕም መድኃኔዓለም ተመሰላ ብሏል። ይህችን ላምም መድኃኔዓለም መስሏታል ይላል መድኃኔዓለም አዳምን ለማዳን በመስቀል ተሰቅሏልና። እረኛዬ እረኛዬ ትላለህሳ እረኛዬ ምንድን ነው? ብለህ ከጠየቅከኝ ሌላ እረኛ ማን አለ ብለህ ነው!? እያወራሁ ያለሁትኩ ስለእረኛዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተመሰረተች የክርስቶስ አካል ናት። የክርስቶስ ሙሽራ ትባላለች። ሁልጊዜ አስተምህሮዋ የክርስቶስ ትምህርት ነው። ሰላም ለክሙ ማኅበራኒሁ ለክርስቶስ ሰላም ለክሙ። በጽባሕ ሐውጽዋ (ወትረ ሐውጽዋ) ለቤተ ክርስቲያን። የቤተክርስቲያን ልኳ ክርስቶስ ነው። በእርሷ ውስጥ ባሉ ሰዎች አትለካም። ድኅነትን ለማግኘት ወደእርሷ የተጠጉ ሰዎች ክፉ ቢሆኑ ራሳቸውን ይጎዳሉ። መልካም ቢሆኑ ራሳቸውን ይጠቅማሉ። ቤተ ክርስቲያን ግን ልኳ ክርስቶስ ስለሆነ ሁልጊዜም ቅድስት ናት። ከፍ ብለን እናስብ። ቤተ ክርስቲያን እውነት ናት። ስለዚህ ለእውነት እንቁም። ቤተ ክርስቲያን ፍቅር ናት። ለፍቅር እንቁም። ቤተ ክርስቲያን ርቱዕ ናት። ለርትዕ እንቁም። ቤተ ክርስቲያንን ተከትሎ ያፈረ የለም። ንዑ ንትልዋ ለቤተክርስቲያን

ስምዐ ጽድቅ

ስለዚህም ተክለ ሃይማኖት ሆይ የእውነት ምስክር ሆንክ። "ወበእንተዝ ተሰመይከ ተሰመይከ ተክለ ሃይማኖት። ስምዐ ጽድቅ ኮንከ ስምዐ ጽድቅ ኮንከ ተክለሃይማኖት"። ዋሽቶ ከመኖር እውነትን ተናግሮ መሞት ይበልጣል። ዋሽቶ ከመከበር እውነትን ተናግሮ መጠላትና መሰደብ ይሻላል። ታላቁ ቅዱስ አባት አቡነ ተክለሃይማኖት ዘመኑን ሁሉ ቅዱስ እግዚአብሔር የገለጠውን እውነት በአንደበቱ በመስበክ በሕይወቱ በመተግበር ኖሯል። በእርግጥ የመኖር ፍሬ ነገርም ለእውነት እስከ ሞት ድረስ ታምኖ መኖር ነው። ቅዱስ አባታችን በዛሬው እለት ነሐሴ ፳፬ ቀን ከዚህ ዓለም ድካም አርፎ ወደ ዘለዓለማዊው ሕይወት የተሸጋገረባት ቀን ናት። ሞቶሙሰ ለጻድቃን ሕይወቶሙ ውእቱ። የጻድቃን ሞታቸው ሕይወታቸው ነው። ቅዱሳን እውነትን በመያዛቸው በሐሰተኞች ቢሳደዱም መከራ ቢደርስባቸውም ሁልጊዜም ደስተኞች

ነበሩ። የደስታቸው ምንጭ እግዚአብሔር ነውና። ለዚያምኮ ነው ቅዱስ ዳዊት ንዑ ንትፈሣሕ በእግዚአብሔር ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን ያለው።

ቤተ ክርስቲያን

ለዓለም ምስቅልቅል ቤተክርስትያን ተጠያቂ አትሆንም። ቤተ ክርስቲያን ሰላምን፣ አንድነትን፣ ፍቅርን፣ ይቅርታን ከዓመት እስከ ዓመት ታስተምራለችና። ጥሪዋን ትምህርቷን አልሰማም ብሎ ብዙ ችግር ካደረሰ በኋላ ቤተ ክርስቲያንን ተጠያቂ ማድረግ ነውር ነው። ለዓለም ምስቅልቅል ዋና ተጠያቂዎች ስግብግብ እና ራስ ወዳድ እንዲሁም ዘረኛ ሰዎች ናቸው። ቤተ ክርስቲያንን እንሰማለን መፍትሄውን ትስጠን የሚል ካለ ግን መፍትሄው በእጁ ነው። ነገር ግን እስራኤላውያን መድኃኒታቸውን እንዳሳደዱት የእኛም ሀገር አንዳንድ ፖለቲከኞች መድኃኒታቸውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አሳደዷት። ልጅ ቢሮጥ አባቱን አይቀድምምና ብዙ ጥፋት ከደረሰ በኋላም የመጨረሻው መቋጫ ያለው እና ሰላም ይሁን፣ አንድ እንሁን፣ ይቅርታ እንባባል የሚለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት ነው። እንግዲህ ከአቅማችን በላይ የሆነውን ጉዳይ እግዚአብሔር ይፍታው ብለን ዝም ብለናል። በደላችንን ሳያስብ የኢትዮጵያን ሰላም ያቅርብልን። አንድነታችንን ይመልስልን። እስኪ የቤተክርስቲያንን ትምህርት ተቀብለን ተግባራዊ እናድርገው። እንግዲህ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ውጭ ሄጄ መፍትሄ አመጣለሁ። ያዋጣኛል ካልክ ሞክር። ነገር ግን ጊዜያዊ ማስታገሻ መሳይ ወይም ጉዳት እንጂ ምንም ዘላቂ መፍትሄ ወይም ውጤት እንደማታመጣ ስነግርህ በእርግጠኝነት ነው።

ይቅርታ

ትልቁ ችግርኮ ጥፋትን አምኖ ይቅርታ ያለመጠየቅ ነው። ሰው ለጥፋቱ ይቅርታ ሳይጠይቅ የፈለገውን ያህል መልካም ቢያደርግ አይታመንም። የብዙዎች ችግር ይህ ነው። "አንትሙሂ ተሐውሩ ግድመ ግድመ አነሂ አሐውር ግድመ ግድመ" እንዲሉ ዋናውን ጉዳይ ትተው ለምክንያት ብለው ባልሆነው ምክንያት ይጣላሉ። በተለይ ሰው አምላኪ ትውልድ መነሳቱ አሳዛኝ ነው። ሰው ከሰው አምልኮ ወጥቶ በነጻ አእምሮው በራሱ ማሰብ ቢችል ኖሮ ችግሮቻችንም ይቀንሱልን ነበር። አሁን ሰው እየተጣላ ያለው በርእዮተ ዓለም ወይም በሐሳብ አይደለም። ሰው በሰው ነው እየተጣላ ያለ። መጀመሪያ አንዱ የአንዱ አምላኪ ይሆናል። ያ ያመለከው ሰው ሲሳሳት ደግሞ ሌላ ሰው ስህተቱን ሲገልጥበት አምላኪው ይጣላል። እገሌን አትንኩብኝ እገሌ አይሳሳትም ወደማለት ያመራል። አሁን ላይ ያለውን መሰዳደብ፣ መጠላላት እንኳ ብናይ ሰው ተኮር እንጂ ጉዳይ ተኮር አይደለም። የምትወደው ሰው ተሳስቶ እያለ ስህተቱን ሌላ ሰው ሲነግርህ ስህተቱን እንዲያርም ለወዳጅህ መንገር ሲገባህ መልካም ሥራው ብቻ እንጂ ስህተቱ አይነገር ብለህ ስህተቱን እንዲያስተካክል የነገሩትን ሰዎች ትሳደባለህ። ሌላው ችግር ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ያለው ነው። ማለትም በጣም የምትጠላውን ሰው ስህተት አፈላልገህ ትፖስታለህ ታሳጣለህ ትሳደባለህ። ነገር ግን ያ የምትጠላው ሰው መልካም ሲያደርግ በዝምታ ጸጥ ትላለህ። በእውነት እንዳንነጋገር አንድ እንዳንሆን የአንድነት ማነቆ የሆነብን ይህ ነው። የበደለው ሰው ይቅርታ እንዳይጠይቅ የሚነፋውም መንጋው ነው። ይቅርታ ከጠየቀ የተከራከረለትን መንጋ የሚያሳዝን ይመስለዋል። ስለዚህም ይቅርታ ሳይጠይቅ እንዲሁ እየሠራ

ይቀጥላል። የበደላቸውን ይቅርታ ሳይጠይቅ ስለ ይቅርታ ቢያወራ ከንቱ ነው። ሁሉም የበደለውን በደል አምኖ ይቅርታ ይጠይቅ። ከዚያ ጉዳዮችን ከመንጋነት በጸዳ አተያይ በእውነት እንገምግማቸው። ያን ጊዜ እውነት አንድ ያደርገናል። በእርግጥ ለትንሽ ሰዎች ይቅርታ መጠየቅ የመሸነፍ ምልክት ሊመስላቸው ይችላል። ግን ራሳቸውን ነው የሚጎዱት። ሰው የፈለገ ጻድቅ መስሎ ለመታየት ቢጥር የሐልዮ ወይ የነቢብ ወይ የገቢር ጽነት (በደል) አያጣውምና። ሳንሆን ጻድቅ መስሎ ከመኖር በደላችንን አምነን በእውነት በይቅርታ በፍቅር መኖር ይሻለናል። ብዙ ሰው ግን በደሉን አምኖ በትሕትና ከመኖር ይልቅ በደሉን በምክንያታዊነት ለመሸፈን ሲጥር ይታያል። ይህ አሳዛኝ ነው። እውነትን በፖሮፖጋንዳ ብዛት አትለውጠውም። እውነታውን አምኖ ይቅርታ የሚጠይቀውም ይቅርታ ጠይቆ መኖር ይሻላል። ከመንጋነት እንውጣ። ሕይወት የሆነው ቃለ እግዚአብሔር ይምራን።

ምክር

ለቤተ ክርስቲያን አሳቢ አንተ ብቻ እንደሆንክ አታስብ። ቤተ ክርስቲያን ራሷ ክርስቶስ ነው። መላእክት ጠባቂዎቿ ናቸው። እልፍ አእላፋት ሊቃውንት በጸሎትም በትምህርትም ሲጠብቋት ኖረዋል። እየጠበቋትም ነው። ሲጠብቋትም ይኖራሉ። አንተን እንደተቆርቋሪ ቆጥረህ ጳጳሳትን፣ መምህራንን፣ አስተዳዳሪዎችን፣ መነኮሳትን፣ ምእመናንን እንደማያስቡ አድርገህ አታቅርብ። በምሥጢርም በጽሑፍም በትምህርትም እየደከሙ ያሉ ብዙ ሊቃውንት ነበሩን። አሉን። ይኖሩናል። በእርግጥ በየዘመኑ ክፉ ካህናት፣ ክፉ ጳጳሳት፣ ክፉ መምህራን ቤተክርስቲያንን ፈትነዋታል። አሁንም እየፈተኗት ያሉ ካሉ ሙሉ መረጃ ማስረጃ ይዞ ማስወገዝ ይቻላል። በመሰለኝና በሐሜት መኖር አይገባም። ታድያ የእኔ ድርሻ ምን ይሁን ካልከኝ ለጥፋቶች መንሥኤ እገሌ ነው እገሌ ነው እያልክ ጣትህን ከምትቀስርና ከማሳበብ የራስህን መንፈሳዊ ድርሻ ተወጣ። ሁሉም የድርሻውን ነው የሚጠየቅ። ድርሻህ ላይ ትኩረት አድርግ። እንዲሁም ከሊቃውንቱ ከምእመናን ከመንፈሳዊ ማኅበራቱ ጋር እየተናበብክ ችግሮችን ለመፍታት ጣር። ክብር ለተርእዮ ለገንዘብ ለዝና ሳይሆን የቤተ ክርስቲያንን ክብር ለመግለጥ ለኖሩ እና እየኖሩ ላሉ ሊቃውንት እንዲሁም ምእመናን ይሁን።

እረኝነት

ታላቁ ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ በአንድ መወድስ ቅኔያቸው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እረኝነት ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ። ክፉ እረኛ የበጎቹን ሥጋና ጸጉር ብቻ ይፈልጋል። በጎቹን ግን ወደለመለመ መስክ አያሰማራም። በእኛ በሰዎች ልማድ መልካም እረኛ የሚባለው በጎቹን ተንከባክቦ ወደለመለመ መስክ የሚያሰማራ ነው። ነገር ግን እንዲህ አድርጎ ቢንከባከባቸውም መጨረሻ ላይ አርዶ ይበላቸዋል። ወይም አርዶ ለሚበላ ይሸጣቸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስን እረኛችን ጠባቂያችን ስንለው ግን ስንደክም ስንታመም እንፈወስ ዘንድ ሥጋውን ቆርሶ እንኩ ብሎ ደሙን አፍስሶ እንኩ ጠጡ የሚል ነው። ስለዚህ ቸር እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ፍቅሩን ሁልጊዜም እናስበው። ሁልጊዜም ንሥሓ እየገባን ሕይወት የሚሆነንን ፈውስ የሚሆነንን ሥጋውን ደሙን እንቀበል።

ውለዱ ምድርንም ሙሏት

አንዳንዱ ሰው እኛን የሚያኖረን ልጅንም የሚያሳድግ እግዚአብሔር መሆኑን ረስቶ ወልጄ ማሳደግ ከሚያቅተኝ እንዳልወልድ የወሊድ መቆጣጠሪያ ልጠቀም ብሎ ከፈጣሪ ጋር ይጣላል። የወሊድ መቆጣጠሪያ በክርስትና ትልቅ ኃጢኣት ነው። ፈጽሞ አይፈቀድም። ሰው መጨነቅ የሚጀምረው ከእግዚአብሔር በላይ ካላሰብኩ ሲል ነው። ክርስቲያን አንድን ነገር ለማድረግ የራሱን ድርሻ ይወጣል። ከዚያ ሲያገኝ ፈጣሪውን ያመሰግናል። ሲያጣም ለበጎ ነው ብሎ ፈጣሪውን ያመሰግናል። ፈጣሪን በንጽሕና ሆነን እናምልከው። በደላችንንም ይቅር እንዲለን ንሥሓ እየገባን ሥጋውን ደሙን እንቀበል።

መሥራት

ማንኛውም ኦርቶዶክሳዊ ሰርቆ ሳይሆን ወጥሮ ሰርቶ ይብላ። በየሙያው ያላችሁ ኦርቶዶክሳውያን ከፈጣሪ የማያጣላ ሙያ ከሆነ በደስታ በወኔ በፍቅር ሥሩ። ስንፍና የኃጢኣት መሠረት ስለሆነ አትስነፉ። በየተሰማራችሁበት ጎበዞች ጀግኖች ሁኑ። አዲሱን ዘመን በአዲስ ልብ እንቀበለው። በዘረኝነት የቆሸሸ ልባችንን አጽድተን በይቅርታ፣ በአንድነት እና በፍቅር ያጌጠ አዲስ ልብን ገንዘብ እናድርግ።

ሀበነ አእምሮ

ጌታ ሆይ ሁል ጊዜ አንተን ያዩ ዘንድ የእውቀት ዓይኖችን ስጠን። አንተን ብቻ ይሰሙ ዘንድም የእውቀት ጆሮዎችን ስጠን። "ሀበነ እግዚኦ አእምሮ አዕይንተ አእምሮ ወትረ ኪያከ ይርአያ። ወአእዛንነሂ ቃለ ዘባሕትቲከ ይስምዓ"። የዓለም ነገር ሁሉ ይሰላቻል። ሠርክ አዲስ፣ ሁልጊዜ አዲስ የሆነ ቃለ እግዚአብሔር ነው። ንዑ ንትምሀር ቃለ እግዚአብሔር ።

አዲስ ዓመት

New Life Principle for New year. New Hope, New Mind set.

በአዲሱ ዓመት ምን እናድርግ? ፤ ሐሳቦች:-

፩ኛ) ካህናትን፣ ጳጳሳትን፣ አባቶቻችንን፣ መምህራንን ማክበር መውደድ። ይህ ካልተቻለ ቢያንስ በአደባባይ አለመስደብ መቻል አለብን። የቤተ ክርስቲያን ተቀርቋሪ መስሎ አባቶቻችንን የሚሳደብ አይኑር። ባመሰገንበት አንደበት አንሳደብበት።

፪ኛ) የሰው ተከታይ አንሁን። ፍጽምት እና የማትሳሳት የክርስቶስ ሙሽራ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናት። ስለዚህ ላልሞተ ሰው ጥብቅና አትቁም። አርዓያ ማድረግ ካለብህም በተጋድሎ ዓለምን አሸነፈው ያለፉ ቅዱሳንን አብነት አድርግ።

፫ኛ) በሰው ከመፍረድህ በፊት ጠይቅ። የእኛ እውቀት በዘመን በቦታ የተገደበ ነው። እኛ የማናውቀው ጉዳይ ብዙ ነው። ስለዚህ ለማወቅ በትሕትና ሆነን ማንበብ፣ መጠየቅ አለብን።

፬ኛ) እውነት ይምራን። ግላዊነትን አጥፍተን አንድነት ላይ እናተኩር። ልዩነቶቻችንን ፊት ለፊት እየተወያየን እያጠበብን የጋራ ዓላማዎቻችን ውጤት እንዲያመጡ የየበኩላችንን እንወጣ።

፭ኛ) የሰው ልጅ በማወቅም ባለማወቅም ፈጣሪንም ሰውንም ይበድላል። ስለዚህ ለበደላችን በንሥሓ ይቅርታ እንጠይቅበት።

፮ኛ) ለሕይወታችን ሕይወት የሆነውን የክርስቶስን ሥጋና ደም ንሥሓ እየገባን እንቀበል።

፯ኛ) ራሳችንን ችለን እናስብ። ለሁላችንም ነጻ አእምሮ ስላለን በመንጋነት ሳይሆን በራሳችን ጎሊና እናስብ። የሰው አምላኪ አንሁን። ሕሊናችንን ለሰዎች ግላዊ ምልከታ ባሪያ አናድርገው። ማንኛውንም ነገር እንመርምረው።

፰ኛ) ቤተ ክርስቲያን የሕይወት ምንጭ ናት። ሕይወት የሆነው ቃለ እግዚአብሔር የሚሰጥባት ናት። ስለዚህ ትምህርቷን ቀርበን እንማር።

፱ኛ) የሰው ሁሉ አባቱ አንድ አዳም ነው። ዝቅ ሲልም አንድ ኖኅ ነው። ስለዚህ በቋንቋ፣ በብሔር ወዘተ ዘረኝነት ሊኖረን አይገባም። ዘረኝነትን ከአእምሯችን እናጽዳ። ሁልጊዜም እግዚአብሔራዊውን ሐሳብ እንያዝ።

፲ኛ) ስሜታችንን የምንገዛ እንሁን እንጂ ስሜት የሚገዛን አንሁን። ትሑት ሰብእና፣ ፍቅረ ቢጽና ፍቅረ እግዚአብሔር አይለየን። በትክክል እንፍረድ። አንድን ነገር ከውጤቱ ጋር እና ከሚያመጣው ተጽእኖ እንዲሁም ከዓላማችን አንጻር እንገምግመው። ጥላቻን ከአእምሯችን እናስወግድ። አዎንታዊ አስተሳሰብ ይኑረን።

በአዲሱ ዓመት ሰይጣንንና ኃጢኣትን አምርረን እንጥላቸው። በሰይጣን የተማረኩ ሰዎችን እና ኃጥዓንን ግን ከሰይጣን ምርኮ ከኃጢኣት ምርኮ የምናድንበትን መንፈሳዊ ጥበብ ገንዘብ እናድርግ። ሰው ተኮር ሳይሆን ጉዳይ ተኮር እንሁን። አእምሯችንን በቤተክርስቲያን አስተምህሮ እናንጸው። ከቅዱሳን ሕይወት ፍቅርን ትሕትናን፣ ሰማእትነትን፣ ትእግስትን፣ ጎዳጌ በቀልነትን እንማር። ነገረ መስቀሉን እናስበው። ቆም ብለን ራሳችንን እንፈትሽ። ከሰዎች ጋር እያጣላን ያለው ግላዊ ችግራችን ሊሆን ይችላል። በሌላ ጣታችንን ከምንቀስር ራሳችንን እንይ። ሁልጊዜም መልካም አሳቢ (positive thinker) እንሁን። በዋናነት ጦርነታችን ከሰይጣን ጋር እና ከክፉ አስተሳሰቦች ጋር ይሁን። ክፉ አስተሳሰብን በመልካም አስተሳሰብ ድል እናድርገው። ኢትማያ ለእኩይ በእኩይ። ክፉን በክፉ አታሸንፍ።

ጉባኤ ቤት

ጉባኤ ቤት የሰው ልጅ በመልካም አስተሳሰብ በጥሩ ሰብእና የሚወለድባት እናት ናት። ጉባኤ ቤት ደጋግ ነገሥታትን፣ ቅዱሳን ሊቃውንትን፣ ቅዱሳን ጳጳሳትን፣ ሰማእታትን፣ ቅዱሳን መነኮሳትን ወልዳለች። የሰው ልጅ በጣም ቢራቀቅ መጨረሻው ኦርቶዶክሳዊ መሆን ነው። ጉባኤ ቤት ኦርቶዶክሳዊነትን በስፋት የምንማርበት ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ

ተራራው ዝቅ ይበል ሸለቆው ይሙላ ብሎ የሰበከው ዮሐንስ ነው። ይህንንን የሀገራችን መተርጉም ጌታው አለቃ ጎሩይ ተራራው ዝቅ ይበል ዘጠኝ መለኮት(አካላት) የሚል ዮሐንስ ተዓቃቢ ዝቅ ብሎ ሦስት አካላት ይበል። ሸለቆው ይሙላ አንድ አካል የሚል ሰባልዮስ ሦስት አካላት ይበል ብለውታል። ተራራው ዝቅ ይበል። በትእቢት የተወጠረው ክርስቲያን እኔማ አፈር ነኝ ብሎ በትሕትና ዝቅ ይበል። ሸለቆው ይሙላ። ከምግባረ ጽድቅ የጎደለ ምእመን በትሩፋት ከፍ ይበል። ዓውደ ዓመትን ቅዱስ ዮሐንስ እንለዋለን። ይህ ዮሐንስ መስከረም ፪ ሰማዕት የሆነው መጥምቁ ዮሐንስ ነው። የብሉይ ኪዳን መጨረሻ የሐዲስ ኪዳን መጀመሪያ ነው። ጸያሔ ፍኖት መባሉ የባሕርይ ንጉሥ ለሆነው ለክርስቶስ ነዋ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት ብሎ በማስተማሩ ነው። እኛም ከብልየት ኃጢኣት በንሥሓ ታድሰን አዲስ እንሁን።

ሁልጊዜም ሰላም

ክርስቶስ የመጣው በኃጢዓት ባርነት የነበርነውን እኛን ሰዎችን ነጻ ሊያወጣን ነው። ኢሳ. ፷፩፣፩ "ወእስብክ ሎሙ ግእዛነ ለጺውዋን" ለተማረኩት ነጻነትን እሰብክላቸው ዘንድ የሚለው ይህንን ነው። ተራርቀን የነበርነውን ሰውና መላእክትን፣ ሕዝብና አሕዛብን በመስቀሉ አንድ አድርጎናል። እኛን ለማዳን እሱነቱን ሳይለቅ እኛን ሆነ። እኛም እኛነታችንን ሳንለቅ የእርሱ ሆንን። በሉ በኃጢዓት በበደል ያለን ሰዎች ንሥሓ ገብተን ክርስቶስ የሰጠንን መንፈሳዊ ነጻነት እንጠቀምበት። ሰላም አንድነት ነው። የአንድነት ማነቆ የሆነው ራስ ወዳድነት ነው። ችግሮቻችንን በርቀት ክፉ ስም ወይም ጥላቻ (Prejudice) በመሰጣጠት ሳይሆን መሬት ላይ ባለው እውነታ ተነጋግረን ፍቅራችንን እናጽና አንድነታችንን እናጎልብት። ከምንም በፊት ራሳችንን ከኃጢዓት እናንጻ። ከዚያ ቀጥለን ሌላውን እናነጻለን።

ይቅርታ

One day I Will go and never come/back. One day i will sleep and never wake up again one day my eyes will close forever. One day there will be no more from me. One day every body will forget me one day somebody will miss me noone knows when this day is may be today maybe tommrow may be after a week a month a year may be after long time so I 'M Sorry If I Made You Sad One Day Just Remember Me And Just Forgive Me። መቼም ፍጹማን አይደለንም ስናጠፋ እየታረምን ይቅር እያልን መልካሙን እያስቀጠልን እንኑር።

የልቤ ሕመም

ከታች በምስሉ የምታዩት ኢትዮጵያውያን በአንድነት ቆመው የውጭን ጠላት ሲመክቱ የሀገራቸው የውክልና ተምሳሌት የሆነው ታሪካዊው ባንድራ ነው። ሙሉ ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው የቆሙበትን አድዋን ያስታውሰናል። አሁን ግን በተሳሳተ የፖለቲካ ርእዮተ ዓለም ልጆቿ እርስ በእራሳቸው ሲገዳደሉ እናያለን። ለዚህ ሁሉ ችግር ተጠያቂው ማን ነው ከተባለ ርእዮተ

ዓለሙ ነው። በአንድነት ሆነን ሀገራችን እየተመራችበት ያለውን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማህበራዊ ህይወት ርእዮተ ዓለም መዳረሻውን ብናየው እና የተሻለውን በጋራ ብንወስን መልካም ነበር። በአጠቃላይ የዓለም ህዝብ ሁሉ ቆም ብሎ ቢያስብ ደስ ይለኝ ነበር። የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆኑ መምህራን፣ ሊቃውንት፣ ምእመናን እርስ በእርስ ከመጠዛጠዝ በትክክል የሃይማኖታችንን ግብ ይዘን ከግላዊ ምልከታ ወጥተን ጎብረታዊ ብንሆን መልካም ነበር። እኒህ ነገሮች ባለመሆናቸው ሁልጊዜም የልቤ ሕመሞች ናቸው። በሐዲስ ዓመት ሐዲስ ርእዮት ይኑረን። ሰውን ክፉ የሚያደርገው ክፉ ሐሳብ ነው። ስለዚህ ሁላችንም ክፉ ሰውን ሳይሆን በዋናነት ክፉ ሐሳብን እንታገል። ሁላችንም የዚህ ዘመን ትውልዶች በመሆናችን ደስ ይበለን። የእኛን ትውልድ የሚያበላሸውን ክፉ ሀሳብንም እንታገል። በነገራችን ላይ ከባንድራ ሰው ይከብራል። ስለዚህ ባንድራ የሚያጣላ ጉዳይ አይደለም። ለክርስቲያን መመኪያው መስቀለ ክርስቶስ ነው። እኔም ከዚህ የተጠቀምኩት የኢትዮጵያን አንድነት ስላስታወሰኝ ነው። ከሁሉ በፊት የሀገር አንድነት ይቀድማልና። በዚያ እሳቤ ነው። ከምንም በፊት እኛ አንድ እንሁን። መጀመሪያ ራሳችንን ዞር ብለን እንይ። ጣት ከምንቀሳሰር ራሳችንን እናርም ። ሌላው ትርፍ ነው። ተራራው ዝቅ ይበል። ሸለቆው ይሙላ። ያን ጊዜ ቀጥ ያለ የተስተካከለ ዓለም ይኖረናል።

የናፈቀኝ ባህል

በቀድሞው ዘመን ሁለት ጎረምሶች ሲጣሉ ገላጋይ ላለማስቸገር ብቻ ለብቻ ይዋጣልን ብለው ሰው ከሌለበት ቦታ በዱላ ይናከታሉ። ከዚያ አንዱ ሲወድቅ የጣለው ሰውየ ከወደቀ በኋላ አይመታውም። የወደቀውም ምክንያት አይደረድርም መሸነፉን ያምንና ለአሸናፊው እውቅና ይሰጣል። ከዚህ ሁለቱም እየተሳሳቁ ወደቤታቸው ይመለሳሉ። ከዚያ ቂም የለ ጥላቻ የለ በፍቅር ይኖራሉ። ይህን ባህል እኔ አልደረስኩበትም። ነገር ግን ታላላቆቼ ሲነግሩኝ ናፈቀኝ። የአሁኑ ትውልድ ግን ፈሪ ስለሆነ የሚጣላም በሰው ፊት ነው። አንዱ ከወደቀ በኋላም ሲነሳ አይምረኝም ብሎ እንዳይነሳ አድርጎ ነው የሚወቃው። የቀድሞ ሰዎች ሰውን በእኩልነት ያያሉ። ፈጣሪን ይፈራሉ። ሲጣሉ እንኳ "እግዚአብሔርን ብዬ ነው እንጂ እመታህ ነበር" ይላሉ። አስበው እግዚአብሔርን ብለው የሚተውት ነገር ነበር። የሚፈልጉትን ለማድረግም ላለማድረግም እግዚአብሔር ምን ይላል የሚለውን ያስቀድሙ ነበር። ሰላም አደርክ ሲባባሉ እንኳ መልሳቸው እግዚአብሔር ይመስገን የሚል ነበር። አያቴ ስትነግረኝ ቀድሞ መሸቶ ስንተኛ ጠዋት እስክንገናኝ እንነፋፈቅ ነበር አለች። ሰው ሁሉ ይዋደድ ነበር። አሁን ግን ራስ ወዳድነት ነግሦ ጎብረታዊነት ጠፍቶ ሲታይ ያሳዝናል። ድሮ ውሸት ትልቅ ነውር ነበር። አሁን ግን ውሸት ሕጋዊ የሆነ እስኪመስለን ድረስ ሚዲያዎች ሁሉ ያራግቡታል።

ሀገርና ሃይማኖት ባንዲራና መስቀል

ሃይማኖት በሀገር አይወሰንም። ኩላዊ ነው። በዘመንም በቦታም የሚወሰን ነገር አይደለም። ሃይማኖት ከሀገር ይሰፋል። ስለዚህ ባንዲራን ከሃይማኖት ጋር አታገናኙት። ባንዲራ የአንዲት ልዑላዊት ሀገር ወካይ ምልክት ነው። ስለዚህ የተለያየ ሀገሮች የተለያየ ባንዲራ ይኖራቸዋል። በባንዲራ ተለያይተው በሃይማኖት አንድ የሆኑ ብዙ ናቸው። ለምሳሌ ግብጻውያን ባንዲራቸው ጥቁር ቀይ ነጭ ቀለም ያለበት ነው። የእኛ ደግሞ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ያለበት ነው። የኮፕት

ክርስቲያኖችም የእኛም በጠቅላላው የርቱዓነ ሃይማኖት ዋና ምልክታችን መስቀል ነው። እና ክርስቲያኖች በባንዲራ የሚጠላሉ መሆን የለባቸውም። ከባንዲራ ይልቅ አንድ የሚያደርጋቸው የክርስቶስ መስቀል አለና። የሀገር ባንዲራም በሀገሩ ሰዎች ስምምነት የሚሆን እንጂ አንዱ የሚወስነው አይደለም። እና በባንዲራ ምክንያት መጣላት አይገባም። ሀገራችንን እንውደዳት። ሀገርን የመውደድ ምልክቱ ደግሞ በሀገሪቱ ያሉትን ሁሉንም ሰዎች እኩል በመውደድ ነው። ይህ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ኢትዮጵያውያን እንደ ሀገር በአንድነት ጠላትን ያሸነፉበት ባንዲራ ነው። ስለዚህ በልብሳቸሁ ይህን ባንዲራ አትልበሱ ማለት ልክ አይመጣም። ማንኛውም ሰው የሌላውን መብት እስካልተጋፋ ድረስ የፈለገውን ይልበስ።

ቤተ ክርስቲያን ምን አለች/ትላለች?

መጋቤ ሐዲስ እሸቱ የሚሉት ነገር አለ። ፓትርያርኩ፣ ጳጳሱ፣ መምህሩ፣ ሊቁ ሊሳሳቱ ይችላሉ። ስለዚህ እነዚህ አካላት የተናገሩት በሙሉ የኦርቶዶክሳዊ ትምህርት መለኪያ አይሆንም። የማንኛውንም ሰው ትምህርት የምንቀበለው ትምህርቱ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተስማማ ሲሆን ነው። ብዙ ሰዎች ግላዊ ስሜታቸውን በቃለ እግዚአብሔር እያስታከኩ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለማስመሰል ሲሯሯጡ እያየን ነው። ነገር ግን እነርሱ ስላሉ የእነርሱ ግላዊ ሐሳብ የቤተክርስቲያን ትምህርት ስለማይሆን የንታ እገሌ፣ አባ እገሌ፣ ዲያቆን እገሌ፣ መምህር እገሌ፣ አባ እገሌ ምን አሉ ሳይሆን ጥያቄያችን መሆን ያለበት ቤተ ክርስቲያን ምን አለች እንበል። የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ምንጩ መሰረቱ እግዚአብሔር ነው። ነቢያት ትንቢት ቢናገሩ፣ ሐዋርያት ቢሰብኩ፣ ሊቃውንት ቢያመሰጥሩ መሰረቱን ሳይለቁ መሰረቱን ይዘው ነው። ስለዚህ ከግለሰብ አምልኮ እንውጣና የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ምንድን ነው የሚለውን ብናውቅ ይበጀናል። የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ትውፊታዊ፣ ኅብረታዊ፣ ሐዋርያዊ እንጂ ግላዊ አይደለም። የግላችሁን ሀሳብ የቤተ ክርስቲያን ለማስመሰል በጥቅስ የምትሸፋፍኑ ሰዎች ይቅርባችሁ። ጥቅስንማኮ ሰይጣንም ለራሱ ስሜት እንዲያግዘው ጠቅሶታል። ነገር ግን የሰይጣን ጥቅስ የራሱን ጊዜያዊ ስሜት የሚደግፍ እንጂ ደንበኛ ትርጓሜው ጌታ የመለሰለት ነው። ስለዚህ የማንኛውንም ሰው ንግግር በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ለክተን እንቀበል። ትምህርታችሁ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ላይ የተመሰረተ ይሁን እንጂ በየንታ እገሌ ግላዊ ስሜት የተመሰረተ አይሁን። ቤተክርስቲያን እውነት ናት። እውነት ደግሞ ከስሜት በላይ ናት። ቤተ ክርስቲያናዊውን እውነት እንያዝ። የመምህራን ንግግር ልብ ወለድ እንዳይሆን ምንጭ እንጠይቃቸው። ያለ መጽሐፋዊ መሰረት ያለ ትውፊት መሰረት እንዲሁ በመሰለኝ የተናገሩትን ሁሉ መቀበል አይገባም። ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ትርጓሜው ኅብረታዊ እንጂ ማንም እንደመሰለው የሚተረጉመው አይደለም። መምህራን ያልፋሉ። እስከ ዘለዓለም የምትጸና ቤተ ክርስቲያን ናት። ስለዚህ የሚያዋጣን የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ መያዙ ነው።

ትምህርት ለምን?

የቀድሞው ትውልድ አኗኗር የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ነው። ሴት ሁልጊዜም ትከናነብ ባለው መሰረት በየትኛውም ቦታ የቀድሞ እናቶቻችን ይህን ሕግ ይጠብቁት ነበር። ውበታቸው የእግዚአብሔር ቃል ነበር። ከእግዚአብሔር ቃል የወጣ አኗኗር መቼም ውበት አይሆንምና።

ትምህርት የአመለካከት የክሂሎት ለውጥ ያመጣል። ሰው ሲማር ሀገር ሰላማዊ ትሆናለች። ሀገራችን ላይ ዘረኛው በቀለኛው ለምን ፊደል የቆጠረው ሆነ ከተባለ ቂምን በቀልን ዘረኝነትን በትምህርት መልኩ ስለጋቱት ነው። መፍትሄውም ሥርዓተ ትምህርቱን መልካሙን ይዞ ክፉውን በማስወገድ ነው። መማር ለማወቅ ነው። ማወቅ ደግሞ ለጥሩ ሕይወት ነው። የትምህርት ሥርዓታችን ሀገራችንን ያልለወጣት ለምንድን ነው? ምን ስለሚጎድለው ነው? አንድ ሰው ተምሮ ያስተማረውን ማጎበረ ሰብእ አኗኗር ወደተሻለ ነገር ካላሳደገ የመማር ጥቅሙ ምንድን ነው? የትምህርት ሥርዓታችንስ ራሳችንን ችለን ማጎበረሰባችንን እንዲያስችል በክሂሎት በአመለካከት በእውቀት ቀርጾናል ወይ? ከእኛ የቀደሙት አባቶቻችን እናቶቻችን በሁሉ ነገር ራሳቸውን የቻሉ ነበሩ። ሀገር በቀል እውቀቶች ነበሯቸው። አሁን ግን እነዚያ ሀገር በቀል እውቀቶች የታሉ? ሰው ሲማር ክፉዎችን ታግሦ መልካም ያደርጋቸዋል። ሐዋርያት ከጥሩ መምህር ክክርስቶስ ተማሩ። ከተማሩ በኋላ መምህራቸውን መሰሉ። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ክፉዱቱን ሮምናን ወደ መልካምነት ለመለወጥ ራሱን ዝቅ አድርጎ በእሳት አንዳጅነት አገለገለ። እኛጋ ራሱን ዝቅ አድርጎ ለሕዝቡ ጥቅም የሚሰራ ምሁር ለምን ጠፋ?። የተማረ ሰው በበጎ አመለካከቱ እርሱ ብርሃን ሆኖ ክፉ አመለካከት ያላቸውን ይቀይራቸዋል። በእውቀቱ ድንቁርናን ያጠፋል። በክሂሎቱ የሕዝቡን ችግር አጥንቶ አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል። የተማረ ሰው ከራሱ በላይ ለሕዝቡ ያስባል። ሕዝቡን እንደራሱ ይወዳል። አንድ ሰው ተምሮ ለማጎበረሰቡ የሚጠቅም ስራ ካልሰራ ምኑን ተማረ ይባላል??። የመማር ፍሬው ለሌላው ብርሃን መሆን ነው። እከብር ባይ ልቡናን ትቶ ለሰው የሚጠቅመውን ነገር የሚናገር ነው። መልካም በማድረጉ ክፉዎች ቢጠሉትንኳ መልካምነትን እስኪረዱ እስከ ሰማእትነት የሚደረግ ሕይወት ነው።ጌታስ ለሰቃዮቹ ምሕረትን ለምኖ የለምን?! ስለዚህ ለህዝቡ ይጠቅማል ብለህ እየሰራህ ህዝቡ ራሱ ቢጠላህንኳ መልካም እስከሆነ ድረስ መልካምነትን አጠንክር። አሁን ግን ምሁርነት የት ገባ?! የአብነት ተማሪን ስፖንሰር ሆኖ የሚያስተምረው ምእመኑ ነው። ምእመኑ ተማሪውን በፍቅር ያስተምረዋል። ተማሪውም መምህር ሆኖ በፍቅር ምእመኑን ያስተምራል። ያገለግላል። ለሕዝቡ ይራራል።

ድንግል ማርያም

እናቲቱን በመስደብ ልጇን የወደዱ ለሚመስላቸው ጥቃቅን ሰዎች ትኩረት መስጠት አይገባም። ኢየሱስ ክርስቶስን እወደዋለሁ ካልክ እንግዲያውስ እርሱም እናቱን ስለሚወዳት የሚወደውን ውደድለት። አይሁድ አብን የወደዱ መስሏቸው ወልድን ሰቀሉት። የዘመናችን አይሁዶች ደግሞ ኢየሱስን የወደዱ መስሏቸው እናቱን ያቃልላሉ ይሰድባሉ። እኛስ አምላክን የወለደች ድንግል ማርያምን እንወዳታለን። በጨለማ ለነበርን ሰዎች ብርሃንን ስለወለደችልን እንወዳታለን። በሲያል እስር ቤት ለነበርን ሰዎች የሲኦልን በር ሰብሮ ነጻ የሚወጣ ክርስቶስን ስለወለደችልን እንወዳታለን።

The 20 Most Common Logical #Fallacies

1. Appeal to ignorance — Thinking a claim is true (or false) because it can't be proven true (or false).

2. Ad hominem — Making a personal attack against the person saying the argument, rather than directly addressing the issue.

3. Strawman fallacy — Misrepresenting or exaggerating another person's argument to make it easier to attack.

4. Bandwagon fallacy — Thinking an argument must be true because it's popular.

5. Naturalistic fallacy — Believing something is good or beneficial just because it's natural.

6. Cherry picking — Only choosing a few examples that support your argument, rather than looking at the full picture.

7. False dilemma — Thinking there are only two possibilities when there may be other alternatives you haven't considered.

8. Begging the question — Making an argument that something is true by repeating the same thing in different words.

9. Appeal to tradition — Believing something is right just because it's been done around for a really long time.

10. Appeal to emotions — Trying to persuade someone by manipulating their emotions — such as fear, anger, or ridicule — rather than making a rational case.

11. Shifting the burden of proof — Thinking instead of proving your claim is true, the other person has to prove it's false.

12. Appeal to authority — Believing just because an authority or "expert" believes something than it must be true.

13. Red herring — When you change the subject to a topic that's easier to attack.

14. Slippery slope — Taking an argument to an exaggerated extreme. "If we let A happen, then Z will happen."

15. Correlation proves causation — Believing that just because two things happen at the same time, that one must have caused the other.

16. Anecdotal evidence — Thinking that just because something applies toyou that it must be true for most people.

17. Equivocation — Using two different meanings of a word to prove your argument.

18. Non sequitur — Implying a logical connection between two things that doesn't exist. "It doesn't follow…"

19. Ecological fallacy — Making an assumption about a specific person based on general tendencies within a group they belong to.

20. Fallacy fallacy — Thinking just because a claim follows a logical fallacy that it must be false.

ነቢዩ ኤልያስ

ለአምላኩ ትእዛዝ የሚቀና፣ ፈጣሪውን በጣም የሚወድ፣ እውነትን ፊት ለፊት የሚናገር፣ መምህር ወመገሥፅ የሚሉ ቃላት ትክክለኛ ትርጉም የሚሰጡን ለቅዱስ ኤልያስ ሲነገሩ ነው። ኤልዛቤል አሳደዋለች። በረሃ ለበረሃ ዋሻ ለዋሻ ፍርሀታ ለፍርሀታ ተሳዷል። ይህ ሁሉ ግን ከእግዚአብሔር ፍቅር አልለየውም። የነቢዩ በረከት ይደርብን።

ጽዮን ማርያም

እግዚአብሔር የቀደሳት ጽዮን ዳጎን የተባለውን ጣዖት አፈራርሳ ጥለዋለች። በእርግጥ በእስራኤል በደል ምክንያት ጽዮን ተማርካ ነበር። ነገር ግን ሰው ንሥሓ ሲገባ ደጋግ ሰዎች ሲነሱ በጊዜው ጊዜ ተመልሳለች። እኛም ክብርን ሁሉ ለማግኘት ከፈለግን ለባለፈው ንሥሓ ገብተን ለወደፊቱ መልካምን እንስራ። አማናዊቷ ጽዮን ቅድስት ድንግል ማርያም የቤተ ክርስቲያንን ጠላቶች ዳጎኖችን ታጥፋልን።

ቅዱስ ሚካኤል

=> ሚካኤል ማለት የስሙ ትርጓሜ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማን ነው ማለት ነው።

=> የመላእክት አለቃ ነው።

=> የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጠባቂ መልአክ ነበር።

=> ለአባ እንጦንስ ሥርዓተ ምንኩስናን ያስተማረው ቅዱስ ሚካኤል ነው።

=> በብሉይ ዘመን በግብጽ ባርነት ስር የነበሩ እስራኤላውያንን ደመና እየጋረደ በሲና በረሀ እየመገበ ማር እና ወተት ወደምታፈሰው ከነዓን ያገባቸው ቅዱስ ሚካኤል ነው።በሐዲስም ቢሆን የባሕራንን የሞት ደብዳቤ የሰረዘ። አፎምያን ከሰይጣን እጅ ያዳነ በሕይወቷ ዘመን ሁሉ

የረዳት ይህ ቅዱስ ሚካኤል ነው። ህዳር 12 እስራኤላውያንን ባሕረ ኤርትራን እንዲያልፉ የረዳበት እለት በመሆኑ ይታሰባል።ሰኔ 12 ቀን ደግሞ አፎሚያን የረዳበት እለት ተብሎ ይከበራል። ቅዱሳን ነቢያትን ቅዱሳን ሊቃውንትን ከእግዚአብሔር በተሰጠው የመርዳት ጸጋ በተለያየ መንገድ ይረዳቸው እንደነበር ተጽፏል። እኛም የመልአኩን ረድኤት ለማግኘት በወር በወር በ12 በ12 እናከብረዋለን።

ነገረ ዓለም

እግዚአብሔር ይህን ዓለም ከምን አምጥቶ ፈጠረው? ዘፍ.1፣1 እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ብሏል። ሰማይንና ምድርን ከምንድን ነው ያዘጋጃቸው? ሰማይና ምድር የተዘጋጁበት አስቀድሞ የነበረ ቁስ (Pre-existing Matter) አለ ወይ? የመሳሰሉ ጥያቄዎች ብንጠይቅ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ከእግዚአብሔር ውጭ ምንም አልነበረም። እግዚአብሔር ይኖርበት የነበረ ሌላ ቦታ እና ጊዜ ሳይቀር አልነበረም። ቦታውም ጊዜውም ኗሪውም እግዚአብሔር ብቻ ነበር። አኗኗሩ እንዴት ነበር ካልን ግን አለማወቅ ይከለክለናል። መናገር የምንችለው እርሱ እግዚአብሔር ስለ ራሱ የተናገረውን መሠረት አድርገን ብቻ ነው። ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ሕዋ ብቻ ነው የነበረ እንዳንል ሕዋ ራሱ የተፈጠረ ነው። ስለዚህ ምን ነበር? ዳቦ ለማዘጋጀት ስንዴ ያስፈልጋል። ቀድሞ ከነበረው ስንዴ መልኩን ጣዕሙን ሁሉ ነገሩን ለወጥ አድርገን ዳቦ እናዘጋጃለን። ይህች ዓለም ሳትፈጠር በፊት ከእግዚአብሔር ውጪ ሌላ የሚታይም ይሁን የማይታይ የሚዳሰስም ይሁን የማይዳሰስ አካል ምንም አልነበረም። ታዲያ ይቺ ዓለምስ ከምንድን ነው የተሠራችው? ስንል ይህች ዓለም በሁለት መንገዶች ተፈጥራለች። እኒህም እምነበ አልቦ ነበ ቦ እና ግብር እምግብር ናቸው። ይህንን እንመልከተው። እምነበ አልቦ ነበቦ ይህም ማለት አንድን ነገር ከሌለ ነገር እንደ አዲስ እንዲኖር ማድረግ ነው። ካለመኖር እንዲኖር ማድረግ ማለት ነው። በመጀመሪያው ቀን እሑድ የተፈጠሩ ፍጥረታት እና አርብ የተፈጠረች የእኛ ነፍስ ካለመኖር የተፈጠሩ ናቸው። እኒህም፦

- ፩ መሬት
- ፪ 7ቱ ሰማያት
- ፫ እሳት
- ፬ ነፋስ
- ፭ ውሃ
- ፮ መላእክት
- ፯ ጨለማ
- ፰ ነፍስ(አርብ የተፈጠረች)

ናቸው። እንግዲህ እነዚህ ፍጥረታት ሲፈጠሩ አካላቸው የአካላቸው ባሕርይ እና ጠባይ ሁሉ አብሮ የተፈጠረ ነው።ለምሳሌ እሳት ያቃጥላል። ብርሃን አለው። በእጅ የሚጨበጥ አይደለም። ብሩህ ነው። ሌላም ሌላም ነገር ልንለው እንችላለን። አጠቃላይ ከነማንነቱ ከነመኖሪያው የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። እኛ እንዲህ እግዚአብሔር የፈጠረልንን ምክንያትና ውጤት እያደረግን እንናገራለን። የምክንያትና የውጤት መነሻው ምክንያት ራሱ እግዚአብሔር ነው። ሁለተኛው ግብር እምግብር ነው። እርሱ አስቀድሞ ከፈጠራቸው ከእሳት፣ ከመሬት፣ ከነፋስና እና ከውሃ አዲስ ፍጥረት መፍጠር ነው ነው። ግብር እምግብር ከተፈጠሩ ፍጥረታት መካከል፦ ሰማይ፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ እፀዋት፣ እንስሳት ይገኙበታል። እነዚህ ፍጥረታት ከ4ቱ ባሕርያት ማለትም ከእሳት፣ ከመሬት፣ ከነፋስ እና ከውሃ የተፈጠሩ ናቸው። ለምሳሌ ዕፀዋትን ብንመለከት ከመሬት መፈጠራቸውን በስብሰው አፈር ወደ መሆን ሲለወጡ ያሳውቃሉ። ከነፋስ መፈጠራቸውን ለሰው ልጅ አየር ሰጥተው ሲያገለግሉ ያሳውቃሉ። ከውሃ መፈጠራቸውን በምሳር ስንፈልጣቸው በውስጣቸው ውሃ በማስገኘት ያሳውቃሉ። ከእሳት መፈጠራቸውን ደግሞ እርስ በእርስ ስናፋትጋቸው እሳት ብልጭ በማድረግ ያሳውቃሉ። እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ቀን እሑድ እስከ ስድስተኛው ቀን አርብ ድረስ በዐቢይ ክፍል 22 ፍጥረታትን ፈጠረ። ይህንንም ያደረገው እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ መፍጠር አቅቶት ሳይሆን እግዚአብሔር ሥራዎችን የሚሠራበት የራሱ ጊዜ ስላለው ነው። ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር ብሎ ቅዱስ ዳዊት እንዲያመጣው። ይህ ሲሆን ያለምንም አገልግሎት የተፈጠረ ፍጥረት የለም። ሁሉም ፍጥረት ለዓላማ ነው የተፈጠረው። እያንዳንዱ ፍጥረት ዓላማው ምንድን ነው? ጥቅሙስ ምንድን ነው? የሚለውን በቀጣይ ክፍል እንመለከታለን። ከየት መጣን? ወዴትስ እንሄዳለን? ለእኛ መኖር ምክንያቱ ምንድን ነው? ማን አመጣን? የምናየውና የማናየው ነገር ሁሉ መነሻው ምንድን ነው? በተፈጥሮ ሕግ የምናያቸው ነገሮች ሁሉ ምክንያታቸው ምንድን ነው? ማር ይጣፍጣል። ለምን ጣፈጠ? ምግብ ስንበላ ረኃባችን ለምን ይቀራል? በዓለም ውስጥ ለእኛ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ምሳሌ አየር፣ ውሃ፣ ምግብ፣ መኖሪያ እና ተፈጥሮን ያመጣው ማን ነው? የሰው ልጅ ለምን ሁለት ዓይን፣ ሁለት ጆሮ፣ እና የመሳሰሉ የአካል ክፍሎች ለምን ሊኖሩት ቻሉ? ለምንድን ነው እንስሳት አራት እግር የኖራቸው? ወፎችስ ለምን ይበራሉ? ክንፋቸውን ለመብረሪያነት የሰጣቸው ማን ነው? ወዘተ እያልን ብንጠይቅ መልሱ ምንድን ነው? መቼም በራሳችን ጉልበት እና እውቀት እንዲሁም የአስተሳሰብ ብቃት አይደለም የኖርነው። ሳንፈልግ እንወለዳለን። ሳንፈልግ እንሞታለን። ስለዚህ በእኛ ወደዚህ ምድር መምጣትና ከዚህ ዓለም በሞት መሰናበት በሰው ኃይል የተደረገ እንዳልሆነ ሁላችንም በተፈጥሮ በተሰጠን አእምሮ ጠንቅቀን እናውቀዋለን። እናት እና አባቶቻችን ነው የፈጠሩን እንዳንል እነርሱም በእኛ መንገድ ከእናት ከአባቶቻቸው የተወለዱ እንጂ የመውለድ እና የመወለድ መነሻ አይደሉም። በዓለም ያሉ ለእ ኛ ለሰውነታችን የሚያስፈልጉ ነገሮችንም እኛ ራሳችን እንዳላስገኘናቸው ጠንቅቀን እናውቃለን። እኛ በተፈጥሮ ያገኘናቸውን ፍጥረታት ለእኛ ሰውነት እንዲስማሙ እያደረግን እንጠቀምባቸዋለን እንጂ አላስገኘናቸውም። ለምሳሌ ጤፍን በተፈጥሮ አገኘነው። ይህንን ያገኘነውን ጤፍ አድርቀን ወቅተን ፍሬውን ፈጭተን ለእኛ ምግብነት እንዲውል አድርገናል እንጂ እኛ አላመጣነውም። በተፈጥሮ ከምድር ያገኘናቸውን ማዕድናት ተጠቅመን ተፈጥሯዊ ባሕርያቸውን አጥንተን ከቦታ ቦታ ለመጓጓዝ የሚያገለግሉንን እነ አውሮፕላንን መኪናን እና ሌሎች ነገሮችንም ሠርተናል።

እነዚህ ነገሮች የተሠሩበትን ማዕድን ከነጠባዩ ያስገኘነው ግን እኛ አይደለንም። ውሃ ያንሳፍፋል ብለን እንናገራለን። ይህን የተናገርነው ግን በተፈጥሮ ውሃ አንሳፋፊ ሆኖ አግኝተነው ነው እንጂ ውሃ አንዳንድ ፍጥረታትን እንዲያንሳፍፍ የሚያስችለውን ውስጣዊ አካላዊ ስሪት እኛ አልሠራነውም። ተሠርቶ የተገኘ ነው።ሥለዚህ የምክንያቶች ሁሉ ምክንያት ምንድን ነው? በመቀት ምክንያት በረዶ እንዲቀልጥ ያደረገው ማን ነው? ስንል ለእርሱ ምክንያት የሌለው ለሌላው ፍጥረት ግን ምክንያት የሆነ እግዚአ ብሔር ነው። ይህንን በምን አወቅን? ምክንያቱም እኛ ሲፈጥር አላየነው? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። እውነት ነው እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ሲፈጥር እኛ ስላልነበርን እንዴት እንደፈጠረውም አላየንም። ታድያ ካላየን ምንን መሠረት አድርገን ነው? እግዚአብሔር ፈጠረ እያልን የምንናገር ከተባለ በሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው። አንደኛ በመገለጥ ነው። መገለጥ ማለት አስቀድመን ባንኖርም ነገር ግን በእኛ ጊዜም እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ ተገልጦ የአምላክነት ሥራ ሲሠራ ታይቷል። የነበረውን እንዳልነበረ ሲያደርግ ያልነበረውን እንዲኖር ሲያደርግ ታይቷል። የግብፅን ውሃ ደም ሲያደርግ። ፀሐይን ለሦስት ቀናት ሲያጨልም ፍጥረታት ሁሉ እኛ ከምናውቀው ጠባያቸው እንዲያፈነግጡ አድርጓል። ከሁሉም በላይ የሞላን ውሃ ያለምንም Dam ወይም ግድብ አቁሟል። ይህንን አድርጎ እርሱ ይሆናል ያለው ሁሉ ሲሆን እና የሚሳነው ነገር ሲጠፋ ራሱን ለቅዱሳን ገልጦ አይተነዋል። ይህ ከሆነ ቅዱሳንስ እሽ አይተው አረጋግጠው አመኑ እኛ መች አየነውና እንመነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። የዚህ መልሱ አባቶቻችን ያቀበሉንን በመያዝ ነው። ለምሳሌ እኛ ስንወለድ እንዴት እንደነበረ መቼ እንደተወለድን አናውቅም። እኛ ስንወለድ ያዩ አባቶቻችን እና እናቶቻችን ግን አሉ።እነርሱ ያሉንን ተቀብለን አምነን እንኖራለን። ነገር ግን እነርሱ ዋሽተውንስ ቢሆን ሌላ ማረጋገጫ አለን ወይ የሚል ጥያቄ ካለም አወ አለን።ምን? ስንል ፈጣሪን አየነው ካላችሁ ስለ እርሱ የነገራችሁ ምንድን ነው? ብለን ያንን መሠረት አድርገን በተሰጠን አእምሮ መመርመር ነው። ለምሳሌ ፈጣሪ አልታይም ብሎናል። ስለዚህ አይታይም ብሎ መቀበል። አይ እስኪ እንየው ብለህ በስሜት ሕዋስህ መርምር ሲያቅትህ እውነታውን አረጋገጥክ ማለት ነው። ከዚያ ክረምትና በጋን የማፈራርቅ እኔ ነኝ ብሏል። እንደዚያ ካለ አለመሆኑን ለማረጋገጥ መርምር ነገር ግን ሌላ የሚያፈራርቅ ስታጣ ቀጥታ የማይታየውን አምላክ ወደማመን ትሄዳለህ። የአንተ ነፍስ አትታይም ነገር ግን ሥጋህን ስታንቀሳቅሰው ስታናግርህ ሰውነትህን ስታሞቀው እንዳለችህ ታምናለህ። ሳታያት ግን በሥራዋ ታምናለህ። እግዚአብሔርንም ሳናየው ግን ደግሞ ቀንና ሌሊትን ሲያፈራርቅ በትንቢት መልኩ የተናገረው ሲፈጸም አይተን እናምናለን።ይህ ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር ደግሞ ከድንግል ማርያም ተወልዶ የማይታየው ታይቶ በደረቅ ግንባር ያልነበረ ዓይንን ሲፈጥር በ2 ዓሳ እና በ5 እንጀራ 5000 ሕዝብ አጥግቦ 12 ቅርጫት ሲተርፍ አሳይቶናል። 2 ዓሳ እና 5 እንጀራ እንዴት በዝቶ 12 ቅርጫት ሆነ ካልከኝ ይህችን ምድር ካለመኖር እንዳመጣት ሁሉ ያንንም በችሎታው አድርጎታል። ስለዚህ ለፍጥረታት እና ለተፈጥሮ ሕግ ሁሉ መነሻ አለው። ያውም "ዘፍ.1፣1 በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ"።የሚለው ነው። ሰማይንና በሰማይ ያለውን ምድርንና በምድር ያለውን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ለፍጥረታት መጀመሪያ አላቸው። ለፈጣሪ ግን መጀመሪያ የለውም።ፈጣሪ ሲኖር ይኖርበት የነበረ ቦታ እና ጊዜ የለም።

ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር በየት ይኖር ነበር ካልከኝ። ራሱ በራሱ ነው። ቦታውም ጊዜውም ኗሪውም እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነበር።

ጽንሰት

የላይ ቤት ትርጓሜ ለምን ገብርኤል የምስራች ይነግራት ዘንድ ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም ተላከ የሚለውን ሲያትት ገብርኤል ብሂል ብእሲ ወአምላክ ገብርኤል ማለት ሰውም አምላክም ማለት ነው። ስለዚህ አምላክ ሰው ሊሆን ሰውም አምላክ ሊሆን ነውና ምሥጢርን ከምስጢር ለማገናኘት ነው ይላል። ሊቃውንቱም ገብርኤል ብሂል ብእሲ ወአምላክ እምኀበ እግዚአብሔር ዘተፈነወ ላእክ እያሉ ይዘምራሉ።

ቅዱስ ገብርኤል

=> በመላእክት ዓለም ዲያብሎስ ሁከት ባስነሳ/ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ንቁም በበህላዌነ ብሎ/ያረጋጋ መልአከ ሰላም ነው።

=> ለዓለም የምሥራችን ዜና ይዞ የመጣ መልአከ ፍሥሓ ነው።

=> ቅዱሳንን የረዳ እና የሚረዳ ቅዱስ መልአክ ነው። የመልአኩ ረድኤት አይለየን። እንኳን አደረሳችሁ።

መድኃኔዓለም

ወልድኪ መድኃኔዓለም ሥጋ ዚኣኪ ዘለብሰ።

በዐውደ ጲላጦስ ተወቅሰ መድኃኔዓለም።

ሊቃውንት ፍቅሩን የማዳን ሥራውን ቸርነቱን በቅኔያቸው በትርጓሜያቸው በማኅሌታቸው ይገልጻሉ። ሊቁ በሞት የተገለጠ ፍቅር እንዳሉት። ክርስቶስ እኛን ለማዳን በመስቀል ተሰቀለ። እውነት በአደባባይ ተሰቅሎ ሁሉ አየው። ጌታችን ሆይ በቸርነትህ በቀኝህ ከሚቆሙት ደምረን።

ግቢ ጉባኤ የሚናፍቅ ሕይወት

ዩኒቨርሲቲ ከገባን በኋላ ቅዱስ ሲኖዶስ በሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማህበረ ቅዱሳን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆችን ከዘመናዊው ትምህርት ጎን ለጎን መንፈሳዊ ትምህርት አስተምሮ ኮትኩቶ ያስመርቃል። አሁን ዩኒቨርሲቲ ያላችሁ ከወጣችሁ በኋላ እንዳይጸጽታችሁ እየሄዳችሁ በደንብ ተማሩ። ከትውልድ ቦታው፣ ከቤተሰቡ ተለይቶ የመጣን፣ ትኩስ ኃይል ያለውን ወጣት በግብረ ገብነት (ethics) አሸብርቆ እንዲወጣ ግቢ ጉባኤ ታላቅ አስተዋጽኦ አለው። የአገልግሎት ሥራዎች የሚሰሩት በስምምነት በውይይት እና አንድ ልብ በመሆን ነው። ግቢ ጉባኤ ለሕይወታችን መሰረታዊ የሆኑ ኮርሶችን፣ አጫጭር ሥልጠናዎችን፣ እና ሌላም ብዙ ነገሮችን የምንማርበት ነው።ሽንገላ የሌለበት ንጹሕ ፍቅር እና መተሳሰብ ያለው የት ነው ካልከኝ ግቢ ጉባኤ ነው ብየ እመልስልሀለሁ። ወደተለያዩ ገዳማት እና አድባራት የምንጓዘው ጉዞ፣ በበዓላት

ጊዜ ያለው ዝግጅት፣ የውይይት መርሐ ግብር፣ መንፈሳዊ የውይይት የአዳር መርሐ ግብሮች አይረሴ ናቸው። ግቢ ጉባኤ ለሀገር ምን ያበረክታል?

- ✓ 1ኛ ግብረ ገብ ዜጋ/መልካም ሰው
- ✓ 2ኛ ኃላፊነቱን በአግባቡ የሚወጣ ምርጥ ሰው
- ✓ 3ኛ ከራሱ ይልቅ ሀገሩን የሚያስቀድም ሰው
- ✓ 4ኛ ሐቀኛ እና ታማኝ ሰው
- ✓ 5ኛ ሌላውን ሰው እንደራሱ አድርጎ የሚወድ ሰው
- ✓ 6ኛ ሙስናን የሚጠላ ሰው

እኔ በጅማ ዩንቨርሲቲ ዋናው ግቢ በግቢ ጉባኤ ቆይታየ የኦዲትና ኢንስፔክሽን አባል፣ ሥራ አስፈጻሚ (የአባላት ጉዳይ ተጠሪ) ነበርኩ። እስኪ በዚያ የወጣችሁ የምን ክፍል አባል ነበራችሁ?

ትምህርተ አጋንንትን አለመስማት

ብዙ ሰው ስለ አጋንንት ብቻ ስለተማረ አጋንንትን የሚፈራ ሆኗል። በነገራችን ላይ በጣም ደካማ ፍጥረታት አጋንንት ናቸው። በጣም ፈሪዎች ናቸው። መስቀለኛ መንገድ እንኳ ሲያዩ ይፈራሉ ይባላል። ስናማትብ እልፍ አእላፋት አጋንንት ይርዳሉ ይንቀጠቀጣሉ። እና ሕዝቤ ሆይ ሰው ከሰይጣን በላይ ነው። ስለዚህ ሰይጣናት ራሳቸው ይፍሩን እንጂ ድኩማን ፍጡራንን ለምን እንፈራለን? ሰይጣናት እኛን ለምን እንደሚፈሩን ልንገርህ፦

፩ኛ፦የእያንዳንዳችን ጠባቂ መላእክቶቻችን ኃያላን ስለሆኑ እነርሱን ደግሞ አጋንንት በጣም ስለሚፈሯቸው ነው።

፪ኛ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተልን በክርስቶስ የምንወደድ የኃያሉ አምላክ የክርስቶስ ልጆች ስለሆንን።

፫ኛ፦ እኛ ራሳችን ወደን ለአጋንንት ካልተገዛን በስተቀር ነጻነት ያለን ስለሆንንና መልካም ሥራን እየሰራን በደስታ መኖር የምንችል ስለሆነ።

፬ኛ፦ ራሳችንን ለሰይጣን አስገዝተን ከሆነ እንኳ ንሥሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን ተቀብለን ከሰይጣን ግዞት ነጻ የምንወጣ ስለሆንን።

በጣም ደካማውን ፍጡር ሰይጣንንማ ልንፈራው አይገባንም። ነገር ግን የሰይጣን ገንዘቦች የሆኑትን ክፋቶች ከያዝን የሰይጣን ባሮች እንሆናለን። ስለዚህ ክፉ ስንሰራ ከነበረ ንስሓ ገብተን ከእንግዲህ መልካም እንሁን። ሰይጣን በእኛ ላይ አቅም የለውም። ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ካዳነን በኋላ ሰይጣንን ፈልገን ካልጠራነው በስተቀር በእኛ ሕይወት አይመጣም። ጽድቅንም ክፋትንም ብንሰራ ይስማማናል። ስለዚህ ክፋትን ብንሰራንኳ ሰይጣን አሳስቶን ነው እያልን

ራሳችንን አንሸውድ። በድፍረት እኛው የሰራነውን ኃጢአት በሰይጣናት ማላከክ አይገባም። ሰይጣን አስቦ ኃጢአትን እንደሰራ ሁሉ የሰው ልጅም አስቦ ጽድቅን ወይም ኃጢአትን ሊሰራ ይችላል። ክፋትን ብንሰራ ሰይጣን ሊያስፋፋት ይችላል እንጂ እኛ ራሳችንን ከጠበቅን ሰይጣን በእኛ ላይ ዋጋ የለውም። ቅዱሳን መላእክት ሰውን የሚረዱ እግዚአብሔርን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የሚያመሰግኑ ለእኛ እንደ ታላቅ ወንድም የሚያስቡልን ናቸው። የቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት አይለየን። አጭበርባሪ አጥማቂ ነን ባዮችና ባሕታዊ ነን ባዮች አያታልሏችሁ። ይልቅስ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ከመምህራን እግር ስር ቁጭ ብለን እንማር። አላፊ አግዳሚው አያታለን። ከሰይጣን ግዞት ነጻ ለመውጣት ከፈለግን ለሰራነው ኃጢዓት ንሥሓ መግባት ሥጋውን ደሙን መቀበል ነው። በዚህ በሽታው ካልለቀቀህ ግን ደዌ ዘበአኮቴት የሚባል መዓርግ አለ ብትታመምም እግዚአብሔርን እያመሰገንክ መኖር ነው። ሃይማኖተ አበው ሕንጻ መነኮሳት እንደሚነግረን ከከሃድያን ከአጭበርባሪዎች ሄደህ ከምትፈወስ በሕመሙ ሞተህ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሀልና።

ሞትን ስታስብ ምን ይሰማሀል?

ልክ ስትሞት በዚህ ምድር አለኝ የምትለው ነገር ሁሉ የአንተ ወዳለመሆን ይሸጋገራል። የለፋህበት የተጣላህበት ነገር ሁሉ ከንቱ ይቀራል። በዚህ ምድር ያሉት ሀብት ሥልጣን ክብር ጉልበት ዕውቀት እና የመሳሰሉት በዚህ ምድር እስካለህ ድረስ ብቻ የሚያገለግሉህ ናቸው። ስትሞት እነዚህ ሁሉ ምንም ናቸው። በእርግጥ እኒህን ነገሮች ከሞት በኋላ ለሚመጣው ሕይወት ካዋልካቸው ለነፍስህ ጥቅምን ይሰጣሉ። ብዙ ቅዱሳን የዚችን ዓለም አጭርነት ተረድተው ንቀዋት በምናኔ በየጫካው በየፍርክታው በጾም በጸሎት ተወስነው ያሳልፏታል። ሞት አንዱ የሕይወታችን አካል ነው። ቀድሞ የነበሩ ሰዎች አሁን በሥጋ የሉም። ዓለምን አንቀጥቅጠው የገዙ ዝናቸው በዓለም የታወቀ ሰዎች አሁን የሉም ሞተዋል። መጀመሪያውንም ካለመኖር ያመጣን እግዚአብሔር በሥጋ ወደ አለመኖር ይወስደናል። ሞት ሲታሰብ ይጨንቃል ምክንያቱም ሞተን ስላላየነው አናውቀውም። ሞት በዚህች ምድር ሳሉ ሥልጣናቸውን ጉልበታቸውን እውቀታቸውን ሀብታቸውን በአግባቡ ለመልካምነት ለተጠቀሙት ሰዎች ዕረፍት ነው። በተቃራኒው ሀብታቸውን ሥልጣናቸውን እውቀታቸውን ሌላውን ለመጉዳት ለተጠቀሙት ሰዎች ሁለት ሞት ነው። ስለዚህ ሞትን ላለመፍራት ከፈለግህ በዚህች ምድር እስካለህ ድረስ ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቅ። 3 ነገሮች ያስፈሩኛል ብሏል አንድ ሊቅ። እኒህም አለ፦ 1ኛ ነፍሴ ከሥጋየ ስትለይ፣ 2ኛ ለፍርድ በእግዚአብሔር ፊት ስትቆም፣ 3ኛ ሲፈረድባት ሁላችንም ካለመኖር እንድንኖር ያደረገን እግዚአብሔር ፊት እንቆማለን። ስለዚህ የእርሱን ረድኤት ጋሻ አድርገን በእርሱ ፊት ለመቆም የሚያበቃንን ስራ እንስራ።

ትክምህትና ውሸት

በጅምላ ስትመሰገን ደስ ካለህ በጅምላ ስትሰደብ ለምን ይከፋሀል? ብዙውን ሰው/ስንመለከት በአካባቢው አንድ ጀግና አዋቂ ሰው ሲነሳ በዚያ ይመካል። አካባቢያን የሚወክል ይህ ሰው ነው ይላል።ሌሎች ሰዎችም እርሱን በዚያ አዋቂ ወይም ጀግና እንዲለኩት ይፈልጋል። በሰፈሩ 6 ሌቦች ቢኖሩ ግን እነዚህ ሰዎች ሰፈራችንን አይወክሉም ይልሀል። በእነዚህ መለካትም

አይፈልግም። ብዙ ሰው በሀገሩ በሰፈሩ በጅምላ መመስገን ይፈልጋል። ለምሳሌ አምኖን እኅቱን የደፈረ ነው። የልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ልጅም ነው። አሁን አምኖን በግለሰብ ደረጃ የሚያስነቅፈው እንጂ የሚያስመሰግነው ምንም ዓይነት ስራ እንደሌለው ያውቃል። ስለዚህ በዚህን ጊዜ በአባቱ በዳዊት በመመካት እኔ የዳዊት ልጅ እያለ ሊናገር ይገባልን?? በአዋቂዎች እና በፈጣሪ ዘንድ ዳዊት በዳዊትነቱ አምኖን በአምኖንነቱ ይለካል እንጂ በጅምላ መመስገንም በጅምላ መተቸትም የለም። በነገራችን ላይ በጎጥ በአካባቢ የሚመካ ሰው ሲያጋጥማችሁ እስከ መጨረሻው ሂዱበት። በክልሉ ባሉ ታሪካውያን ሰዎች የሚመካ ሰው ካለ በተለየ የተወለደበትን ዞን ጥቀሱበት። ይህን ጊዜ እነዚያ ታሪካውያን ሰዎች ይቀንሱበታል። ከዚያ አሁንም በዞኑ የሚመካ ሰው ካለ ወረዳውን ጥቀሱበት። ይህን ጊዜ የሚመካባቸው ሰዎች ይቀንሳሉ። በወረዳው የሚመካ ሰው ካለ ደግሞ ቀበሌውን ጥቀሱበት። በቀበሌው ምንም ዓይነት ታሪካዊ ሰው ሲጠፋ ሲያይ ትምክህቱ ውሸት እና የጅምላ መሆኑን ያውቀዋል። ከቀበሌም ወደ ቤተሰብ ማውረድ። ከቤተሰብም ወደ ግለሰቡ መውረድ። የሰው ልጅ ትክክለኛ ማንነት ራሱ ሰውየው ብቻ ይሆናል። ይህን ጊዜ ትምክህት ውሸት መሆኑን እንረዳለን። ከአንድ ቤተሰብ እንኳ ክፉ ልጅ እና ደግ ልጅ ይኖራል። ክፉዎች በቤተሰብ እንዳይደበቁ በቤተሰብነት መለካትን ትተን በግለሰብነት መለካትን እንለማመድ። ያዕቆብና ኤሳው መንታ ወንድማማች ናቸው። ይሁንና ያዕቆብ ጻድቅ ነበር። ኤሳው ክፉ ነበር። ስለዚህ ሰዎችን በቤተሰብ በዘመድ በብሔር በቋንቋ መለካት የለብንም። እያንዳንዱን ግለሰብ ባለው ግላዊ ፕሮፋይል ማድነቅ መተቸት እንጂ እርሱ ስላጠፋ ቤተሰቡን ብሔሩን በጅምላ መስደብ እርሱ ታላቅ ስለሆነ ቤተሰቡን ብሔሩን በጅምላ ማድነቅ የለብንም።

ለምን እንኖራለን??

ጎበዝ እየኖርን ነው አይደል ግን አሁን? ለምንድን ነው የምንኖረው? ራሱ መኖር ምንድን ነው? መኖር በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ መገኘትን ያመለክታል። በእርግጥ ተፈጥረናል።ግን ለምንድን ነው የተፈጠርነው የሚለውን የሚያውቀው የፈጠረን አካል ነው። ምክንያቱም እኛ እኛነታችንን ያወቅነው ከተፈጠርን በኋላ ነው። ከተፈጠርን በኋላ ያለውን እኛነታችንን ስንመረምረው ብዙ ነገሮች ምሳሌ ምግብ አየር ውሃ እና የመሳሰሉ ነገሮች የሚያስፈልጉን እንደሆነ እርግጥ ነው። ታድያ እነዚህ ነገሮች በባሕርያችን እንድንፈልጋቸው ያደረገን አካል ማን ነው? የሚለውን ስንመረምረው ለራሱ መኖር ሌላ ምክንያት የሌለው የሆነ አካል መኖሩ ግድ ነው። ይኽውም እግዚአብሔር ነው። በቅዳሴያችን እስመ አልቦ ውስተ ህላዌ አመክንዮ ለመኖሩ ምክንያት የለውም እንላለን። ደመና ዝናምን እንዲያስገኝ ማር እንዲጣፍጥ ፀሐይ እና ጨረቃ እንዲሁም ከዋክብት እንዲያበሩልን ሬት ለእኛ መራራ እንዲሆን ጤፍን ፈጭተን ስንጋግረው እንጀራ እንዲሆን ያደረገ እሳት እንዲሞቀን በረዶ እንዲቀዘቅዘን አጠቃላይ በፍጥረታት መካከል ላለው የግንኙነት ውጤት እና ምክንያተ ህላዌ ለምክንያቶች ሁሉ ምክንያት የሆነ ለእርሱ መኖር ግን ሌላ ምክንያት የሌለው እግዚአብሔር ነው። ከመፈጠራችን በፊት አልነበርንም። ለመፈጠራችን ምክንያቱ ደግሞ ፈጣሪ ነው። ለምን ፈጠረን የሚለውን የሚያውቀውም እርሱ ብቻ ነው። ስለዚህ ለምን እንኖራለን የሚለውን ለማወቅ መጠየቅ ያለብን ካለመኖር እንድንኖር ያደረገን ፈጣሪን ነው። ፈጣሪ ደግሞ በቸርነቱ ለፍጡራኑ በተለያየ መንገድ እየተገለጸ ራሱን አሳውቆናል። ራሱን ያለምስክር አልተወም እንዲል የሐዋርያት ሥራ። ስለዚህ ለተለያዩ ቅዱሳን

ራሱን በሚችሉት አቅም እየገለጠ የተፈጠርንበትን ዓላማ ነግሯቸዋል። የሰው ልጅ የተፈጠረ እግዚአብሔርን እያመሰገነ በደስታ ለዘላለም እንዲኖር ነው። የሰው ልጅ አፈጣጠሩ በነጻነት እንዲኖር የፈለገውን መርጦ እንዲኖር ነው። ይህ ሲሆን ግን ሲኦል እና ገነት ስላሉ ሲኦል የሚያስገቡ ስራዎችን ከሰራ ሲኦል እንደሚገባ። ገነት የሚያስገቡ ሥራዎችን ከሰራ ገነት እንደሚገባ ተነግሮታል። በዚህች ምድር ብዙ ጊዜ ደስ ብሎን ያውቅ ይሆናል ነገር ግን ያ ደስታ አጭር ነው። የደስታን ስሜት የፈጠረልን በገነት ያለውን ደስታ እንድናስታውስበት ነው። የኀዘን ስሜትን የፈጠረብንም የሲኦልን ኀዘን እንድናስብ ነው። እንግዲህ ጌታ የነጻነት አምላክ ወይም አምላከ ግዕዛን ስለሆነ በግድ እንድናመልከው አላደረገም። የሲኦልን ክፉነት የገነትን መልካምነት ነግሮን ከዚህ በኋላ ምርጫ ሰጥቶናል። እንግዲህ በዚህች ምድር ለአጭር ጊዜም ቢሆን የመኖራችን ምክንያት ከሞት በኋላ ላለው ህይወት የመዘጋጃ ጊዜ እንድትሆነን ነው። ጌታም ቸር ስለሆነ በዚህች በአጭሯ የምድር ህይወታችን ዝግጅት መልካም ከሰራንባት ዘላለማዊ ደስታ ወዳለባት ወደ መንግሥተ ሰማያት እንገባለን። ክፋትን ከሰራንባት ዘላለማዊ ለቅሶ ካለበት ገሐነም እንገባለን። አእምሯችን የተሰጠን በዚህች ምድር በአጭሯ የመዘጋጃ ህይወታችን የሚያስፈልጉንን ነገሮች ፍጥረታትን ተመራምረን ለተለያዩ አገልግሎቶች እንድንጠቀምባቸው ነው። በነገራችን ላይ መንፈሳዊ ፍልስፍና የሚለውን ቃል መጽሐፈ መነኮሳት ላይም እናገኘዋለን ተፈልስፎ መንፈሳዊ ይለዋል። በመንፈሳዊ ፍልስፍና በስሜት ህዋሳቶቻችን አማካኝነት ያወቅነውን እውቀት እንናገራለን እንጂ ከዚያ እውቀት ተነስቶ መገመት አይቻልም። ከመፈጠራችን በፊት በቃ አለመኖራችን ስለሚገድበን የተነገረንን አምኖ ከመቀበል ውጭ አማራጭ የለንም። ሰው ሰራሽ ነገሮችን ግን እየመረመርን ብያኔ መስጠት እንችላለን።ምን እንዴት ለምን የት መች ወዘተ የመሳሰሉ ጥያቄዎችን እያነሳን መነጋገር እንችላለን። እና ፍሬ ነገሩ አሁን የትኛውን ምርጫ በማስፈጸም ላይ ነን? አሁን ገነት የሚያስገባንን ስራ እየሰራን ነው ወይስ ሲኦል የሚያስገባንን ስራ?? አወ በዚህ ጉዳይ ሙሉ ኃላፊነቱን የምንወስድ ራሳችን ስለሆንን በደንብ እናስብበት። የሊቃውንት ቅኔ ስለዝህች ምድር

ለመኑ ሐለየ እግዚአብሔር

ተድላ ዓለማት ዓለመ እምድኅረ ፈጠረ ለነ።

አኮኑ ኀድግዎ ወመንንዎ ይብለነ።

ወቦኑ ለእንስሳት

ዘከረ ለሊሁ ወሐለየ ብነ።

ቅድመ ኢሳይያስ ነቢይነ

ውስተ አእምሮ አማን አምጣነ እንስሳት ይኄይሱነ ።

ዓለምሂ ለእመ ተርፈ ኢያነብዘነ።

አምጣነ ኀሳር ወቅጥቃጤ ፍኖተ ሰናክሬም ዓለምነ።

ወመፍትው እግዚእ ዓለመ ከመ ያኅድገነ።

አምጣነ ለሊሁ መቅድመ ኩሉ ዓለምነ ወርስትነ።

ከዝምታና ከመናገር የቱ ይሻላል?

አቀድም አእኩቶቶ ለእግዚአብሔር። ዝምታ በግእዝ አርምሞ ይባላል። የቅድስና በር ነው። ከ10ሩ መዓርጋተ ቅድስና የመጀመሪያው አርምሞ ነው። በሌላ በኩል ተናገሩ ድንቅ ሥራውን በእውነት መስክሩ ይላል። ታዲያ መቼ በምን ጉዳይ የት ለምን እንናገር ዝምስ እንበል የሚለው ብዙ ጊዜ ያከራክራል። ጠቢቡ ሰሎሞን ቦ ጊዜ ለኩሉ ብሏል። ለመናገርም ጊዜ አለው ዝም ለማለትም ጊዜ አለው። ዝምታን በሚመለከት እምተናግሮ ይኄይስ አርምሞ ከመናገር ዝም ማለት ይሻላል ሲባል። መናገርን በሚመለከት ደግሞ ካለመናገር ደኃዝማችነት ይቀራል ይላሉ። የሆነ ሆኖ መቼ ዝም እንበል መቼስ እንናገር የሚለውን እንመልከት። ዝምታ ነገርን በልብ የመያዝ ታላቅ ጥበብ ነው። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ወንጌል ማርያም ግን ይህንን ሁሉ በልቧ ትጠብቀው ነበር ብሏል። የዝምታ አስፈላጊነት በነቢብ ወይም በንግግር ከሚሰሩ ኃጢአቶች ራስን ለማራቅ ነው። የነቀፋ የስድብ የሐሜት የውሸት የትምክህት የዘፈን የተርእዮ ሀሳብን የሚያንጸባርቁ ነገሮች ሲያጋጥሙን ከመናገር ይልቅ ዝም ማለት ይሻላል። ንግግርህ ለሰሚውም ለአንተም ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ወይም ሥጋዊ ጥቅምን የማይሰጥ ጉዳይ ከሆነ ባትናገረውና ዝም ብትል ይሻላል። የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ለመመስከር ለሌላውም ለማስተማር እና ለማሳወቅ የምንናገረው ነገር የጽድቅ መንገድ ነው። ወተዝያነው እምዕለት ዕለት አድኅኖቶ። በቀን በቀን የእግዚአብሔርን ማዳን ይነጋገሩ ነበር ተብሏል። አሁን ዘመናችን ከፍቶ እንጂ ቀድሞ አባቶቻችን እናቶቻችን ሲገናኙ ነገራተ እግዚአብሔርን ነበር የሚነጋገሩት። የቅዱሳንን ህይወት እያነሱ ይማማሩበት ነበር። ስለዚህ ሰሚው አካል ሰምቶ በመንፈሳዊ ወይም በዓለማዊ ረገድ ጥቅም የሚያገኝበት ከሆነ ተናገር። ተናግረኽው በአንተ ላይ ከንቱ ውዳሴን ተርእዮን ትእቢትን የሚያመጣብህ ከሆነ መጀመሪያውንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ። ሰሚውን የሚያሳዝን የሚያናድድ የሚያበሳጭ ንግግር ከሆነ አለመናገር ነው።በሃይማኖት ጉዳይ ግን ከሃዲውን ይከፋዋል ተብሎ ሃይማኖትን ከመመስከር ወደኋላ ማለት አይገባም። ሌላው ግን አጥርተን በማናውቀው ጉዳይ ባንዘባርቅ መልካም ነው። ብንጠየቅ መልስ መስጠት የምንችለውን ጉዳይ ነው መናገር ያለብን። በሆይ ሆይ ከሌላ ሰው በሰማነው ጉዳይ ግን ዝም ብንል የምናተርፍ ይሆናል።

ትንሣኤ ልብ

የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለማየት ከፈለግን መጀመሪያ የእኛ የእያንዳንዳችን ልብ ትንሣኤ ያስፈልገዋል።

1ኛ ጸሎት፦ ጸሎት ከፈጣሪ ጋር መነጋገር ነው። ስለዚህ ከፈጣሪ ጋር ከመነጋገር የበለጠ ምንም ነገር ስለሌለ ከማንኛውም ነገር በፊት ቢያንስ በ7ቱ ጊዜያት (3, 6, 9, 12, 3, 6, 12) ሰዓት መጸለይ አለብን። ጸሎት ምስጋና ያለበት ልመና ነው። ፈጣሪ በቸርነቱ ስላደረገልን ነገር ሁሉ በፍቅር ማመስገን አለብን። መላእክት ይህን ሁሉ ጸጋ የሰጣቸውን ፈጣሪ በፍቅር

ያመሰግኑታል። ተፈጥሮን እንድንኖርባት የሰጠን አካላችንን ካለመኖር አምጥቶ የሰጠን ለእኛ የሚያስፈልጉን አየርን ውሃን እና ሌሎች ነገሮችን የሰጠንን ፈጣሪ ማመስገን ይገባል።

2ኛ ይቅርታ፦ ከፈጣሪ ውጭ ያሉ ፍጥረታት በሙሉ ፍጹም አይደሉም ሊሳሳቱ ይችላሉ። በዚህን ጊዜ እኛም ብዙ ስህተቶችን እንደሰራን በማስታወስ ፈጣሪ ግን በቸርነቱ በይቅርታ ይቅር እንዳለን በማሰብ እኛም በሌሎች ላይ ስህተት የመሰለ ነገር ስናይ ከቂም ከበቀል ይልቅ በይቅርታ ልብ አይተን ፈጣሪ እኛን ይቅር እንዳለን እነርሱንም ይቅር እንዲላቸው በርኅራኄ ማየት ነው።

3ኛ ፍቅር፦ ይህ እግዚአብሔርን መውደድ እና ሰውን መውደድ ተብሎ ይከፈላል። እግዚአብሔርን መውደድ ማለት ለትእዛዞቹ መገዛት ሲሆን ሰውን መውደድ ማለት ደግሞ በእኛ ሊደረግብን የማንፈልገውን በሌሎች እንዲደረግ አለመፈለግ እና አለማድረግ ሲሆን በአንጻሩ ለእኛ ሊደረግልን የምንፈልገውን የምንመኘውን ነገር ለሌሎችም መመኘትና ማሰብ ነው።

4ኛ እውነት፦ እውነት ማለት ውሸትና ግምት ያልተቀላቀለበት ግነት የሌለበት ነገሩን እንደነገርነቱ ብቻ በጥራት ማቅረብ መናገር ማለት ነው። ከሰዎች ክብርን እና አድናቆትን ሽተን ወይም ሰዎችን ለማበሳጨት ወይም ለማስደሰት ብለን ያልተደረገን ነገር በልብ ወለድ ወይም በእውነታ ላይ ጨመርመር እያደረጉ ማውራት ውሸት ስለሆነ ልንተወው ይገባል።

5ኛ ጾም፦ ጌታችን ዝንቱ ዘመድ ኢይወጽእ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት ብሎ እንደተናገረው ክፉ ሀሳቦቻችንን ከአዕምሮ ለማስወጣት ጾም ወሳኝነት አለው። ጾም ማለት በተወሰነ ጊዜ ከምግብ በተወሰኑ ዕለታት ከጥሉላት መከለከል ለዘላለም ደግሞ ክፉ ከማየት ክፉ ከመስማት አጠቃላይ ሕዋሳቶቻችንን ከክፉ ነገር መጠበቅ ነው። አእምሯችንን ከሚበክሉ ነገሮች መራቅ ነው።

6ኛ ቁርባን፦ የሰው ልጅ የሚቀደሰው ንሥሓ ገብቶ የጌታችንን ክቡር ሥጋውን ክቡር ደሙን በልቶ ጠጥቶ ነው። በዚህም አምላክ የጸጋ ውኅደት ይዋሕደናል። መልካሙን መንገድም ይመራናል።

7ኛ ተግባረ ዕድ፦ ይህም ማለት በዚህች ምድር እስካለን ድረስ የምንበላውን የምንለብሰውን እና ሌሎች ለሥጋችን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማግኘት መስራት ነው። ጌታም ጥረህ ግረህ ብላ ብሎናል። ስለዚህ ከፈጣሪ ሕግ የማያወጡ ሥራዎችን ማረስ መቆፈር ማስተማር መጻፍ ማከም ሕንጻ መስራት ወዘተ የመሳሰሉ ስራዎችን መስራት ነው።

8ኛ ንሥሓ፦ ይህ ደግሞ ቅጣት እንደሚያስቀጣ እያወቅን በድፍረት ሳናውቅ በስህተት የሰራነውን በደል በንሥሓ አባቶቻችን በኩል ተናግረን ቀኖና ተቀብለን እግዚአብሔርን ይቅርታ ጠይቀን ወደ መልካም ስራዎች የምንገባበት በር ነው።ንሥሓ መጸጸት ማለት ነው። ምን ነክቶኝ ነው ይህን ክፉ ስራ የሰራሁት ብለን ጌታዬ ሆይ በቸርነትህ ማረኝ የምንልበትና ጥፋታችንን ለማረም እና መልካም ስራ ለመስራት ከፈጣሪ የሚሰጥ ሁለተኛ ዕድል ነው። ወድቄ ልሰበርና እጠገናለሁ እንደማንል ሁሉ። ኃጢአት ልስራና ንሥሓ ልግባ ግን አይባልም። ኃጢአት

ለመስራት አቅዶ ንሥሓ ለመግባት ማሰብ አይገባም። እስከዛሬም አድርገነው ከሆነ ለዚህም ንሥሓ ገብተን ሕይወታችንን ማስተካከል ይገባናል።

9ኛ ትሕትና፦ ይህ ደግሞ እኛ በብዙ መንገድ ደካሞች አላዋቂዎች መሆናችንን አውቀን በሌሎች አለመፍረድን ያካትታል። አለማወቅ ስለሚገድበን ፈጣሪ በተለያዩ አምሳላት ስለሚገለጽ ለማንኛውም ሰው ራስን ከልብ ዝቅ ማድረግ ነው። ሁሉም ሰው ከአንተ የከበረ እንደሆነ አስበህ መኖር ማለት ነው። ትሕትና ደካማነታችንን አውቀን ረድኤተ እግዚአብሔርን መሻት ነው።

10ኛ ትዕግሥት፦ ይህ ደግሞ ነገር አላፊ ቻይ መሆን ማለት ነው። ክፋትን በክፋት ላለመመለስ መታገል ነው። ሰው ሲሰድበን መልሰን ላለመስደብ ፈጠን ፈጠን የሚል ሕዋሳታችንን መግታት ነው። ወዘአዝለፈ ትዕግሥቶ ውእቱ ይድኅን ብሎናል ጌታችንም። በነገራችን ላይ ልባችን ከተመለሰ እንደ ፈያታይ ዘየማን በአጭር ጊዜ ገነት የሚያስገባንን ስራ መሰራት እንችልለን። ቂርቆስ ታላቅ ሰማእት ለመሆን በዚች ምድር የኖራት 3 ዓመት በቂ ነበረች። እኛም ቀሪ ዘመናችንን 1 ቀንም ትሁን 1 ሰዓት መልካም ሰርተንባት እንለፍ።

ኮከብ

እኔ የተማርኩት ኮከብ "የክርስቶስ ምሳሌ" እንደሆነ ነው እንጂ የ666 ምልክት ነው የሚል አልተማርኩም። ኮከብ ይሠርቅ እም ያዕቆብ የተባለ ክርስቶስ ነው። የክርስቶስ የሆነን ነገር ሁሉ ደግሞ ለሰይጣን መስጠት ትልቅ ነውር ነው። የሰይጣን ተከታዮች የእኛ ምልክት ነው ቢሉ እንኳ ለእናንተ ማን ሰጣችሁ ብለን ዞር በሉ ማለት ነው እንጂ የእኛን ውድ ሀብት ሲያስለቅቁን እኛም የእኛን የእነርሱ ነው ብለን ልንለቀው አይገባም። የቀስተ ደመና ምልክትም እንዲሁ ነው። ድንግል ማርያም የቀስተ ደመና ምሳሌ ናት። ከዚያ ይህን ቀስተ ደመና "ግብረ ሰዶማውያን" የእኛ ምልክት ነው ሲሉ አሥ የእናንተ ነው ብለን ለምን ዝም እንላለን። ይህኮ ዘረፋ ነው። ግብረ ሰዶማውያን ከመነሳታቸው በፊትኮ ቀስተ ደመና ነበረ። ስለዚህ የእኛ የሆነውን ሁሉ ክፉ ሰዎች ሲወስዱት ዝም እያልን መቀጠል የለብንም። የራሳችንን መልቀቅ የለብንም። ክፉ ሥራን ነው መቃወም ያለብን እንጂ ሰይጣን በሰላም ስም ሲመጣ ሰላምን መጥላት አይገባም። መጥላት የብርሃን መልአክን ሳይሆን የብርሃን መልአክ መስሎ የመጣውን ሰይጣን ነው።

መልካም ሐሳብ

ለሥጋም ለነፍስም የማይጠቅም መልካም ሐሳብ የለም። እንዲሁ በሥጋም በነፍስም ጉዳትን የማያመጣ ክፉ ሐሳብም የለም። ሐሳብ ሲቀደስ ንግግርና ተግባርም ይቀደሳሉ። ሐሳብ ሲረክስ ደግሞ ንግግርና ተግባርም ይረክሳሉ። ሰው ልዑል ኀሊና ሲኖረው በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል። ትምክህቱም፣ ደስታውም እግዚአብሔር ይሆናል። በሥጋዊ ጥቅም የማይታለል፣ ሥጋዊ መከራን የማይሰቀቅ፣ ለእውነት ያደላ ንጹሕና ልዑል ኀሊና ሊኖረን ይገባል። አርበኛና ካህን ሞትን የማይፈራ፣ ለሆዱ ሳይሆን ሁልጊዜም ለእውነት የሚኖር መሆን ይገባዋል። በዚህ ምድር የምንኖረው ለአጭር ጊዜ ነው። ስለዚህ ለዚህች አጭር ሕይወት ብሎ ዘለዓለማዊውን ሕይወት የሚያሳጣ ድርጊት ማድረግ አይገባም። መፍራት ያለብን እግዚአብሔርን ብቻ ነው።

አድርባይነት፣ ዘረኝነት፣ የሥልጣን ጥማት፣ ግላዊ ክብርና የመሳሰሉ ጉዳዮች ፍጻሜያቸው ውርደት ነው። እውነትን ይዘን ውሸትን እስከሞት ድረስ መታገል ያጸድቃል እንጂ አያስወግዝም። እውነትን ይዘው ለሚታገሉ ጀግኖች እግዚአብሔር እድሜንና ጤናን ይስጥልን። ከእውነተኞች ጋር እውነት የሆነው መድኃኔ ዓለም ሁልጊዜም ከእነርሱ ጋር አለ። ከሐሰተኞች ጋር ደግሞ የውሸት አባት ዲያብሎስ ከዚያ አለ። ሰይጣን ቢረዳህ እስኪያዋርድህ ድረስ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር እርዳታ ግን ዘለዓለማዊ ሕይወትን እስከማግኘት ያደርሳል። የሚዲያ ጋጋታ መሬት ላይ ያለውን እውነታ አይቀይረውም። ነጩን ጥቁር ቢሉት ነጭነቱን አይቀይረውም። ጥቁሩን ነጭ ቢሉትም ጥቁርነቱን አይለውጠውም።

በእንተ ልደት

ወልድ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአብ ከሰው የማሰብ አቅም በላይ በሆነ መንገድ ከአብ ተወለደ። አብ ኖሮ ወልድ ያልነበረበት ዘመን የለም። ስለዚህ በቀዳማዊ ልደቱ አባት ከልጅ ለቅጽበት ያህል እንኳን አይቀድምም። በዚህ ጊዜ የመወለድ ትርጉምም መውጣት ነው። ይህንንም በምሳሌ ለመረዳት የፀሐይ ብርሃን ከፀሐይ ክበብ እንደሚወጣው ያለ ነው። በዚህ ጊዜ ክበቡ ይቀድማል ብርሃኑ ይከተላል አንልም። የፀሐይ ክበብ ከፀሐይ ብርሃን ተለይቶ አያውቅምና። በዚህ አምሳል አብ ወልድን ስለወለደው ከወልድ በፊት ነበረ አንለውም። በዘመን አንድ ናቸውና። ሊቅ አሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ ወዕሩያን እሙንቱ በቅድምና እንዲል። የወልድ ከአብ መወለድ ዘኢየኀልቅ ልደት ይባላል። ይህም ማለት ሁልጊዜ ሲወለድ ይኖራል ማለት አይደለም። ሁልጊዜም ለዘለዓለሙ ወልድ ወልድ ሲባል ይኖራል ማለት ነው። ዘኢየኀልቅ መባሉ ከአብ በመወለዱ ተመትሮ ስለሌለበት ነው። በእኛ ልማድ ሕፃን ከእናቱ ሲወለድ ከእናቱም በህልውና ይለያል። ወልድ ከአብ ሲወለድ ግን በህልውና ከአብ ሳይለይ ነው። ይህንን ለመግለጽ ዘኢየኀልቅ ልደቱ እየተባለ ይነገራል። ቅድመ ዓለም የነበረ ወልድ ሰውን ለማዳን ከሰው ተወለደ። ይህኛው ልደት ደኃራዊ ልደት ይባላል። ደኃራዊነቱ ለቀዳማዊው ልደት ነው። አንዳንድ ሰዎች ድንግል ማርያም ፈጣሪን ከወለደችው እርሷን መጀመሪያ ማን ፈጠራት እያሉ ሊጠይቁ ይችላሉ። ድንግል የወለደችው ፈጣሪዋን ነው። ድንግል ወለደቶ ለገባሪሃ ወውእቱኒ ፈጠረ ወላዲቶ እንዲል ማር ኤፍሬም። ከድንግል ማርያም የተወለደው እርሷን ቀድሞ የፈጠረ አምላክ ነው። ከእርሷ ሲወለድ አምላክነቱን እና የአምላክነቱን ሥራ ሳይለቅ ነው። ቀድሞ ከአብ ያለ እናት የተወለደ ወልድ በኋላ ያለ አባት ከድንግል ማርያም ተወለደ። የወልድ ህልውና ከማርያም ወዲህ አይደለም። ፎጢኖስ የተባለ ሰው ለፊኤ እማርያም ክዋኔሁ ለወልድ ብሎ የክሕደት ትምህርትን አስተምሮ ነበር። ነገር ግን ጌታ ሲያስተምር አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርኩ ብሎ ስለተናገረ የፎጢኖስ ሐሳብ ልብ ወለድ መሆኑ ታወቀ። ስለዚህ የወልደ እግዚአብሔር ልደታት ሁለት ናቸው። እነዚህም ቀዳማዊ ልደቱ ከአብ ያለ እናት፣ ደኃራዊ ልደቱ ከድንግል ማርያም ያለ አባት በድንግልና ነው። የጌታ ልደት መላእክትንና ሰዎችን አንድ ላይ እንዲያመሰግኑ ያደረገ ልዩ ቀን ነው። ሰይጣን በባርነት ሥር አድርጎ ወደ ሲያል ያግዘን ነበር። አሁን ከዚያ ግዞት ነጻ የሚያወጣ ንጉሠ ነገሥት እግዚአብሔር በሥጋ ተወለደልን። ግዕዛነ ሥጋን ግዕዛነ ነፍስን አገኘን። ሰው ሲፀነስ ሰይጣን የወንዱን ዘር ምክንያት አድርጎ ይቆራኘውና ሰው ከተወለደ ጀምሮ ክፉ ሥራን እንዲሠራ ያስደርገው ነበር። ጌታ ግን መንገድ

ለወጦበታል ያለ ወንድ ዘር ተወልዶ ይህንን የሰይጣንን ክፉ ሥራ አራቀልን። ሊቁ ተወልደ በአምሳሊከ ከመ ይለድከ በአምሳሊሁ ብሎ እንደተናገረው። እኛን የሰው ልጆችን በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ ያደርገን ዘንድ እርሱ ከሰው ተወለደ። እርሱን መስለን እንወለድ ዘንድ እኛን መሰለ ተወለደ። የነቢያት ትንቢት በክርስቶስ መወለድ ተረጋገጠ። ይሁንና ዓለም መድኃኒቷን የተቀበለችው በከብቶች በረት ነው። ድንግል ማርያም ጌታን ከወለደችው በኋላም በድንግልና ጸንታ ኑራለች። ከወለደችው በኋላ አውራ ጣቱን አሰረችው። እንዲህም ማድረጓ የወለደችው ክርስቶስ ምትሐት አለመሆኑን ለማስረዳት ነው። በተጨማሪም ዮሴፍ ኒቆዲሞስ በዕለተ ዐርብ እንዲህ ይገንዙሀል ስትል ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ማቴዎስ፣ ታኅሣሥ 29፣ ማክሰኞ ቀን፣ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ተወለደ። በዘመነ ማቴዎስ ተወለደ እንዳንልማ ማቴዎስ፣ ዮሐንስ፣ ሉቃስ፣ ማርቆስ በኋላ የተነሡ ሰዎች አይደሉምን? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። መነሣቱ መልካም ነው። ይህን የመሰለ ዓለም መጋቢት 29 ቀን በዕለተ እሑድ በዘመነ ዮሐንስ ተፈጠረች እየተባለ ይነገራል። ይህ አቆጣጠር አሁን ያለውን አቆጣጠር ይዘን ወደኋላ በመቁጠር የደረስንበት መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል። ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን አይተውት ስለማያውቁ የእርሱን በሥጋ መወለድ እኛ ብቻ ሳንሆን መላእክትም በናፍቆት ይጠባበቁት ነበር። በጠባብ ደረት ተወስኖ በቤተልሔም ሲወለድም እረኞች አዩት መላእክትም አይተው አመሰገኑት። ርእይዎ ኖሎት አእኮትዎ መላእክት እንዳለ ሊቁ። የተወለደው ጌታ በድንግል ማኅፀን ተወስኖ በዓለም መልቶ የነበረና ያለ ነው። ዓለምን የያዘ ጌታ በድንግል ማኅፀን ዓለምነት ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ተቀመጠ። የዓለማት ዓለማቸው በድንግል ማኅፀን ዓለምነት ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ተቀመጠ። ስለዚህም ድንግል ማርያምን ዓለመ ዓለመ ዓለም እንላታለን። ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ። የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬ ተወለደ። የጌታ መወለድ ለዓለም ሁሉ የምሥራች ነው። ጌታ ጥቂት ቡድኖችን፣ ጥቂት ሀገሮችን፣ ጥቂት ሰዎችን ለማዳን አልመጣም። ዓለምን ሁሉ ለማዳን መጥቷል እንጂ። ስለዚህም መድኃኔዓለም ተብሏል። ዮም ተወልደ መድኃኔ ዓለም። ሰው አእምሮው ሰፊ ሆኖ ከሰፈር አስተሳሰብ ወጥቶ ለዓለም ሲያስብ ጌታን ይመስለዋል። በጌታ መወለድ አጋንንት እና ባለጊዜ የነበሩት እነሄሮድስ ተከፍተዋል። ጌታን የሚያጠፉ መስሏች 144000 ሕፃናተ ሳሌምን አስገድለዋል። ውሸታቸውን በአደባባይ የሚገልጽ ንጉሠ ነገሥት ክርስቶስ ተወለደ። እውነት ክርስቶስ እነሆ ተወለደልን። ለዚህች ልዩ ቀን ያደረሰን እግዚአብሔር ይመስገን።

ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊት ዓለም ናት። ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት ለመዳን የተጠጓት ጥቂቶች ናቸው። ታላላቅ ቀኖናዎቿ ተሸረው፣ ምእመናን ልጆቿ በየቦታው መከራ እየደረሰባቸው ይገኛል። የቤተክርስቲያን መሪዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለሁሉ እንደየሥራው የሚከፍል እርሱ ነው። በእርሱ ሁልጊዜም ደስ ይለናል። እርሱን ጌታችንን መስለው፣ ፍርሃትን አስፈርተው ለእውነት የሚቆሙ ጥቡዓን አበው ማግኘት ከባድ እየሆነ ነው። አድርባይነት ነግሦ፣ ሥጋዊነት ሠልጥኖ፣ እውነት ተጨቁና ውሸት ነግሣ ማየት የተለመደ ሆኗል። ነገር ግን ምን ጊዜም እውነት አሸናፊ ናት። ሁሉ ያልፋል። የማታልፍ እውነት ናት። እውነተኞችም ሁልጊዜ ይደሰታሉ። የምንጠብቀው ንጉሥ ከ2016 ዓመት በፊት ታኅሣሥ 29 ቀን በዕለተ ማክሰኞ

ተወልዶልናል። እውነት ክርስቶስ ተወልዶልናል። ከዚህ በኋላ በእውነት ክርስቶስ መኖር የእኛ ድርሻ ነው። እውነትን በሰውነታችን ማንገሥ ይገባናል።

ኦርቶዶክሳዊነት

ኦርቶዶክሳዊ ጎሊና ቅን ጎሊና ነው። ቀጥ ያለ ነው። ሁልጊዜም ርቱዕ ነው። ኦርቶዶክሳዊ ሰው ክፉ ሥራን ሁሉ አያደርግም። ከቅን ጎሊናው በጎ ሐሳብን ያመነጫል። በአንደበቱም መልካም ነገርን ይናገራል። ኦርቶዶክሳዊ ሰው አይፈራም። ሁልጊዜም ትምክህቱ እግዚአብሔር ነው። ሞት አይፈሬ ነው። በሕይወቱም እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን ሥራ ይሠራል። በሞቱም እግዚአብሔርን ያከብራል። ጌታውን ይመስላል። እውነትን ይዞ እስከ መስቀል ይታመናል። በአይሁድ ጩኽት አይሸበርም። ከራሱ ዓላማ ላይ ያተኩራል እንጂ የአይሁድን ከንቱ ጩኽት አያዳምጥም። ኦርቶዶክሳዊ ሰው ለጥፋቱ በግልጽ ይቅርታን ይጠይቃል። ንስሓ ገብቶም ሥጋውን ደሙን ይቀበላል። ፈርቶ ከውሸት ጋር አይስማማም። እንደሰማዕታት ላመነበት እውነት እስከሞት ይታመናል እንጂ። ለሥጋዊ ሕይወቱ ብሎ በነፍስ ጉዳት የሚያመጣበትን ነገር አያደርግም። እውነትን ይዞ ከእውነት ጎን ተሰልፎ ውሸትን እስከ መጨረሻው ይታገላል። አንዳንድ ሰው በዚህ ምድር ሺ ዓመት ይኖር ይመስል ፈርቶ የውሸታሞች መጠቀሚያ ሆኖ ሲታይ ያሳፍራል። ፈሪ ያስጠቃል። በተቻለን አቅም ከፈሪ መራቅ ይገባናል። ኦርቶዶክሳዊ ጎሊና እንዲኖረን እግዚአብሔር ይርዳን።

ዮሐንስ ወንጌላዊ

ከቻልን እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፣ ፍቁረ እግዚእ፣ አቡቀለምሲስ፣ ቴዎሎጎስ ጨክነን እስከ መጨረሻው ክርስቶስን መከተል ነው። ሥጋዊ ፍርሃትን ፈርተን ከእውነት ተጣልተን ክደን ከነበረ ደግሞ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ በፍጥነት ንስሓ ገብተን ወደ ትክክለኛው መስመር መምጣት ነው። ፍርሃትን፣ አድር ባይነትን፣ ውሸትን ካላስወገድን ለእውነት መቆም አንችልም። መሪያችን እግዚአብሔራዊው እውነት ሊሆን ይገባል።

መናፍቃን

ለመመለስ አፍረው ነው እንጂ እውነቱን ያውቃታል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮዋ እንከን የሌለበት ንጹሕ እውነት እንደሆነ ያውቁታል። አንዳንዶች ለሥጋ አድልተው እውነትን ገፍተው ቢሄዱም ጎሊናቸው ሲያሳድዳቸው ይኖራል። ይሁዳ ለገንዘብ ብሎ ከጎሊናው ተጣልቶ ከእውነተኛው ኢየሱስ ርቆ ነበር። በዚያው ክፋቱ እንደጸና ሞቷል።

ኢየሱስ ክርስቶስ

ኢየሱስ የዓለም መድኃኒት ነው። እኛን ለማዳን ስለእኛ ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ያዳነን ቤዛችን ነው። ተሰቅለ በእንቲኣነ የሚለው በመጽሐፈ ሊቃውንት ሲታተት እንደ ጻድቃን እሴት ሸቶ፣ እንደ ኃጥኣን ስቶ አይደለምና በእንቲኣነ (ስለእኛ) አለ እንላለን። ስለእኛ የሰውነትን ሥራ ሠርቷል። በመስቀል ተሰቅሎም ከአባቱ ጋር አስታርቆናል። ይህንን ቤተክርስቲያን ከሐዋርያት

ጀምሮ እስካሁን የምታስተምረው ትምህርት ቢሆንም ከሓድያን ግን እነርሱ በቅርብ የደረሱበትና ቤተክርስቲያን የማታውቀው ያስመስሉታል። ራሳቸው በፈጠሩት ውሸት ሌላውን ለመውቀስ ይጥራሉ። ቅድስት ቤተክርስቲያን ጻድቃንን የጸጋ ክብር ታከብራለች። አንዳንዶች ጻድቃንን ማክበር ክርስቶስን እንዳለማክበር ቆጥረው ቤተ ክርስቲያንን ሲሰድቧት ይስተዋላል። እንኳንስ በእግዚአብሔር ሕግ ተመርተው እግዚአብሔር የሚወዳቸው ጻድቃንን መውደድና ማክበር ማንኛውንም ሰው እንድንወድኮ ከአሥሩ ሕግ በአንዱ ታዝዘናል። ራሱ ክርስቶስ እንኳ ጻድቃንን "እናንተ የአባቴ ቡሩካን" ብሎ እንደሚጠራቸው በወንጌል ተገልጿል። "ቡሩካን" እንዳላቸው አስተውል። የክርስቶስን እናት ድንግል ማርያምን ለምን ትወዷታላችሁ ብለው ይቀናሉ። ክርስቶስ ሕግን ፈጽሟል። ከሕግ አንዱ ደግሞ እናትን ማክበር ነው። ስለዚህ ክርስቶስ እናቱን አክብሯታል። ታዲያ እርሱ ያከበራትን ብናከብራት ችግሩ ምን ላይ ነው። አምላክ ናት ብለንኮ አይደለም ያከበርናት። አምላክን በሥጋ የወለደች ናት ብለን ነው የምናከብራት። ክብሩም የጸጋ ክብር ነው። ታቦትን የምናከብረው የከበረው የክርስቶስ ሥጋና ደም ስለሚፈተትበት ነው። የኢየሱስ ስም ስለተጻፈበት ነው። የምናከብረው አክብሮትም አምላክ ነው ብለን አይደለም። የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስሙ ስለተጻፈበት ነው። ክርስቶስን ሁልጊዜ እንድናስብ የሚያደርጉንን ብናከብራቸው እንኳ ክብሩ የጸጋ አክብሮት እንጂ አምላክ ስለሆኑ አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቷ፣ አስተምህሮዋ ንጹሕ ነው። ትምህርቷ የተመሠረተው በኢየሱስ አስተምህሮ ነው። የአንዳንድ አማኞችን ስሕተት አጉልቶ በማሳየት ቤተክርስቲያንን ለመንቀፍ መጣር እውነትን ላለማግኘት የሚደረግ ጥረት ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ አማኞች ከምእመን እስከ ፓትርያርክ በግላቸው ሥጋዊ ፍላጎት አይሎባቸው ሊሳሳቱ አልፎም ሊክዱ ይችላሉ። ያ ግን የራሳቸው ችግር እንጂ የቤተክርስቲያን አይደለም። በቤተክርስቲያን አስተምህሮ መሄድ አቅቷቸው ቢወድቁ ችግሩ የራሳቸው ነው። በትእቢት ተወጥረው ከእውነተኛው አስተምህሮ አፈንግጠው የሄዱ ሰዎች ከጨዝትና ከእልህ እንዲሁም ከትእቢት ወጥተው በንጹሕ ኅሊና አስተምህሮዋን አይተው ወደ እውነት ቢመለሱ መልካም ነው።

ጥምቀት

ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ መሬታዊ። እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ። ክርስቶስ ከጎኑ ከፈሰሰ ውሃ (ማየ ገቦ) ዳግመኛ ወለደን። ለእርሱ ዛሬም ዘወትርም ክብር ምስጋና ይግባው።

ያልበላንን ባናክ

የኢትዮጵያ ባንዲራ ታሪካዊ ባንዲራ ነው። ምእመናን በጥምቀት ቀንም በሌላም ጊዜ ቢለብሱት መብታቸው ነው። ሀገሩን፣ ታሪኩን፣ ሃይማኖቱን የሚወድ ምእመን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ያለበትን ባንዲራ ቢለብስ ምንም ዓይነት ነውር የለበትም። ይህንን የማይወዱ ሰዎች ካሉ እነርሱ አመለካከታቸውን ከሦስት ክንድ ከስንዝር (ከጠባብ አመለካከት) መውጣት አለባቸው እንጂ እነርሱን ለማስደሰት ሲባል ምንም ዓይነት ነውር የሌለበትን ጉዳይ መከልከል አይገባም።

ጌታ ለምን ተጠመቀ?

፩) ማያትን ይቀድስ ዘንድ

፪) ለተጠማቅያን አብነት ለመሆን

፫) ትንቢቱን ለመፈጸም

ጌታ የት ተጠመቀ

፩) ዮርዳኖስ በተባለ ወንዝ

ኢየሱስ በማን ተጠመቀ

፩) በዮሐንስ መጥምቅ

ክርስቶስ በምን ተጠመቀ

፩) በውሃ

በዮርዳኖስ ለምን ተጠመቀ

፩) የአዳምንና የሔዋንን የዕዳ ደብዳቤ ለመሻር

መድኃኔዓለም #መቼ #ተጠመቀ

በ30 ዓመቱ፣ ጥር 11 ቀን በዕለተ ማክሰኞ ሌሊት 10 ሰዓት ላይ ተጠመቀ።

አማኑኤል ሲጠመቅ ምን ሆነ

ዮሐንስ መጥምቅ ውሃ በእፍኙ አድርጎ በጌታ ራስ ሲያደርግ ውሃዎች በጌታ ራስ ላይ ሳሉ ይፈሉ ነበር። ማያት ፈልሁ ዲበ ርእሱ እንዲል። በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በራሱ ላይ አረፈ። አብም የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ በደመና ላይ ድምፁን አሰማ።

ምእመናን ልጅነትን ለማግኘት በምን #ይጠመቃሉ

፩) ከክርስቶስ ጎን ከፈሰሰው ማየ ገቦ

ሰዎች ሲጠመቁ ምን ይሆናሉ?

፩ የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ይሆናሉ።

፪) ከጥምቀት በፊት የሠሩት ኃጢአት ይሠረይላቸዋል።

ካህኑ ውሃውን አቅርቦ ጸሎትን ሲጸልይበት ውሃው ከክርስቶስ ጎን የፈሰሰውን ማየ ገቦ ይሆናል። ማየ ገቦ ደግሞ መለኮት የተዋሐደው ውሃ ነው። ስለዚህ በዚያ ተጠምቀን የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን። ሕፃናት ወንዶች በ40 ቀን፣ ሴቶች በ80 ቀን ይጠመቃሉ። ንኡስ ክርስቲያን ደግሞ ሦስት ዓመት የሃይማኖትን ትምህርት ተምረው በማንኛውም የእድሜ ጊዜ ሳሉ ይጠመቃሉ። ምሥጢረ ጥምቀት ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢር ስለሆነ ማንኛውም

ክርስቲያን ሊያውቀው ይገባል። ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ መንግሥተ ሰማያት መግባት እንደማይችል ጌታ በወንጌል አስተምሮናል (ዮሐ. ፫፣፫)። ከመንፈስ ቅዱስ ተብሎ መንፈስ ቅዱስ በስም ተገልጾ ቢመጣም በግብረ ባሕርይ አንዱ ቢጠቀስም ሁለቱም እንዳሉበት ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። የምንወለደው ከአብ፣ ከወልድ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ነውና። ይህንን ምሥጢረ ጥምቀት ከምሥጢረ ሥላሴ ጋር አዋሕዶ መያዝ ይገባል። ሥላሴ በአካላዊ ግብር፣ በአካላዊ ግብር ስም፣ በአካል ስም፣ በአካል፣ በከዊን፣ በከዊን ስም ልዩ ልዩ ናቸው። በእነዚህ ለአብ የተነገረው ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ፣ ለወልድ የተነገረው ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ፣ ለመንፈስ ቅዱስ የተነገረው ለአብ ለወልድ አይሆንም። በግብረ ባሕርይ፣ በግብረ ባሕርይ ስም፣ በባሕርይ፣ በባሕርይ ስም ግን አንድ ናቸውና ለአንዱ አካል የተነገረው ለሁለቱም ይሆናል። ግልጽ ለማድረግ ያህል የአካል ስም የሚባሉት፡-

፩) አብ

፪) ወልድ

፫) መንፈስ ቅዱስ

የአካል ግብር የሚባሉት፡-

፩) መውለድ፣ማሥረጽ

፪) መወለድ

፫) መሥረጽ

የአካል ግብር ስም፡-

፩) ወላዲ፣ አሥራጺ

፪) ተወላዲ

፫) ሠራጺ

ከዊን፡-

፩) ልብ መሆን

፪) ቃል መሆን

፫) እስትንፋስ መሆን

የከዊን ስም፡-

፩) ልብ

፪) ቃል

፫) እስትንፋስ

አብ ልብ፣ ለባዊ፣ ነባቢ፣ አንባቢ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ አለባዊ ነው። ወልድ ቃል፣ ነባቢ፣ አንባቢ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሕይወት፣ ሕያው፣ ለባዊ፣ አለባዊ ነው።

የባሕርይ ስም፡- የሥላሴ የባሕርይ ስም አይታወቅም። ይህን የማይታወቀውን የባሕርይ ስም ለመግለጽ ግን ሊቃውንት መለኮት፣ ዕበይ እያሉ ይገልጹታል።

የባሕርይ ግብር፡- መፍጠር፣ መግዛት፣ ሁሉን ቻይ መሆን፣ ዘለዓለማዊ መሆንና የመሳሰሉት ናቸው።

የባሕርይ ግብር ስም፡- ፈጣሪ፣ እግዚአብሔር፣ አምላክ፣ መለኮት፣ ሕያው፣ ኤልሻዳይ፣ ከኃሌ ኵሉ፣ ጌታ እና የመሳሰሉት ናቸው። ይትባረክ እግዚአብሔር ዘከሠተ ለነ ዘንተ ትምህርተ ከመ ናእምሮ።

እውነት

የሃይማኖት አባት ድርሻ ስለ ሰላም መስበክ ነው። ይህን የማያውቅ ይኖራል ብየ አላስብም። ነገር ግን ስለ ሰላም መስበክ ብቻ አይደለም። እውነትንም በግልጽ ማንንም ሳይፈራና ሳያፍር የሚናገር ነው። ብዙው ሰው ሰላምን በመስበክ ሰበብ እውነታውን ሳይናገር ያልፋል። ፈሪነትን በዚህ መልኩ መደበቅ አይቻልም። ኦርቶዶክሳዊ አባት ፍትሓዊ፣ እውነተኛ፣ ሰላማዊ እና ሌሎችንም ክርስቶሳዊ አስተምህሮዎች አዋሕዶ የያዘ ነው። የሃይማኖት አባት ድርሻ ስለሰላም ብቻ መስበክ ነው ብሎ የሚያስብ ሰው እነ ቅዱስ ሚካኤል ሰይጣንን እንደተቃወሙ ሲሰማ ሰላማውያን አይደሉም ብሎ ሊደመድም ይችላል። ከመላእክት ከቅዱስ ሚካኤል የበለጠ ሰላማዊ ግን ይገኝ አይመስለኝም። ሰይጣንን መቃወም ሰላምን ያለመፈለግ ምልክት ተደርጎ መታሰብ የለበትም። ቅዱስ ሚካኤል መልአከ ምሕረት እየተባለ ይጠራል። የምሕረት የሰላም አባት ነው። ነገር ግን ከአምላኩ የተቀበለውን እውነት የሚቃወም ሌላ አምላክ ነኝ ባይ ፍጡር (ሰይጣንን) ባየ ጊዜ በመላእክት ዓለም ፊታውራሪ ሆኖ የተቃወመው እርሱ ነው። ፈሪ ካህን አስጠቂ ነው። በጎቹ በተኩላ እየተሰቃዩ ተኩላውን የማይቃወም ካህን ወይም ጳጳስ ወይም መምህር የተኩላ ተባባሪ ነው። ወይንም ደግሞ ተኩላውን ፈርቶ በጎቹ ሲበሉ ቆሞ የሚያይ ክፉ እረኛ ነው። መልካም እረኛ ግን ስለበጎቹ ከእነርሱ በፊት ራሱን አሳልፎ ይሰጣል። ሞትን ፈርቶ ምእመናንን የሚያሰቃየውን አካል የማይቃወም ካህን "መኑ የኀድገነ ፍቅሮ ለክርስቶስ" ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? ረኀብ ነውን? ሞት ነውን? ሰይፍ ነውን? ወዘተ ብሎ የመናገርና የመስበክ ሞራል የለውም። ፈሪነትንና ቦቅቧቃነትን ማሸነፍ ያስፈልጋል። በዚህች ምድር ሺ ዓመት አንኖርም። መሞታችን ላይቀር ሞትን ፈርቶ ኢፍትሓዊ ድርጊት ሲደረግ ዝም ማለት አይገባም። ፍቅረ ንዋይ ያየለበት እንደ አባ አጋግዮስ ያለው ሆዳም ጳጳስ በምእመናን ላይ መከራን ያመጣል። እነ ቅዱስ ቴዎድሮስ በናድሌዎስ ሮምን ከገጠሟት ጠላቶች ጋር ገጥመው

ሳለ አባ አጋግዮስ ግን በጎን ገንዘብ ተቀብሎ ከጠላት ጋር ይተባበር ነበር። ቅዱስ ቴዎድሮስ በናድሌዎስ የጀግና ተዋጊዎች ተምሳሌት ነው። ጀግንነቱን ገድለ ቅዱስ ቴዎድሮስ በናድሌዎስን ብታነቡ ታገኙታላችሁ። በአሁኑ ዘመን እንደ አባ አጋግዮስ እኖር ባይ፣ እከብር ባይ ልቡናን ያልተው ሰዎች ምእመናን ሲሰቃዩ በዝምታ ከአሰቃዩ ጋር ይስማሙና ምእመናንን የሚያሰቃየውን አካል አንድ አባት ሲቃወሙ ሲሰሙ ግን ፈሪነታቸውን ለመደበቅና እነርሱ ሰላማዊ ለመምሰል የሃይማኖት አባት ሰላምን ይሰብካል እንጂ ክፉዎችን መቃወም የለበትም ይላሉ። ጀግና እውነቱን ተናግሮ ይሞታል። ቢኖርም እውነትን እየተናገረ ይኖራል። ሲሞትም እውነትን ይዞ ይሞታል። ሰማዕታት በዚህ ይታወቃሉ። ሲኖሩም እውነትን ከሰላም ጋር አዋሕደው ይኖራሉ። ሲሞቱም ስለእውነት ይኖራሉ። ይህንን ከታላቁ ቅዱስ ቅዱስ ቴዎድሮስ በናድሌዎስና ከሌሎችም ቅዱሳን ታሪክ እንረዳለን። ዛሬ የቅዱሱ መታሰቢያ ዕለት ነው። በረከቱ ይደርብን።

ቃና ዘገሊላ

የቃናውን ወይን የቃና ሰርገኞች ጠጥተው ጨርሰውታል። ከትውልድ ወደ ትውልድ ሳይተላለፍ በታሪክ ብቻ እንማረዋለን። የቀራንዮውን ወይን ግን እስከ ዕለተ ምጽአት ምእመናን ንሥሓ እየገቡ ይጠጡታል። እርሱም ንጽሐ ሥጋን ንጽሐ ነፍስን ያጎናጽፋቸዋል። ለምእመና ልዩ ቀን (ዕለት ኀሪት) ንሥሓ ገብተው ከዘለዓለማዊው ወይን የሚጠጡበት ቀን ናት።

ዕለት ኀሪት ወዕለተ መድኃኒት

እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡባት ቀን ዕለት ኀሪት ትባላለች። ባሕረ ኤርትራን የተሻገረባት ቀን ደግሞ ዕለተ መድኃኒት ትባላለች። ጌታ የተፀነሰባት ዕለት ዕለት ኀሪት ትባላለች። የተወለደባት ቀን ደግሞ ዕለተ መድኃኒት ትባላለች። አንድም የተወለደባት ቀን ዕለት ኀሪት ትባላለች። የተሰቀለባት ቀን ዕለተ መድኃኒት ትባላለች። አንድም የተሰቀለባት ቀን ዕለት ኀሪት ትባላለች። ከሙታን የተነሣባት ቀን ዕለተ መድኃኒት ተብላበች። ሰው ንሥሓ የሚገባባት ቀን ዕለት ኀሪት ትባላለች። ሥጋውን ደሙን የሚቀበልባት ቀን ደግሞ ዕለተ መድኃኒት ትባላለች። ዕለት ኀሪት፣ ዕለተ መድኃኒት በንባብ እንጂ በምሥጢር አንድ ናቸው።

ጥምቀት

ጌታ ጥር ፲፩ በውሃ ተጠመቀ። በዕለተ ዐርብ ከጎኑ በፈሰሰው ንጹሕ ውሃ (ማየ ገቦ) ደግሞ እኛ እንድንጠመቅ አደረገን። ጌታ በቃና ዘገሊላ ውሃውን ወደ ወይን ለውጦ ሠርገኞችን አስደሰታቸው። ወይን ያስተፈሥሕ ልበ ሰብእ ማለትኮ ይህ ነው። ወይን ደመ ክርስቶስ ምእመናንን ያስደስታል። በዕለተ ዓርብ ደሙን አፍስሶ አነጻን። ወይን ክርስቶስ እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚነሡ ምእመናን መድኃኒት የሚሆን መጠጥን ሰጠን። ስለ ቃና ወይን ስንናገር ንሥሓ ገብተን ዋናውን ወይን ደመ ክርስቶስን መቀበል ይገባናል። ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በክርስቶስ ላይ ነው። ስለሆነም አካሉ ናት። የቤተክርስቲያን አገልግሎት ሁሉ ማዕከሉ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ብዙ ጊዜ የቤተክርስቲያንን ትምህርት ጠንቅቀው ሳያውቁ ትተዋት የሄዱ ሰዎች ማንነቷን ሳያውቁ ሲሳደቡ ይስተዋላል። በማንነቷ ሳይሆን እነርሱ ናት

ባሏት ማንነት ይሰድቧታል። ነገር ግን ይህ አይገርምም። አካሏ ክርስቶስ ምንም ጥፋት ሳይኖርበት በአደባባይ ተሰድቧል። በአደባባይ ተሰቅሏልና። ስለዚህ የሌላ እምነት ሰዎች ቤተክርስቲያን ስለኢየሱስ የምታስተምረው ምን እንደሆነ መጀመሪያ ጠይቁ እወቁ። የቤተክርስቲያን አካል፣ የቤተክርስቲያን ሕይወት በመስቀል ተሰቅሎ ያዳነን ኢየሱስ ነው። "እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን" እንዲል ቅዱስ ጳውሎስ።

ክርስቶስ ማን ነው?

√ ቅድመ ዓለም የነበረ የአብ ልጅ ነው።

√ ከድንግል ማርያም የተወለደ ፍጹም ሰው ነው።

√ ፍጹም አምላክ ነው

√ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ ነው።

√ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው።

√ አዳምን ለማዳን ሥጋን የተዋሐደ ነው።

√ ቤዛችን፣ መድኃኒታችን፣ ጌታችን ነው።

√ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው።

√ ክርስቶስ ንጉሠ ነገሥት፣ አምላክ ነው

√ ከሁለት አካል አንድ አካል፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የሆነ ነው። ሰው የሆነ አምላክ፣ አምላክ የሆነ ሰው ነው። አምላክም ሰውም ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ራሱ ስለራሱ የነገረን ይህንና የመሳሰለውን ነው። ሁልጊዜም እኛን ለማዳን ስለኛ ቤዛ ሆኖ በመስቀል የተሰቀለልንን ጌታ እናስበዋለን። መመኪያችን፣ ደስታችን፣ ሕይወታችን እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የምዕራባውያን ሴራ

ከሰፈርህ ሁለት ጎረምሶች ሲጣሉም የምዕራባውያን ሴራ ነው። በመንገድ ስትሄድ እንቅፋት ሲመታህም የምዕራባውያን ሴራ ነው። በቃ ማንኛውም ክፉ ነገር ሲያጋጥምህ የምዕራባውያን ሴራ ነው። ለብዙ ችግሮች መፍትሄ እንዳናገኝ ያደረጉን ይህን የመሳሰሉ አስተያየቶች ናቸው። የሴራ ድርሰት እየደረሱ ሰውን ማበሳጨት እና ማስቆጨት በጣም ቀላልና ተራ ስራ ነው። አሁንብአንድ ክርስቲያን ፈረንጅ ቤተክርስቲያን ገብቶ ቢያስቀድስ አብዛኛው ሰው በተነገረው የሴራብስብክት ምክንያት ሴራ ነው ብሎ እንዲያስብ ነው እየተደረገ ያለው። ፈረንጅን የሚጠላ ክርስቲያን ካለ መጀመሪያ የተጣላው ከሃይማኖቱ አስተምህሮ ጋር መሆኑን ይወቅ። የሃይማኖታችን መሰረታዊ ትምህርት እግዚአብሔርን ውደዱ ሰውን ውደዱ የሚል ነውና። ሰውን እየጠሉ እግዚአብሔርን እወዳለሁ ማለት ደግሞ ውሸታምነት ነው። ሰውን እየተሳደቡ

ቅዱሳንን አከብራለሁ ማለት ትልቅ ሰይጣናዊ ስላቅ ነው። አንተ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ፍቅር የቅዱሳን ፍቅር በልብህ አለን??? ካለህማ እስኪ ሰውን ሁሉ ስትወድና ስታከብር ልይሃ። ሰውን እየተሳደቡና እያስቀየሙ የእግዚአብሔር ወዳጅ የቅዱሳን ወዳጅ መሆን ይቻላልን???። በቲዮሪማ በወሬማ ሰይጣንስ ቢሆን ከአንተ የበለጠ ቅዱሳንን ያውቃቸው የለምን?? በወሬማ በቲዮሪማ እግዚአብሔርን ከአንተ ይልቅ ሰይጣን ያውቀው የለምን? ምዕራባውያን አፍሪካውያንን ለመቀራመት ሴራ ሰርተው ነበር። በዚያ ሴራቸውም ከኢትዮጵያ ውጭ ሙሉ አፍሪካን ቅኝ ግዛት አጽንተው ዘርፈዋት ሄደዋል። ይሄ እውነት ነው። ከዚያም በኋላ እስካሁን በሥርዓተ ትምህርት በሥርዓተ መንግሥት እየገቡ ሀገርን እስከማፍረስ እንደ ሚደርሱ በሶርያ፣ በሊቢያ፣ በሩሲያና በዩክሬን ጦርነት፣ በእኛ የእርስ በእርስ ጦርነት ወዘተ አይተናል። እያየንም ነው። ብዙ መልካም ነገሮች እንዳሏቸው ሁሉ ብዙ ክፉ ነገሮችም አሏቸው። መልካሙን መጠቀም ክፉውን መተው ግን የእኛ ድርሻ ነው። ሰይጣንን ክፋቱን አስትተህ መልካም ማድረግ ከባድ ነው። በሰይጣን ክፋት መበሳጨት አያስፈልግም። በሰይጣን ክፋት ለመጎዳት ራስህን ካላመቻቸህ በስተቀር ሰይጣን ዘው ብሎ አንተን ማሳሳት አይችልም። እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ከሰይጣን አገዛዝ ነጻ አውጥቶናል። ከዚህ በኋላ ሰይጣንን ወደ እኛ ማቅረብም ማራቅም የእኛ የሰዎች ስልጣን ነው። የራሳችንን ችግር በሰይጣን ማሳበብ ነውር ነው። ሰው የራሱን ችግር በሰይጣን ካሳበበ መታረም አልፈለገም ማለት ነው። የራሱን ችግር ማስተካከል አልፈለገም ማለት ነው። ሁለት ወንድማማች ተጣልተው ሲደባደቡ ለዚህ ምክንያት ሰይጣን ነው አይበሉ። ራሳቸው ናቸው። ችግራቸውን ቁጭ ብለው በመነጋገር መፍታት ይችሉ ነበርና። ማጠቃለያ:- ምዕራባውያንም ሆኑ ሰይጣን እኛን እርስ በእርስ ለማጣላት በእኛው መካከል ያሉ ልዩነቶችን ይጠቀማሉ። ይህ ደግሞ የጠላት ታክቲክ ነው። ይህ እንዳይሆን በእኛ መካከል ያለውን ልዩነት ፊት ለፊት ተነጋግረን ማጥበብ አለብን። በዚህ ጊዜ ምዕራባውያንም ሰይጣንም ወደ እኛ መግቢያ አያገኙም። በተረፈ ወንድምህን ባንዳ በማለት ለውጥ የምታመጣ አይመስለኝም። ደግሞስ ባንዳው አንተ ራስህ ብትሆንስ? ምዕራባውያንም ሆኑ ሰይጣን በደረሱት ድርሰት እርስ በእርስ እንደ ባንዳ እንድትተያዩ እና አንዱ አንዱን ባንዳ እያለ ጥላቻውን እንዲያከር ቢሆንስ?

በግልጽ መነጋገር

ችግርን ለመፍታት ፊት ለፊት መነጋገርን የሚፈራ ሰው ክርስቲያን አይመስለኝም። የምስክር መምህራንን እነርሱ በሌሉበትና ራሳቸውን መከላከል በማይችሉበት ሁኔታ በአሽሙር በአደባባይ የሚሳደብ መምህር መምህር አይባልም። እንዲህ ዓይነት ሰው ችግርን ተቀራርቦ ከመፍታት ይልቅ ችግርን በማባባስ የሰይጣን ተባባሪ ነው። ክርስቲያናዊ አንድነትን የሚሰብክ የክርስቲያናዊ አንድነት ዋና ጠላት እንዲህ ዓይነቱ ሰው ነው። መምህራንን ፊት ለፊት ማነጋገር እየተቻለ በጓሮ ማማት ነው ሰይጣናዊነት። ኑ ፊት ለፊት እንነጋገር። የራሳችንን ችግር በሌላ ከምናሳብብ የእኛው መሆኑን አምነን ተነጋግረን እንፍታው። የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓለማ የችግሮች ምንጭ እኛ ራሳችን ብንሆንስ ብለን ራሳችንን በደንብ እንድንፈትሽ ነው።

ደብረ መድኃኒት ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ወቅዱስ መርቆሬዎስ ቤተ ክርስቲያን ወንበር ተክለው ያስተማሩ መምህራን ዝርዝር

፩) መምህር ወልደ አብ

፪) መምህር በዛብህ

፫) መምህር አካለ ወልድ

፬) መ/ር ወልደ ሰንበት ወልደ ጊዮርጊስ

፭) መምህር አዲስ አድኃኒ

፮) መምህር ፀጋ ኢየሱስ

፯) መምህር ደሴ

፰) መጋቤ ምሥጢር ነቢየ ልዑል

፱) መምህር ጥዑመ ልሳን

፲) መምህር ፀሐይ ተፈራ

፲፩) መምህር ትሕትና ካሰኝ

፲፪) መልአከ ብርሃናት ቴዎድሮስ መስፍን

፲፫) ሊቀ ብርሃናት ኤልያስ አድማሴ

፲፬) መ/ር ፍሬሕይወት አረጌ

ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተወልዶ ክርስትና የተነሣው ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ነው። ጎንደር አራቱ አፍላጋት ከሚባሉት አንደኛው ዐቢየ እግዚእ የብሉያት ትርጓሜ ጉባኤ ቤት ነው። ሲመደቡም ዐቢየ እግዚእ የብሉያት፣ ግምጃ ቤት የሐዲሳት፣ ሠለስቱ ምእት የመነኮሳት፣ መንበረ መንግሥት የሊቃውንት ነበሩ። አሁን ግን ዐቢየ እግዚእ ሐዲሳትም ይሰጣል። ግምጃ ቤት ሊቃውንትም ይሰጣል። መንበረ መንግሥት ብሉያትና ሐዲሳትም ይሰጣል። መጀመሪያዋ የብሉይ ኪዳን ጉባኤ ቤት ደብረ ሲና ናት። ተማሪው ሙሴ መምህሩ እግዚአብሔር ነው። መምህር ወልደ አብ ከ፬ቱ ጉባኤያት መምህር ከአቃቤ ሰዓት ከብቱ ተማሩ። የዐቢየ እግዚእ ጉባኤ ቤት በ1773 ዓ. ም ተመሠረተ። እርሳቸው መምህር ወልደ አብ ወልደ ሚካኤል ዘግምጃ ቤትን አስተማሩ። ብዙ ሊቃውንትን ያፈራ እና እያፈራ ያለ ጉባኤ ቤት ነው። አምላክ ጉባኤ እግዚአብሔር ጉባኤ ቤቶችን ይጠብቅልን።

እንኳን አደረሳችሁ

፳፭ አማኑኤል (ጌና)

፳፱ በዓለ እግዚአብሔር (ልደት)

ሁለቱ የተለያዩ አይደሉም። ሁለቱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት መታሰቢያዎች ናቸው። ጌና በንዑሳን የጌታ በዓላት ሲከበር፣ ልደት ደግሞ በዐበይት በዓላት ይከበራል። ሁለቱም ግን የጌታ ልደት መታሰቢያዎች ናቸው። ጌታችን የተወለደ ታኅሣሥ ፳፱ ነው። በተአምር ማርያም በ፳፭ም የተወለደበት ነው። በ፳፱ኝም የተወለደበት ነው የሚለው ሁለት ጊዜ ከድንግል ማርያም ተወልዶ አይደለም። በ፳፭ም፣ በ፳፱ም የጌታ ልደት መታሰቢያ እንደሆነ ለማሳየት ነው እንጂ ጌታ የተወለደ በ፳፱ ነው። በልደቱ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑንና በዚህም ምክንያት አማኑኤል መባሉን እያሰብን ታኅሣሥ ፳፭ትን እናከብራለን። ፳፱ ደግሞ የተወለደበት መሆኑን እያሰብን እናከብረዋለን። ሌላው ነገ ማለትም ታኅሣሥ ፳፭ ገሐድ ነው። የሚጾመው እስከ ሥርቀተ ወርኅ። እስከ ምሽቱ ፩ ሰዓት ነው።

ኃጢአት መዳቢዎች

የገና ጨዋታ ኃጢአት ነ፣ ኪስ ጨዋታ ኃጢአት ነው፣ የፈረስ ጉግስ መጫወት ኃጢአት ነው፣ Facebook መጠቀም ኃጢአት ነው፣ የገና ዛፍ ኃጢአት ነው ወዘተ የምትሉ ጥቃቅን ሰዎች ግን ስብከት አልቆባችሁ ከሆነ ብትማሩ አይሻልም ወይ? ያልተጻፈ ኃጢአት መዳቢ ማን ነው ያደረጋችሁ? የኃጢአት ምደባ ኮሚቴ አቋቁማችሁ እንዴ? ነገረ ክርስቶስ፣ ነገረ ማርያም፣ ነገረ ቅዱሳን፣ ነገረ ሥላሴ፣ ነገረ ቤተክርስቲያን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መች ተነግሮ ያልቃል። በእርግጥ ካልተማሩት ያንሳል። ሳይማሩ የማስተማር ትልቁ ችግር ይሄ ነው። ቃለ እግዚአብሔሩ ሲያልቅበት ተረት የሚጨምር ውርጋጥ አይጠቅምም። ሰው በተጻፈው ሕግ መኖር ሲያቅተው ያልተጻፈ ነገር መጻፍ የለበትም። የገና ጨዋታ ባህላችን ነው። ጥቅም አለው ያጸድቃል አንልም። ነገር ግን ኃጢአት ነውም አንልም። ኪስም እንዲሁ ልክ እንደ ሌሎች የሥራ መስኮች ኃጢአት ነው አንልም። ጽድቅ ነውም አንልም። ኪሥ ተጫዋቾች በደንብ በርትታችሁ ሀገራችሁን ወክላችሁ ሀገራችሁን በሙያችሁ ከፍ ብታደርጓት እንደ ሀገር ጥሩ ነው። እንደ ሃይማኖት ግን ጽድቅም አይደለም። ኃጢአትም አይደለም። ሯጮች ሩጣችሁ ሀገራችሁን ከፍ አድርጓት። ሥራችሁን ኃጢአት ነው የሚሏችሁን ጥቃቅኖች መስማት አያስፈልግም። መሮጥ ጽድቅም ኃጢአትም ሊሆን አይችልም። ማንኛውም ሥራ ቃለ እግዚአብሔርን እስካልተቃወመ ድረስ ኃጢአት ነው አይባልም። ለምሳሌ እርሻ ኃጢአትም አይደለም ጽድቅም አይደለም። ኃጢአት የሚሆንበት ጊዜ ግን አለ። ለምሳሌ በቅዱሳት በዓላት ማረስ ኃጢአት ነው። በዓል ያስሽራል። ጽድቅ የሚሆንበት ጊዜም አለ። ለአቅመ ደካሞች በሬ ጠምደን ብናርስላቸው ጽድቅ ይሆናል። ከዚያ ውጭ ሥራው በራሱ ግን ጽድቅም ኃጢአትም ሊሆን አይችልም። ፌስቡክ አደባባይ ነው። ጥሩ ጽሑፍ ከጻፍክበት መልካም ነገር ነው። ክፉ ነገር ካደረግክበት ደግሞ ክፉ ነው። ፌስቡክ ኃጢአት ነው ማለት ግን ድንቁርና ነው። የፈረስ ጉግስ መጫወት በቅዱሳን ነገሥታትና መኳንንት ታሪክ ውስጥ እናገኘዋለን። ፈረስ ጉግስ በራሱ ኃጢአት አይደለም። ጽድቅም አይደለም።ለክፉ ከተጠቀምነው ግን ይሆናል። ውሃ ዋና፣ ፈረስ

ጉግስ፣ ስፖርት ወዘተ በራሳቸው ኃጢአት ሊሆኑ አይችሉም። ጽድቅም አይደሉም። የገና ዛፍ የእኛ ሀገር ባህል አይደለም። በእኛ ሀገርም አንጠቀመውም። ነገር ግን እኛ ስለማንጠቀመው የእኛ ሀገር ባህል ያልሆነ ሁሉ ኃጢአት ነው አይባልም። ነውር ነው። የራስን ባህል ለማስከበር የሌላውን ማናናቅ አይገባም። ስለዚህ ባልተጻፈ ነገር ኃጢአትም ጽድቅም ያልሆነን ነገር እኛ በጉልበታችን ኃጢአት የምናደርገው ወይም ጽድቅ የምናደርገው መሆን የለበትም። እውቀት ይስፋ፣ ድንቁርና ይጥፋ፣ ሳይማሩ ማስተማር ይቅር። የራስን መሰለኝ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ አስመስሎ ማቅረብ ይቅር።

ኮቲባነት

ኮቲባ የትእማን ገረድ የነበረች ሴት ናት። ድንግል ማርያም ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዛ ወደ ግብፅ ስትሰደድ ውሃ ለመጠጣት ከእነ ትእማን ቤት ጠየቀች። ትእማን ግን ነገረኛ ስለነበረች ድንግል ማርያምን አንቺን የመሰለች መልከኛ ጸባይሽ ክፉ ሆኖ ነው እንጂ ትሰደጂ ነበርን እያለች በነገር መሳንተል ጀመረች። በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ውሃ ካለሽ ልትሰጪን ይገባ ነበር። ከሌለሽ ደግሞ ካለበት ያድርሳችሁ ብለሽ መመረቅ እንጂ ሌላ ክፉ ነገር ለምን ትናገሪያለሽ አላት። ይህን ጊዜ ኮቲባ ገረድ የሆነችላትን ትእማንን ያስደሰትኩ መስሏት ሕጻኑን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ከድንጋይ ላይ ጣለችው። ጌታም ትእማንን ከነ ቤተሰቦቿ ዝንጆሮ አደረጋቸው። ኮቲባነት ሌሎችን ለማስደሰት ሲባል ከእውነት ጋር መጣላት ነው። የኮቲባነት ዋና መርሕ ሌላውን ለማስደሰት የእግዚአብሔርን ቃል መጣል (አለመፈጸም) ነው። እባካችሁ እንደኮቲባ አንሁን። ሰውን ለማስደሰት ብለን የእግዚአብሔርን ቃል አንጣል። መርሓችን እውነት ይሁን። መርሓችን ቃለ እግዚአብሔር ይሁን። በነጻነት ልናስብ በነጻነት ተፈጥረናል። የትእማን ገረድ ሆነን ጌታን እንዳንጥል እንጠንቀቅ። ትእማን ኃላፊ ናትና። ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙም የሚኖረው ጌታ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ ራሳችንን በትእማን ግላዊ አስተሳሰብ ሳይሆን በእግዚአብሔራዊው ቃል እንለካው። ኮቲባነት ይቁም። ኮቲባነት መንጋነት ነው። ኮቲባ ትእማንን ያስደሰትኩ መስሏት ጌታን ጣለችው። ሰውም የሰው መንጋ ሲሆን መንጋ የሆነለትን አካል ያስደሰትኩ እየመሰለው ከፈጣሪው ቃል ሲያፈነግጥ ይውላል። ማንኛውንም ነገር የምንለካበት ፍጹም የሆነ መለኪያ ቃለ እግዚአብሔር ይሁን እንጂ ግለሰቦች አይሁኑ። ኮቲባነት ይቅር። መቼም መች የማይሳሳተውን እግዚአብሔርን እንከተል።

፩=> እገሌ ቃለ እግዚአብሔርን ቢያበላሽም ዝም በለው አትናገርብኝ የእግዚአብሔርን ቃል ያሳወቀኝ እርሱ ነውና።

፪=> ስለ ቅዱሳን እንዳውቅ ያደረገኝ አጥማቂ እገሌ፣ ሰባኪ እገሌ፣ ዲያቆን እገሌ፣ መምህር እገሌ ስለሆነ እርሱ ቢሳሳትም በውስጥ ንገረው እንጂ በአደባባይ ለተሳሳተው ስሕተት በአደባባይ አትመልስለት።

፫=> የእግዚአብሔርን ቃል ያሳወቀኝን አባ እገሌን፣ አጥማቂ እገሌን፣ ባሕታዊ እገሌን፣ መምህር እገሌን ከተናገርክብኝ ከዛሬ ጀምሮ ጠልቼሃለሁ። ወዘተ ወዘተ ወዘተ የምትሉ ሰዎች ግን እውነት ከቅዱሳን ሕይወት የተማራችሁት ይህንን ነውን? እውነት የተማራችሁት ቃለ እግዚአብሔር ይህ ነውን? እኔንስ ጥላኝ ችግር የለውም። አንተ ወደድከኝ አልወደድከኝ ምን

ትሠራለህ?? ግን ፍቅረ ቢጽን (ባልጀራን መውደድን) ከቅዱሳን ሕይወት እንዲህ ነው የተማርከው??? ማንኛውም ሰው የሚለካው እግዚአብሔርን በመውደዱና ባለመውደዱ እንጂ እገሌ የተባለ ግለሰብን ከተናገርከው እጠልሃለሁ unfriend አደርግሃለሁ block አደርግሃለሁ ይባላልን???? ደግሞስ አንተ ከጓደኝነት ብትወጣ እኔ የምጎዳ መሰለህን??? "ይሁዳ ቢወጣ ማትያስ እንደሚተካ አታውቅምን"? የቅዱሳን ሕይወት የሚያስተምረን ጭምትነትን፣ ፍቅርን፣ ትሕትናን፣ ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ መሆንን፣ ትዕግሥትን፣ እውነትን፣ ትክክለኛ ፍርድን ነው። በየትኛውም የቅዱሳን ታሪክ ውስጥ በቅድስና ሕይወታቸው ጊዜ ሰውን ጠልተው አልተሳደቡም። እንዲያውም ቅድስናቸውን ከፍ አድርገው ንጽሐ ልቡና የሚባለው የቅድስና ደረጃ ላይ ደርሰው ሰውን ሁሉ እኩል ሲወዱ ሰምተናል ተምረናል። ለቅዱሳን ጠላታቸው አንድ ነው። ቅዱሳን የሚጠሉት ሰይጣንን እና ኃጢአትን ነው። ከቅዱሳን ሕይወት የተማርነው ይህንን ነው። የተማርሽው የቅዱሳን ሕይወት ለአንድ ግለሰብ ፍቅር ብለሽ ሊቃውንትን መሳደብ ነውን?? ለአንድ ግለሰብ ፍቅር ብለሽ ሌላውን መጥላት ነውን? ደግሞስ ሰውን መውደድ ማለት ሲሳሳት ለስሕተቱ ሽፋን መስጠት ነውን? ደንበኛውና ትክክለኛው ፍቅር ስሕተቱን እያረመ መልካም ሥራውን እያበረታቱ መቀጠል አይደለምን? የቅዱሳን ሕይወት ይህንን ነበር የሚያስተምረን?? ነው ወይስ ከዚህ የሚቃረን የተማርሽው ሌላ የቅዱሳን ሕይወት አለ? ማንኛውንም ሰው በእኩልነት በሰውነቱ መውደድ ይገባል። ክፉ ሥራ ሲሠራ ደግሞ ገልጾ ስሕተቱን መንገር ያስፈልጋል። የአደባባይ ስሕተት በአደባባይ የሚታረምበት ምክንያት አስቀድሞ ብዙ ሰው ስለሰማው በአደባባይ የሰማው በስሕተቱ እንዳይጠፋ መልሶ በአደባባይ ማሳወቅ ስለሚያስፈልግ ነው። ሰውን ለማስደሰት ተብሎ የእግዚአብሔር ቃል ሲሰደብ ዝም ማለት ትልቅ ነውር ነው። ሰው ይጠላኛል ተብሎ የእግዚአብሔርን ቃል ሰዎች ሲያሳስቱ ዝም ማለት የሊቅነት ተግባር አይደለም። ሊቅ እከብር ባይ ልቡናን ካላወለቀ እግዚአብሔራዊ አይባልም። ቅዱስ ጴጥሮስንኳ ኀደግነ ኵሎ ወተሎናከ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ያለው እከብር ባይ እወደድ ባይ ልቡናን ትቶ ለእግዚአብሔር ቃል መኖርን የሚነግረን ቃል ነው። ስለዚህ ከምንም በላይ ከግለሰቦች በላይ የሆነውን ቃለ እግዚአብሔር እናስብ። የሁሉንም አስተያየት በግለሰብ ደጋፊነት መንፈስ ሳይሆን በክርስትና ሕይወት በቅዱሳን ሕይወት ቀስ ብሎ በጭምትነት በትሕትና በፍቅር ማየትን ገንዘብ እናድርግ። ጌታዬ ሆይ እኔ የተማርኩት ምእመናንን ለክርስቶስ መንጋ ለማድረግ ነው እንጂ የራሴ መንጋ (አንጃ) ልፈጥር አይደለም። ሀገር እያጠፋ ያለ መንጋው ነው። እና ጌታዬ ሆይ አደራህን የማስተምራቸው የአንተ መንጋ ይሁኑ እንጂ እኔ ስሳሳት ለእኔ ስሕተት ጥብቅና የሚቆሙ እንዳይሆኑ እለምንሃለሁ። እኔ ሰው ነኝ እሳሳታለሁ። ስለዚህ ማንኛውም ሰው የማትሳሳተውን አንተን እንዲከተል እንጂ እኔን ደካማውን እንዲከተል አልፈልግም። ማናችሁም ሰዎች ለእኔ እንድትከራከሩልኝ አልፈልግም። ሰው እኔን ቢሰድበኝ ቢያንቋሸሸኝ እንኳ ከመለስኩለትም እኔው ልመልስለት እንጂ እናንተ ዝም በሉ። እናንተን አይመለከታችሁም። በእኔ ጉዳይ እናንተ ጥልቅ ካላችሁ ግን መንጋዎቼ ሆናችኋል ማለት ነው። ስለዚህ ንሥሓ ግቡን የማይሳሳተውን ፍጹሙን አምላክ ክርስቶስን ተከተሉት። ሰው አምላኪነት ጥሩ አይደለም።

የመንጋው ስነልቡና

፩) መንጋው የሚከተለው መምህር ሲሳደብ መንጋው "መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ" ብሎ ያወድሰዋል። ለስድቡ ንሥሓ እንዳይገባበት ተግሣጽ ነው ብሎ ይሸውደዋል።

፪) መንጋው የሚከተለው ሰው ሲሳሳትና ሊቃውንቱ ሲያርሙት ደግሞ መንጋው ይመጣና "ከእናንተ ምን እንማር በውስጥ አትመክረውም???" ይሉሃል። እንዴት ነው ነገሩ ውግንናችሁ ለእውነት ከሆነ ይህንንም መምህር ወመገሥጽ በሉት እንጂ።

ሲጀምር ከማንኛውም መምህር መልካም መልካሙን ያዙለት ክፉ ነገሩን ደግሞ ተውት። የማይሳሳተውን እግዚአብሔርን ተከተሉ። መምህራን ደግሞ ማስተካከያ ሲሰጡ ፍቅርን መሠረት አድርገው እንዲታረም ፈልገው እንጂ ከጥላቻ አይደለም። በመምህራን ንግግር መካከል እየገባችሁ ነገር አታክርሩ። የሁሉንም አስተያየት እያያችሁ በኦርቶዶክሳዊው ሚዛን እየለካችሁ ያዙት። ውግንናችሁ ለግለሰቦች ሳይሆን ለእውነት ይሁን። እውነት ትምራን።

አባዬ አባዬ ወዴት ወዴት

ሊቀ ጳጳሳቱ (ፓትርያርኩ) ካልፈቀዱ ማንም ቢሆን ኤጲስ ቆጶስነት እንዳይሾም ፍትሐ ነገሥቱ ይነግረናል። ከተሾመም ሲኖዶስ ያወግዘዋል ተብሎ በግልጽ አማርኛ ተጽፏል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ቁጥር ፶፩ ወለእመ ኀሠሠ አሐዱሂ ኤጲስ ቆጶስና ወሠምሩ ቦቱ ኵሉመ· ሰብአ ሀገሩ። አንዱ ኤጲስ ቆጶስነት ሊሾም ቢሻ ወሠምሩ ቦቱ ኵሉመ· ሰብአ ሀገሩ የሀገሩ ሰዎች ቢፈቅዱለት። ወኢሠምረ ቦቱ ጳጳሰ ብሐሩ ኢይደልዎ ኤጲስ ቆጶስና። የሀገሩ ጳጳስ ቢፈቅድ ነው እንጂ የሀገሩ ጳጳስ ካልፈቀደለት መሾም አይገባውም። ወዘንተ ለእመ ተዐደወ ሲኖዶስ ያወግዞ ይህን አፍርሶ ቢሾም ጉባዔ ይለየዋል። ወእመሰ ኀብሩ በእንቲአሁ ዘይበዝኑ ብዙዎች አንድ ሆነው ሹመቱን ቢፈቅዱለት ግን ወሠምሩ ቦቱ ጳጳስ ወሊቀ ጳጳሳት ይግበሩ በምክሮመ· ለእለ ይበዝኑ። ጳጳሱ ሊቀጳጳሱ ከወደዱ በብዙዎች ፈቃድ ይሾም። ሲሾምም "፪ ወይም ፫ ኤጲስ ቆጶሳት ይሹመት" ተብሎ ቁጥር ፶፪ ተጽፏል። አቡነ ዜና ማርቆስ ይችኛዋን ብቻ ይዘው የላይኛውን ትተው እንደ መ*ና*ፍ*kan ግማሹን ይዘው ግማሹን ትተው ሕገወጥነትዎትን ለመሸፋፈን አይሞክሩ። ፍትሐ ነገሥትም ሌላውም ቅዱሳት መጻሕፍት በምልዐት ይጠቀሳሉ እንጂ አንዱን ትቶ አንዱን አንጠልጥሎ አይጠቀስም። ሊቀ ጳጳሳቱ (ፓትርያርኩ) ካልፈቀዱ ማንም ቢሆን ኤጲስ ቆጶስነት እንዳይሾም ፍትሐ ነገሥቱ ይነግረናል። ከተሾመም ሲኖዶስ ያወግዘዋል ተብሎ በግልጽ አማርኛ ተጽፏል። ጵጵስና ሦስት መዓርጋት አሉበት። የመጀመሪያው ኤጲስ ቆጶስ ነው። አዲስ ተሿሚ ነው። ከዚያ የተወሰኑ ኤጲስ ቆጶሳትን አቅፎ መሪ የሆነው ጳጳስ (መጥሮጳሊስ) ይባላል። ከዚያ የጳጳሳትም የኤጲስ ቆጶሳትም የበላይ ደግሞ "ሊቀ ጳጳሳት (ፓትርያርክ)" ይባላል። ሌላው አቡነ ዜና ማርቆስ ሊያጭበረብሩ የሞከሩት ሥርዐት ስለሚሻሻል ማሻሻል እንችላለን የሚል ምክንያት ጠቅሰው የሰሩትን ሕገ ወጥነት ለማለባበስ ሞክረዋል። እውነት ነው ሥርዐት ከዘመን ዘመን ከቦታ ቦታ ሊለወጥ ይችላል። ለዋጩ ግን ማን ነው? የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፶፩ ቁጥር ፲፱፻፰፲፮ (1816) ወዘሰ ብውሕ ለሊቅ ዘውእቱ ሊቀ ጳጳሳት ከመ ይወስክ ዲቤሁ ወያንትግ እምኔሁ። በተጻፈው ላይ ይጨምር ዘንድ ከተጻፈው ይከፍል ዘንድ ለሊቀ ጳጳሳት የሚገባው ዝኒ

ይህ ነው። ካለ በኋላ ዶግማ እንደማይለወጥ በቁጥር 1817 "በተጻፈው ላይ መጨመር ከተጻፈው መክፈል ግን ለማንም አይገባውም" ተብሎ ተገልጿል። ሊቀ ጳጳሳት ማሻሻል ይችላል የተባለውን ሥርዓት በቁጥር 1818 "ላይ ጉባኤ ያልቆመለት በመጻሕፍት ያልተገለጸ ሥርዐት ከሆነ ነው" ይላል። ይህንን የማድረግ ሥልጣን ያለውም ሊቀ ጳጳሳቱ (ፓትርያርኩ) እንጂ ጳጳስ አይደለም። ፓትርያርክ እንኳ ይህንን ለማድረግ ቅድመ መሥፈርቶች አሉት። እነዚህም ከቁጥር 1821 ጀምሮ ተጠቅሷል። የቅዱሳት መጻህፍትን ትርጓሜ የሚያውቅ ምሁር ይሁን። የቅዱሳን አባቶችን የጉባዔ ውሳኔዎች የሚያውቅ ይሁን። በተጨማሪም ትሩፊ ምግባር የሆነ ደግ ሊሆን ይገባል ይላል። ይህ ሁሉ ሲሆን እንኳ ጳጳሳት ሁሉ ተስማምተውበት እንጂ ብቻውን ፓትርያርክ እንኳ ሥርዐት መለወጥ አይችልም። ፍት. ነገ. ፱፩፣ ፲፱፭፱፭፮ "ይደሉ ከመ ይትጋብኡ በእንቲኣሁ ኤጲስ ቆጶሳት" ስለ ጉዳዩ ኤጲስ ቆጶሳት ይሰብሰቡና ይምከሩበት ተብሏል። ስለዚህ አቡነ ዜናማርቆስ ያነሱት ሐሳብ ፍጹም የተጭበረበረ። ሕገ ወጥነትዎን ለመሸፋፈን ያቀረቡት ነው። ነገር ግን ፍትሐ ነገሥቱ የእርስዎን ሕገ ወጥነት እንደማይፈቅድ ይመልከቱት።

እውነት ትቅደም

በውኑ ኢትዮጵያ በሕገ ወጥነት በራሷ ፈቃድ ጳጳስ ሾማለችን???? በፍጹም አልሾመችም። ሰይጣንን ለምን ካድክ ቢሉት በውሸት ለአዳም አልሰግድም ብየ ነው አለ እንደሚባለው (ገድለ ጊዮርጊስ)። የግሉ ትእቢትና ከንቱ ውዳሴ ከልዕልናው ጥሎት ሳለ መውደቁን በአዳም ለማሳከክ መሮጡ የሰይጣንን ቀላልነት ያሳውቃል። በፍትሐ ነገሥቱ የኢትዮጵያ ሰዎች ከራሳቸው ጳጳስ አይሹሙ የሚል ሥርዋጽ ተቀምጦ ለብዙ ዘመናት ጳጳስ ከግብጽ እየመጣ ኖረናል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፬፣ ቁጥር ፱-፱፩። በዚህም ምክንያት ቋንቋውን የማያውቅ የማያስተምር ሰው እየመጣ ኖሯል። ኢትዮጵያም በሊቃውንቶቿ ትጋት ወንጌልን ለሕዝቡ እያስተማረች ክርስትናን ጠብቃ ቆየች። የጵጵስና ዋና ሥራው ሕዝቡን ማስተማር፣ ከሃድያንን ወደ አሚነ ሥላሴ ማምጣት፣ ሕዝቡን ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ መመለስ፣ ደጋጉን በመልካም ሥራ ማጽናት ነው። በቋንቋ ምክንያት ግን ከግብጽ ተሹሞልን የሚመጣው ጳጳስ ይህንን ሊያደርግልን አልቻለም ነበር። በኋላ ሊቃውንት ተሰብስበው ይህ ለምን ይሆናል ኢትዮጵያ የራሷ ጳጳስ ይኑራት ብለው መከሩ። ነገር ግን ምንም እነርሱ ቢመክሩ የግብጽ ፓትርያርክ ካልፈቀደ ጉዳዩ እንደማይሆን ስላወቁ ሊቃውንት ተመርጠው ለግብጽ ፓትርያርክ አስረዱ። የግብጽ መንበረ ማርቆስም በጉዳዩ ተስማምቶ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስን ሹመልንና ወደ ኢትዮጵያ ላከልን። የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ ናቸው። ስለዚህ ኢትዮጵያ በራሷ እምቢተኝነት ጳጳስ አልሾመችም። ከመንበረ ማርቆስ አስፈቅዳ አደረገችው እንጂ። ክህነት ፲ መዓርግ አላት። እኒህም:-

- ፩) ሊቀ ጳጳሳት (ፓትርያርክ) [ፍት. ነገ. ፬]
- ፪) ጳጳስ (መጥሮጶሊስ)
- ፫) ኤጲስ ቆጶስ [ፍት. ነገ. ፬]

- ፬) ቆሞስ (አብሮጥሮስ) [ፍት. ነገ. ፬፣፳፪-፳፫]
- ፭) ቄስ (ቀስ) [ፍት. ነገ. ፭]
- ፮) ዲያቆን [ፍት. ነገ. ፮]
- ፯) ንፍቀ ዲያቆን [ፍት. ነገ. ፰]
- ፰) አናጉንስጢስ [ፍት. ነገ. ፰]
- ፱) መዘምራን [ፍት. ነገ. ፰]
- ፲) አጻዌ ሥጋት [ፍት. ነገ. ፰]

የእነዚህም የየራሳቸው የሥራ ድርሻ አላቸው። ዐጻዌ ሥጋት ዘበኞች ናቸው። በወንዶች መግቢያ ሆነው ወደ ቤተክርስቲያን የሚገባውን ይቆጣጠራሉ። በስሕተትም በድፍረትም የተወገዙ ሰዎች እንዳይገቡ ይጠብቃል። መዘምራን ዳዊት ደጋሚዎች ናቸው። ይጸልያሉ ይዘምራሉ። አናጉንስጢስ አንባቢዎች ናቸው። ቅዱሳት መጻሕፍትን በቤተክርስቲያን የሚያነብ ነው። ንፍቅ ዲያቆንም ከሦስቱ በመዓርግ ከፍ ያለ ነው። ይሁንና እኒህ ሁሉ በአንብሮተ እድ አይሾሙም። እንዲሁ በኤጲስ ቆጶሱ ቃል ይሾማሉ። ንዋየ ቅድሳትን ልብሰ ተክህኖን መንካት መልበስ አይፈቀድላቸውም። ዲያቆናት በአንብሮተ እድ የሚሾሙ ናቸው። ተንሥኡ ለጸሎት እያሉ ምእመናንን የሚያተጉ ናቸው። ቀሳውስት ማቁረብ ማስተማር ይችላሉ። ቄስንም ዲያቁንንም የሚሾማቸው ኤጲስ ቆጶሱ ነው። ቆሞስ መነኩሴ ሆኖ ከቄስ በመዓርግ ከፍ ያለ የኤጲስ ቆጶሱ አማካሪ ነው። ኤጲስ ቆጶስን በፓትርያርኩ ፈቃድ በሲኖዶስ ፈቃድ ሦስት ወይም ከዚያ በላይ ኤጲስ ቆጶሳት አንብሮተ እድ አድርገው ይሾሙታል። ዘመኑ ከፍቶ ሦስት ኤጲስ ቆጶሳት ካልተገኙ ግን በሁለት ኤጲስ ቆጶሳትም ተፈቅዷል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ጳጳሱና ሊቀ ጳጳሳቱ ፈቅደው እንጂ ሳይፈቅዱ መሆን አይችልም። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፬ ስለ ሊቃነ ጳጳሳት ይናገራል። ፓትርያርክ (ሊቀ ጳጳሳት) ርእሰ ኤጲስ ቆጶሳት ነው። ሊቃነ ጳጳሳትሰ ውእቶሙ ተላውያነ ክርስቶስ። ሊቃነ ጳጳሳትስ እንደምናቸውብብትል ክርስቶስን የመሰሉ የክርስቶስ ተከታዮች ናቸው። የሊቀ ጳጳሳት ሊቅነቱ በምእመናንና በኤጲስ ቆጶሳት ላይ ነው። የኒቅያ ሊቃውንት ሊቃነ ጳጳሳት በዓለም ላይ አራት ብቻ እንዲሆኑ አዝዘዋል። ፍት. ነገ. ፬፣ ቁጥር ፴። አራቱ የተባሉትም መንበረ ማርቆስ (እስክንድርያ)፣ መንበረ ዮሐንስ ቴዎሎስ (ኤፌሶን)፣ መንበረ ጴጥሮስ (ሮምያ)፣ መንበረ ጴጥሮስ ካልእ (አንጾኪያ) ናቸው። በየዘመናቱ የተነሡ አባቶቻችን ደግሞ እንደየዘመኑ ሥርዐትን ማሻሻል ስለሚችሉ አሁን የአኃት አብያተ ክርስቲያናት ሊቃነ ጳጳሳት ፮ ደርሰዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን በሲኖዶስ ፈቃድ እንጂ በጉልበትና በማን አለብኝነት አልሆነም። አንቀጽ ፭ ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ይናገራል። ኤጲስ ቆጶሳትን እንድናከብር እንድንወድ ታዘናል። ፍት ነገ. ፭፣ ፱፴፬ ኤጲስ ቆጶስ ውእቱ አቡክሙ እምታሕተ እግዚአብሔር ዘወለደክሙ ዳግመ እማይ ወእመንፈስቅዱስ። ኤጲስ ቆጶስ ከውሃ ከመንፈስቅዱስ የወለዳችሁ ከእግዚአብሔር በታች ያለ አባታችሁ ነው። ተብሏል። በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር ፱፯፮ ወበእንተ ዝንቱ ይደልወክሙ ከመ ታፍቅርዎ ለኤጲስ ቆጶስ በፍቅረ አብ።

ስለዚህ ኤጲስ ቆጶስን በአባት ፍቅር ልትወዱት ይገባል ተብሏል። በመሆኑም ያልተረጋገጠ ወሬ ይዞ እንኳንስ ጳጳስን ማንኛውንም ሰው ማማት ትልቅ ነውር ነው። ጳጳስን የምንወደው ግን ከእግዚአብሔር በታች ነው። ምን ማለት ነው?የምንወደው የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዐት ጠብቆ ሲገኝ ብቻ ነው። ካልጠበቀ ግን አናከብረውም አንወደውም። ረስጣ ፱፪ "እመቦ ኤጲስ ቆጶስ ዘፈቀደ በሕጸተ አእምሮቱ በቀለ ኢኮነ ውእቱ ኤጲስ ቆጶስ። ዳእሙ ስም ሕስው ሀሎ ላዕሌሁ። አኮ ውእቱ እምነበ እግዚአብሔር ዳእሙ እምነበ ሰብእ" እንዲል በቀለኛ የሆነ ነውር ያለበት ከሆነ ቆብ ብቻ አደረገ እንጂ ኤጲስ ቆጶስ ሊባል አይገባውም አይደለም ተብሏል። የተሾመውም ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከሰው ነው ተብሏል። በቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ጉዳይ ችግር አለ ብሎ ያሰበ ሰውም በሕገ ወጥነት ጳጳስ መሾም ሳይሆን በሲኖዶስ ስብሰባ ጉዳዩን ማቅረብ ነው። ፍት. ነገ. ፭፣ቁጥር ፻፷፭ "ኤጲስ ቆጳሳት ከጳጳሳቸው ወይም ከሊቀ ጳጳሳታቸው በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰብሰቡ። በዘያሰስሉ እከየ ወቀጥዐ። ቂም በቀልን ያርቁ ዘንድ" ተብሎ እንደተጻፈው። በዚህ ጉባኤ አጀንዳ አስይዞ ተነጋግሮ ችግርን መፍታት ነው። ፍት. ነገ. ፭፣፻፫ "ኢይሠየሙ ክልዔቱ ኤጲስ ቆጶሳት ላዕለ አሐቲ ሀገር" ይላል። የሎዶቅያ ሊቃውንትም በ፶፭ኛው አንቀጽ ይህንኑ ብለዋል። ስለዚህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ከተመደቡት ጳጳሳት ውጭ ሌላ በእነ አባ ሳዊሮስ በወሊሶ ያለ ሥርዐት የተሾመ ኤጲስ ቆጶስን ምእመናን ሊቀበሉት አይገባም። እንዲያውም በዚሁ አንቀጽ ይህን ያደረገ ቢኖር ይወገዝ ተብሏል። ስለዚህ ከሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ወጥታችሁ በሕገ ወጥነት የተሾሙትን ግለሰቦች እንዳትቀበሉ። ብትቀበሉ ግን ጠባችሁ ከሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ባለቤት ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን ከወዲሁ እወቁት። ጽጽስና በጉበ፣ በጉልበት፣ በተንኮል ኤጲስ ቆጶስነትን የተቀበለ ይሻር። የሾመው ጳጳስም ይሻር። ተብሎ ፍት.ነገ. ፭፣ ቁጥር ፻፫፲-፻፫፬። ተገልጿል። ቤተ ክርስቲያን ባለቤቷ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ ባለቤት ያላትን ቤተክርስቲያንን ባለቤት እንደሌላት በጉልበት የሚሿሿመባት አይደለችም።

ትርጓሜን በተመለከተ

፩) እንደ ጋ*(ላ) እንደሻንቅላ አንዲቱን ሴት ለብዙ ደፍረዋት ነበርና ዘር አስክሯት ሞተች

፪) እንደ አባ ባይሉ ልጆች ፍናፍንት አለና። እንደ ሽንበራ አፍንጫ መሸኛ ብቻ ትንሽ ነበራቸው እንጂ

፫) ናዝሬት እንደ ጭልጋ የቀጥቃጭ ሀገር ነበረች

፬) ሳኦልን እንደ ወሎ ቃልቻ ዘፈን የሚያስወድድ ጋኔን አደረበት

፭) ተፈሥሒ ወለተ ጽዮን። የጽዮን ልጅ ደስ ይበልሽ። የአማራ ልጅ የጎጃም ልጅ እንዲል

፮) እንደ ሐማሴን ልጅ ጀግና ነውና

፯) የእንጦጦ መምህር ቢናገር በዓመት ያውም ሬት

፰) እንደ ቆብ አስጥል ኃይሌ ዓይነቶች

፱) ነገሩን ሳይሰሙ እንደ ቅማንት አንዱ ሲጮህ ተከታትለው ይጮኻሉና

፲) አይዶለም (የሸዋ አማርኛ)

፲፩) ለውሃ ለውሃ ምን አለኝ ቀሃ

፲፪) እንደ ደንቢያ፣ እንደ በረንታ ለም ሀገር ናትና

ይህንንና ይህን የመሳሰሉትን ቃላት ከአንድምታ ትርጓሜ መጻሕፍት በመምዘዝ አንዱን ያደነቀ፣ አንዱን ያጥላላ ነው፣ ቤተክርስቲያን የብሔር ብሔረሰቦች ጠላት ናት፣ ወዘተ እያሉ የመጻሕፍትን ሐሳብ በተጻፉበት ዓውድ ጠይቆ ከመረዳት ይልቅ ለራሳቸው የዘረኝነት ሐሳብ በማዋል ቤተ ክርስቲያንን ሲከሱ የሚስተዋሉ ብዙ ሰዎች አሉ። አንድን ጽሑፍ የተጻፈበትን ዘመን፣ በተጻፈበት ዘመን የነበረውን ማህበራዊ እሳቤ፣ በዘመኑ የነበረውን የቋንቋ አገባብ ሳይረዱ የቀድሞውን ጽሑፍ በአሁኑ ልተርጉመው ማለት ትልቅ ስሕተት ውስጥ ያስገባል። ለምሳሌ ቋንቋን በተመለከተ አንድ ቃል ላንሣ "እኔ የተከበርኩ ባለጌ ነኝ" የሚልን ጽሑፍ በቀድሞው የቋንቋ አገላለጽ እና በአሁኑ ብናነጻጽረው ትልቅ ልዩነት አለው። በአሁኑ ባለጌ የሚባለው አመንዝራውን ዘማዊውን ክፉውን ሰው ነው። ስለዚህ እኔ የተከበርኩ ዘማዊ ነኝ የሚል ትርጓሜን ያመጣል። በቀድሞው የቋንቋ አገላለጽ ደግሞ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም በመጽሐፈ ግሣቸው እንደገለጹት "ጌ" ሀገር ማለት ነው። ስለዚህ ባለጌ ማለት ባለ ሀገር፣ ሀገር ያለው ማለት ነው። በዚህ እሳቤ እቴጌ ማለት እግዝእተ ሀገር እመቤት ማለት ነው ተብሎ ይተረጎማል። ስለዚህ እኔ የተከበርኩ ባለጌ ነኝ የሚል ጽሑፍ በቀድሞው አረዳድ ብታስበው የተከበርኩ ሀገር ያለኝ ሰው ነኝ የሚል ትርጉም ይኖረዋል። የአንድምታ ትርጓሜ በጎንደር ዘመነ መንግሥት በአፄ ኢያሱ ጊዜ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች የመጡ ሊቃውንት ነው የተዘጋጀው። ስለዚህ የአንድምታ ትርጓሜን ሐሳብ ለመረዳት የተጻፈበትን ዘመን እና በዘመኑ የነበረውን ባህል መረዳት ያስፈልጋል። ለምሳሌ በትርጓሜ መጻሕፍት የተጠቀሱ የሰው ስሞች አሉ። ምሳሌ ቆብ አስጥል ኃይሌ፣ አባ ባይሉ፣ አቶ አደራህን፣ መሻፍቃን የተባለ ሊቅ፣ ወዘተ አሉ። ሁሉም ግን ለጊዜው ለነበረው ሕዝብ በዘመኑ በነበረው ቋንቋ ለመግለጽ የቀረቡ እንጂ ማንንም ለማስጠላት የቀረቡ አልነበሩም። ለምሳሌ እንደ አባ ባይሉ ልጆች ፍናፍንት አለና የሚለው የተጠቀሰው ፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ ላይ ነው። ይህ የተጠቀሰው ስለ ጋብቻ የሚናገረው አንቀጽ ላይ። ፍናፍንት አያግባ ይልና ምክንያቱም ፍናፍንት ማለት የወንድም የሴትም ጾታ ያለው ሰው ነው። ሴት ቢያጋቡት ወንድ አምጡልኝ፣ ወንድ ቢያጋቧት ሴት አምጡልኝ ይላልና። ስለዚህ ፍናፍንት ሊያገባ አይገባውም። ካለ በኋላ አንዳንድ ለምልክት ብቻ በጣም ትንሽ አባለ ዘርእ ያላቸው ሰዎችም አያግቡ ይላል። ይህንን ለማስረዳት ይህ ትርጓሜ በሚሠራበት ዘመን የአባ ባይሉ ልጆ አባለዘርእ እንደ ሽንብራ አፍንጫ ሽንት ለመሽናት ብቻ ያላቸው ስለነበሩ ለዘመኑ ሰው በዘመኑ ቋንቋ ለመግለጽ ተጠቅሞበታል። ከዚሁ ጋር አያይዞ አፈ ማኅፀኗ እጅግ በጣም ጠባብ የሆነች ሴትን ትግሬ ስፍ ይላታል። እንግዲህ ትግራይን እየተሳደበ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በዘመናቸው ትግሬ ስፍ የሚባለው በቅርብ በቅርቡ መስፋት ነው። ስለዚህ በጣም ጠባብ የሆነን (ሰፊ ያልሆነን ስፍ) ለመግለጽ ትግሬ ስፍ ብሎታል። ይህ ትርጓሜ በሚጻፍበት ዘመን ትርጓሜው የተተረጎመላቸው ሰዎች ሁሉ የሚረዱትና በዘመኑ

የነበረ ባህል አለ። ለምሳሌ አንዲትን ሴት ለብዙ መድፈር በዚያ ዘመን "ጋ*ላ፣ ሻንቅላ" ከሚባሉት ወገኖች ታይቷል ተሰምቷል። ይህንን በዘመኑ የነበረው ሕዝብ ያውቃል። ስለዚህ በብሉይ ትርጓሜ አንዲትን ሴት ለብዙ ደፍረዋት ዘር አስክሯት ሞታ ነበር። የእርሷን አጽም ለ፲፪ ቆራርጦ ባሏ ለ፲፪ቱ ነገደ እስራኤል ይኸው በእስራኤል የዳን ልጆች ይህን አደረገብኝ ብሎ አንድ ካህን ለ፲፪ቱ ነገድ አለቆች ልኳል። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ለመግለጥ በዘመኑ ሕዝቡ በሚረዳው በዘመኑ ይደረግ በነበረ ድርጊት የተገለጠ እንጂ ሊቃውንቱ ኦሮሞን እየተሳደቡ አይደለም። ይህ የኦሮሞን ሕዝብ ከመስደብ ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም። ይህንን መነሻ አድርጎ አሁን ላይ ቀኖና ካላፈረስኩ፣ ተበድያለሁ ማለት ትልቅ ስሕተት ነው። ሊቃውንቱ የጽዮን ልጅ ደስ ይበልሽ የሚለውን ሲተረጉሙ ልጅ የአማራ፣ ልጅ የጎጃም እንዲል ይላል። በዚህ ጊዜ ጎጃምን እያደነቃት ስለሆነ። ሊቃውንቱ ዘረኞች ስለሆኑ ጨምረውት አይደለም። በዘመኑ እንዲህ የጎጃም ልጅ፣ የአማራ ልጅ የሚለው በብዙ ሰው ዘንድ የሚታወቅ ስለነበረ ነው። በዘመኑ ለነበረው ሕዝቡ በዘመኑ በነበረው ቋንቋ ለማስረዳት ሊቃውንቱ የተናገሩት ነው። እንደ ጭልጋ የቀጥቃጭ ሀገር ናትና። ይህ በዘመኑ ቋንቋ ቀጥቃጭ ይባሉ የነበሩ እና የተናቁ ሰዎች ይኖሩባት ነበረ ማለት ነው ጭልጋ። የአሁኑን ዘመን አይመለከትም። ስለዚህ በወንጌል ማቴዎስ ሲጽፍ "በውኑ ከናዝሬት ደግ ሰው ይወጣልን?" የሚለውን ለማብራራት ናዝሬት የተናቀች ሀገር ናትና እንዲህ አለ። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ይህንን ሲተረጉሙ ናዝሬትን እንደ ጭልጋ ነበረች ይላል። ይህን በሚተረጉሙበት ዘመን ሕዝቡ ሁሉ ጭልጋን የተናቀች አድርጎ ያስባት ነበር። ሕዝቡ በሚገባው ቃል ሊቃውንቱ ነገሩት። ይህ የተባለው በተተረጎመበት ዘመን የነበረችውን ጭልጋ እንጂ የአሁኗን ጭልጋ አይደለም። የአሁኗ ጭልጋ አሁን ባሉ ሰዎች ነው የምትመዘነው። እንደ ወሎ ቃልቻ የሚለውም በዘመኑ የነበረው አብዛኛው ሕዝብ የሚያውቀውን ጉዳይ እየገለጠ ነው እንጂ ወሎን እየተሳደበ አይደለም። እንደ ሐማሴን ጀግና የሚለውም በዘመኑ ሐማሴን ጀግና የሚወጣበት ቦታ መሆኑን አብዛኛው ሕዝብ ያውቅ ነበር። በዘመኑ ቋንቋ፣ በዘመኑ ባህል ለመግለጥ እንዲህ ብለዋል። የእንጦጦ መምህር ቢናገር በዓመት ያውም ሬት ያለውም ይህ በተነገረበት ዘመን ዝምተኛ የእንጦጦ መምህር ነበር። ከዚያ አንድ ቀን ሊቃውንት ተሰብስበው ሃይማኖቱን እንዲያብራራ ሲጠየቅ የክህደት ቃልን ተናገረ። ከዚያ ሊቃውንቱ የእንጦጦ መምህር ቢናገር በዓመት ያውም ሬት ብለውታል። ይህ ሁሉ በዚያን ዘመን የነበረውን ሁኔታ ይናገራል እንጂ አሁን ያለውን የእንጦጦ መምህር እየተሳደበ አይደለም። በመጻሕፍተ ብሉያት ስመረቅ በጥናታዊ ጽሑፍ መልኩ በተወሰነ ለማቅረብ ሞክሬ ነበር። ምናልባት በቅርብ ሊታተም በሚችል መጽሐፍ እያዘጋጀሁት ነው። በስፋት እያንዳንዱን ጉዳይ ማቅረብ ይቻላል። ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም አሁን ላይ ያለን ሰው በዘረኝነት ለማሳመፅ እና የተበዳይነት ስሜት እንዲሰማው አድርጎ ቤተክርስቲያንን እንዲጠላ እያደረጉ ዘርን እንዲያመልክ እያደረጉ ያሉት በተሳሳተ መልኩ እየተረጎሙት እንጂ እውነታው ሌላ ነው። ቤተክርስቲያን ትምህርቷ አንድ ነው። ትምህርቷ ፍቅር አንድነት ነው። በጅምላ የምትሰድበው ብሔር ጎሳ የለም። በክርስቶስ መሠረትነት የተመሠረተች ስለሆነች እንከን የለባትም። በሰፊው በሌላ ቀን እመጣበታለሁ። በትርጓሜ ጎንደር በሰፊው ተነስታለች። ጎንደር የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ስለነበረች ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች የመጡ ሊቃውንት የተረጎሙት ጎንደር ስለሆነ ነው። ለውሃ ለውሃ ምን አለን ቀሃ ሲል ቀሃ ወንዝ ጎንደር ያለ

ነው። አንገርብ፣ ደብረ ብርሃን ሥላሴ፣ ቁስቋም፣ የልደታ ውሃ ወዘተ እያለ ይጠቅሳል። ለውሃ ለውሃ ምን አለኝ ቀሃ የተጠቀሰው ነቢዩ ኤልሳእ ንእማንን ዮርዳኖስ ተጠመቅና ዳን ይለዋል። ይህን ጊዜ ንእማን ጸልዮ ያድነኛል ብየ እንጂ ለውሃ ለውሃማ የሀገሬ ወንዞች ባብናና ፋርፋ ምን አሉኝ ብሎ ነበር። ይህን ለመግለጽ በዘመኑ በሚታወቀው ምሳሌያዊ አነጋገር ለሕዝቡ ለማስረዳት ለውሃ ለውሃ ምን አለኝ ቀሃ ብሏል። በተረፈ ትርጓሜ በየዘመናቱ ይተረጎማል። አያልቅም። ስለዚህ በእነዚህ ጉዳዮች የሚቀየም ካለ ደግሞ ማውጣት ነው። ምክንያቱም ድሮም ለዘመኑ ሰው ለማስረዳት የቀረቡ እንጂ በመሠረታዊነት የቀረቡ አይደሉም። አንድምታ ይሻሻላል። ይታረማል። የሊቃውንት ጉባኤው ባይተኛብን ኖሮ ሥራው ይህ ነበር። ስለዚህ በዘረኝነት እሳቤ እየተዋጡ የሐዋርያት ቀኖና ተሸሮ በዘር ካልተሾም ማለት ትልቅ ነውር ነው። ቤተክርስቲያን ልዕልት ናት። መሠረቷና አካሏ ልዑል እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ሰፈር ለሰፈር ጎጥ ለጎጥ እየተርመጠመጡ ቀኖና ሽረው ካልተሾምን ማለት እጅግ በጣም ትልቅ ነውር ነው። ከ25ቱ ሕገወጦች በጭራሽ ሊሾም አይችልም። ቀኖና እንደሚከለክል ከዚህ ቀደም ተማምረናል። ያ ብቻ ሳይሆን እነ አባ ሳዊሮስ እንኳ ከተወገዙ በኋላ የክህነት ሥራ ስለሠሩ በምእመንነት ነው መቀጠል የሚችሉት። ያው በድፍረት ካመጣችኋቸው ግን ፈጣሪ ይጠይቃችኋል።

ስማዕትነት

ሞት ሌላ አዲስ ዓለም ነው። ብዙዎቻችን እንገምተዋለን እንጂ አናውቀውም። ለመኖራችን ምክንያት የሆነው እግዚአብሔር ግን በቅዱሳን አድሮ ከሞት በኋላ ሁለት ዓይነት ሕይወቶች እንዳሉ ነግሮናል። አንደኛው ዘለዓለማዊ ደስታና ዕረፍት ያለበት ፍጹም ሰላማዊ ዓለም ነው። ሁለተኛው ደግሞ ዘለዓለማዊ መከራና ስቃይ ያለበት ፍጹም የሰቆቃ ዓለም ነው። አጭር እና ኃላፊ የሆኑት የዚህ ዓለም መከራዎች በጣም የሚያሰቅቁን ሆነው ከተገኙ ዘለዓለማዊው ሰቆቃ ደግሞ በጣም ሊያሳስበን ይገባል። አጭር እና ኃላፊ የሆኑት የዚህ ዓለም ደስታዎች ጥሩ ስሜትን ከሰጡን ዘለዓለማዊው ደስታ ደግሞ ከዚህ እጅግ እጥፍ የሆነ ስለሆነ ልንናፍቀው ይገባል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተናገረው የመንግሥተ ሰማያት ደስታ እና የገሐነመ እሳትን ሰቆቃ ሁልጊዜም በዓይነ ሕሊናችን ልንሥለው ይገባል። ብዙዎች የዚህን ዓለም ኑሮ ወደው ከእግዚአብሔር ሕግ በተቃራኒ እየኖሩ ይገኛሉ። የዚህ ዓለም ኑሮ ሁላችንም እንደምናውቀው ኃላፊ ነው። አንድ ቀን ሁሉንም ነገር ትተን ወደዚያኛው ዓለም በሞት እንሄዳለን። የወዲያኛው ዓለም ሕይወት የሚወሰነው በዚህኛው ዓለም በሠራነው ሥራ መሠረት ነው። ስለዚህ በዋናነት ሊያሳስበን የሚገባው በዚህ ምድር ምን እንሥራ የሚለው ነው። ጠቅልለን ብናስበው ጽድቅን መሥራት ኃጢአትን መተው ብለን ልንናገር እንችላለን። ዝርዝር ጉዳዩን ብንመለከተው ግን ጽድቅም ተሠርቶ ተሠርቶ ተሠርቶ አያልቅም። ኃጢአትም ካልተውት እንሥራህ ቢሉት ተሠርቶ አያልቅም። ኃጢአትን ጠልቶ ጽድቅን ማብዛት የማንኛውም ሰው ዋና ዓላማ ሊሆን ይገባል። በዚህ ምድር ስንኖር መሪያችን የእግዚአብሔር ቃል ሊሆን ይገባል። ልንፈራው የሚገባን እግዚአብሔርን ነው። ሁለት ጉዳዮች ቢያጋጥሙን ለእግዚአብሔር ማድላት ይገባናል። ለምሳሌ የእግዚአብሔር ቃል ሲሻር ዝም ከምትልና ተናግረህ ከምትሞት የሚል ምርጫ ቢመጣ ቃሉን ተናግሮ መሞትን በደስታ መምረጥ ይገባል።

ሰማእትነትን የምንወደው ለዚህ ነው። ብዙውን ሰው ስንመለከት ግን በዚህች ምድር መኖርን ወዶ ክፋትን ሲቃወም ጽድቅን ሲሠራ አይስተዋልም። አንዳንዱ ደግሞ ብልጥ የሆንኩ መስሎት ጽድቅን ይናገራል ክፋትን ግን አይቃወምም። ጽድቅን መናገሩ ያስመሰግነዋል። በዚህ እንዲጸናም ሁላችንም በጸሎት እናግዘው። ክርስትና ግን ጽድቅን ማስተማር ብቻ አይደለም። ክርስትና ክፋትንም መቃወም ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ሰይጣንን እምቢ ማለት ያስፈልጋል። ሰይጣንን እምቢ ማለት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን እሺ ማለትም ይገባል። ሁለቱም በአንድ ላይ ቢሠሩ ትልቅ ዋጋን ያስገኛሉ። ሰው ሰውን ሊፈራው አይገባም። ማንኛውንም ሰው በእውነት መዝኖ መያዝ ይገባል። ከጳጳስ ጋር ከመምህር ጋር ፎቶ መነሳትን ከጽድቅ የሚቆጥር ሰው ጳጳሱ ሲሳሳት አድርባይነቱን በዝምታ ሊያሳልፍ ይችላል። እነ ንስጥሮስ ፓትርያርኮች ነበሩ። እግዚአብሔር ከገለጠው እውነት ባፈነገጡ ጊዜ ግን ተወግዘዋል። ከማንኛውም ፍጡር በላይ መጀመሪያ ሊፈራና ሊከበር የሚገባው እግዚአብሔር ነው። በግልጽ የሐዋርያት ቀኖና የተሻረ፣ የእግዚአብሔር ቃል መሳለቂያ እየሆነ ዝም ማለት ግን ከእግዚአብሔር ይልቅ ጳጳስ ይበልጣል ማለት ስለሆነ ወደ ጣዖት አምልኮ እንዳናመራ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ጳጳስ መታየት ያለበት ከእግዚአብሔር በታች ነው። እግዚአብሔር የሠራውን ሕግና ቀኖና የሚያፈርስ ጳጳስ ካለ ከሹመቱ ይወርዳል። ማንኛውንም ጳጳስ በአባትነት የምናከብረው አባት ተብሎ የተሾመበትን ሥልጣን የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቆ ሲሠራበት ብቻ ነው። ፈሪ ሰው ለምንም አይጠቅምም። ከቻልክ ክፋትን ተቃወም። ካልቻልክ ደግሞ ክፋትን የሚቃወሙትን አትቃወም። ብትቃወምም ግን የአሸቃባጭነትህን እና የአድርባይነትህን ጥግ እንረዳበታለን እንጂ ምንም አታመጣም። ልንፈራው የሚገባን እግዚአብሔርን ነው። ሰውን ልንፈራ አልተማርንም። ሞት፣ ረኃብ፣ መከራ፣ ሰቆቃ ሁሉም ከእግዚአብሔር በታች ናቸው። ስለዚህ ዳኛችን እግዚአብሔር ስለሆነ ፈራሽ፣ በስባሽ፣ ሟች ሰውን መፍራት አይገባም። ሁላችንም ሟች ነን። በዚህች ምድር ለዘለዓለም ነዋሪ አይደለንም። እኛን የሚያሳልፍ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ እውነትን ይዘን ከባለስልጣናት፣ ከአድርባዮች፣ ከሆዳሞች፣ ከሙሰኞች፣ ከክፉዎች የሚደርስብንን ማንኛውም ነገር በደስታ መቀበል ይገባናል።

ቤተ ክርስቲያን

የቤተ ክርስቲያን ባለቤቷ ክርስቶስ ነው። ሌላው ከምእመን እስከ ፓትርያርክ ለመዳን እርሷን የተጠጋ ነው። ለመዳን እሷን ተጠግቶ መሠረታዊ አስተምህሮዋን፣ ዶግማዋን፣ ቀኖናዋን ሲሸር ከታየ ግን ከምእመን እስከ ፓትርያርክ ያለምንም ልዩነት እኩል ይወገዛል። ለቤተ ክርስቲያን ሁላችንም ልጆቿ ነን። ከዶግማ ብረዛ፣ ከቀኖና ፍርሻ ልንጠብቃት ይገባል። የአደባባይ ወንበዴዎች ቆብ ጭነው ሲመጡ ዝም በሉ የሚል አስተምህሮ የለም። ሁላችንም ለቤተ ክርስቲያን እንቁም። ይህን በማድረጋችን ደግሞ ከፈጣሪ ዘንድ ሽልማትን እናገኛለን። የዚህ ዓለም ኑሮ ብዙም አያጓጓን። ምኑምኮ አይመሰጥም። ትላንት አብረውን ይጫወቱ የነበሩ ወንድሞቻችን እህቶቻችን እናቶቻችን አባቶቻችን ሞተዋል። ያው እኛም ቀኑን አናውቀውም እንጂ እንሞታለን። ስለዚህ ሞት የማይቀርልን ከሆነ እውነትን ተናግረን፣ በእውነት ኖረን፣ እግዚአብሔርን ፈርተን እንኑር።

ጉባኤ ቤት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን 10 ዓይነት ጉባኤ ቤቶች አሉ።እነዚህም፦

1ኛ የቁጥር ትምህርት ቤት፦ በዚህ ጉባኤ ቤት ከፊደል ጀምሮ ውዳሴ ማርያም መልክአ ማርያም መልክአ ኢየሱስን እና አንቀጸ ብርሃንን በቃል የሚያጠኑበት ክፍል ነው።የዮሐንስ ወንጌልንና መዝሙረ ዳዊትን እንዲሁም መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞንና መኃልየ ነቢያትን በንባብ የሚማሩበት ጉባኤ ቤት ነው።

2ኛ የዜማ (ድጓ) ጉባኤ ቤት፡- ይኽውም ከውዳሴ ማርያም ጀምሮ ምዕራፉን ጸመ ድጓውን እና ድጓውን በዜማ የሚማሩበት ጉባኤ ነው። የአጫብር ዜማ፣ የቤተልሔም ዜማ፣ የቆማ ዜማ እየተባለ ይከፋፈላል።

3ኛ የዝማሬ መዋስእት ጉባኤ ቤት፡- ይህ ደግሞ ቅዱስ ያሬድ ከደረሳቸው መንፈሳዊ ድርሰቶች ሁለቱ ማለትም ዝማሬ መዋስእት የሚሰጥበት ጉባኤ ቤት ነው።

4ኛ የቅዳሴ ጉባኤ ቤት፡- ይህ ደግሞ የቅዳሴ እና የሰዓታት እንዲሁም ሌሎች የቅዳሴ ጓዝ የሆኑ ትምህርቶች የሚሰጥበት ጉባኤ ቤት ነው። የደብረ ዓባይ ቅዳሴ እና የሰደድኩላ ቅዳሴ ተብሎ ይከፋፈላል።

5ኛ የአቋቋም ጉባኤ ቤት፡- ይህ ደግሞ በክብረ በዓላት ጊዜ እንዲሁም እሑድ እሑድ በሚቆመው መዝሙር የሚባል የማኅሌት ትምህርት ነው። በዚህ ጉባኤ ቤትም ጸናጽል አጣጣልን ጨምሮ ወረቡን ዝክረ ቃሉን መዳልውን ወዘተ የሚማሩበት ጉባኤ ቤት ነው። ይህም የላይ ቤት አቋቋም፣ የታች ቤት አቋቋም፣ የሳንካ አቋቋም፣ የተክሌ አቋቋም፣ የቤተማርያም አቋቋም ተብሎ ይከፋፈላል።

6ኛ የቅኔ ጉባኤ ቤት፡- ግእዝ ቋንቋን ጠንቅቀን የምንማርበት ከዚህም አልፎ ተራቅቀን አምላካችንን በአዲስ ድርሰት የምናመሰግንበት የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ የፍልስፍና ትምህርት ነው። የዋሸራ ቅኔ፣ የጎንጅ ቅኔ፣ እና የዋድላ ቅኔ በመባል ይከፈላል።

7ኛ የመጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ ጉባኤ ቤት፡- ይህ ደግሞ 46ቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የሚተረጎሙበት ጉባኤ ቤት ነው።

8ኛ የመጻሕፍተ ሐዲሳት ጉባኤ ቤት፡- ይህ ደግሞ 35ቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሚተረጎሙበት ጉባኤ ቤት ነው።

9ኛ የመጻሕፍተ ሊቃውንት ጉባኤ ቤት፡- ይህ ደግሞ ሃይማኖተ አበው፣ 14ቱ ቅዳሴያት፣ ድርሳነ ቂርሎስ ተረፈ ቂርሎስ ጳላድዮስ፣ ርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ፍትሐ ነገሥት፣ ተግሣጽ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እና አቡሻህር የሚተረጎሙበት ጉባኤ ቤት ነው።

10ኛ የመጻሕፍተ መነኮሳት ጉባኤ ቤት፡- ይህ ደግሞ ሦስቱ መጻሕፍት ማለትም ፊልክስዩስ፣ አረጋዊ መንፈሳዊ እና ማር ይስሐቅ የሚተረጎሙበት ጉባኤ ቤት ነው። በመጻሕፍት ትርጓሜ

ጉባኤ ቤትም የላይ ቤት ትርጓሜ እና የታች ቤት ትርጓሜ እየተባለ ይከፈላል። እንግዲህ ከላይ ያሉት ጉባኤ ቤቶች በብዛት በትግራይ በወሎ በጎጃም በጎንደር በሸዋ በስፋት ይገኛሉ። አምላከ ጉባኤ እግዚአብሔር ጉባኤ ቤቶቻችንን ይጠብቅልን።

የኩሽ ዘር ነህ ወይስ የሴም ?

ሰው መጣላት ሲፈልግ የውሸት መለያያ ይፈጥራል። የሴምና የካም በማለት ለማለያየት ይሞክራል። ድንቁርና ሰልጥኖብንና ጠበን ነው እንጂኮ ከፍ ብንል የሴምና የካም አባታቸው ኖኅ ነው። የኖኅ ልጆች ነን ብለን ብናስብ የጠራ እውነት ነው። ምክንያቱም አሁን በዓለም ያለ ሰው ሁሉ የኖኅ ልጅ ስለሆነ። የካም ነኝ የሴም ነኝ የሚለው አነጋገር ግን የነሲብ የግምት አነጋገር ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ ስንመለከት የሚከተሉትን ጉዳዮች ያነሣል። "የኩሽ ዘር በእስር ደቡብ ከዚያም ወደ አፍሪካ ተሻግረው ተራብተው በርክተው ከዛሬው ሱዳን ጀምሮ እስከ ኤርትራ ባሕር ያለውን ሀገር ይዘውት ይኖሩ ነበር። በኋላ ዘመን ደግሞ የሴም ዘሮች ነገደ ሳባና ነገደ ዮቅጣን ከደቡብ አረብ የኤርትራን ባሕር እየተሻገሩ ከካም ዘር ጋር ተደባልቀው በመጻተኝነት ቆዩ። ረኀብ በተነሳ ጊዜም አንደኛው ነገድ ተሰዶ ወደ አንደኛው ነገድ ሄዶ ይደባለቃል" [ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ናፓታ መርዋ]። የሆነ ሆኖ ኢትዮጵያ ሴማውያንና ካማውያን ተደባልቀው የሚኖሩባት ሀገር ናት። አረቦች ሐበሻ ይሉናል። ድብልቅ ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው ዘፍ.10፣6 ኖኅ ካምን፣ ካም ኩሽን ይወልዳል። ኩሽ ራጌምን ይወልዳል። ራጌም ሳባን ይወልዳል። ኢትዮጲስ የኩሽ ሁለተኛ ስሙ ነው። በእርሱ ሀገሪቱ ኢትዮጵያ፣ የኩሽ ምድር ተብላለች። ከዚሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል 10፣21 ከሴም ዘር ዮቅጣን ይወለዳል። ዮቅጣን ሳባን ይወልዳል። ከሴምም ከካምም ሳባ ሳባ የሚባሉ እንደነበሩ አስተውል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የካምና የሴም ድብልቅ ነው። "የሴም የልጅ ልጆች የመንን ለቀው ወደ ኢትዮጵያ ተሻግረው ሳባ በትግሬ፣ አባል በአዳል (አፋር?)፣ ኦፌር በውጋዴን (ሶማልያ) ተቀመጡ። የቀድሞው የኢትዮጵያ ግዛት የአሁኑን ሱዳን ያካተተ ነበር። ኑብያ የሚባለው የዛሬው ሱዳን ነው" [ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ናፓታ መርዋ]። "ካም ኩሽን ይወልዳል። ኩሽ ሳባንና አቢስን ይወልዳል። ኢትዮጵያ በአቢስ አቢሲኒያ ተብላለች። ሳባ የትግሬዎች አቢስ የአማሮች ሀገር ነው። በኋላ የአቢስ ክፍል አምሐራ ተብሏል። አምሐራ ማለት ነጻ ሕዝብ ጨዋ የጨዋ ልጅ ማለት ነው" ይላሉ [አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍል፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ]። አማራን፣ አፋርን፣ ሶማልያን፣ ትግራይን የሴም ዘሮች አድርገው ሌላውን የኢትዮጵያ ክፍል ደግሞ የካም ዘር ነው ብለው የሚሉ ጸሐፍያን አሉ። ነገር ግን አሁን ላይ ይህ የካም ይህ የሴም ነው ለማለት የሚያበቃ በቂ ማስረጃ የለም። ምክንያቱም ሁሉም የታሪክ ጸሐፍያን የሴም ዘሮችም ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ጽፈዋል። የካም ዘሮችም ወደኢትዮጵያ እንደመጡ ጽፈዋል። ያ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ ተደበላልቋል። ለምሳሌ በ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በኦሮሞ እንቅስቃሴ (Oromo Movement)፣ በተለያዩ ክፍለ ዘመናት በነበሩ ጦርነቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ ተደበላልቋል። ይህ ምሳሌ ነው እንጂ ብዙ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። አውሮፓውያንም በተለያየ ምክንያት ኢትዮጵያ ገብተው እንደኖሩም ታሪክን እናያለን። ስለዚህ ያፈታውያን ድብልቅም ሊኖሩ ይችላሉ። በአመክንዮ ደረጃ አንድ ሰው የካም ዘር ነኝ ለማለት በእናቱም በአባቱም እስከመጨረሻው እስከ

ካም ቆጥሮ ማቅረብ አለበት። የሴም ዘር ነኝ ለማለትም እንዲሁ። ብዙ ሰው ጠይቄያለሁ ከአሥርኛ ትውልድ በላይ ቅድመ አያቶቹን ስማቸውን ሳይቀር አያውቀውም። ይህ ከሆነ 11ኛው የአያት ትውልድ ከአውሮፓ መጥቶ ኢትዮጵያ ኗሪ ሆኖ ወልዶህስ ቢሆን?! 11ኛው አያት የሴም ይሁን የካም ምን ማስረጃ አለህ!? ከፍ ብለህ 20ኛ 30ኛው አያትህስ ማን እንደነበር ታውቃለህ? ይህ በማይታወቅበት ሁኔታ እኔ የካም ነኝ እኔ የሴም ነኝ ብሎ ብጥብጥ ማንሳት ድንቁርና ነው። አንድ እውነታ ግን አለ። ኢትዮጵያ አሁን ላለነው ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሀገራችን ናት። እንዲህ ከሆነ በአንዲት ሀገራችን በአንድነት በእኩልነት እንዴት መኖር እንዳለብን ብንነጋገር መፍትሔው ቅርብ ይሆናል። ከዚያ ውጭ በ1984 በተፈጠረ የብሔር ማንነት አንዱን ለመጥቀም ሌላውን እየጎዱ መኖር እየቆየ ትልቅ ጉዳትን ያመጣል። እያንዳንዱ ሕዝብ በፍቅር በእኩልነት የሚኖርባት ሀገር ማድረግ ከመሪዎችም ከሕዝቡም ይጠበቃል። ሕዝብን በሕግ ማስከበር ስም ቤቱን እያፈረሱ ሜዳ ላይ የጣሉ መሪዎችን ከመሪነታቸው አንስቶ ሕዝብን በሚያከብሩ መሪዎችን መተካት ያስፈልጋል።

ሌብነት

ሌባን የምናስተናግድበት ባህላችን ቢቀጥል ባይ ነኝ። ባለፈው አንዱ ሌባ የሆነ ነገር ይሰርቅና ሊያመልጥ ሲል እጅ ከፍንጅ ተያዘ። ከዚያ የመጣው ሁሉ ያሻሸው ጀመር። ከዚያ የሆኑ ትልቅ እናት መጡና ተዉ ተዉ ብለው ገላገሉትና ለመሆኑ ምን አጥፍቶ ነው ብለው ጠየቁ። ሰርቆ ነው አሏቸው። እኒያ እናት ይህንን እንደሰሙ እንደገና በሉት አሉና እርሳቸውም ደቋቀሱት። ከዚያ በኋላ ክፍል ሁለት የማሸት መርሐ ግብር ቀጠለ። መቼም እንዲያ ታሽቶ ሁለተኛ ይሰርቅ አይመስለኝም። ስርቆት በሃይማኖትም በባህልም ትልቅ ነውር ነው። ከአስሩ የፈጣሪ ሕግጋት አንዱ አትስረቅ ነው። ሌላው በስንት መከራ ለፍቶ፣ ጥሮ፣ ግሮ ያገኘውን ለትልቅ ዓላማ ያዘጋጀውን ገንዘብ በመስረቅ ከዓላማው መጎተት አይገባም። አንዲት የገጠር እናት ከተማ መጥታ ገንዘቧን ሰርቀውባት ስታለቅስ ስታዩ እንኳ አታሳዝናችሁምን??? የአንዷን እናት ስልኳን ሰርቀውባት ከተማ መጥታ ለልጇ ደውላ ደርሻለሁ እንዳትል ስልኳ የለም። እኛ እንዳንደውልላት የልጇን ስልክ አታውቀውም። ቀጥታ እንዳትሄድ ቤቱን አታውቀውም። ወደ ሀገሯ እንዳትመለስ ብሯንብሰርቋታል። የተከበረችዋን እናት ለልመና ዳረጋት። እና ሌብነት ጥሩ አይደለም። በዚህ ጎዳና ያላችሁ ሰዎችም ንስሓ ገብታችሁ ተመለሱ።

ሃይማኖት ቋንቋ ባህል

ሃይማኖትን በቋንቋችን መማር አለብን። ለሐዋርያት 72 ቋንቋ የተገለጠላቸውም ሰውን በቋንቋው ለማስተማር እንዲያመቻቸው ነው። ስለዚህ ማንኛውም አማኝ በቋንቋው የመማር መንፈሳዊ መብት አለው። ማመን ከመስማት ነውና። መስማት ደግሞ ቋንቋን ከመቻል ነው። ይህንን መሠረት አድርጎ "የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ሽሮ" ጳጳስ ልሹም/ልሾም ማለት ግን ትልቅ ነውር ነው። ቤተ ክርስቲያን የሁሉ ናት። ባለቤቷ ክርስቶስ ነው። ሁሉ ነገሯ መለኪያዋ ቀኖናዋ ዶግማዋ እና አስተምህሮዋ ነው። ይህንን ሽሬ እመጣለሁ ያለ አካል ከክርስቶስ አይደለምና መቀበል አይገባም።

ወንጌል ይስፋፋ

ወንጌል ይስፋፋ ዘንድ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚችሉ ሰዎችን በጀት በጅቶ አስተምሮ ማብቃት ነው። ይህ በጣም ግፋ ቢል የ10 ዓመት ፕሮጀክት ቢሆን ነው። በአስር ዓመት ውስጥ ለምሳሌ ኦሮምኛ ተናጋሪ 50 የአቋቋም መምህራንን፣ 50 የድጓ መምህራንን፣ 50 የትርጓሜ መጻሕፍት መምህራንን፣ 50 የቅኔ መምህራንን፣ 50 የቅዳሴ መምህራንን ማስመረቅ ይቻላል። እነዚህ ቀጥታ ወንበር ተክለው እንዲያስተምሩ ማድረግ። እነርሱ 5 ዓመት ቢያስተምሩ። በጠቅላላው በ15 ዓመት ውስጥ እያንዳንዱን ምእመን በቋንቋው ማስተማር ይቻላል። እንዲህ እያልን በሁሉም ቋንቋዎች ብንሠራ በአጭር ጊዜ አትራፊ እንሆናለን። ቋንቋን መሠረት አድርገው ቀኖና ሽረን እንሾም ያሉትን ግን መቀበል አይገባም። ምክንያቱም አላማቸው ክርስትና ሳይሆን ሌላ ነው። አላማቸው ክርስትና ቢሆን ኖሮማ የክርስትናን ቀኖና አይሽሩም ነበር።

ባህል

ማንኛውም ባህል በቤተክርስቲያን አስተምህሮ መለካት አለበት። የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ የሚቃረን ባህል ካለ በግልጽ መቃወም ይገባል።

ቋንቋ

የሁላችንም ፍላጎት እያንዳንዱ ምእመን በቋንቋው ተምሮ ክርስቶስን እንዲያውቅ ነው። ቋንቋውን የሚችሉ አባቶች ኤጲስ ቆጶስነት እንዲሾሙ የሁላችንም ፍላጎት ነው። የኤጲስ ቆጶስ ዋና ሥራ ማስተማር ስለሆነ። ለማስተማር ደግሞ ቋንቋውን ማወቅ ይገባዋልና።ብቋንቋውን የሚያውቁ ኤጲስ ቆጶሳት ይሾሙ ስንል ግን በሐዋርያት ቀኖና መሠረት ነው እንጂ ቀኖና ተሽሮ ይሾሙ እያልን አይደለም። የሚሾሙበትን ሀገረ ስብከት ቋንቋውን የሚችሉ ቀኖናውን የጠበቁ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ብቁ የሆኑ አባቶች እንዲሾሙ ነው ፍላጎታችን። ይህ ከሆነ ሁላችንም በደስታ እንቀበላለን። እንደ ባለፉት 25ቱ ሕገ ወጥ ተሿሚዎች ቀኖና ተሽሮ ከተሾሙ ግን ለክርስትና ሃይማኖት ትልቅ ጉዳት ነው። እነዚህ ሰዎች መልሰው እንዳይሾሙም የሐዋርያት ቀኖና ያዝዛል። ስለዚህ ከእነዚህ ሰዎች ውጭ የሆነ ቋንቋውን የሚችል የቤተክርስቲያንን አስተምህሮ ጠንቅቆ የተማረ የሐዋርያትን ቀኖና ያልሻረ ሰው እንዲሾም እንፈልጋለን።

ኢየሱስ ክርስቶስ

"ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ በሕፃንነቱ ዮሴፍ በጣም ይወደው ስለነበር እንደ መጠኑ ወንበር ሠርቶ ከፊቱ ያስቀምጠው ነበር። መዓዛውን አሽትተው ደስ እያላቸው የዮሴፍ ልጆች እኔ ልያዝ እኔ ልያዝ ይነጣጠቁት ነበር። ኢየሱስን አይቶ የልቡን ኀዘን ያልዘነጋ የለም። እርሱን ማየት ኀዘንን ያርቃል። እርሱን ማየት ችግርን ያባርራል። ቃሉን መስማት የልብ ኀዘንን ነቅሎ ይጥላል። አንድ ጊዜ ፊቱን አይተው ሁልጊዜ እርሱን ለማየት ያልሳሳ ያልናፈቀ የለም። ሕፃናትም እርሱን አይተው በፍቅሩ ይቃጠሉ ነበር። ጎልማሶች ባዩት ጊዜ ደስታ ያድርባቸው ነበር። እርሱን ማየት ስንቅ ደስታ ይሆናቸው ነበር።

እርሱን አይቶ ቃሉን ሰምቶ የሰለቸ የለም። ዘመድ የሞተባቸው ሰዎች ጌታን ሲያዩ ኀዘናቸው ይጠፋላቸው ነበር። እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ግብፅ ይዛው በተሰደደች ጊዜ የግብፅ ልጆች ንዑ ንርአዮ ለወልደ መንክራት እያሉ እየሄዱ ያዩት ነበር"። ምንጭ:-አረጋዊ መንፈሳዊ ትርጓሜ ድርሳን 24 በተለያየ ኀዘን እና መከራ ያላችሁ የተከበራችሁ ክርስቲያኖች ከኀዘን ከመከራ ትወጡ ዘንድ ኑ ክርስቶስን በዓይነ ኅሊና ተመልከቱ፣ ቃሉን ስሙ። ቂም በቀል የያዛችሁብኝ ሰዎች የእኔን ደካማነት ተረድታችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ። የይቅርታ አባት የኢየሱስ ክርስቶስ ልጆች ናችሁና። ይቅር ተባብለን አንድነታችንን እናጽና። ያለፈውን ጥፋታችንን እግዚአብሔር ይቅር ይበለን። ወደፊትም እንዳናጠፋ ይጠብቀን። ክፋትን ምቀኝነትን ጥላቻን ከልቡናችን እናስወግድናብበምትኩ ፍቅርን፣ አንድነትን፣ ጽድቅን ገንዘብ እናድርግ። ክርስቶስን በዓይነ ሕሊናቸው እያዩ፣ በዕዝነ ኅሊናቸው እየሰሙ ሁልጊዜም ያለኀዘን የሚኖሩ ቅዱሳን ብዙ ናቸው። እኛም እኛን ለማዳን በመስቀል ተሰቅሎ ያዳነንን የፍቅር አባትብየሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ኑ እናመስግነው።

በዓለ ጰራቅሊጦስ

እስመ አሐዱ ውእቱ መንፈስቅዱስ ዘተሰውጠ ላዕለ ሐዋርያት። በመንፈስ ቅዱስ ነበቡ በነገረ ኵሉ በሐውርት። እንኳን ለበዓለ ጰራቅሊጦስ አደረሳችሁ። ፍቅሩን፣ አንድነቱን፣ ሐሴቱን ያድለን። ትሕትናን፣ ትዕግሥትን፣ ራስን መግዛትን፣ የይቅርታ ልብን ያኅናጽፈን።

ዕርገት

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሃይ. አበ 67፣ 13 "ኃይላት አዕረግዎ ለኤልያስ ኀበ ተአዘዙ ወቃለ እግዚአብሔር ዋህድ ለሊሁ ዐርገ በሥልጣኑ እስመ እግዚአ ኃይላት ውእቱ" ይላል። ትርጓሜው ኤልያስን የታዘዙ መላእክት ወደታዘዙበት ቦታ አሳረጉት። አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የመላእክት ጌታ ነውና በሥልጣኑ ዐረገ ይላል። ክርስቶስ ያረገው ዕርገት የባሕርይ ዕርገት ነው። ኤልያስ ያረገው ዕርገት ደግሞ የጸጋ ነው ያውም ደግሞ በሠረገላ ነው። ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የሆነ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው። በክርስቶስ ዘንድ ምንታዌ (ሁለትነት) የለም። ቅዱሳት መጻሕፍትም ጠንቅቀውብወልድ ዋሕድ ይሉታል። ክርስቶስ ዐረገ በአብ ቀኝ ተቀመጠ ሲባል ሥጋ በተዋሕዶ አምላክ መሆኑን ያሳውቀናል። ይህም የሆነው ገና በማኅፀን በጊዜ ተዋሕዶ ነው። በ፵ ቀን ዐረገ በአብ ቀኝ ተቀመጠ ሲል የማዳን ሥራውን ፈጸመ ማለት ነው እንጂ ቀድሞውንም ከጊዜ ተዋሕዶብበኋላ ንቡር ነው። ቅዱስ ቄርሎስ በሃይ. አበ. 124፣34 "እስመ ክርስቶስ ኢተቀብዐ በእንተ መፍቅድ ዘቦቱ አላ ለሊሁ ቀባኢ ውእቱ። እጠቀም ብሎ የከበረ አይደለም። እርሱ ሌላውን ያከብራል እንጂ። ወዐርገ ኀበ ሥልጣነ መለኮቱ እንዘ ሰብእ ውእቱ ሰው ሲሆን በአምላክነቱ ሥልጣን ከበረ። ተብህለ በእንቲኣሁ ከመ ውእቱ ተለዐለ ፈድፋደ በእንተ ትሕትና ወሕፀፅ እንተ ዘትስብእት ወንደ ትሑት ሥጋን ስለተዋሐደ ከበረ ተባለ" ይላል። ክርስቶስ ማለት ቅቡዕ (የተቀባ) ማለት ነው። ይህም ሥለ ሥጋው የተነገረ መሆኑን ይህ ቃል በግልጽ ይነግረናል። በቃልነቱ ከጊዜ ተዋሕዶ በፊትም ክቡር ነውና። ቅድመ ተዋሕዶ አምላክ ያልነበረ ሥጋ በጊዜ ተዋሕዶ አምላክ መሆኑን ይነግረናል። ተቀብዐ ማለት ከበረ አምላክ ሆነ ተብሎ ይተረጎማል።

ሥጋ አምላክ የሆነው ደግሞ ከቃል ጋር ሲዋሐድ ነው። ወልድ ዋሕድ በተዋሕዶ ከበረ የሚባለው ለዚህ ነው። መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ (ክብር) ሆነው የሚል ትምህርት የለም። ይህን የሚሉ ቅብዐቶች ናቸው። ሥላሴ በክብር አንድ ናቸውና። በሥላሴ ዘንድ አብ ቀባዒ፣ ወልድ ተቀባዒ፣ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ የሚባል አካላዊ ግብር የለም። አካላዊ ግብር ወላዲነት፣ አሥራጺነት፣ ተወላዲነት፣ ሠራጺነት ነው። ኩነታትም ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ናቸው። አካላዊ ግብር ሦስቱ አካላት የሚለዩበት ነው። በአካላዊ ግብር ተገናዝቦ የለም። ይህም ማለት በአብ ወላዲነት ብወልድ ይወልዳል አይባልም። በኩነታት ግን ተገናዝቦ አለ። ይህም ለምሳሌ በአብ ልብነት ወልድ ያስባል፣ በወልድ ቃልነት አብ ይናገራል እንላለን። አብ ለባዊ ለርእሱ ሆኖ በእርሱ ወልድ እና መንፈስቅዱስ ለባውያን ሆነው ይኖራሉ። አለባውያን ለፍጡራን ነው። ወልድ ነባቢ ለርእሱ ሆኖ በእርሱ አብና መንፈስቅዱስ ነባብያን ሆነው ይኖራሉ። አንባብያን ለፍጡራን ነው። መንፈስቅዱስ ሕያው ለርእሱ ሆኖ በእርሱ አብና ወልድ ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ። ማኅየውያን ለፍጡራን ነው። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሥልጣናዊ ግብር አንድ ናቸው። በክብር፣ በሥልጣን፣ በመዓርግ አንድ ናቸው። በአንዲ ክብር ሦስቱም አካላት ይጠሩባታል። ይኽውም አብ ክቡር፣ ወልድ ክቡር፣ መንፈስቅዱስ ክቡር ቢል አንድ ክብር ነው። አብ ቀባዒ (አክባሪ)፣ ወልድ ቀባዒ (አክባሪ)፣ መንፈስቅዱስ ቀባዒ (አክባሪ) ቢል ይሆናል። ለዚያ ነው ሃይ. አበ. 124፣34 ወልድን ለሊሁ ቀባዒ ውእቱ ያለው። በሥልጣናዊ ግብር አንዱ አካል የተጠራበት ለሌኛው አካልም መጠሪያ ይሆናል። ወልድን አብ አስነሳው ሲል ብታየው ማስነሣት የአብ ግብር ብቻ አይምሰልህ። በሌላ ቦታ ወልድ ወተንሣእኩ በሥልጣን ባሕቲትየ ሲል ይገኛልና። በሥልጣናዊ ግብር (ባሕርያዊ ግብር) አብ ወልድ መንፈስቅዱስ አንድ ናቸው። ሥላሴ በክብር አንድ ናቸው። ስለሆኑም አንዱ አክባሪ አንዱ ከባሪ አይደሉም። ሠለስቱ አካላት በክብር አንድ የሆኑ አክባርያን (ቀባዕያን) ናቸው እንጂ። ሃይ. አበ 113፣2 ዕሩያነ መዓርግ ወክብር እንዲል። ከበረ ሲል ብታገኘው እንኳ ስለተዋሐደው ሥጋ እየተናገረ መሆኑን ልብ በል። ምክንያቱም ቅዱስ ቄርሎስ በሃይ. አበ 74፣37 እንደገለጸው "ወመጻሕፍትሰ ቦ ዘይቤላ በእንተ መለኮቱ ወቦ ዘይቤላ በእንተ ትስብእቱ እንዘ ውእቱ ከመ አምላክ ወሰብእ ወቦ ዘይቤላ በእንተ መለኮቱ ወትስብእቱ ኅቡረ"። መጻሕፍት ስለአንዱ ክርስቶስ ሲናገሩ አምላክም ሆኖ ሳለ ስለሰውነቱ የሚናገሩበት ጊዜ አለ። በዚህ ጊዜ አምላክነቱን ዘንግተው አይደለም። ራሱ ክርስቶስ ሲያስተምር ብዙ ቦታ ላይ ራሱን የሰው ልጅ እያለ ይናገር ነበር። በዚህ ጊዜ አምላክነቱን ዘንግቶ አይደለም። ሰው ሆኖም ሳለ ስለአምላክነቱ የሚናገሩበት ጊዜ አለ። በዚህ ጊዜ ሰውነቱን ዘንግቶ አይደለም። በአንድ ጊዜ ስለሰውነቱም ስለአምላክነቱም የሚናገሩበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና ሲል ሁለቱን በአንድ ላይ እንደተናገረ ለቡ። ስለዚህ ጌታ ራሱን የሰው ልጅ ባለበት መንገድ ቅቡዕ ተብሏል። የከበረው ሰውነቱ ነውና። በቃልነቱማ ድሮም ክቡር ነው። ወዐርገ ኀበ ሥልጣነ መለኮቱ ሲልም ሰው ሲሆን በአምላክነቱ ሥልጣን ከበረ ማለት ነው። ቅዱስ ባስልዮስም በሃይ. አበ 96፣53 "ወሶበ ተንሥአ ዐርገ ውስተ ሰማያት ወዘኒ ወረደ ዘእንበለ ሥጋ ውእቱ ዘዐርገ ሥግው ወአሐዱ ውእቱ ዘእምቅድስት ሥላሴ ወኢወሰከ ኍልቆ ራብዐየ ወኢካልዐ ገጸ ወነበረ በየማነ አብ" ይላል። ትርጉሙ ከተነሣም በኋላ ወደሰማይ ዐረገ። ሥጋ ሳይይዝ የመጣ እርሱ ሰው ሆኖ ዐረገ። ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እርሱ ነው። ለሥላሴ አራተኛ ለቃል ሁለተኛ አልሆነም። በአብ ዕሪና ኖረ ይላል። ከተዋሕዶ በኋላ ይህ የሥጋ ይህ

የቃል አንልም። አንድ ክርስቶስ እንላለን እንጂ። የተራበውም፣ የተራቡትን ያጠገበውም ያው አንዱ ክርስቶስ ነው። ሰው የተባለውም፣ አምላክ የተባለውም ያው አንዱ ክርስቶስ ነው።

የሥጋ ዕርገት በማኅፀን

የቃል ዕርገት በ፴ ቀን

በሁሉ ቦታ የሚኖርና ያለ እግዚአብሔር ወረደ፣ ዐረገ፣ መጣ፣ ሄደ ወዘተ የሚል ቃል ሲነገርለት እንደጊዜ ግብሩ ይተረጎማል። በብሉይ ኪዳን ለምሳሌ መዝ. ፺፱ እግዚአብሔርሰ ገሐደ ይመጽእ ሲል ይመጣል የሚለው መጀመሪያም አልኖር ብሎ አይደለም። በብሉይ ሲተረጎም ረድኤት ይሰጣል ተብሎ ይተረጎማል። ረድኤት መስጠትን ከመምጣት ቆጥሮት ነው። እግዚአብሔርሰ ገሐደ ይመጽእ ለሐዲስ ኪዳን ትንቢት ለክርስቶስ ሲነገር "ይመጽእ" ይትወሐድ ወይም ይከውን ሰብአ (ሰው ይሆናል) የሚል ትርጉም ይኖረዋል። እግዚአብሔርሰ ገሐደ ይመጽእ ለዳግም ምጽአት ሲነገር ይመጽእ "ይፈትሕ" (ይፈርዳል) የሚል ትርጉም ይኖረዋል። እግዚአብሔርን ወረደ ስንል በሐዲስ ኪዳን ሰው ሆነ ተብሎ ይተረጎማል። ከሰማየ ሰማያት ወረደ ስንል መጀመሪያ ከምድር አልኖር ብሎ አይደለም። ሰው ሆነ ተብሎ ይተረጎማል እንጂ። ለቃል ርደትን ስንናገር በአንጻሩ ለሥጋ ዕርገትን እንናገራለን። ወረደን አምላክ ሰው ሆነ ብለን እንተረጉመዋለን። ዐርገን ደግሞ ሰው አምላክ ሆነ ብለን እንተረጉመዋለን። ይህ የሆነው መጋቢት ፳፱ የጽንሰት ቀን ነው። ይህንን ዕርገት ሊቃውንት የርኅቀት ያይደለ የርቀት ዕርገት ይሉታል። የመራቅ ያይደለ የመርቀቅ ዕርገት ነው። ሥጋ ቃልን የባሕርይ ገንዘቡ ሲያደርግ ግዙፍነቱን ሳይለቅ ረቂቅ ሆነ። ይህንን የርቀት ዕርገት ብሎታል። ቃል ደግሞ ሥጋን የባሕርይ ገንዘቡ ሲያደርግ ምልዐቱን ሳይለቅ ተወሰነ፣ ርቀቱን ሳይለቅ ገዘፈ ይህንን ርደት ብለውታል። ሊቃውንት ድንግል ማርያምን የቃል ርደት የሥጋ ዕርገት ምክንያት የሆነችን እያሉ ሲናገሩ ይህንን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተው ነው። ቅዱስ ቄርሎስ እንቲኣሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲኣሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል እንዲል። የሥጋ ዕርገት በማኅፀን ያለው ይህንን ነው። ከትንሣኤ በኋላ በአርባኛው ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ የርቀት ያይደለ የርኅቀት ዕርገት ዐረገ። ርኅቀት ማለት መራቅ ማለት ነው። ወእንዘ ይባርኮሙ ተለዓቆሙ ወዐርገ ሰማየ ሉቃ. ፳፬፣፶፩ እንዲል። ሐዋርያት እያዩት ከእነርሱ እየራቀ እየራቀ ሄዶ ከዓይናቸው ተሠውሯቸዋል። የቃል ዕርገት በ፴ ቀን ያለው ይህንን ነው። በቅዳሴያችን በሰማይ የሀሉ ልብክሙ እንላለን። ሰማይ ከሁሉ ከፍ ያለ ነው። የምእመናን ልብ ከፍ ካለ ነገር ላይ እንዲሆን ቤተክርስቲያን ታሳስባለች። እኛ ክርስቲያኖች በምድር ያለን የሰማይ ዜጎች ነን። ልባችን በሰማይ ነው። እንደ ንስር ከፍ ብለን እንበራለን እንጂ እንደትል መሬት ለመሬት አንርመሰመስም። ሰማያዊውን ሕይወት ተስፋ አድርገን በምድርም የተረጋጋ ሕይወትን እንኖራለን። ሞት ሁላችንንም ያገኘናል። ነገር ግን ሞተን አንቀርም እንነሳለን። በእግዚአብሔር ቸርነት በቀኙ ከሚቆሙት ከሆንንም ለዘለዓለም ደስታ ወደመንግሥተ ሰማያት እናርጋለን። ዐርገ ከመ ያለቡ ዕርገተ ጻድቃን ንጹሓን እንዲል።

ቤተ ክርስቲያን

በቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ታላቅ ደስታ ነው የሚሰማኝ፣ በእርሷ መቼም ተስፋ አልቆርጥም። ምክንያቱም መሠረቷ ክርስቶስ ነው። በውስጧ በሕይወተ ሥጋ ባሉ አገልጋዮች ግን ተስፋ

ማድረግን አቁሜያለሁ። ምክንያቱም ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካሉ እንደመሆኗ ክርስቶስን የተከሉት ዓይነት ሰዎች ናቸው የሚከተሏት። ክርስቶስ የተራበ ያጠግባል ሲባል ሰምተው ለሆዳቸው ሲሉ የተከተሉት ነበሩ። ቤተክርስቲያንንም ለምድራዊ ሕይወታቸው፣ ለደሞዝ፣ የሚፈልጓት አሉ። ከምእመን እስከ ጳጳስ ሰው ሲክድ ሲዋሽ ሲያጭበረብር አይቻለሁ። ይህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ የነበረና እስከ ዕለተ ምጽአት ሊቀጥል የሚችል ነው። ክርስቶስ ለዘለዓለም ሕይወት የተከተሉት ነበሩ። የክርስቶስ አካሉ ቤተክርስቲያንንም ለሕይወት የሚፈልጓት አሉ። መከራ ቢመጣ እንደ ሐዋርያት እስከሞት የሚታመኑላት፣ እንደቅዱስ ጳውሎስ ሁልጊዜ የሚያስቡላት አሉ። ሐዋርያው ዕለት ዕለት የሚያሳስበኝ የአብያተ ክርስቲያናት ጉዳይ ነው እንዳለ። በምድር ያለችዋ ቤተክርስቲያን ተጋድሎዋን አልጨረሰችም። ሁልጊዜም ፈተና አይለያትም። ፈተናው ደግሞ በታሪክም እንደ ምናስተውለው ከውስጥም ከውጭም ከጳጳስም ከንጉሥም ሊመነጭ ይችላል። ሁሉንም ፈተና በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ተቋቁሞ ለድል መብቃት ግን ከእያንዳንዱ አማኝ ይጠበቅበታል። ኑሉ ጻድቅ በጊዜ ርቱዕ እንዲል መከራ በሌለበት ወቅት ሁሉም ጻድቅ ይመስላል። መከራ ግን አጭበርባሪውን ከእውነተኛው ይለያል። በምጽአት ጊዜ የሰው ልጅ ሁሉ ትክክለኛ ማንነት በሰው ሁሉ እና በመላእክት ፊት ይገለጣል። ለቤተክርስቲያን ክብር እና አስተምህሮ መቆም ክብሩ ለራስ ነው። ከተወለድንበት ጀምሮ እስከምንሞት ድረስ ከቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ጋር የማያቋርጥ ጦርነት አለን። ስለዚህ መንፈሳዊ ተጋድሏችንም የማያቋርጥ መሆን አለበት። እግዚአብሔር በቸርነቱ ይቅር ይበለን። ክፉ ሥራችንን እየተውን መልካም ሥራን እናበዛ ዘንድ ይርዳን። በመጨረሻው የፍርድ ሰዓትም በምሕረቱ በቀኙ ከሚቆሙት ያድርገን። ብንኖርም ለእግዚአብሔር እንኖራለን ብንሞትም ለእግዚአብሔር እንሞታለን እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ በሕይወታችንም (በኑሯችንም) እግዚአብሔርን እንስበክ። በሞታችንም እግዚአብሔርን እንስበክ። የቤተ ክርስቲያን ኃላፊ መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ ኤጲስ ቆጶሳት መንፈስ ቅዱስ ባዘዘው የቀኖና መሥፈርት ይመረጣሉ እንጂ በብልጽግና መሥፈርት አይመረጡም። በዚህ ሂደት ደግሞ 25ቱ ሕገወጦች እንኳን ለጵጵስና ለምንኩስና ብቁ አይደሉም። ቁምስናቸውንና ቅስናቸውን በቀኖናው መሠረት ሲኖዶስ ሊሽረው ይገባል። እየተንገዳገደ ያለውን የብልጽግና መንግሥት ሳይሆን ፈጥሮ የሚያኖረን እግዚአብሔርን ፍሩ። እግዚአብሔር በሠራልን ዶግማና ቀኖና ተመሩ። እንደባለፈው የሲኖዶስ ስብሰባ ቀኖና ሽራችሁ እንዳትወጡ እግዚአብሔር ይርዳችሁ። የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ ብዑዓን አባቶች የቤተክርስቲያንን ዶግማና ቀኖና አፍርሰው ጳጳስ እንዳይሾሙ ስንናገር "ድሮም አለቃ አያሌው ሲኖዶስን አውግዘውታል" ብለው የሚመልሱ ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን የሚባሉ አጭበርባሪዎች አሉ። ምእመናን ከዚህ ቀደም በ፲፱ ክፍል ስለኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን አጭበርባሪነት እንደተማማርነው ከዚህ አጭበርባሪ ራሳችሁን እንድታድኑ ደግሜ እናገራለሁ። አለቃ አያሌው አቡነ ጳውሎስን ማውገዝ አይችሉም። ምንም እንኳ አቡነ ጳውሎስ አጥፍተው የነበረ ቢሆን እንኳ እርሳቸውን የማውገዝ ስልጣን ያለው ቅዱስ ሲኖዶስ እንጂ ቄስ አይደለም። በፍትሐ ነገሥት እንደተገለጠው ቄስ ጳጳስን ማውገዝ አይችልም። ጳጳስም ሊቀጳጳሳትን ማውገዝ አይችልም። አንድ ሰው በራሱ የምግባር ክፋት ኖሮበት ሰው ሳያውቅበት ቢቀድስ እግዚአብሔር ራሱን ይመራመረዋል። ምእመናን ግን የሰውየውን ክፋት ባለማወቃቸው ጸጋ እግዚአብሔር

አይቀርባቸውም። የቀረ ክህነት የለም። አሁንም ማንኛውም ምእመን ቤተ ክርስቲያን እየሄደ መጠመቅ፣ መቁረብ፣ ንስሓ መግባት፣ ምሥጢራትን መካፈል አለበት። ምእመናንን ከካህናት ለመነጠል ከመንግሥት ቀጥሎ በጣም እየሠራ ያለው ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን የሚባለው አጭበርባሪ ነው። ስለዚህ ምእመናን ከድኅነት ራሳችሁን እንዳታርቁ ከዚህ ማፍያ ድርጅት ራሳችሁን ጠብቁ። ጳጳሳት ተስማምተው ክፋት ቢሠሩ በዋናነት ተጠያቂዎቹ ራሳቸው ናቸው። በእነርሱ በደል ምእመናን አይጠየቁም። ዶግማና ቀኖና እንዳይሻር እንደ ምእመንነታችን ለብፁዓን አባቶቻችን እናሳውቃለን። ቀኖናን ሽረው ውሳኔ ቢያስተላልፉ እንደልጅነታችን እንቃወማለን። (የምንቃወመው ግን ውሳኔያቸውን እንጂ ክህነታቸውን አይደለም)። ከቻልን የአምስቱም አኃት አብያተ ክርስቲያናት የጳጳሳት ጉባኤ አድርገው ጉዳዩን እንዲያዩልን መጠየቅ ነው። ቀኖናን እና ዶግማን ያላፈረሱ አባቶቻችንን መከተል ነው። ስለዚህ በጥቂት ሆዳሞችና፣ መለካውያን ጳጳሳት ምክንያት የተሻረ ክህነት የለም። ክህነት እስከ ዕለተ ምጽአት ይቀጥላል። ስለዚህ ቴዎድሮስ ይነግሣል እያሉ በሕልም ሊያኖሯችሁ የሚፈልጉ እነዚህ ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን ድርጅቶች እንዳያታልሏችሁ ተጠንቀቁ። ቅዱሳት መጻሕፍትን እያጣመሙ እንዳያታልሏችሁ የትርጓሜ መምህራንን ጠይቁ።

ሕገ ወጥ ጳጳሳት

ከ25ቱ የባለፈው ሕገወጥ ኤጲስ ቆጶስ ሆንን ባዮች አንዱስ እንኳ ለእጩነት መቅረብ አይችልም። ይህ ብቻ ሳይሆን በቅስና እና በቁምስና መሳርግ እንኳ መቀጠል አይችሉም። ስለዚህ እነዚህን ሰዎች ቅዱስ ሲኖዶስ ክህነታቸውን አንስቶ በንስሓ በጨዋነት (ጨዋ ሆነው እንዲኖሩ) እንዲኖሩ ቢያደርግ መልካም ነው። ምክንያቱም የቤተክርስቲያን ቀኖና የሚያዝዘው ይህንን ነው። ካልጳጳስኩ አገባለሁ የሚል ካለም ያግባ። ቅዱስ ሲኖዶስ ባለፈው የሠራውን ስሕተት ሁለተኛ መድገም የለበትም። ባለፈው እነ አባ ሳዊሮስን፣ አባ ዜና ማርቆስንና አባ ኤፎስጣቴዎስን የሐዋርያትን ቀኖና ሽሮ ነበር የመለሳቸው (ይህንን በጊዜው የብዙ አጨብጫቢ አድርባዮችን ስድብ ታግሼ ድርሻዬን ለመወጣት ጽፌ ነበር)። ቢቻል ይህንንም እንደገና ዐቢይ እና ሽመልስ ፊት ተስማምተናል በሚል እሳቤ ሳይሆን እግዚአብሔር ምን ይለናል በሚለው ለክታችሁ ወደ ጨዋነታቸው ብትመልሷቸው መልካም ነው። ይኸው አሁን የሲኖዶሱ ፈተና ሆኑ። የእግዚአብሔርን ሕግ ሽራችሁ የምታደርጉት ነገር በሙሉ መጀመሪያ በእናንተው ላይ ነው መከራ የሚያመጣው። በመንፈስ ቅዱስ መመራት ያለበት ቅዱስ ሲኖዶስ በመለካውያን ትእዛዝ እና ዛቻ የሚመራ ከሆነ ግን ምእመናን ለመንፈስቅዱስ አድልተው ይቃወሙታል። ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ሕግ እና ቀኖና ትመራለች እንጂ በእጅ ብልጫ እና በመንግሥት ጫና አትመራም። ለቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አድልቶ እምቢ የሚል መኖር አለበት። የእግዚአብሔርን ቀኖና ከማስፈጸም ይልቅ የመንግሥትን ጉዳይ አስፈጽማለሁ የሚል ጳጳስ ካለ ግን ወደ ሀገረ ስብከቱ እንዳይመጣ፣ በእነርሱ ላይም እንዳይሾም ምእመናን እምቢ ማለት ይችላሉ። ቤተክርስቲያን የሁላችን ናት እንጂ ጳጳሱ እንደፈለገ ያለቀኖና እና ዶግማ የሚያዝዝባት አይደለችም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በቀኖናዋ መሠረት ትመራለች። ቀኖናዋን ሳያውቁ ጳጵሰው መለካዊ ሆነው ካስቸገሩ ደግሞ እነዚህን አውግዞ መለየት ይገባል። ውግዘት የተሠራው ለዚህ ነውና። ለቤተክርስቲያን ዶግማና ቀኖና መከበር እስከመጨረሻው መታመን

ያስፈልጋል። ሥጋዊ መከራን ፈርቶ የቤተክርስቲያን ዶግማና ቀኖና ሲፈርስ ዝም ማለት ትልቅ ነውር ነው። ፈሪና ቦቅቧቃ ጳጳስ መኖር የለበትም። ለእውነት እስከመጨረሻው የሚቆም እንደ አቡነ ጴጥሮስ (በፋሽስት የተገደሉት) ለእግዚአብሔር የታመነ ጳጳስ መሆን ያስፈልጋል። ብፁዓን አባቶቻችን ዶግማውንና ቀኖናውን መሠረት አድርጋችሁ ከወሰናችሁ እስከሞት ድረስ በፍቅር እንታዘዛችኋለን። እንደባለፈው ስብሰባችሁ መለካዊ ውሳኔ ብትወስኑ ግን ተቃውሟችንን እንገፋበታለን። የተወሰነ ቀን ጨኽን ዝም የምንለው ጉዳይ አይደለም። ይህ ሃይማኖት ነው። በሃይማኖት ቀልድ የለም።

ደብረ ሊባኖስ

ሐዲስ ሐዋርያ አቡነ ተክለሃይማኖት የኖሩበት ቡሩክ ቦታ ነው። የደጋጎች ገዳም ነው። ደብረ ሊባኖስ ስትሄድ መንፈስህ ይታደሳል። ሁልጊዜ አዲስ ነው። ብፁዕ አባታችን ተክለሃይማኖት ሆይ ምልጃህ አይለየን።

ዕለተ ዓርብ

ዛሬ ዕለተ ዓርብ ነው። ሁሉም የአይሁድን ግርማ ፈርቶ በሸሸበት ወቅት እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምና ትልቁ ሐዋርያ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ (አቡቀለምሲስ፣ ታያሎጎስ፣ ቴያሎጎስ፣ ታዎሎጎስ፣ ቴዎሎጎስ፣ ቴዎሎጎስ፣ ፍቁረ እግዚእ) ብቻ ከመስቀሉ ሥር ተገኝተዋል። ጌታ በተአምራት ምግብ ሲያበረክት ለመብላት የተሰበሰበው ሰው ብዙ ነበር። የድግሱ ጊዜ ሁሉም በልቷል። የመከራው ጊዜ ግን ከአንተ ጋር እንሞታለን ያሉት ሁሉ አልተገኙም። እንዲያውም አናውቀውም ያሉ ሁሉ አሉ። ትክክለኛ ፍቅር ቆራጥ ጥቡዕ ያደርጋልና ጌታን የሚወዱት ድንግል ማርያምና ቅዱስ ዮሐንስ ግን የአይሁድን ግርማ ሳይፈሩ እስከ መጨረሻው ድረስ ጌታን ተከትለውታል።

አነ ዘክርስቶስ

ቅዱሳንም ሌላው የሚያስመካ እንዳልሆነ አውቀው የሚመኩት በእግዚአብሔር ነበር። አነ ዘክርስቶስ ነበር የሚሉት። ኑ በሉ እኛም በዘረኝነት ታውረን እውነትን እና ፍትሕን ከምንጨቁናት ይልቅ ለእውነት፣ ለፍትሕ፣ ለፍቅር ቆመን እንደ አባቶቻችን አነ ዘክርስቶስ እንበል።

ምስጋና

እግዚአብሔርን ማመስገን ለልብ የንጽሕና ምንጭ ይሆናል። ሕይወት ሁልጊዜም ተወዳጅ የምትሆነው በምስጋና ስንኖር ነው። ቅዱሳን ሰማዕታት ከእሳት ሲጣሉ፣ በሰይፍ ሲቀረደዱ እግዚአብሔርን ማመስገንን ግን ትተው አያውቁም ነበር። በመከራ ውስጥም ሆነው ያመሰግኑታል። በደስታቸው ጊዜም ያመሰግኑታል። በአጸደ ሥጋ እያሉም ያመሰግኑታል። በአጸደ ነፍስም ያመሰግኑታል። ምስጋና የሚገባው ምስጋና የባሕርይው የሆነ እግዚአብሔር ነውና። ስለሁሉ ነገር እግዚአብሔርን ማመስገንን አንዘንጋ። የቅዱሳን መላእክት ምግባቸው፣ ዕረፍታቸው ምስጋና ነው። በሀገራችንም ውስደ ያሬድ ሊቃውንት እግዚአብሔርን ስቡሕ

ውዱስ ቅዱስ እያሉ በፍቅር ያመሰግኑታል። "ጸጋ ነሣእነ ወሕይወተ ረከብነ በኃይለ ጸሎቱ ለያሬድ አቡነ። ኪያከ ነአኵት ነሢአነ ጸጋ ዘእመንፈስ ቅዱስ" የሰው ልጅ የተፈጠረው እግዚአብሔርን እያመሰገነ በክብር ላይ ክብር እየተጨመረው ይኖር ዘንድ ነው። ሰው እግዚአብሔርን በማመስገኑ ራሱ ሰው ይጠቀማል እንጂ ለእግዚአብሔር የሚጨምርለት ነገር የለም። እርሱ በባሕርይው ምስጉን ነውና። ኑ ካለመኖር በቸርነቱ የፈጠረንን እግዚአብሔርን እናመስግነው። ኑ ክረምትና በጋን፣ መዓልትና ሌሊትን እያፈራረቀ ምድር እንድታበቅል እያደረገ የሚመግበንን የሚያኖረንን እግዚአብሔርን እናመስግነው። ኑ ብንበድል መመለሻ ንስሓን የሰጠን፣ ከሕይወት ብንራቆት እንታደስ ዘንድ ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ ብሎ የሰጠንን እግዚአብሔርን እናመስግነው። ኑ ስለእኛ በመስቀል ተሰቅሎ ያዳነንን ኢየሱስ ክርስቶስን እናመስግነው። በእውነት ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል። እንኳን አደረሳችሁ።

ቅዱስ ያሬድ

"ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ። ወበዳግም አርአዮ ለሙሴ ዘከመ ይገብር ግብራ ለደብተራ" ቅዱስ ያሬድ። ቅዱስ ያሬድ እግዚአብሔርን በጥዑም ዜማና በረቀቀ ምሥጢር በማመስገኑ ይታወቃል። ድጓውን ስናነብ የሚነግረን ቅዱስ ያሬድ እግዚአብሔርን የሚወድ፣ ነገረ ሥጋዌንና ነገረ ሥላሴን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ቅዱሳኑን የሚያከብር፣ ሰባኬ ወንጌል፣ ተርጓሚ መሆኑን በሚገባ እንረዳለን። ብሉያቱን እና ሐዲሳቱን እያስማማ በዜማ ቀምሞታል። ያልተተረጎመውን ዘይቤ ዘይቤ እያለ ተርጉሞታል። የሊቁ የቅዱስ ያሬድ በረከት ይደርብን።

ግፍዐ ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተደረገ ግፍ የለም። በደካማው መንግሥት ምክንያት እስከ 4 ሚልዮን የሀገር ውስጥ ተፈናቃይ አለ። በጦርነቱም በሌላም ምክንያት በሚልዮን የሚቆጠሩ ንጹሓን ተገድለዋል። በብልጽግና ዘመን ያልተደረገ ግፍ ምን አለ!? ይህ ሁሉ ሲሆን ሰው መሞትና መፈናቀል የለበትም የሚሉ ፖለቲከኞችን፣ አክቲቪስቶችን፣ የዩንቨርሲቲ ምሁራንን ሁሉ መንግሥት ሰበብ እየፈለገ ያሥራቸዋል። ሐሳብና ትችትን የሚፈራ ደካማ መንግሥት ነው ያለን። በጠራራ ፀሐይ በመንግሥት በተቋቋመ ግብረ ኃይል የብዙዎች ቤት በላያቸው ላይ ፈርሷል። ይህንን ሁሉ ድርጊት ትክክል እንዳልሆነ መምህራን ሁልጊዜም ይናገራሉ። የሚሰማ ግን የለም። መንግሥት የዜጎችን ደኅንነት መጠበቅ አልቻለም። የመንግሥት ኃይሉ ጥፋቱን ይተው ዘንድ የሚናገሩትን ሰዎች በማሰር ነው። በማንኛውም መንግሥት ኅሊና ውስጥ ሊታሰብ የሚገባው የእያንዳንዱ ዜጋ ጥቅም ነበር። አሁን የምናየው መንግሥት ግን አንዱን ለመጥቀም አንዱን መጉዳት ዋና መርሑ ሆኗል። ሁሉንም እኩል ተጠቃሚ ማድረግ እየተቻለ በአንዱ ኀዘን የአንዱን ደስታ ለመገንባት እየሞከረ ነው። በመንግሥት ኅሊና ውስጥ ሁሉም ዜጋ እኩል መታየት ነበረበት። ይህ ሁሉ ግን የለም። ነቢዩ ኤርምያስ ትክክለኛውን የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር እስራኤላውያን ይጠሉት ነበር። እንዲያውም እርሱን እስር ቤት አሳስረው ሐሰተኛ ነቢያትን ይሰሙ ነበር። ነቢያት ደግሞ ንነግርሂ ወኢንዘብጥ እንናገራለን እንጂ አንማታም ይሉ ነበር። ደጉን መምህር ኤርምያስን አስረው ይሳለቁበት ነበር። ነገር ግን በደላቸው በዝቶ በባቢሎን እስከመማረክ አድርሷቸዋል። ሐሰተኛ ነቢያት ሰላም ሳይኖር ሰላም ነው ይሉ ነበር።

ውንብድና በዝቶ ሳለ ዝም ብለው ነበር። በእስራኤላውያን ለመወደድ እውነታውን ከመናገር ይልቅ ሕዝቡ መስማት የሚፈልገውን ይናገሩ ነበር። ነቢዩ ኤርምያስም ነገራቸውን አይቶ "ወይቤሉ ሰላም ሰላም ወአልቦ ሰላም" ሰላም ነው ሰላም ነው ፍቅር ይደረጋል ይላሉ ሰላም ግን የለም ብሏል። እግዚአብሔር ከቀድሞ ጀምሮ ለሕዝቡ ቃሉን ያስተምሩ ዘንድ ነቢያትን ይልክ ነበር። የመጀመሪያው ነቢይ አዳም ነው። ሀብተ ትንቢት ተሰጥቶት ነበርና። እርሱ ከእግዚአብሔር የሰማውን ለልጆቹ ያስተምር ነበር። ከእርሱም በኋላ እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ ለሰው ልጅ መልካሙን መንገድ እያስተማሩ ነበር። የመምህር ዋና ሥራ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ አድሮ የሠራውን ዶግማና ቀኖና ማወቅና ማሳወቅ ነው። ብዙ ሰው ከተሳሳተው ሰው ይልቅ የተሳሳተውን ተሳስተሀል የሚለውን ነው እየጠላ ያለው። ይህ ደግሞ አድርባይነት ነው። ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር በታች ነው መታየት ያለበት። ፍቅረ ቢጽ ከፍቅረ እግዚአብሔር ቀጥሎ ነው። ፍቅረ እግዚአብሔርን የሚያፈርስ ፍቅረ ቢጽ ፍቅር አይደለም። አንድን ቄስ ወይም ጳጳስ እወደዋለሁ ብለህ የእግዚአብሔርን ሕግ ሲሸር ዝም ካልከው ለፍቅረ ቢጽ ብለህ ፍቅረ እግዚአብሔርን ጣልከው ማለት ነው። ሰውን መውደድ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ነው። እግዚአብሔርን እንውደድ። እግዚአብሔርን መውደድ ሕጉን በመጠበቅና በማስጠበቅ ይገለጣል። ሰውን እንውደድ። ሰውን መውደድ በአንተ ሊደረግብህ የማትፈልገውን በሌላውም አለማድረግ ነው። ለአንተ ሊሆንልህ የምትፈልገውን ለሌላው ማድረግ ነው። መንፈሳዊነት እግዚአብሔርን መውደድ ብቻ አይደለም ሰይጣንንም መቃወም ጭምር ነው። እንቢ በልዎ ለጋኔን እንዳለ ሐዋርያ። መንፈሳዊነት ጽድቅን ማስተማር ብቻ አይደለም። ክፋትን ማውገዝም ጭምር ነው። በጥምቀት ጊዜ ተጠማቂውን ፊቱን ወደ ምዕራብ አዛውረን እክህደክ ሰይጣን እንዲል የምናደርገውም ለዚህ ነው።

እውነት

ውሸትን በመደጋገም እውነት ማድረግ አይቻልም። በሕወሀትና በማዕከላዊው መንግሥት መካከል በነበረው ጦርነት ብዙዎች አልቀዋል። ብዙዎችም አካለ ጎደሎ ሆነዋል። ቤት፣ ንብረት ወድሟል። ለዚህ ሁሉ ተጠያቂዎች ደግሞ ብልጽግና እና ሕወሀት ናቸው። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ቤተክርስቲያንን ተጠያቂ ማድረግ ትልቅ ነውር ነው። በጦርነቱ ወቅት መቀሌ የነበሩ ጳጳሳትም፣ አዲስ አበባ የነበሩ ጳጳሳትም ሁለቱም በግል ይናገሯቸው የነበሩት ንግግሮች የቤተ ክርስቲያን ድምፆች አይደሉም። የራሳቸው የግለሰቦች ድምፅ ነበሩ። ከመቀሌ አካባቢ የነበሩ አንዳንድ መነኮሳትኮ ኢትዮጵያን በጣም ሰድበዋታል። ኤልዛቤል ናት እያሉ ኮንነዋታል። ከዚህ አዲስ አበባ ያሉት ደግሞ ሕወሀት እስከመጨረሻው መደምሰስ አለባት እያሉ ተናግረዋል። አንዳንድ ዲያቆናትና አንዳንድ ጳጳሳት ከዚያም ከዚህም ያለውን ሰው ሊያስቀይም የሚችል ንግግር ተናግረዋል። ያ ንግግር ግን የቤተ ክርስቲያን አይደለም። በፖለቲካ ጥላቻ የሰከሩ ዲያቆናት፣ ጳጳሳት እና መነኮሳት ንግግር መሆኑን ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። በዝርክርክ አገልጋዮች ምክንያት ቤተ ክርስቲያንን መውቀስ አይገባም። ራሳቸውን አገልጋዮችን መውቀስ መናገር ይገባል እንጂ። አንዳንዶች ቤተክርስቲያን ጦርነቱን ማውገዝ ነበረባት የሚል ሐሳብ የሚያነሱ አሉ። ነገር ግን ከጦርነት በፊት ነገሮች እንዳይካረሩና በሰላም እንዲፈቱ ቤተክርስቲያን መግለጫ ሰጥታለች። እርሷን እምቢ ብሎ ጦርነት መጀመር ነውር ነበር።

ጦርነት እንዳይኖር ከማሳሰብ በላይ ምን ታድርግ!? በሁለቱም ወገን ሆነው ከሚገጥሙትኮ ብዙዎቹ ልጆቿብነበሩ። ወንድ ለወንድ፣ ብረት ለብረት ጦርነቱ ሲከናወንና የብልጽግና ሠራዊት መቀሌ ሲገባ አውግዙልን ማለትኮ ነውር ነው። ይህኮ ስልታዊ የጦር እርዳታ አድርጉልን እንደማለት ያለ ነው። እንደገና የሕወሀት ሠራዊት (TDF) የብልጽግናን ሠራዊት እስከ ጣርማ በር ሲያሯሩጡት ከዚህኛው ወገን አውግዙልን ማለት አያስኬድም። በጦርነቱ ሁሉም ተጎድቷል። ለዚህ ሁሉ ተጠያቂዎቹ ደግሞ ሕወሀትና ብልጽግና ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ድሮንና ሌላም መሣሪያ ያላት ይመስል የጥፋቱን መንሥኤ መጋፈጥ ሲያቅታችሁ ንጽሕቷን እመቤት ቤተ ክርስቲያንን ተጠያቂ ማድረግ ትልቅ ነውር ነው። የጦርነቱ ቀስቃሾች ተነፋፍቀው ሲተቃቀፉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በፖለቲከኞች ሴራ መጠላላት የለባቸውም። የቤተክርስቲያን አካሏ ክርስቶስ ነው። ሊያለያየን የሚችል የአስተምህሮ ልዩነት ካለ ብቻ ነው። ከዚያ ውጭ ፖለቲካዊ ሐሳብን አንግቦ ሰማያዊት ቤተ ክርስቲያንን በዘር ለመከፋፈል መጣር ከክርስቶስ አይደለም። ይህ የሰይጣን ፈረስ መሆን ነው።

በእንተ መንበረ ጵጵስና

አዲስ መንበር እናቋቁማለን የሚሉ የመቀሌ ጳጳሳት እግዚአብሔርን ቢፈሩ መልካም ነው። በአንድ ሀገር ሁለት መንበር ሁለት ሲኖዶስ የለም። ጦርነቱ ሁላችንንም ነው የጎዳን። ስለዚህ ያለፈውን ጥፋት አርሞ ለወደፊቱ ሰላም በጋራ መሥራት ይገባል እንጂ በኩርፊያ በመለያየት የሚመጣ ለውጥ የለም። ክርስቶስ በሕሊናው የሌለበት ጳጳስ ይውጣ። ክርስቶስን በሕሊናዬ ይዣለሁ የጸጋ ተዋሕዶ ተዋሕጃለሁ የሚል ጳጳስ ካለ ደግሞ ዘረኝነቱን ያውልቅና ስለቤተ ክርስቲያን ያስብ። ምድራዊ መንግሥትነትን የሚሹ ፖለቲከኛ ጳጳሳት ካሉ ይውጡልን። አይበጥብጡን።

ጉባኤ ቤትና መንፈሳዊ ኮሌጆች

አብነት ጉባኤ ቤቶችም፣ መንፈሳዊ ኮሌጆችም የቅድስት ቤተክርስቲያን ናቸው። አንዱ ሌላ አንዱ ሌላ መስሏችሁ አንዱን ስትንቁ አንዱን ስታደንቁ ሳይ ቤተክርስቲያንን እንደማታውቋት ነው እየተረዳሁ ያለሁት። ቤተ ክርስቲያንን እንወቅ። ቤተ ክርስቲያን በሁለቱም የምታስተምረው አንዱን ወንጌል ነው።

ማኅበረ ቅዱሳን

ኖላዊ ትጉህ ዘኢትነውም።

ማኅበረነ ማኅበረነ ዕቀብ በሰላም (፪*)።

በግቢ ጉባኤ የወለደን ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳን ነው። በሚልየኖች የሚቆጠሩ የዩንቨርሲቲ ተማሪዎችን መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ኮርሶችን አስተምሮ ያስመረቀ ድንቅ ማኅበር ነው። ገና ግቢ ጉባኤ ስንገባ ታላላቆቻችን እግራችንን አጥበው በፍቅር ተቀበሉን። ግቢ ጉባኤ ሁሉ ነገር አለ። ሁሉ ነገር ይናፍቃል። እውነተኛ አገልግሎት ከዚያ አለ። ወደ 20 የሚጠጉ ኮርሶችን አስተምሮናል። ከእነዚህ ውስጥ የማስታውሳቸው;-

፩) ትምህርተ ሃይማኖት

፪) አዕማደ ምሥጢር

፫) ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን

፬) ክርስቲያናዊ ስነምግባር ክፍል ፩

፭) ክርስቲያናዊ ስነምግባር ክፍል ፪

፮) የቤተክርስቲያን ታሪክ ክፍል ፩

፯) የቤተክርስቲያን ታሪክ ክፍል ፪

፰) ቤተክርስቲያንህን እወቅ

፱) ነገረ ማርያም

፲) ሥነ ፍጥረት

፲፩) ነገረ ቅዱሳን ክፍል ፩

፲፪) ነገረ ቅዱሳን ክፍል ፪

፲፫) ሐዋርያዊ ተልእኮ

፲፬) የቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር

፲፭) ሥርዓተ ቤተክርስቲያን

፲፮) ኦርቶዶክሳዊ የጾታ ትምህርት (አጾት)

፲፯) የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል ፩

፲፰) የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል ፪

በጣም ሰነፍ ስለነበርኩ አራቱን ረሳኋቸው። (ሁለቱን በአስተያየት መስጫው ስላስታወሱኝ ጨምሬያቸዋለሁ) እስኪ ቀሪ ሁለቱን የሚያስታውስ በአስተያየት መስጫው ይጻፍልኝ። የአጾት ትምህርት ጊዜ ግን የሚቀር ተማሪ አልነበረም። በግቢ ጉባኤ ባሕረ ሐሳብ እና የግእዝ ትምህርትን እንዲሁም የአብነት ትምህርት ተምረንበታል። ከምንም በላይ ጂማ ዩንቨርሲቲ ዋናው ግቢ ጉባኤ ደግሞ ልዩ የሚያደርገው፦

፩) ላይ ቤት (ማሜ ቤት)

፪) ታች ቤት (ጽርሐ ጽዮን)

ናቸው። ከራድዮን እና አቡነ ሐራ አዳራሽም ልዩ መልካም ትዝታን በልብ ውስጥ ያስቀምጣሉ። የአገልግሎት ክፍል ስብሰባዎች፣ መንፈሳዊ የውይይት የአዳር መርሐ ግብሮች፣ መንፈሳዊ ጉዞዎች ሁሉም ልዩ ነበሩ። በሕይወት ዘመኔ ከኖርኩት ዘመን በጣም ወርቃማው ጊዜ በግቢ ጉባኤ ያሳለፍኩት ጊዜ ነው። የነበርኩባቸው የአገልግሎት ክፍሎች አባላት ጉዳይ፣ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ናቸው። ከግቢ ጉባኤ ያገኘኋቸው እህት ወንድሞቼ የልብ ወንድሞች የልብ እህቶች ናቸው። ማኅበረ ቅዱሳን ለቤተክርስቲያን ትልልቅ መንፈሳዊ ፕሮጀክቶችን ሠርቷል። እየሠራም ይገኛል። የአብነት ትምህርት ምንጩ እንዳይደርቅ ታላላቅ የምስክር ጉባኤ ቤቶችን ቤት ሠርቷል፣ ለተወሰኑ ደቀመዛሙርት ሠርክ ጉብኝት ይችላል። ለገዳማት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመሥራት ራሳቸውን እንዲችሉ አድርጓል። ወንጌል ለሁሉ ተደራሽ ይሆን ዘንድ በመጻሕፍት፣ በማኅበራዊ ድረገጽ፣ በቴሌቭዥን፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔት እና በመሳሰሉት ያስተምራል። እንግዲህ ምን እንላለን። ማኅበራችንን ያስፋልን። ክቡራን ወንድሞቼና እህቶቼ በያላችሁበት ሰላም።

ፈሪ ሰው

ፈሪ ሰው ፍርሀቱን ሳያሸንፍ ወደማንኛውም ትግል መግባት የለበትም። ሁልጊዜ የአሸናፊዎች ባሪያ ሆኖ መኖር የለበትም። በንጉሡ ጊዜ የንጉሡ አጨብጫቢ፣ በደርግ የደርግ አጨብጫቢ፣ በኢሕአዴግ የኢሕአዴግ አጨብጫቢ፣ በብልጽግና የብልጽግና አጨብጫቢ የሚሆን ሰው የቆመለት እውነት የሌለው ሰው ነው። ሞትን ፈርቶ ከውሸት ጋር ተስማምቶ ከመኖር ይልቅ ለእውነት መሞት በሰማይም በምድርም የበለጠ መሆኑን አያውቅም። ብዙ ሰዎች ሌሎች ሰማዕት ሆነውላቸው እነርሱ መኖር ነው የሚፈልጉት። ይህ ማፈሪያነት ነው። ሰማዕትነት ራሱ የጥሩ ኑሮ መግቢያ መሆኑን አያውቁትም። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ለእውነት፣ ለትክክለኛ ፍርድ፣ ለፍትሐዊነት፣ ለአንድነት እስከመጨረሻው ይታመን ዘንድ መጀመሪያ ፍርሀቱን ያሸንፈው። መንፈሳውያን ከሰይጣን ጋር ሲጋደሉ ፍርሀትን አሸንፈው ነው። ሰይጣንም የማስፈራራቸው እየመሰለው በክፉ ሰዎች እያደረ ሲያሳስራቸው፣ አካላቸውን ሲያጎድል፣ ሲያስገድላቸው፣ ሲያሳድዳቸው ይኖራል። ቅዱሳኑ ግን ፍርሀትን አሸንፈው ስለሆነ የሚታገሉት እውነትን በመመስከር ለትክክለኛ ፍትሕ እስከመጨረሻው ይታገሉታል። ትግሉም በእነርሱ አሸናፊነት ይጠናቀቃል። ስለዚህ ፈሪ ሰው ወደ ትግል አይግባ። ወደ ትግል መግባትም ከፈለገ መጀመሪያ ፍርሀቱን ያሸንፍ። የሚሞትለት እውነት፣ የሚኖርለት ፍቅር፣ የሚታገልለት ፍትሕ ይኑረው። ፍርሀትን ለማሸነፍ ከፈለግህ እግዚአብሔርን ፍራ። ቅዱሳን ከሁሉ በላይ የሆነ እግዚአብሔርን ብቻ ይፈሩታል። ይህም ፍርሀት የፍቅር ፍርሀት ነው። ክፉ ሥራ ሠርተው አባትነቱን እንዳያጡ ሁል ጊዜ ከክፉ ሥራ ይርቃሉ መልካም ሥራን ደግሞ አብዝተው ይሠራሉ። ሰውን ግን በሠራዊቱ ብዛት፣ በመንጋው ብዛት፣ በሥልጣኑ፣ በሀብቱ ብዛት፣ እና በመሳሰሉት ነገሮች መፍራት አይገባም። ሟች ሰውን መፍራት ነውር ነው። ስለዚህ በመንፈሳዊውም በሥጋዊውም በኩል ያላችሁ ታጋዮች መጀመሪያ ፍርሀትን አሸንፉ። ከዚያ ጠላታችሁን ማሸነፍ ትችላላችሁ።ለሕዝብ ቆሜያለሁ ያለ ሰው እስከ ሞት ድረስ ሕዝቡን በፍቅር ማገልገል አለበት። ሕዝቡ ባይረዳው እንኳ እግዚአብሔር ዋጋውን አያሳጣውም።

ታሪክን መደበቅ

የራስን ስሕተት በቀድሞ ታሪክ መደበቅ ትንሽነት ነው። አምኖን የዳዊት ልጅ ነው። አምኖን እህቱን ሳይቀር የደፈረ ዘማዊ ነው። አምኖን መለካት ያለበት በአምኖንነቱ ነው። አሁን አምኖን "እኔኮ የዳዊት ልጅ ነኝ" እያለ ቢመካ ያምርበታል እንዴ?! ብዙ ትንንሽ ሰዎች ራሳቸው የረባ ሥራ ሠርተው ስለማያውቁ በአያቶቻቸውና በወንድሞቻቸው ሥራ ለመደበቅ ይሞክራሉ። የሕዝቡን ሥራ የግላቸው ያደርጉታል። የግለሰቡን ሥራም የሕዝቡ ያደርጉታል። ግለሰብ በቡድን መደበቅ የለበትም። ቡድንም በግለሰብ መለካት የለበትም። ሁሉም ለየብቻቸው ሊታዩ ይገባል። ማንም ሰው መለካት ያለበት በራሱ ማንነት ነው እንጂ በወንድሞቹ በአባቱ በእህቱ ማንነት አይለካም። እግዚአብሔር እንኳ ፍርድ ሲሰጥ ለየብቻ ነው እንጂ በጅምላ አይፈርድም። ጀግና የትም ሀገር ይወለድ፣ የትም ሀገር ይደግ በጀግንነቱ ሊደነቅ ይገባዋል። ጻድቅ የትም ሀገር ይወለድ፣ የትም ሀገር ይደግ በጽድቁ ሊደነቅ ይገባዋል። ክፉ ሰው የትም ሀገር ይወለድ፣ የትም ሀገር ይደግ በክፋቱ ሊፈረድበት ይገባል። ክፉን በጎጥ፣ በዝምድና መደበቅ ትንሽነት ነው። ጻድቅን በጎጥ፣ በዝምድና መለካት ነውር ነው። አምኖን የዳዊት ልጅ ቢሆንም ክፉ ነበር። ዳዊት ደግሞ ልበ አምላክ ነበረ። ስለዚህ ዘረኛ ሰው ሲገጥማችሁ በራሱ ማንነት ለኩት። በክልሉ የሚመካ ሰው ካገኛችሁ በዞኑ ጠይቁት፣ በዞኑ የሚመካ ሰው ካገኛችሁ በወረዳው ሂዱበት፣ በወረዳው የሚመካ ሰው ካለ በቀበሌው ሂዱበት፣ በቀበሌው የሚመካ ሰው ካለ በጎጡ ሂዱበት፣ በጎጡ የሚመካ ሰው ካለ በቤተሰብ ሂዱበት፣ በቤተሰብ የሚመካ ሰው ካለ በራሱ ማንነት ጠይቁት። ይህን ጊዜ የሚመካበት ነገር ሁሉ ውሸት መሆኑን ይረዳል። ታላቅ ሥራን የሠሩ ሰዎች የእርሱ ምኑም እንዳልሆኑ ይረዳል። የሚመካው በውሸት መሆኑን ይረዳል። ምክንያቱም በዞን የሚመካ ሰው በጅምላ በሁሉም ወረዳ የነበሩ ጀግኖችን በእኔ ዞን የነበሩ ናቸው እያለ ይመካል። በዚህ ሰው በተወለደበት ወረዳ ስትገቡበት ያ በዞን ይመካበት የነበረው ሰው ከእርሱ ወረዳ እንዳልተወለደ ሲያስበው ትምክህቱ የጅምላ ውሸት እንጂ እውነት እንዳልሆነ ይረዳዋል። ማንኛውም ሰው በዘረኝነት ሰክሮ በጅምላ ከሚመካ በጅምላ ከሚሳደብ ራሱን ቢመረምር መልካም ነው። የትም ይወለዱ የመልካም ሰዎችን አርአያነት ምሳሌ ያድርግ። የትም ይወለዱ የክፉ ሰዎችን አርአያ አይከተል። አንድ አካል በሆነ ስያሜ ተፈርጆ በውሸት ጥፋት እየደረሰበት ከሆነ ግን ተደራጅቶ መመከት ይገባዋል። ይህንን ክፉ ሥራም ማንኛውም ጤነኛ ሰው ሊደግፍ ይገባል። ምክንያቱም ክፉ ሥራን ለመቃወም ዘር ጎጥ ዝምድና ሊገድበን አይገባም። ክፉ ሥራን በዘረኝነት ምክንያት ካልተቃወምን ግን ፈጣሪ እንደሚጠይቀን ልብ ማድረግ ይገባል።

ተግሣጽ

ጳጳስ ሲያጠፋ ጳጳስ ያርመው እንጂ አንተ ዝም በል የሚል ትምህርት የለም። መምህር ሲያጠፋ መምህር ያርመው እንጂ ጨዋው ዝም ይበል አይባልም (ይህ የአድርባዮች ጥቅስ ነው)። ማንም ቢሆን እንደ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ከተጓዘ እንወደዋለን። ማንም ቢሆን ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ ካፈነገጠ ይወገዛል። ስሕተቱንም እናሳውቃለን። ቤተክርስቲያን የጳጳሱም፣ የቄሱም፣ የዲያቆኑም፣ የመምህራንም፣ የምእመናንም ናት። ሁሉም ድርሻ አላቸው። ጳጳሱም፣ ቄሱም፣ መምህራንም፣ ምእመናንም የሚዳኙት በቃለ እግዚአብሔር እና በኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ

ነው። ኦርቶዶክሳዊውን ዶግማና ቀኖና ካፈረሰ ጳጳሱም፣ ምእመኑም፣ ቄሱም እኩል ይወገዛል እንጂ አድልዎ የለም። የሁላችንም የበላይ አዛዥ እግዚአብሔር ነው። ብዙ አድርባዮች አውቃለሁ። ጨዋ ሲያጠፋ ሀገር ይያዝልኝ ብለው የሚቀውጡት፣ ጳጳስ ሲያጠፋ ግን አይጥ እንደጎረሰች ድመት ዝም ጭጭ የሚሉ አሉ። ትንሽ ደጋፊ ያላቸውን ሰዎች ሌት ከቀን የሚናገሩ፣ ብዙ መንጋና ደጋፊ ያለውን ሰው ግን ቢያጠፋም ዝም ጭጭ የሚሉ አድርባዮች ብዙ ናቸው። ሺ ዓመት ላንኖር ሰውን መፍራት ትልቅ ነውር ነው። መፍራት ያለብን እግዚአብሔርን ነው። የማንኛውም መምህር መሪው ቃለ እግዚአብሔር ቢሆን መልካም ነው። የሰው ልጅ ሊከተለው የሚገባው የማይሳሳተውን እግዚአብሔርን እና አካሉ የሆነችውን የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ነው። እንጂ የጳጳስ፣ የቄስ፣ የዲያቆን፣ የመምህር ተከታይ መሆን የለበትም። እነዚህ ሁሉ ሰዎች ናቸው። ብዙ ችግር ሊኖርባቸው ይችላል። እነርሱ ሲሳሳቱ እንዳንሳሳት ልንከተላቸው አይገባም። ቤተ ክርስቲያንን ለመበጥበጥ በተለያየ ተልእኮ እስከ ጽጽስና የደረሱ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ታዲያ ጳጳስ ቢያጠፋም ዝም በሉት የሚሉ ሰዎች የእነዚህ ቅጥረኞች ሊሆኑ ይችላሉ። ኖርንም ሞትንም የክርስቶስ ነን። ስለዚህ ዋና መመሪያችን "አነ ዘክርስቶስ" የሚለው ይሁን። ጳጳሳትን፣ ካህናትን፣ መምህራንን ማክበር ያለብን እና እንደ አባት መንከባከብ ያለብን "ከኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ" ካላፈነገጡ ብቻ ነው። ቀኖናዋን ዶግማዋን የሚያፈርሱ ከሆኑ ግን አባቶቻችን አይሆኑም። አባትነታቸው ይፈርሳል።

ኤጲስ ቆጶሳት

፭ኛ ክብራቸው፦ ኤጲስ ቆጶሳት የእግዚአብሔር ደጋግ ሹማምንት ናቸው (ፍት. ነገ. ፭)። (ድስቅ ፱፣፯)። ከእግዚአብሔር በታች አባት ለሆነህ ለኤጲስ ቆጶሱ እጅ ንሣ እንዲል ኤጲስ ቆጶሳት ከእግዚአብሔር በታች የሃይማኖት አባቶቻችን ስለሆኑ ክቡራን ናቸው። ምእመናን አባማዕ ከተባሉ ዘንድ ኤጲስ ቆጶሳት ደግሞ ምእመናንን የሚጠብቁ ጠባቂዎች ናቸው (ድስቅ.፭፣፬)። ቤተ ክርስቲያን በምድርም በሰማይም በሁሉ ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት ናት። ትምህርቷን የሚያስተምሩ፣ ሥርዓቷን የሚፈጽሙ ሹማምንትን ደግሞ እግዚአብሔር ከዐፃዌ ኖኅት እስከ ፓትርያርክ ይሾሞላታል። ኤጲስ ቆጶስ የምእመናን አባት እንደመሆኑ ይራራላቸው። (ድስቅ ፮፣፲፭) ኤጲስ ቆጶስ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ያዝን ዘንድ ይገባል እንዲል። (ድስቅ ፮፡፴፭) ኤጲስ ቆጶሱ ሕዝቡን እንደልጆቹ ሊወዳቸው ይገባል። ዲድስቅልያ ፬፣፳፮ ኤጲቆጶሳት ሆይ ሕዝቦችን አስተምራችሁ ከስሕተት ታድኗቸው ዘንድ ለእናንተ ይገባል።

፮ኛ የሹመት መስፈርታቸው፦ ኤጲስ ቆጶስነትን የሚሾም ሰው ነውር ነቀፋ የሌለበት ይሁን (ፍት. ነገ. ፭)። ሕዝቡ (ምእመናን) እና ጳጳሳቱ ካልፈቀዱለት ማንም ቢሆን ኤጲስ ቆጶስነት አይሾምም። ቤተ ክርስቲያን የምእመናንም የካህናትም የጳጳሳትም ስለሆነች ምእመናንም ካህናትም ያልፈለጉትን እንዳይሾም ማድረግ ይችላሉ። የፈለጉትን እንዲሾምም ማድረግ ይችላሉ። የሚከተሉት የቀኖና መጻሕፍት ምእመናን ያልፈቀዱለት ኤጲስ ቆጶስ መሆን እንደማይችል ይናገራሉ። ሁሉንም አስተውሏቸው። ፍት. ነገ.፭፣፴፮ "ኤጲስ ቆጶስ በሚሾምባቸው ሕዝብ ፈቃድና በሊቀ ጳጳሱ ፈቃድ ይሾም" ስለሚል ሕዝቡ ያልፈቀደለት ሰው ጽጽስና መሾም አይችልም። ስለዚህ በጳጳሳት ሹመት ሕዝቡም ድርሻ ስላለው ድርሻውን ሊወጣ ይገባል። እንዲሁም ሐዋርያት በአብጥሊሳቸው አብጥሊስ ፪፡- ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ሊሾም የቀረበ

ሰው ካለ ይህ በሀገረ ስብከቱ ባሉ ሰዎች ሁሉ ስምምነት ይሁን ብለዋል። በተጨማሪም ቀሌምንጦስ ቀኖና ፪:- ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ እንዲሾም ያመጡት (የመረጡት) ሰው ሹመቱ የሚሰጠው በሀገሩ ሰዎች ስምምነት ይሁን ይላል። ቀኖና ዘኒቅያ ቁጥር ፬:- ኤጲስ ቆጶሳትና ሕዝቡ ሁሉ የወደዱት ኤጲስ ቆጶስ ይሾም። ቀኖና ዘኒቅያ ቁጥር ፮:- ኤጲስ ቆጶስ ያለ ጳጳሱና ያለሕዝቡ ፈቃድ አይሾም። ሲኖዶስ ዘአንጾኪያ ትእዛዝ ፲፱:- ኤጲስ ቆጶስ በሀገሩ ሰዎችና በኤጲስ ቆጶሳት ሥምረት ይሾም። በትእዛዝ ሲኖዶስ ፶፩ እንደተገለጸውም መስማት የተሳነውና ዓይነ ሥውር ኤጲስ ቆጶስነት አይሾምም። ኤጲስ ቆጶስ ሊቃውንትን የሚወድ መሆን እንዳለበትም አብጥሊስ ፴፫:- ኤጲስ ቆጶስ የሊቃውንትን ክብር የሚያውቅ ይሁን ተብሎ ተገልጿል። እድሜን በተመለከተ ደግሞ ዲድስቅልያ ፬፣፭-፬ "ኤጲስ ቆጶስ የሚሾም ሰው 50 ዓመት የሞላው ይሁን። ሀገሪቱ ትንሽ ብትሆን እና 50 ዓመት የሞላው ባይገኝ ሌላውን መሥፈርት ካሟላ ከ50 ዓመት በታችም ይሾም ተብሏል። ኤጲስ ቆጶስነት የሚሾም ሰው ሃይማኖት ከምግባር አስተባብሮ የያዘ መሆን ይገባዋል። ዲድስቅልያ ፬፣፲-፲፭ ኤጲስ ቆጶስ የሚሾም ሰው ቂም ክፋትና ዐመፅ የሌለበት ልበ ንጹሕ ይሁን። የማይቆጣ፣ የማይሰክር፣ የማይበቀል፣ ጸብና ክርክር የሌለው፣ የማይሳደብ ይሁን እንዲል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭ ኤጲስ ቆጶስነት የሚሾመው ድንግልና ከምንኩስና ያለው ነው። ይህ ሥርዓት ከሠለስቱ ምእት ወዲህ የሆነ ነው። ከዚያ በፊት አንድ ያገባ ኤጲስ ቆጶስ ይሆን ነበርና።

፫ኛ የኤጲስ ቆጶሳት አሿሿም:-አንድ ሰው ሕዝቡም ጳጳሳቱም ተስማምተው ኤጲስ ቆጶስነት እንዲመረጥ ከሆነ በኋላ የአሿሿም ሥርዓቱ እንደሚከተለው ነው። ኤጲስ ቆጶስ ሲሾም ቢያንስ ሁለት ወይም ሦስት ኤጲስ ቆጶሳት ሊኖሩ ይገባል። ትእዛዝ ሲኖዶስ ፩:- ሁለት ወይም ሦስት ኤጲስ ቆጶሳት በተገኙበት ይሾም እንዲል። ዲድስቅልያ ፲፮:፶፯። ዝኒ ከማሁ። የሚሾመውም በዕለተ እሑድ ነው። ሥርዓተ ጽዮን ቁጥር ፩:- ኤጲስ ቆጶስ እሑድ ቀን ይሾም እንዲል።

፬ኛ ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ:- ትእዛዝ ሲኖዶስ ፲፩:- የተሾመበትን ሀገረ ስብከት ትቶ ወደሌላ ሊሄድ አይገባውም። ትእዛዝ ፰፩:- ኤጲስ ቆጶስ የሀገረ ስብከቱ ኤጲስ ቆጶስ ካልፈቀደለት በስተቀር የራሱ ባልሆነ ሀገረ ስብከት ክህነት አይሹም። ቀሌምንጦስ ቀኖና ፶፬። ዝኒ ከማሁ። ሥርዓተ ጽዮን ቁጥር ፶፭:- የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር የተሾመባቸውን ሀገረ ስብከት ሕዝብ ልብ (ስምምነት) ካላገኘ እስከሚቀበሉት ድረስ ታግዶ ይቆይ ይላል። ይህ የሚያመለክተው ሕዝብ ያልወደደው ኤጲስ ቆጶስነት ቢሾም ከተሾመ በኋላም ሕዝቡ በምክያት ያለመቀበል መንፈሳዊ ሥልጣን እንዳለው ነው። ሌላው አሁን አሁን የቀረ የሚመስል ኤጲስ ቆጶሳት ግን ሊያደርጉት ይገባል ብለው የቀኖና መጻሕፍት የሚናገሩት በዲድስቅልያ ፮፣፶፩ "ኤጲስ ቆጶሱም ለድሃዎች፣ የዕለት ራት ለሌላቸው ጦም አዳሪዎች፣ ለባልቴቶች፣ እናትና አባት ለሞቱባቸው ልጆች፣ ለስደተኞች፣ ምንም ለሌላቸው ሰዎች ፍላጎታቸውን ሊያሟላላቸው ይገባል" የሚለውን ነው። ኤጲስ ቆጶሱ ግዳጃቸውን ባይፈጽም ግን እግዚአብሔር ይመራመረዋል። ክርስቲያን ሆኖ የሚቸገር እንዳይኖር እና ቢኖር እንኳ መፍትሔ መስጠት የኤጲስ ቆጶሱ ሥራ መሆኑን ይነግረናል። ሲኖዶስ ዘሰርዶቂስ ትእዛዝ ፮:- ኤጲስ ቆጶስ ለተቸገረ ሁሉ እርዳታን ማድረግ ይገባዋል። እናት አባት የሞቱባቸውን ልጆች፣ መበለቶችን፣ መጠጊያ ያጡትን ችግረኞችን ሁሉ ሊረዳቸው ይገባል እንዲል። (ፍት. ነገ. ፭) ለተሿሚ ኤጲስ ቆጶስ በትንሣኤ አምሳል ሦስት ቀን

በዓል ያድርጉለት። ኤጲስ ቆጶስ በተሾመ ጊዜ ሦስት ሱባኤ በጾም ይኑር። ትእዛዝ ፹፰:- ኤጲስ ቆጶስ የእግዚአብሔርን ገንዘብ ለሥጋ ዘመዶቹ አይስጥ።

፭ኛ ኤጲስ ቆጶስ የሚሻርበት:- የሚከተሉት ቀኖናት ኤጲስ ቆጶስ የሚሻርበርን ምክንያቶች ይናገራሉ። ትእዛዝ ፩:- ኤጲስ ቆጶስ በጉቦ ቢሾም ከሹመቱ ይሻር። ጉቦ ተቀብሎ የሾመውም ይሻር። ትእዛዝ ፬፬:- ኤጲስ ቆጶስ የተቸገሩ ካህናትን አይቶ ቸል ቢል ይለይ (ይሻር)። ትእዛዝ ፵፮:- ኤጲስ ቆጶስ ሁለት ጊዜ ተሹሞ ቢገኝ የሾመውም እርሱም ይሻሩ። ትእዛዝ ፵፯:- ኤጲስ ቆጶስ ደዌ ካልከለከለው በስተቀር ዐቢይ ጾምንና ዓርብ ረቡዕን ባይጾም ይሻር። ሥርዓተ ጽዮን ፹፬:- መኳንንትን የሚያገለግል ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር ይሻር። ሥርዓተ ጽዮን ፺፮:- ከአይሁድ ጋር የሚጾም ወይም በዓላቸውን የሚያከብር ከበዓላቸው ቂጣ ወይም ሌላ ስጦታ የሚቀበል ኤጲስ ቆጶስ ይሻር። አብጥሊስ ፴፩:- ኤጲስ ቆጶስ ሕዝብን ማስተዳደር ባይችል ይህን እስኪያሻሽል ድረስ ከሕዝቡ ይለይ። አብጥሊስ ፵፩:- የክሓድያንን ጥምቀት የተጠመቀ ወይም ከቁርባናቸው የተቀበለ ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር ከሹመቱ ይሻር። አብጥሊስ ፶፩:- ኤጲስ ቆጶስ የተቸገረን ሰው አይቶ ለችግሩ የሚያስፈልገውን ባይሰጠው ችግሩንም ባይቀርፍለት ይሻር። ቀሌምንጦስ ቀኖና ፶፫:- ኤጲስ ቆጶስ ሕዝቡን ባያስተምራቸው ይሻር። ቀሌምንጦስ ቀኖና ፶፬:- በአንድ ሀገር ላይ የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ ከካህናት የተቸገር ሰው አይቶ የሚፈልገውን ባይሰጠው ችግሩንም ባያስወግድለት በአጋጠመው ችግርም ባይረዳው ይሻር። ዲድስቅልያ ፬፣፵፯ ኤጲስ ቆጶስ ባያስተምር ውግዘት ይገባዋል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፭:- በዚህ ዓለም መኳንንት ኃይል ተረድቶ የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር ይሻር።

፮ኛ ጉባኤ ሲኖዶስ:- ሲኖዶስ የጳጳሳት ጉባኤ ነው። ትእዛዝ ፹፯:- የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሁን። አንዱ ጥቅምት ፲፱ ይሁን። አንዱ በበዓለ ኃምሳ መካከል (ርክበ ክህነት) ይሁን። ሥርዓተ ጽዮን ቁጥር ፵፮። ሲኖዶስ ዘአንጾክያ ትእዛዝ ፳። የጎደለውን ሊሞሉ፣ የተጣመመውን ሊያቀኑ ጳጳሳት በዓመት ሁለት ጊዜ ጉባኤ ያደርጋሉ።

፯ኛ ውግዘት:- አንድ ኤጲስ ቆጶስ ባጠፋው ጥፋት ምክንያት ከተወገዘ በኋላ ከውግዘቱ እስኪመለስ ምንም ዓይነት የክህነት ሥራ መሥራት የለበትም። ከሠራ ግን የሚከተሉት ቀኖናት እስከመጨረሻው እንዲሻር ያዝዛሉ። ትእዛዝ ፲፯:- በታወቀ ኃጢአት ምክንያት በትክክል የተሻረ ኤጲስ ቆጶስም ቢኖር ቁስም ቢኖርና ከተሻረ በኋላ ከመሻሩ በፊት በክህነቱ ይሠራ የነበረውን ሥራ ሲሠራ ቢገኝ ፈጽሞ ከቤተክርስቲያን ይራቅ። ሥርዓተ ጽዮን ቁጥር ፹፯:- በታወቀ በደል በትክክል የተሻረ ኤጲስ ቆጶስ ቢኖርና ቀድሞ በተሰጠው ሥልጣን ለመሥራት ቢደፋፈር እስከዘለዓለሙ ድረስ ከቤተክርስቲያን ይሻር። አብጥሊስ ፹፯:- ባደረገው በደል ከቤተክርስቲያን ያስወጡት ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር ከተሻረ በኋላ ከመሻሩ በፊት ይሠራው የነበረውን የክህነት ሥራ ሲሠራ ቢገኝ እስከ መጨረሻው ከቤተክርስቲያን ይሰናበት። ቀሌምንጦስ ቀኖና ፹፯:- ባደረሰው በደል ምክንያት ሥልጣኑ ተይዞ ከቤተክርስቲያን የተባረረ ኤጲስ ቆጶስ ከተወገዘ በኋላ ውግዘቱን አቃሎ በክህነት ቢያገለግል እስከመጨረሻው ከቤተ ክርስቲያን ይሰናበት። ዲድስቅልያ ፮፣፹፰-፹፱ "ቸር እረኛን የማይከተል ይጠፋ ዘንድ ለጅብ እንደሚሆን እንደዚሁ ሰነፍና ክፉ እረኛን የሚከተል ለሞት ይሆናል። ስለዚህ ከማይራሩና መንጋቸውን ከማያድኑ ከክፉዎችና ከከዳተኞች እንርቅ ዘንድ አግባብ ነው" ተብሎ እንደተገለጸው ክፉ እረኞች

እንዳይሾሙብን ሁላችንም በቅርበት መረጃዎችን እየተለዋወጥን መሥራት ይጠበቅብናል። ምእመናንም ሊቃውንትም ጳጳሳትም ሁላችንም የየራሳችን ድርሻ ስላለ ድርሻችንን እንወጣ። ለቤተ ክርስቲያን የማይመጥን ክፉ እረኛ ለመመረጥ ቢቀርብ እምቢ አይሾምብን የማለት መንፈሳዊ መብት አለን። መልካም እረኞች እንዲመረጡ ክፉ እረኞች እንዳይመረጡ ሁላችንም የየራሳችንን ድርሻ እንወጣ።

ርቱዕ ፍትሕ

በዚህ ምድር ትክክለኛ ፍርድ እንደሌለ ያየሁት ብዙዎች በጅምላ ሲገደሉ በዝምታ ያለፈ ሚድያ ለአንድ ባለስልጣን ሞት ግን ሳምንቱን ሙሉ ዜና ሲሠራ ስታዩ ነው። ሰው ከሰው እኩል ነው። የማንኛውም ግድያ በእኩልነት መታየት ነበረበት። ሚች እንደሥራው በፈጣሪ ዘንድ ይፈረድበታል። ጌታ በአጨብጫቢ ብዛት የሚፈርድ አይደለም። ጌታ እውነትን መሠረት አድርጎ ነው የሚፈርደው። ሁሉም በእግዚአብሔር ፊት ምግባሩን ይዞ ነው የሚቀርበው። እስመ አንተ ትፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ እንዲል። ትክክለኛ ፍርድ ናፍቆናል። በአደባባይ የሚዋሽ ውሸታም መሪ ነው ያለን። ከውሸታም እውነትን መፈለግ ራሱ ሞኝነት ነው። ባለሥልጣናት ላጠፉት ጥፋት ይቅርታ መጠየቅ ሲገባቸው ስሕተታቸውን የሚገልጡባቸውን ሰዎች በማሰር ላይ ተጠምደዋል። ደህና ዳኛ ጠፍቶ እንጂ በአደባባይ በስንት ልፋት የሠሩትን ቤት በዶዘር ያስፈረሱ ሰዎች ለፍርድ ይቀርቡ ነበር። ዳኛ የለም እንጂ ቢኖር ኖሮ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት የቀጠፈውን ጦርነት ያስጀመሩትን ለፍርድ ማቅረብ ይገባ ነበር። በየቀኑ በየሳምንቱ በየወሩ ሰዎች በብሔራቸው በቋንቋቸው ምክንያት ይገደላሉ፣ ይታሠራሉ፣ ይሞታሉ። ነገር ግን አሁን የንጹሓንን ሞት ለመድነውና እኛም ዝም አልን። እግዚአብሔር ይፍረድ ብለን ዝም ካልን ብዙ ጊዜ ሆኖናል። ትክክለኛ ፍርድን የምንጠብቀው ከእግዚአብሔር ነው። የሰው ፍርድ አድሎ አይታጣበትም። በእውነት ሳይሆን በስሜት ላይ የተመሠረተ ነው። ስሜት ደግሞ ሁልጊዜ ትክክል አይደለም። እንስሳዊ ስሜት ለሆዱ ሲል፣ በዚች ምድር ለመኖር ሲል፣ ሞትን ፈርቶ እውነትን ይጨፈልቃል። በፍትሐ ነገሥታችን አንቀጽ ፶፫ ፈራጅ ዳኛ የማያዳላ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ የሚያስቀድም፣ የማይፈራ፣ መሆን አለበት ተብሏል። ስለዚህ የማያዳሉ ዳኞች እና ባለሥልጣናት እስኪነሡ ድረስ እንናፍቃለን። በክልል፣ በጎጥ፣ በብሔር፣ በቋንቋ ማሰብ ሀገራችንን ጎድቷታል። ሁሉንም ኢትዮጵያውያን በእኩልነት የሚመለከት መሪ ያስፈልገናል። የሁሉንም ኢትዮጵያውያን ጥቅም የሚያስከብር መሪ ያስፈልገናል። መሪዎች ሞትን ሳይሆን በዋናነት መፍራት ያለባቸሁ ኃጢአትን ነበር። እናንተ ባትሰሙ ወደፊት የምትነሡ መሪዎች ይህንን ብታስቡበት መልካም ነው። ኢትዮጵያ እንደባለፉት አምስት ዓመታት የተዋረደችበት ዘመን በታሪክ አላስታውስም። ጥፋትን ወደሌላ ከመጠቆም ሁሉም በየራሱ ያለውን ጥፋት አይቶ ቢያርም መልካም ነበር።

አነ ዘክርስቶስ

ለአላዋቂ ፎገራ ዱሩ ነው እንዲሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ሳያውቁ በመሰለኝና በግምት ሲሳደቡ የሚውሉ ብዙ ናቸው። የቤተ ክርስቲያናችን አካሏ ራሱ ክርስቶስ ነው። የቤተ ክርስቲያን ትምህርቷ፣ ቅዳሴዋ፣ ማኅሌቷ፣ ትርጓሜዋ፣ ቅኔዋ፣ ዝማሬዋ፣

መዋሥእታ ሁሉ ነገሯ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ነው። እርሱ የቤተ ክርስቲያን መሠረቷና አካሏ ነውና። ብዙ ሰው የእኔ ብሎ በሚያስበው ይመካል። የእኔ ዘመድ፣ የእኔ የትውልድ ስፍራ፣ የእኔ ክልል፣ የእኔ ሀገር፣ የእኔ አህጉር፣ የእኔ ንብረት፣ የእኔ መልክ፣ የእኔ ሰው፣ የእኔ መምህር፣ የእኔ ጳጳስ፣ የእኔ እውቀት ወዘተ ብሎ በሚያስበው ሲመካ ይስተዋላል። ነገር ግን ሁሉም ለሁለንተናችን ዋስትና አይሆኑም። ምክንያቱም እኒህ የጠቀስናቸው ሁሉ ፍጡራን ስለሆኑ ሕጸጽ አለባቸው። ሁሉም ደካሞች ናቸው። ለሰው ልጅ ለመኖሩ ምክንያት ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ብንወድቅ ያነሣን፣ እኛ ብንሞት ሞቶ ያዳነን እርሱ ነው። ብንራብ ሥጋውን ቆርሶ እንኩ ብሎ አለን። ብንጠማ ደሙን አፍስሶ እንኩ ጠጡ አለን። እኛ ክርስቲያኖች የምንመካው በክርስቶስ ነው። ከክርስቶስ ፍቅርም የሚለየን የለም። ቅዱስ ጳውሎስ መኑ የኀድገነ ፍቅሮ ለክርስቶስ ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል!? ረኀብኑ ረኀብ ነውን!? ተሰዶኑ መሰደድ ነውና!? መጥባሕትኑ ሾተል ነውን!? እያለ ይዘረዝራል። እኒህ ሁሉ ከክርስቶስ ፍቅር አይለዩንም። ክርስቲያኖች በዚህች ምድር ኖረውም በአኗኗራቸው ክርስቶስን ይሰብካሉ። ሞተውም በሞታቸው ክርስቶስን ይሰብካሉ። እመኒ ሐዮነ ለእግዚአብሔር ነሐዩ ብንኖር ለእግዚአብሔር እንኖራለን። እመኒ ሞትነ ለእግዚአብሔር ንመውት ብንሞትም ለእግዚአብሔር እንሞታለን።

ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ

ክርስቲያኖች አንድን ነገር የሚለኩት በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ነው። ኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ደግሞ ከእግዚአብሔር የተገለጠ፣ በነቢያት የተነገረ፣ በክርስቶስ የተሰበከ፣ በሐዋርያት የተነገረ፣ በሊቃውንት የተመሠጠረ ነው። የክርስቲያኖች ሀገራቸው እውነት ናት። ንጉሣቸው ክርስቶስ ነው። ምግባቸው ፍቅር ነው። አኗኗራቸው በትሕትና ያሸበረቀ ነው። በወንዝ አይታጠሩም። ወንዜኛ፣ መንደረኛ፣ ጎጠኛ፣ ብሔርተኛ አይደሉም። ክርስቲያኖች ማንንም ሰው በእኩልነት ያያሉ። ከየትም ይወለድ ከየትም ይኑር ጻድቅን ያከብራሉ። ከየትም ይወለድ ከየትም ይኑር ኃጥእን ይገሥፃሉ። አሁን ዘረኝነት አይሎ ብዙው አእምሮውን አጥብቦ ሲታይ ከእውነት ምን ያህል እንዳፈነገጠ ያሳየናል። ሰው ወደ ሰውነቱ ሊመለስ ይገባዋል። በዘረኝነት ዓለም እየኖረ ራሱን በውሸት ባያኖር መልካም ነው። ዘረኛ ሰው ቅዱሳንን ሳይቀር በዘረኝነት እሳቤ ይመለከታል። በተወለዱበት ቦታ ብቻ ለማጠር ይሞክራል። ይሄ አሳዛኝ ነገር ነው። የቅዱሳን አለቃቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ ለዓለም ተሰቅሎ ዓለምን እንዳዳነ በዚህም ምክንያት መድኃኔዓለም እንደተባለ ሁሉ ቅዱሳንም አለቃቸውን አብነት አድርገው የጸለዩት ለዓለም ነው። በረከታቸውም በጸሎታቸው ለታመነ ሁሉ ነው። ስለዚህ ሰው ከታጠረበት የዘረኝነት አጥር ወጥቶ፣ ትምክህቱን በፍጡራን አገልጋዮች ላይ አድርጎ አነ ዘጳውሎስ አነ ዘአጵሎስ ማለቱን ትቶ አነ ዘክርስቶስ ማለት ይገባዋል። የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ እንዲሉ ሐዋርያት ቢያስተምሩ ጸጋን የሚሰጥ ክርስቶስ ነውና። ጸጋዊ ጸጋ እግዚአብሔርን መውደድ የሚገለጠው ደግሞ ትእዛዙን በማክበር ነው።

ወንጌልንና ተረት ተረትን እንለይ

በተለይም ማንኛውም ሰው ጉባዔ ያልዋለበትን እና ያላደላደለውን መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ

መሰለኝ መተርጎም አይገባም። ጥቅስን ለራስ ዓላማ ማዋል ሰይጣናዊ ጠባይ ነው። ጌታን እንዲህ ተብሎ ተጽፏል ብሎ ሰይጣን ለራሱ ዓላማ መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሶ ነበር። ነገር ግን ጌታ እንዲህም ተብሎ ተጽፏል ብሎ ነገሩን ከንቱ አድርጎበታል። ያልተማሩትን ቃል መጥቀስ ያላሳደጉትን ውሻ ጆሮ እንደመቆንጠጥ ነው። ያ እንዲናከስ። ይህም ያሰናክላል። አጥዐወ ጣዖት አመለከ ከሚለው የግእዝ ግሥ "ጣዖት" የሚል ምዕላድ ይወጣል። ጣዖት ምሥጢራዊ ትርጓሜው ሳይፈጥር የሚመለክ የሚፈራ ማለት ነው። ሰማይንና ምድርን የፈጠረ አንድ አምላክ ነው ያለው። ሳይፈጥሩ በውሸትና በተንኮል የሚመለኩ ፍጥረታት ጣዖታት ይባላሉ። እግዚአብሔር ግን ፈጥሮ የሚገዛ ስለሆነ ከእኔ ውጭ ሌላ አምላክ አታምልክ ብሎ ተናግሯል። ዘጸ. ፳፣፪ "ወይቤ አነ ውእቱ እግዚእ እግዚአብሔር ዘአውፃእኩከ እምድረ ግብፅ እምቤተ ቅንየት። ጽኑ አገዛዝ ከምትገዛበት ከግብፅ አገር ያወጣውህ ፈጥሬ የምገዛህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። ኢታምልክ አማልክተ ወኢምንተኒ ዘእንበሌየ። አሁንም ያለ እኔ ምንም ምን ሌላ ባዕድ አምላክ አታምልክ። ካለ በኋላ ቁጥር ፭ ላይ ኢትስግድ ሎሙ ወኢታምልኮሙ ይላል። አትስገድላቸው ተብሏል። ይህ ስግደት የአምልኮ ስግደት ነው። አምልኮ ተገገርነትን፣ ፈሪሐን፣ አክብሮን፣ እና ሰጊድን አጠቃሎ የያዘ ቃል ነው። ራእየ ዮሐንስ ፳፪፣፲፭ ላይ እንደተገለጸው አምስቱ ውሾች ከተባሉት አንዱ "ጣዖት አምላኪ" ነው። ጣዖት አምላኪ የሚባለው እንጨት ጠርቦ፣ ድንጋይ አለዝቦ አምላኬ ነህ ፈጣሪዬ ነህ የሚልና ራሱ ለሠራው ጣዖት መሥዋዕትን የሚያቀርብ አሳዛኝ ሰው ነው። ማንኛውም ሃይማኖተኛ ከሁሉም በፊት ሊጠብቀው የሚገባ ሕግ "ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ" ያለውን ቃል ነው። እግዚአብሔርን ትቶ በሌላ ያመለከ ሰው ጣዖት አምላኪ ይባላል። ዋናው የፍቅረ እግዚአብሔር መገለጫ እግዚአብሔርን ማምለክ ነው። እግዚአብሔርን የማምለክ መገለጫው ደግሞ ተጠምቆ ቆርቦ የእርሱ የጸጋ ልጅ ሆኖ፣ ምሥጢራትን መፈጸምና መልካም ሥራን መሥራት ነው።

ነገረ ሃይማኖት

አንድ እግዚአብሔር አንድ አምላክ አንድ ሃይማኖት እያለ ይህ ሁሉ እምነት ከምን መጣ? ማቴ. ፲፫፣፳፭ "ሰዎቹ ሲተኙ ግን ጠላቱ መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ" ተብሎ እንደተገለጸው ክፉ አስተሳሰብንና ትምህርትን ሰይጣን በሰዎች ልቡና እያሳደረ ብዙ ቤተ እምነቶች እንዲመሠረቱ ሆኗል። በተጨማሪም በጉሥዐተ ልብ (በልብ ወለድ) ሰው የራሱን መሰለኝ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ እያደረገ ቤተ እምነት እስከ መመሥረት ደርሷል። በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አርዮሳውያን ያደረሱት በደል የጉሥዐተ ልብ ውጤት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ትቤ ጥበብ ፈጠረኒ አብ መቅድመ ኩሉ ተግባሩ ያለውን ጥቅስ ያለ አግባብ ጠቅሶ ጥበብ ወልድ ነው። ስለዚህ ወልድን አብ ፈጠረው ብሎ የራሱን መሰለኝ የሃይማኖት አስተምህሮ አስመስሎ አቀረበ። ነገር ግን ዝቅ ብሎ ቢያየው እምቅድመ አድባር ወአውግር ወለደኒ ሲል ያገኘው ነበር። ፈጠረ ወለደ ተብሎ ይተረጎማል። ወለደም ፈጠረ ተብሎ የሚተረጎምበት ወቅት አለ። ኦሪት ዘልደት ባለ ጊዜ ኦሪት ዘፍጥረት ማለት መሆኑን ልብ ይሏል። የራስን መሰለኝ የሃይማኖት አስተምህሮ አድርጎ ማቅረብ ይህ ሁሉ ቤተ እምነት እንዲፈበረክ ምክንያት ሆኗል። ጣዖት ማምለክን ሴሩህ ጀምሮታል። ይህ ሴሩህ ብኑ የሚባል ልጅ ነበረው። በሕግንነቱ ተቀሠፈበት። ይወደው ነበርና እንቅበረው ቢሉ ከመውደዱ የተነሣ

አላስቀብርም አለ። ሲወጣ ሲገባ ልጄ ብኑ፣ ልጄ ብኑ እያለ ኀዘን ጸናበት። የሀገሩ ሰዎች ወጥቶ በሄደበት ያንን ልጅ ቀብረው እንጨት ጠርበው ጆሮ፣ አፍንጫ፣ ዓይን፣ እጅ፣ እግር ቀርጸው ቀለም ቀብተው ቀሚስ አጥልቀው በኋላው አቁመው ልጅህ ተነሣልህ አሉት። ልጄ ብኑ ነህን አለው። በዚያ በእንጨት ያደረ ሰይጣንም "እ" አለ። አምላክ ካልሆነ ተነሥቶ ተነጋገረውን? ብለው የሚያመልኩበት ሆኗል። ንጉሠ እስራኤል ዳዊት ስለጣዖታት በመዝ.፻፲፫፣፲፫-፲፰ ላይ "አፍ አላቸው አይናገሩም። ዓይን አላቸው አያዩም። ጆሮ አላቸው አይሰሙም፣ አፍንጫ አላቸው አያሸቱም፣ እጅ አላቸው አይዳስሱም፣ እግር አላቸው አይሄዱም" ብሎ ተናግሯል። ጣዖት የሚባሉት እንዲህ ናቸው። ሰው ያመልካቸዋል እንጂ ማንንም አልፈጠሩም። በማንም ላይም ጉዳትን አያመጡም። ደካሞች ናቸው። ሰው ዝም ብሎ ነው የሚፈራቸው።

ቴክኖሎጂ

የሰው ልጅ ጥሮ ግሮ ይበላ ዘንድ ከፈጣሪው ትእዛዝ ተሰጥቶታል። ስለዚህም ሰው በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰልፎ ይሠራል። ያርሳል፣ ይቆፍራል፣ ይጽፋል፣ ይደጉሳል፣ ይሮጣል፣ ቤት ይሠራል፣ ወዘተ። ይህንን ሥራውን ደግሞ በየዘመናቱ በተሠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ያሳልጣል። ለምሳሌ በበሬ ያርስ የነበረው በትራክተር እያለ ድካሙን ይቀንሳል። ነገር ግን አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በተሠሩ ቁጥር ተፈጥሮን እና ለሰው ልጅ ጥበብን የሰጠ እግዚአብሔርን ከማመስገን ይልቅ ሰይጣናዊ አሠራር አድርጎ የማቅረብ ክፉ ልማድ አለ። ለምሳሌ በአጼ ምኒልክ ዘመን ስልክ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ሲመጣ እና ንጉሠ ነገሥቱ ሲነጋገሩበት የሰሙ አንዳንድ ቄሶች ንጉሡ ከሰይጣን ጋር ተነጋገረ ብለው እንደነበር ይነገራል። ሕዝቡም ስላልተማረ የእነ ቄሴ ንግግር ለተወሰነ ጊዜ ተስማምቶት ነበር። በኋላ ዓይናማ ሊቃውንት ከንጉሡ ጋር ሲሆኑ ውሸት እየቀለሉት መጣች። ብዙ አትፍረዱባቸው። ብዙ ያልተማረ ሰው ትምህርቱ ካለቀበት አላዋቂ መባልን ስለሚፈራ እርሱ የማያውቀውን ነገር ሁሉ ከሰይጣን ጋር ያያይዘዋል። በእርግጥ ትሕትና ያለው ከሆነ ዝቅ ብሎ ይማራል። ምሁራኑ ሊቃውንቱ ግን የማያውቁት ጉዳይ ከገጠማቸው አላውቀውም ይላሉ እንጂ በግምት አይናገሩም። ስፖርት ከሳይንስ ክፍሎች አንዱ ነው። በውስጡም ብዙ ዘርፎች አሉት። ሩጫ፣ ውርወራ፣ ዝላይ፣ እግር ኳስ፣ መረብ ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ ፈረስ ጉግስ፣ ዋና እና የመሳሰሉት የስፖርት ዓይነቶች ናቸው። እነዚህ ነገሮች እንኳንስ ጣዖት አምልኮ ሊሆኑ በራሳቸው ኃጢአት ሊሆኑ እንኳ ፈጽሞ አይችሉም። ጣዖት አምልኮ የሃይማኖት ነው። ኃጢአት ደግሞ በሃይማኖት ውስጥ ያለ ሰው ሆኖ ምግባረ ጽድቅን አለመሥራት ነው። በሀገራችን ሀገራችንን በበጎ ያስጠሩ እነ አትሌት አበበ ቢቂላ፣ እነ መሠረት ደፋር፣ እነ አትሌት ደራርቱ ቱሉ፣ እነ ቀነኒሳ በቀለ፣ እነ ጥሩነሽ ዲባባ እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ። ሩጫ አንድ የሙያ ዘርፍ ነው። ስለዚህ በሩጫው ዓለም ያላችሁ ውድ ክርስቲያኖች ካላችሁ በርትታችሁ ሥሩና እንደቀደሙ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ አሳውቁት። እግር ኳስ አንድ የሙያ መስክ ነው። በእግር ኳስ ያላችሁ ወንድሞች ጠንክራችሁ ሥሩና ሀገራችሁን በሙያችሁ አስጠሯት። ይህ ሥራችሁ ጽድቅ ነው አንልም። ኩነኔም እንዳልሆነ ግን አስረግጬ እናገራለሁ። ቤተ ክርስቲያን ዘፋኝነትን ነው አጥብቃ የምትቃወመው። ስለዚህ ዘፋኞች ደግሞ ንስሓ ገብታችሁ ሌላ ሙያ ቀይሩ። ስፖርተኛ ስፖርት ሠርቶ አሥራቱን ለቤተክርስቲያን ይስጥ። አራሽም አርሶ አሥራቱን

ለቤተክርስቲያን ይስጥ። የዘፋኝንና የዘማውያንን አሥራት ግን ቤተ ክርስቲያን አትቀበልም። መጀመሪያ ንስሓ መግባት አለባቸውና። ስለዚህ እግር ኪስም ልክ እንደ እርሻ እና ንግድ ሁሉ አንድ የሥራ መስክ ስለሆነ በራሱ ኃጢአት አይደለም። ሰው ካመለከው ግን እግር ኪስ ብቻ ሳይሆን እርሻም ንግድም እንጀራም ዳቦም ጣዖት አምልኮ ነው። በተረፈ እግር ኪስ ተመልካች ጣዖት አምላኪ ነው የሚል ትምህርት ግን የለም። ምናልባት ከመበለቶች መጽሐፍ ከተገኘ እንጃ። የመበለት አጫዋቾችን ጠይቁ። አንዱ ስለዶሮ ብልት ይተነትናል። አንዱ ወንጌል በሚነገርበት ዓውደ ምሕረት ስለኪስ ይሰብካል። እረ ተው ጎበዝ እንዳታስቀስፉን። መጋቤ ኪስ ወቡና ወዶሮ ብልት ወእንቁላል እየሆናችሁ ስንት አመስጥሮ ያላትን ቤተ ክርስቲያን በእናንተ ተራ ወሬ አታሰድቧት ለማለት ያህል ነው። ሌላው የምዕራባውያን የሆነውን ሁሉ እንደ ርኩስ መቁጠር ነውር ነው። መልካሙን መያዝ ክፉውን መተውን እንልመድ። ምዕራባውያንን መጥላትምኮ ክርስትና አይደለም። ክርስትና ሁሉንም ሰው መውደድ ነው። ለይተን ክፉ ሥራቸውን ለመጥላት እንሞክር። በአሁኑ ጊዜኮ ከእኛ አይብሱም። በሚልየን ሕዝብ የተገዳደልን እኛ ነንኮ። ከእኛም ከእነርሱም ክፉውን እንተወው። ከእኛም ከእነርሱም መልካሙን እንያዝ። በኪስ ምክንያት፣ በእርሻ ምክንያት፣ በትምህርት ምክንያት፣ እና በመሳሰሉት ከቅዳሴ መቅረት አይገባም። አንድ ሰው በእነዚህ ምክንያት ከቅዳሴ ስለቀረ ግን ትምህርት፣ እርሻ፣ ኪስ፣ ጽሕፈት ጣዖት አምልኮ ናቸው አይባልም። ፍልጠኪ አርቄ ምድር___አንቺ እባብ ለዩ

የመበለት ዱላ

መበለት ማለት አሮጊት ሴት ማለት ነው። የኔታ ቡሩክ በደብረ ሊባኖስ ገዳም የነበሩ የመጽሐፍና የቅኔ መምህር ነበሩ። እና አንድ ቀን "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለ" ብለው ይናገራሉ። ይህን የሰሙ መበለቶች ዱላቸውን ይዘው የኔታን ሊደባደቡ ግርርርርር ይላሉ። ይህንን የተመለከቱ አንድ ሽምገል ያሉ ሰውየ "ቆይ እስኪ ከዱላው በፊት እንጠይቀው" ይሉና። ሄደው አንተን ብሎ መምህር ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለ ብለሃል አሉ እውነት ነው ይሏቸዋል። የኔታም "አዎ እውነት ነው ለእግዚአብሔርኮ የሚሳነው ነገር አለ" ብለው ይደግሙታል። የሰው ብስጭት ጨመረና "ምንድን ነው እግዚአብሔርን የሚሳነው?" ይሏቸዋል። የኔታም ሲመልሱ "ውሸት ነዋ" ብለው መለሱ። እግዚአብሔር ጻድቅነት የባሕርይው ነው ካልን ውሸት ይሳነዋል ማለት ነው ብለው ሲናገሩ ዱላ ይዞ የመጣው መበለት ሁሉ አፍሮ ወደየቤቱ ሄደ ብሎ አንድ የኔታን በቅርበት የሚያውቃቸው ሰው ነግሮኛል። እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ያለ ምሉዕ ነው፣ ጻድቅ ነው፣ ኃያል ነው ወዘተ ካልን ይህ የባሕርይው ስለሆነ አይለወጥም ማለት ነው። ምክንያቱም የባሕርይ ማለት የማይለወጥ የራስ የሆነ ነገር ማለት ነው። እግዚአብሔር አይለወጥም። እንደማይለወጥም በትን. ሚል.፫፣፮ እንዲሁም መዝ. ፩፻፩፣፳፯ ተገልጿል። እግዚአብሔር ምሉዕነት የባሕርይው ከሆነ ምሉዕነቱን መተው አይችልም ማለት ነው። እግዚአብሔር ኃያልነት የባሕርይው ነው ካልን ኃያልነቱን አይተውም ማለት ነው። ነገረ ሥጋዌን ስንናገር እንኳ ቃል ቃልነቱን ሳይለቅ ሥጋን ሆነ ሥጋም ሥጋነቱን ሳይለቅ ቃልን ሆነ ነው የምንለው። ኃያሉ ኃያልነቱን ሳይለቅ ድኩም ሥጋን ተዋሐደ። የማይሞተው የማይሞትነትን ሳይለቅ የሚሞት ሥጋን ገንዘቡ አደረገ። ይህንም ተዐቅቦ በተዋሕዶ እንለዋለን። የአንድን ሰው ሐሳብ ምክንያቱን እና የሐሳቡን መነሻ ሳይረዱ በግምት

መናገር አይገባም። ዱላን ከማንሳት መጠየቅ ይቀድማል። በተለይ ሴት ልጅ ጭምት ዝም ያለች በትሕትና የምትኖር መሆን አለባት። ፈጠን ፈጠን የምትል ቀባጣሪ መሆን የለባትም። የቤተ ክርስቲያን ያልሆነን ትምህርት የቤተ ክርስቲያን እያስመሰሉ ማቅረብ ይቅር። ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮዋ ከወርቅ የጠራ ነው። በነቢያት የተነገረ፣ በሐዋርያት የተሰበከ፣ በሊቃውንት የተመሠጠረ ትምህርት አላት። ከዚያ ውጭ የራስን ግላዊ እይታ አስተምህሮዋ አስመስሎ ማቅረብ አይገባም። አርዮስ በመሰለኝ በካደ ጊዜ ሊቃውንቱ "ከመጽሐፍ አላገኘኽው፣ ከመምህር አልተማርከው እባክህ ይቅርብህ። አስብኽው ከሆነ አትናገረው፣ ተናግረኽው ከሆነ አትድገመው" ብለውት ነበር። እርሱ ግን ስላልሰማቸው ራሱን ጎዳ። በክፋት እና በስሕተት ጎዳና ያለ ሰው መጀመሪያ የሚጎዳው ራሱን ነው። በሰው ጭብጫቦ ሰክሮ እውነትን መጨቆን አይገባም። የሰውን ጨኽት ፈርቶም እውነትን መደበቅ አይገባም። ሰው መዋቲ ነው። ፈራሽ በስባሽ የሆነ ሰውን መፍራት አይገባም። ነቢዩ ቅዱስ ኢሳይያስ እንኳ ንጉሡ ያዝያንን ፈርቶ እውነትን ቢሸሻት ለምጻም ሆኗል። በዓመተ ሞተ ያዝያን ንጉሥ ብሎ ራሱ ያመጣዋል። ያ የምትፈራው የምታፍረው ንጉሥ ሞተ ለማለት። የማይሞተው አምላክን መፍራት እንደሚገባው ለማመልከትም ቀጥሎ ርኢክሆ ለእግዚአብሔር እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ነዊኅ ብሎ ያመጣዋል። ሰው ቤተ ክርስቲያንን ሊከተል ይገባዋል። አስተምህሮዋን መጠንቀቅ ይገባዋል። እውነት በአጨብጫቢ ብዛት አትለካም። የእውነት ልኳ ራሱ ክርስቶስ ነው። በምጽአት ጊዜ ለሁሉ በአደባባይ ትገለጣለች። እስከዚያው ግን ኃጥአን ጻድቃን መስለው ሊኖሩ ይችላሉ። ጻድቃንም ኃጥአን ተብለው ሊኖሩ ይችላሉ። ያች የእውነት ቀን ስትመጣ ሁሉ ይገለጣል። እርሱ ሞቶ እኛን ያዳነን መድኃኔዓለምን እናስበው። ፍቅርን በተግባር አሳየን። እውነት እርሱ ነው። እርሱን እንከተል።

ተግሣጽ ስድብ

በአንድ ወቅት በአንድ ቤት ብዙ ሰዎች ተኝተው ሳለ አንዱ ፈርቶ ሌሎች የተኙ ሰዎች/ሳይሰሙ ከዚያው ከቤት ይጸዳዳል። በኋላ ሲያስበው ሰው ሊስቅበት ነው። ከዚያ ሰገራውን/በእጁ ይዞ የሁሉንም ልብስ እንደተኙ ይቀባዋል። እርሱም እጁን አባብሶ መልሶ ይተኛል።/እነዚያ የተኙት ሰዎች በኋላ ነቅተው ወደ ውጭ ወጣ ብለው ሳሉ ልብሳቸውን ቢያዩት ሰገራ በሰገራ ሆኗል። ሰው እንዳይስቅብን ብለው እነርሱ እንዳላደረጉት እያወቁ ጠፍተው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ይባላል። ያ አራም ግን በሰላም ከቤት ተኝቶ አደረ ይባላል። አሁን እየሆነ ያለው ነገር ይህን ይመስላል። አራሞች በሰላም እየኖሩ ንጹሓን የሚሸማቀቁበት ክፉ ዘመን ነው። ነውረኞች ተወደው በሰላም እየኖሩ ነውረኞች ነውራቸውን የቀቧቸው ንጹሓን ሰዎች እየተሰደቡ ይኖራሉ። ምሁራን ዝም ብለው ተሳዳቢዎች ተናጋሪ የሆኑበት ዘመን ነው። ስድብና ተግሣጽ ይለያያል። ገሠጸ ተቆጣ፣ መታ፣ ደበደበ፣ አስተማረ ከሚለው የግእዝ ቃል ተግሣጽ የሚል ባዕድ ዘር ይወጣል። ትርጉሙ ቁጣ፣ ትምህርት ማለት ነው። መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ በሚልበት ጊዜ መገሥጽ የሚያስተምር ተብሎ ይተረጎማል እንጂ የሚሳደብ ተብሎ አይተረጎምም። ስድብ ጸዐለ ሰደበ ከሚለው የግእዝ ቃል የሚወጣ ሲሆን "ጽዕለት" መስደብ፣ መሰደብ ስድብ ይላል። ለምሳሌ ሕፃናትን መገሠጽ ይገባል ሲባል ትምህርት ሲገድፉ እና አልማር ሲሉ መቆጣት ይገባል ማለት ነው። እየቀጡ እየመቱ ማረም ይገባል ማለት ነው።

ስንማታ ግን ሕይወታቸው እንዳያልፍብን ባለፈው በፍትሐ ነገሥት እንደተማርነው የምንማታበትን ኃይል በራሳችን ጉልበት ፈትነን አማትበን ሊሆን ይገባል። የሞት ብዙ ምክንያት አለውና ተብሎ ተገልጿል። የተግሣጽ ትርጓሜ ይህ ነው። ከዚያ ውጭ ጥርግርግ እያደረጉ እየተሳደቡ ያሉ ሰዎችን መምህር ወመገሥጽ ማለት ትልቅ ነውር ነው። ንስሓ እንዳይገቡም መሰናክል መሆን ነው። እየተሳደበ የሚያስተምር ሰው መምህር ወመገሥጽ ሳይሆን መምህር ወመጽዕል ነው የሚባለው። ለቤተክርስቲያን ትልቅ ሸክም እየሆኑ ያሉት እነዚህ ናቸው። እናርማለን ይላሉ። ነገር ግን እነርሱ ተሳስተው ስታርማቸው ተሳዳቢ መንጋቸውን ይለቁብሃል። ደግሞ መንጋን መፍራት ተገቢ አይደለም። ማንኛውም መምህር በቀዳሚነት ሊፈራው የሚገባው እግዚአብሔርን ነው። ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር ዳኝነት በመላእክትና በሰው ሁሉ ፊት ይቀርባል። ይህንን ነው ማሰብ። በክፉዎች መሰደብ ለመምህራን ክብር ነው። ከታገሡት ሐዋርያዊ ክብርን ያሰጣቸዋልና። ስለዚህ ተሳዳቢነትን እንተው። ተምረን እናስተምር። ሳይማሩ ማስተማር ጥፋት ይኖረዋልና። ከተሳሳትን ይቅርታ እንጠይቅ። ሰው አምላኪ አንሁን። የሰውን መልካምነቱን ብቻ እንውሰድ። ክፉ ነገሩን አብነት ማድረግ አይገባም።

በእንተ ትርጓሜ

በቀድሞ ዘመን የላይ ቤትና የታች ቤት መተርጉማን በምሳሌ ምክንያት አይግባቡም ነበር ይባላል። ወንጌላውያን ለምን አራት ሆኑ ለሚለው ሐተታ ሲሰጡ አራት ወቅት፣ አራት ኪሩቤል፣ አራት ባሕርያት_____ እያሉ ከሰጡ በኋላ አራትነት ያለውን ነገር ሁሉ ካልመሰልን ይላሉ። ይህን የተመለከተ አንድ ሊቅ ወደ ቤቱ ሲገባ ከግርግሙ ላይ አራት አሞሌ ጨው ተሰቅሎ ያያል። እና ሚስቱን ጠርቶ "እኒያ ሰዎች የአራቱ ወንጌላውያን ምሳሌ እንዳያደርጉት ደብቂው" አሉ ይባላል። ምሳሌ ሲሰጥ መጽሐፍን ሳይለቁ ነው። እንጂ ጥቂት መመሳሰል ያለውን ነገር ሁሉ ምሳሌ ካላደረግነው አይባልም። ሊቃውንት አባቶቻችን ምሥጢረ ሥላሴን በፀሐይ ሲመስሉ በውስተ ፀሐይ ሜመ ጽላሎቶ የሚለውን የመዝሙረ ዳዊት ክፍል አብነት አድርገው ነው። ጽላሎት የአካል ምሳሌ ነውና። ሰውን የምሥጢረ ሥጋዌ ምሳሌ ያደረጉት ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ የሚለውን የኦሪት ዘልደት ቃል መሠረት አድርገው ነው። አርአያ በቁሙ ምሳሌ ነውና። ምሥጢረ ሥላሴን በእሳት ሲመስሉት በቀሌምንጦስ አቡየ እሳት ወአነ ብርሃኑ ወመንፈስ ቅዱስ ዋዕዩ የሚለውን ኃይለ ቃል መሠረት አድርገው ነው። ምሳሌያትን ሁሉ ብንመለከት መጽሐፋዊ መሠረት ያላቸው ናቸው። ስለዚህ ከአበው ትምህርት፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት ባንወጣ መልካም ነው። አንዱ ምሳሌ ለሁለት ተቃራኒ ነገሮች የሚመሰልበት ወቅትም አለ። ምሳሌ ኮከብ የቅዱሳን ምሳሌም ይሆናል። ለአብርሃም አበዝኖ ለዘርዕከ ከመ ኮከበ ሰማይ ወከመ ጥፃ ዘድንጋገ ባሕር ሲል ኮከብ የቅዱሳን ጥፃ የኀጥአን ምሳሌ ሆኗል። ሲታተትም ኮከብ ብሩህ እንዲሆነ ጻድቃንም ብሩሃነ አእምሮ ናቸውና ይላል። የሰይጣን ምሳሌም ሆኗል። እፎ ወድቀ ኮከበ ጽባሕ ሲል ኮከበ ጽባሕ ያለው ሰይጣንን ነው። ለሁሉም ግን መጽሐፋዊ መሠረት አለው። መቼም ሁሉም ምሳሌ ዘየኀፅፅ ነው በማለት ሁሉን ለሁሉ ምሳሌ ላድርግህ ማለት አይገባም። ሕፀፁ እንዳይጎላብን መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

፩) ሴት ልጅ ወንዶች ባሉበት በዓውደ ምሕረት መዘመር አትችልም። ይህንን ቅዱስ ጳውሎስ በግልጽ ነግሮናል። 1ኛ ቆሮ. ፲፬፣ ፴፬ "ሴቶችም በቤተ ክርስቲያን ዝም ይበሉ። ሊታዘዙ እንጂ ሊናገሩ አልተፈቀደምና። ኦሪትም እንዲህ ብሏልና። ለሴት በቤተክርስቲያን መናገር ክልክል ነው" እንዲል። በተጨማሪም 1ኛ ጢሞ. 2፣11 "ሴት ግን በጸጥታ ትኑር እንጂ እንድታስተምር ወይም በወንድ ላይ እንድትሰለጥን አንፈቅድም" እንዲል። የሙሴ እኅት ማርያም እንኳ በሴቶች መካከል ዘመረች ይላል እንጂ በወንዶች መካከል አልዘመረችም። ዘጸ. ፲፭፣፳ "የአሮን እኅት ነቢይቱ ማርያምም ከበሮ በእጇ ወሰደች። ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዝማሬ በኋላዋ ወጡ። ማርያምም አስቀድማ ለእግዚአብሔር እንዘምር አለች" እንዲል። ሴት ሴቶችን ማስተማር ትችላለች። ቲቶ ፪፣፫ "ባልቴቶችም___በጎ የሆነውንም ትምህርት ራሳቸውን ያነጹ ዘንድ ለሴቶች ያስተምሩ" እንዲል። ሴቶች ዘማርያት ሆነው በዓውደ ምሕረት ሲዘምሩ ጳጳሱ ዝም ስላለ ልክ ነው አይባልም። ይህ በቸልተኝነት የመጣ ክፉ ልማድ ነው። ወደፊት ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከፍትሐ ነገሥት፣ ከሥርዓት የተጣላ ትውልድ እንዳይፈጠር እሰጋለሁ። ምክንያቱም አሁን አሁን በተለይ ከ1900 ዓ. ም ወዲህ ብዙ ነገሮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ያፈነገጡ ናቸው። ልምድ ሆነው ሰውም ዝም ብሏል። ክፉ ልማድ ሥር ሳይሰድ ካልነቀልነው የወደፊት ምእመናን ሃይማኖታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ያፈነገጠ እየመሰላቸው ይቸገራሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከፍትሐ ነገሥት የተጣሉ የልማድ ሰዎች ይሆኑብናል። በእርግጥ አንዳንድ ታላላቅ አድባራት ላይ አሁንም ቢሆን ሴቶች በዓውደ ምሕረት አይዘምሩም። ይህ በሁሉም ሊሆን ይገባል።

፪) የጾም ሰዓት ከዐቢይ ጾም ውጭ ያሉት እስከ ፱ ሰዓት ይጾማሉ። ሰው ግን ጾሙ 7 ሰዓት ላይ ይበላል። ከየት የመጣ ሥርዓት ነው ይሄ??? ጾሙን ሳይጨርሰው ገደፈኮ?። ይህ ሊስተካከል ይገባል። አንድ ቀን ቆማ ፋሲለደስ አቡነ እንድርያስ ዐቢይ ጾም ሊገባ ሲል ዘወረደ እስከ ፲፪ ሰዓት ይጾማል፣ ሰሙነ ሕማማት እስከ ምሽቱ ፩ ሰዓት ይጾማል። ከቅድስት እስከ ኒቆዲሞስ ዓርብ እስከ ፲፩ ሰዓት ይጾማል ብለው አስተማሩና እንኳን እውነቱን ነገርኳችሁ እንጂ ከዚህ በኋላ የራሳችሁ ውሳኔ ነው አሉ። እና ብዙ እውነታዎች አሉ። ያው መረር ቢላችሁም እውነታዋን መናገር ይሻላል። አንዳንዱ ይህ አንገብጋቢ ጉዳይ አይደለም ይልሀል። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ካለመጠበቅ በላይ አንገብጋቢ ጉዳይ አለ ወይ? በሉ ደህና ዋሉ።

በእንተ ሲኖዶስ

ሲኖዶስ አይሳሳትም፣ ፓትርያርክ አይሳሳትም የሚል አስተምህሮ የለንም። እንዲህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ካቶሊኮች ናቸው። ሲኖዶስም ይሳሳታል። በታሪክም የኬልቄዶን ሲኖዶስ ተሳስቶ ጉባኤው ራሱ ተወግሏል። ብዙ ፓትርያርኮች ተሳስተው ተወግዘዋል። በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማይሳሳት እግዚአብሔር ነው። እንዲሁም የእርሱ አካል የሆነችዋ ቤተ ክርስቲያን አትሳሳትም። ሁልጊዜም ልክ ናት። ሲኖዶስ የማይሳሳት የመጨረሻ ወሳኝ አካል ስለሆነ ሁልጊዜ እንቀበለው አይባልም። ሲኖዶሱ ሲሳሳትም ስሕተቱን እናከብራለን እንቀበላለን አይባልም። ነውር ነው። ሲኖዶስ ራሱ በእግዚአብሔር ሕግ ይለካል። ከእግዚአብሔር ሕግ ካፈነገጠ ውሳኔው ተቀባይነት አይኖረውም። የሲኖዶስ የበላይ አካል መንፈስ ቅዱስ ነው።

ስለዚህ ከመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ የሚቃረን ሲኖዶስ ከመጣ ይታረማል። ቀኖናን ሦስት ሰዎች ሲሽሩት ለምን ተሻረ ማለትና 70 ሰዎች ሲሽሩት ደግሞ ዝም ማለት አሳፋሪ ነው። እመሰ አማን ጽድቀ ትነቡ እውነትን የምትናገሩ ከሆነ ሁልጊዜም እውነትን መናገር ነው እንጂ አንዳንድ ጊዜ በዋልድባም ይዘፈናል በሚል የተሳሳተ ብሂል ዘፈንን ማጽደቅ ነውር ነው። የሲኖዶሱን ስሕተት justify ለማድረግ የምትለፉ ሰዎች አድርባይነታችሁንና አጨብጫቢነታችሁን ከማሳወቅ በላይ ፋይዳ የለውም። ገና ለገና አለቅነት፣ የደብር መምህርነትን እና ሹመትን ፈልጋችሁ ከእውነት ጋር ባትጣሉ ጥሩ ነው። ለምእመናንም ክፉ ትምህርትን አታስተምሩ። አንዳንዱ ደግሞ የሥጋ ሞትን ለማስቀረት የነፍስ ሞትን የሚያስከትል ውሳኔን ሲደግፍ እናየዋለን። በእርሱ ምክንያት መላእክት ከሚከፋፈሉ የሰይጣንንም ሐሳቡን ተቀብለን በሆደ ሰፊነት በፍቅር ከመላእክት ጋር ቢኖር ልንል የምንፈልግ ጥቃቅን ሰዎችም አለን። በሃይማኖት እንዲህ ዓይነት ቀልድ አለ እንዴ!? ሰይጣን እንዳይተናኮልህና አካላዊ ጉዳት እንዳያደርድብህ ተስማምተኸው ኑርኮ አይባልም። በጳጳሳቱ ስሕተት ተጠያቂዎቹ ራሳቸው ጳጳሳቱ ናቸው። ምእመናን ምንም ሊጠራጠሩ አይገባም። ራሳቸው በተሳሳቱት ስህተት በፈጣሪ ይጠየቁበታል። እነርሱ ያልፋሉ። ቤተክርስቲያን ግን ለዘለዓለሙ ትኖራለች። የተሳሳቱት ጳጳሳቱ እንጂ ቤተክርስቲያን አይደለችም። ስለዚህ ሁልጊዜም ንጽሕት ቅድስት የሆነች ቤተ ክርስቲያንን እንጠብቃት። ወደፊት እንዲህ ዓይነት ጳጳሳት እንዳይሾሙ ጥንቃቄ እናድርግ። ለቤተ ክርስቲያን የሚቀርቧት ሃይማኖታቸው ሌላ የሆኑ ሰዎች ሽመልስ አብዲሳና ዐቢይ አሕመድ ሳይሆኑ የሊቃውንት ጉባኤ ነው። ተወግዘው የነበሩ ሰዎች የመጡት ይቅርታ ጠይቀው አይደለም። ለጳጳሳት የሚበጀው ጠቅላይ ሚኒስትርን ከመፍራት ይልቅ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። አንዳንዱ ደግሞ ከሲኖዶስ አትበልጥም ይልሃል። ከሲኖዶስ እበልጣለሁ ማን አለ!? ደግሞስ ሲኖዶሱ ከእኔ ስለሚበልጥ ስሕተቱንም አሜን ልበል ይባላል እንዴ!? እንዲያማ ካልን ዲዮስቆሮስም ከሲኖዶሱ አልበልጥም ብሎ ከኬልቄዶናውያን ጋር ተስማምቶ መኖር ነበረበት ይባላል እንዴ!? ቅዱስ ገብርኤል በመዓርግ ከእርሱ ከፍ ያለው ሳጥናኤል ሲሳሳት በመዓርግ ስለሚበልጠኝ ብሎ ዝም ብሎታል እንዴ!? ተው እንጂ።

መለካዊነት

፩) ምእመናን በጭራሽ መጠራጠር አያስፈልግም። ይህንን በደል የበደሉት የሲኖዶስ አባላት ጳጳሳት ስለሆኑ በደሉም ኩነኔውም በራሳቸው ነው የሚሆነው። እግዚአብሔርም በእነርሱ ውንብድና ምእመናንን አይጠይቅም።

፪) ይህንን ታላቅ ጥፋት ያጠፉት የሲኖዶስ አባላት ናቸው እንጂ ቤተክርስቲያን እና መንፈስቅዱስ አይደሉም። ስለዚህ ቤተክርስቲያንን ካህናትን ሊቃውንትን ከመቼውም ጊዜ በላይ መጠበቅ መውደድ እንጂ በዚህ ምክንያት መራቅ አይገባም።

፫) በዚህ ምክንያት ጳጳሳቱ ክፉዎች ቢሆኑም ሐዋርያዊ የክህነት ቅብብሎሹ አልተቋረጠም አይቋረጥም። ስለዚህ ከእነርሱ ክህነት አልቀበልም፣ አልቆርብም ማለት አይገባም። ምክንያቱም ፍትሐ ነገሥት ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ክፉዎች ካህናትን በመጨረሻው ሰዓት

በራሳቸው ኃጢአት ይጠይቃቸዋል። ጸጋውን ግን በክፉ ካህንም በደግ ካህንም አድርጎ ይሰጣል። ስለዚህ በራሳቸው ኃጢአት ራሳቸው ይጠየቁበታል። እኛ ግን ሳንጠራጠር መስቀል መሳለም፣ መቁረብ፣ ክህነትን መቀበል ወዘተ እንችላለን። በተቻለን አቅም ወደፊት ደጋግ ጳጳሳት እስኪነሱ መጸለይ መሥራት ከእኛ ይጠበቃል። እኒህ አሁን ያሉት ዘለዓለማዊ አይደሉም። ያልፋሉ። ተተኪዎቹ ደጋግ እንዲሆኑ፣ ለእግዚአብሔር ሕግና ቀኖና የሚኖሩ እንዲሆኑ ከአሁኑ መሥራት ከእኛ ይጠበቃል። እስከዚያው ግን የአሁኖቹን ክፉነታቸውን ተረድተን ነገር ግን እግዚአብሔር በደግም በክፉም ካህን አድሮ ጸጋውን እንደሚሰጥ አስበን በደላቸውን ለራሳቸው ትተን እኛ በእነርሱው መመራት ይገባናል እንጂ በዚህ ምክንያት ወደሌላ ቤተ እምነት መፍለስ እና ምሥጢራት አልፈጽምም ማለት አይገባም።

፬) በቤተ ክርስቲያን ትምህርት እውነትን እውነት፣ ሐሰትን ሐሰት ማለት ይገባል እንጂ ንጉሥ የወደደውን ዘመን የፈለገውን ተብሎ ከእውነት ማፈግፈግ ጥሩ አይደለም። አድርባይነትና ሥጋዊ ፍርሃትን ከጥበብ ባንቆጥረው መልካም ነው። እከብር ባይ ልቡናን ካልጣልነው ለእውነት መኖር አንችልም። እና አንዳንድ መምህራን ፈሪነታችሁን በዝምታ ውጣችሁ ከጥበብ አትቁጠሩት።

የኬልቄዶን ጉባዔ መለካዊ ይባላል። መለካዊ ማለት ፈጻሜ ፈቃደ ንጉሥ ማለት ነው። ከእግዚአብሔር እውነት ይልቅ ሥጋዊ ፍርሃትን ፈርቶ ለንጉሥ ፈቃድ መገዛት መለካዊነት ይባላል። የሊቃውንት ጉባዔ ያስቀመጠውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምትመራበትን ሕግና ቀኖና ትተህ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባስቀመጡልን ስምምነት መሠረት ብለህ ውግዘት ከፈታህ መለካዊ ነህ። ኢትዮጵያ ሊቃውንት፣ ካህናት፣ ደጋግ ምእመናን እስካሏት ድረስ ምንም አትሆንም። ሲጀምር እስካሁንም ያለችው በሊቃውንቱ በካህናቱ በምእመናኑ ጥረት ነው። ወደፊትም እንዲሁ ትኖራለች።

ወሊድን በተመለከተ

ልጅን መውለድ ብዙ ተባዙ ያለውን አምላካዊ ቃል መፈጸም ስለሆነ ትልቅ ክብር ነው። ወላድ እናቶቻችንም ክቡራት ናቸው። ባለማወቅ (ላለዝበው ብየ ነው እንጂ በድንቁርና ልል ነበር) የወለደች ሴት እስላም ናት፣ ርኩስ ናት የሚሉ ሰዎች ከእውቀት ጋር የተጣሉ ሰዎች ናቸው። ወንድ ከወለደች በኋላ ለ40 ቀን ቤተ ክርስቲያን አትገባም። የማትገባበት ምክንያት ግን እስከዚያ ድረስ ደም ስለሚፈሳት ነው። ደም የሚፈሰው ሰው ደግሞ ቤተክርስቲያን አይገባም። ይህ ለወላድ ሴት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ወንዱም ቢሆን እንቅፋት መትቶት አካሉ ቢደማ ቤተ ክርስቲያን አይገባም። አፍንጫው ቢነስር ብቻ ከመድማት ወገን በአንዱ ቢደማ ቤተ ክርስቲያን አይገባም። ርስሐት (ዝንየት) ካገኘውም 24 ሰዓት ጠብቆ ይገባል እንጂ ከዚያ በፊት እንዲገባ ሥርዐት አልተሠራም። ሴት ልጅ የወለደች እናትም እስከ 80 ቀን ቤተ ክርስቲያን አትገባም። ይኽውም ደም ስለሚፈሳት ነው። በወር አበባ ያለች ሴትም ቤተ ክርስቲያን አትገባም ይኽም ደም ስለሚፈሳት ነው። ቤተ ክርስቲያን መፍሰስ ያለበት የክርስቶስ ደም ብቻ ነው። የፍጡር ደም መፍሰስ የለበትም። ይህ ሥርዐት የተሠራውም ለቤተ ክርስቲያን ክብር ተብሎ እንጂ የወር አበባ፣ በወሊድ ጊዜ የሚፈሰው ደም ርኩሰት ሆኖ አይደለም። ክቡራት ወላድ እናቶቻችንን እንደ

ርኵስ ማሰብ የርኵስ ሰዎች እሳቤ ነው። እናቶችን ልጅ ስለወለዱ እናከብራቸዋለን እንጂ ርኵስ ናቸው አንልም። የወለዱ እናቶችን በወለዱ ቀን በሌላ ቀንም ሄዶ "እንኳን ማርያም ማረችሽ" ማለት የክርስቲያን ሥራ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከመግባትና፣ ሥጋውን ደሙን ከመቀበል አይከለክልም። ፍትሐ ነገሥት አንቀጸ ቀሳውስት ላይ ቁጥር ፪፻፴፯ (237) ላይ፣ በደስ ፰ (8)፣ አቡሊዲስ በጻፈው መጽሐፍ በስምንተኛው አንቀጽ ቂስ ሚስቱ ብትወልድ ከአገልግሎት አይከልከል ይላል። ቀሲስ ሶበ ወለደት ብእሲቱ ኢይትከላእ እንዲል። አንዳንድ ቦታ ላይ ገጠር የወለደችን ሴት በአሥረኛው ቀን ጸበል የሚረጩ ቄሶች አሉ። ጸበል በረከት ያለው ስለሆነ መረጨቷ ጉዳት የለውም። ነገር ግን ርኵሰቷን ስለሚያስለቅቅ ተብሎ ከሆነ የሚረጨው ነውር ነው። መጀመሪያም ልጅ በመውለዷ ርኵስት አልሆነችምና። ይሄ ከትምህርቷ ገፋ ያለማድረግ ችግር ነው። ጸበል ተረጨችም አልተረጨችም ምንም ዓይነት ነውር የለባትም። ያ ብቻ ሳይሆን በማየ ገቦ (ሕጻኑ በተጠመቀበት ማይ) እናቲቱንና ክርስትና የሚያነሱ ሰዎችን መርጨት ትልቅ ውንብድና ነው። ማየ ገቦ ልጅነት የሚያሰጥ ስለሆነ ሕጻኑ ብቻ ይጠመቅበታል እንጂ ለሌላ ሰው አይረጭም። ስለ አዋላጆች (መወልዳት) በፍትሐ ነገሥት ተነግሯል። ይኸውም ሴት ያዋለዱ አዋላጆች እስከ ፴ ቀን ቤተክርስቲያን እንዳይገቡ፣ ወንድ ያዋለዱ አዋላጆች ደግሞ እስከ ፵ ቀን እንዳይገቡ ሥርዓት ተሠርቷል። በዘመናችን ደግሞ አዋላጅ ነርሶች (Midwives) አሉ። ሥራቸው ማዋለድ ነው። ለእነርሱ ዘለዓለም ቤተክርስቲያን አይግቡ የሚል ትምህርት የለንም። ሥርዓቱ ሲሠራ በነበረው ዘመን የነበሩ አዋላጆች እና አሁን ያሉ አዋላጆች ሚናቸው የተለያየ ስለሆነ ለአሁን ዘመን አዋላጆች የሚመጥን ሥርዓት እንዲሠራልን በዚሁ አጋጣሚ ለቅዱስ ሲኖዶስ የምናሳስበው ይሆናል ማለት ነው። ምክንያቱም የአሁን አዋላጆች ያለምንም ደም ንክኪ ሊያዋልዱ የሚችሉበት መንገድ ስለሚኖርና ጥንቃቄያቸው ከቀድሞው ከፍ ያለ ስለሆነ ነው። ሕክምናን በተመለከተ የቀዶ ሕክምና ሐኪሞችን ሁሉ ያካተተ ሥርዓት ቢሠራ መልካም ነው።

ማኅበራዊ ሚዲያ ያስተማረኝ

፩) ጠንካራ ሰዎች ትችትን፣ መሰደብን እንደማይፈሩ እንዲያውም የበለጠ እንደሚያጠነክራቸው አይቻለሁ። ስለሌላው ሰው ሲናገሩም ለሥነ ልቡናው ተጠንቅቀው ቀጥታ ሰውየውን ከመናገር ይልቅ ግብሩን ይኮንኑታል። ይጠነቀቁለታል። የሰው ልጅ መልካም ነገሩን እንዲቀጥልበት ባላቸው አቅም ሁሉ ይተባበሩታል። እንዲህ ዓይነት ሰዎች በጣም የታደሉ ናቸው። ሁላችንም እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ብንሆን በነፍስም በሥጋም የምንጠቀም ይመስለኛል። ጠንካራ ሰዎች ለሰው ልጅ ጠንካራ ፍቅር አላቸው። ንግግራቸው ፍቅርን መሠረት ያደረገ ነው። እግዚአብሔርን እንደሚወዱት የምታውቀው ሰውንም በመውደዳቸው ነው። ለሰው ጥላቻ የላቸውም። ክፉ ሰውን እንዴት ወደ መልካምነት እንደሚመልሱት ነው ጭንቀታቸው። መልካም ሰውን ደግሞ በመልካምነት እንዲጸና ባላቸው አቅም ሁሉ ይተባበሩታል። ጥፋታቸውን ለማረም ደስተኞች ናቸው። ለጥፋታቸው ምክንያት አይደረድሩም። በአደባባይ ይቅርታ ይጠይቃሉ እንጂ። በሰው ጭብጨባ አልቆሙም። በእውቀትና በእውነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

፪) ደከም ያልን ሰዎች ደግሞ ትችትን፣ መሰደብን እንደምንሰቀቅ አስተውያለሁ። የሚያሰድበን፣ የሚያስተቸን መልካም ያልሆነ ሥራችን መሆኑን መገንዘብና ማስተካከል ሲገባን ለተቸንና

ለሰደበን ሰው አጻፋ ለመመለስ እንሞክራለን። ግን ስሕተት እንደሆነ ይሰማኛል። እንዲያውም መልካም ባልሆነ ሥራችን ምክንያት የተቸንንና የሰደበንን ሰው በጣም ልንወደው ይገባል። መልካም እንድንሆንለት ፈልጎ ነው። ለእኛ በጣም ትልቁ ጉዳት ስናጠፋም ጥፋታችንን ዝም ከተባልን ነው። በትርጓሜያችን ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል የሚለውን ስንተረጉም ወደ ቀኝማ ምን ችግር አለውና ነው ቢሉ ግራን ሲያይ ነው ካለ በኋላ አንድም ቀኝ (መልካም) መስሎ የሚሰራ ግራ (ክፉ ሥራ) አለና ይላል። እኛ ያደረግነው መልካም ሊመስለን ቢችልም በዓይናማዎቹ ሊቃውንት ሲታይ ስሕተት ሊገኝበት ይችላል። ስለዚህ ስሕተታችን ሲነገረን በደስታ መታረምን እንውደደው። ያልሆንነውን እንደሆንን አድርገው የሚያወሩ ስም አጥፊዎች ካሉ ደግሞ ለእኛ በረከት ስለሆነ በዝምታ በትዕግሥት ማለፍ ነው። በሌሎች ላይ አሉታዊ ተጽእኖን የሚፈጥር ከሆነ ግን እውነታውን መግለጥ ይገባል።

፫) ብዙዎቻችን ስሜታችንን የሚደግፍ ጽሑፍና ንግግር ስናይ እንደምንደሰት አይቻለሁ። ነገር ግን አሁን ሳስበው ስሜታችን ሁል ጊዜ ትክክል ላይሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ከስሜታችን በላይ ሆነን ነገሮችን በእውነት ሚዛንነት ብንለካቸው እንጠቀማለን። ነገሮችን በንስር ዓይን ብናያቸው እላለሁ። ነገሮችን መለካት ያለብን ከራሳችን ጥቅምና ጉዳት አንጻር ብቻ ሳይሆን በሌላ ሰው ላይ ያላቸውን ተጽእኖም ብናስተውል መልካም ነው። በእኛ ሊደረግብን የማንፈልገውን በሌላ ልናደርግ አይገባንም። ለእኛ ሊደረግልን የምንፈልገውን ለሌላውም እንዲደረግለት እንመኝ። ቂም፣ በቀል፣ ጥላቻ እና ሌሎችም የሰይጣን ግብሮችን እንጣላቸውና በምትኩ ሕይወት የሚሆኑንን መልካም ሥራዎችን እንሥራ።

፬) እንተቻለን፣ እናርማለን፣ ሒስ እንሰጣለን ብለን የምናስብ ሰዎችም እኔን ጨምሮ ብዙ ነገር እንደሚጎድለን ተረድቻለሁ። ጠቢብ ሐኪም በሽተኛን ሲፈውስ ብዙ ነገሮችን ታግሦ እያባበለ ነው። ጠቢብ ካህንም ኃጥኣንን ሲያስተምር ቀስ ብሎ ነው። የእኛ ትችት አሰጣጥ ግን በሽተኛውን የበለጠ የሚያቆስል እንጂ የሚፈውስ ሆኖ አላገኘሁትም። በርኅራኄ የሚሰጥ መድኃኒት አልሆነም። የአንድን ሰው ጉድለት በርኅራኄ ማሳየትን አልቻልንበትም። በእውነትና በፍቅር ማከም አልቻልንበትም። ጉዳይ ተኮር መሆኑ ቀርቶ ባለጉዳዩ ላይ ያነጻጽራል። ኃጢአቱን ከመጥላት ይልቅ ኃጢአተኛውን ወደ መጥላት ያነጻጽራል። ይህንን ብናርም መልካም ይመስለኛል።

፭) አንዳንዱ ሰው አይሳሳትም ብሎ በሕሊናው የያዘው የሆነ መምህር አለ። ያ ሰው ተሳስቶ ስሕተቱን ስትገልጥበት የሚጠላህ ሰው አለ። ያ ብቻ ሳይሆን ለስሕተቱ ሽፋን ፍለጋ የሚኳትን አሳዛኝ ሰውም አለ። ሰው ይሳሳታል። ሌሎች ስሕተቱን አይተው ሲተቹት ብታይ ለሰውየው ተከላካይ ሆነህ ከምትገባ ይልቅ ዝም በል። ሰው ማምለክ ጥሩ አይደለም። ሰውን በጥፋቱ እንዲቀጥል ባትተባበሩት መልካም ነው። ማንኛውም ሰው ሊሳሳት ይችላል። ሲሳሳቱ መተራረም ጥሩ ነው። ስሕተቱን እያዩ ዝም እያሉ መልካም የሠራ ሲመስለን ብናሞጋግሠው ግን እየጎዳነው ነው። ስሕተት ብቻ እየፈለጉ መተቸትም ጥሩ አይደለም። ምቀኝነት ይሆናል። መልካም ሲሠሩ ማበረታታትንም እንልመድ። የመምህሮቻችንን ጽሑፍ እያየን እንማር። እንዲያ ከሆነ የአመለካከት ለውጥ እናመጣለን። በነገራችን ላይ ማንንም ሰው ብሎክ አላደርግም። ምክንያቱም ብሎክ ማድረግ የሕሊና ማፈግፈግ ነው። ማንኛውም ሰው የፈለገውን

አስተያየት ይስጥ። እውነት ከሆነ ሰው ይማርበታል። ውሸት ከሆነ ራሱ ይጎዳበታል። የአስተያየት መስጫውንም አላጠፋውም። አስተያየት የሚፈራ ሰው ባይናገር ባይጽፍ ይመረጣል። አንፍሬንድ ላደርግ ግን እችላለሁ። [ለምሳሌ ከአንተ ጽሑፍ ጉዳትን እንጂ ጥቅምን አላገኘሁም የሚለኝ ሰው ካለ ሁለተኛ እንዲጎዳብኝ ስለማልፈልግ አንፍሬንድ አደርገዋለሁ_____በሌላም ምክንያት]። ብሎክ ግን በፍጹም አላደርግም። አንድ ሰው ራሱን መከላከል በማይችልበት ሁኔታ ስለእርሱ ብጽፍ ብናገር የእኔን ትንሽነት ከመግለጥ ውጭ ፋይዳ የለውምና። ከማኅበራዊ ሚዲያ መልካሙን እንውሰድ ክፉውን እንተው።

ፍርድ

ክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል "በዚህ ምድር ለሁሉም ሰው እንደየሥራው የሚፈረድበት ከሆነማ በዳግም ምጽአት ክርስቶስ ምን ሊያደርግ ይመጣል?" ይላሉ።ብዙዎቻችን ክፉ ሰው በዚህ ምድር ቅጣቱን እንዲያገኝ እንፈልግ ይሆናል። ውድቀቱን ማየት እንመኛለን። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው በዚህ ምድር እንደየሥራው አይቀጣውም። የሚቀጣቸው አንዳንድ ሰዎች ካሉም ለሌላው ትምህርት ይሆኑ ዘንድ ነው። ዋና ክፉ ሰው በዚህ ምድር የተመቻቸ ኑሮን ሊኖር ይችላል። ደግ ሰው ደግሞ በዚህ ምድር የመከራ ኑሮን ሊኖር ይችላል። ምክንያቱም በዚህ ምድር የመጨረሻ ፍርድ አይሰጥም። ክፉ ሰው እንደ ክፋቱ፣ ደግ ሰው ደግሞ የመልካምነት ዋጋውን የሚያገኘው በዳግም ምጽአት ጊዜ ነው። ያን ጊዜ የእውነት ጻድቃንንና የእውነት ኃጥአንን እንለያቸዋለን። በዚህ ምድር ዋናው ሌባ መጽዋች መስሎ ሊኖር ይችላል። ደጉ እንደ ክፉ ታይቶ ሊኖር ይችላል። በዚህ ምድር ወንጀለኛ ተመቻችቶ እየኖረ የተበደለው ሰው ግን ታስሮ ሊኖር ይችላል። ምክንያቱም ትክክለኛ ፍርድ የለም። በዳግም ምጽአት ግን ልብን የሚመረምር እግዚአብሔር በትክክል ይፈርዳል። እውነተኞች እውነታቸው በአዳም ልጅ ሁሉ ፊት ተገልጦ ደስ ይላቸዋል። ኃጥአን ክፋታቸው በአዳም ልጆች ሁሉ ፊት ተገልጦ ሲታይ ያፍራሉ። ዘለዓለማዊ ውርደትን ይጎናጸፋሉ። ሙሉ ፍርድ ያለ በዳግም ምጽአት ስለሆነ ክፉ ሰዎች በዚህ ምድር የተመቻቸ ኑሮ ሲኖሩ ብታይ አትደንግጥ። ፍርዳቸው በሰማይ ዘንድ ሊበዛባቸው ነውና። ጻድቃን በዚህ ምድር መከራ ሲበዛባቸው ስታይ አትጠራጠር። በሰማይ ክብራቸው ይበዛ ዘንድ ነውና። ለሁሉም በዚህ ምድር ፍርድ የሚሰጥ ቢሆን ኖሮማ ዳግመኛ ምን ሊያደርግ ይመጣል ማለታቸው ለዚያ ነው።ደጋግ ሰዎች ብቻ የሚኖሩባት ደግ ዓለም መንግሥተ ሰማያት ናት። በዚያ ደግ ንጉሥ ክርስቶስ ነግሦልን ይኖራል። ከዚያች ለመግባት ኑ መልካም ሥራን አብዝተን እንሥራ። በትክክል የምትፈርድ አባታችን ሆይ በቸርነትህ ብዛት በቀኝህ ከሚቆሙት ጎን ከሚቆሙት አድርገን።

ዘኢየኀልቅ ልደቱ

በወቅታዊ ጉዳይ ተወጥረን ደገኛውን ምሥጢር ምሥጢረ ሥላሴን እንዳንረሳው። ወልድ ከአብ የሚወለደውን ልደት "ልደት ዘኢየኀልቅ" ብሎ ገልጾታል። ይህ ማለት ግን አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ሁልጊዜ ሲወለድ ይኖራል ማለት አይደለም። ወልድ ወልድ ሲባል ይኖራል ማለት ነው እንጂ። ሥጋዊ እሳቤ በሃይማኖት አስተምህሮ ውስጥ እንዳይገባ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። አንዳንዶችን ሁልጊዜ ሲወለድ ይኖራል ለማለት ያደረሳቸው ሁልጊዜ የማይወለድ ከሆነ ሲወለድ

መነሻ አለው ያሰኛል የሚል ሥጋዊና ደማዊ አስተሳሰባቸው ነው። የወልድ ከአብ መወለድና የመንፈስቅዱስ ከአብ መሥረጽ ከጎሊና በላይ መሆኑን ቅዱሳን ሊቃውንት አባቶቻችንም ልደተ ወልድ ወፀአተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ይትነከር ወኢይትነገር ብለው ገልጸዋል። ከሰው ምርምር በላይ ነው። ኢየኑልቅ ልደቱ በሚልበት ጊዜ ልደት የሚለው ሳቢ ዘር መውለድ መወለድ ተብሎ አይተረጎምም። የወለደን ምሥጢር ባልለቀቀ የአማርኛ ስም ይተረጎማል እንጂ። ይኽውም ልደት ብሎ ልጅነት ተብሎ ይተረጎማል። በዚህ ጊዜ የልደት ትርጓሜ ከወልድና ጋር ይገጥማል። ስለዚህ ዘኢየኑልቅ ልደቱ___ልጅነቱ አያልቅም ማለትም ወልድ ወልድ ሲባል ይኖራል ተብሎ ይተረጎማል። ሃይማኖተ አበውን የተረጎሙ ሊቃውንትም የተረጎሙት እንዲህ ብለው ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትም ቀዳማዊ ልደት ተአውቀ በደኃራዊ ልደት ወልድ ከአብ የተወለደው ቀዳማዊ ልደት ወልድ ከድንግል ማርያም በተወለደው ደኃራዊ ልደት ታወቀ እያሉ ጻፉ እንጂ ልደት ዘለዓለም ተአውቀ በደኃራዊ ልደት አላሉም። ሳዊሮስ የፀሐይ ብርሃን ከክበበ ፀሐይ ሳያቋርጥ እንደሚወጣ ሁሉ የወልድ ከአብ መወለድም እንዲሁ ነው ብሏል። ይህም ብርሃን ከክበብ ሲወጣ ተመትሮ ተፈልጦ የለበትም። ወልድም ከአብ ሲወለድ ተፈልጦ ተመትሮ የለበትም። ይህንን ለማስረዳት ሊቁ የጠቀሰው ነው። ተመትሮ ተፈልጦ ማለትም መለየት ማለት ነው። ለምሳሌ እናት ልጇን ስትወልድ፣ በእርሷ ማኅፀን ኖሮ ሲወለድ ከማኅፀን አፍአ ይሆናል። ከእርሷ በህልውናም ተለይቶ ብቻውን ህልው ይሆናል። ወልድ ከአብ ሲወለድ ግን ከህልውና ሳይለይ ነው። አነ በአብ ወአብ ብየ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ አለ ብሎ ራሱ ክርስቶስ እንዳስተማረን። ለሰው ልጅ ከሁሉ አስቀድሞ ስለ ሥላሴ ማወቅ ይገባዋል። መቅድመ ኩሉ ንሰብክ ሥላሴ ዕሩየ ወቅዱሰ ዘውእቶሙ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዳለ ሊቁ። ይቆየን።

አንቂ ሆይ

_____1ኛ) ቅድሚያ ራስህ ንቃ፣ ራስህ ዳን

_____2ኛ) ሌሎችን አንቃ፣ ሌሎችን አድን

የሁላችንም ኃላፊ እግዚአብሔር እስካለ ድረስ በምንም ነገር ተስፋ አንቆርጥም። በዚህ ምድር ተስፋ አስቆራጭ የሚባል ነገር የለም። እስከ መጨረሻው እውነትን ይዞ መኖር ይገባል። አንድን ክፉ ሰው ከክፋቱ ለማስለቀቅ መስደብ መፍትሄ አይሆንም። ከሰደብነው ግን በክፋት ላይ ክፋትን እየጨመረ ይሄዳል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ የምንፈልገውን ሰላማዊ ሕይወት ማግኘት አንችልም። ጻድቃን ክፉ ሰውን አለዝበው መልካም ለማድረግ ይጥራሉ። ኃጥኣን ግን ክፉ ሰውን ተሳድበው የበለጠ ማበሳጨታቸውን እንደ ድል ይቆጥሩታል። ስኬታቸውን የሚለኩት ክፉ ሰዎችን በማበሳጨታቸውና በማሳዘናቸው ልክ ነው። ጻድቃን ግን ስኬታቸውን የሚለኩት ክፉ ሰዎችን በፍቅር ወደ ትክክለኛው መስመር ባመጡበት ልክ ነው። አክቲቪስቶቻችን፣ ፖለቲከኞቻችን፣ መምህራኖቻችን፣ ታላላቆቻችን መሰዳደባቸውን ተውትና በእውነትና በፍቅር ላይ እንዲሁም በጠንካራ አመክንዮ የተመሠረተ ነገር ተናገሩ፣ ጻፉ። የሰውን ክብር በጠበቀ መልኩ ሥሩ። ሰው የእግዚአብሔር አምሳል የሆነ ክቡር ፍጥረት ነው። ስለዚህ ማክበርና መውደድ ካቃተንኳ ማዋረድ መሳደብ አይገባም። ይህንን የምለው ሁላችንም ችግር ፈቺነትን ከራሳችን እንድንጀምር

ነው። የራሳችንን ግላዊ ችግር ስንፈታ ጎብረተሰብኣዊው ችግር ይፈታል። የእኛን ድርሻ ከተወጣን ሌላውም የየራሱን ድርሻ ይወጣል። የተቸገርነው እንዲህ አልሆን ስላለ ነው። አንዳንዱ ሰው ራሱ በኃጢአት ተዘፍቆ እየኖረ ሌሎችን ጻድቃን ለማድረግ ይጥራል። ወንድማለሞቹ እህታለሞቹ መጀመሪያ ራሳችንን እናንቃ፣ ራሳችንን እናድን። ሰው የሚለካው መጀመሪያ በራሱ ግላዊ ሕይወት ነው። ከዚያ ቀጥሎ በጎብረት ውስጥ ባለው አስተዋጽኦ ነው። በግላዊ ሕይወቱ ጠንካራ ሆኖ በጎብረተሰብኣዊው ሕይወቱ ምንም አስተዋጽኦ የሌለው ሰው ራሱ ብቻ እንዲደነቅና እንዲመለክ የሚፈልግ አሳዛኝ ሰው ነው። በጎብረተሰብኣዊው ሕይወቱ የተመሰገነ ሆኖ በግላዊ ሕይወቱ ደካማ የሆነ ሰውም አስመሳይ ሰው ነው። ስለዚህ እንዲህ እንዳይሆን "ሰው መጀመሪያ ራሱን ከክፋት ያድን፣ በመቀጠል ሌሎችን ከክፋት ያድን" ከዚህ በኋላ ሀገር ሰላም ትሆናለች። ሁላችንም የአንድ አዳም ልጆች ነን። የክፋት ተሸካሚ ሆነን ጽድቅን ባንገፋት መልካም ነው። አለበለዚያ ግን የምንጎዳው ራሳችንን ነው። ሰው ክፉ በሆነ መጠን በዋናነት የሚጎዳው ራሱን ነው። እውነትን በፍቅር መግለጥ ይገባናል። በክፋት የኖርንበት ያለፈው ዘመን ይበቃናል። ላለፈው በደል ይቅርታን እንጠይቅ። ለጥፋታችን ከልብ ይቅርታ እያልን እንኑር። ጽሑፋችን ንግግራችን ማንኛውንም የሰው ልጅ ክብር የሚነካ መሆን የለበትም። ኃጢኣትን ከኃጢኣተኛው እንለይ። ልንጠላው የሚገባን ኃጢኣትን ነው እንጂ ኃጢኣተኛን አይደለም። ለእውነት የቆምን ደፋርና ጀግኖች መሆን ይጠበቅብናል። ኃጢኣትን እስከ ሞት ልንታገለው ይገባናል። ኃጢኣትን አሜን ብሎ ተቀብሎ ከመኖር እምቢ ብሎ መሞት ይገባል። ሰውን አትግደሉ፣ አትዋሹ፣ አትስረቁ ወዘተ እያልን እናስተምራለን። እኒህን ነገሮች ማድረግ በሌላው ሰው ላይ የነፍስ ጉዳት ስለሚያመጡ ነው። መገዳደልን የምንኮንነው መሞትን ፈርተን አይደለም። የማይቀርልንን ሞት ለምን እንፈራዋለን!? አንፈራውም። ነገር ግን አንድ ሰው ዘመዱ ሲገደልበት ቂም ይይዛል እስከ መግደልም ይደርሳል። ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያጣላውና የነፍስ ሞትን የሚያስከትልበት ነው። ክፋት እንዳትነግሥ ጽድቅን ማብዛት አለብን።

አፄ ምኒልክ

ኢትዮጵያውያንን በአንድነት አስተሳስሮ ቅኝ ገዢዎችን ገጥሞ ያሸነፈ፣ ለአፍሪካውያን የነጻነት ተምሳሌት የሆነ ንጉሥ አፄ ምኒልክ ነው። ለኢትዮጵያ ልጆቿ በአንድነት ሆነው የውጭ ጠላትን መክተውላታል። ከንጉሡ እስከ ሕዝቡ፣ ከጦር መሪዎች እስከ ሠራዊቱ በመናበብ ያመጡት ድል ነው የአድዋ ድል በዓል። የሰው ልጅ ክቡር ነው። በነጻነት እንዲኖር ተፈጥሯል። ይህንን ነጻነቱን ማንም ሊወስድበት አይገባም። ጀግንነት ለእውነት ለነጻነት መሞት ነው። የአድዋ በዓል የኢትዮጵያውያን በዓል ነው። ምክንያቱም ጦርነቱን ያሸነፉት ኢትዮጵያውያን ናቸው። የጦር መሪዎቹ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የመጡ ናቸው። ሠራዊቱ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የመጣ ነው። ሕዝቡ፣ መሪው፣ የሃይማኖት አባቶች አንድ ቢሆኑ ለድል በቅተዋል።አንድ እንሁን።

እረ በቅጡ ንገረኝ!!!

አንድ ጊዜ ራስ ዓሊና ራስ ውቤ እርስ በእርስ ጦርነት ይገጥማሉ። እና በጦርነቱ ራስ ውቤ

የራሲ ዓሊ ወታደሮች የእርሱን ወታደሮች ሲያጠቋቸው ያያል። ራስ ዓሊም የእርሱን ወታደሮች የራስ ውቤ ወታደሮች ሲያጠቋቸው ያያል። ይህንን ያይና ራስ ዓሊ ሸሽቶ ጦርነቱ ሳያልቅ ወደ ሌላ ሀገር ይሄዳል። ጦርነቱ ገፍቶ የራስ ዓሊ ወታደሮች ራስ ውቤን ማርከው ወደራስ ዓሊ ቤተ መንግሥት ይወስዱታል። በቤተ መንግሥት ግን አልነበረም። እና የራስ ዓሊን መሸሸና የራስ ውቤን መማረክ የሰማውን ባላገር ሌላኛው ባላገር ጦርነቱ እንዴት ሆነ ይለዋል? ከዚያ ሲመልስለት ራስ ዓሊም ሸሹ፣ ራስ ውቤም ተማረኩ ይለዋል። ይህን ጊዜ ባላገሩ "እረ አንተ ሰው በቅጡ ንገረኝ" ይለዋል። ያኛው ባላገርም ሲመልስለት "እነርሱ በቅጡ ያልሆኑትን እኔ እንዴት አድርጌ በቅጡ ልንገርህ" አለው ይባላል። በቅጡ ሁኑልን እንጂ።

ሐሰተኛ ጳጳሳት

ውሸትን በመደጋገም እውነት ማድረግ አይቻልም። እነ አቶ አካለ ወልድና እነ አራርሳ 3 ኤጲስ ቆጶሳት ኤጲስ ቆጶሳትን መሾም ይችላሉ ስለዚህ ያፈረስነው ቀኖና የለም ብለው ተሳስተው ሰሚውን ሕዝብም ሊያሳስቱ ይሞክራሉ። በጥዑም አንደበት ብዑዕ አባታችን አቡነ ኤርምያስ የቀኖና ጥሰቱን አንቀጽ ጠቅሰው ሐሰታቸውን ገልጠውባቸዋል። ፍትሐ ነገሥቱ የሦስቱን ሰዎች ሕገ ወጥ ሹመት አይደግፍም። ሦስት ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ የሚፈቀደው ፓትርያርኩ እና ቅዱስ ሲኖዶስ ሲፈቅድ ነው። ፓትርያርኩ ሳይፈቅዱ የሾሙ ሰዎችም የተሾሙትም ይወገዙ ተብሏል። ይህችኛዋን ክፍል እየዘለሉ ማለፍ ትልቅ ነውር ነው። በዚህ ዙሪያ ፍትሐ ነገሥቱ ምን ይላል የሚለውን ከዚህ ቀደም የጻፍኩትን ጽሑፍ ከዚህ ላይ በድጋሚ አቀርበዋለሁ። ለብዑዕ አቡነ ኤርምያስ ረጅም እድሜን ይስጥልን።

አንድነት

የሆነው ሆኖ እኛ ምእመናን ክርስቶሳዊ አንድነታችንን እናጠንክር። የፖለቲካው እርሾ ከክርስቶሳዊ አንድነታችን አውርዶ በሰፈር በጎጥ በክልል እንድናስብ ሊያደርገን አይገባም። የክርስቲያኖች አንድነት በዓለም ላይ ካሉ አንድነቶች ሁሉ ትልቁ አንድነት ነው። ምክንያቱም የአንድነቱ የመሠረት ድንጋይ ክርስቶስ ነውና። ቀኖናዊ ጉዳዮች ቢጣሱ በዋናነት የጣሰው አካል ይጠየቅበታል። በዚህ ምድር እኛ ባንጠይቀው በመንፈስ ቅዱስ ረቂቅ አሰራር ይጠየቃል። ማንም ቢሆን ለሠራው ሥራ ይጠየቅበታል። ስለዚህ ቀኖናን የጣሱ አካላት ራሳቸው ይጠየቁበት። ከእኛ የሚጠበቀው ማሳወቅ ነው። የእኛን ድርሻ ከተወጣን። ሌላውም በራሱ ድርሻ ይጠየቅበት። እኛ አንድነታችንን አሰራራችንን ወደማጠንከሩ እንሂድ። መንፈሳዊ ሕይወታችንን ከፍ እናድርግ። እንጹም እንጸልይ። ቂምን ጥላቻን እንተው። ባጠፉት ሰዎች ላይም ፍርድን ለእግዚአብሔር እንስጥ። ሰው ተንኮለኛ ቢሆን የሚጎዳው በዋናነት ራሱ ነው። የቅድስት ቤተክርስቲያን ትግል እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ይቀጥላል። ትግሏ የማያቋርጥ ነው። ሰይጣንም ዘመኑ እንዳለቀበት እያሰበ ፈተናውን እጅግ እያጠነከረ እና እያወሳሰበ ይመጣል እንጂ ዝም አይልም። በዚህ ጊዜ ምእመናን፣ ካህናት፣ ሊቃውንት፣ ጳጳሳት ፈተናውን በድል ለመወጣት ልዩ ክርስቲያናዊ ጥበብ ያስፈልገናል። ትግላችን የ7515 ዓመት ሰውን በኃጢአት የመጣል ልምድ ካላቸው ረቂቃን ርኩሳን መናፍስት ጋር ነው። ከእኛ ያሉት ደግሞ ሰይጣንን በቅድስናቸው በረድኤተ እግዚአብሔር ያሸነፉ ቅዱሳን መለእክት፣ ቅዱሳን ሰማእታት፣ ሁሉም ቅዱሳን ናቸው። ከምንም

በላይ የትግላችን መሪ ራሱ ክርስቶስ ነው። እና ሰይጣንን ለማሸነፍ የሚያስፈልጉን ነገሮች አሉ።

- ፩) እውነትን መያዝ
- ፪) ትሕትና
- ፫) ለበደልነው ንሥሓ መግባት
- ፬) ይቅርታ
- ፭) ፍቅረ እግዚአብሔር ወፍቅረ ሰብእ
- ፮) ኅብረታዊ መሆን
- ፯) እከብር ባይ ልቡናን መጣል
- ፰) ዘለዓለማዊነትን ማሰብ
- ፱) ረድኤተ እግዚአብሔርን መጠየቅ
- ፲) ክርስቲያናዊ ምግባራትን ሁሉ መፈጸም

ናቸው። ብንኖርም ለእግዚአብሔር እንኖራለን። ብንሞትም ለእግዚአብሔር እንሞታለን እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ። ኑሯችን ዘለዓለማዊነትን ማዕከል ያደረገ ሊሆን ይገባል። ሰይጣን በሰዎች አድሮ ሲፈትነን በጥበብ እናሸንፈው።

ሐሰተኛ ጳጳሳት

፩) ውሸትን በመደጋገም እውነት ማድረግ አይቻልም። የተወገዙት ሰዎች በፍትሐ ነገሥት የተቀመጠውን የቤተክርስቲያኒቱን ቀኖና ስለሻሩ ነው። ፓትርያርኩ ሳይፈቅዱ ጳጳሳትን በመሾማቸው ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ በግልጽ የሾመውም የተሾመውም ይወገዙ ተብሏል። ተወጋገዮቹ የተወገዙት በዚህ የመንፈስቅዱስ ቀኖና መሠረት ነው እንጂ በቋንቋችን ካላስተማርን በሚል አይደለም። በቋንቋ ማስተማር የቤተ ክርስቲያን ዋና ተልዕኮዋ ነውና።

፪) እነ አቶ አካለ ወልድ እና እነ አቶ አራርሳ ራሱኮ ቀድሞ ተሹመው የነበረው በቋንቋቸው እንዲያስተምሩ ነበር። የራሳቸውን ያለማስተማር ችግር በሌላ ማላከክ ነውር ነው። አሁንም በኦሮምኛ የሚሰብኩ፣ የሚቀድሱ፣ የሚያስተምሩ ድንቅ ድንቅ አባቶች በቅዱስ ሲኖዶሳችን አሉ። እነ አቡነ ናትናኤልን መስማት ትችላላችሁ። ስለዚህ በቋንቋ ማስተማርን ቤተ ክርስቲያን ትደግፋለች። እየሠራችበትም ትገኛለች። ስለዚህ ሕገ ወጦች እንደሚሉት በቋንቋ አትገልገሉ አላለችም። ውሸትን ደጋግሞ በመናገር ከሰይጣን ለመብለጥ መሞከራችሁ ራሳችሁን ያቀላችኋል እንጂ እውነታውን አይለውጠውም።

፫) ቤተ ክርስቲያን አልተከፈለችም። በአባቶች መካከልም መለያየት የለም። 28 ሽማግሌዎች በዘረኝነት ስካር ሰክረው፣ የመንፈስ ቅዱስን ቀኖና ሽረው ሲወጡ ቤተክርስቲያን አውግዛ ለይታቸዋለች። ይህ ደግሞ የቤተክርስቲያኒቱ ውስጣዊ አሰራር ነው። ስለዚህ ይህን ችግር ቤተ ክርስቲያኒቱ መፍትሄ ሰጥታ ቋጭተዋለች። ሌላ የሚቀየር ነገር የለም። 28ቱን ሕገ ወጥ ሽማግሌዎች ሕጋዊ አስመስሎ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥም መጥራት ግልጽ ውንብድና ነው።

፬) ከተወጋገዮች ጋር በጸሎት የተሳተፈ እና የተባበረ ካለ እርሱም የተወገዘ ይሁን ተብሎ በፍትሐ ነገሥት ስለቀረበ በዚህ በደል ባለማወቅ የተሳተፋችሁ ካላችሁ ይቅርታ ጠይቃችሁ ወደ እናታችሁ ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያን ኑ። ቤተ ክርስቲያን ዘለዓለማዊት ናት። ሞትን ፈርታ፣ የመንፈስ ቅዱስን ቀኖና ትታ፣ ለመንግሥት አትገዛም። መንግሥት ሕጋዊ ከለላ ያላትን ቤተ ክርስቲያን መጠበቅ ኃላፊነቱ ነው። ይህን ካላደረገ ግን እንደ መንግሥት ልንቀበለው አንችልም። እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ልንፈራ አልተማርንም። መምህራችን ክርስቶስ ነው። እውነትን ይዞ ውሸትን ተቃውሞ መሞትን መምህራችን አስተምሮናል።

የሞትና የሕይወት ትርጉም

የማሸነፍና የመሸነፍ ትርጉም

ሰው በሕይወት አለ የሚባለው የእግዚአብሔርን ሕግና ቀኖና እየጠበቀ ሲኖር ነው። የእግዚአብሔርን ሕግና ቀኖና አፍርሶ የሥጋ ሞትን ፈርቶ ዘመን የወደደውን ብሎ የሚከተል ሰው ግን ተንቀሳቃሽ ሟች ነው። ይህ ሰው ሥጋና ነፍሱ ሲለያዩም "የሞተው ሞተ" ይባላል። የዚህ ዓለም ኑሮ በሞተ ሥጋ ይደመደማል። መሞታችሁ ላይቀር ከዘለዓለማዊው ሕይወት የሚያርቅ ሥራ አትስሩ። ዘለዓለማዊው ኑሮ መልካም ሥራን በመሥራት ተጀምሮ በትንሣኤ አሸብርቆ በማያልቅ ደስታ መኖር ነው። ለእግዚአብሔር ሕግና ቀኖና የሚኖር ሰው በሥጋ ቢሞትም ሕያው ነው። በመከራ ቢኖርም አሸናፊ ነው። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግና ቀኖና ጠብቆ ቢታሰርና መከራ ቢደርስበትም አሸናፊ ነው። ቢገደልም አሸናፊ ነው። ሁልጊዜም አሸናፊ ነው። አሸናፊነትን የተጎናጸፉት የእግዚአብሔርን ሕግና ቀኖና ከጠበቀባት ጊዜ ጀምሮ ነው። አንድ ሰው ሥጋዊ መከራንና ሞትን ፈርቶ የእግዚአብሔር ቀኖናና ሕግ ሲጣስ ዝም ካለ ግን ተሸናፊ ነው። ይህ ሰው በዚህ ምድር ቢኖርም ተሸናፊ ነው። በዚህ ምድር እየኖረ እንኳ ከሆነ ተንቀሳቃሽ ሟች ይባላል። ነፍስ ከሥጋው ሲለይም ሰይጣን ከገባበት ይገባል። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሕግና ቀኖና ጠብቀን እንሙት። ሞተን ሕያው እንሁን። መከራን ተቀብለን ደስ ይበለን። የክርስቶስን በመስቀል መሰቀል እንደ ተሸናፊነት ቆጥረው በሚስማር የሚቸነክሩት፣ የሚዘባበቱበት ነበሩ። ክርስቶስ ግን እውነት ስለሆነ እውነትን ለያዙ ሰዎች አብነት ለመሆን አሸናፊነቱን እውነትን ይዞ በመሰቀል ገለጠው። ክርስቶስ ሲሰቀልም አሸናፊ ነበር። ሲነሳም አሸናፊ ነው። የአሸናፊነት ዋና መለኪያው እውነትን ይዞ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ነው። ስለዚህ የአሸናፊ የክርስቶስ ልጆች ማንንም ሳንፈራ እውነትን ይዘን ሐሰትን እየተቃወምን እንኖራለን። እውነትን ይዘን የምንሰደበው ስድብ፣ የሚዘባበቱብን መዘባበት፣ የሚገድሉን ግድያ ዋጋ ያለው ስለሆነ ደስ ይበለን። መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ

በሄደበት ርቀት ራሱ ይፈራርሳል። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ አካልነት የተመሠረተች ስለሆነች ጎርፍ ቢጎርፍ፣ የብልጽግና መንግሥት ከሕገ ወጦች ጋር አብሮ ቢንቀሳቀስ፣ ከሃድያን ቢነሱ፣ አትነዋወጥም። ራሱ ይፈርሳል እንጂ ቤተክርስቲያን መቼም መች አትፈርስም። ራሷ ክርስቶስ ነውና። ብንሞትም የእግዚአብሔርን ሕግና ቀኖና ይዘን እንሞታለን። ብንኖርም የእግዚአብሔርን ሕግና ቀኖና ይዘን እንኖራለን።

ውግዘት

አንድ ሰው ከተወገዘ በኋላ ቁጥሩ ሌላ እምነት ካላቸው ሰዎች ጋር ነው።በሐዲስ ኪዳን ያለን እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ ከማንኛውም እምነት ተከታይ ሰዎች ጋር በፍቅር እንኖራለን። ሮሜ ፲፪፣፲፰ "ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ" ተብሎ እንደተገለጸው። በማኅበራዊ ሕይወት ከሌሎች ጋር እንደ ፈትል ተጋምደን ተከባብረን ተፋቅረን እንኖራለን። ስለዚህ ለተወገዙ ሰዎች፣ ለእስልምና ተከታዮች፣ ለካቶሊኮች፣ ለፕሮቴስታንቶች ጥላቻ የለንም። ክርስትና ፍቅር ነውና። ይህ ማለት ግን ስለምንዋደድ በአንድ ቤተክርስቲያን እንጸልይ፣ በአንድ መስጊድ እንጸልይ አንልም። አይባልምም። ከተወገዙት ሰዎች ጋር ተደራደሩ፣ ታረቁ የምትሉ ሰዎች ያልገባችሁ ነገር ይህ ነው። ክርስቲያንና ሙስሊም ተደራድረው በመስጊድና በቤተ ክርስቲያን በአንድ ላይ ይጸልዩኮ አይባልም። የተወገዘው ሰው ራሱን ችሎ ሌላ እምነት ፈጥሮ የራሱን ቸርች ከፍቶ መኖር ይችላል። የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ አካፍሉኝ ማለት ግን አይችልም። ከተወገዘው ሰው ጋር ተደራደሩና በአንድ ቤተክርስቲያን አገልግሉ ማለት ትልቅ ነውር ነው። ስለሃይማኖት ፍጹም እውቀት የሌላችሁ ሰዎች አስተያየት ነው። ሕገ ወጥ በሕጉ መሠረት ይወገዛል። ተወግዟልም። ፍት.ነገ.ሣሏ፣፲፱፭፱፮-፲፱፭፱፯ [45፣1567-1568] "እስመ መፍቅድ እምኔሁ ውስተ ሕግ ቀዳማዊ ኮነ ከመ ኢይደመሩ ሕዝበ እግዚአብሔር ምስለ አሕዛብ እለ ኢያመልክዎ ለእግዚአብሔር" በብሉይ ኪዳን ሕግ ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉ እስራኤል እግዚአብሔርን ከማያመልኩ አሕዛብ ጋር እንዳይኖሩ ይታዘዙ ነበር። ይኽውም ወደ አሕዛብ አምልኮትና ክፉ ሥራ እንዳይገቡ ነበር። ከመ ኢይትመየጡ ኀበ አምልኮቶሙ ወልማዳቲሆሙ እኪት እንዲል። ወሶበ ሰፈነ አሚን ላዕለ ኵሉ አሕዛብ- ወንጌል በአራቱ መዓዝን በተነገረ ጊዜ። ደለዎ ፈቂድ ኀበ ተጋብኦቶሙ ለመሃይምናን- ምእመናን ከአሕዛብ ጋራ አንድ ሆኖ መኖር ተገባቸው ተብሎ እንደተገለጸው ከሌላ እምነት ሰዎች ጋር በአንድ ሰፈር መኖር በሐዲስ ኪዳን ተፈቅዷል። በአንድ ቤትንኳ ሃይማኖታችንን ሳንቀይር እንደየሥርዐታችን ተከባብረን መኖር እንችላለን። ሌላ እምነት ካለቸው ሰዎች ጋር በማኅበራዊ ሕይወት በአንድ ላይ ስንኖር የማናደርጋቸውና የተከለከሉ ነገሮች ግን አሉ። እነዚያን መለየት ያስፈልጋል።

- ፩) አብሮ መጸለይ አይቻልም
- ፪) ክርስቲያኑም መስጊድ አይገባም፣ ሙስሊሙም ቤተክርስቲያን አይገባም
- ፫) የተወገዙ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን አይገቡም። ክርስቲያኖችም ወደ ፕሮቴስታንቶች ቸርች መግባት አይችሉም።

- ፬) ክርስቲያኖች ሌላ እምነት ያላቸው ሰዎች ለአምልኮ ካረዱትና ካቀረቡት ምግብ መብላት አይቻልም። ለአምልኮ ያልቀረበ ምግብ ከሆነ ግን ሳይጠራጠሩ ባርከው ቢበሉት ነውር አይደለም።

ስለዚህ ከተወገዙ ሰዎች ጋር ድርድር፣ እርቅ፣ መግባባት፣ የሚባል ትምህርት የለም። የሃይማኖታችን ሕግ አይፈቅድም። እነ አቶ አካለ ወልድ ላጠፉት ቀኖናዊ ጥሰት ምንም ማስተባበያ ማቅረብ አይችሉም። እና የሌላ እምነት ተከታዮችና ስለ ሃይማኖት ቀኖና የማታውቁ ሰዎች ጉዳዩን ቀለል አድርጋችሁ አታስቡት። የሌላ እምነት ተከታዮችም ጉዳዩን በደንብ እንድትረዱት መንግሥት እያለው ያለው ክርስቲያን እና ሙስሊም ተደራድሮ በአንድ መስጊድ (በአንድ ቤተ ክርስቲያን) ይስማሙና ይጸልዩ ነው እያለ ያለው። ይህን እንዳናደርግ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ሕግና ቀኖና ይከለክለናል። በድፍረት እንዳንደርገው ከሕጉ ባለቤት እግዚአብሔር ጋር እንጣላለንና። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳንጣላ ያለን ብቸኛው አማራጭ እንደ እግዚአብሔር ሕግና ቀኖና መኖር ነው።

ቤተ ክርስቲያን

ቤተክርስቲያን የፍቅር፣ የይቅርታ፣ የሰላም፣ የትሕትና ቤት ናት። ይህንን ወደራስ አላማ አውርዶ መተርጎም ግን ትልቅ ነውር ነው። ቤተ ክርስቲያን የትሕትና፣ የፍቅር ቤት ናት ማለት የተወገዙ ሰዎችና ሌላ እምነት ያላቸው ሰዎች አብረን እንቀድስ ሲሉ እሺ ትበል ማለት አይደለም። ትሕትናዋ እውነትን ይዞ ነው። ትሕትናዋ ፍቅሯ ይቅርታዋ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግ ተይዞ የሚገለጥ ነው። መንግሥት የሕገ ወጥ ተባባሪ ሆኖ ስናይ ጉዳዩ የመንግሥት መሆኑ ገብቶናል። ሕጋዊውንና ሕገ ወጡን ከዚያም እውነታ አለ ብሎ ውሸትንና እውነትን ጎን ለጎን አድርጎ ሊያደራድር መፈለጉ አጭበርባሪነቱን፣ ውሸቱን ለሕዝብ አጋልጦበታል። አንዳንዶች ደግሞ የጠቡ ምንጭ እኔ ያልኩት ካልሆነ ባይነት መስሏችሁ የምትናገሩ አላችሁ። መጀመሪያ በማታውቁት ጉዳይ በግምት ባትናገሩ መልካም ነው። የተወገዙት የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ጥሰው እንጂ ከግለሰቦች ጋር ተጣልተው አይደለም። ፓትርያርኩ ሳይፈቅዱ ጵጵስና መሾም በቀኖና ቤተክርስቲያን ያስወግዛል። ይህንን መሠረታዊ ቀኖና ትተው በመሾማቸው ነው ተሿሚዎችም ሿሚዎችም የተወገዙት። ሌላ ምክንያት የለም። ቤተ ክርስቲያን ጎብረታዊት ናት። እያንዳንዱ ምእመን እስከ ሞት ድረስ የቤተ ክርስቲያኑን ሕግና ቀኖና ይጠብቃልም ያስጠብቃልም። ይህንን እወቁት።

ሰማዕትነት

ሰማዕትነት ከቁጥር መቀነስ አይደለም። ሰማእትነት ወደ ታላቁ የክርስትና አንድነት መቀላቀል ነው። ሰማዕትነት መቀነስ እንዲሁም ከቁጥር ማነስ ተደርጎ የሚታሰበው በዓለማውያን ዘንድ ነው። በእኛ በክርስቲያኖች አስተምህሮ ግን ሰማዕትነት ከፍ ያለና ብዙ ቅዱሳን የሚመኙት ነው። ሰማዕትነት ኃጢአትን ያስተሰርያል። ደመ ሰማዕት አለውና። ውሸትን ሊጭንብን የሚፈልገውን የብልጽግና መንግሥት እምቢ ብሎ መሞት ጽድቅ ነው። ከውሸት ጋር ተስማምቶ ከመኖር እውነትን ይዞ መሞት የክርስትና ዋና መርሕ ነው። የሁላችን አባት ቅዱስ እግዚአብሔር መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን ይህንን ነው ያስተማረን። ልጅ አባቱን

እንደሚመስል በተግባር የምናሳይበት ትልቁ መንፈሳዊ ሥራ ሰማዕትነት ነው። ሰማዕትነት አያምልጠን። እውነትን ይዞ በሐሰተኛ ሰዎች በአደባባይ የተሰቀለው ክርስቶስ መሪያችን ነው። በሞቱ ከመሰልነው ክብሩን ያወርሰናል። የሰማዕትነት ጊዜ ስለመጣልን እንኳን ደስ አለን። እስከ መጨረሻው እውነትን ይዘን እንሙት። እውነትን ይዘን በመሞታችን ክርስቶስን በተግባር እንሰብካለን።" ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን" (ወደ ሮሜ ሰዎች 6:5) እንዲል። ቤተ ክርስቲያን እልፍ አእላፋት ሊቃውንት አሏት። ምናልባት ጭምቶች ስለሆኑ ብዙ ጊዜ ዝም ብለው ስለሚኖሩ የሌሉ መስሏችሁ ብዙዎች ቤተ ክርስቲያንን ለማጥቃት አትሞክሩ። በቤተ ክርስቲያን ከመጣህባቸው እስከ ሞት ድረስ በደስታ የሚቃወሙ ሊቃውንት እንዳሏት ልብ በል። ሊቅነታቸው ደግሞ ዝም ብሎ በተጭበረበረ ሰርተፍኬት እንዳልሆነ እወቅ። በዘመናዊው ፕሮፌሰሮች፣ ዶክተሮች ሲሆኑ በጥራት ተምረው የሆኑ ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ትምህርትም ሊቀ ማእምራን፣ ሊቀ ሊቃውንት ሲባሉ መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቀው አውቀው ነው። በዚህ ሰሞን ጳጳሳቱ፣ ሊቃውንቱ የሰጧቸው ብስል አስተያየቶች የጠቅላይ ሚኒስትሩን ጥራዝ ነጠቅነት እንዲሁም አጭበርባሪነትና ውሸታምነት ያሳወቁ አስተያየቶች ነበሩ። ሁላችንም ቢሆን ዘለዓለም ለማንኖርባት ምድር የመኖር ጉጉት ይዞን፣ ፈርተን ውሸትን ዝም አንልም። እውነትን ተናግረን ውሸትን ተቃውመን እስከ ሞት እንታመናለን። በቅዱስ ጳውሎስ ቃል እመኒ ሐዮነ ለእግዚአብሔር ነሐዩ ወእመኒ ሞትን ለእግዚአብሔር ንመውት ብንኖር ለእግዚአብሔር እንኖራለን ብንሞትም ለእግዚአብሔር እንሞታለን እንላለን። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለቤተ ክርስቲያን አደረግሁት ብለው ይናገሩት የነበረውንኳ ሌላ ትልቅ ክፉ ሥራ ለመሥራት ሽፋን እንዲሆናቸው በማሰብ እንደነበረ ለካቢኔዎቻቸው በሰጡት መግለጫ ቁልጭ ብሎ ታወቀባቸው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለማስፈራራት የሄዱበት ርቀት ደግሞ አስቂኝ ነው። የትምህርት ጥልቀታቸው አናሳ ስለሆነ እንጂ የእርሳቸው ሥልጣን ምንጭኮ ሕዝቡ፣ ወታደሩ፣ ነው። የቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑ እልፍ አእላፋት ወታደሮች፣ የሕግ ባለሙያዎች መኖራቸውን ዘነጉ እንዴ? የሥልጣናቸው ምንጭ እኛ መሆናችንን እንዴት ይዘነጉታል!? ከፈሩንስ የሥልጣናቸው ምንጭ የሆንነውን እኛን ይፍሩን እንጂ እኛ ምን ብለን እንፈራቸዋለን??? መዋቲ ደግሞ ከመቼ ጀምሮ ነው የሚፈራው (ፈራ ይጥበቅ)?። መዋቲ እንደማንፈራ ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል።ለመጀመሪያ ጊዜ ዋናው ንጉሣችን እግዚአብሔር ነው። ከእርሱ ቀጥሎ ያስተዳድረን ዘንድ እኛው የሾምነው ምድራዊ ንጉሥ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ናቸው። ከእግዚአብሔር የሚያጣላ ነገር ከተናገሩ ግን ውግንናችን ለዘለዓለማዊው ንጉሥ ሆኖ እኛው እንደሾምናቸው እስከማውረድ ድረስ ሥልጣኑ የእኛ የሕዝቡ ነው። የዲሞክራሲ ጽንሰ ሐሳብ ከገባቸው እንዲህ ነው። ሕገ መንግሥቱም ቢሆን የሕዝብ አገልጋይ መሆን አለበት እንጂ የአንድ ጠቅላይ ሚኒስትርና ፓርቲ አገልጋይ ብቻ መሆን የለበትም። ብልጽግና ሕጋዊ ተቋማትን የማይጠብቅና ለሕገ ወጥ አካላት አሳልፎ የሚሰጥ ከሆነ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ውንብድና ነው። የወንበዴ ተባባሪ ነው። ስለዚህ ከአባቶቻችን ጋር እንደ አባቶቻችን እስከ መጨረሻው የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና እና ዶግማ ለማስጠበቅ ተዘጋጅተናል።

ንጉሥ ሆይ አያጭበርብሩ

በአዲስ አበባ ለሃይማኖት ተቋማት የተሰጠውን የቦታ ድልድል ሲገልጹ ከሌሎች የሃይማኖት ተቋማት በበለጠ ሦስት እጥፍ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እንደተሰጠ ተናግረዋል። ሳያላምጥ ለሚውጥ ሰው እንዲያውም ለኦርቶዶክስ ብልጫ እንዳደረጉ ሊያስብ ይችላል። ውሸትዎትን እናቆየውና በተናገሩት ንግግር ብቻ ጉዳዩን እንመዝነው እስኪ። በመጨረሻው የሕዝብ ቆጠራ በአዲስ አበባ ከተማ ከሌሎች ሃይማኖቶች በበለጠ ኦርቶዶክሱ 74.7 % ነበር። ከ2007 ዓ.ም ወዲህ የሕዝብ ቆጠራ ስላልተደረገ እንጂ ሊበዛም ሊያንስም ይችላል። ትላንት እንደገለጹት በጠቅላላው ለሃይማኖት ተቋማት የተሰጡ ቦታዎች በካሬ ሜትር 1395000 ገደማ ነው። ይህ በአዲስ አበባ 74.7% ለሆነው ኦርቶዶክስና 25.3% ለሆኑት ሌሎች ቤተ እምነቶች ሲከፋፈል የሚደርሰው ቁጥር ለኦርቶዶክስ 1042065 (1. 045 ሚልዮን ካሬ ሜትር ገደማ) የደረሳት የሚገባት እንጂ ብልጫ ወይም ውለታ አይደለም። ይህንን ብልጽግና ያደረገው ቸርነት አድርጎ ማሰብም ትልቅ ነውር ነው። የብልጽግና መንግሥትዎ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያደርሰውን በደል ለቤተ ክርስቲያን ዋልኩላት ብለው ባሰቡት ውለታ ለመሸፋፈን አይሞክሩ። ዳሩ ግን ውለታ ሳይሆን የመሬት ካርታውም የሚገባት ኮታዋ ነው። ሁለተኛው ስለተመለሱት ሕንጻዎች የተናገሩት ንግግር ነው። የተመለሱት ሕንጻዎች ከመንግሥት የተሰጡ አይደሉም። ለአገልግሎት ራሷ ቤተ ክርስቲያን ሰርታቸው የነበሩ ቤቶች ናቸው። ቀድሞም ደርግ በጉልበት ወሰዳቸው። ኢሕአዴግም የደርግን አስቀጠለ። ያን ጊዜ ደግሞ እርስዎም የኢሕአዴግ ዋና ሹም ነበሩ። ስለዚህ እኩል ነው ቤተ ክርስቲያንን የበደሏት። በኋላ የብልጽግና መሪ ሲሆኑ የክርስቲያኑን ድጋፍ ለማግኘት መለስኩ አሉ። ይህ ውለታ አይደለም። ሌባዎች ሰርቀው በሰረቁት ነገር ሲጠቀሙ ከኖሩ በኋላ አንደኛው ሌባ መጨረሻ ላይ ለባለቤቱ የሰረቀውን ቢመልስ ባለውለታ አይባልም። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ስለሆነች ደግ ሆና እንጂ የነበራትን መሬት ብቻ ሳይሆን ካሣም ያስፈልጋት ነበር። እርስዎ የኢህአዴግ ሹም ከነበሩ ጀምሮ ተዘርፈው የነበሩ ቤቶች በኪራይ እንኳ ቢታሰቡ የመለሷቸውን ቤቶች ሦስት እጥፍ ገደማ የሆኑ ሌላ ቤቶችን ያሠሩ ነበር። ስለዚህ የራሷን ንብረት መመለስ ውለታ አይደለም። ውለታ የሚሆነው ሕንጻዎቹ ከተወሰዱ ጀምሮ ያተረፉትን ትርፍም ለቤተ ክርስቲያን ቢመልሱ ኖሮ ነበር። እና አያጭበርብሩ። የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ላይ የተፈቀደውን የቤተ ክርስቲያን ቦታ ማስፈቀድ ላይ Creditውን እኔ ብቻ ልውሰደው ካላሉ በስተቀር በክፍሉ ሊቀ ጳጳስ፣ በአረብ ኤምሬትስ መሪ (ንጉሥ) ተባባሪነት የተደረገ ነው። ጥያቄውም ከቀድሞ ጀምሮ የነበረ ነው። ብልጽግና እንደ አዲስ ጠይቆ ያደረገው አይደለም። በነበረው ጥያቄ ላይ ትንሽ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል እንጂ ሙሉውን ጉዳይ ብልጽግና እንዳደረገው አድርጎ ለሕዝብ ማስተላለፍ ነውር ነው። የሲኖዶስን እርቅ በተመለከተም ያው ነው። ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን እየላከች ብዙ ለፍታለች። ሊቃውንቱ በኢህአዴግ ደህንነቶች በመርዝ እየተገደሉ እንዳይሳካ ተደርጓል። አሁን ስጠይቅ እርስዎ ለካ በኢህአዴግ ጊዜ የደህንነት ኃላፊም ነበሩ። የጳጳሳቱን፣ የምእመናኑን፣ የሊቃውንቱን ሁሉ ጥረት የብልጽግና መንግሥት ብቻ አስመስለው ሲያቀርቡ ስለ እርስዎ እኔ አፈርኩ። መንግሥትዎ አንድ መልካም ነገር አድርጓል። ይኸውም በአባቶቻችን እርቅ ልክ እንደ ቀድሞ ድርጅትዎ እንደ ኢህአዴግ መሰናክል አልሆነም። እንዲያውም የተሾመበት ወቅት ስለነበረ ሙሉ ክሬዲቱን እርስዎ እንዳስታረቁ ታስቦ የሕዝብ ድጋፍ

አግኝተውበታል። ለሥልጣንዎት Power አግኝተውበታል። ስለዚህ ለቤተክርስቲያን ጥቅም ያደረጉት ሳይሆን ለራስዎ ሥልጣን ድጋፍ ማግኛ ያደረጉት ነው። የሲኖዶስ እርቅም በአቡነ መርቆሬዎስ በጳጳሳቱ፣ በአቡነ ማትያስና በጳጳሳቱ ጥረት እንዲሁም በሊቃውንቱና በሽማግሌዎቹ ጥረት የሆነ ነው። እርስዎም በጊዜው መሰናክል አለመሆንዎና እንዲያውም ቶሎ ብለው ለሥልጣንዎት የክርስቲያኑን ድጋፍ ለማግኘት ይፍጠንልኝ ብለው እግር ላይ ወድቀው መለመንዎት መልካም ነው። ይህን እንደውለታ መቁጠር ግን "እትዬ ስመኝ ለማያውቁሽ ታጠኝ" ያሰኛል።

የተወገዙ ጳጳሳት

በትላንትናው መግለጫዎ አቶ አካለ ወልድ ከሾሟቸው ጳጳሳት አንዱ ነበር የመሰሉኝ። ምክንያቱም ያስተጋቡት ንግግር ሁሉ እነ አቶ አካለ ወልድ የተናገሩትን ነው። በቋንቋ እንገልገል የሚል መልካም ሀሳብ ያላቸው ነበር አስመስለው ያቀረቡት። የትኛውም ቦታ ላይ ክርስቲያኖች የሚገለገሉት በቋንቋቸው ነው። ቅዳሴው ደግሞ ከየትኛውም ቦታ የሚቀደሰው በግእዝ ነው። ግእዝ ደግሞ ብሔር አይለይም። ጳጳሳት ሲሾሙ እንኳ ይህንን ታሳቢ ተደርጎ ነው። እነ አቶ አካለ ወልድ ጳጳስ ሲሆኑኮ በቋንቋቸው ህዝብን ያገለግላሉ ተብሎ እንጂ በቤተክርስቲያኒቱ እውቀት ከእርሳቸው እጥፍ የሚበላልጡ እልፍ አእላፋት ሊቃውንት በተሾሙበት ዘመን ነበሩ። አሁንም በሲኖዶሳችን ውስጥ በኦሮምኛ የሚቀድሱ ከእነ አቶ አካለ ወልድ በተሻለ በተመደቡበት ሀገረ ስብከት በኦሮምኛ አገልግሎት የሚፈጽሙ አባቶች አሉ። ስለዚህ ጥያቄው በቋንቋ እንገልገል የሚል አይደለም። ቤተ ክርስቲያንም አውግዛ የለየቻቸው በቋንቋችን እንገልገል ስላሉ አይደለም። እንዲያማ ቢሉ ኖሮ እኛ ክርስቲያኖች ሁሉ በደገፍናቸው ነበር። ምክንያቱም ለሐዋርያት ፳፪ ቋንቋ የተገለጠ አገልግሎትን ለማፋጠን ነውና። ነገር ግን የእነ አቶ አካለ ወልድ ጥያቄ የዘረኝነት ጥያቄ ነው። ይህንን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን አትቀበልም። ዘረኝነትን አካሏ ክርስቶስ የሚጠላው ሥራ ነውና። ሁለተኛውና ዋናው ደግሞ ያለምንም ሥልጣናቸው ኤጲስ ቆጶስ ሹመናል በማለታቸው ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ የሾመውንም የተሾመውንም የማውገዝ ሥልጣን የቤተ ክርስቲያን ነው። ትክክለኛ ሥርዐቷን ነው የፈጸመችው። ስለዚህ ንጉሥ ሆይ በማያውቁት ጉዳይ ባይዘባርቁ መልካም ነው። መንግሥት ሕጋዊ ለሆነችው ተቋም ሕጋዊ ከለላ ማድረግ አለበት። ነገር ግን ይህንን ሳያደርግ ቀርቶ ለሕገ ወጥ አቶዎች ጥበቃ አድርጎ ለሕጋዊዋ ቤተ ክርስቲያን ጥበቃ አለማድረጉ ደጋፊነቱን በአደባባይ አይተናል። ስለዚህ ገለልተኛ ለመምሰል የሄዱበት ርቀት ውሸታምነትዎትን አጋለጠብዎ። ከምንም በላይ ሀገሬ እንደእርስዎ ያለ ውሸታም ንጉሥ ስላጋጠማት ጎዘኔ ከፍ ያለ ነው። ካቢኒዎችዎንም ስላስፈራሯቸው ምንም እንደማይናገሩ ገብቶናል። ነገር ግን እውነት እውነት ስለሆነች እርስዎም ዘለዓለማዊ ስላልሆኑ እንደሌላው ሰው እንጂ የተለዩ ስላልሆኑ እውነታውን ተቀብለው ቢመለሱ መልካም ነው። ካልሆነ ግን ለመንግሥትዎ አስቸጋሪ ይሆንብዎታል።

እውነት ትንገሥ

አጭበርባሪነ ይጥፋ፣ ውሸት ይውደም።

ድንግል ማርያም

ድንግል ማርያምን ቤዛዊተ ኩሉ ዓለም እንላታለን። ክርስቶስን ቤዛችን ስንለው በመስቀል ተሰቅሎ እኛን ስላዳነን ነው። ድንግል ማርያምን ቤዛዊት ስንላት ግን ቤዛኩሉ ክርስቶስን ስለወለደችልን ነው። ከእርሷ ተወልዶ ዓለምን አድኗልና ነው። ምክንያተ ድኂን ስለሆነች ነው። ልጇ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ ብሎ እንዳስተማረን እሱን ብርሃን እርሷን ደግሞ የብርሃን እናት እንላታለን።ልጇ አምላክ ስለሆነ እርሷ እመ አምላክ ወላዲተ አምላክ ትባላለች። አምላክን የወለደች የአምላክ እናት ማለት ነው። ንስጥሮስን ክርስቶስ ላይ ያለው የምንታዌ (Dualism) እይታ ድንግል ማርያምን ወላዲተ ሰብእ ከማለት አደረሰው። ድንግል ማርያም የወለደችው ሰው የሆነ አምላክን አምላክ የሆነ ሰውን ነው እንጂ ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻን) አልወለደችም። ነገረ ክርስቶስን ከድንግል ማርያም በበለጠ የሚያውቀው ፍጡር የለም። እርሷ ልጇን ይዛ ከሀገር ሀገር ተንከራታለች። በመስቀልም ጊዜ ከጽንዐ ፍቅሯ የተነሳ ከመስቀሉ ሥር አልቅሳለች። ድንግል ማርያምን እናከብራታለን፣ እናመሰግናታለን፣ እንሰግድላታለን። ነገር ግን ለእርሷ የምናቀርበው ስግደት እና ምስጋና የአክብሮት ስግደትና ምስጋና ነው እንጂ እንደ አምላክ የአምልኮ ስግደት አይደለም። ድንግል ማርያም ዓለም ጣዖትን በማምለክ ጨለማ ውስጥ ሳለ ብርሃንን የወለደችልን እናታችን ናት። ድንግል ማርያም ዓለም ለሰይጣን በመገዛት ባርነት ውስጥ ሳለ በመስቀል ተሰቅሎ የእኛን ሞት ሞቶ ነጻነት የሚያጎናጽፍ ጌታን ወለደችልን። ዓለም ተርቦ ነበር። እሷ ግን የሕይወት እንጀራን ወለደችልን። ድንግል ማርያም የትሕትና እናት ናት። ምሥጢራዊም ናት። ማርያም ግን ይህንን ሁሉ በልቧ ትጠብቀው ነበር ተብሏል። እውነትን ይዛ ሳለ በሐሰተኞች ወደ ግብጽ እንድትሰደድ ሆነች።

ስለ ተወጋገዮች በታሪክ

፩) ብዙ ብጥብጥና ሁከት ያስነሳሉ። በዓለም ታሪክ የመጀመሪያ ውግዘት የተላለፈበት ፍጡር ሰይጣን ነው። ሰይጣን በውሸት አምላክ ነኝ በማለቱ ከዓለመ መላእክት ተወግሏል። ክብሩንም ቦታውንም ተነጥቆ ወደ ሲኦል ተወርውሯል። ቅዱስ የሚለው ስያሜ ተነስቶበት ርኩስ ተብሏል። አምላክ ፈታሒ በጽድቅ ስለሆነ በአምላክ ፍርድ ደስተኞች ነን። አምላክ ዲያብሎስን ከመላእክት ጎብረት ሲለየው እስከ ዕለተ ምጽአት ምእመናንን እንደሚረብሽና እንደሚያጋድል ጠፍቶት አይደለም። ነገር ግን እውነትና ውሸት ጎብረት ስለሌላቸው ውሸትን አውግዞ እውነትን ማንገሥ ተገቢ ስለሆነ ነው። ሰይጣን በክፉዎች አድሮ ምእመናንን ቢያስገድል ቢያስጨፈጭፍ በራሱ ላይ ኩነኔን ከማብዛት ውጭ ምንም የሚያመጣው ነገር የለም። ምእመናንም እውነትን ይዘው ቢሞቱ ሰማዕታት ናቸው። ይህንን በጣም የሚፈልጉት እና የሚመኙት ነገር ነው። ከውሸት ጋር ተስማምታችሁና ተደራድራችሁ ኑሩ የሚል ሃይማኖታዊ አስተምህሮ የለንም። ውሸትን አውግዘህ በተወጋገዮች የሚደርስብህን መከራ ታግሦ መቀበል ትልቅ ዋጋ እንዳለው ማመን ይገባል። ስለዚህ መከራ ተፈርቶ ከውሸት ጋር ድርድር የለም። ምንም ዓይነት መከራ ይምጣ እውነትን አንግሠን እንኖራለን።

፪) ከነገሥታት ጋር ተባብረው ቤተ ክርስቲያንን ሊጎዷት ይችላሉ። ይሄንን በደንብ ለመረዳት ወደ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታሪክ መሄድ እንችላለን። አርዮስ ከተወገዘ በኋላ እንኳ

የአርዮስን ሐሳብ የያዙ አርዮሳውያን ጳጳሳት ትክክለኛ እና ሕጋዊ አባቶችን አውግዘናል ብለው እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ከመንበራቸው ወደ ፫ ጊዜ ሲሳደዱ ሰምተናል። ስለዚህ አትናቴዎስ እርሱም ከሚሰደድ በምእመናንም መከራ ከሚደርስ ከአርዮሳውያን ጋር ቢተባበር ኖሮ ይባላልን??? በፍጹም አይባልም። ከውሸት ጋር ከምትደራደር እውነትን ይዘህ ዓለሙ ሁሉ ቢጠላህ ይሻላል። ብትሳደድ መከራ ቢደርስብህ ብትሞት ይሻላል። ስለዚህ ነገሥታትም የውሸት ተባባሪ ሆነው መከራ ሥጋ ሊያደርሱብን ይችላሉ። ነገር ግን የእነርሱም የእኛም ኃላፊ ክርስቶስ ስለሆነ ከእርሱ ቅጣት አያመልጡም። በሀገራችንም በጎንደር ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ አካባቢ የነበረውን ስናስተውል እነ ሱስንዮስ ኮትልከው ወደ 8000 የሚጠጉ ከላስታ፣ ከጎጃም፣ ከጎንደር፣ ከትግራይ፣ ከሸዋ የመጡ ሊቃውንትን በአንድ ጀንበር ጠዳ ላይ አስገድለዋል። ለክርስቲያን እውነትን ይዞ መሞቱ ጌጡ ነው። ያው ኖረን ኖረን በሥጋ መሞት ነው። የማይቀርልንን የሥጋ ሞት ፈርተን ዘለዓለማዊ ከሆነው ሕይወት መቅረት አንፈልግም። ሌላው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሃይማኖት ሳይሆን የምግባር ችግር ያለባቸው ቄሶችን አውግዟቸው ሳለ እነዚያ ቄሶች ደግሞ ከንግሥቲቱ ከአውዶክስያ ጋር ተስማምተው ዮሐንስ አፈወርቅን አግዘውታል። ታላቁ ሊቅና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በግዞት እንዳለ አርፏል። ስለዚህ ተወጋገዮች መከራ ቢያደርሱ፣ ብዙውን አላዋቂ ከጎናቸው ቢያቆሙ ራሳቸውንና ባለማወቅ የሚከተላቸውን ከመጉዳት ውጭ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ምንም አያደርጓትም። የፈጠረንን እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ልንፈራ አልተፈጠርንም። ስለዚህ ምእመናን ሁልጊዜም እውነትን በመያዛችሁ ደስ ሊላችሁ ይገባል። በማንም ተጽእኖ እውነትን መልቀቅ የለብንም። ብንኖርም እውነትን ይዘን እንኖራለን። ብንሞትም እውነትን ይዘን እንሞታለን። የክርስትና ሕይወት ለእውነት እስከ ሞት የሚታመኑበት ሕይወት ነው። እውነትን በማይወዱ ሰዎች ፊት እውነትን መመስከር ነው። የሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ ሕይወት ይህንን ያስተምረናል። ዓለም እየጠላው፣ እየሰደቡት፣ እየደበደቡት፣ እየገደሉት እውነትን ከመመስከር ወደ ኋላ አላለም ነበር። በእውነት መኖር ለእውነት መሞት የቅዱሳን ሰማዕታት በጠቅላላው የክርስቲያኖች መርሕ ነው። ይህንን ደግሞ ከአባታቸው ከክርስቶስ ተምረውታል።

፩) ፍቅር

፪) ትሕትና

፫) ቅንነት

፬) እውነት

የሰማዕታት ገንዘቦች ናቸው። የሰማዕቱ በረከት አይለየን። እንኳን አደረሳችሁ።

የሐዋርያት እና የሊቃውንት ሲኖዶስ

ሲኖዶስ የግሪክ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙ ጉባኤ፣ ሸንጎ፣ የጳጳሳትና የሊቃውንት ማኅበር ማለት ነው። የሐዋርያት ሲኖዶስ የሚባሉት አራት መጻሕፍት ናቸው። እነዚህም:-

- ግጽው (ረስጠጅ)
- ትእዛዝ (ረስጠብ)

- ሥርዓተ ጽዮን (ዓይን)
- አብጥሊስ (ረስጣ/ረስጠአ) ናቸው።

የሲኖዶስ ውሳኔ የቤተክርስቲያኗ ሕግ እና ሥርዓት ሆኖ ይሠራል። በቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚታወቀው ኤጲስ ቆጶስ ድንግል መሆን እንዳለበት የተወሰነው በአልቪራ ጉባኤ ስፔን በ305/6 ዓ. ም ነው። በኋላ በኒቅያው ጉባኤ ቀርቦም ጸድቋል። የኒቅያ ጉባኤ አርዮስን ካወገዘ በኋላ ሌሎች የሥርዓት ጉዳዮችንም ወስኗል። አንዳንድ ሲኖዶሶች ወቅትንና አካባቢን መሠረት አድርገው የተደነገጉ ናቸው።

ግጽው ሲኖዶስ

ቁጥር ፲፩:- በቅዱስ ጴጥሮስ ጸሎትና ልመና እግዚአብሔር ጠንቋዩን ሲሞንን አጠፋው። ትእዛዝ ፩:- ጸሎታችን ወደ ምሥራቅ ይሁን። ምጽአቱ ከምሥራቅ እንደሚሆን በዚህ አወቅን። ሰንበት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የቃል ኪዳን ምልክት ነው። ትእዛዝ ፪:- ለጸሎት፣ መጻሕፍትን ለማንበብና ቁርባን ለማቅረብ በየእሑዱ በሦስት ሰዓት ይሰብሰቡ። በዚህች ቀን መልአኩ ክርስቶስን እንደምትፀንስ ለማርያም አብሥሯታልና። ጌታ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶበታልና። ትእዛዝ ፫:- በዕለተ ረቡዕ ተሰብስበው ጸሎት ያድርጉባት። በዚህች ቀን አይሁድ ይዘው እንደሚሰቅሉትና እና በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ነግሯቸዋልና። በዚህም ቀን አዝነዋል ተክዘዋልና። ትእዛዝ ፬:- በዕለተ ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት ተሰብስበው ጸሎት ያድርጉ። ክርስቶስ መከራ ተቀብሎበታልና። ትእዛዝ ፭-፮:- ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት ለምእመናን ሊቃውንትን ይሹሙላቸው። ቀሳውስትን፣ ዲያቆናትን፣ ንፍቅ ዲያቆናትን፣ አናጉንስጢሶችን ይሹሙላቸው። ትእዛዝ ፯:- የጌታችንን የልደት በዓል በተወለደባት ቀን ታኅሣሥ ፳፱ን አክብሩ። እስመ ውእቱ ርእሰ ኵሉ በዓላት። ትእዛዝ ፰:- የጌታችንን የጥምቀት በዓል ጥር 11 ቀን ያድርጉ። የምስጋና ቀን ናትና። ትእዛዝ ፱:- በየዓመቱ ፶ ቀን ይጹሙ። የክርስቶስን ሕማሙን፣ ስቅለቱን፣ ሞቱንና ወደ መቃብር መውረዱን ያስቡ። በትንሣኤው ቀንም ፋሲካን ያድርጉ። ከሰንበታት በስተቀር ቅዳሜና ዓርብን ጨምሮ ፶ ቀን ጾመው ሲጨርሱ በዓል ያድርጉ። እሑድ ትንሣኤው ነው። ከእነዚህ ቀናት በኋላ እስከ ኃምሳኛው ቀን መጨረሻ ድረስ ጾም የለም። ትእዛዝ ፲፩:- ከትንሣኤው በኋላ በ፵ኛው ቀን ጌታችን ወደ ሰማይ ያረገበትን በዓል አክብሩ። ትእዛዝ ፲፪:- ከአሪት ከነቢያት መጻሕፍት ሁሉ እና የሐዋርያትን ዜና በቤተክርስቲያን በታላቅ አትሮንስ ላይ ያንብቡ። ከዚያ በኋላም የመጻሕፍት ሁሉ ፍጻሜ ነውና ከወንጌል ያንብቡ። ሕዝቡም ሁሉ በእግሩ ቆሞ ይስማ። የሕይወትና የመድኃኒት የምሥራች ነውና። ትእዛዝ ፲፫:- ሕግና ሥርዓትን የማያውቅ ሰው በምእመናን ላይ አይሾም። በምእመናን ላይ ሊሾም የሚገባው በጠባዩ ቸር፣ ታጋሽ፣ በጉዞው ሁሉ ጥሩና ትሑት ይሁን። ይህን ካላደረገ ይሻር። ቃሉንና ትእዛዙንም አይቀበሉት። በአሠራሩ ታማኝ አይደለምና። ትእዛዝ ፲፬:- ሐሰተኛን እና ሐሜተኛን ሰው ከሹመት ይከልክሉት። ትእዛዝ ፲፭:- በኮከብ ቆጠራ የሚታመንና በጥንቆላ የሚያምን ሁሉ ከሹመት ይወገድ። ክርስቲያኖችን እግዚአብሔርን ከማያውቁት ጋር የሚያስተካክል ከክህነት ሥልጣን ይሻር። ትእዛዝ ፲፮:- በዝሙትና በስስት የሚታወቅ እንዲሁም የዚህን ዓለም ጥቅም የሚፈልግ ቄስም ሆነ ዲያቆን ከሹመቱ ይሻር። ትእዛዝ ፲፯:- የዚህን ዓለም ሥራ የሚሠራን ሰው በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ላይ እንዲያገዝ ሹም አያድርጉት። ጸሎት የያዘ ቄስም ሆነ ዲያቆን ጸሎቱን አቋርጦ ወደሌላ ነገር አይሂድ። እንደዚህ የሚያደርግ ከሆነ

ወደቀድሞ ቦታው መመለስ አይሆንለትም (አይገባውም)። ትእዛዝ ፳፩፡- ለቅዱሳን ሰማዕታት በሞቱበት ቀን መታሰቢያ ያድርጉላቸው። ትእዛዝ ፳፪፡- መዝሙረ ዳዊትን ቀንም ሌሊትም ይጸልዩት። መዝሙረ ዳዊት ተአምኖ ኃጣውእ፣ ጸሎት፣ ምስጋና አለበትና። ችግር፣ ሐዘንና፣ መከራ በአጋጠማቸው ጊዜ ከጥፋት ያመልጡ ዘንድ ይጸልዩ። ትእዛዝ ፳፫፡- በቤተመቅደስ ለማገልገል ከሕዝብ የተመረጡ ካህናት ሰባት ይሁኑ። ትእዛዝ ፳፬፡- ዐመፀኛውን ጻድቅ የሚያደርግ፣ ንጹሑን የሚያበሳጭ የተወገዘና ርጉም ይሁን። እንደዚህ የሚያደርገውን ከሹመቱ ይከልክሉት። ስለዐመፀኛነቱም ይመስክሩበት። ዐመፀኛ ከሆነ ጽጽስናው አያስፈራህ። (በእንተ ዐመፃሁ ወኢያፍርህከ ጽጽስናሁ)። ትእዛዝ ፳፭፡- በሰዎች ላይ የሚኩራራና በራሱ የሚታበይ ወደ ሹመት አይቅረብ። ከሌሎች ሰዎች እንደሚበልጥ እንደሚከብርና እንደሚሻል ራሱን የሚያይ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በንቀት ዓይን የሚመለከት በሹመት ላይ አይቀመጥ። ትእዛዝ ፳፮፡- በየአውራጃው ባሉ ቀሳውስት ላይ በመካከላቸው ሆኖ የሚያዛቸውና የሚገሥጻቸው ሊቀ ካህናት ይሹመ። ትእዛዝ ፳፯፡- በጸሎት ጊዜ ንጉሥ በሰው ሁሉ ፊት ከምእመናን ጋር ይሁን። ለቁርባን ወደ መሠውያው ቦታ ይግባ። መቆሚያውም ከሊቃውንትና ከተሾሙ ካህናት ጋር በዚያ ይሁን። ትእዛዝ ፳፰፡- ቁርባንን በዕለቱ ያቀብሉት እንጂ ለነገ አያሳድሩ። ሊቃነ ካህናቱ ኒቆዲሞስና ገማልኤል፣ ሐና፣ ቀያፋ፣ ሊቃነ ካህናት ሌሊት ወደክርስቶስ ይመጡ ነበር። በክርስቶስም ያምኑ ነበር። ነገር ግን አይሁድን ፈርተው ይህንን አልገለጹም። ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ሁላቸውም አምነዋል። የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እርስ በእርሳቸው ይተባበራሉ። ሐዋርያት ከጠንቋዮች ጋር ይጋደሉ ነበር። ስለ ሃይማኖታቸው ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ እኛም የፈጠረንን አስቆጥተነዋልና ይህች የደረሰችብን ችግር ታስታርቀናለች ይሉ ነበር። ከእነርሱ መካከል ብዙ ጊዜ ንብረቱ የተዘረፈበት አለ፣ ከገንዘቡ ከልጆቹና ከቤቱ የራቀም አለ፣ የሰቀሉትም አለ። እስኪሞቱ ድረስ በፈቃዳቸው ይታገሡ ነበር። ምእመናን ለአማልክት የተሠዋንና በክት የሆነውን ከመብላት፣ ደምን ከመጠጣት፣ ለባዕድ አምላክም ከመሳል እንዲታቀቡ ያዝዟቸው ነበር።

ትእዛዝ ሲኖዶስ

ትእዛዝ ፩፡- ኤጲስ ቆጶስ ሁለት ወይም ሦስት ኤጲስ ቆጶሳት በተገኙበት ይሾም። ቂስ ዲያቆንና የቀሩት ሹማምንት በአንድ ኤጲስ ቆጶስ ሥልጣን ብቻ ይሾሙ። ትእዛዝ ፪፡- ጌታችን ካዘዘው (ስንዴ፣ የወይን ፍሬ፣ መብራት፣ ዘይት፣ ንጹሕ ዕጣን) ውጭ ቁርባን ያሳረገ ይሻር። ትእዛዝ ፫፡- ካህን በአገልግሎት ምክንያት ሚስቱን አይፍታ። ከፈቱ ይለዩ። ካልመለሷት ግን ይሻሩ። ትእዛዝ ፬፡- ካህናት ቀንና ሌሊቱ እኩል ከመሆኑ በፊት ከአይሁድ ጋር ቅድስት ፋሲካ እንድትውል ካደረጉ ይሻሩ። ትእዛዝ ፭፡- ኤጲስ ቆጶስ፣ ቂስና ዲያቆን ከዚህ ዓለም ተግባር ውስጥ አይግቡ። ገብተው ከተገኙ ግን ይለዩ። ትእዛዝ ፮፡- ኤጲስ ቆጶስ ወይም ከካህናት አንዱ ምክንያቱን ሳይናገር በቅዳሴ ግን ቁርባን ባይቀበል የማይገባው ሆኖ ከተገኘ ይቅር ይበሉት። ምክንያቱን ካልተናገረ ግን ይባረር። በአሳረገው መሥዋዕት ላይም በንጽሕና እንዳላሳረገው ሆኖ ለሕዝብ እንቅፋት ሆኗልና። ትእዛዝ ፯፡- ወደ ቤተክርስቲያን የሚገባ አማኝ ሁሉ መጻሕፍትንም የሚሰማ ነገር ግን ጸሎት እስከሚያደርጉ ድረስ የማይቆም ቁርባንም የማይቀበል ከሆነ በላዩ ላይ አይጸልዩለት። ሊባረርም ይገባዋል። በቤተክርስቲያን ክርክርንና ብጥብጥን ፈጥሯልና። ትእዛዝ ፰፡- ከቤተክርስቲያን ከተባረረ ሰው ጋር አይጸልዩ። ትእዛዝ ፱፡- ካህን ከተባረረ ካህን ጋር

ቢጸልይ እርሱም ይባረር። ትእዛዝ ፲፩፡- ኤጲስ ቆጶስ የሹመት ቦታውን ትቶ በሌላ ሀገረ ስብከት ሊሾም አይገባም። ትእዛዝ ፲፪፡- ያለ ኤጲስ ቆጶሱ ሥልጣን የሥራ ቦታውን ቢተውና ወደሌላ የሥራ ቦታ ቢሄድ እንዳያገለግል እኛ እናሳለን። በይበልጥም ኤጲስ ቆጶስ ወደቦታው እንዲመለስ ቢልክበትና ባይሰማው ከሹመቱ ይባረር። ባለበት ቦታ እንደ ሕዝባዊ ሆኖ ይቁረብ። ትእዛዝ ፲፫፡- ወደ ተውኔት ቤት የምትሔደውን ያገባ ክህነት ሊሾም አይገባውም። ትእዛዝ ፲፬፡- ዋስ የሚሆን ካህን ይሻር። ትእዛዝ ፲፭፡- በራሱ ፈቃድ ራሱን የሰለበ ክህነት አይሾም። ትእዛዝ ፲፮፡- በዝሙት፣ በሐሰት መማል፣ በመስረቅ የሚገኝ ካህን ይሻር። ትእዛዝ ፲፯፡- ክህነት ወደሚገቡበት ጊዜ አናጉንስጢስና መዘምራን ማግባት ቢፈልጉ ያግቡ። ከተሾሙ በኋላ ግብ ማግባት አይገባቸውም። ትእዛዝ ፲፰፡- ሰዎች ይፈሩት ዘንድ የሚደባደብ ካህን እንዲሻር እናዛለን። ትእዛዝ ፲፱፡- በታወቀ ኃጢአት ምክንያት በትክክል የተሻረ ኤጲስ ቆጶስም ቢሆን ቄስም ቢሆን ዲያቆንም ቢሆን ከተደፋፈረና ሥልጣን ባለው ጊዜ ይሠራውን የነበረውን መሥራት ከጀመረ ፈጽሞ ከቤተክርስቲያን ይራቅ። ትእዛዝ ፳፡- ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን መማለጃ በመስጠት የሹመት መዓርግ ቢይዝ ይሻር። የሾመውም ይሻር። ከክህነት ሥርዓትም እስከ መጨረሻው ይባረር። ትእዛዝ ፳፩፡- ኤጲስ ቆጶስ ቤተክርስቲያንን በዚህ ዓለም የአገዛዝ ሥርዓት ለመግዛት የሚፈልግን ሰው ከረዳ ይሻር። ትእዛዝ ፳፪፡- ቄስ ኤጲስ ቆጶስን ቢንቅ ይለይ። ትእዛዝ ፳፫፡- ኤጲስ ቆጶስ ያባረረውን ቄስ ወይም ዲያቆን ራሱ ካልፈቀደ በስተቀር ሌላ ኤጲስ ቆጶስ እንዲመለስ አያድርገው። ትእዛዝ ፳፬፡- ሊቀ ጳጳሳት የሁሉንም ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶሳት ያውቅ ዘንድ ይገባል። ትእዛዝ ፳፭፡- ኤጲስ ቆጶስ የሀገረ ስብከቱ ኤጲስ ቆጶስ ካልፈቀደለት የእርሱ ባልሆነ ሀገረ ስብከት ላይ ለመሾም አይደፋፈር። ተደፋፍሮ የተገኘ ካለ እርሱም የሾማቸውም ይሻሩ። ትእዛዝ ፳፮፡- የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ በዓመት ሁለት ጊዜ ይደረግ። በቤተክርስቲያን ላይ ስለአለ ስሕተትና እንቅፋት ስለሚሆኑ ነገሮችም ይተርጕሙ። የመጀመሪያው ጉባኤ በበዓለ ኃምሳ መካከል ይሁን። ሁለተኛው ጉባኤ ጥቅምት 12 ይሁን። ትእዛዝ ፳፯፡- ኤጲስ ቆጶስ የእግዚአብሔርን ገንዘብ ለዘመዱ ልጆች መስጠት የለበትም። ትእዛዝ ፳፱፡- ከቀሳውስት ወይም ከዲያቆናት ማንም ኤጲስ ቆጶሱን ሳያማክር ምንም አያድርግ። ትእዛዝ ፴፩ [የጦር ሠራዊት]፡- የንጉሥ ሠራዊትም ከጠላት ጋር ጦርነት የሚያደርጉት በራሳቸው ምግብ አይደለም። ትእዛዝ ፴፪፡- ወደ ጭፈራ ቤት የሚሔድና የሚዞር ስካርም የሚያበዛ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ይተው። አልተውም ካለ ግን ይባረር። ሕዝባውያንም ቢሆኑ እንደዚሁ ይሁኑ። ትእዛዝ ፴፫፡- ወደ ከኃድያን ጥምቀት ወይም ወደ ቁርባናቸው የሚሔድ ካህን ይሻር። ትእዛዝ ፴፬፡- ሥጋ መብላት፣ ጋብቻ፣ ወይን መጠጣት እንደ ርኩስ የሚቆጥር ቢኖር ይህን ሐሳቡን ይተው ዘንድ ይንገሩት። ካልተወ ግን ይሻር። ሕዝባዊ ቢሆንም እንዲሁ ይደረግ። ትእዛዝ ፴፭፡- ከኃጢአት ንስሓ የሚገቡትን አልቀበልም የሚል ካህን ቢኖር ይሻር። ትእዛዝ ፴፮፡- ከካህናት መካከል በገበያ የሚበላ ወይም የሚጠጣ ቢገኝ ከካህናት አንድነት ይለይ። ከካህናት መካከል አንዱ ኤጲስ ቆጶስን ቢሳደብ ይሻር። በሕዝብ ላይ በተሾመ ሰው ላይ መጥፎ ቃል አትናገር ይላልና። ቄስን ዲያቆንን የሚሳደብም ይባረር። ትእዛዝ ፴፯፡- ካህናትን ወይም ሕዝብን የሚንቅና የእግዚአብሔርን መልእክት የማያስተምር ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ይባረር። በንቀቱ ቢቀጥልበት ይሻር። ትእዛዝ ፴፰፡- ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ከካህናት የተቸገረን አይቶ ቸል ቸል ካለ የሚፈልገውን ነገርም ባይሰጠው ይለይ። በዚሁ በቸልታው ከቀጠለም ወንድሙን

እንደገደለ ይቆጠራልና ይሻር። ትእዛዝ ፶:- ከኃድያን በውሸት የጻፉትን መጽሐፍ ያሳየ ሕዝብንና ካህናትንም ለማጥመድ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ቆጥሮ ወደ ቤተክርስቲያን ያስገባ ሰው ቢኖር ይሻር። ትእዛዝ ፶፪:- ከካህናት መካከል ከኃድያንን ከመፍራት የተነሣ ቢክድ የካደው የክርስቶስን ስም ከሆነ ይባረር። የካደው ክህነትን ከሆነ ይሻር። ንስሓ ከገባ ይቀበሉት እንደ ሕዝብ ሆኖም ይግባ። ትእዛዝ ፶፫:- ከካህናት አንዱ ደም ያለው ወይም ያልታረደ ወይም አውሬ የነከሰው ወይም በክት ከበላ ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነም ይለይ። ትእዛዝ ፶፬:- ከቀዳም ስዑር በስተቀር በሰንበትና በዕለተ እሑድ ከካህናት መካከል አንዱ ሲጾም ቢገኝ ይሻር። ትእዛዝ ፶፭:- ከካህናት መካከል በከኃድያን ቦታ ይጸልይ ዘንድ ቢገባ ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነም ይባረር። ትእዛዝ ፶፮:- ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ሁለት ጊዜ ተሹሞ ቢገኝ እርሱም የሾመውም ይሻር። ትእዛዝ ፶፯:- ደዌ ሕመም ካልከለከለው በስተቀር ጾመ አርብዓን፣ ረቡዕና ዓርብን የማይጾም ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ወይም አናጉንስጢስ ወይም መዘምር ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነ ደግሞ ይባረር። ትእዛዝ ፶፰:- ከካህናት አንዱ ከአይሁድ ጋር ቢጾም ወይም ፋሲካን ከእነርሱ ጋር ቢያደርግ ወይም ለበዓላቸው ስጦታ ቂጣ ቢቀበል ወይም ይህን የመሰለ ቢያደርግ ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነ ይባረር። ሕዝባዊ ሆኖ ዘይትና መብራት ወደ አይሁድ ምኵራብና ወደ አሕዛብ ምኵራብ ቢወስድ ከምእመንነቱ ይሻር። ትእዛዝ ፶፱:- የተሾመ ካህን ከቤተክርስቲያን ሠም ወይም ቅባት ቢሰርቅ ይባረር። የሰረቀውንም አምስት እጥፍ አድርጎ ይክፈል። ትእዛዝ ፷:- በኤጲስ ቆጶስ ላይ የከኃድያንን ምስክርነትና የአንድን ኤጲስ ቆጶስ ምስክርነት አይስሙበት። ኤጲስ ቆጶስነትን ይዋረሱ ዘንድ ትክክል አይደለም። ኤጲስ ቆጶስ የቤተክርስቲያንን ሀብት ለፈለገው ሰው አይስጥ። አንድ ዓይኑ የታወረ ወይም አንድ እግሩ አንካሳ የሆነ ሰው ኤጲስ ቆጶስነት የሚገባው ቢሆን ይሾም። ነውረ ነፍስ እንጂ ነውረ ሥጋ አያረክስምና። መስማት የተሳነውና ዐይነ ስውር ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ አይሾም። ትእዛዝ ፷፩:- ጋኔን ያደረበት ካህን ሆኖ አይሾም። ከምእመናን ጋርም አብሮ አይጸልይ። ጌቶቹ እንዳያዝኑ ነጻ ያልወጣ ሰው ካህን ሆኖ ይሾም ዘንድ አናዝም። ትእዛዝ ፷፫:- ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ዓለማዊ ሹመትንና ክህነትን ሁለቱን ለመሥራት ወታደር ሆኖ ማገልገል ቢፈልግ ይሻር። [መንግሥትነት] ንጉሥን ወይም መኮንንን የሚያቃልል ይበቀሉት። ካህን ከሆነ ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነ ደግሞ ይባረር። ትእዛዝ ፷፬-፷፭:- ሕዝባውያን ሆይ ቀጥለው ያሉት መጻሕፍት በእናንተ ዘንድ ሁሉም ተቀባይነት ይኑራቸው። ፩) ኦሪት ዘፍጥረት ፪) ኦሪት ዘጸአት ፫) ኦሪት ዘሌዋውያን ፬) ኦሪት ዘኍልቊ ፭) ኦሪት ዘዳግም ፮) መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ ፯) መጽሐፈ መሳፍንት ፰) መጽሐፈ ሩት ፱) አንደኛ ነገሥት (፩ኛ ሳሙኤል) ፲) ሁለተኛ ነገሥት (፪ኛ ሳሙኤል) ፲፩) ሦስተኛ ነገሥት (፩ኛ ነገሥት) ፲፪) አራተኛ ነገሥት (፪ኛ ነገሥት) ፲፫) መጽሐፈ ዕዝራ (፩&፪) ፲፬) መጽሐፈ ኢዮብ ፲፭) መጽሐፈ አስቴር ፲፮) መጽሐፈ ጦቢት ፲፯) መጽሐፈ መክብብ ፲፰) መዝሙረ ዳዊት ፲፱) መጽሐፈ ምሳሌ ፳) መኃልየ መኃልይ ፳፩) ፲፪ቱ ንዑሳን ነቢያት ፳፪) ትንቢተ ኢሳይያስ ፳፫) ትንቢተ ኤርምያስ ፳፬) ትንቢተ ሕዝቅኤል ፳፭) ትንቢተ ዳንኤል ፳፮) መጽሐፈ ጥበብ ፳፯) መጽሐፈ ዮዲት ፳፰) ሦስቱ የኩፋሌ መጻሕፍት ፳፱) መጽሐፈ ሲራክ ፴) የማቴዎስ ወንጌል ፴፩) የማርቆስ ወንጌል ፴፪) የሉቃስ ወንጌል ፴፫) የዮሐንስ ወንጌል ፴፬) የሐዋርያት ሥራ ፴፭) አንደኛ ጴጥሮስ ፴፮) ሁለተኛ ጴጥሮስ ፴፯) አንደኛ ዮሐንስ ፴፰) ሁለተኛ ዮሐንስ ፴፱) ሦስተኛ ዮሐንስ ፵) የያዕቆብ መልእክት ፵፩)

መልእክተ ይሁዳ ፸፪) ራእየ ዮሐንስ ፸፫) ፲፬ቱ የጳውሎስ መልእክት ፸፬) ፪ቱ የቀሌምንጦስ መልእክታት ፸፭) ሕጹጻን (፪ቱ)

ሥርዓተ ጽዮን

ቁጥር ፩) ኤጲስ ቆጶስ ሁለት ወይም ሦስት ኤጲስ ቆጶሳት ባሉበት እሑድ ቀን ይሾም። ቁጥር ፪) ቂስ ዲያቆንና ሌሎች እሑድ ቀን በአንድ ኤጲስ ቆጶስ ይሾሙ። ቁጥር ፫) ፋሲካን ከአይሁድ ጋር ያደረገ ካህን ይሻር። ቁጥር ፬) በቤት የሚጸልይ ቢኖር ቆሞ ይጸልይ። ቁጥር ፭) ሁለት እህትማማቾችን ወይም የወንድሙን ልጅ ወይም የእህቱን ልጅ ያገባ መሾም አይችልም። ቁጥር ፮) በዝሙት ወይም በሐሰት በመማል ወይም በሌብነት የተገኘ ካህን ይሻር። ቁጥር ፯) ሕዝባዊ ሆኖ ራሱን የሰለበ ለሦስት ክረምቶች ይታገድ ለራሱ ሕይወት ጠላት ነውና። ቁጥር ፰) ለመፈራት የሚደባደብ ካህን ይሻር ዘንድ እናዛለን። ቁጥር ፱) በታወቀ በደል በትክክል የተሻረ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቂስ ወይም ዲያቆን ቢኖርና ቀድሞ በተሰጠው ሥልጣን ለመሥራት ቢደፋፈር ፈጽሞ እንደዚህም ቢያደርግ እስከ ዘለዓለሙ ድረስ ከቤተክርስቲያን ይሻር። ቁጥር ፲) በገንዘብ ሹመት ያገኘ ካህን ይሻር። ቁጥር ፲፩) ቤተክርስቲያን የያዙ የዓለም ሰዎች የሆኑ መኳንንትን የሚያገለግል ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር ይሻር። ይታገድም። ከእርሱ ጋር የተባበሩት ሁሉም ይታገዱ። ቁጥር ፲፪) ደብዳቤ ካልያዘ በስተቀር እንግዳ የሆኑ ኤጲስ ቆጶስን ወይም ቂሶችን ወይም ዲያቆናትን አይቀበሉ። ቁጥር ፲፫) የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር የተሰጠችውን ሀገረ ስብከት ሕዝብ ልብና እሺ በጎ ብሎ መገዛት ካላገኘ እስቀሚቀበሉት ድረስ ታግዶ ይቆይ። ቁጥር ፲፬) የኤጲስ ቆጶሳት ሲኖዶስ በዓመት ሁለት ጊዜ ትደረግ። አንደኛው በአራተኛው የጰንጠቆስጤ ሳምንት ይደረግ። ሁለተኛው በጥቅምት ፲፪ ቀን ይደረግ። ቁጥር ፲፭) ቀሳውስትና ዲያቆናት ከኤጲስ ቆጶስ ምክር ውጭ ምንም አያድርጉ። ቁጥር ፲፮) ኤጲስ ቆጶስ ሀብት ካለው የእርሱ ለብቻ የታወቀ ይሁን። የቤተክርስቲያን ተለይቶ የታወቀ ይሁን። ቁጥር ፲) ኤጲስ ቆጶስ በቤተክርስቲያን ሀብት ላይ ሥልጣን ያገኘ ዘንድ እናዛለን። ቁጥር ፲፩) በዘፈንና በስካር ላይ የሚገኝ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቂስ ወይም ዲያቆን ይተው። አለበለዚያ ይሻር። ቁጥር ፲፫) ካህን ከከሓድያን ጥምቀት ቢቀበል ወይም መሥዋዕትን ቢቀበል ይሻር ዘንድ እናዛለን። ቁጥር ፲) መንገድ ሲሔድ ደክሞት ለማረፍ ብሎ ካልሆነ በስተቀር ሹም ሆኖ በጠጅ ቤት የሚበላ ቢኖር ይታገድ። ቁጥር ፲፰) ከኃድያንን በመፍራት የክርስቶስን ስም የካደ ይባረር። ከሹመቱ ስምም ይሻር። ቁጥር ፲፱) ለአምልኮ ባዕድ የተሠዋውን የሚበላ፣ ወይም ነፍስ ያልተለየውን ሥጋ የሚበላ ወይም በአውሬ ተነክሶ የሞተን የሚበላ ወይም በክት የሚበላ ካህን ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነም ይታገድ። ቁጥር ፳፩) ከከኃድያን ጋር ቤተ ጸሎት ገብቶ የሚጸልይ ተሿሚ ቢኖር ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነም ይታገድ። ቁጥር ፳፭) ደቄ ሥጋ ካልከለከለው በስተቀር የተቀደሰችውን የፋሲካን ጾም ረቡዕና ዓርብን የማይጾም ካህን ቢኖር ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነም ይታገድ። ቁጥር ፳፮) ከአይሁድ ጋር የሚጾም ወይም ከእነርሱ ጋር በዓላቸውን የሚያከብር ወይም ከበዓላቸው ቂጣም ሆነ ወይም ሌላ የሚመስለውን ስጦታ የሚቀበል ኤጲስ ቆጶስ ወይም ሌላ ሹም ቢኖር ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነም ይታገድ። ቁጥር ፳፬) መጻሕፍት አምላካውያት ፩) ኦሪት ዘፍጥረት ፪) ኦሪት ዘጸአት ፫) ኦሪት ዘሌዋውያን ፬) ኦሪት ዘኍልቊ ፭) ኦሪት ዘዳግም ፮) መጽሐፈ ኢያሱ ፯) መጽሐፈ መሳፍንት ፰) መጽሐፈ ሩት ፱) መጽሐፈ ነገሥት (፬ቱ) ፲) ሕጹጻን (፪ቱ) ፲፩) ዕዝራ (፫ቱ) ፲፪) መዝሙረ ዳዊት ፲፫) መጽሐፈ ምሳሌ ፲፬) መጽሐፈ መክብብ ፲፭) መኃልየ መኃልይ

፲፯) መጽሐፈ ኢዮብ ፲፰) ንኡሳን ነቢያት (፲፱ቱ) ፲፰) ትንቢተ ኢሳይያስ ፲፱) ትንቢተ ኤርምያስ ፳) ትንቢተ ሕዝቅኤል ፳፩) ትንቢተ ዳንኤል ፳፪) ወንጌል (፬ቱ) ፳፫) የሐዋርያት ሥራ ፳፬) የጳውሎስ መልእክት (፲፬ቱ) ፳፭) መልእክታተ ሐዋርያት (፯ቱ)

አብጥሊስ

አብጥሊስ ፩:- ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ሊሾም የቀረበ ሰው ካለ ይህ በሀገረ ስብከቱ ሰዎች ሁሉ ስምምነት መሆን አለበት። **አብጥሊስ ፪:-** ቤተክርስቲያን ውስጥ ከሚያበሩት መብራት፣ ከቅብዐ ሜሮን፣ ከቅብዐት፣ ከዕጣን፣ ከመልካም ሽቱ በስተቀር ምንም ነገር አያስገቡ። **አብጥሊስ ፫:-** ቤተክርስቲያንን ለማገልገል የተመደቡ ኤጲስ ቆጶሳት ወይም ቀሳውስት ወይም ዲያቆናት በዚህ ዓለም ተግባር ላይ መሰማራት አይገባቸውም። እንደዚህ ቢያደርጉም ከቤተክርስቲያን ሀብት ይመገቡ እንጂ የትም አይጣሉ። **አብጥሊስ ፬:-** በቅዳሴ ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን የገባና ቁርባን ያልተቀበለ ከቤተክርስቲያን ይውጣ። **አብጥሊስ ፭:-** ከተወገዘ ካህን ጋር የተነጋገረ በድብቅም ከካህናት ጋር ሲጸልይ ያልከለከለ ሰው ቢኖር ከክህነት ይሻር። ከቁርባንም ይከልከል። **አብጥሊስ ፮:-** በሰዎች ሳይገደድ ራሱን በፍላጎቱ የሰለበ ሰው ክህነት መሾም የለበትም። ራሱን በመግደሉ የራሱ ጠላት ነውና። የእግዚአብሔርንም ፍጥረት የጠላ ነውና። **አብጥሊስ ፯:-** ራሱን የሰለበ ምእመን ቢኖር ከቤተክርስቲያን ሦስት ዓመት ይሰናበት። **አብጥሊስ ፰:-** ወደ ቤተክርስቲያን የገባና ክህነትን በእውነት የተቀበለ ሰው ቢኖር ማግባት ቢፈልግ እንዲያገባ እናዛለን። **አብጥሊስ ፱:-** ባደረገው በደል ከቤተ ክርስቲያን ያስወጡት ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ወይም ከእርሱ የሚበልጥ ክህነቱን ያሰረበት ካህን ቢኖርና ያደረገው በደል ባያሳዝነው በግድም ያለ ፍርሃት የቤተክርስቲያን አገልግሎት ቢፈጽም ሊፈራቅ ይገባው የነበረው ያ በደልም ባይደንቀው እስከመጨረሻው ከቤተክርስቲያን ይሰናበት። **አብጥሊስ ፲፪:-** እንግዳ ሆነው ከሩቅ ሀገር የመጡ ቀሳውስትና ዲያቆናትን ኤጲስ ቆጶስ አይቀበል። የክህነት ሥራንም አይሥሩ። የክህነት ሥራ እንዲሠሩ ደብዳቤ ካላቸው ግን ሥልጣን አላቸው። ደብዳቤ ቢኖራቸውም ምግባራቸውን ይጠይቁ። **አብጥሊስ ፲፫:-** ኤጲስ ቆጶስ የሊቃውንት ክብር የሚያውቅ ይሁን። የተሾመላቸው የአገሩ ሰዎች ሁሉ የሚፈልጉትን ያድርግ እንጂ። **አብጥሊስ ፲፬:-** ኤጲስ ቆጶስ ሕዝብን ማስተዳደር ባይችል ይህን እስከሚያሻሽል ድረስ ከእነርሱ ይሻር። አብጥሊስ ፲፭:- የከሓድያንን ጥምቀት የተጠመቀ ወይም ከቁርባናቸው የቆረበ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ቢኖሩ ከሹመታቸው ይሻሩ። **አብጥሊስ ፲፮:-** ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ከአበደረው ዘንድ ወለድ ቢፈልግ ከመሳርጉ ይሻር። **አብጥሊስ ፲፯:-** ከካህናት ወይም ከሕዝባውያን መካከል በሰው ላይ የተሳለቀ ወይም የሳቀ ቢኖር ይሻር። ከአጋጠመው ችግር ተነሥተህ ማንንም አትሳደብ። **አብጥሊስ ፲፰:-** ኤጲስ ቆጶስ ወይም አገርን የሚያስተዳድር ከካህናት የተቸገረን ሰው በድብቅ ዐይቶ ለችግሩ የሚፈልገውን ባይሰጠው ችግሩንም ባይቀርፍለት ይሻር። **አብጥሊስ ፲፱:-** ከምእመናን መካከል ዝሙት በማብዛት የወደቀ ካለ ይህም የዘወትር ልማድ ቢሆነው ወይም ግብረ ሰዶም የሚፈጽም ሰው ቢኖር ስለ ነፍሱና ስለ ንስሓው ልቅሶ ያብዛ። ከክህነት መሳርግ በየትኛውም አይሾም። **አብጥሊስ ፳፬:-** በመሳርጉ ከመሾሙ በፊት ሁለት ያገባ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ቢኖር ይሻር። የሾመውም ይሻር። የሾመው ኤጲስ ቆጶስ ለሹመት ያበቃው ግብሩን ሳያውቅ ከሆነ ግን የተሾመው ብቻ ይሻር። **አብጥሊስ ፳፮:-** ከካህናት ወይም ከሕዝባውያን ከአይሁድ ጋር ጾማቸውን የሚጾም ፋሲካንም

ከእነርሱ ጋር የሚያደርግ ወይም ከበዓላቸው ስጦታ ወይም ቂጣና የመሳሰለውን የተቀበለ ካህን ቢኖር ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነ ከቤተክርስቲያን ይሰናበት። **አብጥሊስ ፳፫:-** የቤተክርስቲያን የሆነ ንዋየ ቅድሳት ወይም የብር ዕቃ ማንም ወደቤቱ ወስዶ ሊጠቀምበት አይገባም። **አብጥሊስ ፳፪:-** ሐሜት፣ ስድብ፣ ሽንገላ፣ መሳለቅ፣ የሰውን ስም ማጥፋት፣ ለራሳቸው በእነርሱ ዘንድ የሌለውን መልካም ዜና አግዝፎ መናገር ይህ ሁሉ እግዚአብሔርን የመሳደብ ምሳሌ ነው። **አብጥሊስ ፳፯:-** ኤጲስ ቆጶስ ከመኳንንት ሥራ በምን ላይ አይሾም። ለሁለት ጌታ መገዛት የሚችል የለምና። **አብጥሊስ ፴:-** ምእመናን እነዚህን (ቀጥለው ያሉትን) መጻሕፍት ይጠብቁ። ቁጥራቸውም 81 ነው። ፩ ኦሪት ዘፍጥረት ፪ ኦሪት ዘጸአት ፫ ኦሪት ዘኍልቊ ፬ ኦሪት ዘሌዋውያን ፭ ኦሪት ዘዳግም ፮ መጽሐፈ ኢያሱ ፯ መጽሐፈ ሩት ፰ መጽሐፈ ነገሥት (፬ቱ) ፱ መጽሐፈ ዕዝራ (፪ቱ) ፲ ትንቢተ ሶፎንያስ ፲፩ ትንቢተ ሚልክያስ ፲፪ ትንቢተ ሚኪያስ ፲፫ ትንቢተ ኢዩኤል ፲፬ መጽሐፈ መክብብ ፲፭ መጽሐፈ ኢዮብ ፲፮ መዝሙረ ዳዊት ፲፯ መጽሐፈ ምሳሌ ፲፰ መኃልየ መኃልይ ፲፱ ትንቢተ ዕንባቆም ፳ ትንቢተ ሆሴዕ ፳፩ ትንቢተ ዘካርያስ ፳፪ ትንቢተ ኢሳይያስ ፳፫ ትንቢተ ኤርምያስ ፳፬ ትንቢተ ሕዝቅኤል ፳፭ ትንቢተ ዳንኤል ፳፮ መጽሐፈ ጥበብ ፳፯ መጽሐፈ ዮዲት ፳፰ መጽሐፈ ሲራክ ፳፱ መጽሐፈ ኩፋሌ ፴ የማቴዎስ ወንጌል ፴፩ የማርቆስ ወንጌል ፴፪ የሉቃስ ወንጌል ፴፫ የዮሐንስ ወንጌል ፴፬ የሐዋርያት ሥራ ፴፭ የጴጥሮስ መልእክታት (፪) ፴፯ የዮሐንስ መልእክታት (፫) ፴፯ የያዕቆብ መልእክት ፴፰ የይሁዳ መልእክት ፴፱ የጳውሎስ መልእክታት (፲፬) ፵ ራእየ ዮሐንስ ፵፩ የቀሌምንጦስ መጻሕፍት። **አብጥሊስ ፵፩:-** ቅዱሳት መጻሕፍትን ከጠበቃችኋቸው ድኅነት ታገኙባቸዋላችሁ። በመካከላችሁ ሰላምና አንድነት ይሆናል። ባትጠብቋቸው ግን ይፈረድባችኋል።

ቀኖና ዘስምዖን ቀነናዊ

ቁጥር ፩:- ኤጲስ ቆጶስ ይባርክ እንጂ አይባረክ። በሰዎች ራስ ላይ እጁን ይጫን። በእርሱ ላይ ግን ከሊቀ ጳጳሳት በስተቀር ማንም እጁን የሚጭን የለም። **ቁጥር ፪:-** ቂስ ካህናትን አይሹም። ግን ቀሳውስትና መኰሳት የገዳማት አስተዳዳሪዎች ከሆኑ ወደእነርሱ ለምንኩስና የመጣውን በገዳማቸው የፈለጉትን በአንድነት ያመንኩሱ። **ቁጥር ፫:-** ሊቀ ጳጳሳት መሻር የሚገባቸውን ሁሉ ይሽራል። ሊቀ ጳጳሳትን ግን መሻር የሚቻለው እንደእርሱ ያሉ ሊቃነ ጳጳሳትና የኤጲስ ቆጶሳት አንድነት ባሉበት ነው። **ቁጥር ፬:-** ቂስ በዲያቆናትና ከእነርሱ በታች በሆኑ ሕዝባውያን ራስ ላይ እጁን ይጫን ይባርክም። **ቁጥር ፭:-** ዲያቆን አይባርክም። በመዓርግ ከእርሱ በላይ ለሆኑት ደሙን ሊያቀብል አይችልም። በቤተክርስቲያን አገልግሎት ዲያቆን ከእርሱ የሚያንሰውን ማዘዝ ይችላል። በመዓርግ ከእርሱ የሚበልጠውን ግን ማዘዝ አይችልም። ዲያቆን ቀድሞ ጸሎት ማስጀመር አይገባውም። **ቁጥር ፮:-** በቤተክርስቲያን ካለው ሁሉ አራት እጁ ለኤጲስ ቆጶስ ነው። ሦስት እጁ ለቂስ፣ ሁለት እጁም ለዲያቆን ነው። ለሌሎች ሰዎች አንድ አንድ እጅ ነው። የእንስሳት በኩር ለካህናት ብቻ ይገባል **ቁጥር ፯:-** በነጋ ጊዜ ምእመናንና ምእመናት ሳይታጠቡ ምንም ሥራ አይሥሩ። ከዚያም ራስን በማስገዛት ወደ ፈጣሪያቸው ይጸልዩ። **ቁጥር ፰-፲፩:-** ሠራተኞች በየሳምንቱ ሁለት ቀን እንዲያርፉ አዘዝን። እነርሱም ቅዳሜና እሑድ ናቸው። ቤተክርስቲያንን ለማገልገልና እግዚአብሔርን ለመፍራት ለመዘከር ይገናኙባቸው። ቅዳሜ የምታርፉት እግዚአብሔር ያረፈባት ቀን ስለሆነች ነው። እሑድ የምታርፉት የዕለታት መጀመሪያ ስለሆነች ነው። በተጨማሪም የትንሣኤው ዕለት ስለሆነች

ነው። በመጨረሻው ሰዓት ፍርድና ኩነኔ የሚሰጥባትም ዕለት ናት። ቁጥር ፲፩፡- ምእመናን በሰሙነ ሕማማትና በሰሙነ ትንሣኤ እስከ ዳግማይ ትንሣኤ ድረስ ዕረፍት ያድርጉ። ሰሙነ ሕማማት ጌታ በሰውነቱ መከራ የተቀበለባትና የኀዘን ሳምንት ናትና። ሰሙነ ትንሣኤም የደስታ ሳምንት ነውና። ቁጥር ፲፪-፳፫፡- ምእመናን በዕርገት በዓል ይረፉ። በጸራቅሊጦስም ይረፉ። በዕለተ ብሥራትም (መጋቢት ፳፱) ይረፉ። በዕለተ ልደትም (ታኅሣሥ ፳፱) ይረፉ። በጥምቀት ዕለትም (ጥር ፲፩) ይረፉ። በዕለተ ስምዖንም (ግዝረተ ኢየሱስ) (የካቲት ፰) ይረፉ። በዕለተ ደብረ ታቦርም (ነሐሴ ፲፫) ይረፉ። በሐዋርያት የመታሰቢያ ቀንም ይረፉ። በእስጢፋኖስ በዓልም ይረፉ። በሌሎች ሰማዕታትና ቅዱሳን በዓልም ይረፉ። ቁጥር ፳፭-፴፩፡- የጸሎት ጊዜያት (ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት፣ ጸሎተ ሠለስቱ ሰዓት፣ ጸሎተ ነግህ፣ ጸሎተ ስድስቱ ሰዓት፣ ጸሎተ ተስዓቱ ሰዓት፣ ጸሎተ ሠርክ፣ ጸሎተ ምሴት፣ ጸሎተ መንፈቀ ሌሊት)። ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት የምንጸልየው ጌታ ለመፍረድ ይመጣል ብለን ተስፋ ስለምናደርግ ነው። ጠዋት የምንጸልየው ጨለማውን አስወግዶ ብርሃኑን ስላመጣልን ነው። ሦስት ሰዓት የምንጸልየው በክርስቶስ ላይ ሞት ስለፈረዱበት ነው። ስድስት ሰዓት የምንጸልየው ጌታ ስለተሰቀለባት ነው። ዘጠኝ ሰዓት የምንጸልየው የጌታ ነፍስ ከሥጋው ስለተለየባት ነው። በሠርክ የምንጸልየው ዕረፍትን ስላመጣልን ነው። በመኝታ ሰዓት የምንጸልየው ከጨለማ ፍጥረታት እንዲጠብቀን ነው። ቁጥር ፴፪፡- ምእመናን ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ባይቻላቸው በኤጲስ ቆጶሱ ቤት ይሰብሰቡ። በኤጲስ ቆጶሱ ቤት መሰብሰብ ባይችሉ እያንዳንዱ በያለበት ይጸልይ። ወይም ሁለትም ሦስትም ሆነው ይጸልዩ። አማኝ ከማያምኑ ሰዎች ጋር በአንድ ቤት ይጸልይ ዘንድ አይገባውም። ቁጥር ፴፫-፴፮፡- ለሞቱ ሰዎች በሦስተኛው ቀን፣ በሰባተኛው ቀን፣ በሠላሳኛው ቀን፣ በዓመቱ መታሰቢያ ያድርጉላቸው። ለሙት ዓመቱ ዕጣን ያሳርጉለት፣ ከገንዘቡም ለድሆችና ለምስኪኖች ይመጽውቱለት። ለዓላውያን ለክኃድያን ግን ይህን ሊያደርጉላቸው አይገባም። ቁጥር ፴፱፡- ለቀደሙት አባቶቻችን መጽሐፍ ወይን እንዳይጠጡ አላዘዛቸውም። ነገር ግን ለመስከር ወይን አትጠጡ ይላል። ቁጥር ፵፪፡- በሃይማኖት ምክንያት ካሳደዷችሁ ወደሌላኛዋ ሀገር ሽሹ። ቁጥር ፵፬፡- ዲያቆን በእጁ ያቆርብና ያጠምቅ ዘንድ ሕዝብንም ይባርክ ዘንድ አይገባውም። ቁጥር ፵፮፡- ከእኛ ከሐዋርያት ሊቃነ ካህናት ሦስት ወገን ነን፣ ቀሳውስትም በልዩ ሦስት ወገን ናቸው፣ ዲያቆናትም ሦስት ወገን ናቸው እነዚህም ዲያቆናት ንፍቅ ዲያቆናትና አናጉንስጢስ ናቸው። ቁጥር ፵፱-፶፡- ቅዱስ እስጢፋኖስ እስከ ዕለተ ሞቱ በዲቁናው ጸንቷል። ፈጽሞ ቁርባን አላቆረበም። በማንም ላይ እጁን አልጫነም። ቁጥር ፶፪፡- ኢትዮጵያዊው ጃንደረባን ያጠመቀው ፊልጶስና ጳውሎስን ያጠመቀው ሐናንያ ክህነትን ከሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ተቀብለው አጠመቁ። ቁጥር ፶፮፡- ጋኔን ላደረበት ሰው ጋኔኑ እስኪተወው ድረስ ቁርባን አያቁርቡት። ለሞት የሚደርስ ከሆነ ግን ይቀበሉት። ቁርባንም ያቁርቡት። ቁጥር ፶፰፡- ሴት ዘማዊት ብትሆን የዝሙት ሥራን ትተው። እምቢ ካለች ከእኛ ትባረር። ቁጥር ፶፱-፷፡- ወንድ ወይም ሴት ወደ ሕጋችን መግባት ቢፈልጉ ሰካራም ወይም ጣዖት አምላኪ፣ ተዋናይ ወይም ዘፋኝ፣ ወይም ዘፈን የሚያስተምር፣ ወይም ወደዝሙት የሚገፋፋ ቢሆን ሥራውን ይተው። እምቢ ካሉ ግን ከማኅበራችን ወጥተው ይባረሩ። ቁጥር ፷፩፡- ወታደር ከዝርፊያ፣ ከቅሚያና ከበደል ይራቅ። በሚሰጡት ደመወዝ ይኑር። ከዝርፊያ ከቅሚያ ከበደል ካልራቀ ግን ይባረር። ቁጥር ፷፯፡- ወደ ዘፈንና ወደ ዳንኪራ በጭፈራ ቤትም ወደሚደረገው ፉከራ ወይም ወደሚገዳደሉበት

የሚሄድ ካለ ይመለስ። ሥራውንም ይተው የአረመኔ ሥራ ነውና። እምቢ ካለ ይለይ። ቁጥር ፳፰:- ለሰው መልካም ነገርን የሚያስተምር ሕዝባዊ ቢኖር በቃሉ ጭምት ይሁን። በሥጋው ደግ ይሁን። አይኩራራ። አንደበተ ርቱዕ ይሁን። ከዚያ በኋላ ሰውን ያስተምር።

ቀኖና ዘቀሌምንጦስ

ቀኖና ፩:- ሊቀ ጳጳሳት ያለ ኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤና ያለ ጳጳስ መኖር አይሾምም። ቀኖና ፪:- ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ እንዲሾም ያመጡት (የመረጡት) ሰው ሹመቱ የሚሰጠው በአገሩ ሰዎች ስምምነት ይሁን። የሚሾመው ጳጳስ ወይም ሊቀ ጳጳስ ይሁን። በሹመቱ ጊዜ ሁለት ወይም ሦስት ኤጲስ ቆጶሳት መኖር አለባቸው። ቂስና ዲያቆንን እንዲሁም ከዚያ በታች ያሉትን ኤጲስ ቆጶሱ ብቻውን ይሹማቸው። ቀኖና ፫:- በቁርባን ጊዜ ሕግ ተላልፎ በመሥዋዕቱ ላይ ማር ወይም ወተት ወይም በወይን ፋንታ ስኳር ወይም ጠጅ ያቀረበ ኤጲስ ቆጶስም ቢሆን ቂስም ቢሆን ዲያቆንም ቢሆን ከክህነቱ ይሻር። ንጹሕ ከሆነ ስንዴ ጎብስትና ከጠራ የወይን ፍሬ በስተቀር ከአዕዋፍም ቢሆን ከእንስሳትም ቢሆን ይህን ያደረገ ከሹመቱ ይሻር። ስንዴው ያልከረመና የመጀመሪያ ፍሬ የሆነ ይሁን። የወይኑ ፍሬም ያልቆየ ፍሬውን ውኃ የሞላውና የሚጣፍጥ ይሁን። ቀኖና ፬:- ቤተክርስቲያንን ለማገልገል የተመደበ ከዓለም ሥራ ምንም አይሥራ። እንደዚህ ቢሠራ ይሻር። ቀኖና ፭:- ፋሲካን ከአይሁድ ፋሲካ ቀጥሎ ባለው ከእሑድ በስተቀር በአንድ ቀን ከእነርሱ ጋር ያደረገ ከሹመቱ ይሻር። ቀኖና ፮:- በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወደ ቤተክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር ቅዱሳት መጻሕፍትንም ቢሰማ ቅዳሴ እስከሚጨርሱ ድረስ ባይታገሥ ቁርባንም ባይቀበል ከቤተክርስቲያን ይውጣ። በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምን አቃሏልና። ቀኖና ፯:- በውግዘት ምክንያት እንዳይቆርብ ከተከለከለና ከተባረረ ሰው ጋር የተነጋገረ ወይም በጸሎት የተሳተፈ ወይም ለምሳ ወደ ቤቱ የጠራው ሰው ቢኖር ይባረር። ቀኖና ፰:- ካህኑን የሾመው ኤጲስ ቆጶስ ሳይፈቅድለት አገሩን ትቶ ወደሌላ ሀገር የሄደ ካህን ቢኖር እንደካህን ቆጥረው አይቀበሉት። ቢቀበሉት ግን የተቀበለውም ይባረር። እርሱም ይባረር። ቀኖና ፱:- ካህን ድንግል ያልሆነችውን ቢያገባ በማናቸውም የክህነት መዓርግ ላይ ሊሾም አይገባም። ቀኖና ፲:- የእኅቱን ልጅ ወይም የወንድሙን ልጅ ያገባ ካህን ቢኖር ከክህነት መዓርግ በየትኛውም ላይ ሊሾም አይገባውም። ቀኖና ፲፩:- ራሱን የሰለበ ምእመን ቢኖር ለሦስት ዓመታት ከቤተክርስቲያን ይታገድ። ካህን ቢሆን ከሹመቱ ይሻር። ቀኖና ፲፪:- ካህን ቢሰርቅ፣ በዝሙት ቢገኝ፣ በሐሰት ሲምል ቢገኝ ከክህነቱ ይሻር። ቀኖና ፲፫:- ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቂስ ወይም ዲያቆን አንድን አማኝ ቢማታ ከመዓርጉ ይሻር። ቀኖና ፲፬:- ባደረሰው በደል ምክንያት ወይም በትክክል በሥልጣነ ክህነት ከእርሱ በሚበልጠው ሰው ሥልጣኑ በመያዙ ከቤተክርስቲያን የተባረረ ኤጲስ ቆጶስም ቢሆን ዲያቆንም ቢሆን ይህ የሥልጣን መያዝና ግዝት ሳያግደው ያለፍርሀትና ያለመገረም በግድ አገልግሎቱን ቢቀጥል ውግዘቱን አቃሎም ቢያገለግል እስከ መጨረሻው ከቤተክርስቲያን ይወገድ። ቀኖና ፲፭:- አንድ ኤጲስ ቆጶስ ከሩቅ ሀገር የመጡ ሌላ ኤጲስ ቆጶስን ወይም ቀሳውስትን ወይም ዲያቆናትን አይቀበል። ማንነቱን የሚገልጽ ደብዳቤ ያለው ካልሆነ በስተቀር እንደ ካህናት አያድርጉት። ደብዳቤ ካላቸው ምግባራቸውን ይጠይቁ። ቀኖና ፲፮:- ጳጳስ ባልተሾመበት ሀገረ ስብከት ቀሳውስትንና ዲያቆናትን መሾም አይገባውም። ሕግ ከተላለፈና ያለዚያ ሀገረስብከት ሰዎች ፈቃድ እንደዚህ ካደረገ ይሻር። የሾማቸውም ይሻሩ። ቀኖና ፲፯:- ኤጲስ ቆጶስ ከግማሽ በላይ ያሉ ምእመናን ከመረጡት

ይሾም። ከዚህ በኋላ የሚቃወሙ ካህናት አይኑሩ። ካሉ ግን አልተስማሙምና ይሻሩ። ቀኖና ፶፪:- ኤጲስ ቆጶስም ቢሆን ቄስም ቢሆን ዲያቆንም ቢሆን ከአበደረው ገንዘብ ወለድ የሚፈልግ ከሆነ ይህን ሥራውን ካልተወና ካልተመለሰ በስተቀር ከመዓርጉ ይሻር። ቀኖና ፶፫:- ያለምክንያት ሚስቱን ከቤቱ ያስወጣት ወይም ሌላዋን በዝሙት የተፈታችውን ሴት ያገባ ሕዝባዊ ሰው ቢኖር ከቤተክርስቲያን ይሰናበት። ቀኖና ፶፮:- እግዚአብሔር የፈጠረው ጥሩ እንዳልሆነ የሚሳደብና የሚክድ ከእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ይሻር። ቀኖና ፶:- ኤጲስ ቆጶስን የሰደበ ወይም የረገመ እንደ ሰነፍም የቆጠረ ከመዓርጉ ይሻር። እንደዚሁም ኤጲስ ቆጶስ ካህንን ቢረግም ወይም ቢሳደብ እርሱም ይሻር። ቀኖና ፶፩:- ከካህናት ወገን ወይም ከምእመናን ቄስን ወይም ዲያቆንን የሰደበ ወይም የረገመ ቢኖር አስቀድመን እንደተናገርነው ይለይ። ቀኖና ፶፪:- ከካህናት ወገን ወይም ከሕዝባውያን መስማት በተሳነው ሰው ላይ ወይም በዕውር ወይም በአንካሳ ወይም ድውይ ወይም ሽባ ላይ የተሳለቀ ወይም የሳቀ ሰው ቢኖር ይሻር። ቀኖና ፶፫:- ኤጲስ ቆጶስ ሕዝቡን ባያስተምራቸው ይሻር። ቀኖና ፶፬:- በአንድ አገር ላይ የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ቢኖርና ከካህናት የተቸገረ ሰው አይቶ የሚፈልገውን ባይሰጠው ችግሩንም ባያስወግድለት በአጋጠመው ችግርም ባይረዳው ይሻር። ቀኖና ፶፭:- ከካህናት ወገን ወይም ከሕዝባውያን አይሁድን ወይም አረመኔን በመፍራት የእግዚአብሔርን ሕግ የካደ የሕጉን ሥራም ያልገለጸ የክርስቶስን ስም ለመካድና ለመበደልም መርሕ የሆነ ከመዓርጉ ይሻር። ንስሓ ከገባ ግን ከምእመናን ወገን አድርገው ይቀበሉት። ቀኖና ፶፮:- ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ወይም ከካህናት ሌላው ያልታረደ ሥጋ የበላ፣ ወይም ተኩላ የነከሰው ወይም በክት ወይም ሌላ የሞተ ነገር የበላ ከሹመቱ ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነም ይባረር። ቀኖና ፶፯:- ከቀዳም ስዑር ውጭ ቅዳሜ እና እሑድ ሲጾም የተገኘ ካህን ከሹመቱ ይሻር። ሕዝባዊ ቢሆን ከቁርባን ይከልከል። ቀኖና ፶፰:- ከሌላ ሰው ጋር የተጣላ ካህን ቢኖር ቢመታውና ቢሞትበት ከሹመቱ ይሻር። ሕዝባዊ ቢሆን ደግሞ ከቤተክርስቲያን ይሰናበት። ቀኖና ፶፱:- ዳግመኛ የተሾመ ካህን ካለ ከሹመቱ ይሻር። የሾመውም ይሻር። [ቀድሞ የተሾመው ከክኃድያን ከሆነ ግን ያ ስለማይቆጠር ሁለተኛ ነው አይባልም]። ቀኖና ፷:- ከአይሁድ በበዓላቸው ቂጣና የመሳሰሉ ስጦታዎችን የሚቀበል ካህን ከሹመቱ ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነ ከሕዝብ ይለይ። ቀኖና ፷፩:- ከካህናት ወይም ከምእመናን ለአይሁድ ምኩራብ ወይም ለአማልክት መስገጃ ቦታ ወይም ለጠንቋዮች ወይም ለክኃድያን አብያተ ክርስቲያን የሚያበሩት ዘይት ወይም መብራት ቢልክ ከቤተክርስቲያን ይሰናበት። ቀኖና ፷፪:- ከተቀደሰ ልብስ ጀምሮ ሁሉም የቤተክርስቲያን ሀብት ወይም የብር ገንዘብ ሰው በቤቱ ሊሠራባቸው አይገባም። ቀኖና ፷፫:- ኤጲስ ቆጶስ ክህነትን መውረስ ወይም ማውረስ አይገባውም። ቀኖና ፷፬:- ወታደር ሆኖ የቤተክርስቲያን ሹም ለመሆን የሚፈልግ ካህን ካለ ይሻር። ቀኖና ፷፭:- ከመሳፍንት አንዱ በፍርድ ሳይገፋው ያለ አግባብ ንጉሥን የሰደበ ወይም የረገመ ካህን ከሆነ ይሻር። ሕዝባዊ ከሆነ ይባረር። ቀኖና ፷:- ለቀሌምንጦስ የነገርነው ፷፭ መጽሐፍ ነው። እነዚህም:- ፩) ኦሪት ዘፍጥረት ፪) ኦሪት ዘጸአት ፫) ኦሪት ዘሌዋውያን ፬) ኦሪት ዘኍልቊ ፭) ኦሪት ዘዳግም ፮) መጽሐፈ ኢያሱ ፯) መጽሐፈ መሳፍንት ፰) መጽሐፈ ሩት ፱) መጽሐፈ ዮዲት ፲) መጽሐፈ ጦቢት ፲፩) መጽሐፈ አስቴር ፲፪) መጽሐፈ መቃብያን (፫) ፲፫) መዝሙረ ዳዊት ፲፬) መጻሕፍተ ሰሎሞን (፫) ፲፭) መጻሕፍተ ነገሥት (፬) ፲፮) መጽሐፈ ሲራክ ፲፯) መጽሐፈ ኢዮብ ፲፰) መጽሐፈ ዕዝራ (፫) ፲፱) ትንቢተ

ኢሳይያስ ፳) ትንቢተ ኤርምያስ ፳፩) ትንቢተ ሕዝቅኤል ፳፪) ትንቢተ ዳንኤል ፳፫) ትንቢተ አሞጽ ፳፬) ትንቢተ ዮናስ ፳፭) ትንቢተ ዕንባቆም ፳፮) ዖዝያ (ትንቢተ ሆሴዕ?) ፳፯) ትንቢተ ናሆም ፳፰) ትንቢተ ሶፎንያስ ፳፱) ትንቢተ ዘካርያስ ፴) ትንቢተ ሚኪያስ ፴፩) ትንቢተ ሚልክያስ ፴፪) ወንጌል (፴) ፴፫) መልእክታተ ሐዋርያት (፶) ፴፬) የጳውሎስ መልእክታት (፲፬) ፴፭) የሐዋርያር ሥራ ፴፮) ራእየ ዮሐንስ ፴፯) መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ቀኖና ፹፩:- እንድትቀበሏቸው በቀሌምንጦስ እጅ ያዘዝናችሁ መጻሕፍት 8 የቀኖና መጻሕፍት ናቸው።

ጦማር ዘጴጥሮስ

ቁጥር ፩:- ለጥምቀት በዋጋ መማለጃ የተቀበለ የተሻረና የተወገዘ ነው። ቁጥር ፫:- ልጄ ሆይ የክህነትን ስጦታና የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በገንዘብ አትሸጥ። በክህነት ላይ አትነግድ። ቁጥር ፮:- በክህነት መማለጃ የሰጠም የተቀበለም ክህነት የለውም። ቁጥር ፯:- የበደለህን በየሰባቱ ሰባ ጊዜ ይቅር በለው። ቁጥር ፰:- ከኃጢአቱ ንስሓ የሚገባን ተቀበለው የበደለውንም ይቅር በለው። በእጅህም አንሣው ገሥጸውም። የታመመ-ትን ጎብኝ፣ የተራቡትን አብላ፣ የተጠሙ-ትን አርካ፣ የተራቆቱትን አልብስ፣ ወደታሠሩትም ሂድ። ቁጥር ፱:- ከእግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን ስማ። ቁጥር ፲፩:- አባት እናት ለሌለው እራራለት። በራስህ ላይ ለሰይጣን መንገድ አትስጥ። ቁጥር ፲፫:- ችግረኛ ካህን ካየህ ከተቀበልከው ገንዘብ እርዳው። ቁጥር ፲፬:- ለአብያተ ክርስቲያናት፣ ለአድባራትና ለገዳማት ግንባታ ራስህን አትጋ። ቁጥር ፲፮:- ችግረኛን ከቤትህ በር ላይ አታባረው። ቸል ቸል አትበለው። አትናቀው። አታቃለው። ከአንተ ጋርም በማዕድህ እንዲቀመጥ አድርገው። ቁጥር ፲፱:- ምእመናንን ለመጥቀም ካልሆነ በስተቀር ወርቅና ብር አትሰብስብ። ቁጥር ፳-፳፩:- ለምእመናን ልጆች ሰላምን አብዛ። ልጄ አረጋውያንን አክብራቸው። ነገራቸውንም ስማቸው። ገሥፀው ንገረው እንጂ በኃጢአቱ ምክንያት በሰው ላይ አትሳለቅ። እግዚአብሔርን ወደ መፍራትም በየዋህነት መልሰው። ቁጥር ፳፪:- ቀጥተኛ በሆነ ነገር ነገሥታትን እዘዛቸው። በመጥፎ ሥራቸው ውቀሳቸው። ቁርባን መቁረብ ጥፋትን ይከላከላል። ቁጥር ፳፫:- በ3ኛው፣ በ7ኛው፣ በ12ኛው፣ በ30ኛው፣ በ40ኛው፣ በ60ኛው ቀን ሙታንን አስቧቸው። ልጄ ሆይ የተጠመቀ ኃጢአተኛ ነፍሱ በሞተ በ40ኛው ቀን ከክርስቶስ ፊት እንደምትቀርብ እወቅ። እንደ ሥራውም ይከፈለዋል። ቁጥር ፳፬:- ምእመናን የመለኮትን የተቀደሱ መጻሕፍት ለመስማት በእግራቸው ይቁሙ። ለመጠመቅ የሚፈልግን ሰው በውኃ ከመጠመቁ በፊት የደስታ ቅባት ቀባው። ከተጠመቀ በኋላ ደግሞ ቅብዐ ሜሮን ቀባው። ቁጥር ፳፱-፴:- ያልተጠመቀ ሰው ያረደውን አይብሉ። የአይሁድን ቂጣ አትብሉ። ከእነርሱ ጋር አትጋቡ። ቁጥር ፴፪:- አማኝ ሆይ መተኛት በፈለግህ ጊዜ ፊትህን አማትብ። ከሰማዕታት አዕም ተባረክ። ቁጥር ፴፫:- ካህን ሆይ ከንጹሕ ስንዴ በቀር በመሥዋዕቱ ላይ ስብና ሥጋ አታቅርብ። በመሠውያው ላይም አታስቀምጥ። ከወይን ፍሬ በስተቀርም ከጠጅ መሥዋዕት አትሥራ። የስንዴ እሸት በደረሰ ጊዜ የተለቀመ ይሁን። ቁጥር ፴፭:- የፋሲካ በዓል ከሁሉም በዓላት ይበልጣል። ይክብራልም። ከደስታ በስተቀር ሐዘን አይደረግበትም። ቁጥር ፴፮:- በቅዳሴ ጊዜ ሙታንን ሁልጊዜ አስታውሱ። እጅግ ይጠቅማቸዋልና። ቁጥር ፴፯:- ከቂጣ በዓል በኋላ በሚውለው እሑድ የፋሲካን በዓል አክብሩ። ቁጥር ፴፱:- የሕጉን ታቦት ሁሉ ባርክ። በእግዚአብሔር ማኅተም አትመው። በምትባርከው ጊዜ ሰባት ቀሳውስት ከአንተ ጋር ይኑሩ። ክህነትን ለመስጠትም በቅብዐ ሜሮን አትም። እንዲሁም ንጉሥን ለማንገሥ አትም። ቁጥር

፱፩:- ከሊቀ ካህናት ሳያገኝ ክህነትን ነጥቆ የወሰደ ሰው ቢኖር ከእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ይሰናበት። ቁጥር ፱፪:- በሰንበታትና በበዓላት የዮሐንስን ወንጌል በመሠውያው ላይ ያንብቡ። እርሱ የመለኮትን ምሥጢር የሚናገር ነውና። ቁጥር ፱፫:- በሁሉም ቤተ መቅደስ ውስጥ ሁለት መሠውያ ይኑር። አንዱ ከቦታ ወደቦታ የሚንቀሳቀስ፣ ሁለተኛው ከቦታው የማያነቃንቁት ይሁን። ቁጥር ፱፬:- ሕዝባዊ ካህንን ቢሰድበው ወይም ቢረግመው እግዚአብሔር ከሚመለክባቸው አገሮችና ከቤተክርስቲያኑ ይሰደድ። ቁጥር ፱፭:- ከምእመናን ኃጢአቱ የበዛ ሰው ቢኖርና እንዲወገድለት ቢፈልግ ኃጢአቱን ለካህን እና የእግዚአብሔርን መጻሕፍት ለሚያውቁ ሊቃውንት ይግለጣት። ቁጥር ፱፮:- የክህነት ልብስ ከሌሎች ሕዝባውያን ልብሶች የተለየ ይሁን። ልብሱ ከመጠምጠሚያው በስተቀር ሰፊ ይሆን ዘንድ ይገባል። ቁጥር ፱፯:- ካህን ቀን መዝሙረ ዳዊትን ያንብብ፣ ሌሊት ደግሞ የነቢያትን ምስጋና ያንብብ።

ዲድስቅልያ

ስምንቱ የሕግና የሥርዓት መጻሕፍት የሚባሉት:- ፩) ሥርዓተ ጽዮን ፪) ትእዛዝ ፫) ግጽው ፬) አብጥሊስ ፭) ፩ኛ መጽሐፈ ኪዳን ፮) ፪ኛ መጽሐፈ ኪዳን ፯) ቀሌምንጦስ ፰) ዲድስቅልያ ናቸው። ዲድስቅልያ ማለት ትምህርት ማለት ነው። የጽርእ ቃል ነው። ዮሐንስ ቅዱስ ጴጥሮስን አበ ዓለም ይለው ነበር። ይህንን ዲድስቅልያ የተባለ መጽሐፍ ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ከተማ ተሰብስበው ሠርተውታል። አንቀጽ ፩፣፪:- በቤተክርስቲያን ያሉ የሹመት መዓርጋት በሰማያት ባለው አምሳል እንዲሆን አዘዝን። ፬:- ኤጲስ ቆጶሱ እንደ ጠባቂ ነው። ቀሳውስትም መምህራን ናቸው። ዲያቆናትም አገልጋዮች ናቸው። ንፍቀ ዲያቆናትም ረዳቶች ናቸው። አናጉንስጢሳውያንም በማስተዋል የሚያነቡ ናቸው። አብስሊድሳውያን መዘምራን ናቸው። ፭:- (ምእመናን) የትምህርቱን ቃል ያስተውሉ። ፬:- ለእግዚአብሔር ደስ የማያሰኘውን ሥራ አትሥራ። ፯:- ለራሳችሁ የሚበልጠውን ክፍል መውሰድን፣ ለወንድሞቻችሁ ግን ጥቂት መስጠትን አትውደዱ። ፯፮:- የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ብሩህ ሕጉን የሚጠብቁ ሰዎች ይቅርታንና ምሕረትን ያገኛሉ። ለራስህ የምትጠላውን በባልንጀራህ ላይ አታድርግ። አንተ ሌላው ሰው ሚስትህን ያይ ዘንድ ማንም በተንኮል ያስታት ዘንድ እንደማትወድ እንደዚሁ አንተም የሌለውን ሚስት በክፉ ሕሊና አታስብ። ለራስህም መርገምን ስድብንና መመታትን እንደማትወድ እንደዚሁ አንተም በሌላው አታድርግ። ፯፱:- የረገመህም ቢኖር አንተ ግን መርቀው። ፹፪:- ወዳጆቻችን ሆይ የብርሃን ልጆች እንሆን ዘንድ ትእዛዛትን እናስተውል። እርስበእርሳችን ትዕግሥትን እንያዝ። ፹፫:- ወንድ ሚስቱን ይታገሣት። ትዕቢተኛና ግብዝም አይሁን። ነገር ግን የሚራራና ቅን ይሁን። ለብቻዋም በፍቅርና በትሕትና ደስ ያሰኛት። ፹፮:- የራስህን ጠጉር አታሳድግ፣ ጠጉርህን ቁረጥ። ፹፱:- ጽሕማችንን እንላጭ ዘንድ ለእኛ አይገባም። ፺:- እግዚአብሔርን ደስ ታሰኘው ዘንድ ከወደድህስ ክፉ ሥራን አትሥራ። ፈጣሪህም የሚጠላውን ሁሉ ከአንተ አርቅ። ሰካራም አትሁን። በእጆችህ ሥራ ትረህ ግረህ ተመገብ። አንቀጽ ፪፣፭:- ሥራ ፈት ሆነህ አትኑር። በነገሥትና በነቢያት መጽሐፍ ውስጥ ያለውንም ተመልከት። የምስጋና መዝሙርን ዘምር። የሕግ ሁሉ ፍጻሜ የሚሆን የወንጌልንም ቃል ስማ። ፪:- ለማይረባ ለማይጠቅም ለከንቱ ነገር ሁሉ አትጨነቅ። ከወንጌል ልዩ የሚሆን ሕግንና ሃይማኖትን ለውጠው የሚያጠፉ ሐሰተኞች መምህራንን አትሻ። ፴፮:- በሃይማኖትና በኅ በመሥራትም እንጽና። ከክፉ ሥራም ሁሉ እንራቅ። አንቀጽ ፫፣፭:- ሴት ለባሏ በትሕትና

ትታዘዝ። ፳፰:- ክፉ ሴት ለራሷ ውርደትን ታመጣለች። ፳፱:- ያመኑ ሴቶች ራሳቸውን በንጽሕና ሊከናነቡ ይገባል። የፊታቸውን ውበት በማሳመርና ቀለም በመቀባት አይደለም። እግዚአብሔር በፊጠረው መልክ ውስጥ ጥቅም በሌለው ኩል መኳልና ማጌጥም አይደለም። እንዲህ ያለውን ሁሉ አይሥሩ። ነገር ግን እነርሱ ተከናንበው በጎዳና ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ይሂዱ። **አንቀጽ ፬** ይህ አንቀጽ ስለ ኤጲስ ቆጶስ ይናገራል። ፩-፬:- ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ የሚሾመው 50 ዓመት የሞላው፣ ነገር የማይሠራ ሊሆን ይገባል። ሀገሪቷ ትንሽ ብትሆንና 50 ዓመት የሞላው ባይገኝ አዋቂና ብልህ እድሜው ጥቂት የሆነ መሾም ይችላል። ፭-፲፩:- ኤጲስ ቆጶስ የሚሾም ሰው ቂም፣ ክፋትና ዐመፅ የሌለበት ልበ ንጹሕ ይሁን። የማይቆጣ፣ የማይሰክር፣ የማይበቀል፣ ጸብና ክርክር የሌለው፣ የማይሳደብ ይሁን። ፲፪:- የኤጲስ ቆጶስ ምግቡ የላመ የጣመ ይሁን። መጥኖ ይመገብ። ሕዝቡን መክሮ አስተምሮ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ይቻለው ዘንድ። ከክፉም ሁሉ ይርቅ ዘንድ መጻሕፍትን ሁልጊዜ ይመልከት። ፲፬:- ኤጲስ ቆጶስ ማንንም ቸል አይበል። መኳንንቱን አይከተል። እግዚአብሔርን ይፍራ። ፲፭:- የሚያስተምረውን የሚሠራ ሰው በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይሆናል። ፲፮:- ኤጲስ ቆጶሳት ሕዝቡን አስተምራችሁ ከስሕተት ታድኗቸው ዘንድ ለእናንተ ይገባል። ፲፱:- ሰው ሐሰትን በላዩ የተናገረበት ቢኖርም ብፁዕ ነው። ፳፮:- ለኤጲስ ቆጶሱ እውነትን ይመረምር ዘንድ ይገባዋል። ከማንም መማለጃን አይቀበል። ፳፱:- ኤጲስ ቆጶስ ባያስተምርና ባይገሥፅ በቅንነት መንገድም ባይሄድ ውግዘት ያገኘዋል። ፴:- በደል ሳይኖርባቸው ንጹሓንም ሲሆኑ በኤጲስ ቆጶሱ ላይ በሹማምንቱም ላይ የሚበድል ቢኖር ወደ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሊገባ አይገባውም። ደፍሮ በራሱ ፈቃድ በስንፍና ኖሯልና። ፴፪:- ሰው ሆይ እወቅ አስተውልም። በዚህ ዓለም ብትበድል ኃጢአትንም ብትሠራ ንስሓም ባትገባ ድኅነት አይኖርህም። ፴፫:- ለኤጲስ ቆጶሱ በእውነት አስተውሎ ይፈርድ ዘንድ ይገባዋል። ፍርድ ለእግዚአብሔር ነውና። ፴፮:- ድል የነሣ ሰው የድል አድራጊነቱን አክሊል ይቀበላል። እግዚአብሔር ጻድቅን ከኃጥእ ጋር አይቀጣምና። ፴፱:- ኃጥአን በጻድቃን እንደማይቀጡ፣ ጻድቃንም በኃጥአን እንደማይቀጡ የታወቀ ነው። **አንቀጽ ፭፣፷፩:-** ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም። አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም። ፵፩:- ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ። **አንቀጽ ፮፣፩:-** እግዚአብሔር ያለምሕረት በማክበድና በልብ ተንኮል የሚፈርዱትን አይወድም። ፫:- አሁንም ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን በደስታና በፍቅር ንስሓቸውብ እንቀበል። የበደሉትንም ለንስሓ እንደሚገባ በፍቅርና በምሕረት እንፍረድላቸው። ፬:- ኀጢአትን የሚሠራ በስሕተትም የሚሰነካከል ሰው ብታይ ከወደቀበት አንሣው። ሥራውን ብታጣጥምለት ግን እነሆ ወንድምህን ገደልከው። ፱:- ለኃጢአተኛ ሰው ያዘንና ይተክዝ ራሱንም ይንቅ ዘንድ ይገባዋል ፲፫:- ያገኘውን ሁሉ የሚነክስ እብድ ውሻ ካልገደሉት የነከሳቸው ሁሉ በአንድነት ከእርሱ ጋር እንደሚያብዱ እንዲሁ የሚዘብት፣ የሚያስት፣ ክርክርንም የሚያመጣ፣ በሕግ ያለውንም ትእዛዝ የሚያፈርስ ሰው ቢኖር የእግዚአብሔርን ቤት እንዳያጠፋ ከቤተክርስቲያን ወደ ውጭ ያውጡት። ፲፬:- ስለ ኃጥአንና ስለ ዐመፀኞች ዝም እንል ዘንድ አይገባንም። ነገር ግን ክፉ ሥራቸውን ይተው ዘንድ እንምከራቸው። እግዚአብሔርንም መፍራትን ይማሩ ዘንድ እንዘዛቸው። ፲፮:- ኤጲስ ቆጶስ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ያዝን ዘንድ ይገባዋል። ፲፯:- ሕዝቡን በሰላም ይጠብቃቸው ዘንድ ለኤጲስ ቆጶሱ አግባብ ነው። ፳፰-፳፱:- ቸር እረኛን የማይከተል ይጠፋ ዘንድ ለጅብ እንደሚሆን እንደዚሁ

ሰነፍና ክፉ እረኛን የሚከተል ለሞት ይሆናል። ራሱ እረኛው ይውጠዋልና። ስለዚህ ከማይራሩና መንጋቸውን ከማያድኑ ከክፉዎችና ከከዳተኞች እንርቅ ዘንድ አግባብ ነው። ነገር ግን የሚራሩና መንጋቸውን የሚያድኑ ቸሮች እረኞችን እንከተላቸው። ፴፩:- ኤጲስ ቆጶሱ ሕዝቡን እንደ ልጆቹ ሊወዳቸው ይገባል። እነርሱ ልጆቹ ናቸውና። የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምራቸው። ሥርዓትን አያክብድባቸው። ፴:- ለኤጲስ ቆጶስ ኀጢአት በመሥራት የታመመ ድውያንን ያድን ዘንድ፣ ይጎበኛቸውና ያጽናናቸው ዘንድ ቁስላቸውንም ያድናቸው ዘንድ ይገባዋል። ፴፩:- የክርስቶስን መንጋዎች ሳትቆጣ በሥልጣንህም ሹመት ሳትታበይ በትሕትናና በፍቅር ጠብቅ። የክርስቶስ መንጋዎች ጠባቂ አንተ ነህና። **አንቀጽ ፯፣፩:-** ያልበደለውን የሚያሳድድ ሰው ከነፍሰ ገዳይ ይከፋል። ፬:- ኤጲስ ቆጶስ ለቤተክርስቲያን ከሚገባው አሥራትና ከእህሉ ቀዳምያት ይመገብ። ፬፩:- ኤጲስ ቆጶሱም ለድኃዎች፣ የዕለት ራት ለሌላቸው ጦም አዳሪዎች፣ ለባልቴቶች፣ እናትና አባት ለሞቱባቸው ልጆች፣ ለስደተኞች፣ ምንም ለሌላቸው መፍቅዳቸው ይሰጥ ዘንድ ይገባዋል። ኤጲስ ቆጶሱ ግዳጃቸውን ባይሰጣቸው ግን ስለእነርሱ እግዚአብሔር ይመራመረዋል። ፭፭:- ያልነጹትን እንስሳት በኩራትና የሰውን በኩራት መቤዠት ነው። **አንቀጽ ፭፣፱:-** ዲያቆናዊት ሴት ያለዲያቆኑ ፈቃድ ምንም ምን አትሥራ። ማንኛዋም ሴት ከዲያቆናዊት ጋር ካልሆነች በቀር ወደ ዲያቆኑ አትሂድ። እንደዚሁም ሴት ከዲያቆኑ ጋር ካልሆነች በቀር ወደኤጲስ ቆጶሱ አትግባ። ፲:- እንግዲህ ካህናትን አክብሯቸው ይመክሯችኋልና። የእግዚአብሔርንም መንገድ ያስተምሯችኋልና። ፲፩:- ኤጲስ ቆጶሱ ለተቸገሩት ሁሉ ያዝን ዘንድ ሕይወታቸውንም ይመረምር ዘንድ ኑሯቸውንም ይረዳ ዘንድ ይገባዋል። ፲፱:- ዲያቆናት የሕዝቡን ችግር ሁሉ ለኤጲስ ቆጶሳት ይነግሯቸው ዘንድ ይገባል። ፳፪:- ኤጲስ ቆጶሳት የእግዚአብሔር አፍ እንደሆኑ እናስብ። **አንቀጽ ፱፣፩:-** ዲያቆን ለኤጲስ ቆጶሱ መልእክተኛ ነው። ፯:- ከእግዚአብሔር በታች አባት ለሆነህ ለኤጲስ ቆጶሱ እጅ ንሣ። ፲፪:- ክህነት ከመንግሥት ትበልጣለች። **አንቀጽ ፲፣፲፰:-** ኤጲስ ቆጶስ ሆይ ኃጥአንን እርዳቸው በእግዚአብሔር ቃልም አጽናናቸው። አትናቃቸው ከእነርሱም ጋር መብላትን እንቢ አትበል። ጌታችን ከኀጢአተኞችና ከቀራጮች ጋር መብላትን እንቢ አላለምና። ፳፪:- ኤጲስ ቆጶስ ሆይ ንኡሰ ክርስቲያንን በምታጠምቅበት ጊዜ እንዲህ አድርግ። ተቀብለህ በላያቸው ላይ እጅህን ጫንባቸው። በንስሓ ነጽተዋልና። ፬:- ኤጲስ ቆጶስ ሆይ አንተም እንደ ብልህ ባለመድኃኒት ኃጥአንን አድናቸው። ከኃጢአት ቁስልም ፈጽመህ አድናቸው። ፳፩:- ከቤተክርስቲያን ሹሞች በቀር ሕዝባዊ አይፍረድ። ሽማግሌዎችም አይፍረዱ። ፳፪:- ምሥጢራችሁን ያውቁ ዘንድ ለአሕዛብ አትፍቀዱላቸው። ፳፮:- ሐሰትን ከመናገር ተጠበቁ። ሐሰትን የሚናገር ሰው በብዙ ይፈረድበታልና። ፳፯:- የዋሆች፣ የማይቆጡ፣ ንጹሓን፣ ቸሮች፣ ትሕትናን የሚወዱ፣ የታመኑ፣ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሰዎች ምስክር ይሆኑ ዘንድ አግባብ ነው። የንጹሓን ሰዎች ምስክርነት ይገባልና። ፳፱:- ለፍርድ ወደ እናንተ የመጣ ሰው ቢኖር ግብሩና ልማዱ እንዴት እንደሆነ ሕይወቱን መርምሩ። ፴፪:- የከሰሰ ሰው ቢኖር ሁለቱም በአንድነት በአደባባይ ሳይኖሩ ለአንዱ አትፍረዱ። (ከሳሹም ተከሳሹም መኖር አለባቸው)። **አንቀጽ ፲፩፣፫:-** የወንድምህን በደል አራት መቶ ዘጠና ጊዜ ይቅር ብትል ግን ራስህን ታድን ዘንድ ቸርነትህ የበዛ ቁጣህም ያነሰ ሆንክ። እንዲህም ብታደርግ የሰማያዊ አባትህ ልጅ ትሆናለህ። ፬:- ኤጲስ ቆጶሳት ሆይ ቅዱሳት መጻሕፍትን አንብቡ። ፭:- ኤጲስ ቆጶሳት ሰላምን የሚያደርጉ፣

እነርሱንም የበደሏቸውን ይቅር የሚሉ፣ ርኅሩኃን ወይ እግዚአብሔር የሚመለሱትንም ንስሓቸውን የሚቀበሉ ይሆኑ ዘንድ አግባብ ነው። ፳፪:- በንስሓ ፈጽማ የዳነችውን ነፍስ በቁጣና በብስጭት አትግደሉ። ፴:- እንግዲህ ቤተክርስቲያን እንዲህ ትሁን። ርዝመቷ በምሥራቅ በኩል ይሁን። በጎንና በጎንም በመርከብ አምሳል ሁለት ክፍሎች ይኑሩ። የኤጲስ ቆጶሱ መንበርም በመካከል የተዘጋጀ ይሁን። ፴፯:- ወንጌልም በሚነበብበት ጊዜ ቀሳውስት ዲያቆናት ሕዝቡም ሁሉ በታላቅ ፍርሀት ይቁሙ። ፴፩-፴፪:- የሚበቃቸው ቦታ ባይኖር ወንዶች ልጆች በአባቶቻቸው ፊት ይቀመጡ። ሴቶች ልጆችም ብቻቸውን ይቀመጡ። ቦታ ባይኖር ግን ባገቡት ሴቶች ኋላ ይቁሙ። ደናግልና መበለቶች ባልቴቶችም በሴቶች ፊት ይቁሙ። ባልና ልጅ ያላቸው ሴቶች ግን ብቻቸውን ይቀመጡ። ፴፫:- (በቤተክርስቲያን ውስጥ) በሳቅና በዋዛ የሚገኙ ሰዎች ቢኖሩ ዲያቆኑ ይምከራቸው። ዝም እንዲሉም ያድርጋቸው። ፴፮:- ንዑሰ ክርስቲያን ይውጡ ብሎ ዲያቆኑ አሰምቶ በሚናገርበት ጊዜ መምህራንና በንስሐ ያሉ ሰዎች ሕዝቡም ሁሉ ቆመው ወደ ምሥራቅ ይመልከቱ። ፴፮:- ሴቶች ራሳቸውን ተሸፍነው ይቁሙ። ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙንም ይቀበሉ። ፴፰:- በነግህና በሠርክ በቤተክርስቲያን ተሰብስባችሁ መዝ. 62ን እና መዝ. 140ን ዘምሩ ፵:- በክርስቲያን ሰንበት ዕለት የክርስቶስን የትንሣኤውን ስብከት እንሰማ ዘንድ፣ መከራዎቹንም እናስብ ዘንድ፣ መታሰቢያውንም እናደርግ ዘንድ፣ የነቢያትን መጻሕፍትና ቅዱስ ወንጌልንም እናነብ ዘንድ፣ መንፈሳዊ ምግብ የሚሆን መሥዋዕትንና ቁርባንን እናቀርብ ዘንድ ይገባናል። **አንቀጽ ፲፪፣፫-፭:-** ከክፉ ሥራ ራቁ። ይኽውም መዝፈን፣ ጣዖት ማምለክ፣ ጥንቁልና ነው። ፮:- ምእመናን ከክፉዎች ማኅበር ሊለዩ አገባብ ነው። ፲፩:- ተግባረ እድን አናቋርጥ። ቸልም አንበል። ፳:- ጥበበኛ ሰው ለራሱ አላዋቂ መስሎ ይታያል። ፳፪:- ሥራ የማይሠራ ሁሉ ምግብን አይመገብ። **አንቀጽ ፲፫፣፲፫:-** ሕፃናት ሴቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ አይሾሙ። የፈቲውን ያር መታገሥ አይቻላቸውምና። በወጣትነት ኃይል ዳግመኛ ወንድን ያገባሉና። ፳:- ለቆነጃጅቶች ሴቶችም የቀድሞ ባሎቻቸው ከሞቱባቸው መታገድ ባይቻላቸው ሁለተኛ ባል ያገቡ ዘንድ እንዲገባ እናዛለን። ፴:- ለሰው ሁሉ በጎ ነገርን ታደርጉ ዘንድ ይገባል። ፴፪:- ባልቴቶች ትዕግሥተኞች ነገርን የማያበዙ ክፋትና ቁጣ የሌለባቸው ይሆኑ ዘንድ አገባብ ነው። ፴፯:- ሥርዓትን ይማሩ ዘንድ የሚሹ ወደ መምህራን ሄደው ይማሩ። የምክር ቃልንም ይስሙ። **አንቀጽ ፲፬፣፩:-** ሴቶች ያጠምቁ ዘንድ አይገባም። ፬:- ሴቶችን ያስተምሩ ይገሥጹ ዘንድ አታሰናብቷቸው። የክህነት ሥራንም አይሥሩ። ፲:- (ሴቶች) ፈጽመው ብልሆችም ቢሆኑ፣ ሃይማኖትም ቢኖራቸው፣ መጻሕፍትንም ቢያውቁ፣ ያጠምቁና ወንጌልን ያስተምሩ ዘንድ አናሰናብታቸውም። **አንቀጽ ፲፭፣፩:-** ሕዝባዊ የክህነት ሥራን እንዳይሠራ፣ ዕጣንንም እንዳያሳርግ፣ እንዳያጠምቅ፣ በአንብሮተ እድም እንዳይባረክ፣ በረከተ ኅብስቱንም እንዳይሰጥ እናዝዛችኋለን። ፪:- ኤጲስ ቆጶሳትና ቀሳውስት ብቻ ያጥምቁ። ፫:- ቀሳውስት ዲያቆናትንና ዲያቆናዊትን፣ አናጉንስጢስንም፣ መዘምራንንም፣ በር ዘጊዎችንም እንዳይሾሙ እነሄ እናዝዛለን። **አንቀጽ ፲፮፣፲፩:-** መበለት ለሰጧትና ለመጸወቷት ሰዎች ትጸልይ። ፲፬:- ሀብት ከሰው ዘንድ የሚሰጥ አይምሰላችሁ። የጸጋ ሀብት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ፲፱:- የዐመፅ ርግማን ባልበደለ ሰው ላይ አይደርስም። ወደ ረጋሚው ይመለሳል እንጂ። ፳፯:- ኤጲስ ቆጶስም ቢሆን ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ቢሆን ከሹማምንት ወገንም የሆነ ቢሆን ስለበረከት ፈንታ እርግማንን እንዳይወርስ እርግማን ከአፉ አይውጣ። ፴:- ዲያቆናዊት ነውር

የሌለባት ሴቶችን ለማገልገል የተመረጠች ንጽሕት ትሁን። ፴፯:- ከበለሳን የተገኘ ቅብዐ ሜሮን የሃይማኖት ኃይል ነው። ፴፯:- (ዲያቆናት) ለተቸገሩት ሰዎች ማገልገልን እንቢ አይበሉ። ፴፭:- እነሆ ኤጲስ ቆጶስ በሦስት ኤጲስ ቆጶሳት ያም ባይሆን በሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ይሾም ዘንድ እናዝዛለን። ፴፱:- ቀሳውስት፣ ዲያቆናትና ሌሎች የቤተክርስቲያን ሹማምንት ግን በአንድ ኤጲስ ቆጶስ ይሾሙ። **አንቀጽ ፲፯፣፩:-** እናት አባት የሞቱባቸውን ልጆች ያሳድጓቸው ዘንድ ይገባል። **አንቀጽ ፲፰፣፫:-** (ኤጲስ ቆጶሳት ሆይ) ለሚያገለግሉ ደመወዛቸውን ስጡ። የተራቡትን አብሏቸው። ድሆችን አሳድሯቸው። የታረዙትን አልብሷቸው። የታመሙትን ጠይቋቸው። የታሠሩትንም እርዷቸው። ፫:- እያለው ምጽዋትን የሚቀበል እርሱን እግዚአብሔር ይቆጣጠረዋል። የድሃውን ምግብ ነጥቋልና። **አንቀጽ ፲፱፣፮:-** ባልቴቶችንና ድሀ አደጉን ለሚቀበሉ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ደስ ያሰኛቸዋል። **አንቀጽ ፳፣፩:-** ከመሸተኛ መባን እንዳትቀበሉ ተጠንቀቁ። ፫:- ፈጣሪ እግዚአብሔር ከዝሙት ዋጋ መባ አትቀበሉ ብሏልና። ፮:- ክፉ የሚሠራና ዐመፅን የሚናገር ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ ነው። ፲፪:- ከብዙ የኃጢአተኞች ሀብት ጥቂት የጻድቃን ሀብት ይበልጣል። ፳፮:- እግዚአብሔርን ከሚጠሉ ሰዎች መባን ተቀብላችሁ መሳቂያና መዘበቻ ከምትሆኑ ታግሣችሁ በመራብ በመጠማት ትኖሩ ዘንድ አገባብ ነው። ፳፯:- ከወንጀለኞች መባን አትቀበሉ። **አንቀጽ ፳፩፣፩:-** አባቶች የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቻችሁን አስተምሯቸው። የእጅ ሥራንም ይማሩ ዘንድ እዘሏቸው። ፭:- ልጁን የማይገሥጽ አባት አላዋቂ ነው። ፰:- (ልጆች) ወደ መሸታ ቤት ይገቡ ዘንድ አታሰናብቷቸው። **አንቀጽ ፳፪፣፪:-** አገልጋይ ክርስቲያን ቢሆን ጌታው ከሓዲ ቢሆን በሥራው ሁሉ ይገዛለት ዘንድ አገባብ ነው። ነገር ግን ከእርሱ ጋራ በሃይማኖት አይተባበር። **አንቀጽ ፳፫፣፩:-** ደናግል ሰውነታቸውን ሳይፈትኑ ይሣሉ ዘንድ አይገባም። **አንቀጽ ፳፬፣፪-፫:-** በመከራ ላሉ ሰማዕታት ከገንዘባችሁ ምግባቸውን ላኩላቸው። ዳግመኛም ለሚጠብቋቸው ጭፍሮች ምግባቸውን ስጡ። በእነርሱ ላይ መከራ እንዳያጸኑባቸው። ፫:- ሰማዕት የጌታ ወንድም ይባላል። ፮:- ገንዘብ የሌላችሁ ደግሞ መከራ እየተቀበሉ ስላሉ ሰማዕታት ጹሙ። ፲፬:- ንኡሰ ክርስቲያን ቢታመም መከራንም ቢታገሥ ስለ ክርስቶስ ስም ቢሞት መከራው ስለ ጥምቀት ይሆነዋል። **አንቀጽ ፳፰፣፲፯:-** የሙታን ትንሣኤ በክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው። ፳፯-፴:- ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ወንጀለኞችን ስሙ ፊንክስ የሚባል ተፈጥሮው አንድ የሚሆን ወፍ ያስረዳቸዋል። ወደ አመድነት ከተለወጠ በኋላ በትል መልኩ እንደገና ታድሶ ይነሣል ፴፪:- ሰውን ካለመኖር የፈጠረ እግዚአብሔር በፍጹም ከሃሊነቱ ሙታንን ማስነሣት አይችልምን?? (ያስነሣል)። **አንቀጽ ፳፯፣፩:-** እነሆ ሰማዕታትን ከፍ ከፍ አድርጓቸው ፈጽማችሁም አክብሯቸው። **አንቀጽ ፳፯፣፩:-** የምትወደዱ ወንድሞች ሆይ ዘፈንን ከማድመጥና ከጨዋታ ነገር፣ ከተድላ ደስታና ከመባልዕት ጣዕም፣ ረብህ ጥቅም ከሌለው ከብላሽ ሥራም ሁሉ ትርቁ ዘንድ በጎ ምክርን እንመክራችኋለን። **አንቀጽ ፳፰፣፳:-** በራስህ አትማል። አላዋቆች አይሁድ በራሳቸው ይምላሉና። ፳፩:- የምእመናን ነገራቸው እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት ማለት ነው። **አንቀጽ ፳፱፣፩-፱:-** የበዓላትን ቀን ጠብቁ። እነዚህም በዓለ ልደት ታኅሣሥ ፳፱፣ በዓለ ጥምቀት ጥር ፲፩ ፲-፲፪:- በሆሣዕና ማግሥት ሰኞ ቀን ሕማንና ሃይማኖትን የካዱ ክፉዎች አይሁድ ተሰብስበው በጌታ ላይ ተማክረዋል። ማክሰኞ ቀን ምክርን ጨመሩ፣ በረቡዕ ቀን ምክርን ፈጸሙ። ፳፫:- የተለየች የፋሲካ ጾምን ስድስት ቀን እንጹም። ፳፱:- ዳግመኛም ዓርብ

ረቡዕን እንጹም። ፫:- በቀዳሚት ሰንበት እንዳንጾም መሆን አገባብ ነው። መከራን ከተቀበለባት ከቀዳም ሥዑር በቀር። **አንቀጽ ፬፣፭:-** የሕማማትን መታሰቢያ በዓመት አንድ ጊዜ ያድርጉ። ፮:- ትንሣኤ በተቀደሰች የክርስቲያን ሰንበት ይሁን። ፯-፲፪:- በሕማማት ሳምንትም በጨው ከተሠራ ቂጣና ከውሃ በቀር ምንም አትብሉ አትጠጡ። የቻለ በየሁለት ቀኑ ይጹም። ያልቻለ በቀን በቀን ይጹም። ፲፫:- ጌታ ካረገም በኋላ በአሥረኛው ቀን በዓለ ሃምሳ ሲፈጸም በዓልን አድርጉ። **አንቀጽ ፲፭፣፲፮:-** የእግዚአብሔር ልጅ ወልድ በማርያምና በዮሴፍ ሩካቤ በሥጋ ፈቃድ ተወለደ የሚሉ ከኃድያን ፍዮኒዮክን ይባላሉ። **አንቀጽ ፲፯፣፲፯-፲፯:-** የእሪያዎች ሥጋ ንጹሕ ነው የሚሉ አሉ። ነገር ግን ርኩስ ነው እንጂ ንጹሕ አይደለም። በመጽሐፍ ንጹሕ የሆነውን ግን ከእርሱ ይብሉ። (ይህ ሥርዓት ልክ ኤጲስ ቆጶስ አንድ ያገባ ይሁን እንደሚለው በሐዋርያት ዘመን የነበረ በኋላ በሠለስቱ ምእት የተሻሻለ ነው። ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት እርያ የሚበላ ርኩስ ነው አይባልም)። **አንቀጽ ፲፰፣፳:-** (ስለ ሥላሴ) ሁለት አይደለም። በሦስትነቱም አራተኛ አይጨመርበትም። ብቻውን ለዘለዓለሙ የሚኖር አንድ ነው እንጂ። ፳፩:- እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ መልካም እንደሆነ እንናገራለን። ፳፪:- እናንተ ግን ልጆቻችሁን ሕፃናት ሳሉ አጥምቁ። መንፈሳዊ ምግብንም መግቧቸው። በምክርና በጥበብም አሳድጓቸው። ፳፫:- ሥርዓት ጽድቅ ነው። ፳፬፳፭:- ሴቶች ለባሎቻቸው በፍቅርና በፍርሀት ይታዘዙ። ክብርት ሣራ ለባሏ ለአብርሃም ትታዘዘው ጌታዬም ትለው እንደነበረ። ጌታዬ አለቃዬ ትለው ነበር እንጂ በስሙ አትጠራውም ነበርና። ፳፮:- የልጅነት ሚስትህን ውደድ። የአንተ ናትና። ሁልጊዜም ከአንተ ጋር ትኖራለችና። አካልህም ናትና። **አንቀጽ ፳፯፣፭-፱:-** ስለሞቱ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን አንብቡ። ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙንም በምስጋና በቤተክርስቲያን አሳርጉላቸው። በመቃብርም የዳዊትን መዝሙር በፊታቸው አንብቡ። ፱:- የሞቱትን ሰዎች በድን በዳሰሳችሁ ጊዜ አጽማቸውን መሸከም አትጸየፉ። ስለእነርሱ የምትረክሱ አይደላችሁምና። **አንቀጽ ፳፰፣፭-፰:-** ማንንም እንዳትጠሉ ዕወቁ። ሰውን ሁሉ አትጥላ። ግብፃዊውንም ቢሆን ኤዶማዊውንም ቢሆን ሁሉም የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ናቸውና። ፱:- ነገር ግን ክፉ ሰዎችና ከዚህ ዓለም ፈቃድ ራቅ። ፴፪:- ቁጡና ቀናተኛ አትሁን። ፴፫:- በአንተ ላይ የሚመጣውን መከራ ሁሉ ተቀበል። እንደ ኢዮብና እንደ አልዓዛር ከእግዚአብሔር ዋጋህን ትቀበል ዘንድ። ፴:- የእግዚአብሔርን ቃል ያስተማረህን አክብር። በቀንና በሌሊትም አስበው። ፴፪:- ጠብ ያለባቸውን ሰዎች አስታርቃቸው በእውነትም ፍረድ። ፍርድ ለእግዚአብሔር ነውና። ፴፫:- ለንጉሥም ተገዛ ሹመቱም ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ እወቅ። ገገርዎችን አክብር። እነርሱ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸውና። ፴፱:- ከክፉ ሥራህ ሳትመለስ ክፉ እየሠራህ መሥዋዕትን አታቅርብ። **አንቀጽ ፴፮፣፴:-** አሥራትንም ሁሉ ለባልቴቶችና ለድሃ አደጎች፣ እናት አባት ለሞቱበት ለእንግዶች እና ለድሆች ስጡ። **አንቀጽ ፴፯፣፪:-** የመላእክት የወገን ስማቸው መላእክት፣ መናብርት፣ ሥልጣናት፣ አጋዕዝት፣ ኃይላት፣ ሊቃናት፣ ኪሩቤል፣ ሱራፌል ይባላሉ። ሌትና ቀንም እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። **አንቀጽ ፴፰፣፲፪:-** ጌታ በሰንበት እናርፍ ዘንድ አዘዘን። ከሥራው ሁሉ ያረፈባት ቀን ናትና። ፲፫:- (የክርስቲያን ሰንበትንም እናክብር)። **አንቀጽ ፴፱፣፭:-** ለሚጠመቅ ሰው (ንዑሰ ክርስቲያን) የምክር ቃልን ያስተምሩት። ፲፪:- ሊጠመቅ የሚወድ ንዑሰ ክርስቲያን ሰይጣንን ያውግዝ። በክርስቶስ ስም ይመን። የቀደመ ልማዱንም ይተው። **አንቀጽ ፵** በማይ ላይ ስለሚጸለይ ጸሎት ይናገራል። **አንቀጽ ፵፭** በሜሮን ላይ ስለሚጸለይ ጸሎት

ይናገራል። **አንቀጽ ፴፪** ሐዲስ አማንያን ሲጠመቁ የሚጸለይ ጸሎትን ይናገራል። **አንቀጽ ፴፫** በሐዋርያት ስለተሾሙ ኤጲስ ቆጶሳት ስም ዝርዝር ይናገራል።

ቀኖና ዘኒቅያ (ዘሠለስቱ ምእት)

ይህንን ቀኖና ሠለስቱ ምእት አርዮስን ካወገዙ በኋላ የሠሩት ነው። **ቀኖና ፩፡-** በሕመም ምክንያት የተሰለበ ወይም ሌሎች በግድ የሰለቡት ሰው በቅቶ ከተገኘ ክህነት ከመሾም አይከልከል። ሳይታመም ወይም ሳያስገድዱት በፈቃዱ ራሱን የሰለበ ሰው ግን ምእመን ቢሆን ክህነት አይሾም። ካህን ቢሆን ከክህነቱ ይሻር። **ቀኖና ፪፡-** አዲስ አማኝን በደንብ ሳይፈትኑት ወደ ክህነት አያምጡት። **ቀኖና ፫፡-** ኤጲስ ቆጶሳትና ሕዝቡ ሁሉ የወደዱት ኤጲስ ቆጶስ ይሾም። በፈቃዳቸው ተሹሟልና ሕዝቡም ይውደዱት። ፫ ኤጲስ ቆጶሳት ይሹሙት። **ቀኖና ፬፡-** ከባድ ምክንያት ሳያጋጥመው ቤተክርስቲያን አልገባም የሚል ካህን ሕዝባዊ ካለ ይገሥጹት። በኤጲስ ቆጶሱ ላይ ክፉ የሚያደርግ ሰው ካለ ይገሥጹት። ኤጲስ ቆጶሱም በቂምና በቁጣ በአንዱ ላይ ክፉ ቢያደርግ ይሻሩት። ኤጲስ ቆጶሳት ወደ ጳጳሳቸው በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰብሰቡ። **ቀኖና ፭፡-** ኤጲስ ቆጶስ ያለሕዝቡና ያለጳጳሱ ፈቃድ አይሾም። ከግማሽ በላይ ሕዝብ ከተቃወመው ኤጲስ ቆጶስነትን አይሾም። **ቀኖና ፮፡-** ወደ ትክክለኛዋ ሃይማኖት ካልተመለሱ የከሓድያንን ንስሓቸውን አይቀበሏቸው። **ቀኖና ፯፡-** ሳይመረምሩ የሾሙት ቄስ ቢኖር ከተሾመ በኋላ ቀድሞ የሠራው በደል ቢታወቅ ሹመቱ ተቀባይነት የለውም። **ቀኖና ፰፩፡-** ማንም ሳያስገድደው በፈቃዱ የካደ ሰው ቢኖርና በኋላ ንስሓ ቢገባ ይቀበሉት። ያልተገባው ሆኖ ቢገኝ ግን አይቀበሉት። **ቀኖና ፰፪፡-** ዓለምን ከናቃት በኋላ ወደዓለም የሚመለስ ሰው ቢኖር ቀኖናው 10 ዓመት ይሁን። በተጨማሪም 3 ዓመት ከንኡስ ክርስቲያን ጋር ይማር። **ቀኖና ፰፫፡-** ለሞት የደረሰ በንስሓ ከምእመናን የተለየ ሰው ቢኖር ሊቆርብ ቢፈልግ ያቁርቡት። ከቆረበ በኋላ ከዳነም ከምእመናን ጋር ይቀላቀል። **ቀኖና ፰፬፡-** ክዶ የተመለሰ ሰው ቢኖር ሦስት ዓመት ከንኡስ ክርስቲያን ጋር ቆይቶ ወደ ምእመናን ይመለስ። **ቀኖና ፰፭፡-** ቀሳውስት ዲያቆናት የተሾሙባትን ቤተክርስቲያን ትተው ወደ ሌላ ቤተክርስቲያን አይሂዱ። ይህን ያደረጉ ካሉ ሲኖዶስ ያወግዛቸዋል። **ቀኖና ፰፮፡-** ከሌላ ቤተክርስቲያን የመጣን ቄስ ወይም ዲያቆን አይቀበሉት። ወደ ቤተክርስቲያኑ ይመልሱት እንጂ። **ቀኖና ፰፯፡-** አራጣ የሚቀበል ካህን ቢኖር ከሹመቱ ይሻር። **ቀኖና ፰፰፡-** ካህናት ሹመታቸው እንደ ሠራዊተ ብርሃን እንደሆነ ሊረዱ ይገባል። ዲያቆናት ቁርባንን ከቄስ ወይም ከኤጲስ ቆጶስ ይቀበሉ እንጂ በእጃቸው አይቀበሉ። ይህን ሥርዓት ያፈረሰ ቢኖር ከክህነቱ ይሻር። **ቀኖና ፰፱፡-** ከከሓድያን ወደእኛ የተመለሰ ሰው ቢኖር ዳግመኛ ያጥምቁት። የከሓድያን ጥምቀት ከጥምቀት አይቆጠርምና። ከተጠመቀ በኋላ ምግባሩ ያማረ ሆኖ ቢገኝ ክህነት ይሾም። ዲያቆናውያትና መነኮሳይያት ለአገልግሎት ቢለዩም ቁጥራቸው ከሕዝባውያት ነው። **ቀኖና ፺፡-** በሰንበታትና በበዓለ ኃምሳ አይስገዱ።

ሲኖዶስ ዘግንግራ (ግንር.)

እነዚህ ሊቃውንት ብዛታቸው ፲፮ ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው። ሥጋ መብላት እና ማግባት ኃጢአት ነው ያሉ ከሓድያንን ለማውገዝ የተሰበሰቡ ሊቃውንት ናቸው። **ትእዛዝ ፩፡-** ጋብቻንና በጋብቻ የሚደረግ ሩካቤን ኃጢአት ነው የሚል ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን። **ትእዛዝ ፪፡-** ከደምና ለጣዖት ከተሰዋ ውጭ ሥጋ መብላት ኃጢአት ነው የሚል ቢኖር የተወገዘ ይሁን። **ትእዛዝ ፫፡-** ያገባ ቄስ ሊቀድስ አይገባም ብሎ ካገባ ቄስ ቁርባን አልቀበልም ያለ ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን።

ትእዛዝ ፮:- የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እና ምእመናንን የሚያቃልል ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፯:- ቤተክርስቲያንን በመናቅ አልገባም ያለ ሰው ቢኖርና ጥምቀትንና ቁርባንን በቤቱ የሚያደርግ ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፰:- ለቤተክርስቲያን የገባውን አሥራት፣ ብፅዐት፣ በኩራት ኤጲስ ቆጶሱ ሳይፈቅድለት እና ሳይሾመው ለራሱ የሚያደርግ ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፱:- ማንም ቢሆን ኤጲስ ቆጶሱ ሳይፈቅድ ለአሥራት ከገባው ከፍሎ ለነዳያን የሚሰጥ ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፲:- ስለንጽሐ ድንግልና ብሎ ሳይሆን ማግባት ርኩስ ነው ብሎ የመነኮሰ ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፲፩:- ከልጅነቱ ጀምሮ ስለክርስቶስ ብሎ ድንግል የሆነ ሰው ቢኖርና ባገቡት የሚመካ ከሆነ ይወገዝ። ትእዛዝ ፲፪:- ለነዳያንና ለድውያን ምሳ ያዘጋጀ ሰው ቢኖርና ሌላ ሰው ነዳያንና ድውያንን በመናቅ አልመጣም ቢል የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፲፫:- እርሱ የፍየል ሌጦ የሚለብስ ሆኖ ያልለበሱትን ምእመናን የሚንቅ ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፲፫:- የመነኮሰች ሴት ብትኖርና በሴት ልብስ ፋንታ የወንድ ልብስ ብትለብስ የተወገዘች ትሁን። ትእዛዝ ፲፬:- ሩካቤን ርኩስ ነው ብላ ባሏን የከለከች ሴት ብትኖርና እርሱን አልቀርብም ብላ ከባሏ ሸሽታ እምቢ ብትል የተወገዘች ትሁን። ትእዛዝ ፲፭:- ልጆቹን ሳያሳድግ ልጆቹን ትቶ የመነኮሰ ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፲፮:- በሰንበት የሚጾም ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፲፱:- በታወቀ ደዌ ካልሆነ በቀር አጽዋማትን የማይጾም ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፳:- ስለክርስቶስ ስም ሰማዕት የሆኑ ሰማዕታትን የሚንቅ ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን።

ሲኖዶስ ዘሰርዴቂስ (ስርድቅ.)

እነዚህ ሊቃውንት 140 ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው። ትእዛዝ ፩:- ኤጲስ ቆጶስ ሹመትን ወዶ ከትንሿ ሀገረ ስብከት ወደ ትልቅ ሀገረ ስብከት ሊሄድ አይገባውም። ትእዛዝ ፪:- ሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ቢጣሉ ኤጲስ ቆጶሳት በመካከላቸው ይፍረዱ። ትእዛዝ ፫:- ኤጲስ ቆጶሳትና ካህናት በሚሰበሰቡበት ጊዜ አንዱስ እንኳ ወደኋላ አይበል። በማቃለልና በጥላቻ የቀረ ከሆነ ከሹመቱ ይሻሩት። ትእዛዝ ፬:- ኤጲስ ቆጶስ ለተቸገረ ሁሉ እርዳታን ማድረግ ይገባዋል። እናት አባት የሞቱባቸውን ልጆች፣ መበለቶችን፣ መጠጊያ ያጡትን፣ ችግረኞችን ሁሉ ሊረዳቸው ይገባል። ትእዛዝ ፭:- እንዳይሰናከል ኤጲስ ቆጶስን ወደከተማ ይሄድ ዘንድ አታሰናብቱት። ከከተማ የሚፈልገው ነገር ካለ እንኳ ዲያቆንን ልኮ ያስመጣ።

ሲኖዶስ ዘአንጾኪያ (ጾክ.)

እነዚህ ፲፫ ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው። ትእዛዝ ፩:- የኒቅያ ጉባኤ የሠራውን ሥርዓት የሻረ ቢኖር የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፪:- ከቤተክርስቲያን ከተለየ ሰው ጋር በአንድ ቤት መጸለይ አይገባም። ትእዛዝ ፫:- በዚያ ለብዙ ጊዜ ለመኖር ወዶ ኤጲስ ቆጶሱ እየጠራው እምቢ ብሎ ያለ ኤጲስ ቆጶሱ ፈቃድ ሀገሩን ለቆ ወደሌላ ሀገር የሄደ ቄስ፣ ዲያቆን ቢኖር ከሹመቱ ይሻር። ትእዛዝ ፬:- ተሸሮ ሳለ ከመሻሩ በፊት ይሠራው የነበረውን የክህነት አገልግሎት እሠራለሁ የሚል ቄስ፣ ዲያቆን፣ ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር አይቀበሉት። ምእመናንም ከእርሱ ይራቁ። ትእዛዝ ፭:- ኤጲስ ቆጶሱን በመናቅ በራሱ ምሥዋዕን ያዘጋጀ ቄስ ወይም ዲያቆን ቢኖር ኤጲስ ቆጶሱ ሁለት ሦስት ጊዜ ይጥራው። እምቢ ቢል ከክህነቱ ይሻር። ትእዛዝ ፮:- አንዱ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ሌላኛው ኤጲስ ቆጶስ ሊቀበለው አይገባም። ትእዛዝ ፯:- ያለ ኤጲስ ቆጶሱ ፈቃድ እንግዳ ቄስን አይቀበሉት። ትእዛዝ ፰:- ኤጲስ ቆጶሳት ያለ ጳጳሱ ፈቃድ አይሥሩ። ትእዛዝ ፱:- የሾመው

ጳጳስ ሳይፈቅድለት ወደ ንጉሥ የሄደ ከክህነቱ ይሻር። ትእዛዝ ፲፫፡- ጳጳስ የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ ሳይፈቅድለት የእርሱ ባልሆነ ሀገረ ስብከት ዲያቆናትን ካህናትን ሊሾም አይገባውም። ከሾመ ግን ከክህነቱ ይሻር። ትእዛዝ ፲፭፡- በሚገባ ነገር ሕዝቡ የከሠሱት (የጠሉት) ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር ማኅበረ ኤጲስ ቆጶሳት ይፍረዱበት። ትእዛዝ ፲፱፡- ኤጲስ ቆጶስ በሀገሩ ሰዎችና በኤጲስ ቆጶሳት ሥምረት ይሾም። ትእዛዝ ፳፡- የጳጳሳት ጉባዔ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሁን። ይኸውም ከትንሣኤ በአራተኛው ሱባኤና ጥቅምት ፲፪ ይሁን። ትእዛዝ ፳፫፡- ኤጲስ ቆጶስ ኤጲስ ቆጶስነትን አያውርስ። ይህን ካደረገ ይሻራል። ትእዛዝ ፳፭፡- ኤጲስ ቆጶስ ከቤተክርስቲያን ገንዘብ ለነዳያን ለካህናት ከፍሎ መስጠት ይገባዋል።

ሲኖዶስ ዘሎዶቅያ (ዶቅ.)

እነዚህ ፳፱ ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው። ትእዛዝ ፪፡- በደሉ የበዛ ሰው ቢኖር ንስሓ ከገባ ይቀበሉት። ሥጋውን ደሙንም ያቀብሉት። ትእዛዝ ፫፡- አዲስ የተጠመቀ ክህነት አይሾም። ትእዛዝ ፭፡- ካህን አራጣ መቀበል አይገባውም። ትእዛዝ ፮፡- ሃይማኖት የሌላቸው ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይገቡ ይከልክሏቸው። ትእዛዝ ፯፡- ለእግዚአብሔር ሦስት አካላት የሉትም የሚሉ ሰዎችን አይቀበሏቸው። ትእዛዝ ፱፡- ክርስቲያኖች ልጆቻቸውን ከአሕዳድያን ጋር ማጋባት አይገባቸውም። ለጸሎትና ለመፈወስ ብሎ ክርስቲያን ወደ ዓላውያን ቤት አይግባ። ትእዛዝ ፲፡- ሴቶች ክህነትን ይሾሙ ዘንድ አይገባም። ትእዛዝ ፲፩፡- ኤጲስ ቆጶስ የሚሾም ሰው በጽድቁ፣ በየዋህቱ እና በደግነቱ የታወቀ፣ ሕግ አዋቂ፣ ጻድቅ ሊሆን ይገባል። ትእዛዝ ፲፬፡- ሕዝባዊ ምእመን በአትሮንስ ላይ መጻሕፍትን ማንበብ አይገባውም። ትእዛዝ ፲፭፡- በበዓላት ጊዜ ለበዓሉ የሚስማማውን ቃለ እግዚአብሔር ከነቢያት ከወንጌል ያንብቡ። ትእዛዝ ፲፮፡- በዘጠኝ ሰዓትና በምሽት ይጸልዩ ዘንድ ይገባል። ሰኞ ጸሎተ ሙሴን ንሴብሖን፣ ማክሰኞ ጸሎተ ሙሴ ዳግምን፣ ረቡዕ ጸሎተ ሐናን፣ ኃሙስ ጸሎተ ዕንባቆምን፣ ዓርብ ጸሎተ ኢሳይያስን፣ ቅዳሜ ጸሎተ ዮናስን፣ እሑድ እኒህን ሁሉ ይጸልዩ። ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅን ሁልጊዜ ይጸልዩ። ትእዛዝ ፲፯፡- በጸሎት ጊዜ ዲያቆን ከቁስ በፊት ሊቆም አይገባውም። ትእዛዝ ፲፰፡- ከዲያቆን በታች ያሉት ንፍቀ ዲያቆን፣ አናጉንስጢስ፣ መዘምር፣ ዐፃዌ ኖኅት ንዋየ ቅዳሴን ይነኩ ዘንድ አግባብ አይደለም። ንፍቅ ዲያቆን መጽሐፍ መያዝ፣ መብራት ማብራት፣ በር መዝጋት በር መክፈት ይገባዋል እንጂ። ትእዛዝ ፳፩፡- ካህናት በገበያ መካከል እና በዘፈን ቤት አይብሉ። በማኅሌት መካከልም አይጠጡ። ትእዛዝ ፳፪፡- ንፍቅ ዲያቆን ማንንም ይባርክ ዘንድና አልተፈቀደለትም። ትእዛዝ ፳፫፡- በቤተክርስቲያን ውስጥ ሊበሉ ሊጠጡ አይገባም። ትእዛዝ ፳፮፡- ክርስቲያን በዓላትን በክርስቲያናዊ አከባበር እንጂ እንደ አይሁድ አከባበር አያክብር። ትእዛዝ ፳፯፡- ካህናት፣ ምእመናን፣ መኮሳት ከሴቶች ጋር ቤተብለኔ (መታጠቢያ ቤት) መግባት አይገባቸውም። ይህንን የሚያደርጉት ሕግ የሌላቸው አረማውያን ናቸውና። በወንዝ መታጠብም ለካህናት አይገባም። ትእዛዝ ፳፰፡- ምእመናን ልጆቻቸውን ለዐላውያን መዳር አይገባቸውም። ትእዛዝ ፳፱፡- ከዐላውያን መባረክና ቁርባናቸውን መቀበል አይገባም። ትእዛዝ ፴፡- በቤትም በቤተክርስቲያንም ከመናፍቃን ጋር መጸለይ አይገባም። ትእዛዝ ፴፪፡- ምኩራብ መለካውያንን የሚያገለግል ሰው ቢኖር አምልኮ ጣዖት ነውና የተወገዘ ይሁን። ትእዛዝ ፴፫፡- ጠንቋይን ከቤተክርስቲያን ያባሩት። ትእዛዝ ፴፭፡- ቤተክርስቲያን ከአይሁድ ከመenaፍቃን የመጣውን እጅ መንሻ አትቀበል። ከእነርሱ ጋርም አትብሉ። ትእዛዝ ፴፮፡- ክርስቲያኖች ከዐላውያን ጋር በዓልን ማክበር አይገባቸውም። ትእዛዝ

፴፮:- ከካህናት ወገን ማንኛውም ቢሆን ያለኤጲስ ቆጶሱ ፈቃድ አይሂድ። ፴፯:- ሴቶች ወደ መቅደስ ይገቡ ዘንድ አይገባም። ፴፰:- የሚጠመቀውን ሰው ስሙን ይጻፉት። በዐቢይ ጾም ጥምቀት አይገባም። ፴፱:- ከጥምቀት በፊት የሚጠመቀው ሃይማኖቱን ማወቅ አለበት። ፵:- ሞት የሚያሰጋው የታመመ ሰው ቢኖር ያጥምቁትና ያስተምሩት። ፵፩:- የተጠመቀን ሰው ቅብዐ ሜሮን ሊቀቡት ይገባል። ፵፪:- በዐቢይ ጾም ከዘጠኝ ሰዓት በፊት ቁርባን አያድርጉ። ፵፫:- በመዋዕለ ጾም ጥሉላትን (የፍስክ ምግቦችን) አትመገቡ። ፵፬:- በዐቢይ ጾም በዓላት ቢውሉ ቅዳሜ ወይም እሑድ ያክብሯቸው። ፵፭:- በዐቢይ ጾም ሰርግ ሊደረግ አይገባም። ፵፮:- ክርስቲያኖች በሰርግ ጊዜ እግዚአብሔርን ያመስግኑ እንጂ አይዝፈኑ። ፵፯:- ካህናት ዘፋኞች ወደሚሰበሰቡበት ቤተ ተውኔት እንዳይገቡ ይጠንቀቁ። ፵፰:- ካህናት በውርርድ የመጣን መጠጥና መብል አይጠጡ አይብሉ። ፵፱:- ቀሳውስት በምሥዋው ውስጥ ከኤጲስ ቆጶሱ ኋላ ይሂዱ። ፶:- ምእመናን ቁርባንን በቤታቸው ሊያደርጉ አይገባም። ፶፩:- በቤተክርስቲያን ውስጥ ሕገ ቤተክርስቲያን የሚፈቅዳቸው መጻሕፍት እንጂ ሌላ መጽሐፍ ሊነበብ አይገባም።

ሲኖዶስ ዘኒቅያ (ኒቅያ)

ይህ ባለ፫፻፭ዱ አንቀጽ ሲኖዶስ ዘኒቅያ ነው። ፩:- መንፈሰ ጋኔን ያደረበት ሰው ክህነት አይሾም። ምንኩስናም አይመንኩስ። ፪:- ጌቶቻቸው የሰለቧቸው አገልጋዮች ቢኖሩ ለክህነት የበቁ ሆነው ከተገኙ ይሾሙ። ፫:- በደንብ መመለሱ እና በምግባሩና በንጽሐ ሃይማኖቱ ሳይመሰከርለት አዲስ አማኝን ኤጲስ ቆጶስና፣ ቅስና እና ዲቁና አይሹሙት። ሳይመረምሩ ከሾሙት በኋላ ችግር ቢገኝበት በሁለት በሦስት ምስክር ይሻሩት። የሾሙትም ይሻሩ። ፬:- ኤጲስ ቆጶስ፣ ቄስ፣ ዲያቆን አረጋዊት ሴት እና ዘመዶቹ ካልሆኑ በስተቀር ከሴቶቹ ጋር አይቀመጥ። ፭:- ኤጲስ ቆጶስ በሚሾምበት ሀገር ሕዝብና በኤጲስ ቆጶሳት ይሾም። ፮:- አንዱ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ሌለኛ ኤጲስ ቆጶስ አይፍታው። ፯:- ኤጲስ ቆጶሳት በዓመት ሁለት ጊዜ ከጳጳሳቸው ዘንድ ይሰብሰቡ። ይህም በጸንጠቆስጤ ግማሽና በጥቅምት ወር ይሁን። ፰:- ያለ ኤጲስ ቆጶሱ ፈቃድ የመነኮሰ ቢኖር ከሹመቱ ይሻር። ፱:- ዲያቆን ከኤጲስ ቆጶስና ከቄስ በኋላ ይቁረብ። በማንኛውም ቦታ ዲያቆን በቄስ ፊት እና ጎን አይቀመጥ። ፲:- ከጠንቋዮች ጋር የሚበላ የሚጠጣ ካህን ቢኖርና ቃላቸው እውነት ነው የሚል ካህን ከሹመቱ ይሻር። ፲፩:- ሴቶች ወንዶችን ወንዶች ሴቶችን ክርስትና አያንሱ። ፲፪:- ወንድ ከሆንክ እናትህ ክርስትና ያነሳቻትን ልጅ ማግባት አትችልም። በመንፈስቅዱስ እህትህ ናትና። ሴት ከሆንሽ አባትሽ ክርስትና ያነሳውን ልጅ ማግባት አትችይም። በመንፈስቅዱስ ወንድምሽ ነውና። ፲፫:- ቀሳውስት ምእመናንን ከቁርባን አይከልክሏቸው። ፲፬:- ካህናት ተሳዳቢዎች አይሁኑ። ከሆኑ ግን ከሹመታቸው ይሻሩ። ፲፭:- በወር አባባ ያለች ሴት ከደሟ እስክትነጻ ወደ ቤተክርስቲያን አትግባ። በወር አበባዋ ወቅት ተደፋፍሮ ያቆረባት ካህን ቢኖር ከክህነቱ ይሻር። ፲፮:- ካህናት ከገዘቱት ሰው መብዓ መቀበል አይገባም። ፲፯:- ካህናት ቂመኛና ቁጡዓን አይሁኑ። _ ፲፰:- በዕለተ ሰናብት፣ በበዓለ ጸንጠቆስጤ ይጸልዩ እንጂ አይስገዱ። ፲፱:- ከክሕደት ወደ ትክክለኛዋ እምነት የተመለሰ ሰው ቢኖር በቂሱ ወይም በኤጲስ ቆጶሱ ፊት ሆኖ

ከሓድያንን ያውግዝ። ቁሱም ሦስት ጊዜ ቅብዐ ቅዱስ ይቅባው። ከዚያ በኋላ ያጥምቀው ያቁርበው። ትእዛዝ ፴፯:- በዓለም ላይ አራት ሊቃነ ጳጳሳት ይኑሩ። መዓርጋቸው አንደኛ መንበረ ጴጥሮስ ሮም፣ ሁለተኛ መንበረ ማርቆስ ግብፅ፣ ሦስተኛ መንበረ ዮሐንስ ኤፌሶን፣ አራተኛ መንበረ ጴጥሮስ አንጾኪያ ናቸው። ትእዛዝ ፴፰:- ሊቀ ጳጳሳት ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት በየሀገረ ስብከታቸው የሚሠሩትን ሥራ ይመርምር። ትእዛዝ ፴፱:- ኤጲስ ቆጶሳት ወደጳጳሳቸው በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰብሰቡ። ትእዛዝ ፵:- ጳጳስ ወኤጲስ ቆጶሳት ይትጋብኡ ኀበ ሊቀ ጳጳሳት ለሐድሶ ሥርዓት ካዕበ በበዓመት። ምእመናን ለሊቀጳጳሳቱ እጅ መንሻ ገጸ በረከት ይስጡት። ይህ አንቀጽ ግዘት የለበትም። ትእዛዝ ፵፩:- ከካህናት ወገን በበደሉ ምክንያት የተከሠሠ ቢኖር ማኅበረ ኤጲስ ቆጶሳት ይጥሩት። ሁለት ሦስት ጊዜ ይጥሩት። ካልመጣ አውግዘው ይለዩት። ትእዛዝ ፵፪:- አንዱ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን በሕይወት እያለ ሌላኛው ኤጲስ ቆጶስ ሊፈታው አይገባም። ከሞተ በኋላ ግን መርምሮ ሊፈታው ይችላል። ትእዛዝ ፵፫:- ኤጲስ ቆጶስ ሹመቱን ለዘመድም ይሁን ለባዕድ አያውርስ። ማኅበረ ምእመናንና ካህናት ቀጥሎ የሚገባውን ይሹመ እንጂ። ትእዛዝ ፵፬:- በመማለጃ (በጉቦ) ክህነት የተቀበለ ሰው ቢኖር ከክህነቱ ይሻር። ትእዛዝ ፵፭:- በአንዲት ሀገረ ስብከት ሁለት ኤጲስ ቆጶስ ሊሾም አይገባም። ትእዛዝ ፵፮:- ባል ሚስቱ ብትበድለው ይታገሣት። እምቢ ብትል በቂስ ያስመክራት። ቂሱን አልሰማም ብትል በኤጲስ ቆጶሱ ያስመክራት። ኤጲስ ቆጶሱን አልሰማም ብትል ባል የፈለገውን ያድርግ። ሌላ ሊያገባም ቢወድ ያግባ፣ ሊመነኩስም ቢወድ ይመንኩስ። ትእዛዝ ፵፯:- ወላጆች ልጆቻቸውን ለማያምን ሰው አያጋቧቸው። ትእዛዝ ፵፰:- ቤተክርስቲያን የምትመግባቸው እንዳታጣ ካህናት አይብዙ። (ቢያንስ) ሰባት ይሁኑ። ከዚህ የተረፉት ከውጭ ሆነው ያገልግሉ። ይህ ግዘት የሌለበት ነው። ትእዛዝ ፵፱:- በጸሎት ጊዜ የሊቀጳጳሳቱን፣ የጳጳሱንና የኤጲስ ቆጶሱን ስም ይዘክሩ። ይህንን ያላደረገ ቢኖር ሲኖዶስ ያወግዘዋል። ትእዛዝ ፶፬:- ከጳጳሳት አንዱ ቢሞት ካህናት ዲያቆናት አበምኔቶች ኤጲስ ቆጶሳት ጳጳሳት ከበድኑ ፊት ይሒዱ። ለሕዝቡም አባታቸው ነውና ይሰብሰቡ። ትእዛዝ ፶፩:- ኃጢአት ሠርቶ የበደለ ሰው ንስሓ ቢገባ ይቀበሉት። ትእዛዝ ፶፪:- የማያምን ያገባች ሴት ከምእመናን ትለይ። ሁለት ሚስት ያገባ ቢኖርም ይለይ። ትእዛዝ ፶፫:- ሰው ልጁን ወይም እህቱን ያለፈቃዳቸው ሊያጋባቸው አይገባም። ይህን ያደረገ ቢኖር ከምእመናን ይለዩት። ንስሓ ከገባ ይቀበሉት። ትእዛዝ ፶፬:- የምታምን ሴት ስለዝሙት ብላ የማያምን ወንድን ብትከተል፣ የሚያምን ወንድ ስለዝሙት ብሎ የማታምን ሴትን ቢከተል ንስሓው ከቤተክርስቲያን ሦስት ዓመት እንዳይገቡ ይከልከሉ። በኋላ ቁሱ ውሃ አምጥቶ ቅብዐ ቅዱስ ጨምሮ ጸልዮ ይርጫቸውና ወደ ምእመናን ይቀላቀሉ። ትእዛዝ ፶፭:- ለነዳያንና ለድውያን እንዲሁም ለእንግዳ የሚሆን ቤት ይሥሩ። ኤጲስ ቆጶሳቱም ከመነኮሳት መልካም ሥነ ምግባር ያለውን መርጦ ይሹምላቸው። ቤተክርስቲያን ገንዘብ ከሌላት ዲያቆኑ ከምእመናን ይሰብስብላቸው። ትእዛዝ ፶፮:- ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ ሊቃነ ካህናት አብረውት ሄደው ወደሀገረ ስብከቱ ያድርሱት። ከዚያም ለወራት የሠራውን ይገምግሙትና ለጳጳሱ ያሳውቁት። ትእዛዝ ፶፯:- ኤጲስ ቆጶስ ሀገረ ስብከት አነሰኝ ብሎ ወይም ከእርሱ የተሻለ ነው ብሎ ወደሚያስበው ወደሌላ ሀገረ ስብከት ሊሄድ አይገባውም። ትእዛዝ ፶፰:- ዲያቆናዊትነት የምትሾም ሴት ሴቶችን ታስተምራቸው። ፷ ዓመት የሆናት ትሁን። ትእዛዝ ፶፱:- የካህናት

አለባበስ እንደ ሕዝባውያን አለባበስ አይሁን። ራሳቸውን በአክሊል ይሸፍኑ። የብርና የወርቅ ቀለበት አያድርጉ። ትእዛዘ ፫፪:- ኤጲስ ቆጶስ በዝሙት ቢወድቅ ከሹመቱ ይሻር።

አስሩ ትዕዛዛትና ስድስቱ ቃላተ ወንጌል

ሕገጋተ ወንጌል ክፍል ፩

ጌታ ካስተማረን ከስድስቱ ሕግጋተ ወንጌል አንዱ "አትሳደብ፣ አትቆጣ፣ ታረቅ" የሚለው ነው። ሰው እግዚአብሔርን ከማመስገኑ በፊት፣ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ከማቅረቡ በፊት፣ ከመስበኩ በፊት የተጣላውን መታረቅ አለበት። ሳይታረቅ ግን የስብከት መባ የዝማሬ መባ አያቅርብ። ስድብ በኮርስ የሚሰጥበት ዘመን ላይ ደርሰናል። አቡነ ሺኖዳ የሚሉት ነገር አለ። ሰይጣን ዘፈን ኃጢዓት ነው የሚለውን ሰው ሁሉ ስለሚያውቅበት ዘፈንን "ኪነ-ጥበብ" ብሎ የጥበብ ስም ያላብሰዋል። በዚህ ጊዜ ሰው ኃጢዓት ሳይመስለው ይሰራዋል። በዘመናችን እየሆነው ያለውም ይህ ነው። ሰይጣን ስድብ ኃጢዓት ነው የሚለውን ሰው ሁሉ ስለሚያውቅበት ስድብን "ተግሣጽ" የሚል ስም ያላብሰዋል። ሰውም በመሳደቡ ንሥሓ እንዳይገባ የገሠጽኩ መስሎት በሰይጣን ወጥመድ ይገባል። ወንጌል የፍቅር ሕግ ናት። ስድብን፣ መሰዳደብን አትፈቅድም። ሰው ቢያስቀይምህንኳ ይቅር ማለትን ነው ወንጌል የምታስተምረን። ማቴ. ፭፣፳፪-፳፭ "በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል። ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሀነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል። እንግዲህ መብትን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ። አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ። በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ። አብረኽው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ" ። በሐሳብ፣ በእይታ፣ በአመለካከት፣ በአነጋገር፣ በአሰራር ላንስማማ እንችላለን። ይህ አለመስማማትም ወደ ቁጣ ጠብ ወደ መገዳደል ሊያደርሰን ይችላል። ነገር ግን ያለፈውን በይቅርታ አልፈን። የበደለው ክሶ የተበደለው ተክሶ ለወደፊቱ ሰላም ሲባል መታረቅ የታላላቆች ሥራ ነው። ጌታም በአንቀጸ ብጹዓን ማቴ. ፭፣፱ "የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው። የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና" ብሎ ነግሮናል። በትርጓሜያችንም ቆላውን ወርደው ደጋውን ወጥተው የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው ብሎ ስለ አስታራቂዎች ከተናገረ በኋላ የሚያረቁ ታራቂዎችም ብፁዓን ናቸው ብሏል። ስለዚህ ለአፋችን መዝጊያ እናብጅለት። አፋችን ለስድብ ሳይሆን ለምስጋና ይከፈት። ባመሰገንንበት አፋችን አንሳደብበት። ቁጣን በትዕግሥት እናሸንፈው። ከስሜት በላይ እንሁን። የተረጋጋን እንሁን። በክርስቶስ ሕግ እንመራ።

ሕገጋተ ወንጌል ክፍል ፪

የሰው ልጅ ወደ ወጣትነት እድሜው ሲጠጋ ሴት ወንድን፣ ወንድ ደግሞ ሴትን የማግኘት ፍላጎት ያድርበታል። ይህ በራሱ ስህተት/ኃጢዓት አይደለም። የመሳሳብ ስሜት ተፈጥሯዊ ነው። ይህ ደግሞ በሥርዓት እንዲሆን መድኃኔዓለም ክርስቶስ ሕግ ሰርቶልናል ሥርዓት አበጅቶልናል። ይኽውም ጋብቻ ነው። ጋብቻ ለመረዳዳት፣ ዘር ለመተካት እና ለአቅልሎ ፍትወት ነው። ስለዚህ ሰው በፍትወት እንዳይወድቅ ማግባት ይገባዋል። ምክንያቱም አንድ ወንድ ሳያገባ ከሌላይቱ ሴት ጋር ግንኙነት ቢያደርግ አመነዘረ፣ ዝሙት ሰራ ይባላል። ይህ ደግሞ አታመንዝር ያለውን ሕግ አስፈርሶ ወደ ሲኦል ያስገባል። ሰው ደግሞ በደስታ በገነት ይኖር ዘንድ የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ አለበት። ፍትወታዊ ስሜትን ታግሦ በድንግልና

መኖር ታላቅ አክሊልን ያሰጣል። ብዙ ቅዱሳን በድንግልና የኖሩት አልፈተን ብለው አይደለም። ፈተናውን ተቋቁመው አልፈውት ነው። ከሰው ልጆች ፍትወት እንስሳዊት ፈጽሞ ያልነበረባት እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። ወንጌላዊው ዮሐንስም የጌታን መታጠቂያ ከታጠቀ በኋላ ፍትወት እንስሳዊት እንደጠፋችለት ይነገራል። ለዚህም በቅዳሴ ወድንግልና ለዮሐንስ ይባልለታል። የሌላ የሆነችን ሴት አይቶ በልብ መመኘት ቁጥሩ ከማመንዘር ነው። ያለዝሙት ምክንያት ሚስትን መፍታትም ቁጥሩ ከማመንዘር ነው። እዚህ ላይ በወንድ አንቀጽ ይነገር እንጂ ትእዛዙ ለሴትም ጭምር ነው። ለሴት የሌላ የሆነን ወንድ አይታ በልብ መመኘት ማመንዘር ነው። ማየት ኃጢዓት አይደለም። አይቶ መመኘት ግን ኃጢኣት ይሆናል። የሩካቤ ምስል እያዩ ግለ ሩካቤ ማድረግ ትልቅ የአመንዝራነት ኃጢዓት ነው። ሰው እዚህ ደረጃ እስኪደርስ ራሱን ከሚያጎሳቁል አያገባምን!? ከእንዲህ ዓይነት ክፉ ሥራ ያላችሁ ሰዎች ንሥሓ ግቡ። [በብዛት የተጠየቅኩት ጥያቄ ስለሆነ ዛሬ ልመልሰው ብየ ነው]። የጋብቻ ሕግ የተሰራውኮ ሰው እንዲህ በፍትወት እንዳይሰቃይ ነው። በፍትወት እንዳትሰቃዩ አግቡ፣ ተጋቡ። ማቴ. ፭፣፳፰-፴፪ "ወደሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል_ ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል። የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል"። በነውር የተፈታችውን ሴት ንሥሓ እስክትገባ ማንም ሊያገባት አይገባም። ንሥሓዋን ከጨረሰች በኋላ ግን ጨዋነቷ በብዙ ሰዎች ዘንድ ሲመሰከርላት እርሷም ማግባት ትችላለች። ሌላውም ሊያገባት ይችላል። ማንኛውም ሰው እስኪያገባ ድረስ ክብረ ንጽሕናውን ይጠብቅ። ክብሩን ለሚያገባት ይስጥ። እርሷም እንዲሁ። ባለማወቅ ክብራችንን ያጣን ሰዎች ካለንም ንሥሓ ገብተን ለወደፊቱ ለመታመን እንጣር። ትዳር ክቡር ነው። በሆነ ባልሆነው መጣላት አይገባም። ችግሮችን በውይይት በይቅርታ በዕርቅ እየፈቱ መኖር ይገባል።

ሕገጋተ ወንጌል ክፍል ፫

ማርያምን፣ ድንግልን፣ ጊዮርጊስን፣ ተክልየን፣ እግዚአብሔርን፣ በዓታን፣ ሚካኤልን፣ እኔ ልሙት፣ ወዘተ እያሉ መማል አይገባም። በብሉይ ኪዳን በእውነት ከሆነ በእግዚአብሔር ሥም መማል ይቻል ነበር። በሐዲስ ኪዳን ግን ፈጽማችሁ አትማሉ ስለተባለ እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት ማለት እንጂ መሓላ አይፈቀድም። ነገር ግን ዳኛ አዝዞ ከሆነ፣ በሽምግልና ወቅት ባላጋራም ይማልልኝ ቢል መጀመሪያ ተከሳሹ ለከሳሹ መማል ጥሩ እንዳልሆነ ይንገረው። ከሳሹ ፈቅዶ ይማል ካለ ግን በማዩ (በተከሳሹ) በደል የለበትም።ይህንን ፍትሐ ነገሥትን ባለፈው ስንማማር አይተነዋል። በአብነት ትምህርት ቤቶችም በሌላውም "እመቤቴን፣ አዛኝቴን፣ ማርያምን፣ አምላክን" ወዘተ እየተባለ መማል አልተፈቀደም። ምናልባት እንዲህ ሲሉ የሰማናቸውና የምንሰማቸው ሰዎች ካሉ እንኳ ፍቅራቸውን ለመግለጽ የተጠቀሙበት መሆኑን ብንረዳም ስህተት መሆኑን ግን አስምረን እንናገራለን። ነገር ግን ዳኛ አዝዞ፣ ባላጋራ አውርዶም ከሆነ በእግዚአብሔር ሥም ወይም በቅዱሳኑ ስም መማል ይገባል እንጂ በጣዖት ስም መማል አይፈቀድም። ከዚህ ውጭ ግን ዳኛ ሳያዝዝ፣ ባላጋራ ሳያወርድ መማል ፈጽሞ አይቻልም። ሕገ ወንጌል ይከለክላል። የልዑል እግዚአብሔርን ሥም፣ የቅዱሳኑን ሥም በከበረ ነገር ማለትም በማጎሌት፣ በስብከት፣ በጸሎት፣ በመንፈሳዊ ንግግር ነው መጥራት ያለብን። ማቴ. ፭፣፴፬ "ከቶ አትማሉ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና። በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና። በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና። በራስህም አትማል።

አንዲቱን ጸጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና። ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን። ከእነዚህም የወጣ ከክፉው ነው"።

ሕገጋተ ወንጌል ክፍል ፬

ማቴ. ፭፣፴፱ "ክፉን በክፉ አትቃወሙ"። ክፋትን የሚጠላ ሰው ክፋትን ማስወገድ ያለበት በመልካም ነገር ነው። ሐሜትን በሐሜት፣ ስድብን በስድብ፣ ጥፊን በጥፊ፣ ውሸትን በውሸት፣ ሌብነትን በሌብነት፣ ክህደትን በክህደት፣ ኩራትን በኩራት፣ ትዕቢትን በትዕቢት፣ ተንኮልን በተንኮል ማሸነፍ አይቻልም። በዚህ መልኩ አሸነፍኩ ያለ ሰው ካለ እንኳ ያ ሰው ተሸናፊ መሆኑን ይወቅ። ለሰው ልጅ ከምንም በፊት መልካም የሚባሉትንና ክፉ የሚባሉትን መለየት ይገባዋል። ከዚህ በኋላ ክፋትን በመልካም ማሸነፍ ይገባዋል። ኃጢዓትን በንሥሓ፣ ውሸትን በእውነት፣ ትዕቢትን በትሕትና፣ ሌብነትን በምጽዋት፣ ሆዳምነትን እና ስስታምነትን በጾም፣ ስድብን በትዕግሥት፣ ክህደትን በጽድቅ፣ ስንፍናን በጸሎት ማሸነፍ ይገባል። ክርስቲያናዊው አሸናፊነት ይህ ነው። ክፉን በክፉ አንቃወም። እኛ በመልካምነት ላይ ሳንሆን ሌላው መልካም ካልሆነ ብለን ሌላውን ለመንቀፍ መጣር የለብንም። ከምንም በፊት ራሳችንን በእውነት በጽድቅ እናሸንፍ። ራሳችንን ካሸነፍን በኋላ ሌላውን በውሸት ያይደለ በእውነት ለማሸነፍ ቀላል ነው። በሀገራችን ያለውን የመሰለ ውንብድናን ደግሞ በደንበኛ የፍትሕ ሥርዓት ማሸነፍ እንችላለን። የፍትሕ ሥርዓቱ፣ የመንግሥት አስተዳደሩ እና የመሳሰሉት ጉዳዮች የተበላሹ ከሆኑ ደግሞ መጀመሪያ እነርሱን ራሳቸውን እናክም። ኑ በሉ መጀመሪያ ራሳችንን ከማሸነፍ እንጀምር።

ሕገጋተ ወንጌል ክፍል ፭

የክርስትና ሕግ የወንጌል ሕግ የትሩፋት ሕግ ይባላል። አሁን አሁን በሕግ ሳይሆን በስሜት የሚመራው እየበዛብን ነው። ከሕጉ ይልቅ ስሜቱን የሚከተለው በዛ። የክርስትና ሕግ ትምህርት ጠላትን እስከ መውደድ ነው። ይህ ግን መተንተን አለበት። ጠላትን መውደድ ማለት ሲያጠፋ ዝም ማለት አይደለም። ሲያጠፋ ለሕግ ማቅረብ ነው። ጥፋተኛን ወደ ሕግ ማቅረብ ራሱ የመውደድ ምልክት ነውና። በጥፋተኛ ላይ መፍረድ የመውደድ ምልክት ነው። እግዚአብሔርኮ ስለሚወደን ነው ስናጠፋ የሚቀጣን። እግዚአብሔር ይጌሥጽ ዘአፍቀሮ እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻል የሚባለውም ለዚያ ነው። ጠላትህን ውደድ ማለት ፍትሕን አጥፋ ማለት አይደለም። ፍትሕን አጠንክር ማለት ነው። ጥፋተኛ የሚቀጣው ጥፋቱን እንዲተውና እንዲታረም ነው። አንድ ሰው አጥፍቶ ጥፋቱን ማለባበስ እና ለሕግ እንዳይቀርብ ማድረግ ግን የጥላቻ ምልክት ነው። እንዲታረም እድል አልሰጠነውምና። ጠላትን የመውደድ ትርጓሜ ይህ ነው። ሲያጠፋ ተው ማለት መልካም ሲሰራ ማበረታታት ነው። እዚህ ላይ ውደዱ የተባለ ሰው ሆኖ እኛን የሚጠላንን ነው እንጂ ጥንተ ጠላት ዲያብሎስን ውደዱ ማለት አይደለም። ማቴ. ፭፣፵፬_፵፰ "እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ"። ሲጠቃለል ስድስቱ ሕገጋተ ወንጌል የሚባሉት:- ፩) አትሳደብ/አትቆጣ።

፪) ወደሴት አይቶ የተመኘ አመነዘረ (አታመንዝር)። ፫) ያለዝሙት ምክንያት ሚስትህን አትፍታ። ፬) ፈጽመህ አትማል። ፭) ክፉን በክፉ አትቃወም። ፮) ጠላትህን ውደድ ናቸው።

ትእዛዘ ፈጣሪ ክፍል ፩

ዘፀ. ፳፥፫ "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩልህ"

ይህን ዓለም ካለመኖር በከኃሊነቱ የፈጠረ እና ያስገኘ ለእርሱ ግን አስገኝ የሌለው ባሕርየ ባሕርይ፣ መሠረተ መሠረት፣ ሕይወተ ሕይወት፣ ምክንያተ ምክንያት፣ ፈጣሬ ፍጥረታት እግዚአብሔር ነው። እርሱ ሰውና መላእክትን ለክብር ፈጠረ። ሰው ግን ከፈጣሪው የተሰጠውን ነጻነት ለበጎ ማዋል ሲገባው ራሱን ለማጥፋት ተጠቀመበት። ይህ ቢሆንም ግን የሰው ልጅ እንደጠፋ እንዳይቀር በግብረ ባሕርይው፣ በስነ መለኮቱ ይቅር ባይ እግዚአብሔር በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን አሳይቶ አድኖታል። ፈጣሪ ረቂቅ ነው ለማንም አይታይም። በሁሉ ቦታ ያለ ነው። ሁሉን ቻይ ነው። በፍጥረታት ላይ የሰለጠነ እርሱ ነው። የሰው ልጆች እርሱን ፈጣሪን ትተው ራሳቸው የቀረጿቸውን ጣዖታት አመለኩ። እግዚአብሔር ለእኛ ጥቅም የፈጠራቸውን የሰማይ ኃይላትን እነ ፀሐይን፣ እነ ጨረቃን፣ እነ ከዋክብትን አመለኩ። አርሰን ቆፍረን ለምግብ፣ ለቤት፣ ለልብስ እና አጠቃላይ ለእኛ ጥቅም የተፈጠሩትን እፀዋትን፣ እንስሳትን፣ አራዊትን፣ ምድርን አመለኩ። የሰው ልጅ በራሱ ሕሊና በራሱ ልብ ወለድ ጠፋ። እግዚአብሔርም ሰዎች ሊያዩት በሚፈልጉት መልኩ አምላክነቱን ሳይለቅ ሰው ሆነ። ሰዎችም አዩት ዳሰሱት። ስለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ አየነው ዳሰስነው በጆሯችን ሰማነው አለ። ፩ኛ ዮሐ. ፩፥፩ "ንዜንዎክሙ በእንተ ውእቱ ዘሀሎ እምቅድም ውእቱ ዘሰማዕናሁ ወዘርኢናሁ በአዕይንቲነ ወዘጠየቅነ ወዘገሠግሠ እደዊነ በእንተ ነገረ ሕይወት" እንዲል። ስለዚህ የሁሉ አስገኝ ከሆነ ከእግዚአብሔር ውጭ ማንንም ማምለክ አይገባም። ማምለክ ማለት መገዛት ማለት ነው። ከፈጣሪ ውጭ የምንገዛለት፣ የምናመልከው፣ የምንፈራው ሊኖር አይገባም። ከፈጣሪ የሚለየን ምንም ነገር መኖር የለበትም። ከፈጣሪ አስበልጠን የምንወደው ነገር ካለ ግን ሌላ እያመለክን ነው ማለት ነው። ስለዚህ መመለስ አለብን። ከሁሉ አስቀድመን የፈጣሪን ሕግ እንጠብቅ። ፈጣሪን ማምለክ ሕጉን ትእዛዙን በመጠበቅ ነው።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ጣዖት ማምለክንና ተጠራጣሪነትን (Heresy) የሥጋ ሥራ ብሎታል። ገላ. ፭፥፳-፳፩።ሚርተኝነትንም የሥጋ ሥራ ብሎታል። ይህም እግዚአብሔርን ካለማመን ወገን የሆነ እና በሰይጣናዊ አሰራር አምኖ ሰውን የመጉዳት ክፉ ሥራ ነው። ሚርተኝነት ሰይጣንን ከማምለክ ወገን ነው። እኛ ግን እኛን የፈጠረን ፈጥሮም የሚያኖረንን እግዚአብሔርን እናመልካለን። በአምልኮቱ ያጽናን።

ትእዛዘ ፈጣሪ ክፍል ፪

ዘፀ. ፳፥፯ "የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ"

የእግዚአብሔር ሥም ኃይላትን የሚያደርግ፣ ተአምራትን የሚያደርግ፣ እኛን የሚቀድስ፣ ረድኤትን የሚሰጥ ነው። መዝ. ፻፳፬፥፰ "ረድኤታችን ሰማይና ምድርን በሰራ በእግዚአብሔር ስም ነው"። የእግዚአብሔር ስም እኛን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ነው። መዝ. ፹፥፯ " በእግዚአብሔር ስም ከፍ ከፍ እንላለን" እንዲል። በእግዚአብሔር ስም እናሸንፋለን። ስለዚህም የእግዚአብሔር ስም ጠላትን ሰይጣንን የሚያሸንፍ ነው። መዝ. ፻፲፰፥፲፩ "መክበቡንስ ከበቡኝ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኳቸው" እንዲል። ስለዚህ ክቡር የሆነው የእግዚአብሔር ስም በከበረ ቦታ፣ በከበረ

ጊዜ ይነገራል። በምስጋና፣ በጸሎት፣ በመንፈሳዊ ውይይት እና በመሳሰሉት ይጠራል። እንጂ በከንቱ ቦታ፣ በከንቱ ነገር አይነገርም። የፈጣሪን ስም በከንቱ አትጥራ ተብሏልና። እንኳንስ የፈጣሪ ስም የክቡራን ሰዎች ስምም በከንቱ ነገር አይጠራም። ቀድሞ በብሉይ ኪዳን በዓመት አንድ ጊዜ የሚጠራ የእግዚአብሔር ሥም ነበር። ያንንም ስም የሚጠሩት የተከበሩት ሊቀ ካህናቱ ነበሩ። ይህም ለእግዚአብሔር ስም ትልቅ ክብር ስለነበራቸው ነው። የእግዚአብሔር ሥም ክቡር ስለሆነ ይሰገድለታል። ፊል. ፪፣፲ "በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ" ተብሎ እንደተገለጸው። ለታቦት የጸጋ ስግደት የምንሰግደውም የጌታ ስም ስለተጻፈበት ነው። በተጨማሪም ሥጋው ደሙ ስለሚፈተትበት ነው። ስለዚህ በዋዛ በፈዛዛ ነገር መካከል የእግዚአብሔርን ስም መጥራት አይገባም። ዘፀ. ፳፣፯ "የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና"።

ትእዛዝ ፈጣሪ ክፍል ፫

ዘፀ. ፳፣፰-፲፩ "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ"

ሠራተኞቻቸውን በሰንበት እያሰሩ እነርሱ የሚያስቀድሱ አሰሪዎች አሉ። ይህ ልክ አይደለም። በሰንበት ቀን ሠራተኞች፣ አገልጋዮች ሳይቀሩ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ነገራተ እግዚአብሔርን የሚሰሙበት መሆን አለበት። ሰንበትን አክብር ሲባል በዋናነት ሰንበት የሚላት ቅዳሜን ነው። ጌታ ፍጥረታትን ፈጥሮ ያረፈባት ዕለት ናት። ጌታ አረፈ ስንል ግን ጌታ ድካም ኖሮበት አረፈ ማለት አይደለም። መፍጠሩን አቆመ ማለታችን ነው። ወአዕረፈ እግዚእነ እም ኩሉ ግብሩ እንዲል። ሰንበት እግዚአብሔርን ለማመስገን በተለየ እንድናከብራት የታዘዘች ዕለት ናት። ጌታ የተጸነሰባት፣ የተነሣባት ዕለተ እሑድንም ዕለተ እግዚአብሔር ሰንበተ ክርስቲያን ብለን እናከብራታለን። በሰንበት የማይሰሩ ሥራዎች ምን ምን ናቸው ከተባለ ሥጋዊ ሥራዎች ሁሉ ከዕለት ምግብ ሥራዎች ውጭ በሰንበት አይሰሩም። እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ስለባረካት ስለቀደሳት በሥርዓቱ ካከበርናት እንቀደስባታለን እንባረክባታለን። ረድኤትን እናገኝባታለን። ሰንበትን የታመሙትን በመጠየቅ፣ የተጣሉትን በማስታረቅ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ፣ መንፈሳዊ ሥራዎችን በመሥራት ልናከብራት ይገባል። ዘፀ. ፳፣፰-፲፩ "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው፤ አንተ፥ ወንድ ልጅህም፥ ሴት ልጅህም፥ ሎሌህም፥ ገረድህም፥ ከብትህም፥ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ፤ እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም"።

ትእዛዝ ፈጣሪ ክፍል ፬

ዘፀ. ፳፣፲፪ "አባትህንና እናትህን አክብር"

ለእኛ ወደዚህች ምድር መምጣት ምክንያት የሆኑን እናትና አባቶቻችን ናቸው። ስለዚህ እናከብራቸዋለን እንወዳቸዋለን። ማክበር ማለትም መታዘዝ እሺ ማለት ማለት ነው። ብናከብር ምን እናገኛለን ለሚለው መልሱ እድሜያችን እንዲረዝም ነው። የአባት የእናት ቡራኬ ለልጅ ይደርሳል። የያዕቆብ በረከት በልጆቹ አድሯል። በሕገ ልቡና ዘመን የተለያዩ ሀብታት በእናት አባት ምርቃት ይተላለፉ ነበር። እናት አባት የሚደሰቱበትን ሥራ እየሰራን በእነርሱ መመረቅ

ለእኛ ትልቅ በረከት ነው። ሰባት ዓይነት አባቶች አሉ። እነዚህም እግዚአብሔር፣ የቀለም አባት፣ የንሥሓ አባት፣ ወላጅ አባት፣ የክርስትና አባት፣ የጡት አባት እና የቆብ አባት ናቸው። እግዚአብሔርን በባሕርይው ክቡር ስለሆነ የባሕርይ ምስጋና እናመሰግነዋለን። የቀለም አባት የሚባለው ወንበር ተክሎ ጉባኤ ዘርግቶ ደቀመዛሙርትን የሚያስተምር ነው። ይህም ሰውን በእውቀት የሚወልድ ታላቅ አባት ነው። የንሥሓ አባት ስንበድል የሚናዝዘን ወደ መልካም ሕይወት የሚመራን መሪያችን ነው። የክርስትና አባት ከሕጻንነት ጀምሮ የክርስትናን ትምህርት ሊያስተምረን በቤተክርስቲያን ፊት ቃል ኪዳን የገባልን እና እያስተማረ ያሳደገን አባታችን ነው። የጡት አባት የሚባለው በጉዲፈቻ ያሳደገን አባታችን ነው። የቆብ አባት የሚባለው ደግሞ መነኮሳት ምንኩስናን የሚቀበሉበት አባታቸው ነው። ለምሳሌ እንጦንዮስ መቃርዮስን ወለደ ሲባል አመነኮሰው ማለት ነው። እኒህን ሁሉንም አባቶች እናከብራቸዋለን እንታዘዛቸዋለን እንወዳቸዋለን ማለት ነው። እናታችን ቅድስት ቤተክርስቲያንን እንውደዳት። ልጅነትን ያገኘንባት እናታችን ናትና። ዘፀ. ፳፣፲፪ "አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም"።

ትእዛዝ ፈጣሪ ክፍል ፭

ዘፀ. ፳፣፲፫ "አትግደል"

የሰው ልጅ የእግዚአብሔር አምሳል ነው። ዘፍ. ፩፣፳፯ "ሰውን በአርያችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር" ተብሎ እንደተጻፈ። ሰው እግዚአብሔርን የምናይበት የእግዚአብሔር አርዓያ እና ምሳሌ ነው። ስለዚህም ከሌሎች ፍጥረታት የከበረ ነው። በተለይም የክርስቲያን ሰውነት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተብሏል። መግደል የእግዚአብሔርን አርዓያ ወይም ምስል ማጥፋት ነው። መግደል የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ማፍረስ ነው። ሰው ሰውን ማክበር አለበት። ተከባብሮ ተዋዶ መኖር የሰውነት ትክክለኛ ትርጉሙ ነው። አለመግባባትን ያለ ደላላ ቀጥታ በመወያየት መፍታት ልዩነቶችን ያጠባል። በሀገራችን እየሆነ ያለው ጥላቻ መገዳደል ባለጉዳዮች ፊት ለፊት ከመነጋገር ይልቅ በየራሳቸው መሄዳቸው ነው። በመካከል ደላሎች እውነተኛውን ጥያቄ እና ችግር አደብዝዘው የሌለ ፈጥረው፣ ያለውን አስፍተው በማቅረባቸው ነው። አንዳንድ ጉዳዮች ሊያስቆጡን ይችላሉ። ነገር ግን ቁጣችንን በትዕግሥት አብርደን ጥልን በዕርቅ እና በይቅርታ ማፍረስ ይገባናል። ምክንያቱም። ቁጣ፣ ጥል እና መግደል ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው የሥጋ ፍሬዎች ናቸውና። ፍጻሜያቸውም እኛን ወደ ሲኦል ማስገባት ነው።ገላ. ፭፣፳ ። ባንገዳደልምኮ መሞታችን አይቀርም። ስለዚህ መሞታችን ካልቀረ ተስማምቶ፣ ይቅር ተባብሎ፣ በአንድነት መንፈስ ብንኖር እንጠቀማለን። ለልጆቻችን ለወንድሞቻችን የመገዳደል ታሪክ አናውርሳቸው። ይቅር ተባብለን። ሰላምን እናውርስ። ዘፀ. ፳፣፲፫ "አትግደል"።

የፈጣሪ ትእዛዝ ክፍል ፮

ዘፀ. ፳፣፲፬ "አታመንዝር"

ሴት ልጅ/ ወንድ ልጅ ሌላውን በዝሙት ለመሳብ የሚለብሱት ልብስ፣ የሚያደርጉት ጌጥ የምንዝር ጌጥ ይባላል። ይህን ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ የሥጋ ሥራ ብሎታል። ገላ. ፭፣፳፩ "ይህንን የሚያደርግ የእግዚአብሔርን መንግሥት አያይም ተብሏል"። አንድ ሰው ሌላውን ለዝሙት የሚያነሳሳ አለባበስ ማለትም ሰውነትን ጥብቅ አድርጎ የሚያሳይ አለባበስ ወይም ራቁትን የሚያጋልጥ ልብስ መልበስ አይገባውም። ቅዱስ ጳውሎስ ቀጥሎም መዳራትን የሥጋ

ሥራ ብሎታል። መዳራት የሚባለው የእጅ ጉንተላ፣ የዓይን ጥቅሻ፣ የነገር ጉሰማን የሚያጠቃልል ቃል ነው። እኒህ ነገሮች ሁሉ ወደ ዝሙት የሚስቡ ነገሮች ስለሆኑ ሰው ከእነዚህ መራቅ አለበት። ማግባት ቢፈልግ እንኳ በሥርዓት ጠይቆ፣ በሥርዓት ቆይቶ መሆን አለበት። ገና እጮኛማቾች ነን ተብሎ ፍትወት ቀስቃሽ ንግግር፣ እንዲሁም አካላዊ ንክኪ ማድረግ አይገባም። የሰው አካሉ ክቡር ነው። ስለዚህም አካሉንም ሕሊናውንም በንጽሕና ማቆየት ይጠበቅበታል። ሰውነትን ማርከስ አይገባም። ርኩሰት የሥጋ ስራ ነው ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ነግሮናልና። ማንኛውም ሰው የእርሱ/የእርሷ ካልሆነች/ካልሆነ ሴት/ወንድ ጋር ግንኙነት ከፈጸመ/ከፈጸመች ዝሙት ሰራ/ሰራች ይባላል። አታመንዝር ያለውን ሕግ መሻር ስለሆነ በነፍስም በሥጋም ቅጣትን ያመጣል። ማንኛችንም ሰዎች ራሳችንን በብዙ ረገድ በንጽሕና መጠበቅ ይገባናል። ገላ. ፭፣፲፱-፳፩ ዘፀ. ፳፣፲፬ "አታመንዝር"።

የፈጣሪ ትእዛዝ ክፍል ፮

ዘጸ. ፳፣፲፭ አትስረቅ

ስርቆት ያልለፉበትን ገንዘብ ለራስ ማድረግ ነው። ስርቆት ሌሎች የለፉበትን ገንዘብ በውንብድና፣ በማጭበርበር፣ በተንኮል፣ በዝርፊያ መቀማት ነው። የሌላውን ገንዘብ የእኔ ነው ማለት ሌብነት ነው። በቀድሞ ዘመን ሌባ ሲሰርቅ ከተገኘ እጁን ይቆረጥ ነበር። ሌላውም ያንን እያየ አይሰርቅም ነበር። በስርቆት ምክንያት እናት ከልጅ ሳትገናኝ ትቀራለች። የብዙ ሰዎች ሕይወት ምስቅልቅል ይላል። ክርስቲያን ወጥቶ ወርዶ ሰርቶ ባገኘው ገንዘብ መኖር አለበት እንጂ አይሰርቅም። በክርስትና መስራት የማይችል ሰው ቢኖር እንኳ ይለምን እና ይብላ ይላል እንጂ ይስረቅ አይልም። ያጣ ይለምን ነው የተባለ። ጉቦ፣ ሙስና የስርቆት ዓይነቶች ናቸው። ሰው በብቃቱ ተወዳድሮ ሀገርን መጥቀም ሲገባው ብቁ ሰዎች እየተገፉ ደካማ ሰዎችን በዝምድና፣ በጉቦ፣ በዘር፣ በቋንቋ መቅጠር ሀገራችንን በጠቅላላው ዓለማችንን እየበጠበጣት ይገኛል። ሁሉም ከተንኮል ወጥቶ በሚችለው ተከባብሮ እየሰራ ሀገሩን ማሳደግ ይኖርበታል። እግዚአብሔር ለሁላችንም ልዩ ልዩ ጸጋ ሰጥቶናል። በተሰጠን ጸጋ ሳንኮራ አንድም ሳናፍር በትሕትና መስራት ከስርቆት ያድናል። ብዙ ሰው ወደ ስርቆት የሚሄድ ዝቅ ብሎ እንዳይሰራ ወይም እንዳይለምን ኩራት ይዞት ነው። ነገር ግን ኩራት የሥጋ ሥራ ነው። ገላ. ፭፣፳። ሲጀምር ከእግዚአብሔር ባገኘነው ጸጋ ማፈርም መኩራትም አይገባም። ኩራት የአላዋቂዎች ሥራ ነው። ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሥራ እድል ማመቻቸት ከመንግሥት ይጠበቃል። ነገር ግን ሥርዓተ መንግሥቱም ለሌብነት የተስማማ ከሆነ ትልቅ አደጋ ነው። አትስረቅ ብሎ ማስተማር አንድ ነገር ነው። በተጨማሪም አትስረቅ ላልነው አካል ሥራ መፍጠር ግዴታ ነው። በዋናነት ችግሩን ብቻ ሳይሆን የችግሩን ምንጭም ማጥፋት ወሳኝ ነገር ነውና። ሌላው አስራትን አለማውጣትም ሌላኛው የስርቆት ዓይነት ነው። አስራት የሚሰጠው ደግሞ ለቤተክርስቲያን ነው። አስራት ለግለሰብ አይሰጥም ነውር ነው። ዘጸ. ፳፣፲፭ አትስረቅ።

የፈጣሪ ትእዛዝ ክፍል ፯

ዘፀ. ፳፣፲፮ "በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር"

በቀድሞ ዘመን በሐሰት የመሰከረ ሰው ምላሱ ይቆረጥ ነበር። ሌላውም ይህንን እያየ አይዋሽም ነበር። ውሸት እያደር ያቀላል። ውሸት ያልተደረገውን እንደተደረገ የተደረገውን እንዳልተደረገ መናገር ነው። ውሸት የሆነውን እንዳልሆነ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ መናገር ነው። ውሸት

የአንደበት ኃጢዓት ነው። በንግግር ሊገለጽ ይችላል። በጽሑፍ ሊገለጽ ይችላል። የውሸት ተቃራኒ እውነት ነው። በሐሰት መመስከር ትልቅ በደል ነው። ክርስቲያን እውነቱን እውነት ሐሰትን ሐሰት የሚል ነው። ለእውነት ትልቅ ክብር አለው። ቅዱሳን ሰማእታት እውነትን ተናግረው ለእውነት ሞቱ። በውሸት ከመኖር በእውነት መሞት ይበልጣልና። ትልቅ ክብር አለውና። ዋሽ ሰው ለራሱ፣ ለጓደኛው፣ ለዘመድ፣ ለቤተሰብ፣ ለሀገር አይታመንም። ውሸትን መታገል ይገባል። ሰው ለተርእዮ፣ ለመከበር፣ ለሥጋዊ ጥቅም ሊዋሽ ይችላል። ነገር ግን የውሸት እድሜዋ አጭር ስለሆነ በኋላ ከሚያፍር እውነቱን ተናግሮ ቢኖር ይሻለዋል። ሰው እውነት መናገር ቢያቅተውንኳ ውሸት ላለመናገር ዝም ማለት አለበት። ዘፀ. ፳፣፲፮ "በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር"።

ትእዛዘ ፈጣሪ ክፍል ፱

ዘፀ.፳፣፲፮ "የባልንጀራህን ቤት አትመኝ"

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው የሰጠው ጸጋ ልዩ ልዩ ስለሆነ አንዱ በሌላው መመቅኘት፣ መቅናት እንዲሁም መፈካከር አይገባውም። ምክንያቱም ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ምቀኝነት፣ ቅንዐትና ፉክክር የሥጋ ፍሬዎች ናቸው። እኛን ወደሲኦል የሚመሩን ክፉ መንገዶች ናቸው። ገላ. ፭፣፳። ሰው ራሱን ከማንም ጋር ማወዳደር አይገባውም። ራሱንም መለካት ያለበት ከእግዚአብሔር ሕግ አንጻር ነው እንጂ ከሰው አንጻር አይደለም። እግዚአብሔርም ዋጋ የሚሰጠን ከሰዎች ምን ያህል ተሸላችኋል በሚለው ሳይሆን ሕጌን ትእዛዜን ምን ያህል ጠብቃችኋል ብሎ ነው። የሌላ ሰው ንብረት የሌላ ነው። እኛ ልንመኘው አይገባንም። እኛ በራሳችን ሰርተን ያን የመሰለ ልናፈራ እንችላለን እንጂ ያንኑ ራሱን መመኘት ኃጢዓት ነው። ሁሉም በተሰጠው ጸጋ ያመስግን እንጂ አንዱ በአንዱ መቅናት አይገባውም። አንዱ የአንዱን አይመኝ። ዘፀ. ፳፣፲፯ "የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ"።

የፈጣሪ ትእዛዝ ክፍል ፲

ዘሌ. ፲፱፣፲፰ "ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ"

ከአስሩ ትእዛዛት የመጨረሻው ሌላውን ሰው እንደ ራስ መውደድ ነው። ለራሳችን የምናስበውን መልካም ሐሳብ ለሌሎችም መመኘት፣ ለእኛ ሊደረግልን የምንፈልገውን ለሌላውም እንዲደረግ መፈለግና ማድረግ ናቸው። በእኛ ሊሆንብን የማንፈልገውን በሌላውም እንዳይሆን መመኘት ነው። ባልንጀራውን እንደራሱ የሚወድ ሰው በሰዎች ደስታ ይደሰታል በሰዎች ኀዘን ደግሞ ያዝናል። ለሁሉም ሰው መልካም አሳቢ ነው። የማንንም መጥፋት አይፈልግም። አንድ ሰው አጥፍቶ ቢገኝ እንኳ ለንሥሓ እንዲያበቃው ይመኛል እንጂ ጥላቻ የለበትም። ይህንን ሕግ የሚፈጽም ሰው ዘረኝነትን አያውቀውም። ሰው ዘረኛ የሚሆነው ባልንጀራውን እንደራሱ አለመውደድ ሲጀምር ነው። ኦርቶዶክሳዊው ሕይወት ግልጽና ውብ ነው። ሰው ከኦርቶዶክሳዊው ሕይወት እየራቀ ሲሄድ እየከፋ ይሄዳል። አንድ ሰው ጥሩ ነው የሚባለው ኦርቶዶክሳዊ ሲሆን ነው። ኦርቶዶክሳዊነት እውነትን ከጥበብ፣ ፍቅርን ከፍትሕ፣ ትሕትናን ከሙሉ ሰብእና ጋር አጣምሮ የያዘ ማንነት ነው። ኦርቶዶክሳዊው ሕይወት ራስ ወዳድነት የለበትም። አንዱ ለሁሉ ያስባል። ሁሉም ለአንዱ ያስባል። የኦርቶዶክሳዊነት ማዕከሉ ክርስቶስ ነው። ዘሌ. ፲፱፣፲፰ "አትበቀልም፥ በሕዝብህም ልጆች ቂም አትያዝ፥ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፤ እኔ

እግዚአብሔር ነኝ"። አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮም ላስፈጸመን ልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይገባል።

መልካም ሥራ

ጸሎት

ጸሎት ማለት ምስጋና ያለበት ልመና ማለት ነው። በጸሎት ኃጢዓትን መታመን (ተአምኖ ኃጣውእ) አለ፣ በጸሎት ዕበያተ እግዚአብሔርን መመስከር አለ። በጸሎት እውነትን መመስከር አለ። በጸሎት ይቅርታ አለ። ጸሎት ብሂል ተናግሮ ምስለ እግዚአብሔር። ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ነው። በፈጣሪ ፊት የምንናገረው ንግግር ነው። እርሱም በፍቅር የልጆቹን ንግግር ሰምቶ ምላሽ የሚሰጥበት ነው። ጸሎት ሥርዓት አለው። ይኸውም:- ፩) ቀጥ ብሎ መቆም ፪) ፊትን ወደ ምሥራቅ ማዞር ፫) ወገብን መታጠቅ (በንጽሕና መቆም) ፬) ማማተብ ፭) ዓይንን ከቃሉ ከቃሉ ልብን ከምሥጢሩ አድርጎ መጸለይ ናቸው። ስንቆም በደንብ ነጠላችንን መስቀለኛ ለብሰን ይሆናል። ከዚህ በኋላ ውዳሴ ማርያምን፣ መዝሙረ ዳዊትን፣ ትምህርተ ኅቡዓትን፣ ወንጌልን፣ የመሳሰለውን መጸለይ ነው። መሻታችንን ለፈጣሪ ማሳወቅ ነው። ይህም እግዚአብሔር አስቀድሞ ፍላጎታችንን የማያውቅ ሆኖ አይደለም። በእኛ መናገር እና በእኛ ፈቃድ መልካሙን ሁሉ ይሰጠን ዘንድ ነው። ማንኛውም ክርስቲያን ቢያንስ በሰባቱ ጊዜያት መጸለይ አለበት። ሰባቱ ጊዜያት የተባሉትም:- ፩) ጠዋት ፪) ሦስት ሰዓት ፫) ስድስት ሰዓት (ቀትር) ፬) ዘጠኝ ሰዓት ፭) ሠርክ ፮) ምሽት ሦስት ሰዓት ፯) ሌሊት ስድስት ሰዓት ናቸው። ምክንያታቸውን ፍትሐ ነገሥት ስንማማር ስለገለጽነው ከዚያ ይመልከቱ። ሌላው ምግብ ልንበላ ስንጀምር ምግብን የሰጠንን እግዚአብሔርን አመስግነን አቡነ ዘበሰማያት ብለን እንበላለን። በልተን ከጨረስን በኋላም ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ብለን አቡነ ዘበሰማያት ብለን እንጸልያለን። ከጸሎት ሁሉ አቡነ ዘበሰማያትን እና መዝሙረ ዳዊትን ስንደግም እግዚአብሔር ደስ ይሰኝብናል። ውዳሴ ማርያምን መድገምም ይገባል። መንገድ ስንሄድ፣ ሥራ ስንጀምር ወዘተ ጸልየን ብንጀምር ስራችን ይቀደሳል፣ ጉዟችን ይባረካል። በመከራ ሳለን ብንጸልይ እግዚአብሔር ከመከራው ያወጣናል። በጸሎት በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን እናገኛለን።

ምስጋና

ዘፋኝነት ክርስቲያናዊ ሥራ አይደለም ዘፋኝነት የዝሙት ፈታውራሪ፣ የስሜታዊነት አባት፣ የእውነት እና የአመክንዮ ጠላት ነው። ዘፋኝነት ኃጢዓት ነው። ይህም ዘፈን ማዳመጥንም፣ መዝፈንንም ያመለክታል። ሰው በተፈጥሮ ከተደነቀ እንኳን የተፈጥሮ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን ያመስግን። ሰይጣን ዘፈንን ኪነ ጥበብ በማለት የጥበብ ስም ቢያላብሰውም ነገር ግን ዘፈን መንፈሳዊ ጥበብ አይደለም። ሰው የተፈጠረ ፈጣሪውን አመስግኖ በደስታ ይኖር ዘንድ ነው። ሰው የተፈጠረበትን ዓላማ እየኖረ ነው የሚባለው ፈጣሪውን ሲያመሰግን ነው። በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ እግዚአብሔር በዜማ በማኅሌት ይመሰገናል። የዜማን የማኅሌትን ስልት ስልቱን የሚያስተምሩን ደግሞ አቋቋም እና ድጓ ናቸው። ይህንን ስልት ከመምህራን ስር ቁጭ ብለን እንማረው። ምስጋና ለተደረገልንና ለሚደረግልን መልካም ነገር ለፈጣሪ የምናቀርበው የደስታ እና የፍቅር ስጦታ ነው። ክርስቲያን መከራ ሲደርስበት ይጸልያል። ሁልጊዜም ደግሞ የፈጠረውን ፈጣሪ፣ በመስቀል ተሰቅሎ ያዳነውን ፈጣሪ ያመሰግናል። ሁልጊዜም ቢሆን

እግዚአብሔርን እናመስግን። ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ። ምስጉን ሆኖ የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመስግነው። ምነው ምስጉን ሆኖ ለምን አለ ከተባለ ክፉ ሆነው ባለማወቅ የሚመሰገኑ እና የሚመለኩ አሉና ከዚያ ሲለይ ነው። እግዚአብሔር ግን ፈጥሮ የሚገዛ በባሕርይው ምስጉን የሆነ ስለሆነ ስቡሐ ዘተሰብሐ አለ። ፈጣሪን ለምን እናመሰግነዋለን? ፩) ለክብር ስለፈጠረን ፪) ብንሞት ተሰቅሎ ስላዳነን ፫) የንሥሓ እድሜን ሰጥቶ እስካሁን ሰዓት ስላቆየን ፬) ሥጋውን ደሙን ሰጥቶ ሕይወታችንን ስለቀደሰልን ፭) የሚመግበን፣ የሚያኖረን እርሱ ስለሆነ ፮) ዝናሙን የሚያዘንብልን፣ ፀሐይን የሚያወጣ፣ በጠቅላላ ተፈጥሮን ለእኛ የሰጠን እርሱ ስለሆነ ፯)__ወዘተ ብዙ ብዙ መጥቀስ ይቻላል።

ጾም

ጾም ለተወሰነ ጊዜ ከምግብ መከልከል፣ ከጥሉላት መከልከል ነው። ጾም ክፉ ፈቃድን ለማስወገድ፣ መልካም ፈቃድን ለማስረጽ፣ ጽሙናን አርምሞን ለመያዝ ይጠቅማል። ጾም ትፈውስ ቁስለ ነፍስ እንዲል ጾም የነፍስን ቁስል ትፈውሳለች፣ ጾም ኃጢዓትን ያስተሰርያል። በመጾም በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን እናገኛለን። ንጹም ጾመ ወናፍቅር ቢጸነ ወንትፋቀር በበይናቲነ። ጾምን እንጹም፣ ባልንጀራችንንም እንውደድ፣ እርስ በእርሳችንም እንዋደድ እንዲል። ሁለት ዓይነት ጾም አለ። እኒህም የፈቃድ ጾምና የአዋጅ ጾም ናቸው። የፈቃድ ጾም በራስ ተነሳሽነት የሚጾሙት ጾም ነው። ግዴታ የለበትም። ለምሳሌ የጽጌ ጾም የፈቃድ ጾም ነው። ስለዚህ በዚህ ጊዜ የሚበላም ይበላል። የሚጾመውም ይጾማል። ይህ ክርስቲያናዊ ግዴታ አይደለም። ሁለተኛው የጾም ዓይነት የአዋጅ ጾም ነው። ይህም ማንኛውም ኦርቶዶክሳዊ ሰባት ዓመት ከሆነው በኋላ የሚጾመው ጾም ነው። እኒህን አጽዋማት መጾም ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። የአዋጅ አጽዋማት የሚባሉት ሰባት ናቸው። እነዚህም፦- ፩) ጾመ ድኅነት (ዓርብ ረቡዕ) ፪) ጾመ ኢየሱስ (ዐቢይ ጾም) ፫) ጾመ ማርያም (ፍልሰታ) ፬) ጾመ ነቢያት ፭) ጾመ ሐዋርያት ፮) የነነዌ ጾም ፯) የገሐድ ጾም (ጋድ) ናቸው። የዐቢይ ጾም የመጀመሪያው ሳምንት እስከ ፲፪ ሰዓት ይጾማል። ከዚያ ቀጥሎ ያሉ ሳምንታት እስከ ኒቆዲሞስ ዓርብ እስከ ፲፩ ሰዓት ይጾማሉ። ከሆሳእና እስከ ትንሣኤ ያለው ሰሙነ ሕማማት እስከ ምሽቱ ፩ ሰዓት ይጾማል። ሌሎች አጽዋማት እስከ ፱ ሰዓት ይጾማሉ። የልደትም የጥምቀትም ገሐድ አላቸው። ጥምቀት ወይም ልደት ሰኞ ከዋለ ገሐድ እሑድ ቀን ብቻ ይውላል እንጂ ሦስት ቀን ወይም ሁለት ቀን አይጾምም። ፍትሐ ነገሥቱ የበዓሉን ዋዜማ አለ እንጂ የዋዜማውን ዋዜማ አይልምና። ሌላው በዘመነ ዮሐንስም የነቢያት ጾም ህዳር ፲፭ ይጀምራል። እንጂ ፲፬ አይጀምርም። ሁልጊዜም በ፲፭ ይጀመራል። በዓለ ልደቱ ግን በዘመነ ዮሐንስ በሸ፭ ይውላል። {ይህንንም ሲኖዶሱ ተመካክሮ ሁልጊዜም በሸ፱ ቢያደርገው መልካም ነበር}። በዚህ ምክንያት ጠብ ክርክር ሊኖር አይገባም። ሁልጊዜም ቢሆን ሥርዓት ተኮር ጉዳዮችን ሲኖዶሱ ባለው ይጸናሉ። ንጹም ጾመ ወናፍቅር ቢጸነ ወንትፋቀር በበይናቲነ።

ስግደት

ስግደት አክብሮትን፣ መውደድን፣ መታዘዝን፣ እሺ ባይነትን መግለጫ መንገድ ነው። በባሕርይው ክቡር የሆነ እግዚአብሔርን እንደምናከብረው የምንገልጠው ለእርሱ በመስገድ ነው። ስግደት አፈጻጸሙ በሦስት ይከፈላል። እነዚህም፦- ፩) አድንኖ ፪) አስተብርኮ ፫) ወዲቅ ናቸው። አድንኖ የሚባለው ራስን ጎንበስ በማድረግ የምንሰግደው ስግደት ነው። አስተብርኮ የሚባለው

ስግደት ደግሞ ጉልበታችንን መሬት እያስነካን የምንሰግደው ስግደት ነው። ወዲቅ የሚባለው ስግደት ደግሞ ግንባራችንን መሬት እያስነካን የምንሰግደው ስግደት ነው። የማይሰገድባቸው ጊዜያት የሚከተሉት ናቸው። ፩) በዕለተ እሑድ ፪) በዕለተ ቅዳሜ (ሰንበት) ፫) በበዓለ ሃምሳ ፬) ከቆረብን በኋላ ፭) በጌታ በዓላት ፮) በድንግል ማርያም በዓላት ፯) በቅዱስ ሚካኤል በዓል ናቸው። በእነዚህ ጊዜያት አይሰገድም። ነገር ግን በሰሙነ ሕማማት ማንኛውም በዓል ቢውል ይሰገዳል። የስቅለት ቀን በዓለ ማርያምም ቢውል፣ በዓለ ሚካኤልም ቢውል፣ በዓለ እግዚእም ቢውል ይሰገዳል። ስግደት ሁለት ዓይነት ነው። ይኸውም የባሕርይ ስግደትና የጸጋ ስግደት ተብሎ ይከፈላል። የባሕርይ ስግደት ወይም የአምልኮ ስግደት ለፈጣሪ ብቻ የምንሰግደው ስግደት ነው። የጸጋ ስግደት የምንለው ደግሞ እግዚአብሔር ላከበራቸው ቅዱሳን የምንሰግደው ስግደት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ለነገሥታት ለተከበሩ ሰዎች ለሽማግሌዎች ታዛዥነታችንን እና አክብሮታችንን ለመግለጽ ጎንበስ በማለት እጅ እንነሳለን። የባሕርይ ስግደት ግን ለፈጣሪ ብቻ ይሰገዳል።

ጥበብ

የእውቀት ፍሬ ጥበብ ነው። የጥበብ መጀመሪያ ደግሞ ነቢዩ እንደተናገረው እግዚአብሔርን መፍራት ነው። እግዚአብሔርን መፍራት ደግሞ መገለጫው ትእዛዙን መስራት እና ማክበር ነው። ሦስት ዓይነት ጥበብ አለ። እነዚህም:- ፩) ጥበብ ሥጋዊ ፪) ጥበብ መንፈሳዊ ፫) ጥበብ ሰይጣናዊ ናቸው። ጥበብ ሥጋዊ የሚባለው የማረስ ጥበብ፣ የሳይንስ ጥበብ፣ አጠቃላይ ፍጻሜያቸው በዚህ ምድር እስካለን ብቻ የሚጠቅሙንን ነገሮች ብቻ አውቆ በእነዚያ ብቁ ባለሙያ መሆን ነው። ጥበብ ሰይጣናዊ የሚባለው ሌላውን ለመጉዳት የሚያሴሩት ሴራ እና ሽንገላን የሚያጠቃልል ነው። ወአርዌ ምድር ይጠበብ እም ኩሉ ሲል እባብ ግን ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ ነበር ማለት ነው። ሰይጣናዊ ጥበብ ሰውን ከፈጣሪው ሕግ ለማውጣት የሚያሴሩት ሴራ ነው። ለምሳሌ አታመንዝር የሚለውን ሕግ ለማስሻር ሰይጣን የአለባበስ ጥበብ ብሎ ለዝሙት የሚያነሳሱ ልብሶችን ያስለብሳል። ሰይጣን ሰውን ከእግዚአብሔር ሕግ ለማውጣት የሚጠቀምባቸው ጥበቦች ሁሉ ሰይጣናዊ ጥበቦች ይባላሉ። ሰይጣን ጽሉመ ገጽ ሆኖ ሳለ የብርሃን መልአክ መምሰል ፣ ምትሐት ማሳየት፣ ምትሐታዊ ተአምር መስራት፣ ሰይጣናዊ ጥበቦች ናቸው። መንፈሳዊ ጥበብ የሚባሉት ግን ሰውን ለዘለዓለማዊ ሕይወት የሚያበቁ ጥበቦች ናቸው። እነዚህም ጸምን፣ ጸሎትን፣ ስግደትን፣ ምጽዋትን የመሳሰሉ ናቸው።ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ጥበብ ይባላል። ጥበብሰ መድኃኒነ ውእቱ እንዳለ ቅዳሴ። ጥበብ የሚባለው ፍቅር ያለበት ብልህነት ነው። የጥበብ መሰረት ራሱ ፍቅር ነው። ጥበብ እውነት ነው። አባቶቻችን በጥበብ ኖረዋል። በጥበብ ሃይማኖታቸውን ጠብቀዋል። በጥበብ አስተምረዋል።

ትጋት እና ጽናት

ትጋት የስንፍና ተቃራኒ ነው። ሰው ባለው ዘመን ሁሉ ተግቶ መስራት ይገባዋል። መንፈሳዊ ሥራዎች ሁሉ የሚሰሩት በትጋት በጽናት ነው። ቅዱሳን እስከ አስረኛው የቅድስና መዓርግ የደረሱት በትጋት ነው። መካከል ላይ ስንፍና አላስገቡም። ከበለጠ ሥራ ወደ በለጠ ሥራ እየተሸጋገሩ ነው የኖሩት። ጥበብ ሥጋዊም ሆነ ጥበብ መንፈሳዊ ከግብ የማያደርሰን ትጋት ካልተለየው ነው። ትጋት የተለየው ጥበብ መጨረሻው ድንቁርና ይሆናል። ብዙ ርቀት

የሚያስኬድ መንገድ በአንድ እርምጃ ይጀመራል። ሳንሰንፍ ሁለት ሦስት እያልን ከሄድን ካሰብንበት እንደርሳለን። በመንፈሳዊ ሕይወትም መራመድ ከጀመርን በኋላ ወደ ኋላ ማለትና መቆም አያስፈልግም። በትጋት መራመድ አለብን። ፈተናዎች ሲያጋጥሙን እንኳ እነርሱ ወደኋላ ሊጎትቱን አይገባም። ንሥሓ እየገባን ወደፊት መገስገሳችንን እንተው።

ተስፋ (Hope)

ሰው የሚቻለውን ሁሉ እያደረገ እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ አለበት። ተስፋ መቁረጥ ሰይጣናዊ ሥራ ነው። ሰው ፈጣሪው እስካለው ድረስ በምንም ቢሆን ተስፋ መቁረጥ አይገባውም። ተስፋ በፈጣሪ ላይ ያለን የመታመን ኃይል ነው። ሰው በሰው ተስፋ ማድረግ አይገባውም። ሰው በገንዘቡ፣ በኃይሉ፣ በውበቱ፣ በእውቀቱ እና በመሳሰሉት ተስፋ ማድረግ አይገባውም። እኒህን ሁሉ በሚሰጥ በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ ይገባል። ለዚያ ነው ማኅሌታዊው ዳዊት "ይኄይስ ተሰፍዎ በእግዚአብሔር እምተሰፍዎ በእጓለ እመሕያው ያለውን በሰው ተስፋ ከማድረግ በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ ይበልጣል ይላል። ከእግዚአብሔር በላይ የሆነ ምንም ዓይነት ችግር ስለሌለ በማናቸውም ጭንቀትና መከራ ውስጥ ብንሆንኳ እግዚአብሔርን ተስፋ እናድርግ። ተስፋ መቁረጥ እግዚአብሔርን ተስፋ ካለማድረግ የሚመነጭ ክፉ ሐሳብ ነው። እስከ ዕለተ ሞታችን ድረስ በተስፋ ልንኖር ይገባል። ተስፋ ኃይል ነው። ተስፋ ያለው ሰው አይፈራም። ስለዚህ ተስፋን ገንዘብ እናድርግ።

ንሥሓ

በራሳችን ተስፋ መቁረጥ የለብንም። ሥጋዊ ፈቃድ አሸንፎን ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን በድለነው ይሆናል ነገር ግን ንሥሓ ከመግባት ማቋረጥ የለብንም። ጥሩ ሰዎች እስክንሆን ድረስ በንሥሓ እየታደስን እስከ ዕለተ ሞታችን መቀጠል አለብን። ተስፋ በንሥሓ እና በይቅርታ ይቀጥላል። በበደል ዳዊትን መስለነው ይሆናል። ኑ በሉ በንሥሓም እንምሰለው። የሰይጣን ዋና መደበኛ ሥራ ሰውን ማሳሳት ነው። ሰውም በሰይጣን ተንኮል ይታለልና ይወድቃል። ከዚህ በኋላ ሰይጣን ከዚህ በኋላ ንሥሓ ብትገባም ዋጋ የለህም ትልቅ በደል ሰራህ እያለ ተስፋ ለማስቆረጥ ይሞክራል። ነገር ግን በንሥሓ የማይወገድ ኃጢዓት ስለሌለ ሰይጣን በእኛ ላይ የገነባውን የኃጢዓት ክምር በንሥሓ ማጥፋት እንችላለን። ሰይጣን ራሱ አሳስቶ ተስፋ ለማስቆረጥ ብዙ ይጥራል። ሰይጣንን ማሸነፍ የምንችለው ተስፋ ባለመቁረጥ እና በትሕትና ሆነን ረድኤተ እግዚአብሔርን በመጠየቅ ነው።

የመንፈስ ፍሬዎች

ፍቅር

ፍቅር የአንዱን ድካም አንዱ ሲሸከም ነው። ሰማዕትነት የሌለበት ፍቅር ፍቅር አይባልም። በአፍ ብቻ እወድሃለሁ እወድሻለሁ ማለት ውሸት ነው። ይህንንስ ባላገሩ "የአፍ ዘመድ ከገበያም አይገድ" ብሎ ተርቶበታል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐ. ፲፭፣፲፫ "ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" ብሎ የፍቅርን ትርጓሜ አስተማረን። ፍቅር በአፍ የሚናገሩት ብቻ አይደለም በሕይወት የሚኖሩትም ነው እንጂ። ለዚያም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን በቃል ከተናገረ በኋላ በተግባር ደግሞ አዳምን ለማዳን በመስቀል የተሰቀለ። መስቀል ፍቅር በተግባር የተገለጠበት አደባባይ ነው። ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት ብሎ ሊቁ የገለጠው ይህንን ነው። ፍቅር ራሱ

እግዚአብሔር ነው። ፩ኛ ዮሐ.፬፣፰-፳ "ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና----ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው" ይላል። ይህ የሚነግረን በፍቅር ጥላቻ እንደሌለ ነው። ፍቅር ሌላውን እንደ ራስ መውደድ ነው። ማቴ. ፯፣፲፪ "ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው" ተብሎ እንደተጻፈ ሰውን መውደድ በእኛ ሊደረግብን የማንፈልገውን በሌላውም እንዲደረግ አለመፈለግ ሲሆን እግዚአብሔርን መውደድ ደግሞ ትእዛዙን በመፈጸም ይገለጣል።ዮሐ. ፲፬፣፳፩ "ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው" እንዲል። ማቴ. ፮፣፳፩-፳፫ "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን ይሉኛል። የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብየ እመሰክርባቸዋለሁ" እንዲል የጌታን ስም ብዙ ጊዜ ብትጠራ፣ በስሙ ተአምራትን ብታደርግ፣ በስሙ ትንቢትን ብትናገር፣ በስሙ አጋንንትን ብታወጣ ይህ የፍቅር ምልክት ተደርጎ አይያዝም። እግዚአብሔርን የመውደድ ዋናው ምልክቱ ፈቃዱን መፈጸም ነው። ፈቃዱ ምንድን ነው ከተባለ ዘጸ. ፳፣፭ ጀምሮ ያሉ አስሩን ሕግጋት መፈጸም ነው። ማቴ. ፲፱፣፲፯ "ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ" እንዳለ። ዮሐ. ፲፪፣፶ "ትእዛዙም የዘለዓለም ሕይወት እንደሆነች አውቃለሁ" እንዲል። ቅዱስ ጳውሎስ ፍቅርን ጠቅለል አድርጎ ሲያቀርበው እንዲህ ብሎታል። ፩ኛ ቆሮ. ፲፫፣፩-፰ " ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ድኾችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም። ፍቅር ይታገሣል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፣ ፍቅር አይቀናም፣ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፣ የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ በደልን አይቆጥርም፣ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለዓመፃ ደስ አይለውም። ሁሉን ይታገሣል፣ ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም" ብሎ ገልጾታል።

ራስን መግዛት

ራስን ከመግዛት የበለጠ ንጉሥነት የለም። ራስን መግዛት በምን ከተባለ በእግዚአብሔር ሕግ ነው። ራስን መግዛት ስሜታችንን አሸንፎ እውነት በሆነው ቃለ እግዚአብሔር መመራት ነው። ከስሜት በላይ መሆን ነው። ነፍስን በሥጋ ላይ ማሰልጠን ነው። ራስን በራስ መቆጣጠር ነው። ለሰውነታችን ሕግ መሥራት ነው። ዓይናችን ክፉ እንዳያይ፣ ጆሯችን ክፉ እንዳይሰማ፣ እጃችን ክፉ እንዳይዳስስ፣ ምላሳችን ክፉ እንዳይናገር፣ አፍንጫችን ክፉ እንዳያሸት መቆጣጠር ነው። አንድ ነገር ክፉ የሚባለው ፍጻሜው የእግዚአብሔርን ሕግ ወደመሻር የሚያደርስ ከሆነ ነው። ዓለምን ከመግዛት ራስን መግዛት ይበልጣል። ራሱን የገዛ ሰው ፍጻሜው መንግሥተ ሰማያት ነውና። ንዴትን፣ ሐሜትን፣ ቁጣን፣ ስሜትን መግራት ነው። አርምሞ (ዝምታ) አንደበትን ለመግዛት ዋናው መሳሪያ ነው። የፈቲው ጾርን (አመንዝራነትን) ለማስወገድ መጾም፣ ውሃ አለማብዛት እና እንቅልፍን መቀነስ ዋና መድኃኒቶች ናቸው። ራሳችንን በጾም፣ በጸሎት

መግራት መልካም ነው። ራስን መግዛት ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ ነው። ገላ. ፭፣፳፪። ። ኑ በራሳችን ላይ እንንገሥ (ንጉሥ እንሁን)።

እምነት

እምነት አካሌን የሰጠ፣ የሚያስፈልገኝን ነገር ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር እስከ ዕለተ ሞቴ ይመራኛል ብሎ ሙሉ ተስፋን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ ነው።እምነት ካለመኖር የፈጠረኝ እግዚአብሔር በመግቦት ያኖረኛል ብሎ ቁርጥ ሀሳብን ለእግዚአብሔር መስጠት ነው። ብዙዎቻችን እምነት የለንም። እምነት ያለው ሰው ስለምንም አይጨነቅም። ከምንም በላይ የሆነው እግዚአብሔር አለኝ ብሎ በልቡ ስለሚያምን የሚያሳስበው የሚፈራው እና የሚያስጨንቀው ጉዳይ አይኖርም። እምነት ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ ነው። ገላ. ፭፣፳፪። እምነት ያለው ሰው ተስፋ አይቆርጥም። ምክንያቱም ምንም ዓይነት ፈተና ውስጥ ቢኖር እግዚአብሔር በጥበቡ ከዚያ እንደሚያወጣው ተስፋ ያደርጋልና። እምነት ያለው ሰው እንደ ዳንኤል አንበሳ ጉድጓድ ውስጥ ሊጣል ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር አንበሶች እንዳይበሉት ያደርጋል። እምነት ያለው ሰው ሰማዕት ሊሆን መከራ ሊደርስበት ይችላል። ነገር ግን ከሁሉም የምትበልጠውን መንግሥተ ሰማያት ያገኛል። መዓልትና ሌሊትን፣ ክረምትና በጋን እያፈራረቀ የሚመግበን የሚያኖረን እግዚአብሔር ስላለን አንፈራም አንጨነቅም። ሰው እምነት እያጣ ሲሄድ ይጨነቃል፣ ያዝናል። ነገር ግን ከእኛ የሚጠበቀውን የድርሻችንን እየተወጣን ረድኤተ እግዚአብሔርን እየጠየቅን በተስፋ እንኑር። እምነታችን አይጉደል። ቀድሞ ቅዱሳንን የረዳ እግዚአብሔር ነው። አሁንም ያለው ራሱ ነው። እኛንም ይረዳናል። ይረድአነ አምላክነ ወመድኃኒነ። አምላክነሰ አምላከ አድኅኖ። ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ። እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን እንመነው። መልካም የሆነውን ሁሉ ያደርግልናል።

በጎነት

በጎነት ለራስም ለሌላውም መልካም መሆን ነው። ደግነት እና ቅንነት ይመሳሰሉታል። ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ሲባል ለመልካም ነው ለማለት ነው። የመልካምነት መለኪያው የእግዚአብሔር ቃል ነው። አንድ ሰው በጎ የሚባለው እንደ እግዚአብሔር ቃል ሲኖር ነው። በሌሎች ሰዎች ክፉ አለማድረግና ለሌሎች ሰዎች መልካም ማድረግ በጎነት ነው። ስለሌሎች ሰዎች ጥሩ አስተያየት አነጋገር ካለው በጎ ነው ይባላል። ብናጠፋ፣ ብንበድል እንኳ እግዚአብሔር ፈጥኖ አያጠፋንም። ለእኛ በጎ ስለሆነ የንሥሓ እድሜን ይሰጠናል። እንዲህ ከሆነ ታድያ አንዳንድ ክፉዎችን እግዚአብሔር ፈጥኖ የሚያጠፋቸው ስለምንድን ነው? ቢባል ቢቆዩ ኃጢዓትን አብዝተው ስለሚሰሩ በሰማይም ፍዳቸው ይቀንስ ዘንድ ቶሎ ያጠፋቸዋል። አንዳንድ መልካሞችንስ ወዲያው የሚያጠፋቸው ለምንድን ነው? ከተባለ ከቆዩ ኃጢዓት ሊሰሩ ይችላሉና። በአሁኑ ጽድቃቸው ዋጋቸውን ለመስጠት ነው። አንዳንድ መልካሞች ብዙ ዘመን ይቆያሉ ለምንድን ነው? ከተባለ ለክብር የሚያበቃቸውን ሥራ አብዝተው ይሰሩ ዘንድ እና ለኃጥዓን ተግሣጽ ይሆኑ ዘንድ ነው። አንዳንድ ክፉዎችን ደግሞ ብዙ ያቆያቸዋል ለምንድን ነው? ቢሉ የሰሯት መልካም ሥራ ካለች እርሷን በዚህ ምድር በድሎት እንዲኖሩ አድርጎ በሰማይ ፍዳቸው ይበዛ ዘንድ ነው። አንዳንድ ኃጢዓተኞች በዚህ ምድር ደስተኛ ሆነው ይኖራሉ አንዳንድ ኃጢዓተኞች ደግሞ በዚህ ምድር በመከራ ይኖራሉ ለምንድን ነው? ከተባለ። በዚህ ምድር ደስተኛ የሆኑት እንደ ነዌ በሰማይ ፍዳቸው የሚበዛ ሰዎች ናቸው። በዚህ ምድር ኃጢዓተኛ

ሆነው በመከራ የሚኖሩት ደግሞ የኃጢዓታቸውን ፍዳ ጥቂቱን በዚህ ምድር ስለተቀበሉ በሰማይ ይቀልላቸዋል። ድኃው አልዓዛር በዚህ ምድር ለምን ተሰቃየ ቢሉ ምንም እንኳ ጻድቅ ቢሆን ሰው ከድንግል ማርያም በስተቀር ጽነት አያጣውምና ለዚያ ፍዳውን በዚህ ምድር ተቀብሎ በሰማይ ዋጋው ይበዛለት ዘንድ ነው። ሰው በዚህ ምድር እስካለ ድረስ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ስለማያውቀው ሁልጊዜም ለሁሉም ሰው በጎ ሊሆን ይገባል። አንዳንዱን በደለኛ እግዚአብሔር ወዲያው ይቀስፈዋል ለምን ቢሉ በሕይወተ ሥጋ ላሉት ምሳሌ ይሆን ዘንድ ነው። አንዳንዱን በደለኛ እግዚአብሔር በዚህ ምድር ያቆየዋል ለምን ቢሉ ንሥሓ ይገባ ዘንድ ነው። በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ቦታ በማንኛውም ሁኔታ በጎ እንሁን።

የዋህነት

የዋህ ማለት ጎዳጌ በቀል ማለት ነው። በዚህ ጊዜ ለቅዱሳን፣ ለቅድስት ድንግል ማርያም፣ ለእግዚአብሔር ይነገራል። እግዚአብሔር የዋህ ነው ብትል ጎዳጌ በቀል ነው መሓሪ ነው ማለት ነው። ቅድስት ድንግል ማርያምን የዋሂት የሚያሰኛት ርግብየ ሠናይትየ የሚያሰኛት ጎዳጌ በቀልነቷ፣ መሓሪትነቷ ነው። ጎዳጌ በቀል ማለት ተበድሎ እንዳልተበደሉ መሆን፣ በደልን ይቅር ማለት ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ፍሬዎች ብሎ ከጠቀሳቸው ውስጥ ገላ. ፭፣፳፪ የተጠቀሰው የውሃት ይህኛው የውሃት ነው። የዋህነት (Mildness) ጠቢብነትንም (Wisdom) የያዘ ነው። ኩኑ የውሃነ ከመ ርግብ ወጠቢባነ ከመ አርዌ ምድር እንዲል። እባብ ጠቢብነቱ "ዕፀ ዘዌ የምትባል ዕፅዋት አለች። ፍሬዋን ይወዳታል። ነገር ግን ጥላዋ ካረፈበት መንቀሳቀስ ስለማይችል ጠዋት በምሥራቅ ሆኖ ማታ በምዕራብ በኩል ሆኖ ፍሬዋን ይበላል" ተብሏል። በዚህ በመጀመሪያው ትርጓሜ አንድ ሰው የዋህ ነው ሲባል ገራገር ነው። መልካም አሳቢ (Positive thinker) ነው ማለታችን ነው። የዋህ ነው ማለት ክፉ ላደረጉባት እንኳ ቂም፣ ጥላቻ፣ በቀል የሌለበት ማለት ነው። የዋህ ማለት ሰውን እንደራሱ የሚያይ ደግ ሰው ማለት ነው። ንኩን የዋሃነ። የዋሃን እንሁን። ባለፈው የደረሰብንን በደል እንተወው። የወደፊቱን ሕይወት በጋራ ሆኖ በፍቅር ሆነን ያማረ የሰመረ እናድርገው። ሁለተኛው ትርጓሜ የላይኛው ተቃራኒ ነው። በግእዝ አንድ ቃል ለሁለት ተቃራኒ ነገሮች ሊያገለግል ይችላል። ለምሳሌ ባረከ "ባረከም ይሆናል ረገመም ይሆናል" ወባረከ ኢዮብ ዓመተ ልደቱ ሲል ረገመ ማለት ነውና። የዋህ ማለት ሞኝ፣ አላዋቂ ማለት ነው። የዋህ ብእሲ ኵሎ ዘነገርዎ የአምን እንዲል። ሞኝ ሰው፣ አላዋቂ ሰው የነገሩትን ሁሉ ያምናል እንደማለት ነው። ነገርን እንደወረደ የሚያምን፣ የማይመረምር፣ በራሱ ሳይሆን በመንጋ የሚያስብ የዋህ ይባላል። ይህ የየዋህ ሁለተኛ ትርጉም ነው። የዚህ ተቃራኒ ብልጥ ነው። ብልጥ የሚባለው ራስ ወዳድ ለራሱ ብቻ የሚያስብ፣ ራሱን ለመጥቀም የዋህ የሆኑ ሰዎችን የሚያታልል ተንኮለኛ ማለት ነው። በመጀመሪያ ትርጉም ያለውን የዋህ እንሁን። ኢየሱስ ክርስቶስ መፍቀሬ የውሃት እምተቀይሞ እንዳለ ደራሲ የዋህ ስንሆን ክርስቶስን እንመስለዋለን።

ቸርነት

ቸርነትን ግእዙ "ምጽዋት" ይለዋል። ከተቀባዩ ምንም ሳይፈልጉ የሚሰጡት ስጦታ ነው። አሁን ያሉ የኢትዮጵያ የአብነት መምህራን በችግር ተምረው ያገኙትን እውቀት በነጻ ያስተምራሉ። እውቀት ይመጸወታል። ገንዘብ ይመጸወታል። ጉልበትም ይመጸወታል። ሁሉም የቸርነት ሥራዎች ናቸው። ቸሩ እግዚአብሔር እንዲምረን እኛም ቸር እንሁን። ሰው በቸርነት

ፈጣሪውን ይመስላል። እግዚአብሔር ቸር ስለሆነ እኛነታችንን፣ አካላችንን፣ ተፈጥሮን ሰጥቶናል። ከዚህ በኋላ በታናናሾች አድሮ ምጽዋትን እየተቀበለ ሰማያዊ ዋጋን ይሰጠናል። በኋላ በምጽአት ጻድቃንንና ኃጥዓንን ሲለይ በዋናነት የሚጠይቀው ቸርነትን (ምጽዋትን) ነው። ብራብ አብልታችሁኛል፣ ብጠማ አጠጥታችሁኛል፣ ብታረዝ አልብሳችሁኛል፣ እንግዳ ብሆን ተቀብላችሁኛል፣ ብታመም ጠይቃችሁኛል፣ ብታሰር አስፈትታችሁኛል የሚሉት ቃላት ምሥጢራቸው ቸርነት ነው። ምጽዋት (ቸርነት) ሰው ፈጣሪን የሚመስልበት መልካም ሥራ ነው። ፈጣሪ ሁሉን በነጻ እንደ ሰጠን የሚመጸውት ሰውም ፈጣሪ ከሰጠው ጸጋ በነጻ የሚሰጥ ነው። ቸርነት (ምጽዋት) በከንቱ ዘነሳእክሙ በከንቱ ሀቡ ያለውን የሐዋርያውን ቃል በተግባር ማዋል ነው። ቸርነት ሰው ሌላውን ሰው እንደራሱ ከመውደዱ የተነሳ የሚደረግ የመንፈስ ፍሬ ነው። ለዚያ ነው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የመንፈስ ፍሬዎችን ሲነግራቸው አንዱ ቸርነት ነው ያላቸው። ገላ. ፭፣፳፪። የቸርነት ሥራዎች ለከንቱ ውዳሴ ከዋሉ ዋጋ አያሰጡም። ጌታ ሲያስተምር ቀኝህ የሰጠችውን ግራህ አትወቅ ምጽዋትህ ሰው ይይልኝ ብለህ ሳይሆን በስውር ይሁን ያለን። አሁን ሰው መጽውቶ በማኅበራዊ ሚዲያ ካልተነገረለት ይከፋል። መምህር አስተምሮ ማስተማሩ በሁሉ ካልታወቀለት ይከፋዋል። ቸርነትና ውዳሴ ከንቱ አይስማሙም። በአደባባይ ከመወደስ በአደባባይ መሰደብ ይሻላል። ቸሩ መድኃኔዓለም ይቅር እንዲለን ቸርነትን ገንዘብ እናድርግ።

ሰላም

ቅድስት ድንግል ማርያምን ሰላማዊት ይላታል። ልጇም ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ይባላል። አንድ ሰው ውስጣዊ ሰላም ይሰማኛል ሲል ብትሰማው የሐሳብ ስምምነት የአእምሮ ዕረፍት እንዳገኘ ትረዳለህ። ውስጣዊ ሰላም የሕዋሳቶቻችን ስምምነት ውጤት ነው። ሰላም ተሳለመ_ተፈቃቀረ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ዘመድ ዘር ነው። ሰላም ፍቅር ማለት ነው። ምሥጢራዊ ትርጓሜው ግን ከተሰናአዎ ጋር ይቀራረባል። የነገር እና የሐሳብ ስምምነት ማለት ነው። ሰላም ሆነ ማለት ስምምነት ላይ ተደረሰ ማለት ነው። አምላክ ሰላም ክርስቶስ ሰላምን እሰጣችኋለሁ ብሏል። ለሰውነታችን የተስማማች ገነትን ሰጥቶም አረጋገጦልናል። ሲኦል ግን ለእኛ ሰውነት የማይስማማ ቦታ ነው። በሲኦል ሰላም የለም። ሁከት ብጥብጥ ዋይታ ለቅሶ ይበዛል። ውስጣዊ ሰላም የሚገኘው በድለን ከነበረ ንሥሓ ገብተን ኃጢዓታችንን አስወግደን መልካም ሥራ ስንሰራ ነው። ነገር ግን ሌላውን እያስቀየምን፣ እያናደድን፣ እየተሳደብን ውስጣዊ ሰላም ይሰማናል ብንል ውሸታም እንባላለን። ነቢዩ ኤርምያስ እንደተናገረው "ወይቤሉ ሰላም ሰላም ወአልቦ ሰላም" እንዳሉት ሐሰተኛ ነቢያት እንሆናለን። የልቡና ሰላም የሚገኘው እውነትን ፍቅርን ትሕትናን ስንይዝ ነው። ፍጹም ሰላማዊት ወደ ሆነችው መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ከተጣላናቸው ጋር በይቅርታ ታርቀን፣ የበደልነውን ክሰን በፍቅር እንኑር። ክርስቶስ ሰላምን የሰጠን በደላችንን ይቅር ብሎ ነው። እኛም በትክክለኛ ፍትሕ ያጠፋው ክሶ፣ የተበደለው ተክሶ በሰላም እንኑር። ውስጣዊ ሰላም ለማግኘት ከፈለጉ የተጣሉትን ይታረቁ፣ ቂም በቀል ጥላቻ ዘረኝነት ካለብዎ ያስወግዱ። ከእርስዎ የሚጠበቀውን መልካምነት ያድርጉ። የድርሻዎትን ይወጡ። ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ ሰላም ነው (ገላ. ፭፣፳፪)።

ደስታ

አራት ዓይነት ደስታዎች አሉ። እነዚህም:- ፩) ፍሥሓ መላእክት ፪) ፍሥሓ ኖሎት ፫) ፍሥሓ

ቊንጽል (የቀበሮ ደስታ) ፬) ፍሥሓ መስቴማ ናቸው። ፍሥሓ መስቴማ ማለት የሰይጣን ደስታ ማለት ነው። ሰይጣን ሌሎች ሰዎች ሲሳሳቱ፣ ሲወድቁ፣ ሲሞቱ፣ ሲጎዱ በጣም ይደሰታል። በሌሎች ሰዎች ኀዘን እና ጉዳት የሚደሰቱት ደስታ የሰይጣን ደስታ ይባላል። ሁለተኛው የደስታ ዓይነት የቀበሮ ደስታ ነው። ቀበሮ የጣዝማ ማር ስታገኝ ከደስታዋ ብዛት የተነሳ ማሩ እስኪጠፋት ትዘላለች። የደስታዋ ምንጭ የሚበላ አገኘሁ ብላ ነው። የሰው ልጅ በሥጋዊ ነገሮች የሚደሰተው ደስታ የቀበሮ ደስታ ይባላል። ሦስተኛው ደስታ የእረኞች ደስታ ነው። እኒህም ጌታ በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ የተደሰቱት ደስታ ነው። ይህ ደስታ ነፍሳዊ ደስታ ነው። በጌታ መወለድ በሲኦል ተግዞ የነበረ አዳም ወደ ገነት የሚመለስበትን የምሥራች ከመልአኩ የሰሙበት ነውና። እስመ ናሁ ተወልደ ለክሙ ዮም መድኀን ዘይከውን ፍሥሓ ለክሙ እንዲል። የመላእክት ደስታ የፍጹማን ደስታ ነው። መላእክት አንድ ኃጥእ ንሥሓ በገባ ጊዜ በሰማያት ታላቅ ደስታ ይሆናል ተብሎ የተነገረላቸው ናቸው። የመላእክት ደስታ ከግላዊ ጥቅም የተለየ ደስታ ነው። ሌላው ሲጠቀም፣ ሌላው ሲያገኝ፣ ሌላው ሲሾም፣ ሌላው ሲደሰት የሚደሰቱት ደስታ ነው። እንግዲህ ገላ. ፭፣፳፪ ደስታ የመንፈስ ፍሬ ነው የተባለው በሁለቱ ዓይነት ደስታዎች ነው። እነዚህም ፍሥሓ ኖሎት እና ፍሥሓ መላእክት ናቸው። ትክክለኛው ደስታ የሚገኘው በቁስ አይደለም። በእግዚአብሔር ነው። መዝ. ፷፬፣፩ "ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን" ተብሏል። ቅዱስ ጳውሎስም በመልእክቱ ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ብሏል። በሌላ ቦታ ቅዱስ ዳዊት "ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ" ብሏል። ደስታ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ቤት ነውና። ደስታ የራቃችሁ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ። ያን ጊዜ ደስ ይላችኋል። ሰማእታት እየተገደሉ ግን ደስተኞች ነበሩ። ለምንድን ነው ስንል የደስታቸው ምንጭ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ሕይወተ ሕይወት ብርሃነ ብርሃን መሠረተ መሠረት ስለሆነ ነው። ደስታችንን በእግዚአብሔር እናድርግ።

ትዕግሥት

አሁን አሁን ከትዕግሥተኞች ይልቅ ስለ ትዕግሥት የሚያወራው ይበልጣል። ትዕግሥት የክብር እናት ናት። ከክርስቶስ መስቀል በረከትን ማግኘ ነው። ክርስቶስ እኛን ለማዳን በመስቀል ተሰቀለ። እስኪ ራስህን አድን እያሉ አይሁድ ሲሳለቁበት፣ ምራቃቸውን ሲተፉበት፣ ተነበይ ለነ ክርስቶስ መኑ ጸፍዐከ እያሉ በጥፊ ሲመቱት እነርሱን ማጥፋት እየቻለ ለእኛ ትዕግሥትን ያስተምረን ዘንድ መከራውን ሁሉ በዝምታ ተቀበለ። ሰማዕታት ስለ እውነት መራራ ሞትን ታገሡ። ወተዐገሡ ሞተ መሪረ በእንተ መንግሥተ ሰማያት እንዲል። የታገሠ የድል አክሊል ያገኛል። ይህችውም መንግሥተ ሰማያት ናት። አባቶቻችን ዕጉሣን ነበሩ። ለመናገር የዘገዩ ለመስማት የፈጠኑ ነበሩ። ታጋሽ ሰው ሕይወቱ የተረጋጋ ነው። አርምሞ (ዝምታ) የትዕግሥት አጋዥ ነው። ትዕግሥት የጠብ ማብረጃ ነው። ትዕግሥትን እንለማመዳት። ሲታገሡ ያማል። ሕመሙ ግን አጭር ነው። ከሕመሙ በኋላ ያለው ደስታ ልዩ ነው። እናት ልጇን ስትወልድ የምጥ ጊዜዋ አስጨናቂ ነው። ነገር ግን ልጇን ከወለደች በኋላ ወንድ ልጅ ወለድሽ ብለው ሲያስታቅፏት ያለፈውን መከራ ሁሉ በልጇ ትረሳዋለች። ስንሰደብ ዝም ስንል ልናዝን እንችላለን። ነገር ግን እየቆየ ሲሄድ ምን ስድብማ አየር የሚወስደው አይደለምን ብለን ደስ ይለናል። ቅዱሳንም ይህችን ዓለም ያሸነፏት በትዕግሥት ነው። ሊቁ መዋዕያነ ዓለም አንትሙ በብዙኅ ትዕግሥት ያለው ይህንን ነው። ታጋሽ ሰው የሰማእታቱ የእነ ቅዱስ መርምህናም፣

የእነ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የእነ ቅዱስ ፊቅጦር፣ የእነ ቅዱስ መርቆሬዎስ፣ የእነ ቅዱስ ፋሲለደስ፣ የእነ ቅዱስ ገላውዴዎስ፣ የእነ ቅዱስ ቂርቆስ እንዲሁም የቅዱሳን ሰማእታት ሁሉ ወዳጅ ነው። ታጋሽ ሰው የመነኮሳቱ የእነ ቅዱስ መቃርስ፣ የእነ አባ እንጦንስ እንዲ የቅዱሳን መነኮሳት ሁሉ ወዳጅ ነው። ታጋሽ ሰው የቅዱሳን ሁሉ ወዳጅ ነው። እግዚአብሔር ይወደዋል። በሉ ኑ ታጋሽነትን እንለማመድ። ታጋሽ እንሁን።

ትሕትና

ትሕትና "እኔ ደካማ ነኝ፣ እኔ ኃጢዓተኛ ነኝ___ወዘተ ማለት ብቻ አይደለም። ሲሰድቡህ አለመመለስ፣ "ኃጢዓተኛ ነህ፣ ደካማ ነህ" ሲሉህ አዎ ነኝ ማለት ነው። የትሕትና መለኪያው ይህ ነው። አንድን ሰው ሰድበኽው፣ መትተኽው፣ ተናግረኽው ነገር ግን ለአንተ ያለው ፍቅር ካልቀነሰ በትክክል ትሑት ሰው ነው ማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ አሉልህ እኔ ኃጢዓተኛ ስለሆንኩ ወደፊትም ልፋታ ስለምችል በቁርባን አላገባም የሚሉ። እኒህ ሰዎች ያልተረዱት ነገር ይህ ትሕትና ሳይሆን ውንብድና መሆኑን ነው። ጋብቻ የሚጸናው በቁርባን ሲሆን ነው። ፍትሐ ነገሥታችን ያለ ቁርባን የሚደረግ ጋብቻ ቁጥሩ ከዝሙት ነው ብሎታል። ስለዚህ ኃጢዓተኛ ነኝ ያለ ሰው እንኳ ቢሆን ንሥሓ ገብቶ በቁርባን ያገባል እንጂ በኃጢዓት ላይ ኃጢዓትን አይጨምርም። ትሕትና ትልቅነትን ይዞ ከትልቅነት ሳይወርዱ ታናሽ መሆን ነው። ይህንንም ራሱ ክርስቶስ አስተምሮናል። አምላክ ሲሆን ሰውን ለማዳን አምላክነቱን ሳይለቅ ሰው ሆነ። ለሰው ልጅ የትሑት ሰብእናው ምክንያት ደካማነቱ፣ ሁሉን አዋቂ አለመሆኑ፣ በእግዚአብሔር ቸርነት የሚኖር መሆኑ እና የመሳሰሉት ናቸው። ትሕትና ክብርን ለእግዚአብሔር መስጠት ነው። ትሑት ሰው ከራሱ ይልቅ ሌሎችን ያስቀድማል። ልክ ቅዱስ ጴጥሮስ በደብረ ታቦር ጌታ ሆይ አንድ ለአንተ አንድ ለሙሴ አንድ ለኤልያስ ቤት እንስራ ብሏል። ቅድስት ድንግል ማርያምም የትሕትና እናት ስለሆነች እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ያለውን የኢሳይያስ ትንቢት ስታነብ "እኔ ብሆን" አላለችም። ከዚህችስ ከዘመኗ ደርሼ ባገለግልኳት ነው ያለች። እስመ ምሥጢራት ይትከሠታ ለትሑታን እንዲሉ እውቀት ጸጋ ለትሑታን ይሰጣል። ትሑታን ሲሰደቡ የማይሳደቡ ስድብ የማያውቁ ሆነው አይደለም። ነገር ግን በትሕትናቸው ይገባኛል ብለው ያስቡና አፋቸውን እንዳይሳደብ ተቆጣጥረውት ነው። በሌላ ምክንያት ደግሞ ፍቅር ስለሚበልጥባቸው ነው። በትእግስታቸው ጸጋ እንደሚያገኙም ስለሚያውቁ ነው። ፍትሐ ነገሥት "ሰው ሁሉ ከአንተ የከበረ እንደሆነ አስብ" ይላል። ቅዱሳን በዚህ መርሕ ለሁሉ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ኖረዋል።

አንድነት

"ሐንካስ በእግረ እውር ሖረ። እውርኒ በዓይነ ሐንካስ ነጸረ። ወበክልዔሆሙ ወይንየ ተመዝበረ።" የእባብና የሰይጣን ጎብረት የክፉ አንድነት ምሳሌ ነው። ምክንያቱም አንድ የሆኑት ሁለቱም ሌላውን ለመጉዳት ነውና። ይህ ቅኔ የክፉ ጎብረትን ምሳሌ ይነግረናል። "አንካሳ በዕውር እግር ሄደ፣ ዕውርም በአንካሳ ዓይን አየ፣ በሁለቱ አንድነት ምክንያት ወይኔ ተዘረፈ" ማለት ነው። የሁለቱ አንድነት ወይን ለመዝረፍ ነበር። ይህን የመሰለ አንድነት በጎንደር ዘመነ መንግሥት ሆኖ ነበር። ሁለት ንጉሡ ያሳደጋቸው ሰዎች ንጉሡን በመፈንቅለ መንግሥት ሊጥሉ ሲዘጋጁ በሌሎች በቁጥጥር ስር ይውላሉ። ይህን ጊዜ ንጉሡ ባለቅኔ ስለነበሩ እንዲህ አሉ ይባላል:- ዕዕ ወሳእር እለ በዝናም ልሕቁ። ለዝናም ዘአልጎቆሙ ከመ ይክልእዎ ተላጸቁ። በዝናም ያደጉ ሣር

እና እንጨት ያሳደጋቸው ዝናምን ለመከልከል አንድ ሆኑ ማለት ነው። የሳር ቤት የሚሰራው ከእንጨትና ከሣር ነው። ከተሰራ በኋላ ዝናም አያስገባም። ከዚህ ላይ ሣርና እንጨት ተባብረው ዝናም የማያስገቡት መጀመሪያ እነርሱም ሕይወት አልባ ሆነው ነው። እነርሱ ሕይወት አልባ ሆነው ለሌሎች ሕይወት የሚሆነውን ዝናም ይከለክላሉ እንደማለት ነው። ከክፉ አንድነት እንራቅ። መልካም አንድነትን ቅዱስ ጳውሎስ አብራርቶታል። ሁላችንም የአንድ የክርስቶስ አካል ነን ብሏል። ቅዱስ ዳዊት ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሄልው አኃው ኅቡረ ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው ብሏል። አንድነት ኃይል ነው። ለአንድነት መሰረቱ የተመሳሳይ ግብ መኖር ነው።የሰው ልጅ ኅብረታዊ ነው። ሰው ግላዊ ሲሆን ከእውነት ያፈነግጣል። ምክንያቱም ለማንነቱ መሠረት የእናት አባቱ አሳዳጊነት፣ የማኅበረሰቡ ባህልና ወግ ይጠቀሳልና። ለሰው ልጅ የማንነቱ መሠረት ቤተሰቡ፣ ማኅበረሰቡ ነው። ስለዚህ ሰው ከግላዊነት ወጥቶ ኅብረታዊ ሲሆን ከእውነት ጋር ታረቀ ይባላል። በኅብረት/በተቋም ውስጥ የእያንዳንዱ አባል የተለያዩ ውስንነቶች ይኖሩታል። እነዚያን ውስንነቶች ግን ኅብረትን ለማፍረስ መጠቀም የለብንም። ኅብረታዊነት/ተቋማዊነት ግቡ ሰላማዊ ሕይወትን መምራት ነው። ለአንድነት መሰናክል የሆነውን ግላዊ ስሜታችንን እንዲሁም እኔ ያልኩት ካልሆነ ባይነትን ትተን እግዚአብሔር ያዘዘንን ሥራ እንስራ። ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ሳይሆን ከፍ ያሉ ጉዳዮች ላይ እናተኩር። ግለሰብ ተኮር ሳይሆን ጉዳይ ተኮር እንሁን።

ይቅርታ

ዘመን ሲከፋ መልካሙ ነገር እንደ ውርደት፣ ክፉው ነገር እንደ ጥሩ ሥራ ይታያል። በእርግጥ ዘመንን የሚያከፋውም የሚያሳምረውም ሰው ነው። እውነታው "ይቅርታ" የታላላቆች እና የአሸናፊዎች ምልክት ነው። አሁን ላይ ግን "ይቅርታ"ን መጠየቅ የተሸናፊዎች ምልክት ተደርጎ ይታያል። ብዙዎችም ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ እንዳይጠይቁ ታናሽ እንባላለን በማለት ከነጥፋታቸው በኩራት ይኖራሉ። በዚህም ምክንያት ትልልቅ ትንሾች ተፈጠሩ። ታዋቂ ትንሾች በዙ። በእርግጥ የይቅርታን ዋጋ የሚያውቁት የክርስቶስ ፍቅር የገባቸው እና የክርስቶስን ሁሉን አዋቂነት የተረዱ ናቸው። በተጨማሪም የይቅርታን ዋጋ የሚያውቁት የራሳቸውን ውስንነት የተረዱ ትሑታን ናቸው። ብዙዎች ይቅርታ ሲጠየቁ አሸናፊ የሆኑ ይመስላቸዋል። ይቅርታ የጠየቀው ደግሞ ተሸናፊ ይመስላቸዋል። ይህ ትንሽነት የወለደው ክፉ ሐሳብ ነው። ለክፋት ለውሸት ማስተባበያ ከመስጠት ይልቅ እውነታውን ተቀብሎ ጥፋትን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ ትልቅነት ነው። ከቅድስና መንገዶች አንዱ "ተአምኖ ኃጣውእ" ነው። ትርጉሙ ኃጢኣትን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ ማለት ነው። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ይህንን አድርጓል። መዝ. ፶ "ተሣሀለኒ እግዚኦ እስመ ድውይ አነ_ድውይ ነኝና አቤቱ ማረኝ" ብሏል። በደልን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ ትልቅነት ነው። በእርግጥ ሰሚ በሌለበት መናገር ትርፉ ድካም ነው። የዐቢየ እግዚእ ጉባኤ ቤት መምህር የነበሩት የኔታ ፀሐይ ብዙ ችግር እያዩ ዝም ይሉ ነበር ይባላል። ለምንድን ነው ዝም የሚሉ ሲሏቸው "ሰሚ በሌለበት መናገር ምን ይጠቅማል" ይሉ ነበር ይባላል። አንድ ሊቅም "እመ ተናገርኩ ጽድቀ ሰብአ ዛቲ ዓለም ይጸልኡኒ።ወከመ ኢይንብብ ሐሰተ ኩነኔ ዚኣከ ያፈርሀኒ።ወእምኩሉሰ አርምሞ ይኄይስ ወይሜኒ"።ብለዋል ይባላል። ትርጉሙ እውነትን ብናገር የዚህ ዓለም ሰዎች ይጠሉኛል። ሐሰትንም እንዳልናገር ጌታ ሆይ የአንተ ፍርድ ያስፈራኛል። ከሁሉም ግን ዝምታ ይሻለኛል" ማለት ነው። እውነት፣ ትሕትና፣ ፍቅር አይለየን።

ባሕረ ሐሳብ

፩ መግቢያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ንዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር መጽሐፈ ባሕረ ሐሳብ። በአብ ስም አምነን አብን ወላዲ ብለን በወልድ ስም አምነን ወልድን ተወላዲ ብለን በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ ብለን ምንም ለአጠይቆተ አካላት ሠለስቱ አካላት በስም በግብር በአካል ሦስት ብንል በባሕርይ በህልውና በፈቃድ አንድ አምላክ እንደሆኑ አምነን በእግዚአብሔር አጋዥነት ባሕረ ሐሳብን እንጀምራለን። በእግዚአብሔር አጋዥነት እንጀምራለን አለ ስንኳን መንፈሳዊ ሥራ ሥጋዊ ሥራ ቅሉ አርስ እቆፍር፣ እጽፍ እደጉስ፣ ቢሉ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይፈጸምምና። ኩላኬ ፍድፋዴ እንተ ይገብራ ብእሲ ኢትትፈጸም ዘእንበለ በረድኤተ እግዚአብሔር በከመ ቃሉ ለእግዚእነ እስመ ዘእንበሌየሰ አልቦ ዘትክሉ ገቢረ ወኢምንትኒ ዮሐ. ፲፭፣፭። ባሕረ ሐሳብ አለ ሐሳበ ባሕር ሲል ነው። የተዘዋወረ ቀለም ነው። ባሕር ያለው ዘመን ነው። እስመ በመዳልው ደለወ ዓለመ ወበመስፈርት ሰፈራ ለባሕር ለባሕርከኒ አልቦቱ ሐሳብ እንዲል። ሐሳብ ያለው ቁጥር ነው። ኢትትሐሰብዎሙ ወርቆሙ ወብሩሮሙ፣ ወእለ ኢሐሰበ ሎሙ ኵሎ ጌጋዮሙ እንዲል መዝ. ፶፩፣፭። አንድም እንዳለ ይሆናል ባሕረ ሐሳብ ማለት ቁጥር ያለው ዘመን ማለት ነው። እግዚአብሔር ቅድመ ዓለም እንዲህ እንደ ዛሬው ሁሉ በአንድነት በሦስትነት ሲሠለስ ሲቀደስ ይኖራል። ቅድመ ዓለም ፍጥረት ሳይኖር ማን ያመሰግነው ነበር ቢሉ ምሥጋና የባሕርዩ ስለሆነ አንድም ዛሬ የሚመሰገነው አካሉ ቅድመ ዓለም የነበረ ስለሆነ። እምቅድመ ይፍጥር መላእክተ ለቅዳሴ አኮ ስብሐቲሁ ዘተጸርዐ አላ ምሉዕ ውእቱ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዲል ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት። ከዚህ በኋላ ክብሩ በባሕርዩ እንደቀረ አውቆ ዓለምን ልፍጠር ብሎ አሰበ። አስቦም አልቀረ ፈጠረ። ሰውንና መላእክትን ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ ፈጠረ። የቀረውን ፍጥረት ግን ለአንክሮ ለተዘክሮ ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ ሊሆን ፈጠረ። ወኵሉ ዘተፈጥረ ለመፍቅደ ነባብያን። ቦ እምኔሆሙ ለምህሮ ወቦ እምኔሆሙ ለተዘክሮ እንዲል አረጋዊ መንፈሳዊ። እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት እያንዳንዱ ቢቆጠር ፍጡር ተናግሮ ባልፈጸመውም ነበር። ነገር ግን ሁሉን እየወገኑ እየወገኑ ብዙውን አንድ ብዙውን አንድ እያሉ ቢቆጥሩ ከአሑድ እስከ ዓርብ የፈጠረው ፍጥረት ፳፪ ነው። ፳፪ኛውም አዳም ነው። ጌታ አዳምን በነፍስ በሥጋ ሕያው አድርጎ ፈጥሮ በመንፈስ ቅዱስ አክብሮ ከአንዲት እፀ በለስ በቀር ከሰማይ በታች ከምድር በላይ

ያለውን ሁሉ ብላ ጠጣ ግዛ ንዳ ብሎ በገነት አኖረው። እርሱም ፮ ዓመት ከሁለት ወር ከአስራ ሰባት ቀን በሕጉ ጸንቶ ኖረ። ኩፋ.፬፣፲፯። ከዚህ በኋላ ግን ምክረ ከይሲን ሰምቶ አምላክነትን ሽቶ እፀ በለስን በልቶ ከፈጣሪ ተጣልቶ ከገነት ወጣ። ጌታም በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ርደተ ገሀነምን ፈረደበት። አዳምም በፈታሒነቱ አንጻር መሓሪነቱ እንዳለ አውቆ ንሥሓ ገባ። ንሥሓ ቢገባ በኃሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድህክ ውስተ መርህብከ ወእትቤዘወከ በመስቀልየ ወበሞትየ ብሎ ተስፋውን ነገረው (ቀሌምንጦስ)። አዳምም ይህን ተስፋ ሰምቶ ለልጆቹ ነገራቸው። ልጆቹም ይህን ተስፋ ይዘው እኩሉ በፀሐይ እኩሉ በጨረቃ እኩሎቹም በሰዋክብት ሲቆጥሩ ኖሩ። ነቢያትም ከዚህ አያይዘው ትንቢት ሲናገሩ ሱባዔ ሲቆጥሩ እስከ ዘመነ ሥጋዌ ደረሱ። ቁጥር የተጀመረበት ምክንያቱ ይህ ነው። ከዚህ በኋላ የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሳ አምላክ ቅድመ ዓለም በልቡና ያሰበውን ድኅረ ዓለም በነቢያት ያናገረውን ለመፈጸም ሰው ሆነ። ሥጋ ለበሰ። ሰው ሆኖም ሕግ ጠባይዓዊን ሕግ መጽሐፋዊን ሲፈጽም አደገ። ሕግ ጠባይዓዊ አበ እመ ማለት፣ ጽሕም ጥፍር ማብቀል፣ ለእናት ለዘመድ መታዘዝ፣ በየጥቂቱ ማደግ ነው። ልህቀ በበሕቅ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ እንተ ይእቲ እሙ እንዲል። ወለይእቲ እሙም ይላል። ሕግ መጽሐፋዊ በ፷ ቀን ወደ ግዝረት መግባት፣ በ፸ ቀን እጕለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ ይዞ ወደ ቤተ መቅደስ መግባት፣ በዓመት ፫ ጊዜ ለበዓል ወደ ኢየሩሳሌም መውጣት ነው። ለያስተርኢ ተባእተከ ሥልሰ ጊዜያተ ምዕረ በበዓመት ወዘኢዐርገ ለበዓል ርጉም ውእቱ እንድትል ኦሪት። እግዚኣ ለኦሪት ገብረ በሕገ ኦሪት ከመ ይሳየጦሙ ለእለ ውስተ ኦሪት እንዲል። ገላ. ፬፣፬: ዘሌ. ፲፪። ጌታ በ፲፪ ዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። መውጣቱም ለማስተማር ነው እንጂ ለሌላ አይደለም። በሌሎች ግን ከ፳ ዓመት በታች እንዳይወጡ ሥርዓት ተሠርቶባቸዋል። እሱ ግን በ፲፪ ዓመቱ ወጥቷል። እንዲህም አድርጎ ፴ ዓመት ሲሞላው በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ተጠመቀ። አብ በደመና ሆኖ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ መሰከረለት። መንፈስ ቅዱስም በአምሳለ ርግብ ወርዶ ከራሱ ላይ ተቀመጠ። ወልድ በክበበ ትስብእት ተገለጠ። አንድነት ሦስትነት ታወቀ። ማቴ. ፫። የባሕርይ ልጅነቱን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ካስመሰከረ በኋላ አልዋለም አላደረም። ዕለቱን ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ ፵ መዓልት፣ ፵ ሌሊት ጾመ። መዋዕለ ጾሙን ሲፈጽም ሰይጣን በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ፈተነው። በስስት፣ በትዕቢት፣ በፍቅረ ንዋይ።ሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ የሚሰኙ እኒህ ናቸው። ዛሬም ሰው እነዚህን ድል ከነሳ ሌሎች ኃጣውእ አይቆሙበትም አይቀዋወሙትም። ጌታም

በሦስቱ አርእስተ ምግባራት ድል ነሥቶታል። ሰይጣንን ድል ነስቶ ከዚያ ወጥቶ ምድረ እስራኤል ገብቶ ትምህርት ተአምራት ጀመረ። የእጁን ተአምራት አይተው የቃሉን ትምህርት ሰምተው ከአሥር አህጉር ከብዙ መንደር ተወጣጥተው የአምስት ገበያ የሚያህሉ ሰዎች ተከተሉት። ከእነዚያም ፲፪ ቤተሰብን ይመርጣል። መጀመሪያ ፲፪ቱን ሐዋርያት መረጠ። ወነረየ እምሰብአ ዚኣሁ ፲ወ፪ተ ሐዋርያተ እንዲል። ቀጥሎ ፸፪ቱን አርድእት መረጠ። ወረሰየ ካልዐነ ሰብx እንዲል። ፸ም ይላል በአነዙ። ቀጥሎም ፴፯ቱ ቅዱሳት አንስትን መረጠ። ፲፰ የጌታ ቤተሰብ የሚሰኙ እነዚህ ናቸው። እነዚህም ከዋለበት ይውላሉ ካደረበት ያድራሉ። ትምህርት ተአምራት አይከፈልባቸውም። ሌሎችን ግን ምሽት ይከለክላቸው ነበር። ለ፲፪ቱ ነገደ እስራኤል በየዕዛቸው እየገባ አንድ አንድ ወር ይሰብክላቸው ነበር። ፫ ዓመት ከ፫ ወር ወንጌልን ዙሮ አስተማረ። ትምህርቱ በምር ሲረዳለት ለመድኃኒተ ዓለም በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ተሰቀለ። ምነው ሌላ ብዙ መካናት አልነበሩምን ስለምን በቀራንዮ ተሰቀለ ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው። ትንቢት ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር ተብሎ ተነግሯል። መዝ. ፸፫፣፲፪። እርሱም ባለቤቱ ኢይደልዎ ለነቢይ መዊት በአፍኣ ዘእንበለ በኢየሩሳሌም ብሏል። ምሳሌውም አዳምን ያሳተ ርእሰ ከይሲ ከዚያ ወድቆ ነበርና እርሱን ፈጽሞ ድል እንደነሳው ለማጠየቅ። ትንቢቱን ባወቀ አናግሮታል። ምሳሌውንም ባወቀ አስመስሎታል። ምስጢሩ እንደምን ነው ቢሉ ዐፅመ አዳም ከዚያ ተቀብሮ ነበርና ለእርሱ ፈጽሞ እንደካሰ ለማጠየቅ ፫ መዓልት ፫ ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ዓለሙን በሞቱ አድኖ ተነሣ። በሰኑይ ዕለት ይሜርየነ ወየሐይወነ ወአመ ሣልስት ዕለት ሦጣ ለነፍሱ ውስተ ሥጋሁ። ወአመ ሣልስት ዕለት ንትነሣእ ወንቀውም ምስሌሁ እንዲል ሆሴዕ ፮፣፫። ተነስቶም ፴ ቀን መጽሐፈ ኪዳንን ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ለሐዋርያት አስተማረ። እንዲህ ስለሆነ ግን እንደቀድሞው ሰው ሰብስቦ ጉባኤ ሰርቶ ያስተማረ አይደለም። ለአንዱም ለሁለቱም ባለሚሉቹ እየተገለጸ ነው እንጂ። ማቴ. ፳፰፡ ማር. ፲፮፣፳፬፡ ዮሐ. ፳። ዛሬም ምድራዊ ንጉሥ ልሰወር ባለጊዜ ለአንዱም ለሁለቱም ባለሚሉቹ ሳይገልጥ እንዳይውል። ለመላው ግን የተገለጠላቸው ሦስት ቀን ነው። የትንሣኤ፣ የአግብኦተ ግብር (ዳግም ትንሣኤ)፣ የጥብርያዶስ (ዓሣ ሲፈልጉ)። ወዝንቱ ሣልሱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ያስተርእዮሙ ለአርዳኢሁ ተንሢአ እምነ ምውታን እንዲል። ዮሐ. ፳፣፲፬። ከዚህ በኋላ ትእዛዙን አሏቸው ተስፋውን ነግሯቸው ዐረገ። ትእዛዝ ሑሩ ወመሀሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ያለው ነው። ማቴ.

፳፰፣፲፱። ተስፋ ጽንሑ ተስፋሁ ለአብ አንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም ያለው ነው። ሉቃ. ፳፬፣፵፰። በተነሳ በኃምሳ ቀን ባረገ በአሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ለሐዋርያት ሰደደላቸው። እስከዚያ ወዴት ኑሮ ቢሉ ከአሥረኛው መዓርግ የወጣን እኛ ነበርንና ወደ ጥንት ቦታችን እንደመለስን ለማጠየቅ። አንድም ከዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት አንዱ ነገድ ሥጋዌውን ያላወቁ ነበሩና እነዚያን ሲያስተምር ቆይቶ። ምነው ይህማ እንዳይሆን ፈጣሪ ፍጡር ይመስል አንዱን ሥራ ሲሰራ አንዱ ሥራ ይከፈልበታልን ወዲያስ ቢያስተምራቸው ወዲህስ መንፈስ ቅዱስን ቢሰድላቸው ይሆንለት አልነበረምን ቢሉ ነገር ከቀደመው ይገባል። አንድም እኔ አሥሩን ቃላት አሥሩን ሕዋሳት ጠብቄ መንፈስ ቅዱስን ሰጠኋችሁ። እናንተም አሥሩን ቃላት አሥሩን ሕዋሳት ብትጠብቁ መንፈስ ቅዱስ ይሰጣችኋል ለማለት። ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ከብልየት ታደሱ በአእምሮ ጎለመሱ ምሥጢር ተረጎሙ። ብልየት ኃጢአት፣ ተሐድሶ ልጅነት። ልጅነትንስ በዕለተ ኃሙስ በሕጽበተ እግር አግኝተውታል ብሎ ብልየት ድንቁርና፣ ተሐድሶ እውቀት፣ ብልየት ፍርሀት፣ ተሐድሶ ጥብዐት፣ ብልየት በአንድ ቋንቋ መናገር፣ ተሐድሶ በ፸፪ ቋንቋ መናገር ነው። አንድ ዓመት በሕብረት መዲናይቱ ኢየሩሳሌምን ሲያስተምሩ ኖሩ። ወነበሩ ሐዋርያት ዓመተ ፍጽምተ በኢየሩሳሌም እንዲል። ከዚህ በኋላ ሑሩ ወመሀሩ ያላቸውን ያውቃሉና ለስብከተ ወንጌል ሲፋጠኑ ይህን ባሕረ ሐሳብ ሳያስተምሩት ቀርተዋል። አንድም ዲሜጥሮስ እንዲነሳ አውቀው እርሱ ያስተምረዋል ብለው ትተውታል። ከሐዋርያት ቀጥለው የነበሩ ምእመናን ዐቢይ ጾምን በጥር ፲፪ ቀን ጀምረው በየካቲት ፳፩ እየፈጸሙ በዓል ሳይዙ ከጾም ላይ ያርፉ ነበር። ሰሙነ ሕማማትንም በመጋቢት ፳፪ ጀምረው በ፳፯ እየፈጸሙ በ፳፱ ትንሣኤን ሰኞም ቢውል ማክሰኞም ቢውል ያከብሩ ነበር። ይህም ሥርዓት ሲያያዝ እስከ ዘመነ ድሜጥሮስ ደርሷል። ይህም ዲሜጥሮስ ጌታ ባረገ በ፱፻ ዘመን በእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ሆኖ ተሾመ። በተሾመ በ፳፯ ዘመን ይህ ባሕረ ሐሳብ ተገለጸለት። እርሱም ለ፫ቱ ሊቃነ ጳጳሳት ፬ኛ በኢየሩሳሌም ለነበረው ኤጲስ ቆጶስ ጽፎ ሰደደላቸው። እነርሱም ሐዋርያት በዲድስቅልያ ካስተማሩት ጋራ አንድ ቢሆንላቸው ተቀብለው አስተምረውታል። ሐዋርያት በዲድስቅልያ ምን ብለው አስተምረውታል ቢሉ ወኢይኩን ትንሣኤ ዘእንበለ በዕለተ እሑድ ብለው አስተምረዋል። ሠለስቱ ምእትም ጉብኤ ሠርተው አስተምረውታል። ወአስተላጸቅዋ ለጾመ ፶ ቅድስት ምስለ ሰሙነ ሕማማት ወሠርዐ አበቅቴ ወሐሳበ ውስተ ኵሎን አብያተ ክርስቲያናት እንዲል። ቁጥሩም ቢፋለስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ይመስክር

ብለዋል። ወአዘዙ ከመ ኵሉ ዘስሕተ አበቅቱ ወሐሳበ ይትመራሕ በሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ እንዲል። ይህን ባሕረ ሐሳብ ሁሉ ሊማረው ይገባል። ባሕረ ሐሳብን የማያውቅ ካህን ውሃ የሌለው ደረቅ ወንዝን ይመስላል። ደረቅ ወንዝ ነጋድያን አልፈው ሲሄዱ ጫፉ ረዝሞ ቅጠሉ ለምልሞ ታላቅ ዛፍ ባዩ ጊዜ ውሃ ያለው መስሏቸው ከጥላው አርፈን ጥሬ ቆርጥመን ውሃ ጠጥተን እንነሳ ብለው ይሄዳሉ። ውሃ ሲያጡበት አዝነው ተሰቅቀው ይመለሳሉ። ባሕረ ሐሳብንም የማያውቅ ካህን ምእመናን አምሞ ጠምጥሞ መነሳንሱን ይዞ ሠናፊሉን አንሰርቶ ልብሱን አንጽቶ በአዩት ጊዜ የተማረ መስሏቸው አጽዋማትን በዓላትን አውጥቶ ይነግረናል ብለው ሊጠይቁት ይሄዳሉ። ፍሬ ነገር ሲያጡበት አዝነው ተሰቅቀው ይመለሳሉ። ካህን ዘኢተምህረ መጽሐፈ ባሕረ ሐሳብ ይመስል ከመ ፈለግ ዘአልቦ ማይ ውስቴቱ ወከመ ሀገር ዘአልቦ ጥቅም።

፪ የዲሜጥሮስ ታሪክ

ትውልዱንም ከዚህ ይናገሩታል። አርማስቆስ ደማስቆስ የሚባሉ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ። ልጆቻቸውም ድሜጥሮስ ልዕለተ ወይን ይባላሉ። አርማስቆስ የድሜጥሮስ አባት ነው። ደማስቆስ የልዕልተ ወይን አባት ነው። አስቀድሞ የልዕልተ ወይን አባት ሞተ። ከአጎቷ ቤት ከድሜጥሮስ ጋር አደገች። የልዕልተ ወይን አባት ሲሞት ልጁ ልዕልተ ወይንን ከ፲፭ ዓመት በታች አታጋቧት። ከ፲፭ ዓመት በላይም አታሳልፏት። ለአሕዛብ አትስጧት ብሎ ተናዘ ዐረፈ። ያን ጊዜ ምዕመናን ያነሱበት አሕዛብ የበዙበት ወራት ነበርና ለእርሷ የሚሆን ደግ ሰው አጡ። እነርሱም ሕንፃ ሃይማኖት ከሚፈርስ ሕንፃ ሥጋ ይፍረስ ብለው ለአጎቷ ልጅ ለድሜጥሮስ አጭተው አጋቧት። ሥርዓተ መርዓዊ ወመርዓት ያድርሱ ብለው ከጫጉላ ቤት አግብተው መጋረጃ ጥለውባቸው ሄዱ። እርሷም ወንድሜ እኔን ንቀህ ነው? ወይስ ተዘምዶውን አለችው። እርሱም እኔስ አንችንም ተዘምዶውንም ንቄ አይደለም። የአባት የእናት ፈቃድ እፈጽማለሁ ብየ ነው እንጂ አሁንም ንጽሕናውን ከወደድሽው አብረን እንኑር የተለያየን እንደሆነ እኔን ለአንዲቱ አንችንም ለአንዱ ያጋቡናል አብረን ብንኖር ግን እግዚአብሔር ልጅ ባይሰጣቸው ነው መክነው ነው ይሉናል እንጂ በዚህ የሚጠረጥረን የለም አላት። እሷም ይሁን አለችው። ከዚህ በኋላ በአንድ አልጋ እየተኙ አንድ ምንጣፍ እያነጠፉ አንድ ልብስ እየለበሱ ፯፭ ዘመን በንጽሕና አብረው ኖረዋል። ይህም ይታወቅ ዘንድ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል መጥቶ ቀኝ ክንፉን ለእርሱ ግራ ክንፉን ለእርሷ አልብሷቸው አድሮ ጧት በአምሳለ ርግብ በመስኮት ወጥቶ ሲሄድ ይታይ ነበር። ድሜጥሮስም ድኮ ታጥቆ ተክል አጽድቆ እርፍ አርቆ የተጣላ አስታርቆ

የታመመ ጠይቆ ይኖር ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን ወደ ተክል ቦታ ቢገባ ያለጊዜው ያፈራ የስንዴ ዛላ የወይን ዘለላ አገኘ። ይህንስ ወደ ሊቀ ጳጳሱ ወስጀ በረከት ልቀበልበት ብሎ አሰበ። አስቦም አልቀረ ወስዶ ለሚስቱ ሰጣት። እርሷም ይህማ ለአባታችን ለሊቀጳጳሱ ነው እንጂ መች ለእኛ ይገባናል ብላ በንጹሕ ሙዳይ አድርጋ እንካ ወስደህ በረከት ተቀበልበት አለችው። በፈቃደ እግዚአብሔር የባልና የሚስት ሐሳብ አንድ ሆኗል። ያንጊዜ ሊቀ ጳጳሱ ዮልዮስ ወይም ዩልያኖስ ይባል ነበር። አርጅቶ ነበርና ሕዝቡ ተሰብስበው አባታችን አንተ አረጀህ ወደደገኛው ዓለም ልትሄድ ሆነ። እኛን የሚጠብቀን ደግ ሰው ተካልን አሉት። እርሱም ከእኔ ቀጥሎ የሚሾመውን እንድናውቀው ቀኖና እንግባ አላቸው። ተያይዘው ቀኖና ገቡ። ለእርሱ ዕለቱን ተገለጸለት። እነርሱ ሱባዔያቸውን ሲጨርሱ አገኛችሁን አላቸው። እኛስ አላገኘንም አሉት። እኔ አግኝቼዋለሁ ከእኔ ቀጥሎ የሚሾመው ያለጊዜው ያፈራ የስንዴ ዛላ የወይን ዘለላ ይዞ የሚመጣው ነው አላቸው። ወዲያውም ድሜጥሮስ መጥቶ ከበር ቁሞ ንገሩልኝ አለ። ግባ በሉት ብሎ አስገብቶ ሕዝቡን አሰባስቦ ያ ያልኳችሁ ሰው ይህ ነው። ይቀመጥ በወንበሬ ይናገር በከንፈሬ እሱን ተክቼላችኋለሁ ብሎ በሦስተኛው ቀን አረፈ። ወቀበርዎ በዝማሬ ወበማህሌት ይላል። እርሱን ቀብረው ሲመለሱ ወንበር ያለ ሹም አያድርምና አባታችን የሰጠን አንተን ነውና ተሾምልን አሉት። እርሱም ጳድቁ በተቀመጠበት ወንበር እኔ ኀጥኡ ድንግል በተቀመጠበት ወንበር እኔ ሕጋዊው ምሁሩ በተቀመጠበት ወንበር እኔ ጨዋው መቀመጥ አይገባኝም አይሆንም አላቸው። ወአኀዝዎ በሶርሕ ይላል ግድ ብለው ሹመውታል። እርሱም ለመንበረ ማርቆስ ፲፪ኛ ተራ ቁጥር ነው። በተሾመ ጊዜ የሕዝቡ ኃጢአታቸው ተገልጾ እየታየው አንተ በቅተህል ቁረብ አንተ አልበቃህም አትቁረብ እያለ ይከለክላቸው ጀመር እነርሱም እርሱ በማይገባው ከሚስቱ ጋር ሁኖ እኛን እንዲህ ይለናል እያሉ በዚህ ምክንያት ያሙታል። ይጠሉታል። ከዕለታት በአንድ ቀን የሚሸሩበትን ምክንያት ሲሹ ቀድሞ አባታችን ዮልዮስ አንቀፀ ብፁዓንን አንቀፀ አባግዕን አንብቦ ተርጉሞ ይነግረን ነበር። አንተም አባታችን አንቀጸ ብፁዓንን አንቀፀ አባግዕን አንብበህ ተርጉመህ ንገረን አሉት። ጨዋ ነው አይሆንለትም በዚህ ምክንያት እንሸረዋለን ሲሉ ነው።ለጊዜው ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ በአካለ ነፍስ መጥቶ በእርሱ ተገብቶ አሰምቷቸዋል። ፍጻሜው ግን ብሉይ ከሐዲስ ተገልጦለታል። ከዚህ በኋላ መልአኩ መጥቶ ኢትፍቅድ አድኅኖ ርእስከ አላ ክስት ሎሙ ክብረከ ዘሀሎ ማዕከሌከ ወማዕከለ ብእሲትከ ከመ ኢይትኀነሉ ሕዝብ በእንቲኣከ። ሕዝቡ አንተን እያሙ እንዳይጎዱ ክብርህን ግለጽላቸው አለው።

እርሱም እኔ በማስተዳድረው ሀገረ ስብከት ያላችሁ ምእመናን ሁሉ አንድ አንድ ሽክም እንጨት እየያዛችሁ ተሰብሰቡ ብሎ አዋጅ ነገረ። ሕዝቡም አንድ አንድ ሽክም እንጨት እየያዙ ተሰበሰቡ ያነን ደመራ አስደምሮ በእሳት አቃጥሉት ብሎ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ቅዳሴ ገባ ቅዳሴውን ሲጨርስ ልብሰ ተክህኖውን እንደለበሰ ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ ከእሳቱ ውስጥ እየገባ እየወጣ ያጥን ጀመር አንድም ከደመራው ላይ ቁሞ በእሳት አቃጥሉት አላቸው። በምን ምክንያት እንሸረዋለን ስንል ከእሳት ገብቶ ሊሞት ነው አሉ። ነገር ግን ነበልባሉ በርዶ ፍሕሙ መርቶ ከፍሕሙ ላይ ቁሞ ሲጸልይ አዩት። አለሳ አልሞተም አሉ። አሁንም አላመኑኝምን ብሎ ሚስቱ ከምቅዋመ አንስት ቁማ ነበረችና አስጠርቶ ንዒ ስፍሒ አጽፈኪ ነይ ልብስሽን ወይም ኩፋርሽን ዘርጊ አላት። ነጭ ሐር ልብስ ለብሳ ነበርና። ፍሕሙን በእጁ እያፈሰ ከልብሷ ላይ አድርጎ ሂጂ እየዞርሽ ለሕዝቡ ሁሉ አሳዩ አላት። እሷም ይህው ከተጋባን ፴፰ ዘመናችን ነው። በልማደ ብእሲ ወብእሲት አንተዋወቅም። የንጽሕናችንም ምስክር ይህ ነው። በከንቱ አትሙን እያለች ለሕዝቡ ሁሉ እየዞረች አሳይታለች። ከልብሷም አንዱ ዝሀ ስንኳ አልቀነበረም። ሕዝቡም ኦ አቡነ ሥረይ ለነ አሉት። እርሱም ይፍታሕ ይጎድግ ያንጽሕ ወይቀድስ ወያስተሥሪ ሊቀ ካህናት ሠራኤ ኃጢአት ወደምሳሴ አበሳ ዘወሀቦሙ ስልጣነ ለአበዊነ ሐዋርያት በዘአእመረ መንፈስ ቅዱስ ይስረይ ለክሙ ኃጢአተክሙ ዘገበርክሙ እምንእስክሙ እስከ ይእዜ አበውየ ካህናት ወአኃውየ ዲያቆናት አግብርተ እግዚአብሔር ወአእማተ እግዚአብሔር ኩኑ ፍቱሐነ ወንጹሐነ ይረስየነ ይረሲክሙ ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ብሎ ናሂቸዋል። ኑሣዜ ያን ጊዜ ተጀምሯል። የዲሜጥሮስም ጸሎቱ ቀን ሰባት ሰባት፣ ሌሊት ፷፫ ሱባኤ እየሰገደ ይጸልይ ነበር። ስለምን የቀኑ አነሰ የሌሊቱ በዛ ቢሉ ቀን ሲፈርድ ሲተች፣ የተጣላ ሲያስታርቅ፣ የተበደለ ሲያስክስ፣ የተቀማ ሲያስመልስ፣ ድውይ ሲጠይቅ፣ የሞተ ሲቀብር ይውል ነበር። በሌሊት ግን ይህ ሁሉ የለበትምና። ስለዚህ የቀኑ አነሰ የሌሊቱ በዛ። አጽዋማት በዓላት እንዲህ እንደዛሬው ሁሉ አልተወሰኑም ነበርና ነነዌ ዓቢይ ጾም ጾመ ሐዋርያት ከሰኞ፣ ደብረ ዘይት ሆሳእና ትንሣኤ ጸራቅሊጦስ ከእሑድ፣ ስቅለት ከዓርብ፣ ዕርገት ከኃሙስ፣ ርክበ ካህናት ጾመ ድኅነት ከረቡዕ ባይወጡ በወደድኩ ነበር ብሎ ተመኘ። ከዚህ በኋላ መልአኩ መጥቶ ነገር በተምኔት ይፈጸማልን ሱባኤውን ገድፈህ የተረፈውን ያዝ አለው። የቀኑ ሰባት ሰባት ሱባኤ ቢገጥሙት ፶፱ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፲፱ ይተርፋል። ይህን መጥቅዕ በለው ብሎታል። የሌሊቱ ፷፫ ሱባኤ ፻፷፩ ይሆናል። ፻፺ውን በ፷ ሠላሳ ገድፎ ፲፩ ይተርፋል። ይህን አበቅቴ በለው ብሎታል። ፲፱ኝና ፲፩ን

ቢገጥሙት ፴ ይሆናል። መጥቅዕ ቢበዛ አበቅቱ ቢያንስ አበቅቱ ቢበዛ መጥቅዕ ቢያንስ ከ፴ አይወጡም ከ፴ አይወርዱም። ሁልጊዜ ፴ ሆነው ይኖራሉ እንጂ። መጥቅዕ ወአበቅቱ እመ ይበዝኑ ኢየዐርጉ እም፴ ወእመ ይውህዱ ኢይወርዱ እም፴ ወትረ ይከውኑ ፴ እንዲል። ያንጊዜ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው። መስከረም ማክሰኞ ብቶ ነበርና ማክሰኞ ለማክሰኞ ፮፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፲፭፣ ረቡዕ ፲፯፣ ኃሙስ ፲፯፣ ዓርብ ፲፰፣ ቅዳሜ ፲፱፣ የቅዳሜ ተውሳክ ፳፣ ፳ እና ፲፱ን ቢገጥሙት ፳፯ ይሆናል። ድሜጥሮስ በመጀመሪያ ያወጣው መባጃ ሐመር ፳፯ ነው። በመስከረም ሳኒታ ጥር ረቡዕ ይውላል። ረቡዕ ለረቡዕ ፳፣ ረቡዕ ለረቡዕ ፲፭፣ ረቡዕ ለረቡዕ ፳፪፣ ኃሙስ ፳፫፣ዓርብ ፳፬፣ ቅዳሜ ፳፭፣ እሑድ ፳፯፣ ሰኞ ፳፯። ጥር በባተ በ፳፯ኛው ቀን ነነዌን አዋለ። እንደተመኘ አገኘ። የነነዌ የራሷ የሆነ ተውሳክ የላትም። በደረቅ መባጃ ሐመር ብቻ ትወጣለች። የዐቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬፣ የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩፣ የሆሳእና ተውሳክ ፪፣ የስቅለት ተውሳክ ፯፣ የትንሣኤ ተውሳክ ፳፯፣ የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ፳፱፣ የጾመ ድኅነት ተውሳክ ፩ ነው። የዐቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬ትንና ፳፯ን ቢገጥሙት ፵፩ ይሆናል። ፴ ገድፎ ፲፩ ይሆናል። የካቲት ዓርብ ይብታል። ዓርብ ለዓርብ ፳፣ ቅዳሜ ፱፣ እሑድ ፲፣ ሰኞ ፲፩። የካቲት በባተ በ፲፩ ሰኞ ቀን ዓቢይ ጾምን አዋለ።እንደተመኘ አገኘ። የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩ንና ፳፯ትን ቢገጥሙት ፴፰ ይሆናል። ፴ ገድፎ ፳ ይተርፋል። መጋቢት እሑድ ይብታል። እሑድ ለእሑድ ፳። መጋቢት በባተ በ፳ ቀን እሑድ ቀን ደብረ ዘይትን አዋለ። እንደተመኘ አገኘ። የሆሳዕና ተውሳክ ፪ንና ፳፯ትን ቢገጥሙት ፳፱ ይሆናል። በዚሁ ብተት ይሄዳል። እሑድ ለእሑድ ፳፣ እሑድ ለእሑድ ፲፭፣ እሑድ ለእሑድ ፳፪፣ እሑድ ለእሑድ ፳፱። መጋቢት በባተ በ፳፱ እሑድ ቀን ሆሳዕናን አዋለ እንደተመኘ አገኘ። የስቅለት ተውሳክ ፯ትንና ፳፯ትን ቢገጥሙት ፴፬ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፬ ይተርፋል። ሚያዚያ ሰኞን አስግሮ ማክሰኞ ይብታል። ማክሰኞ ፩፣ ረቡዕ ፪፣ ኃሙስ ፫፣ ዓርብ ፬። ሚያዝያ በባተ በ፬ ቀን ዓርብ ቀን ስቅለትን አዋለ። እንደተመኘ አገኘ። የትንሣኤ ተውሳክ ፱ንና ፳፯ትን ቢገጥሙት ፴፮ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፮ ይቀራል። በዚህ ብተት ይሄዳል። ማክሰኞ ፩፣ ረቡዕ ፪፣ ኃሙስ ፫፣ ዓርብ ፬፣ ቅዳሜ ፭፣ እሑድ ፮። ሚያዝያ በባተ በ፮ እሑድ ቀን ትንሣኤን አዋለ። እንደተመኘ አገኘ። የርክበ ካህናት ተውሳክ ፫ትንና ፳፯ትን ቢገጥሙት ፴ ይሆናል። በዚሁ ብተት ይሄዳል። ማክሰኞ ለማክሰኞ ፮፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፲፭፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፳፪፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፳፱፣ ረቡዕ ፴። ሚያዝያ በባተ በ፴ ረቡዕ ቀን ርክበ ካህናትን አዋለ እንደተመኘ አገኘ። የዕርገት ተውሳክ ፲፮ትንና ፳፯ትን ቢገጥሙት ፵፭ ይሆናል።

ሠውን ገድፎ ፲፭ ይተርፋል። ግንቦት ረቡዕን አስግሮ ኃሙስ ይብታል። ኃሙስ ለኃሙስ ፰፣ ኃሙስ ለኃሙስ ፲፭። ግንቦት በባተ በ፲፭ኛ ቀን ኃሙስ ቀን ዕርገትን አዋለ። እንደ ተመኘ አገኘ። የጳራቅሊጦስ ተውሳክ ፳፯ትንና ፳፯ትን ቢገጥሙት ፶፭ ይሆናል። ሠ ገድፎ ፳፭ ይተርፋል። በዚሁ ብተት ይሄዳል። ኃሙስ ለኃሙስ ፰፣ ኃሙስ ለኃሙስ ፲፭፣ ኃሙስ ለኃሙስ ፳፪፣ ዓርብ ፳፫፣ ቅዳሜ ፳፬፣ እሑድ ፳፭። ግንቦት በባተ በ፳፭ እሑድ ቀን ጰራቅሊጦስን አዋለ። እንደተመኘው አገኘ። የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ፳፱ኝንና ፳፯ትን ቢገጥሙት ፶፮ ይሆናል። ሠውን ገድፎ ፳፮ ይተርፋል። በዚሁ ብተት ይሄዳል። ኃሙስ ለኃሙስ ፰፣ ኃሙስ ለኃሙስ ፲፭፣ ኃሙስ ለኃሙስ ፳፪፣ ዓርብ ፳፫፣ ቅዳሜ ፳፬፣ እሑድ ፳፭፣ ሰኞ ፳፮። ግንቦት በባተ በ፳፮ ሰኞ ቀን ጾመ ሐዋርያትን አዋለ። እንደተመኘው አገኘ። የጾመ ድኅነት ተውሳክ ፭ድንና ፳፯ትን ቢገጥሙት ፳፰ ይሆናል። በዚሁ ብተት ይሄዳል። ኃሙስ ለኃሙስ ፰፣ ኃሙስ ለኃሙስ ፲፭፣ ኃሙስ ለኃሙስ ፳፪፣ ኃሙስ ለኃሙስ ፳፱። አንዱን ታግሦ ግንቦት በባተ በ፳፰ ረቡዕ ቀን ጾመ ድኅነትን አዋለ። እንደተመኘው አገኘ። ቅዱስ ዲሜጥሮስ በመጀመሪያ ያወጣው የአጽዋማትና የበዓላት ቀመር ይህ ነው።

፫ ሰባቱ አዕዋዳት

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ዘመን ቢቆጠር በፀሐይ ፷፻፭፻፲፮ ዓመት ሆነ ይሏል። ለዚህም መስፈሪያ መቁጠሪያ ፯ አዕዋዳት አሉ። ምንና ምን ናቸው ቢሉ ዓውደ ዕለት፣ ዓውደ ወርኅ፣ ዓውደ ጨረቃ፣ ዓውደ ዓመት፣ ዓውደ ዐቢይ ቀመር፣ ዓውደ ማዕከላዊ ቀመር፣ ዓውደ ንዑስ ቀመር ናቸው። ዓውደ ዕለት ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት ሰባቱ ዕለታት ናቸው። ዓውደ ወርኅን ለማስገኘት ሁልጊዜ በሰባት በሰባት ሲመላለሱ ይኖራሉ። ዓውደ ወርኅ በጨረቃ አንድ ጊዜ ፳፱ አንድ ጊዜ ፴ ነው። በፀሐይ ግን ሁልጊዜ ፴ ሁኖ ይኖራል። ዓውደ ዓመትን ለማስገኘት ሁልጊዜ በ፴ በ፴ ሲመላለስ ይኖራል። ዓውደ ጨረቃ ፫፻፶፬ ዕለት ነው። ዓውደ ዓመት ፫፻፷፭ ዕለት ነው። ፫፻፷፮ም ይሆናል። በዘመነ ዮሐንስ ፬ቱ በዕለት የቀሩት በዓመት ይቆጠራሉ። ዓውደ ዐቢይ ቀመር መደቡ ፲፬ ቁጥሩ ፭፻፴፪ ነው። በዚህ ዕለት ወንጌላዊ አበቅቱ ይገናኙበታል። ዓውደ ማዕከላዊ ቀመር መደቡ ፯ ቁጥሩ ፷፯ ነው። በዚህ ዕለት ወንጌላዊ ይገናኙበታል። ዓውደ ንዑስ ቀመር መደቡ ፬ ቁጥሩ ፲፱ ነው። በዚህ ፀሐይና ጨረቃ ጎዳናቸውን ፈጽመው በተፈጠሩበት ኖኅት ተራክቦ ያደርጉበታል።

፬ የአጽዋማትና በዓላት አወጣጥ

የ፳፻፲፯ን ዓ.ም አጽዋማትንና በዓላትን ለማውጣት ይህንን ፷፻፭፻፲፮ ዘመን በዓቢይ

ቀመሩ ቢቀምሩት ፲፬ ዐቢይ ቀመር ሆኖ ፷፷ ይተርፋል። ፷፷ን በንዑስ ቀመር ቢቀምሩት ፫ ንዑስ ቀመር ሆኖ ፲፩ ይተርፋል። ስለተጀመረ ተቆጠረ ስላልተፈጸመ ታተተ አሐደ አእትት ለዘመን ይላል ብሎ አንዱን አትቶ ፲ ወንበር ወጣ ይሏል። በዘመነ ዮሐንስ አበቅቴን ለማግኘት ፲ሩን ወንበር አስራ አንድ አስራ አንድ ቢሰጡ ፻፲ ይሆናል። ፭ውን በሦስት ፴ ገድፎ ፳ ይተርፋል። አበቅቴ ፳ ወጣ ይሏል። በዘመነ ዮሐንስ መጥቅዕን ለማግኘት ለአሥሩ ወንበር ፲፱፡ ፲፱ ቢሰጡ ፻፺ ይሆናል። ፻፺ውን በስድስት ፴ ገድፎ ፲ ይተርፋል። ፲ መጥቅዕ ወጣ ይሏል። በዘመነ ዮሐንስ ፲ መጥቅዕንና ፳ አበቅቴን ቢገጥሙት ፴ ይሆናል። መጥቅዕ ቢበዛ አበቅቴ ቢያንስ አበቅቴ ቢበዛ መጥቅዕ ቢያንስ ከሠላሳ አይወጡም ከሠላሳ አይወርዱም። ሁልጊዜ ፴ ሆነው ይኖራሉ እንጂ። መጥቅዕ ወአበቅቴ እመ ይበዝኑ ኢየዐርጉ እም ሠላሳ ወእመ ይውህዱ ኢይወርዱ እም ሠላሳ ወትረ ይከውኑ ሠላሳ እንዲል። የሚነሳው ዕለት የሚነሳለት ዓመት ነው። አበቅቴ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ ጉልቄ ተረፈ ዘመን ማለት ነው። አበቅቴ ብሂል ዘበትርጓሜሁ ጉልቄ ተረፈ ዘመን እንዲል። ጨረቃ ከፀሐይ ፲፩ ታጎድላለችና። መጥቅዕ ማለትሳ ምን ማለት ነው ቢሉ በቁሙ መጥቅዕ ነጋሪት ማለት ነው። መጥቅዕ ነጋሪት ሲመታ ብዙ ሰው እንዲሰበሰብ እርሱም አጽዋማትንና በዓላትን ሰብስቦ የሚያውል ስለሆነ መጥቅዕ ብሂል አስተጋባኢ ብሂል እንዲል። እንዲህ ከሆነ ስለምን ዕለቱን መጥቅዕ አለው ቢሉ እስራኤል ፮ ዓመት ምድራቸውን አርሰው በ፯ኛው ዓመት በመጀመሪያው ወርኅ በ፲፱ኛው ቀን መጥቅዕ (ነጋሪት) መትተው ሕዝቡን ሰብስበው ጉባኤ ሠርተው በዘመነ ብሉይ የተሠሩ አጽዋማት በዓላትን አውጥተው ይለያዩ ነበር። መምህራነ ቤተክርስቲያንም የቅዱስ ዮሐንስ ዕለት መጥቅዕ (ነጋሪት) መትተው ሕዝቡን ሰብስበው ጉባኤ ሰርተው በዘመነ ሐዲስ የተሰሩ አጽዋማት በዓላትን አውጥተው የሚለያዩ ስለሆነ እንዲህ አለ። እስመ ከመ መጥቅዕ ዘብርት ወዘኀሊን ዘዕፀ ወዘዕብን ያስተጋብእ ዝርዋነ ከማሁ ውእቱኒ ያስተጋብዕ አጽዋማተ ወበዓላተ ዘሎሉን ዓመታት እንዲል። መጥቅዕ ፲፬ትን አይነካም። ከ፲፬ በላይ ያለ መጥቅዕ በመስከረም ይውላል። ነነዌ በጥር ትውላለች። እንዲህ ስለሆነ ግን መባጃ ሐመር ፴ መልቶ ቢተርፍ ፴ውን ገድፎ በተረፈው ቆጥሮ ነነዌ በየካቲት ትውላለች። አልቦ አበቅቴ በሆነ በ፲፭ኛው ዓመት ይገኛል። ከ፲፬ በታች ያለ መጥቅዕ በጥቅምት ይውላል። ነነዌ በየካቲት ትውላለች። በ፭ እና በ፲፬ መጥቅዕ አይውልም። ዘይገብር አሐደ መጥቅዐ ኑፋቅ ወስሑት ውእቱ እንዳለ ዮሐንስ አቡሻህር። የዕለታት ተውሳክ በቅዳሜ ይጀምራል። የቅዳሜ ተውሳክ ፰ ነው። የእሑድ ተውሳክ ፯ ነው። የሰኞ ተውሳክ ፮ ነው። የማክሰኞ

ተውሳክ ፮ ነው። የረቡዕ ተውሳክ ፬ ነው። የኃሙስ ተውሳክ ፫ ነው። የዓርብ ተውሳክ ፪ ነው። መስከረም ማክሰኞ ይብታል። ጥቅምት ረቡዕን አስግሮ ኃሙስ ይብታል። ኃሙስ ለኃሙስ ፮፣ ዓርብ ፱፣ ቅዳሜ ፩። የቅዳሜ ተውሳክ ፮ትንና መጥቅዑን ፩ን ቢገጥሙት ፲፮ ይሆናል። መባጃ ሐመር ፲፮ ወጣ ይሏል። በዘመነ ዮሐንስ በጥቅምት ሳኒታ የካቲት ዓርብ ይብታል። ዓርብ ለዓርብ ፮፣ ዓርብ ለዓርብ ፲፭፣ ቅዳሜ ፲፯፣ እሑድ ፲፯፣ ሰኞ ፲፰። የካቲት በባተ በ፲፰ ቀን ነነዌ ትውላለች። የዓቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬ ነው። ፲፬ትንና ፲፰ትን ቢገጥሙት ፴፪ ይሆናል። በሠላሳ ሲገደፍ ፪ ይሆናል። መጋቢት ቅዳሜን አስግሮ እሑድ ይብታል። መጋቢት በባተ በ፪ ሰኞ ቀን ዐቢይ ጾም ይውላል። የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፭ን ከ፲፰ ቢገጥሙት ፳፱ ይሆናል። መጋቢት እሑድ ይብታል። እሑድ ለእሑድ ፮፣ እሑድ ለእሑድ ፲፭፣ እሑድ ለእሑድ ፳፪፣ እሑድ ለእሑድ ፳፱። ደብረ ዘይት መጋቢት በባተ በ፳፱ እሑድ ይውላል። የሆሳዕና ተውሳክ ፪ንና ፲፰ን ቢገጥሙት ፳ ይሆናል። ሚያዝያ ሰኞን አስግሮ ማክሰኞ ይውላል። ማክሰኞ ለማክሰኞ ፮፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፲፭፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፳፪፣ ሁለት ታግሦ ሚያዝያ በባተ በ፳ እሑድ ቀን ሆሳዕና ይውላል። የስቅለት ተውሳክ ፯ትንና ፲፰ትን ቢያገናኙት ፳፭ ይሆናል። በዚሁ ብተት ይሄዳል። ማክሰኞ ለማክሰኞ ፮፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፲፭፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፳፪፣ ረቡዕ ፳፫፣ ኃሙስ ፳፬፣ ዓርብ ፳፭። ሚያዝያ በባተ በ፳፭ ዓርብ ቀን ስቅለት ይውላል። የትንሣኤ ተውሳክ ፱ንና ፲፰ትን ቢያገናኙት ፳፯ ይሆናል። በዚሁ ብተት ይሄዳል። ሚያዝያ ማክሰኞ ይብታል። ማክሰኞ ለማክሰኞ ፮፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፲፭፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፳፪፣ ማክሰኞ ለማክሰኞ ፳፱፣ ሁለት ታግሦ ሚያዝያ በባተ በ፳፯ እሑድ ቀን ትንሣኤ ይውላል። የርክበ ካህናት ተውሳክ ፫ትንና ፲፰ትን ቢያገናኙት ፳፩ ይሆናል። ግንቦት ረቡዕን አስግሮ ኃሙስ ይብታል። ኃሙስ ለኃሙስ ፮፣ ኃሙስ ለኃሙስ ፲፭፣ ኃሙስ ለኃሙስ ፳፪፣ አንድ ታግሦ ግንቦት በዋለ በ፳፩ ረቡዕ ቀን ርክበ ካህናት ይውላል። የዕርገት ተውሳክ ፲፰ትንና ፲፰ትን ቢያገናኙት ፴፯ ይሆናል። ፴ ገድፎ ፯ ይተርፋል። ሰኔ ዓርብን አስግሮ ቅዳሜ ይብታል። እሑድ ፪፣ ሰኞ ፫፣ ማክሰኞ ፬፣ ረቡዕ ፭፣ ኃሙስ ፮። ሰኔ በባተ በ፮ ኃሙስ ቀን ዕርገት ይውላል። የጰራቅሊጦስ ተውሳክ ፳፭ንና ፲፰ትን ቢያገናኙት ፵፮ ይሆናል። ፴ ገድፎ ፲፮ ይተርፋል። ሰኔ ዓርብን አስግሮ ቅዳሜ ይብታል። ቅዳሜ ለቅዳሜ ፮፣ ቅዳሜ ለቅዳሜ ፲፭፣ እሑድ ፲፮። ሰኔ በባተ በ፲፮ እሑድ ቀን ጰራቅሊጦስ ይውላል። የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ፳፱ንና ፲፰ትን ቢያገናኙት ፵፮ ይሆናል። ፴ውን ገድፈው ፲፮ ይተርፋል። ቅዳሜ ለቅዳሜ ፮፣ ቅዳሜ ለቅዳሜ ፲፭፣ እሑድ ፲፮፣

ሰኞ ፲፯። ሰኔ በባተ በ፲፯ ሰኞ ቀን ጾመ ሐዋርያት ይውላል። የጾመ ድኅነት ተውሳክ ፩ንና ፲፰ትን ቢያገናኙት ፲፱ ይሆናል። ቅዳሜ ለቅዳሜ ፳፣ ቅዳሜ ለቅዳሜ ፳፩፣ እሑድ ፳፯፣ ሰኞ ፳፯፣ ማክሰኞ ፳፰፣ ረቡዕ ፳፱። ሰኔ በባተ በ፳፱ ረቡዕ ቀን ጾመ ድኅነት ይጀምራል። አልቦ አበቅቴ በሆነ ዘመን መስከረም ፴ የዋለበትን የዕለቱን ተውሳክ መባጃ ሐመር አድርጎ አጽዋማትንና በዓላትን ማውጣት ነው። ሌሊቱንም ሕፀፁንና መዓልቱን ጨምሮ ማሳደር ነው።

፭ የዕለታት፣የበዓላት፣የአጽዋማት ተውሳኮች

የዕለታት ተውሳክ የትመጣው ከምን ይገኛል ቢሉ ከመጥቅዕ ሳኒታ አንስቶ እስከ ነነዌ ቢቆጥሩ ፱፳፰ ይሆናል። ፱፳ውን በ፬ ፴ ገድፎ ፰ ይተርፋል። የቅዳሜ ተውሳክ ፰ ይሆናል። ፱፳፮ ቢሆን ፱፳ውን በ፬ ፴ ገድፎ ፮ ይተርፋል። የእሑድ ተውሳክ ፮ ይሆናል። ፱፳፮ ቢሆን ፱፳ውን በ፬ ፴ ገድፎ ፮ ይተርፋል። የሰኞ ተውሳክ ፮ ይሆናል። ፱፳፭ ቢሆን ፱፳ውን በ፬ ፴ ገድፎ ፭ ይተርፋል። የማክሰኞ ተውሳክ ፭ ይሆናል። ፱፳፬ ቢሆን ፱፳ውን በ፬ ፴ ገድፎ ፬ የረቡዕ ተውሳክ ይሆናል። ፱፳፫ ቢሆን ፱፳ውን በ፬ ፴ ገድፎ ፫ የኃሙስ ተውሳክ ይሆናል። ፱፳፪ ቢሆን ፱፳ውን በ፬ ፴ ገድፎ ፪ የዓርብ ተውሳክ ይሆናል። የዕለታት ተውሳክ የትመጣ ይህ ነው። የአጽዋማትና የበዓላት ተውሳክ የትመጣው ከምን ይገኛል ቢሉ ከነነዌ ሣኒታ አንስቶ እስከ ዐቢይ ጾም ቢቆጥሩ ይገኛል። ከነነዌ ሣኒታ አንስቶ እስከ ዐቢይ ጾም ቢቆጥሩ ፲፬ ይሆናል። ይህን ባለው ይይዟል። እስከ ደብረ ዘይት ቢቆጥሩ ፵፩ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፲፩ ይተርፋል። የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩ ይሆናል። እስከ ሆሳዕና ቢቆጥሩ ፷፪ ይሆናል። ፷ውን በ፪ ፴ ገድፈው ፪ ይቀራል። ፪ የሆሳዕና ተውሳክ ይሆናል። እስከ ስቅለት ቢቆጥሩ ፷፯ ይሆናል። ፷ውን በ፪ ፴ ገድፎ ፯ የስቅለት ተውሳክ ይሆናል። እስከ ትንሣኤ ቢቆጥሩ ፷፱ ይሆናል። ፷ውን በ፪ ፴ ገድፎ ፱ ይተርፋል። ፱ የትንሣኤ ተውሳክ ይሆናል። እስከ ርክበ ካህናት ቢቆጥሩ ፶፫ ይሆናል። ፶ውን በ፫ ፴ ገድፎ ፫ የርክበ ካህናት ተውሳክ ይሆናል። እስከ ጰራቅሊጦስ ቢቆጥሩ ፭፲፰ ይሆናል። ፶ውን በ፫ ፴ ገድፎ ፳፰ የጰራቅሊጦስ ተውሳክ ይሆናል። እስከ ጾመ ሐዋርያት ቢቆጥሩ ፭፲፱ ይሆናል። ፶ውን በ፫ ፴ ገድፎ ፳፱ የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ይሆናል። እስከ ጾመ ድኅነት ቢቆጥሩ ፭፳፩ ይሆናል። ፭፳ውን በ፬ ፴ ገድፎ ፩ የጾመ ድኅነት ተውሳክ ይሆናል። የአጽዋማትና የበዓላት ተውሳክ የትመጣው ይህ ነው።

፮ ኢይወርድና ኢየዐርግ

ከዚህ ቀጥሎ የኢይወርድን መባጃ ሐመር እንናገራለን። ኢይወርድ መጥቅዕ ፲፭ ተገኝቶ መስከረም ዓርብ ቢብት ዓርብ ለዓርብ ፳፣ ዓርብ ለዓርብ ፲፭። የዓርብ

ተውሳክ ፪ትንና ፲፭ትን ቢገጥሙት ፲፯ ይሆናል። የኢይወርድ መባኃ ሐመር ፲፯ ነው። ነነዌ ብትወርድ ፲፯ትን እንጂ ፲፯ትን አትነካም። የዓቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬ ነው። ፲፬ትንና ፲፯ትን ቢገጥሙት ፴፩ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፩ ይይዛል። ዐቢይ ጾም ቢወርድ የካቲት ፩ን እንጂ ጥር ፴ን አይነካም። የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩ድንና ፲፯ትን ቢገጥሙት ፳፰ ይሆናል። ደብረ ዘይት ቢወርድ የካቲት ፳፰ን እንጂ የካቲት ፳፯ትን አይነካም። የሆሳዕና ተውሳክ ፪ትንና ፲፯ትን ቢገጥሙት ፲፱ ይሆናል። ሆሳዕና ቢወርድ መጋቢት ፲፱ን እንጂ ፲፰ትን አይነካም። የስቅለት ተውሳክ ፯ትንና ፲፯ትን ቢገጥሙት ፳፬ ይሆናል። ስቅለት ቢወርድ መጋቢት ፳፬ን እንጂ ፳፫ትን አይነካም። የትንሣኤ ተውሳክ ፱ኝንና ፲፯ትን ቢገጥሙት ፳፮ ይሆናል። ትንሣኤ ቢወርድ መጋቢት ፳፮ትን እንጂ ፳፭ትን አይነካም። የርክበ ካህናት ተውሳክ ፫ትንና ፲፯ትን ቢገጥሙት ፳ ይሆናል። ርክበ ካህናት ቢወርድ ሚያዝያ ፳ን እንጂ ሚያዝያ ፲፱ኝን አይነካም። የዕርገት ተውሳክ ፲፰ትንና ፲፯ትን ቢገጥሙት ፴፭ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፭ ይተርፋል። ዕርገት ቢወርድ ግንቦት ፭ትን እንጂ ግንቦት ፬ትን አይነካም። የጰራቅሊጦስ ተውሳክ ፳፰ትንና ፲፯ትን ቢገጥሙት ፶፭ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፲፭ ይተርፋል። ጰራቅሊጦስ ቢወርድ ግንቦት ፲፭ን እንጂ ግንቦት ፲፬ትን አይነካም። የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ፳፱ኝንና ፲፯ትን ቢገጥሙት ፶፮ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፲፮ ይይዛል። ጾመ ሐዋርያት ቢወርድ ግንቦት ፲፮ትን እንጂ ግንቦት ፲፭ትን አይነካም። የጾመ ድኅነት ተውሳክ ፩ንና ፲፯ትን ቢገጥሙት ፲፰ ይሆናል። ጾመ ድኅነት ቢወርድ ግንቦት ፲፰ትን እንጂ ግንቦት ፲፯ትን አይነካም። ከዚህ ቀጥለን የኢየዐርግን መባኃ ሐመር እንናገራለን። ኢየዐርግ መጥቅዕ ፲፫ ተገኝቶ ጥቅምት ሰኞ ቢብት ሰኞ ለሰኞ ፭፣ ማክሰኞ ፱፣ ረቡዕ ፲፣ ኃሙስ ፲፩፣ ዓርብ ፲፪፣ ቅዳሜ ፲፫። የቅዳሜ ተውሳክ ፭ትንና ፲፫ትን ቢገጥሙት ፳፩ ይሆናል። የኢየዐርግ መባኃ ሐመር ፳፩ ነው። ነነዌ ብትወጣ የካቲት ፳፩ድን እንጂ ፳፪ትን አትነካም። የዐቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬ትንና ፳፩ድን ቢገጥሙት ፴፭ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፭ትን ይይዛል። ዐቢይ ጾም ቢወጣ መጋቢት ፭ትን እንጂ ፮ትን አይነካም። የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩ንድን ከ፳፩ ቢገጥሙት ፴፪ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፪ ይይዛል። ደብረ ዘይት ቢወጣ ሚያዝያ ፪ን እንጂ ፫ትን አይነካም። የሆሳዕና ተውሳክ ፪ትንና ፳፩ንድን ቢገጥሙት ፳፫ ይሆናል። ሆሳዕና ቢወጣ ሚያዝያ ፳፫ትን እንጂ ፳፬ትን አይነካም። የስቅለት ተውሳክ ፯ትንና ፳፩ንድን ቢገጥሙት ፳፰ ይሆናል። ስቅለት ቢወጣ ሚያዝያ ፳፰ትን እንጂ ፳፱ኝን አይነካም። የትንሣኤ ተውሳክ ፱ኝንና ፳፩ንድን ቢገጥሙት ፴ ይሆናል። ትንሣኤ ቢወጣ ሚያዝያ ፴ን እንጂ ግንቦት

፩ንድን አይነካም። የርክበ ካህናት ተውሳክ ፫ትንና ፳፩ንድን ቢገጥሙት ፳፬ ይሆናል። ርክበ ካህናት ቢወጣ ግንቦት ፳፬ትን እንጂ ፳፭ትን አይነካም። የዕርገት ተውሳክ ፲፰ትንና ፳፩ንድን ቢገጥሙት ፴፱ ይሆናል። ፴ውን ገድፎ ፱ ይይዟል። ዕርገት ቢወጣ ሰኔ ፱ኝን እንጂ ፲ርን አይነካም። የጰራቅሊጦስ ተውሳክ ፳፰ትንና ፳፩ንድን ቢገጥሙት ፶፱ ይሆናል። ፴ውን ገድፈው ፲፱ ይይዟል። ጰራቅሊጦስ ሰኔ ፲፱ኝን እንጂ ፳ን አይነካም። የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ፳፱ኝንና ፳፩ንድን ቢገጥሙት ፱ ይሆናል። ፴ውን ገድፈው ፳ን ይይዟል። ጾመ ሐዋርያት ቢወጣ ሰኔ ፳ን እንጂ ፳፩ንድን አይነካም። የጾመ ድኅነት ተውሳክ ፩ንድንና ፳፩ንድን ቢያገናኙት ፳፪ ይሆናል። ጾመ ድኅነት ቢወጣ ሰኔ ፳፪ን እንጂ ፳፫ትን አይነካም። ኢይወርድ ታሕታይ ቀመር ኢየዐርግ ላዕላይ ቀመር ይባላሉ።

፮ ወንጌላዊውንና ዕለቱን ለማወቅ

ዓመተ ወንጌላውያንን ለማወቅ ዕለቱን ለመረዳት ይህንን ፎየ፭የ፲፮ ዘመን ለ፬ቱ ወንጌላውያን ትክክል መድቦ ፩ ቢተርፍ ማቴዎስ፣ ፪ ቢተርፍ ማርቆስ፣ ፫ ቢተርፍ ሉቃስ፣ ትክክል ቢሆን ዘመነ ዮሐንስ ነው።ይህንን ፎየ፭የ፲፮ ለ፬ቱ ወንጌላውያን ትክክል መድቦ ቢያካፍሉት ፲የ፳የፎ፬ ደርሷቸው ትርፍ የለም። ዘመነ ዮሐንስ መሆኑ በዚህ ይታወቃል። ዕለቱን ለመረዳት ይህንን ፲የ፳የፎ፬ ከዓመተ ዓለሙ ጋር ደምሮ በሰባት መግደፍ ነው። ይህም ፯የ፫የ፯፭ ይሆናል። ይህንን በሰባት ስንገድፈው ፲የ፫፶፪ ደርሶ ቀሪ ፩ ይሆናል። ትርፉ ፩ ከሆነ ማክሰኞ፣ ፪ ከሆነ ረቡዕ፣ ፫ ከሆነ ኃሙስ፣ ፬ ከሆነ ዓርብ፣ ፭ ከሆነ ቅዳሜ፣ ፮ ከሆነ እሑድ፣ ያለምንም ትርፍ ከተካፈለ ሰኞ ይሆናል።

፯ የሕጸጽና የጳጉሜን አወጣጥ

ፀሐይ ከጨረቃ የዕለት የዕለት በማብራት የምታበልጣው በአማካይ በቀን ፩ ኬክሮስ: ከ፶፪ ካልዒት: ከ፴፩ ሣልሲት ነው። ሣልሲት በካልዒት ኬክሮስ በዕለት ይጠቀለላል። ሣልሲት ፮ ሲሞላ ፩ ካልዒት ይሆናል። ካልዒት ፮ ሲሞላ ፩ ኬክሮስ ይሆናል። የዕለት የዕለት ፩ ኬክሮስ ሲወጣ የወሩ ፴፣ የ፪ ወሩ ፶ ኬክሮስ ፩ ዕለት ይሆናል። የ፬ ወሩ ፪፣ የ፮ ወሩ ፫፣ የዓመቱ ፮ ዕለት ይሆናል። የዓመቱ ፮ ሕፀፅ የት መጣው ይህ ነው። የዕለት የዕለት ፱ ካልዒት ሲወጣ የወሩ ፲የ፭የ ካልዒት ይሆናል። ይህን በኬክሮስ ቢያካፍሉት የወሩ ፳፭ ኬክሮስ ይሆናል። የ፪ ወሩ ፱፣ የ፬ ወሩ ፱፣ የ፮ ወሩ ፪፱፣ የዓመቱ ፫፱ ኬክሮስ ይሆናል። ይህን በዕለት ቢከፍሉት ፭ ዕለት ይሆናል። የ፭ ጳጉሜን የት መጣው ይህ ነው። የዕለት የዕለት ፪:፪ ካልዒት ሲወጣ የወሩ ፮ ካልዒት ፩ ኬክሮስ ይሆናል። የ፪ ወሩ ፪፣ የ፫ ወሩ ፫፣ የ፬ ወሩ ፬፣ የ፭ ወሩ ፭፣ የ፮ ወሩ ፮፣ የዓመቱ ፲፪ ኬክሮስ ይሆናል። ይህ

ባለው ይቆይ። የዕለት የዕለት ፴፡፴ ሣልሲት ሲወጣ የወሩ ፱፻ ሣልሲት ይሆናል። ይህን በካልዒት ቢከፍሉት የወሩ ፲፭፣ የ፪ ወሩ ፴፣ የ፬ ወሩ ፷ ካልዒት ይሆናል። ይኸውም ፩ ኬክሮስ ይሆናል። የ፷ ወሩ ፪፣ የዓመቱ ፫ ኬክሮስ ይሆናል። ፫ትንና ፲፪ትን ቢገጥሙት ፲፭ ኬክሮስ ይሆናል። የማቴዎስ ፲፭፣ የማርቆስ ፲፭፣ የሉቃስ ፲፭፣ የዮሐንስ ፲፭ ቢገጥሙት ፷ ኬክሮስ ፩ ዕለት ይሆናል። የ፯ኛው ጳጉሜን የት መጣው ይህ ነው። የዕለት የዕለት ፩፡፩ ሣልሲት ሲወጣ የዓመቱ ፮ ካልዒት፣ የ፪ ዓመቱ ፲፪፣ የ፬ ዓመቱ ፳፬፣ የ፷ ዓመቱ ፸፪፣ የ፲ ዓመቱ ፷ ካልዒት አንድ ኬክሮስ ይሆናል። የ፳ ዓመቱ ፪፣ የ፸ ዓምቱ ፬፣ የ፹ ዓመቱ ፭፣ የ፱ ዓመቱ ፲፣ የ፪፱ ዓመቱ ፳፣ የ፬፱ ዓመቱ ፸፣ የ፯፱ ዓመቱ ፷ ኬክሮስ ፩ ዕለት ይሆናል። እንተ ባቲ ተወለድኩ ወእንተ ባቲ ተጠመቁ ወእንተ ባቲ ትንሣኤየ አግሀድኩ የሚላት ዕለተ ምርያ ይህች ናት። የ፯ተኛ ጳጉሜን ሁለተኛ መንገድ የት መጣው ይህ ነው። ጌታችን በ፶፱፭፱ ዘመን በዘመነ ዮሐንስ በወርኃ መጋቢት በ፳፱ መዓልት በ፩ ሌሊት እሑድ በሠለስት ተፀነሰ። በ፶፱፭፱፩ ዘመን በዘመነ ማቴዎስ በወርኃ ታኅሣሥ በ፳፱ መዓልት በ፲ ሌሊት ማክሰኞ በመንፈቀ ሌሊት ተወለደ። በ፶፱፭፱፴፩ ዘመን በዘመነ ሉቃስ በወርኃ ጥር በ፲፩ መዓልት በ፳፭ ሌሊት ማክሰኞ በመንፈቀ ሌሊት ተጠመቀ። በ፶፱፭፱፴፫ ዘመን በዘመነ ማቴዎስ በወርኃ ነሐሴ በ፲፫ መዓልት በ፳፪ ሌሊት እሑድ በቀትር ብርሃነ መለኮቱን በደብረ ታቦር ለሐዋርያት ገለጠ። በ፶፱፭፱፴፬ ዘመን በዘመነ ማርቆስ በወርኃ መጋቢት በ፳፯ መዓልት በ፲፭ ሌሊት ዓርብ በቀትር ተሰቀለ።

፱ ዕለተ ጠቢባን

ዕለተ ጠቢባንን ለማወቅ ከፅንስ እስከ ልደት መቁጠር ነው። ከፅንስ እስከ ልደት ቢቆጥሩት ፪፻፷፭ ዕለት ይሆናል። ይህን በ፯፡በ፭ ሱባዔ መግደፍ ነው። ሲገደፍም ከ፪፻ው ፬ ይተርፋል። ከ፷፭ቱ ፷ው ሱባኤ ነው ፭ ይተርፋል። ፭ትንና ፬ትን ቢገጥሙት ፱ ይሆናል። ሱባዔውን ቢገድፉት ፪ ይተርፋል። ዕለተ ጠቢባን የተባሉ እሊህ ናቸው። ወደኋላ እንዳይመጡ ዓለም አልተፈጠረም። ወደፊትም እንዳይሄዱ ሚያዝያ ባተባቸው። ዓለም የተፈጠረ በመጋቢት ፳፱ ቀን ነው። ጠቢባን የተባሉ ሥላሴ ናቸው። ይህን ዓለም እምኀበ አልቦ ኀበቦ አምጥተው ስለፈጠሩ ጠቢባን ተብለዋል። አንድም ጠቢባን የተባሉ መምህራን ናቸው። ይህን ተመራምረው ስላወቁ ጠቢባን ተብለዋል።

፲ አሥርቆት (ዘመኑን አስቦ ፈጣሪን ማመስገን)

ነአኩቶ ለገባሬ ሠናያትን እስከ ተፍጻሜቱ ብለህ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ሃሌ ሉያ በዘንዜከር ሐሳባተ ሕጉ ወትእዛዛቲሁ ለእግዚእነ

ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ሀሎነ በዘመነ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ዘመነ ማቴዎስ ዜናዊ። በ፼፻ ወበ፷፻፲፮ ኮነ ዓመተ ዓለም። በ፶፻፷፻ ኮነ ዓመተ ኵነኔ ዓመተ ፍዳ። በ፷፻፲፮ ኮነ ዓመተ ምሕረት ዮም ሠረቀ ለነ ወርኀ መስከረም ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ወርኃ ጥቅምት በሰላመ እግዚአብሔር አብ አሜን። ፩ ሠርቀ መዓልት፣ ፸፩ ሠርቀ ሌሊት፣ ፸፩ ሠርቀ ወርኅ፣ ፯ ጥንተ ያን፣ ፫ ጥንተ ዕለት፣ ፩ ጥንተ ቀመር ዮም ኮነ በዛቲ ዕለት ዘተበስረ በአፈ ካህን ኀሩይ ወለባዊ ዝ ዕጣን ወዝ ጸሎት ወዝ አስተብቊዖት ወዝ መሥዋዕት ይዕርግ በእንተ ስመ እግዚአብሔር አብ ወበእንተ ተገሥረ ወልዱ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወበእንተ ስሙ ለመንፈስ ቅዱስ ጸራቅሊጦስ ወበእንተ ስማ ለእግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ። ጸልዩ በእንተ ዕጣን ከመ ይኵን ኀሩየ ወሥሙረ። ከዘመን መለወጫ ቀን ውጭ ለሆነው ጸሎት ሁሉ ኀሩየ ወሥሙረ ካለ በኂላ ስብሐት ይበል። የዘመን መለወጫ ዕለት የሆነ እንደሆነ አዋጅ ስትነግር ስብሐት የለውም። ጸልዩ በእንተ ዕጣን ከመ ይኵን ኀሩየ ወሥሙረ ካልክ በኂላ ጸሎተ ዕጣንን ከቅዳሴው በል። ፀጋ ዘአብ ኂሩት ዘወልድ ሱታፌ ዘመንፈስ ቅዱስ ወበረከታ ለእግዝእትነ ማርያም ወላዲተ አምላክ ተፋቅሮ ዘነቢያት ወሐዋርያት ዘጻድቃን ወሰማዕት ወዘአበው ቀደምት ቅዱሳን ወዘትጉሃን መላእክት ወትረ የሃሉ ምስሌየ ወምስለ ኵልክሙ። ይ.ሕ አሜን። ፫ ጊዜ በል። እግዚአብሔር የሃቦ ለብፁዕ ወለቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አባ.....ወብፁዕ ሊቀ ጳጳስነ አባ.....ወኵሉሙ ሊቃነ ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ርቱዓነ ሃይማኖት ጸሎተ ዘጸለዩ ወዕጣነ ዘወገሩ ውስተ ኑኃ ሰማይ ዘየዐርግ ወመዓተ እግዚአብሔር ዘያቄርር ወኃጢአተ ዓለም ዘያስተሰሪ ለይኵን። ይ.ሕ አሜን። እግዚአብሔር የሃቦ ለመፍቀሬ እግዚአብሔር ንጉሥነ ኀበ ኀለየ በልቡ ወነበ አንጸረ በአጽባዕቱ ፀሩ ወጸላዕቱ ዘርጉቅ ወዘቅሩብ በኃይለ መስቀሉ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ግሩራነ ለይኵኑ ታሕተ እገሪሁ ፍጡነ። **ይ.ሕ አሜን።** እግዚአብሔር የሀብክሙ ለክሙኒ ለሕዝበ ክርስቲያን ፈሪሀ ስሙ ወስነ አምልኮቱ ወጸጋ ረድኤቱ። **ይ.ሕ አሜን።** እግዚአብሔር ያቀርር መዓቶ ወይፈኑ ሣህሎ ወምሕረቶ ለምድር (፫ ጊዜ በል)። **ይ.ሕ አሜን (፫ ጊዜ)።** ይ.ካ እነግረክሙ አኃውየ ከመ ታእምሩ ጸጋሁ ለመንፈስ ቅዱስ ወትረ የሃሉ ምስሌየ ወምስለ ኵልክሙ አሜን። ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን። ከዚህ ቀጥሎ ከመዝሙረ ዳዊት ፺፱ኙን መዝሙር የብቡን በል። ከዚህ በመቀጠል። ዘመነ ሉቃስ አለፈ ዘመነ ዮሐንስ ተተካ። (ይህንን እንደዘመኑ በል)። ሉቃስ ተሻረ ዮሐንስ ተተካ (፫ ጊዜ

በል)። ሕዝቡም በእልልታ ይቀበሉ። በጭብጨባ ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ በሰላም እንዳደረሰን እንዲሁም ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ በሰላም ያሻግረን አሜን። አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይግባው አሜን ወአሜን ለይኵን ለይኵን። በመጨረሻም የቀረበውን ዕጣን፣ ሥርናይ፣ ዘቢብ ይባርክና ስንብት ይሆናል። የተባረከው ዕጣን ሥርናይ ዘቢብ ከንጹሕ ስፍራ ተቀምጦ ትንሽ ትንሽ እየተጨመረ ለዓመት መቀደሻ ይሆናል።

፲፩ ዕለትን ማወቂያ መንገድ

ይህም ማለት ለምሳሌ መስከረም አንድ ቀን መቼ እንደሚውል ከታወቀ በኋላ በዓመቱ ውስጥ ያሉ ቀኖችን ዕለታቸውን ለማወቅ የሚረዳን አጭር መንገድ አለ። ይኸውም የሚከተሉትን ማለትም፡-

፩) ማወቅ የፈለግነውን ቀን ቁጥር

፪) መስከረም ፩ የዋለበት ጥንተ ዖን

፫) አጽፈ ወርኅ

እኒህን ደምረን በሰባት አካፍለን ቀሪው ፩ ከሆነ እሑድ፣ ፪ ከሆነ ሰኞ፣ ፫ ከሆነ ማክሰኞ፣ ፬ ከሆነ ረቡዕ፣ ፭ ከሆነ ኃሙስ፣ ፮ ከሆነ አርብ፣ ያለቀሪ ከተካፈለ ቅዳሜ ይሆናል። ለምሳሌ የካቲት ፲፭ ቀን የሚ፲፭ መቼ ዕለት ይውላል የሚለውን ለማወቅ መጀመሪያ ሚ፲፭ ዓ.ም መስከረም ፩ ቀን የዋለው እሑድ ቀን ነው። እሑድ ደግሞ ለጥንተ ዖን አምስተኛ ቀን (፭) ነው። የየካቲት ወር ስድስተኛ ወር ነው። የዚህ እጥፍ (አጽፈ ወርኅ) ፲፪ ይሆናል። ማወቅ የፈለግነው ቀን የካቲት ፲፭ ነው። ስለዚህ $\overline{ሥ} + \overline{፲፪} + \overline{፭} = \overline{ሚ፲፭}$ ይሆናል። $\overline{ሚ፲፭}$ን በሰባት ስንገድፈው አራት ጊዜ ደርሶ ፬ ይቀራል። ፬ ከቀረ ረቡዕ ይውላል ማለት ነው ስላልን። የካቲት ፲፭ ረቡዕ ይውላል።